አማረኛ

# ከታላቁ ቁርአን
# የመጨረሻዎቹ
# ‹‹የሶስቱ ክፍሎች››
# ማብራሪያ
# ዋና ዋቢ
# ዙብደቱ ተፍሲር

በመቀጠልም
ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ
ጉዳዮች ፡፡

ISBN : 978-603-90056-2-9

www.tafseer.info

# መግቢያ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህና በጣም አዛኝ በኾነው እጀምራለሁ፡፡**

ለአላህ ምስጋና ይገባው፡፡ የአላህ ሰላምና እዝነት በአለቃችን፣ በነብያችንና በወዳጃችን በአላህ መልዕክተኛ ላይ ይሁን፡፡

ከዚህ በመቀጠል፡- ሙስሊም ወንድሜና ሙስሊም እህቴ ሆይ! አላህ እዝነቱን ይቸራችሁና በእያንዳንዳችን ላይ አራት ነገሮችን ማወቁ የግድ ነው ፡-

**አንደኛው፡-** **እውቀት** ሲሆን፡- እሱም አላህን፣ መልዕክተኛዉን እና ኢስላምን ማወቅ ነው፡፡ ምክንያቱም አላህን ያለ እውቀት መገዛት አይፈቀድምና፡፡ አላህን ያለ እውቀት ያመለከ የጠመመ ሰው ሲሆን በዚህም ተግባሩ ልክ እነዚያን ያለ እውቀት የሚለፋትን ነሷራዎችን/ ክርስቲያኖችን ይመስላል፡፡

**ሁለተኛው፡-** **ተግባር** ሲሆን፡- በእውቀቱ ያልሰራ እነዚያን በእውቀታቸው ያልሰሩትን አይሁዶች ይመስላል፡፡ ምክንያቱም አይሁዶች አውቀው በእውቀታቸው አልሰሩምና፡፡

ከሰይጣን የተንኮል ዘዴዎች አንዱ ሰዎችን ካወቁ በሀላፊነት እንደሚጠየቁና ካላወቁ ግን ከዚህ ችግር ነፃ ሊሆኑ እንደሚችሉ በማስመሰል ከትምህርት መድረክ ማሸሽ ነው፡፡ ይህም ዘዴ በእነዚያ አላህ፡- **“ጣቶቻቸዉን በጆሮዎቻቸው ዉስጥ አስገቡ፡፡ በልብሶቻቸውም ተሸፈኑ”** ባላቸው የነቢዩ ኑህ (عليه السلام) ሰዎች ላይ የተጠቀመው ዘዴ ነው፡፡

**ሶስተኛው፡-** **ወደዚሁ ዲን ጥሪ ማድረግ** ሲሆን፡- አዋቂዎችና ዳዒዎች የነቢያት ወራሾች ናቸው፡፡ አላህ የኢስራኢል ልጆችን፡- **“ይሰሩት ከነበረው መጥፎ ተግባር አንዱ ሌላኛውን አይከላከሉም ነበር ይሰሩት የነበረው ነገር ከፋ”** እንዳላቸው ስለነበሩ እረገማቸው፡፡ ደእዋ ማድረግና ማስተማር ሁሉም ሰው ከተወው ሁሉንም ወንጀለኛ የሚያደርግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህም በከፊል ህብረተሰብም ቢሆን እንኳን ሊሸፈን የሚገባው ግዴታ ነው፡፡

**አራተኛው፡-** **በመማር፣ በማስተማር፣ በመተግበርና** ወደ እሱው ጥሪ በማድረግ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችንና መሰናክሎችን ፀንቶ ለማለፍ ትእግስት ማድረግ ነው፡፡

ድንቁርናን ለማስወገድና ግዴታ የሆኑ ነገሮችን ለማወቅ የሚፈልጉ ወገኖችን ሁሉ ለማገዝ በማሰብ በዚህች አጭር መፅሐፍ ውስጥ በጣም አስፈላጊ እና መሠረታዊ የሆኑ ሸሪዓዊ እውቀቶችን እንደዚሁም ከታላቁ የአላህ ቅዱስ ቁርአን የመጨረሻ አስርቶች ሶስት ክፍሎችን ተፍሲርና ኢስላምን በተመለከተ ማንም ሙስሊም ሊያውቀው ግዴታ የሆነብትን ሊያሳዉቅ የሚችለዉን ነገሮች ለማጠቃለል ሞክረናል፡፡ ሁሉም ተዳስሶ የማይደርስበት ነገር ንኳን አንኳሩ አይተውምና፡፡

በዚሁ ስራችን ነገሮችን ማሳጠርና ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በተሰማው ብቻ መወሰንን መርጠናል፡፡ በዚህ ስራችንም ምሉዕነትን አንሞግትም፡፡ ምክንያቱም ይህ ባህሪ አላህ ለራሱ እንጂ ለማንም ያልሰጠው ባህሪ ነውና፡፡ ነገር ግን ይህ ጥረት የአቅም ያህል ሙከራ ነው፡፡ እናም ስራው ትክክል ከሆነ ከአላህ (ﷻ) ነው፡፡ ስህተት ከሆነ ግን ከኛና ከሰይጣን ሲሆን፣ አላህ እና ነቢዩ (ﷺ) ከዚህ ስህተት የፀዱ ናቸው፡፡ ነውራችንን በማመላከት ገንቢ ሐሳቦችን ወደኛ በመላክ ለተባበረን ሰው ሁሉ አላህ እዝነቱን ያውርድለት፡፡

ይህን መፅሐፍ በማዘጋጀት፣በማተምና በማከፋፈል የተባበሩንን ሁሉ አላህ መልካሙን ምንዳ እንዲከፍላቸው፣ ስራቸዉን እንዲቀበላቸው፣ የልፋት ዋጋቸዉን እጥፍ ድርብ እንዲያደርግላቸው እንለምነዋለን፡፡ አላህ ሁሉንም ያውቃል፡፡

አላህ ሰላሙንና ረድኤቱን በነቢዩ ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በሁሉም ባልደረቦቻቸው ላይ ያውርድ፡፡

ተጨማሪ ነገሮችን ለመረዳት ወይም ለመርዳት ወይም ለመተባበርና መፅሐፉን ከፈለጉ በ amh@tafeseer.info

የአማርኛው ሁለተኛው እትም ሲሆን ዐረብኛው አስራ ሰባተኛው እትም ነው፡፡ እስካሁን ከዓለም ቋንቋዎች ከ40 በላይ ተተርጉሟል፡፡ የተጨመረበትና የታረመ ነው፡፡

www.tafseer.info amm@tafseer.info 1432 ሂ.አ

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| ቁርአንን በማንበብ የሚገኘው አጅር / ምንዳ:: | 1 |
| ከታላቁ ቁርአን የመጨረሻዎቹ ‹‹የሶስቱ ክፍሎች››ማብራሪያ | 4 |
| ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ ጥያቄዎች | 73 |
| የልብ ተግባራት | 88 |
| በአብደላህና በዐብዱ ነቢይ መካከል የተደረገ ለስላሳና አስተማሪ ዉይይት:: | 97 |
| ላኢላሀ ኢለሏህ /ከአሏህ በቀር በእውነት ሊገዙት የሚገባ አምላክ የለም/ ብሎ ስለመመስከር:: | 110 |
| ሙሐመድ ረሱሉላህ – ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር | 111 |
| ስለ ጠሃራ /ንፅህና /በኢስላም | 113 |
| ሴት ነክ ህግጋት የሴት ልጅ የተፈጥሮ ደሞች መጀመሪያ (ሐይድና የበሽታ ደም):: | 118 |
| ሴት ልጅ በኢስላም | 120 |
| ሶላት | 123 |
| ዘካህ | 128 |
| ፆም | 130 |
| ሐጅና ዑምራ፡ | 133 |
| ልዩ ልዩ ጠቃሚ ትምህርቶች | 137 |
| ሸሪዓዊ ሩቅያች / መንፈሳዊ ህክምና አደራረግ | 142 |
| ዱዓ | 149 |
| ሁሉም ሰው በቃሉ ሊሐፍዛቸው የሚገቡና አስፈላጊ የሆኑ ዱዓዎች ዱዱዓዎች:: | 151 |
| ትርፋማው ንግድ | 156 |
| በጧትና በማታ ዕለት ከዕለት የሚደረጉ ዚክሮች ዉዳሴዎች /ዱዓዎች/ :: | 159 |
| ከፍተኛ ምንዳ እንዳላቸው ከነቢዩ ሙሐመድ የተነገረላቸው አንደበታዊና ተግባራዊ ጉዳዮች :: | 162 |
| እንዳንሰራቸው የተከለከሉ ነገሮች:: | 167 |
| ዘላለማዊዋ ጉዞ | 170 |
| የዉዱእ ስርአት | |
| የሶላት ስርአት | |
| እውቀት ተግባርን ስለ መጠየቁ | |

# ቁርአንን በማንበብ የሚገኘው አጅር/ምንዳ

የተከበረው ቁርአን የአላህ ቃል ነው:: ከንግግሮች ሁሉ ያለው ታላቅነት አላህ (ﷻ) በፍጡራኑ ላይ ያለውን ታላቅነት ያህል ነው:: ምላስ ከሚንቀሣቀስባቸዉ ነገሮች ሁሉ የሚበልጠዉ እሱን ማንበብ ነው::

ቁርአንን በመማር፤ በማስተማርና በማንበብ ከሚገኙ ምንዳዎች መካከል:-

| | |
|---|---|
| የማስተማሩን ምንዳ በተመለከተ: | ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ከሁላችሁም የሚበልጠው ቁርአንን ተምሮ ያስተማረ ሰው ነው) ብለዋል:: |
| ማንበብን በተመለከተ | ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ (ከአላህ ቁርአን አንድን ፊደል ያነበበ ሰው በያንዳንዱ ፊደል አንደ ሐሰና/መልካም ምንዳ/ አለው:: አንድ ሐሰና በአስር ተመሣሣይ ይቆጠራል) ብለዋል፡፡ |

❖ ኢብኑ ረጀብ መልካምስራ ምንዳ በአስር መከፈሉ ለሁሉም ነው:: ለዚህም ቁርኣን ‹-------›ብሏል:: ከአስር በላይ ለመጨመር ግን አላህ ለሻለት ብቻ ነው:: ጭማሬው እስከ ሰባት መቶና ከዚያም በለጠ ሊሆን ይችላል:: ለዚህም ምክንያቱ ከአላህ ትሩፋት ከመሆኑም በተጨማሪ የልብ ፍርሃትና ቁርአንን ለመረዳትና መልዕክቱን ለማወቅ በሚደረገው ጥረት ነው:: እናም ቁርአንን በፍፁምነት /በኢኽላስ/ የሚያነብ ሰው ሁሉ ከፍተኛ ምንዳ አለው፡፡ ሁኖም ይህ ምንዳ በህያዉና በሙሉ ልብ በተነበበ ቁጥር ምንዳው ይጨምራል፡፡ እናም አንድን ፊደል ማንበብ ከአስር እስከ ሰባት መቶ እጥፍ ድረስ ድርብርብ ምንዳን ያስገኛል፡፡

| | |
|---|---|
| የመማሩ የመሐፊዙና በሱ ላይ ዕውቀትን ማዳበሩ ምንዳዉ ደግሞ | ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ቁርአንን የሐፊዘ ሆኖ ያሚያነብ ሰው ከተከበሩ መላይኮች ጋር ነው፡፡ ቁርአን እየከበደው የሚያነበው ሰው ደግሞ ሁለት ምንዳ አለው) ብለዋል። በሌላም ሀዲስ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቲርሚዚ እንደ ዘገቡት (በአኺራ ቀን ቁርአንን ይቀራ ለነበረ ሰው አንብብና ደረጃን ዉጣ በዱንያ ታነብ እንደነበርከ ሁሉ አንብብ የአንተ ደረጃህ ማብቂያው በንባብህ መጨረሻ ላይ /ከምታነባት አንቀፅ ዘንድ/ ነዉና ይባላል፡፡) |

ኸጧቢ የተባሉ ታላቅ ዐሊም (የቁርአን አንቀፆች ቁጥር በጀነት ደረጃዎች ልክ ናቸው:: እናም ለቁርአን አንባቢዉ በም ነበው ልክ ወደ ደረጃ ዉጣ ይባላል ማለት ሁሉንም ቁርአን በንባብ ያዳረሰ ሰው የጀነትን ማዕረጎች በሙሉ ያጠቃልላል:: ትንሽን የቀራ ሰው ደግሞ በዚያው በልኩ ያድጋል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የምንዳው መጨረሻ ባነበበው የቁርአን አንቀፅ ቁጥር ልክ ይሆናል ማለት ነው ብለዋል::

| | |
|---|---|
| ልጁ ቁርአን የቀራለት ሰው ምንዳ፡- | ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሐኪም በዘገቡት ሐዲስ (ቁርአንን የቀራ የተማረውና የተገበረው ሰው የቂያማ ዕለት ወላጆቹ እንደ ፀሐይ የሚያበራ የኑር አክሊል ይደፋሉ፡፡ ወላጆቹ የዚህች ዐለም ኑሮና ሀብት የማይስተካከላቸው ሁለት የሀር ልብስ ይለበሳሉ፡፡ እነሱም ‘በምን ምክኒያት ነው ይህን የተለበስነው?’ በማለት ይጠይቃሉ፡፡ የሚሰጣቸው መልስም ‘ልጃችሁ ቁርአንን በመቅራቱ ምክኒያት ብቻ ነው’ ይባላሉ፡፡) ብለዋል፡፡ |
| ቁርአን ለአንባቢው የሚያበረክተው ሽምግልናን ፡- | ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድና ሐኪም በዘገቡት ሐዲስ (ቁርአንን አንብቡ፡፡ እሱ የቂያማ ዕለት ለአንባቢው ሰው ሽምጋይ ሆኖ ይመጣልና) ብለዋል፡፡ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስም (ያምና ቁርአን የቂያማ ዕለት ለሰዎች ይሸመግላሉ) ብለዋል፡፡ |
| ቁርአንን ለመማማር መሰባሰብ ያለውን | ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡዳዉድ በዘገቡት ሐዲስ (ሰዎች ከአላህ ቤቶች በሆነዉ በአንዱ ቁርአንን ለመማርና ለማንበብ አይሰበሰቡም:: በእነሱ ላይ እርካታና የአላህ (ﷻ) ረድኤት |

| | |
|---|---|
| ምንዳ፡- | የወረደላቸው፤ መላይኮች የሸፈኗቸው፤ አላህም በእሱ ዘንድ ባሉት ያወሳቸው ቢሆን እንጂ) ብለዋል፡፡ |

**ቁርአንን የማንበብ ስርአት በተመለከተ ደግሞ**

| | |
|---|---|
| የማንበብ ስርዓት | ኢብኑ ከሲር የተባሉ ዐሊም አንዳንድ ስርአቶችን እንዲህ አውስተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል-ቁርአንን/ በጠሐራ/ ንፁህ ሳይሆኑ አለመንካትና አለማንበብ፤ ከማንበቡ በፊትም ሲዋክን መጠቀም /ጥርስን መፋቂያ/፤ ለማንበብ ሲዘጋጁም መልካምና ንፁህ ልብስ መልበስ፤ ሲያነቡም ፊትን ወደ ቂብላ ማዞር፤ ሲፋሸገው /ሲያዛጋው/ ቁርአኑን ከማንበብ ማቆም፤ በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር በተራ ወሬ ቁርአን ከማንበብ አለማቋረጥ፤ አዕምሮዉን ሙሉ በሙሉ በዚሁ ላይ ማሰማራት /በተኩረት ማንበብ /፤ አላህ ለአማኞች በሰጠዉ የቃል ኪዳን አንቀፅ ላይ በደረሱ ቁጥር ቆም ብሎ አላህን (ﷻ) መለመን፤ የዛቻ አንቀፅ በመጣች ጊዜም እንዲሁ ቆም ብሎ በአላህ (ﷻ) መጠበቅ/ ጠብቀን ማለት/፤ ቁርአንን ከፍቶ አለመተው፤ በላዩ ላይ ምንንም ነገር አለማስቀመጥ፤ ሌሎችን በሚያስቸግር መልኩ ድምፅን ከፍ አለማድረግ፤ በገበያ ዉስጥና በጩኸት ቦታዎች ላይ አለማንበብ የሚሉት ናቸው፡፡ |
| ቁርአን እንዴት ይነበባል ? | *ቁርአንንም ሆነ ሌሎችን ዚክሮች በሶላት ሆነ በሌላ ቦታ እንደተገበረው የሚቆጠረው ድምፁን ራሱ እስከሰማውድረስ ነው፡፡<br>*አነስ ኢብኑ ማሊክን ዋቢ አድርገው ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የቁርአን አነባበብ ተጠይቀው (ነቢዩ ሲያነቡ እያንዳንዱ ይስቡት ነበር፡፡ ለምሳሌ (ቢስሚላህ አረህማኒ አረሂም) የሚለዉን ሲያነቡ - ቢስሚላህ- የሚለዉን ለብቻው ይስቡት ነበር፡፡ - አረህማኒ - የሚለዉንም ለብቻው ይስቡት ነበር፡፡ - አረሂም - የሚለዉንም እንደዚሁ ለብቻው ይስቡት ነበር) ብለዋል፡፡ |
| በቀንና በሌሊት መነበብ ያለበት አነስተኛው የቁርአን አንቀፅ መጠን፡- | የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ባልደረቦች በየቀኑ ከቁርአን የሆነ ልክ ያነቡ ነበር፡፡ ሆኖም ሙሉ ቁርአንን ከሰባት ቀን ባነሰ ጊዜ ውስጥ መጨረስ የብዙዎቹ ተግባር አልነበረም፡፡ ብሎም ከሶስት ቀን ባነሰ ሙሉዉን ማንበብ መከልከሉ ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ተዘግቧል፡፡ ስለዚህ ዉድ ወንድሜ ሆይ! ቁርአንን በማንበብ ጊዜህን በመልካም ነገር አሳልፍ፡፡ |

* አደራ፡- በየቀኑ ምንም ከባድ ችግር ቢገጥምህ እንኳን የማትተወው የተወሰነ መጠን ከቁርአን የማንበብ ልምድ /ዉርድ/ ይኑርህ፡፡ በብዛት ተጀምሮ ከሚቋረጥ አነስተኛ ሆኖ የሚቀጥል ነገር ይሻላል፡፡ ከዉርድህ ብትዘናጋ ወይም ብትተኛና ቢያልፍህ በበነጋው ቀዷ አውጣው፡፡ ይህን በተመለከተ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ከዉርዱ ወይም ከሌላ ነገሩ የተኛና ከሱብሂ እስከ ዙህር ድረስ ባለው ሰዐት ቀዷ ማውጣት የቻለ ሰው በሌሊት እንዳነበበው /እንደሰራው/ይቆጠርለታል) ብለዋል፡፡

ቁርአንን በየትኛዉም መልኩ ከመቅራት፤ በአንቀፆቹ ላይ ከመመራመር ማሰተንተንን ከሚዘናጉት፤ ትዕዛዛቱን ከመተግበርና ቁርአንን ለመድሀኒትነት ከመጠቀም ችላ ካሉት ዉስጥ አትሁን አደራ፡፡

## 1ኛው ምዕራፍ፡- (ሱረቱ አል-ፋቲሀ) የመክፈቻው ምዕራፍ ነው ::[1] አንቀጾቹ 7 ናቸው ::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው(እጀምራለሁ)።




(1) በአላህ[2] ስም እጅግ በጣም ሩህሩህና በጣም አዛኝ በኾነው እጀምራለሁ[3]።
(2) ምስጋና[4] ሁሉ[5] የዓለማት[6] ጌታ[7] ለኾነው፣ ለአላህ ይገባው ።
(3) (4) እጅግ በጣም ሩህሩህ፤ በጣም አዛኝና የፍርዱ[8] ቀን ባለቤት ለኾነው ።[9]
(5) አንተን ብቻ እንገዛለን፣[10] አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን።
(6) ቀጥተኛውን[11] መንገድ ምራን።

---

[1] የመክፈቻው ምዕራፍ ከሱረቱ አል-ሙደሲር በኋላና ከሱረቱ አል-ሙዘሚል በፊት በ3ኛነት መውረዱን ብዙ አሊሞች አስተምረዋል። እንደዚሁም ብዛት ያላቸው ዐሊሞች ይህ ምዕራፍ በመካ የወረደ ምዕራፍ መሆኑን ሲናገሩ፤
አንዳንዶች ደግሞ በ1ኛነት የወረደ ነው ይላሉ። ሆኖም ይህ አባባል ሙሉው ምዕራፉ በአንድ ጊዜ በመውረድ የመጀመሪያው ነው ማለት እንደሆነ ተናግረዋል። ሌሎች አሊሞች ደግሞ ይህ ምዕራፍ በመዲና ነው የወረደው ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ ሁለቱን አባባሎች ለማስማማት ሁለት ጊዜ ነው የወረደው በማለት ልዩነቱን ለመፍታት ሞክረዋል። አንቀፃቹ ሁሉም አሊሞች ሰባት መሆናቸውን ሲስማሙ ሐሰኑል በስሪ የተባሉ አንድ አሊም ብቻ ስምንት ናቸው ብለዋል።
*መግቢያ፡-* ይህ የቁርአን ምዕራፍ በተከበረው ቅዱስ ቁርአን አቀማመጥ ቅደም ተከተል መሰረት በመጀመሪያው ረድፍ ላይ ይገኛል። የምዕራፉ ሰባት አንቀጾች ለሁለት ይከፈላሉ። ሶስት አንቀጽ ተኩል ስለ አላህ ሲያወሱ ሶስት አንቀጽ ተኩል ደግሞ ስለ አገልጋዩ ያስታወሳሉ።
ምዕራፉን ከሌሎች የቁርአን ምዕራፎች ለየት ከሚያደርጉት ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-
1ኛ ማንኛውም ሙስሊም በየቀኑ ቢያንስ ለ17 ጊዜ በየሰላቱ ረከዐ ላይ እንዲያነበው መገደዱ፣ 2ኛ በቁርአን አቀማመጥ ቅደም ተከተል መሰረት በአንደኛ ተራ ቁጥር ላይ መቀመጡ፣ 3ኛ የተለያዩ መጠሪያዎች ያሉት መሆኑ ነው።

[2] ይህ ስም ከአላህ ሌላ ለማንም የማይጠቀሙት ስም ነው። አንዳዶቹ እንዴዉም አላህ ተለምኖበት እንቢ የማይልበት ታላቁ ስሙ ይህ ነዉ ብለዋል።

[3] አር-ረህማን የሚለው ቃልም ከአላህ ሌላ ለማንም የማይጠቀሙበት ስም ሲሆን፤ መልዕክቱም ከአረሂም የበለጠና የሰፋ ነው። ምክኒያቱም ይህ ስሙ ፍጡር የተባለን ሁሉ አማኝ፤ ከሃዲ፤ አመፀኛ፤ ታዛዥ፤ ሰው፤ እንስሳ፤ ትልቅ፤ ትንሽ ሳይባል የሚያጠቃልል ነውና።

[4] ምስጋና ማለት ለተለገሰለት ውለታ በምላስ ማወደስ ነው። ሐምድና ሹክር የተባሉት የዓረብኛ ቃላት ተቀራራቢ መልዕክት ያላቸው ሲሆኑ ሐምድ በምላስ፣ ብቻ ማወደስን የሚወክል ሲሆን፤ ሹክር ደግሞ በምላስ በልብና በአካል ማወደስን ይወክላል። ሹክር ከዉለታ በኋላ ሲሆን ሐምድ ደግሞ ተመስጋኙ ካለው ምሉዕ ባህሪ ብቻ ተነስቶ የሚፈፀም ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ለአላህ ሐምድም ሆነ ሹክር ይገባዋል።

[5] ‹ሁሉ› የሚለው መልዕክት (አል) ከምትለው የዐረብኛ ቃል የተወሰደ መልዕክት ነው። ይህም ማለት ምስጋና ሁሉ የአላህ ብቻ ነው ማለት ነው። እዚህ ላይ የሰው ልጅ ምንም አስተዋፆኦ ያላደረገባቸው ነገሮችን አስታውሶ የሚደረጉ ምስጋናዎችን በተመለከተ ለአላህ የመሆኑ ጉዳይ ለሁሉም ግልጽ ሲሆን፤ ሰው ለሰው ከሚዉለው መልካም ተግባር በመነሳት ሰዎች በሚመሰገኑበት ጉዳይ ላይም ቢሆን መልካም ሰሪዎችን በመፍጠርና መልካሙን ተግባር እንዲፈጽሙ ያስቻለ እሱ ብቻ በመሆኑ ከዚህ አኳያ ሲታይ ምስጋና የተባለው ሁሉ ለአላህ መሆኑ ግልፅ ነው።

[6] ዓለም ማለት ብዙ ዐሊሞች ከአላህ ሌላ የሆነው ነገር ሁሉ ማለት ነው ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ ዓለም ማለት የእውቀት ባለቤት የሆኑት ፍጡራን ብቻ፣ ማለትም፤- ሰው፤ መላኢካ፤ ጋኔንና ጂን ማለት ነው ብለዋል። ይህ ሁሉ ደግሞ የአላህ ታዛዥ ነው። የእሱንም እርዳታ ፈላጊ መሆኑ ግልፅ ነው።

[7] (ጌታ) የሚለው ቃል ከአላህ ስሞች መካከል አንዱ ሲሆን ያለምንም ገደብ ከሆነ መጠቀም የሚቻለው ለአላህ ብቻ ይሆናል። ከገደብ ጋር ከሆነ ግን፡- ለምሳሌ የቤቱ ጌታ፤ የንብረቱ ጌታ፤ የመርከቡ ጌታ…በሚል ለሌላም አካል መጠቀም ይቻላል። ከዚህ በመነሳት በሀገራችን ካሉ ስሞች መካከል ጌታነህ፤ ጌታመሳይ፤ ጌታቸውና ›…የመሳሰሉት ስሞችን ሙስሊሞች ሊርቁት ግዴታ ነው።

[8] የምንዳው ቀን ማለት ነው። ቀታዳ የተባሉ አንድ ዓሊም የምንዳው ቀን ማለት፡- አላህ ሰዎችን በተግባራቸው መጥፎም ይሁን ደግ የሚመነዳበት ቀን ማለት ነው ብለዋል።

[9] አምላክነት፤ ጌትነትና ንጉስነት በዚህ ሱራህ በአንድ እንደሰበሰባቸው ሁሉ የቁርአኑ መጨረሻ ላይ በተቀመጠው ሱራህም ላይ እንዲሁ በአንድ ሰብስቧቸዋል ። ይህ ድርጊት የሚያስተምረው ነገር ቢኖር በእነዚህ ወሳኝ በሆኑ ቦታዎች ማለትም በቁርአን መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በአንድ የመጠቀሳቸው ሚስጥር በጣም አስፈላጊ በመሆናቸው መሆኑን አውቆ በደንብ ሊጤኑ ይገባል ለማለት ነው ።

[10] አምልኮ ማለት ቋንቋዊ ትርጉሙ የመተናነስ የመጨረሻው ጣራ ማለት ነው። ይህም በሸሪዓችን የማፍቀር፤የመተናነስና የመፍራት ጣራ መድረስ ማለት ነው። አምልኮን በቅድሚያ የማውሳቱ ምክኒያት የመጀመሪያዉ ወደ ሁለተኛው መዳረሻ በመሆኑ ነው። ኢብኑ ዐባስ፡- “አንተን ብቻ እንገዛለን” ባለው አንቀፅ ላይ፡- “አንተን ብቻ አንድ እናደርጋለን፤ ሌላን ሳይሆን አንተን ብቻ እንፈራለን ። አንተን ለመታዘዝም ለሌሎቹ ጉዳዩቻችን አንተን ብቻ እርዳታ እንጠይቃለን ማለት ነው” ብለዋል።

[11] ቀጥተኛውን/ቅንነት የሚለው ቃል ለሁለት ይከፈላል። አንደኛው፡- መንገዱን በትክክልና በተግባር ማስያዝ ማለት ሲሆን፤ ይህ አይነቱ ማቅናት የአላህ ብቻ ስልጣን ነው ። ሁለተኛው፡- ደግሞ የማመላከት ማቅናት ሲሆን ይህ ደግሞ የነቢያትና የተከታዩቻቸው የአስተማሪዎችና የዱዓቶች ተግባር ነው ። ሆኖም አንቀፁ ሁሉንም ያመለክታል ። ምክኒያቱም አላህ ኸይርን የሚያሰራው ራሱ ሲሆን፤ ወደ እዚሁ እንዲመሩንም ነቢያትን የላከው

(7) የእነዚያን በእነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን[1] በእነርሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውን [2]እና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ ምራን (በሉ)

## 58 ኛው ምዕራፍ፡-(ሱረቱ አል-መጃደለህ/ሙጃዲለህ) የክርክሩ/የተከራካሪዋ ሴት/ ምዕራፍ ነው፡፡[3] አንቀጾቹ 22 ናቸው ፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

(1) አላህ[4] የዚያችን በባሏ ጉዳይ ላይ የምትከራከርህንና ወደ አላህ ስሞታ የምታሰማውን ሴትዮ ቃል ሰማ። አላህ በንግግር መመላለሳችሁን /መወያየታችሁን/ ይሰማል። አላህ ሰሚና ተመልካች ነውና።
(2) እነዚያ ከእናንተ ውስጥ ሚስቶቻቸውን እንደእቱቋበባን ጀርባዎች ይሁኑብን በማለት የሚምሉ እነሱ እናቶቻቸው አይደሉም፡፡ ትክክለኛ እናቶቻቸው እነዚያ የወለዷዋቸው ሴቶች ብቻ ናቸው። እነርሱ (በዚህ ቃል) የተጠላ ንግግርንና ውሸትን በእርግጥ ይናገራሉ[5]፡፡ አላህ (ለሚጸጸት ሰው ሁሉ) ይቅር ባይና መሓሪ ነው።

| | |
|---|---|
| سُورَةُ المُجَادلَة | ترتيبها ٥٨ — آياتها ٢٢ |

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

قَدۡ سَمِعَ ٱللَّهُ قَوۡلَ ٱلَّتِي تُجَٰدِلُكَ فِي زَوۡجِهَا وَتَشۡتَكِيٓ إِلَى ٱللَّهِ
وَٱللَّهُ يَسۡمَعُ تَحَاوُرَكُمَآۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعُۢ بَصِيرٌ ١ ٱلَّذِينَ يُظَٰهِرُونَ
مِنكُم مِّن نِّسَآئِهِم مَّا هُنَّ أُمَّهَٰتِهِمۡۖ إِنۡ أُمَّهَٰتُهُمۡ إِلَّا ٱلَّٰٓـِٔي
وَلَدۡنَهُمۡۚ وَإِنَّهُمۡ لَيَقُولُونَ مُنكَرٗا مِّنَ ٱلۡقَوۡلِ وَزُورٗاۚ وَإِنَّ
ٱللَّهَ لَعَفُوٌّ غَفُورٞ ٢ وَٱلَّذِينَ يُظَٰهِرُونَ مِن نِّسَآئِهِمۡ ثُمَّ يَعُودُونَ
لِمَا قَالُواْ فَتَحۡرِيرُ رَقَبَةٖ مِّن قَبۡلِ أَن يَتَمَآسَّاۚ ذَٰلِكُمۡ تُوعَظُونَ
بِهِۦۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ خَبِيرٞ ٣ فَمَن لَّمۡ يَجِدۡ فَصِيَامُ شَهۡرَيۡنِ
مُتَتَابِعَيۡنِ مِن قَبۡلِ أَن يَتَمَآسَّاۖ فَمَن لَّمۡ يَسۡتَطِعۡ فَإِطۡعَامُ سِتِّينَ
مِسۡكِينٗاۚ ذَٰلِكَ لِتُؤۡمِنُواْ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦۚ وَتِلۡكَ حُدُودُ ٱللَّهِۗ
وَلِلۡكَٰفِرِينَ عَذَابٌ أَلِيمٌ ٤ إِنَّ ٱلَّذِينَ يُحَآدُّونَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ كُبِتُواْ
كَمَا كُبِتَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡۚ وَقَدۡ أَنزَلۡنَآ ءَايَٰتِۢ بَيِّنَٰتٖۚ وَلِلۡكَٰفِرِينَ
عَذَابٞ مُّهِينٞ ٥ يَوۡمَ يَبۡعَثُهُمُ ٱللَّهُ جَمِيعٗا فَيُنَبِّئُهُم بِمَا
عَمِلُوٓاْۚ أَحۡصَىٰهُ ٱللَّهُ وَنَسُوهُۚ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ ٦

(3) እነዚያ ሚስቶቻቸውን (እንደእናቶቻችን ጀርባዎች ሁኑብን) በማለት የሚምሉና ከእዚያም ወደ ተናገሩት የሚመለሱ[6] ሳይነካኩ[7] በፊት በባርነት የተያዙትን ጫንቃን[8] ነጻ ማውጣት ግዴታ አለባቸው። ይህ ህግ[9] በእርሱ ትገሰጹበታላችሁ[10]፡፡ አላህ ለምትሰሩት ነገር ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው።
(4) ይህን ያላገኘም[11] ሰው ከመነካካታቸው በፊት ሁለት ተከታታይ[12] ወሮችን መጾም አለበት፡፡ ይህን ያልቻለም[13] ሰው ስልሳ

---

፤ዐሊሞችን የፈጠረዉና ለማስተማር ያበቃው እሱው ራሱ ነውና ፡፡ ቀጥተኛው መንገድ ማለት አባጣ ጎባጣ የሌለው መንገድ ማለት ሲሆን፤ በእዚህ አንቀፅና በመሰሎቹ ላይ የታሰበው ኢስላም ማለት ነው ፡፡

1 እነሱም ከነቢያት፤ ሰምአ ት ...) በሚለው የቁርአን አንቀፅ የተወሱት ስመ ጥሩ አካሎች ናቸው ፡፡

2 እንደ አይሁድ ያሉ አውቆ ጠፎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም አይሁዶች እውነትን አውቀው ስለተዉት የአላህ ቁጣ ወረደባቸው ፡፡ ክርስቲያኖች ደግሞ ባለማወቅ ሀቅን በመተዋቸው ስለ ነቢዩ ጉዳይ በግልፅ ስህተት ላይ ሆኑ ፡፡ በዚህ ሱራ ንባብ መጨረሻ ላይ አሚን (ዱዓችንን ተቀበለን) የሚለዉን ቃል ማንበብ ተገቢ ነው ፡፡ አህመድና ኢብኑ ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ ነቢዩ (ﷺ) (አይሁድ በሰላምታ እና በአሚን የተመቀኟችሁን ያህል በምንም ነገር አልተመቀኟችሁም ፡፡ ብለዋል፡፡

3 ምዕራፉ በመዲና ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው፡፡

4 1ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክኒያት፡- ኸውለህ ቢንቱ ሰዕለባህ የተባለች አንዲት ሴት ሰሃቢይ በቀላል ነገር አውስ ቢን ሳቢት ከተባለ ባሏ ጋር ተኮራርፌው ሳሉ «ከዛሬ ጀምሮ አንቺ እንደ እናቴ ነሽ» ስላላት ወደ ነቢዩ (ﷺ) በመምጣት፡- “ይህ ሰው ወጣትነቴን በልቶ እድሜዬ ሲገፋና መውለድ ሳቋርጥ እንደ እናቴ ነሽ አለኝ፡፡ ምን ይሻለኛል?» አለቻቸው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)፡- “ምንም መፍትሄ እስከ አሁን እኔ ጋር የለሽም» በማለታቸው እሳቸው አጠገብ ቁማ፡- «ጌታዬ ሆይ !ወደ አንተ ስሞታዬን አቀርባለሁ» እያለች ስታማርር ነው እነኚህ አንቀጾች የወረዱት፡፡ ስለዚህ ታሪክ ተአምርነት እሜቴ አይሻ ሲናገሩ ኸውላ ነቢዩን ስለዚህ ጉዳይ ስታናግር ግማሽ አባባሏን ብቻ እሰማ ነበር እንጂ ሙሉ በሙሉ አልሰማሁም፡፡ ሁሉን ነገር የሰማው ጌታ አላህ ግን አንድም ነገር ሳይቀር ሰምቷት ቁርአን አወረደላት» በማለት ገልፀውታል፡፡ (ዋሂዲ ና ሱዩጢ)

5 ሸሪዐው የሚጠላዉን ነገር አትናገሩ፡፡ እሱም ሚስትን በእናት መመሰል ነው። ምክኒያቱም የእናትን ክብር ይነካል።

---

6 «እንደ እናቴ ናች»ያሏቸዉን ሴቶች ለግንኙነት የሚፈልጉ ወይም እንደ እናቴ ነሽ ያሏቸዉን ሴቶች መፍታት እየቻሉ በሚስትነት የያዙ ማለት ነው፡

7 የግብረ ሥጋ ሳይፈፅሙ ማለት ነው፡፡

8 ወንድ ባሪያን ወይም ሴት ባሪያን ከባርነት ኑሮ ነፃ ማውጣት አለባቸው ማለት ነው፡፡

9 ከላይ የተጠቀሰው ህግ፡፡

10 ሚስትን፡- «አንቺ እንደ እናቴ ነሽ» ከማለት ወንጄል ትመከሩበታላችሁ፡፡

11 በእጁ የሌለውና መግዛትም አቅም የሌለው ወይም የሚገዛ ባሪያ ፈልጎ በገበያ ላይ ያጣ፡፡

12 አንድም ቀን ሳያፈጥር ይጹም፡፡ ያለበቂ ምክኒያት ካፈጠረ በአዲስ ይጀምራል፡፡ በቀንም ሆነ በማታ ሆን ብሎ ከእርሷ ጋር ግንኙነት ቢፈፅምም እንደዚሁ እንደ አዲስ ይጀምራል፡፡

13 ሁለት ወራት አከታትሎ መፆም ያልቻለ፡፡

أَلَمْ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يَعْلَمُ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۖ مَا يَكُونُ
مِن نَّجْوَىٰ ثَلَٰثَةٍ إِلَّا هُوَ رَابِعُهُمْ وَلَا خَمْسَةٍ إِلَّا هُوَ سَادِسُهُمْ
وَلَآ أَدْنَىٰ مِن ذَٰلِكَ وَلَآ أَكْثَرَ إِلَّا هُوَ مَعَهُمْ أَيْنَ مَا كَانُوا۟ ۖ ثُمَّ يُنَبِّئُهُم
بِمَا عَمِلُوا۟ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمٌ ﴿٧﴾ أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ
نُهُوا۟ عَنِ ٱلنَّجْوَىٰ ثُمَّ يَعُودُونَ لِمَا نُهُوا۟ عَنْهُ وَيَتَنَٰجَوْنَ بِٱلْإِثْمِ
وَٱلْعُدْوَٰنِ وَمَعْصِيَتِ ٱلرَّسُولِ وَإِذَا جَآءُوكَ حَيَّوْكَ بِمَا لَمْ يُحَيِّكَ
بِهِ ٱللَّهُ وَيَقُولُونَ فِىٓ أَنفُسِهِمْ لَوْلَا يُعَذِّبُنَا ٱللَّهُ بِمَا نَقُولُ ۚ حَسْبُهُمْ
جَهَنَّمُ يَصْلَوْنَهَا ۖ فَبِئْسَ ٱلْمَصِيرُ ﴿٨﴾ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ إِذَا
تَنَٰجَيْتُمْ فَلَا تَتَنَٰجَوْا۟ بِٱلْإِثْمِ وَٱلْعُدْوَٰنِ وَمَعْصِيَتِ ٱلرَّسُولِ وَتَنَٰجَوْا۟
بِٱلْبِرِّ وَٱلتَّقْوَىٰ ۖ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ ٱلَّذِىٓ إِلَيْهِ تُحْشَرُونَ ﴿٩﴾ إِنَّمَا ٱلنَّجْوَىٰ
مِنَ ٱلشَّيْطَٰنِ لِيَحْزُنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَلَيْسَ بِضَآرِّهِمْ شَيْـًٔا
إِلَّا بِإِذْنِ ٱللَّهِ ۚ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلْيَتَوَكَّلِ ٱلْمُؤْمِنُونَ ﴿١٠﴾ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ
ءَامَنُوٓا۟ إِذَا قِيلَ لَكُمْ تَفَسَّحُوا۟ فِى ٱلْمَجَٰلِسِ فَٱفْسَحُوا۟ يَفْسَحِ
ٱللَّهُ لَكُمْ ۖ وَإِذَا قِيلَ ٱنشُزُوا۟ فَٱنشُزُوا۟ يَرْفَعِ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟
مِنكُمْ وَٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْعِلْمَ دَرَجَٰتٍ ۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ ﴿١١﴾

ድሆችን ማብላት አለበት፡፡[1] ይህ በአላህና በመልዕክተኛው እንድታምኑ ነው[2]። እነኚህ (ህግጋት) የአላህ ህግጋት ናቸው፡፡ (እናም አትተላለፏቸው፡፡) ለከሓዲዎችም[3] አሳማሚ ቅጣት አለባቸው።

(5) ግልጽ ማስረጃዎችን ያወረድን ስንሆን እነዚያ አላህንና መልዕክተኛውን የሚከራከሩ ሰዎች[4] እነዚያ ከእነሱ በፊት የነበሩት ሰዎች እንደተዋረዱት ሁሉ ተዋርደዋል፡፡ ለከሓዲዎች አዋራጅ ቅጣት አለባቸው።

(6) አላህ ሁላቸውንም በአንድ አድርጎ/አንድም ሳይቀር በአንድ አይነት/ በሚቀሰቅሳቸው ቀን (ይቀጣቸዋል ፡፡) ከዚያም በዚህች ዐለም የሰሩትን (መጥፎ ነገር) ሁሉ ይነግራቸዋል ፡፡ እነሱ የረሱት ሲሆኑ በየግል መዝገባቸው ተመዝግቦ ያገኙታል፡፡ አላህ ግን አንድም ሳይቀር አውቆታል። አላህ ሁሉንም ነገር ተመልካች ነውና።

(7) (ሙሐመድ ሆይ!) አላህ በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያውቅ መሆኑን አታውቅምን? (በእውቀቱ ሁሉንም አካቢል ፡፡) የሦስት ሰዎች መሾካሾክ አይከሰትም፣ አላህ አራተኛቸው[5] ቢሆን እንጂ፤ የአምስትም ሰዎች መሾካሾክ አይከሰትም እርሱ ስድስተኛቸው ቢሆን እንጂ፤ ከዚያ ያነሰም ይሁን[6] የበዛ ሰው መሾካሾክ አይከሰትም[7] እርሱ ባሉበት ቦታ አብሮዋቸው ቢሆን እንጂ ፡፡[8] ከዚያም በትንሳኤ ቀን የሰሩትን ሁሉ ይነግራቸዋል ። አላህ ሁሉን ነገር አዋቂ ነው።

(8) (ሙሐመድ ሆይ!) ወደ እነዚያ በመጥፎ ነገር ከመመሳጠር ወደ ተከለከሉት፣ ከዚያም ከእርሱ ወደ ተከለከሉት ነገር ወደ ሚመለሱትና[9] መልዕክተኛውን በመቃወም[10] ወደ ሚመሳጠሩ አላየህምን ? ሰላም ሊሉ ወደ አንተ በመጡም ጊዜ አላህ ባላናገረብህ ቃል ያናግሩሃል፡፡[11] በዉስጣቸው-(ይህ ሰው ነቢይ ከሆነ) በምንለው ነገር አላህ አይቀጣንም ሮአልን?(ነቢይ ከሆነስ) የለመነዉን ነገር አላህ ተቀብሎት በሞትን ነበር፣ ይላሉ። ገሀነም -የሚገቡባት ሲሆኑ (ከአሁኑ ሞት ይልቅ) በቂያቸው ናት፡፡ ገሀነም መመለሻነቷ ከፋች!

(9) እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! በተመሳጠራችሁ ጊዜ በኃጢአት፤ወሰንን በማለፍና መልዕክተኛውንም በመቃወም አትሾካሾኩ። ግን በበጎ ስራና አላህን በመፍራት ተወያዩ፡፡ ያንንም ወደ እርሱ የምትሰበሰቡበትን አላህን ፍሩ።

(10) በመጥፎ መመሳጠር[12] ከሰይጣን (ማስዋብና ማሳመር የሚመጣ ብቻ ነው። እነዚያ ያመኑ ሙስሊሞች ያዝኑ ዘንድ(ይቀሰቅሰዋል) ፡፡ በአላህ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር (ሰይጣን ወይም መመሳጠር) በምንም (ነገር) አይጎዳቸውም፡፡

---

[1] ለእያንዳንዱ ድሃ አንድ ኪሎ ተኩል ስንዴ፣ ተምር፣ እሩዝ፣ መሰሉን እህል ወይም የተዘጋጀ ምግብን መስጠት ይቻላል ፡፡ ወይም ስልሳ ሰዎችን የሚያጠግባቸዉን ያህል መስጠት ይችላል፡፡

[2] ይህን የደነገገው አላህ (ﷻ) ማዘዙንና መደንገጉን አምናችሁ በህጉ እንድትመሩ፤ በቸልተኝነት እንዳታልፉትና ክልክል ወደ ሆነው ወደ ዚሃር እንዳትመለሱ ነው ፡፡

[3] ህግጋትን የማያከብሩ ፡፡

[4] የሚፃረሩ፤ የሚነቅፉ ፡፡

[5] ያችን ዉይይት የተጋራቸው ፡፡ የሰማቸው፡፡

[6] አንድና ሁለትን ይመስል፡፡

[7] ስድስትና ሰባትን ይመስል፡፡

[8] አላህ ምንጊዜም ከሰዎች ጋር ነው ፡፡ ከርሱ የተሰወረ ነገር የለም፡፡

[9] ከ8-10 ያሉት አንቀፆች የወረዱበት ምክንያት ፡- አይሁዶች በአጠገባቸው ሙስሊሞች ሲያልፍ በእነሱ ተንኮል እያሰቡ ነው ብለው እንዲጠራጠሩ እርስ በራሳቸው ይሾካሾኩ ነበርና ከዚህ ተግባራቸው ተከልክለው ስላልተዉት ነው፡፡

[10] በኃጢአት-አማኞችን በማማት; በማስቃየት እና የመሳሰሉትን ወንጀሎች ዉሸትና ሰዎችን መበደል የመሳሰለዉን በመፈጸም፣ እንዲሁም ድንበርን በማለፍና ሙስሊሞችን አዛ በማድረግ፡፡

[11] ነቢዩን ሰላም ሲሉ «አሳሙ ዐለይኩም» በማለት ሰላምታ ያቀረቡ መስለው ዉስጡን ግን ሞት ይመኙባቸው ስለነበርና ነቢዩ መልስ ሲሰጡ «በእናንተም ላይ» ይሉ ስለነበር ነው ፡፡

[12] በኃጢአት፤ ወሰንን በማለፍና መልክተኛውንም በመቃወም)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا نَٰجَيۡتُمُ ٱلرَّسُولَ فَقَدِّمُواْ بَيۡنَ يَدَيۡ نَجۡوَىٰكُمۡ
صَدَقَةٗۚ ذَٰلِكَ خَيۡرٞ لَّكُمۡ وَأَطۡهَرُۚ فَإِن لَّمۡ تَجِدُواْ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٌ
﴿١٢﴾ ءَأَشۡفَقۡتُمۡ أَن تُقَدِّمُواْ بَيۡنَ يَدَيۡ نَجۡوَىٰكُمۡ صَدَقَٰتٖۚ فَإِذۡ لَمۡ تَفۡعَلُواْ
وَتَابَ ٱللَّهُ عَلَيۡكُمۡ فَأَقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُواْ ٱلزَّكَوٰةَ وَأَطِيعُواْ ٱللَّهَ
وَرَسُولَهُۥۚ وَٱللَّهُ خَبِيرُۢ بِمَا تَعۡمَلُونَ ﴿١٣﴾ ۞ أَلَمۡ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ تَوَلَّوۡاْ قَوۡمًا
غَضِبَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِم مَّا هُم مِّنكُمۡ وَلَا مِنۡهُمۡ وَيَحۡلِفُونَ عَلَى ٱلۡكَذِبِ
وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ ﴿١٤﴾ أَعَدَّ ٱللَّهُ لَهُمۡ عَذَابٗا شَدِيدًاۖ إِنَّهُمۡ سَآءَ مَا كَانُواْ
يَعۡمَلُونَ ﴿١٥﴾ ٱتَّخَذُوٓاْ أَيۡمَٰنَهُمۡ جُنَّةٗ فَصَدُّواْ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ فَلَهُمۡ
عَذَابٞ مُّهِينٞ ﴿١٦﴾ لَّن تُغۡنِيَ عَنۡهُمۡ أَمۡوَٰلُهُمۡ وَلَآ أَوۡلَٰدُهُم مِّنَ ٱللَّهِ
شَيۡـًٔاۚ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿١٧﴾ يَوۡمَ يَبۡعَثُهُمُ
ٱللَّهُ جَمِيعٗا فَيَحۡلِفُونَ لَهُۥ كَمَا يَحۡلِفُونَ لَكُمۡۖ وَيَحۡسَبُونَ أَنَّهُمۡ عَلَىٰ شَيۡءٍۚ أَلَآ
إِنَّهُمۡ هُمُ ٱلۡكَٰذِبُونَ ﴿١٨﴾ ٱسۡتَحۡوَذَ عَلَيۡهِمُ ٱلشَّيۡطَٰنُ فَأَنسَىٰهُمۡ ذِكۡرَ
ٱللَّهِۚ أُوْلَٰٓئِكَ حِزۡبُ ٱلشَّيۡطَٰنِۚ أَلَآ إِنَّ حِزۡبَ ٱلشَّيۡطَٰنِ هُمُ ٱلۡخَٰسِرُونَ
﴿١٩﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ يُحَآدُّونَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥٓ أُوْلَٰٓئِكَ فِي ٱلۡأَذَلِّينَ ﴿٢٠﴾
كَتَبَ ٱللَّهُ لَأَغۡلِبَنَّ أَنَا۠ وَرُسُلِيٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ قَوِيٌّ عَزِيزٞ ﴿٢١﴾

እናም አማኞች በአላህ ብቻ ይመኩ።[1]
11 እናንተ[2] ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ለእናንተ በመቀመጫዎች ስፍራ ተስፋፉ በተባላችሁ ጊዜ[3] ስፍራን አስፉ። አላህ (በጀነት) ያሰፉላችኋልና።[4] ተነሱ በተባለም ጊዜ ተነሱ። አላህ ከእናንተ እነዚያን ያመኑትንና እነዚያንም እውቀትን የተሰጡትን በደረጃዎች (በዚች ዐለምም ሆነ በአኺራ)ከፍ ያደርጋል[5]። አላህ በምትሰሩት ነገር ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነውና።
12 እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ከመልዕክተኛው ጋር በተወያያችሁ ጊዜ[6] ከመወያየታችሁ በፊት ምጽዋትን አስቀድሙ (ሰደቃ ስጡ)። ይህ (ምጽዋትን አስቀድሞ መስጠት)[7] ለእናንተ መልካምና አጥሪ ነው ። ባታገኙም (ምንንም ሳትከፍሉ ብትወያዩ ችግር የለባችሁም ።) አላህ መሓሪና አዛኝ ነውና።
13 ከውይይታችሁ[8] በፊት ምጽዋቶችን ከማስቀደም (ድህነትን)ፈራችሁን?[9] (የታዘዛችሁትን) ባልሠራችሁም ጊዜ አላህ ከእናንተ ጸጸትን የተቀበለ ሲሆን፣ ሶላትን ስገዱ። ዘካንም ስጡ። አላህንና መልዕክተኛውን ታዘዙ። አላህ ውስጥ ዐዋቂ ነውና።
14 ወደ[10] እነዚያ አላህ በእነርሱ ላይ የተቆጣባቸውን ህዝቦች (አይሁዶችን) ወደ ተወዳጁት (መናፍቃን) አላየህምን? እነርሱ[11]

---

[1] ጉዳያቸዉን ሁሉ ወደ አላህ ያስጠጉ። ከሰይጣንም በእሱ ይጠበቁ። እሱ በሚሰጠው ማሳሳቻ ዘዴም አይሞኙ ።

[2] 11ኛው አንቀጽ የወረደበት ምክንያት፦ አንድ ቀን ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በጠባብ ቦታ ላይ ሳሉ የበድር ዘመቻ ተሳታፊ የነበሩ ሰዎች በጣም በህዝቡ ዘንድ ይከበሩ ስለ ነበር፤ ከእነሱ የተወሰኑ ሰዎች መጥተው መቀመጫ ቦታ አጥተው ከነቢዩ (ﷺ) ፊት ለፊት ቁጢጥ ብለው ተቀምጠው ሲጠባበቁ ነቢዩ (ﷺ) ካጠገባቸው ላሉ ሰዎች፦ «ተነሱና እነሱን አስቀምጡ»አሉ። ሙናፊቆች ይህችን ቀዳዳ በመጠቀም፦ «ይኸውላችሁ ሙሐመድ ፍትሐዊ ነው ስትሉ አልነበር? እሱን ወደው ከአጠገቡ የተቀመጡትን ሰዎች ለጓደኞቹ ሲል ያስነሳል» በማለት ስማቸውን ለማጥፋት ሲሯሯጡ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው (ዋሂዲ ና ሱዩጢ ።)

[3] ቀታዳና ሙጃሂድ ይህ አባባል ሙስሊሞች ከነቢዩ ሙሐመድ አጠገብ ለመቀመጥ ከነበራቸው ጉጉት የተነሳ አንዱ ለሌላው ቦታ እንዲያሰፋለት የታዘዙበት አንቀፅ ነው ብለዋል።

[4] ይህ አባባል ለጦርነትና ለዚክር ወይም ለጁሙዐና መሰል የኸይር ቦታዎች ሁሉ ያገለግላል። ሁሉም ሰው ቀድሞ ለያዘዉ ቦታ ባለቤት ነው። ሆኖም ለወንድሙ ያስፋለት። ነበዩ ሙሐመድ (ﷺ) "አንዱ ሌላዉን ከቦታው አያስነሳው ። ነገር ግን ተጠጋጉ›› ብለዋል።

[5] ስለዚህ ኢማንና እውቀት ያሰባሰበ ሰው በእምነቱና በእውቀቱ በደረጃው ከፍ ይላል።

[6] ሚስጥር ማውራት ባሰባችሁ ጊዜ።

[7] አላህ ይህን አንቀፅ ባወረደ ጊዜ አማኞች መክፈል ባለመቻላቸው ሲጨነቁ ምንንም መስጠት የማይፈልጉ ከሃዲዎች ግን ተገቱ;

[8] 13ኛው አንቀፅ የወረደበት ከእሳቸው ጋር በትንሽ በትልቁ ከመዋያየት ምክኒያት፦
በዚህው ሱራ ላይ (እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ከመልዕክተኛው ጋር ለመወያየት ባሰባችሁ ጊዜ ከመወያየታችሁ በፊት ምጽዋትን አስቀድሙ፣ የሚለው 12ኛው አንቀጽ ሲወርድ ነቢዩ ሙሀመድ ስለምጽዋቱ መጠን አንድ ዲናር ትሻላለች ይሆን? ብለው ሲጠይቋቸው ዐሊይ እሱንም አይችሉትም አሉ፡ ፡ ነቢዩ (ﷺ) መለስ አድርገው «ግማሽ ይሁን»አሉ። አልይም «እሱንም አይችሉም» ሲሉ ነብዩ (ﷺ) ታዲያ ምን ይሻላል? ሲሏቸው ገብስ ይሻላል አሏቸው «አንተ ራስህን ዝቅ ታደርጋለህ» አሉ። (ሱዩጢ)

[9] ሙቃቲል የተባሉ አንድ ዐሊም (ይህ ኢስላማዊ ህግ ለአስርት ቀናት ብቻ ቆይቶ ወዲያው የተሻረ ህግ ነው) ብለዋል።

[10] ከ14-19ኛው ያሉት አንቀፆች የወረዱበት ምክንያት፦ አብደላህ ቢን ነብተል የተባለ ሙናፊቅ ከነብዩ (ﷺ) ጋር ቆይቶ ለአይሁዶች ወሬ ያቀብልና ከዚያም ከዚህም እያለ ነገር ያመላልስ ነበር። አንድ ቀን ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) በቤታቸው ታዛ ሥር ተቀምጠው ባሉበት አሁን አይኑ የሰይጣን አይን፤ ልቡ አረመኔ የሆነ ሰው ይመጣል ብለው ተናገሩና ሲመጣ እንዳትናገሩት ብለው አስጠንቅቀው አንድ አይኑ ቢጫማ ከለር የሆነ ሰውዬ መጣና ነቢዩም (ﷺ) አንተና ጓደኞችህ ለምን ትሰድቡኛ አላችሁ በማለት ሲጠይቁት በፍጹም አልሰደብንም ሲል ሰዎችን አስጠሩዋቸውና፣ እንደሱው ብለው በመካዳቸውና ማስረጃ ሲጠፋ ነው ለምስክርነት የወረደው ። (ዋሂዲ እና ሱዩጢ።)

[11] አላህ ስለ እነሱ (ወላዋዮች ሆነው ወደ እነዚህም ወደ እነዚያም አይደሉም) እንዳለው ሁሉ ከእናንተ አይደሉም ለአይሁዶችም ሊሆን ይችላል ማለት

لَّا تَجِدُ قَوْمًا يُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْـَٔاخِرِ يُوَآدُّونَ مَنْ
حَآدَّ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَلَوْ كَانُوٓا۟ ءَابَآءَهُمْ أَوْ أَبْنَآءَهُمْ
أَوْ إِخْوَٰنَهُمْ أَوْ عَشِيرَتَهُمْ ۚ أُو۟لَـٰٓئِكَ كَتَبَ فِى قُلُوبِهِمُ
ٱلْإِيمَـٰنَ وَأَيَّدَهُم بِرُوحٍ مِّنْهُ ۖ وَيُدْخِلُهُمْ جَنَّـٰتٍ تَجْرِى
مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَـٰرُ خَـٰلِدِينَ فِيهَا ۚ رَضِىَ ٱللَّهُ عَنْهُمْ وَرَضُوا۟
عَنْهُ ۚ أُو۟لَـٰٓئِكَ حِزْبُ ٱللَّهِ ۚ أَلَآ إِنَّ حِزْبَ ٱللَّهِ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ ﴿٢٢﴾

## سُورَةُ الحَشْرِ

ترتيبها ٥٩ — آياتها ٢٤

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَـٰنِ ٱلرَّحِيمِ

سَبَّحَ لِلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۖ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ
﴿١﴾ هُوَ ٱلَّذِىٓ أَخْرَجَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ مِنْ أَهْلِ ٱلْكِتَـٰبِ مِن دِيَـٰرِهِمْ
لِأَوَّلِ ٱلْحَشْرِ ۚ مَا ظَنَنتُمْ أَن يَخْرُجُوا۟ ۖ وَظَنُّوٓا۟ أَنَّهُم مَّانِعَتُهُمْ
حُصُونُهُم مِّنَ ٱللَّهِ فَأَتَىٰهُمُ ٱللَّهُ مِنْ حَيْثُ لَمْ يَحْتَسِبُوا۟ ۖ وَقَذَفَ
فِى قُلُوبِهِمُ ٱلرُّعْبَ ۚ يُخْرِبُونَ بُيُوتَهُم بِأَيْدِيهِمْ وَأَيْدِى ٱلْمُؤْمِنِينَ
فَٱعْتَبِرُوا۟ يَـٰٓأُو۟لِى ٱلْأَبْصَـٰرِ ﴿٢﴾ وَلَوْلَآ أَن كَتَبَ ٱللَّهُ عَلَيْهِمُ
ٱلْجَلَآءَ لَعَذَّبَهُمْ فِى ٱلدُّنْيَا ۖ وَلَهُمْ فِى ٱلْـَٔاخِرَةِ عَذَابُ ٱلنَّارِ ﴿٣﴾

ከናንተ አይደሉም። ከእነርሱም አይደሉም ።
እያወቁ በውሸት[1] ይምላሉ ።
15 አላህ ለእነርሱ (በዚህ መወዳጃና የሐሰት
መሐላ) ብርቱን ቅጣት አዘጋጀ ። እነሱ
ይሰሩት የነበሩት መጥፎ ስራ ምንኛ ከፋ!
16 መሓሎቻቸውን ጋሻ[2] አድርገው ያዙ።
ሰዎችንም ከአላህ መንገድ አገዱ[3] ። ስለ
እዚህ ለእነሱ አዋራጅ ቅጣት አለባቸው ።
17 ገንዘቦቻቸውና ልጆቻቸው ከአላህ (ቅጣት)
ምንም አያድኗቸውም ። እነዚያ የእሳት ጓዶች
ናቸው። እነሱ በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው።
18 ይህ የሚሆነው አላህ የተሰበሰቡ ሆነው
በሚያስነሳቸው (የቂያማ) ቀን ነው።
ለእናንተ እንደሚምሉላችሁ፣ (በሚጠቅም)
ነገር ላይ መሆናቸውን የሚያስቡ ሆነው
ለእርሱም (ለአላህ) ይምላሉ[4]። ንቁ!
ውሸታሞች እነርሱ ብቻ ናቸው።
19 በእነርሱ ላይ ሰይጣን ተሾመባቸው
(ተመቻቸባቸው)። እናም አላህን
ማስታወስን አስረሳቸው (ትዕዛዛቱን ተዉ)።
እነዚያ የሰይጣን ጭፍሮች (ቡድኖች፤
ሰራዊቶች)ናቸው። ንቁ! የሰይጣን ጭፍሮች
(ቡድኖች)[5] ከሳሪዎች እነርሱ ብቻ ናቸው።
20 እነዚያ አላህንና መልዕክተኛውን የሚከራከሩ
ሁሉ እነዚያ (በዱንያም ሆነ በአኺራ)
በጣም ከተዋረዱ ወገኖች ውስጥ ናቸው።
21 አላህ፦ እኔ አሸንፋለሁ።
መልዕክተኞቼም እንዲሁ (ያሸንፋሉ) ሲል
ድሮዉኑ ጽፏል። አላህ ብርቱና አሸናፊ ነውና።
22 በአላህና[6] በመጨረሻው ቀን
የሚያምኑትን ህዝቦች አላህንና
መልዕክተኛውን የሚከራከሩትን ሰዎች
አባቶቻቸው፤ ወይም ልጆቻቸው፤ ወይም
ወንድሞቻቸው፤ ወይም ዘመዶቻቸው
ቢሆኑም እንኳ የሚወዳጁ ሆነው
አታገኛቸውም። እነዚያ[7] በልቦቻቸው ውስጥ
እምነትን ጽፏል። ኢብኑ አቢሐቲም ጦበራኒ
እና ሐኪም በዘገቡት ታሪክ ‹‹የአቡዐበይዳህ
የበድር ዕለት ሆን ብሎ ልጁን አቡዐበይዳህ
ያድን ነበር አቡዑበይዳህ ግን ከፊት ለፊቱ
እያሻሱከአባታቸው ጋር ፊት ለፊት
ላለመገናኘትና በእጃቸው እንዳይሞት
ቢሞክሩም አባታቸው በግድ ስለመጣበት
ገደለው። ከእርሱም በሆነ መንፈስ[8]
ደገፏቸዋል ። ከስሮቻቸውም ወንዞች
የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው
ዘውታሪዎች ሲሆኑ ያስገባቸዋል ። አላህ
ተግባራቸውን ወዷል[9]። እነርሱም የእርሱን
(ችሮታ) ወደዋል[10]። እነዚያ የአላህ ህዝቦች
ናቸው። ንቁ! የአላህ ህዝቦች ምኞታቸውን[11]
የሚያገኙ እነሱ ብቻ ናቸው።[12]

---

አይሁዶች ከእናንተም አይደሉም ። ከሙናፊቆችም አይደሉም። ታዲያ እንዴት ሙናፊቆች ወዳጅ አያደርጓቸውም ።

1 ሙስሊም ነን እያሉ ወይም ወደ አይሁዶች ምንንም ወሬ አላቀበልንም ብለው ።

2 የሞት ቅጣት መከላከያ

3 በማሳነፍ፤ ሙስሊሞቹን በማናናቅ፤ ሀይላቸዉን በማዳከም።

4 አዋራጅ ቅጣት አለባቸው። ይህ መሐላቸው የእነሱን ቂልነት በግልጽ ያሳያል። ምክኒያቱም የእዚያ እለት ሁሉ ነገር ተጋልጦ ያለበት ነውና።

5 ጀነትን በእሳት የሸጡ፤ ጥመትን በቅኑ መንገድ የለወጡ፤ በአላህ እና በመልእክተኛው ላይ የቀጠፉና የሐሰት መሐላዎችን የሚደረድሩ በመሆናቸዉ ።

7.22ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦

ሀ. በበድር ዘመቻ ቀን እሱ ቢሸሸውም ከሃዲ አባቱ ግን እያሳደደው ሊገለው በመከታተሉ አባቱን በገደለው ጀግና አቡ ዑበይዳህ በተባለው ሶሐቢ ምክንያት ነው ። ጦበራኒ፤ ሓኪም፤ ኢብን አቢ ሐቲም ፤ዋሂዲ ና ሱዩጢ።

ለ. የአቡበከር ሲዲቅ አባት ነብዩ ሙሐመድን (ﷺ) ተሳድቦ አቡበከር በመሬት ላይ እስኪወድቅ ድረስ ስለመቱትና ይህን ሁኔታ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሲሰሙ፦ “አቡበከር ሆይ፣ ይህ አይነት ተግባር እንዳይደግምህ ሲሏቸው አቡበከር ወላሂ ሰይፍ ከአጠገቤ ቢኖር ኑሮ እገድለው ነበር ስለ አሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው ። ዋሂዲ ና ሱዩጢ የዘገቡት ሐዲስ።

7 የአላህንና የመልዕክተኛዉን ጠላቶች የማይወዳጁ ።

8 ይህን ድል ‹ሩህ› (መንፈስ) ብሎ የመጥራቱ ምክኒያት የሁሉ ነገር ሕይወት በእሱ ነውና ።

9 ተግባራቸዉን ተቀብሏል።

10 በዱንያም ሆነ በአኺራ በሰጣቸው ተደስተዋል።

11 የዚህችን ዐለምም ሆነ የመጭውን ዐለም ደስታ ።

12 .የምእራፉን መልዕክት በሰፊው ለመረዳት

## 59 ኛው ምዕራፍ:- የማስወጣት ምዕራፍ (ሱረቱ አል-ሐሽር) ነው::[1] አንቀጾቹ 24 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

(1) በሰማያትና[2] በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ አላህን አሞገሰ/አጠራ/:: እርሱም አሸናፊና ጥበበኛ ነው።
(2) እርሱ ያ! ከመጽሐፉ ሰዎች እነዚያን

---

የሚከተሉትን ነጥቦች ማየት ይጠቅማል ::

**1ኛ** አላህ የባሮቹን ችግር በመስማት በኩልም ሆነ በሁሉ ነገር የተሟላ አቅምና ርህራሔ ያለው መሆኑን እንረዳለን ። ኸውለት ቢንት ሰዕለባህ የተባለች ሴት ሶሐቢይ ከባሏ ጋር ተኮራርፋ ሳለች ባሏ «ከዛሬ ጀምሮ አንቺ እንደ እናቴ ነሽ» ባላት ጊዜ ወደ ነብዩ የመጣችበትንና ያጋጠማትን ነገረቻቸው ። ነብዩም «እስካሁን ምንም መፍትሔ ከኔ ዘንድ የለም» በማለታቸው «ጌታዬ ሆይ! ወደ አንተ ስሞታዬን አቀርባለሁ» በማለት ወደ ጌታዋ ተማፀነች ። አሏህም ሁሉን ሰምቷት የቁርአን አንቀጽ አወረደላት፣ በማለት የተዘገበው የዚህ ማረጋገጫ ይሆናል።

**2ኛ** ሚስትን እንደ እናቴ ነሽ ማለት በኢስላም አሏህ የሚጠላው ክልክል ነገር መሆኑን፤ ነገር ግን ይህን ማለት እንደፍቺ የሚቆጠር እንዳልሆነና ሚስትን እንደ እናት መመሰል በሸሪአው የተጠላ ነገር ነው። የእናትን ክብርም የሚነካ ነው ።

**3ኛ** ሚስትን እንደ እናቴ ነሽ ያለና ወደ እሷው ለመመለስ የፈለገ ሰው የሚከፍለው ቅጣት ወይም ማካካሻ ተገልጿል ። እርሱም አንድ ባሪያ ነጻ ማውጣት ይህን ካልቻለ፤ ሁለት ወራትን በተከታታይ መፆም፤ ይህን ካልቻለ ደግሞ ስልሳ ሰዎችን የአንድ ጊዜ ምግብ ማብላት ነው። ባሪያን ነጻ በማውጣቱ ረገድ ወንድ፣ ሴት፣ ህጻን ወይም አዋቂንም ቢሆን ነጻ የሚያወጣው ልዩነት የለውም። ቅጣቱን በፆም መወጣት ያለበት ሰው በጾም ሊያሳልፋቸው የሚገባውን ሁለት ወራት ያለማቋረጥ መፆም ይኖርበታል። ያቋረጠ ከሆነ ግን እንደ አዲስ አንድ ብሎ መጀመር አለበት ። ስልሳ ሰዎችን የአንድ ጊዜ ምግብ በማብላት ቅጣቱን የሚያወጣ ሰው የስልሳ ሰዎችን ምግብ ለአንድ ሰው ቢሰጥ አይፈቀድለትም ። በዚህ ነጥብ ውስጥ ሌላ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው፤ ሰውየው ይህንን ቅጣት ማውጣት የሚኖርበት እናቴ ነሽ ካለት ሚስቱ ጋር ግንኙነት ከማድረጉ በፊት ነው ። ሆኖም ቅጣቱን ሳያደርግ ከሚስቱ ጋር ግንኙነት የፈጸመ እንደሆነ ወንጀለኛ ነው። ወደ ጌታው መመለስ ያለበትም ሲሆን ቅጣቱንም እንደገና ማውጣት ይኖበታል ።

**4ኛ** በተጨማሪ እናት ማለት የወለደች እናት ብቻ መሆኗን፤

**5ኛ** በአላህ ላይ መመካት ግዴታ ነው ።

**6ኛ** አላህ በእውቀቱና በጥበቡ ሁሉን ነገር የሚያውቅ ጌታ ነው። አሏህን እና መልዕክተኛውን ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) መታዘዝ የእምነት አንኳር መሆኑን እንማራለን ። አላህ እና መልዕክተኛውን አለመታዘዝ ደግሞ የክህደት ዋናው መሆኑንም እንገነዘባለን ። አላህንና መልዕክተኛውን የሚከራከሩ ሁሉ ከፍተኛ ውርደትና ሽንፈት አለባቸው። (. . . እነዚያ አላህንና መልዕክተኛውን የሚከራከሩ፣ የሚፃረሩ፣ የሚነቅፉ እነዚያ ከእነሱ በፊት የነበሩት ሰዎች እንደተዋረዱት ሁሉ ተዋርደዋል) ።

**7ኛ** ውይይትና ምክክር ለማካሄድ «ነጠላ ቁጥር» በሆኑ ሰዎች መካሔዱ ይመረጣል ይኸውም ሶስት፣ አምስት፣ ሰባት. . . በሆኑ ሰዎች መካከል ማለት ነው ። ይህ የመሆኑ አስፈላጊነትም የሚንሸራሸሩ ሐሳቦችን በድምጽ ብልጫ ለውሳኔ ለማብቃት የሚረዳ በመሆኑ ነው ። ከዚሁ ነጥብ ሳንወጣ ማወቅ የሚገባን መወያየትና ምክክር ማድረግ ለኸይር ነገር ብቻ ካልሆነ በስተቀር የተከለከለ መሆኑን ነው ። አላህንና መልዕክተኛው መሐመድን ለመወንጀል በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ መገኘት ከፍተኛ ወንጀል ስለሆነ በዚህ ውስጥ መሳተፍ ተገቢ አለመሆኑን፤ የሰው ልጅ የቱንም ያህል ቢደበቅ ከአላህ መሰወር እንደማይችል፤

**8ኛ** አብሮ ያለን ሰው በማግለል የሚደረጉ ጨዋታዎችን አስመልክቶ በቀረበው ትምህርት፤ ሁለት ሰዎች ሶስተኛውን ሰው ትተው በሌላ ቋንቋ መነጋገራቸው ክልክል መሆኑ ተገልጿል ። ምክንያቱም ይህ የሁለቱ ሰዎች ድርጊት ሶስተኛውን ሰው ያሳዝነዋልና ነው።

**9ኛ** የሰላም ምላሽን በተመለከተ የምናገኘው ነጥብ አንድ ከሃዲ ለአማኝ ሰላም «አሰላሙ አለይኩም» ሲል «ወአለይኩም» በማለት ሁሉንም ሊያሰማ በሚችል መልኩ መልስ መስጠት ተገቢ ስለ መሆኑ፤

**10ኛ** የአይሁድና የሙናፊቅ ባህሪ ምን እንደሚመስል በተቀመጠው ነጥብ /ዋሒዲ እና ሱዩጢ/ በዘገቡት ሐዲስ፤ ከነብዩ ጋር ቆይቶ ወሬ ያቀባብል ስለነበረ ሙናፊቅ ሰው የተገለፀውን እናስተውላለን ።

**11ኛ** የአላህ (ﷻ) ቁጣና መኣት የወረደባቸውን አይሁድን ወዳጅ ከማድረግ መቆጠብ እንዳለብንና ቅርብ የሥጋ ዘመድም ቢሆን ከሃዲን ወዳጅ ማድረግ በኢስላም ክልክል መሆኑን እንረዳለን ። ይህ ጉዳይ ሙስሊሞች በህይወታቸው ከሚፈተኑባቸው ነገሮች ውስጥ ዋነኛው ነው ።

**12ኛ** በየትምህርትና በየሰብሰባ ቦታዎች ማስፋፋት፤ መጠጋጋት የሚወደድ ነው ።

**12ኛ** በግዴ ነገሮች አላህን ቀጥ ብሎ መገዛት ከጥቃቅን ነገሮች የሚሸፍን መሆኑን ንዲሁም የአላህን መንገድ የያዙ ሰዎች ሁሉ አሸናፊዎች መሆናቸውን ተምረናል። የአሏህን መልዕክተኛ መርዳት፤ ተልዕኮውን በመወጣት ላይ መተባበር ግዴታ እንደሆነ ተገልጿል ።

**13ኛ** በኢስላም፤ በውሸት መማል ስለመከልከሉ የተቀመጠው ነጥብ፤ ውሸታም ከሰዎች አልፎ በአሏህ (ﷻ) ዘንድ ምንም ቦታ እንደሌላቸውና በውሸታቸው ሰዎችን ቢያልፉም ከአላህ (ﷻ) ቅጣት ግን መዳን እንደማይችሉ ።

**14ኛ** ሰይጣን የራሱ ቡድን እንዳለው እና የሱ የሆኑ ሁሉ ከሳሪዎች መሆናቸውን ሰይጣን የአንድን ሰው ልቦና መቆጣጠሩን ከሚያሳዩ ምልክቶች መካከል በልቡም ሆነ በምላሱ አሏህን (ﷻ) አለማንሳቱ፣ በተግባሩም ሆነ በአንደበቱ የአላህን ቃልና ዛቻውን አለማስታወሱ መሆናቸውን እንረዳለን።

[1] ምዕራፉ በመዲና ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ።

[2] **1ኛው አንቀፅ- የወረደበት ምክኒያት:-** ነቢዩ ሙሐመድ ወደ መዲና በተሰደዱ ጊዜ በኒ ነዲሮች ከተባሉ ከአይሁድ ነገዶች ጋር ወደው እና ከእሳቸው ጋርም ሀገርን ለማስከበር ላይዋጉ ተስማምተው ነበር። ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ከመኮች ጋር ባደረጉት የበድር ዘመቻ ጦርነት የበላይነታቸውን ሲያረጋግጡ በኒ ነዲሮች ይህ ሰውማ እውነትም በተውራት የተነገረለት ነቢይ ነው ማለት ነው ። በማለት ተቀብለው ሣሉ በኡሁድ ዘመቻ ላይ ሙስሊሞች ሲሸነፉና ጥቃት ሲደርስባቸው በኒ ነዲሮች አቋማቸውን ቀይረው ቃላቸውን አፍርሰው ለሙስሊሞች ጠላትነታቸውን በይፋ አወጁ። በዚህ ጊዜ ነበር ቀያቸውን ከበው እንዲለቁ አሳምነው የታረቋቸው ። (ሱዩጢ)

ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ شَآقُّوا۟ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ ۖ وَمَن يُشَآقِّ ٱللَّهَ فَإِنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ
ٱلْعِقَابِ ﴿٤﴾ مَا قَطَعْتُم مِّن لِّينَةٍ أَوْ تَرَكْتُمُوهَا قَآئِمَةً
عَلَىٰٓ أُصُولِهَا فَبِإِذْنِ ٱللَّهِ وَلِيُخْزِىَ ٱلْفَٰسِقِينَ ﴿٥﴾ وَمَآ أَفَآءَ ٱللَّهُ
عَلَىٰ رَسُولِهِۦ مِنْهُمْ فَمَآ أَوْجَفْتُمْ عَلَيْهِ مِنْ خَيْلٍ وَلَا رِكَابٍ
وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ يُسَلِّطُ رُسُلَهُۥ عَلَىٰ مَن يَشَآءُ ۚ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ
قَدِيرٌ ﴿٦﴾ مَّآ أَفَآءَ ٱللَّهُ عَلَىٰ رَسُولِهِۦ مِنْ أَهْلِ ٱلْقُرَىٰ فَلِلَّهِ وَلِلرَّسُولِ
وَلِذِى ٱلْقُرْبَىٰ وَٱلْيَتَٰمَىٰ وَٱلْمَسَٰكِينِ وَٱبْنِ ٱلسَّبِيلِ كَىْ لَا يَكُونَ
دُولَةًۢ بَيْنَ ٱلْأَغْنِيَآءِ مِنكُمْ ۚ وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا
نَهَىٰكُمْ عَنْهُ فَٱنتَهُوا۟ ۚ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلْعِقَابِ ﴿٧﴾
لِلْفُقَرَآءِ ٱلْمُهَٰجِرِينَ ٱلَّذِينَ أُخْرِجُوا۟ مِن دِيَٰرِهِمْ وَأَمْوَٰلِهِمْ
يَبْتَغُونَ فَضْلًا مِّنَ ٱللَّهِ وَرِضْوَٰنًا وَيَنصُرُونَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥٓ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ
هُمُ ٱلصَّٰدِقُونَ ﴿٨﴾ وَٱلَّذِينَ تَبَوَّءُو ٱلدَّارَ وَٱلْإِيمَٰنَ مِن قَبْلِهِمْ
يُحِبُّونَ مَنْ هَاجَرَ إِلَيْهِمْ وَلَا يَجِدُونَ فِى صُدُورِهِمْ حَاجَةً
مِّمَّآ أُوتُوا۟ وَيُؤْثِرُونَ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمْ وَلَوْ كَانَ بِهِمْ خَصَاصَةٌ ۚ
وَمَن يُوقَ شُحَّ نَفْسِهِۦ فَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ ﴿٩﴾

የካዱትን ወገኖች[1] ከቤቶቻቸው የመጀመሪያውን ማስውጣት ያስወጣቸው ነው፡፡ ሙስሊሞች ሆይ መውጣታቸውን አላሰባችሁም ነበር፡፡ እነሱም ምሽጎቻቸው ከአላህ (ኃይል) የሚከላከሉላቸው መሆናቸውን አሰቡ(ገመቱ) ፡፡ አላህ ግን ካላሰቡት በኩል መጣባቸው ይኸውም ነብዩ እንዲዘምኖቱባቸው በማድረጉ ሲሆን ጉዳዩ እዚህ ላይ ይደርሳል ብለው አላሰቡም ነበር፡፡ ቢሞክርም አቅማቸው ከፍተኛ ነው ብለው ያምኑ ነበር ፡፡ እናም በልቦቻቸውም ውስጥ መርበድበድን ጣለባቸው፤ ቤቶቻችውን በገዛ እጆቻቸውና በአማኞች እጅ ያፈርሳሉ፡፡ እናንተ የአእምሮ ባለቤቶች ሆይ! አስተውሉ፡፡
3 በእነሱም ላይ አላህ ከአገር መውጣትን ባልፈረደ ሮ በቅርቢቱ ዓለም በቀጣቸው ነበር፡፡ ለእነርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም የእሳት ቅጣት አለባቸው፡፡
4 ይህ አላህንና መልዕክተኛውን በመከራከራቸው ምክንያት ነው፡፡ አላህን የሚከራከር ሰው ሁሉ አላህ ቅጣቱ ብርቱ ነውና ይቀጣዋል፡፡
5 ከዘንባባ[2] (ከተምር ዛፍ) ማንኛዋም የቆረጣችኋት ወይም በግንዶቿ ላይ የቆመች ሆና የተዋችኋት በአላህ ፈቃድ ነው[3]፡፡ አመጠኞችንም ያዋርድ ዘንድ (መቁረጥን ፈቀደ)፡፡
6 ከእነርሱ (ገንዘብ) ወደ መልዕክተኛው አላህ የመለሰውን በእርሱ ላይ ፈረሶችንና ግመሎችን እርሱን ለማግኘት አላስጋለባችሁበትም፡፡ ግን አላህ መልዕክተኛውን በሚሻው ሰው ላይ ይሾማል፡፡ አላህ ሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነውና፡፡
7 አላህ ከከተሞች ሰዎች (ሀብት) በመልዕክተኛው ላይ የመለሰው[4] (ሀብት) ከእናንተ ውስጥ በሀብታሞች መካከል ተዘዋዋሪ እንዳይሆን ለአላህና ለመልክተኛው፣ ለዝምድና ባለቤትም፣ አባት ለሌላቸው /የቲም/ ልጆችም፣ ለድሆችም፤ ለመንገደኛ፤ (የሚሰጥ) ነው፤ መልዕክተኛውም የሰጣችሁን ማንኛውንም ነገር ያዙት ፡፡ ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ፡፡

[1] በኒ ነዲሮች ናቸው፡፡ እነሱም የነብዩ ሀሩን ዝርያዎች እንደሆኑ ይነገርላቸዋል፡፡ ወደ መዲና የመጡት በበኒኢስራኢሎች መካከል ተፈጥሮ በነበረው ችግር ጊዜ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ነብዩን በድንገት የመግደል ሙከራ አደረጉ ከመኮች ጋር አበሩ በዚህ ጊዜ ነብዩ ሲከቧቸው ሀገር ለመልቀቅ ተስማሙ፡፡ ከልቢ የተባለ ዓሊም ‹‹ እነዚህ ሰዎች ከመፅሐፍት ቤቶች ለመጀመሪያ ከዐረብ ደሴት የተባረሩ ናቸው፡፡ የመጨረሻው ደግሞ በዑመር ጊዜ የተባረሩ ናቸው፡፡ ብለዋል እናም የመጀመሪያው መባረር የእነሱ መውጣት ሲሆን የመጨረሻው ደግሞ የዑመር መባረር ነው ፡፡ ቤቶቻቸው ሀገር እንደሚለቁ ሲያውቁ ቤታቸውን ሙስሊሞች እንዳይኖሩበት ውስጥ ውስጡን ማፍረስ ጅምሩ ሙስሊሞች ከውጭ ማፍረስ ጀመሩ ፡፡ ዚህርና ዐርወት ኢብኑዙበይር እንደሚሉት ነብዩ ግመሎቻቸውን የቻሉትን ያህል ሊወስዱ እንደሚችሉ ሲፈቀድላቸው የቤቶቹን ቋሚዎች እያፈረሱ ለመውሰድ ሲሞክሩ ሙስሊሞች ደግሞ የቀረውን ጨረሱት ፡፡

[2] **5ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክኒያት -:** ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በኒ ነዲሮችን በከበቡ ጊዜ እጅ አልሰጥ ሲሉ ተምሮቻቸውን እንዲቆርጡባቸውና እንዲያቃጥሉባቸው ሲያዙና ሲተገብሩ፡- ሙሐመድ ሆይ፣ ይህን መሰል የጥፋት ተግባር ውግዝ አልነበረም እንዴ? ዛሬ እንዴት ፈቀድክ? በማለት ሲጠይቋቸው ነው፡፡ (ዋሂዲ እና ሱዩጢ፡፡)

[3] የበኒ ነዲሮች ዘመቻ ጊዜ አንዳንድ ሙስሊሞች የካፊሮች ሞራል ለማዳከም አትክልት መቁረጥ ሲጀምሩ በኒ ነዲሮች ሙሐመድ ለመልካም ነገር ከአላህ የተላኩኝ ነኝ ትል አልነበረም? አትክልት መቁረጥ ዛፍ ማቃጠል ከመልካም ተግባር ነውን? ከአላህ ከወረደልህ መመሪያ ውስጥ እንዲህ ያለው ግፍ መስራት ተፈቅዶልሃልን አሏቸው ፡፡ ነብዩም ሆኑ ሙስሊሞች ይህ ለሰው በጣም ስለተሰማቸው የተደረገው ድርጊት በአላህ ፈቃድ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡

[4] በዚህ አንቀፅ ለነብዩ ያለምንም ጦርነት የተመለሰ ገንዘብ ለነብዩ መሆኑን ከገለፀ በኋላ ነብዩ ለማን ለማን እንደሚያደርጉት የገለፀበት ነው፡፡ እሱም ነብዩም ሆኑ ሙስሊሞች ያለምንም ጦርነት የሚቆጣሩት ሀገር ሁሉ ገንዘብ በዚህ አንቀፅ መሰረት እንዲከፋፈል ነው፡፡ ለአላህ የተባለው ነብዩ (ﷺ) እንደፈለጉ የሚወስኑበት ክፍል ሲሆን ለነብዩ የተባለው ደግሞ በዋነኛነት የግል ንብረታቸው ይሆናል ፡፡ ከሞቱ በኋላ ደግሞ ለሙስሊሞች ጠቅላላ አገልግሎት ይውላል፡፡ ለዝምድና ባለቤቶች የሚለው ድግሞ ሰደቃ የማይፈቀድላቸው የሐሺም እና የሙጦሊብ ልጆች ናቸው፡፡

وَٱلَّذِينَ جَآءُو مِنۢ بَعۡدِهِمۡ يَقُولُونَ رَبَّنَا ٱغۡفِرۡ لَنَا
وَلِإِخۡوَٰنِنَا ٱلَّذِينَ سَبَقُونَا بِٱلۡإِيمَٰنِ وَلَا تَجۡعَلۡ فِي قُلُوبِنَا
غِلّٗا لِّلَّذِينَ ءَامَنُواْ رَبَّنَآ إِنَّكَ رَءُوفٞ رَّحِيمٌ ﴿١٠﴾ ۞ أَلَمۡ تَرَ إِلَى
ٱلَّذِينَ نَافَقُواْ يَقُولُونَ لِإِخۡوَٰنِهِمُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنۡ أَهۡلِ
ٱلۡكِتَٰبِ لَئِنۡ أُخۡرِجۡتُمۡ لَنَخۡرُجَنَّ مَعَكُمۡ وَلَا نُطِيعُ فِيكُمۡ
أَحَدًا أَبَدٗا وَإِن قُوتِلۡتُمۡ لَنَنصُرَنَّكُمۡ وَٱللَّهُ يَشۡهَدُ إِنَّهُمۡ لَكَٰذِبُونَ
﴿١١﴾ لَئِنۡ أُخۡرِجُواْ لَا يَخۡرُجُونَ مَعَهُمۡ وَلَئِن قُوتِلُواْ لَا يَنصُرُونَهُمۡ
وَلَئِن نَّصَرُوهُمۡ لَيُوَلُّنَّ ٱلۡأَدۡبَٰرَ ثُمَّ لَا يُنصَرُونَ ﴿١٢﴾
لَأَنتُمۡ أَشَدُّ رَهۡبَةٗ فِي صُدُورِهِم مِّنَ ٱللَّهِۚ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ قَوۡمٞ
لَّا يَفۡقَهُونَ ﴿١٣﴾ لَا يُقَٰتِلُونَكُمۡ جَمِيعًا إِلَّا فِي قُرٗى
مُّحَصَّنَةٍ أَوۡ مِن وَرَآءِ جُدُرِۭۚ بَأۡسُهُم بَيۡنَهُمۡ شَدِيدٞۚ تَحۡسَبُهُمۡ
جَمِيعٗا وَقُلُوبُهُمۡ شَتَّىٰۚ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ قَوۡمٞ لَّا يَعۡقِلُونَ ﴿١٤﴾
كَمَثَلِ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡ قَرِيبٗاۖ ذَاقُواْ وَبَالَ أَمۡرِهِمۡ وَلَهُمۡ عَذَابٌ
أَلِيمٞ ﴿١٥﴾ كَمَثَلِ ٱلشَّيۡطَٰنِ إِذۡ قَالَ لِلۡإِنسَٰنِ ٱكۡفُرۡ فَلَمَّا كَفَرَ
قَالَ إِنِّي بَرِيٓءٞ مِّنكَ إِنِّيٓ أَخَافُ ٱللَّهَ رَبَّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿١٦﴾

አላህንም ፍሩ፤ አላህ ቅጣቱ ብርቱ ነውና ።
8 ለእነዚያ የአላህን ችሮታና ውዴታውን የሚፈልጉና አላህንና መልክተኛውንም የሚረዱ ሆነው ከአገሮቻቸውና ከገንዘቦቻቸው ለተወጡት ስደተኞች ድሆች (ይሰጣል) ። እነዚያ እነርሱ እውነተኞች ናቸው።
9 እነዚያ[1] ከበፊታቸው ሀገሪቱን (መዲናን) መኖሪያ ያደርጓትና እምነትም የሰረፀባቸው ወደ እነርሱ የተሰደዱትን ሰዎች ይወዳሉ። (ስደተኞች) ከተሰጡትም ነገር በልቦቻቸው ውስጥ ቅሬታን አያሳድሩም ። በእነሱ ላይ ችግር ቢ ርባቸውም እንኳን በነፍሶቻቸው ላይ ሌላውን ያስቀድማሉ ። ከነፍሶቻቸው ንፍገት የሚጠበቁ ሰዎች እነዚያ የተሳካላቸውና ምኞታቸውን አግኚዎች ማለት እነሱ ናቸው።
10 እነዚያ ከበኋላቸው የመጡት ጌታችን ሆይ፣ ለእኛም ለእነዚያም በእምነት ለቀደሙን ወንድሞቻችን ምህረት አድርግ። በልቦቻችንም ውስጥ ለእነዚያ ለአመኑት (ሰዎች)ጥላቻን አታድርግ[2]። ጌታችን ሆይ አንተ ሩህሩህና አዛኝ ነህና ይላሉ።
11 ወደ እነዚያ[3] ወደ ነፈቁት (ንፍቅና የገቡት) አላወቅክምን? ከመጽሐፉ ሰዎች ውስጥ ለእነዚያ ለካዱ ወንድሞቻቸው (ከአገር) ብትባረሩ አብረናችሁ እንወጣለን። በናንተም (ጉዳዩ) አንድንም ሰው በፍጹም /ሁል ግዜም/ አንታዘዝም። በእርግጥ እንረዳችኋለን ይሏቸዋል። አላህም እነሱ ውሸታሞች መሆናቸውን ይመሰክራል።
12 ቢወጡም አብረዋቸው አይባረሩም ። ቢገደሉም /ቢወጉም/ ቢዘመትባቸውም/ አይረዱዋቸውም ። ቢረዷቸውም (ለሽሽት) ጀርባዎችን ያዞራቁ ። ከዚያም እርዳታን አያገኙም ።
13 እናንተ በልቦቻቸው ውስጥ በማስፈራት ከአላህ ይልቅ የበረታችሁ/ የከበዳችሁ/ ናችሁ ። ይህም የሆነው እነርሱ የማያውቁ ህዝቦች በመሆናቸው ነው ።
14 በተመሸጉ ከተሞች ውስጥ ወይም ከአጥሮች በስተጀርባ ሆነው እንጂ የተሰበሰቡ ሆነው አይዋጉዋችሁም ። ኃይላቸው በመካከላቸው ብርቱ ነው ። ልቦቻቸው የተበታተኑ ሲሆኑ የተሰበሰቡ ናቸው ብለህ ትጠረጥራቸዋለህ /አንድ ይመስሉሃል/። ይህ እነሱ አእምሮ የሌላቸው ህዝቦች በመሆናቸው ነው።
15 (ብጤያቸው) እንደነዚያ ከእነሱ በፊት በቅርብ ጊዜ የተግባራቸውን ቅጣት እንደቀመሱት ወገኖች ብጤ ነው። ለእነርሱም አሳማሚ ቅጣት አለባቸው /ይጠብቃቸዋል/።
16 እንደ ሰይጣን ብጤ፣ ለሰውየው ካድ ባለው ጊዜና በካደም ጊዜ እኔ ከአንተ ንጹህ ነኝ። እኔ

---

[1] 9ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክኒያት፡
ሀ/ -የመዲና አንሷሮች ወደ ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) መጥተው ለሙሀጀር ወንድሞቻችን መሬቶቻችንን በእኩል ክፈሉልን ብለው ጥያቄ ሲያቀርቡና ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ነገሩ እንዲህ ሳይሆን እነሱ ጉልበት ሁነው እናንተ መሬት ሁናችሁ እኩል ተካፈሉ በማለት ሲነግሯቸው ሀሳቡን ተቀብለናል በማለታቸው ነው። (ዋሂዲ።)
ለ/ ቀደም ከመካ የተሰደዱ ሙሀጂሮች በመዲና ሰዎች ጋር ተጠጋግተው ይኖሩ ነበር። ሐኪም በዘገቡት ሐዲስ የበኒ ነዲሮችን ገንዘብ ሲያገኝ አንሷሮች ጠርተው ለሙጃሂሮች ወንድሞቻቸው ለሰሩት መልካም ነገር አመስግነው ‹‹ከፈለጋችሁ አሁን አላህ የሰጠኝን በእናንተና በሙሀጂሮች መካከል በኩል ለአካፍላችሁና እነርሱም የነበሩበት አብረዋችሁ ይኖሩ፤ ከፈቀዳችሁ ደግሞ ይህን ለእነሱ ልስጣቸውና ከእናንተ ወጥተው እራሳቸውን ይቻሉበት››በማለት ሲጠይቋቸው ለእነሱ እንዲሰጣቸው መስማማታቸውን ነው የሚያወሳው ፡ ፡

[2] ለእነዚያ በዚህ አባባል በአንደኛ ደረጃ የሚገቡት የነብዩ ሶሃቦች ናቸው። ምክንቱም ምርጥ አማኞች በመሆናቸውና አንቀፁም እያወሳ ያለው የእነሱን ጉዳይ በመሆኑ ነው። በልብ ውስጥ በእነሱ ላይ ትንሽም ጥላቻ ያለው አንዱ ሺዓዎች ሰይጣን ተጫውቶበታል የአላህን ወዳጆች በመጥላቱ የአላህም ቁጣ አርፎበታል። እነደዚሁም የሰደባቸውን ያስቸገራቸውን የእዚሁ ቢጤ ነው። እናም ከፋይ ምን ድርሻ የለውም።

[3] 11ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክኒያት፡-
የበኒ ቁረይዟ አይሁዳ ኢስላምን ተቀብለናል ብለው የነበሩና ለበኒ ነዲሮች ደግሞ ከተባረራችሁ እኛም አብረን እንሰደዳለን ይሉ ስለነበር ነው። (ሱዩጢ።)

فَكَانَ عَٰقِبَتَهُمَآ أَنَّهُمَا فِي ٱلنَّارِ خَٰلِدَيۡنِ فِيهَاۚ وَذَٰلِكَ جَزَٰٓؤُاْ
ٱلظَّٰلِمِينَ ١٧ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَلۡتَنظُرۡ
نَفۡسٞ مَّا قَدَّمَتۡ لِغَدٖۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرُۢ بِمَا تَعۡمَلُونَ
١٨ وَلَا تَكُونُواْ كَٱلَّذِينَ نَسُواْ ٱللَّهَ فَأَنسَىٰهُمۡ أَنفُسَهُمۡۚ أُوْلَٰٓئِكَ
هُمُ ٱلۡفَٰسِقُونَ ١٩ لَا يَسۡتَوِيٓ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِ وَأَصۡحَٰبُ
ٱلۡجَنَّةِۚ أَصۡحَٰبُ ٱلۡجَنَّةِ هُمُ ٱلۡفَآئِزُونَ ٢٠ لَوۡ أَنزَلۡنَا هَٰذَا
ٱلۡقُرۡءَانَ عَلَىٰ جَبَلٖ لَّرَأَيۡتَهُۥ خَٰشِعٗا مُّتَصَدِّعٗا مِّنۡ خَشۡيَةِ
ٱللَّهِۚ وَتِلۡكَ ٱلۡأَمۡثَٰلُ نَضۡرِبُهَا لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمۡ يَتَفَكَّرُونَ
٢١ هُوَ ٱللَّهُ ٱلَّذِي لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ عَٰلِمُ ٱلۡغَيۡبِ وَٱلشَّهَٰدَةِۖ
هُوَ ٱلرَّحۡمَٰنُ ٱلرَّحِيمُ ٢٢ هُوَ ٱللَّهُ ٱلَّذِي لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ
ٱلۡمَلِكُ ٱلۡقُدُّوسُ ٱلسَّلَٰمُ ٱلۡمُؤۡمِنُ ٱلۡمُهَيۡمِنُ ٱلۡعَزِيزُ
ٱلۡجَبَّارُ ٱلۡمُتَكَبِّرُۚ سُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ عَمَّا يُشۡرِكُونَ
٢٣ هُوَ ٱللَّهُ ٱلۡخَٰلِقُ ٱلۡبَارِئُ ٱلۡمُصَوِّرُۖ لَهُ ٱلۡأَسۡمَآءُ ٱلۡحُسۡنَىٰۚ
يُسَبِّحُ لَهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٢٤

ترتيبها ٦٠ — سُورَةُ المُمۡتَحنَةِ — آياتها ١٣

የዓለማትን ጌታ አላህን እፈራለሁ እንዳለው ነው።
17 መጨረሻቸውም እነርሱ በውስጡ ዘውታሪዎች ሲሆኑ በእሳት ውስጥ መሆን ነው። ይህም የበዳዮች ዋጋ ነው።
18 እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ። ማንኛይቱም ነፍስ ለነገ ያስቀደመችውን ትመልከት፤ አላህን ፍሩ፤ አላህ በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው።
19 እንደ እነዚያም አላህን እንደረሱትና ነፍሶቻቸውን እንዳስረሳቸው (ሰዎች) አትሁኑ። እነዚያ እነሱ አመፀኞች ናቸው።
የእሳት ጓዶችና የገነት ጓዶች አይስተካከሉም/እኩል አይደሉም።/ የገነት ጓዶች ምኞታቸውን አግኝዎች ናቸውና።
21 **ሙሐመድ ሆይ!** ይህንን ቁርአን በተራራ ላይ ባወረድነው ሮ ከአላህ ፍራቻ (የተነሳ)ተዋራጅና ተሰንጣቂ[1] ሆ ባየኸው ነበር። እነዚህን ምሳሌዎች ለሰዎች ያስተነትኑ ዘንድ እንገልፃቸዋለን።
22 እርሱ አላህ ነው። ያ! ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ የሆነ ነው። እርሱ እጅግ በጣም ሩህሩህና በጣም አዛኝ ነው።
23 እርሱ አላህ ነው። ያ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፤ንጉሡ፤ ከጉድለት ሁሉ የጠራ፤ የሰላም ባለቤት፤ ጸጥታን ሰጪ፤ ባሮቹን ጠባቂ፤ አሸናፊ፤ ኃያልና ኩሩ[2] ነው። አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።
24 እርሱ አላህ ፈጣሪ፤ አስገኚ፤ ቅርጽን አሳማሪ ነው ። ለእርሱ መልካሞች ስሞች አሉት። በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ እርሱን ያሞግሳል (ያጠራል) ። እርሱም አሸናፊና ጥበበኛ ነው ።[3]

---

1 ይህ ቁርአን በምክሩና በግሳፄው እንኳንስ ሰውን ያን በጣም ደረቅ፡ ጠንካራ ግዙፍ የሆነውን ጋራን እንኳን ለእርሱ ወርዶ ቢመሰክሩበት ኑሮ ቅጣቱን ፈርቶ የተጣለበትን ሃላፊነት አላውጣም ይሆናል በሚል በተሰነጣጠቀ ነበር ።

2 ኩራት ለአላህ ማሞገስ ሲሆን ለሰዎች ግን መጥፎ ባህሪ ነው ።

3 ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. የአሏህ (ﷻ) ትልቅነትና ክብር፣የአሏህ አንድነትና የነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) መልዕክተኝነት ማረጋገጥ፤
2. «ተውሒድ» ማለት ላኢላሃ ኢለሏህ መሐመድ ረሱሉሏህ ማለት መሆኑን፣ አሏህ (ﷻ) መልካም ስሞች እንዳሉት፣ እንዲሁም የአሏህን (ﷻ) ስሞች ማፅደቅና ሁሉም መልካም መሆናቸውን ማረጋገጥ በምእራፏ ውስጥ የምናገኘው ነጥብ ነው ። አሏህ (ﷻ) ስሞችም በመጥቀስ ከሚገኙ ትምህርቶች መካከል አሏህን (ﷻ) በእነሱ /በስሞቹ/ መጠየቅ እንደሚቻልና ይህንንም ማሳወቁ፤ እንዲሁም የአሏህን (ﷻ) ስሞች ማውሳቱ፣ በዝርዝር መደርደሩ እሱን ለሚፈልጉ ሁሉ ለማስተማር መሆኑን እንገነዘባለን።
3. ቁርአን ያጠቃለላቸው ጠቃሚ ምክሮችና አያሌ ቁም ነገሮች ክብደት፤ጋራ እንኳን እንደ ሰው ግንዛቤ ተሰጥቶት ቁርአን ቢወርድበት ኑሮ በፍርሃት ይፈራርስ እንደነበር፤
4. ለማስተማር ምሳሌዎችን ማምጣት /ማቅረብ/ ከመልካም የማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ እንደሆነ፤
5. በኢስላም ቃልን ማፍረስ ከንፍቅና ምልክቶች አንዱ ስለመሆኑ
6. ለበኒ ነዲሮች ሽንፈት ምክንያት ምን እንደነበር ተምረናል ። ዋሒዲና ሱዩጢ በዘገቡት ሐዲስ መሠረት ነብዩ (ﷺ) በበድር ዘመቻ የበላይነትን ባረጋገጡ ጊዜ በኒነዲሮች «ይህ ሰውማ እውነትም በተውራት የተነገረለት ነብይ ነው» በማለት ተቀበሉ ። ሆኖም በኡሁድ ዘመቻ ላይ ሙስሊሞች ጥቃት ሲደርስባቸው በኒነዲሮች አቋማቸውን ቀይረው ቃላቸውን አፈረሱ ። ይህን በማድረጋቸው ለሽንፈት ተዳረጉ።
7. ሙስሊሞች በዘር፣ በቀለም፣ በቋንቋ መለያየት እንደሌለባቸው
8. የውርስ ገንዘብ በምን ላይ መዋል እንዳለበት፣ ገንዘብ የሃብታሞች ብቻ መጠቀሚያ እንዳልሆነ፣ ንፉግነት በባለሃብቱ ላይ ሊያስከትለው ስለሚችለው ችግር፤
9. የመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች የሙሃጂሮች፣ አንሷሮችና ከዚያም በኋላ የመጡ ተብሎ መከፋፈሉን እንረዳለን። በተጨማሪም የሙሃጂሮችና የአንሷሮች ክብር ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ፤
10. ሌላን ከራስ ማስበለጥ ከአሏህ (ﷻ) ዘንድ ያለውን ክብር መጠቆም
11. ስደተኞችን ማስጠጋት ያለው አጅር፤
12. መፍራትና መስጋት የአይሁድ ቋሚ ባህሪ እንደሆነና ከሃዲዎች ኢስላምን በመውጋት አንድ ቢመስሉም በመሃከላቸው ግን ጥላቻ በጣጥሷቸው ያሉ መሆናቸውን እንማራለን ።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ
يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَتَّخِذُواْ عَدُوِّي وَعَدُوَّكُمۡ أَوۡلِيَآءَ تُلۡقُونَ
إِلَيۡهِم بِٱلۡمَوَدَّةِ وَقَدۡ كَفَرُواْ بِمَا جَآءَكُم مِّنَ ٱلۡحَقِّ يُخۡرِجُونَ ٱلرَّسُولَ
وَإِيَّاكُمۡ أَن تُؤۡمِنُواْ بِٱللَّهِ رَبِّكُمۡ إِن كُنتُمۡ خَرَجۡتُمۡ جِهَٰدٗا فِي سَبِيلِي
وَٱبۡتِغَآءَ مَرۡضَاتِيۚ تُسِرُّونَ إِلَيۡهِم بِٱلۡمَوَدَّةِ وَأَنَا۠ أَعۡلَمُ بِمَآ أَخۡفَيۡتُمۡ
وَمَآ أَعۡلَنتُمۡۚ وَمَن يَفۡعَلۡهُ مِنكُمۡ فَقَدۡ ضَلَّ سَوَآءَ ٱلسَّبِيلِ ١ إِن
يَثۡقَفُوكُمۡ يَكُونُواْ لَكُمۡ أَعۡدَآءٗ وَيَبۡسُطُوٓاْ إِلَيۡكُمۡ أَيۡدِيَهُمۡ وَأَلۡسِنَتَهُم
بِٱلسُّوٓءِ وَوَدُّواْ لَوۡ تَكۡفُرُونَ ٢ لَن تَنفَعَكُمۡ أَرۡحَامُكُمۡ وَلَآ أَوۡلَٰدُكُمۡۚ
يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ يَفۡصِلُ بَيۡنَكُمۡۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٞ ٣ قَدۡ
كَانَتۡ لَكُمۡ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ فِيٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَٱلَّذِينَ مَعَهُۥٓ إِذۡ قَالُواْ لِقَوۡمِهِمۡ
إِنَّا بُرَءَٰٓؤُاْ مِنكُمۡ وَمِمَّا تَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ كَفَرۡنَا بِكُمۡ وَبَدَا بَيۡنَنَا
وَبَيۡنَكُمُ ٱلۡعَدَٰوَةُ وَٱلۡبَغۡضَآءُ أَبَدًا حَتَّىٰ تُؤۡمِنُواْ بِٱللَّهِ وَحۡدَهُۥٓ إِلَّا
قَوۡلَ إِبۡرَٰهِيمَ لِأَبِيهِ لَأَسۡتَغۡفِرَنَّ لَكَ وَمَآ أَمۡلِكُ لَكَ مِنَ ٱللَّهِ مِن شَيۡءٖۖ
رَّبَّنَا عَلَيۡكَ تَوَكَّلۡنَا وَإِلَيۡكَ أَنَبۡنَا وَإِلَيۡكَ ٱلۡمَصِيرُ ٤ رَبَّنَا لَا تَجۡعَلۡنَا
فِتۡنَةٗ لِّلَّذِينَ كَفَرُواْ وَٱغۡفِرۡ لَنَا رَبَّنَآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٥

## 60 ኛው ምዕራፍ (ሱረቱ አል-ሙምተሒነህ) የሞካሪዋ ምዕራፍ ነው::[1] አንቀጾቹ 13 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 እናንተ[2] ያመናችሁ ሆይ! ጠላቶቼንና ጠላቶቻችሁን ወዳጆች አድርጋችሁ አትያዙ:: የመጣላችሁን እምነት /ሃይማኖት/ የካዱ ሲሆኑ ውዴታን ለእነሱ ትጥላላችሁ /ታደርሳላችሁ/::[3] መልዕክተኛውንና እናንተን በጌታችሁ /በአላህ/ ስላመናችሁ ብቻ[4] ከሀገራችሁ ያወጣሉ፤ በመንገዴ ለመታገልና ውዴታዬን ለመፈለግ የወጣችሁ እንደሆናችሁ እነሱን (ወዳጆች አድርጋችሁ አትያዟቸው):: እኔ የምትደብቁትንና የምትገልጹትን የማውቅ ስሆን ከእነርሱ ጋር በፍቅር ትመሳጠራታላችሁ:: ከእናንተ መካከልም ይህንን የሚፈፅም ሰው ቀጥተኛውን መንገድ በእርግጥ ስቷል።

2 ቢያሸንፏችሁ /ቢያገኟችሁ/ ለእናንተ ጠላቶች ይሆናሉ:: እጆቻቸውና ምላሶቻቸውንም ወደ እናንተ በክፉ ይዘረጋሉ::[5] ብትክዱም ተመኙ::

3 ዘመዶቻችሁም ሆኑ ልጆቻችሁ በትንሳኤ ቀን አይጠቅሟችሁም::[6] አላህ በትንሳኤ ቀን በመካከላችሁ ብይን በመስጠት ይለያል[7]:: አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና።

4 በኢብራሂምና በእነዚያ ከእርሱ ጋር አብረው በነበሩት ምዕምናን መልካም መከተል/ ለአርአያ የምትሆን ተግባር/ አለቻችሁ። ለህዝቦቻቸው:- እኛ ከእናንተና ከእዚያ ከአላህ ሌላ ከምትግገዙት (ጣኦት) ንጹሆች ነን::[8] በእናንተም[1] ካድን:: በአላህ

---

[1] በመዲና ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው::

[2] 1ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-
ብዙ የተወሩ ዘገባዎች ቢኖርም ብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ከዚህ ቀጥሎ የተወሳው ነው። ሀጢብ ቢን አቢ በልተዓህ በተባለ ሷሀቢይ ምክንያት ነው። ታሪኩም በአጭሩ፡- ሳራህ የተባለች አንዲት ሴት ከመዲና ወደ መካ እንደምትሄድ ያወቀው ይህ ሰሃቢ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በመኮች ላይ ሊዘምቱባቸው እንዳሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የሚገልጽ ደብዳቤ ጽፎላቸው ሳለ ጅብሪል ከሰማይ ወረደ:: ለነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ድርጊቱን በዝርዝር ነገራቸውና ዓሊይ፣ ዓማር ፣ዙበይር፣ ጦልሃ፣ ሚቅዳድና አቡ መርሰድን ደብዳቤውን ይዛ በመኳዝ ላይ ያለችው ሴት ወደ ምትገኝበት ቦታ ሄደው መልዕክቱን እንዲያመጡት አዘዟቸው:: በተባለው ቦታም ሴትዮዋን አግኝተው ሲጠይቋት በፍጹም አልያዝኩም ስትል ማለች። እነሱ ግን እቃዋን ፈትሸው ሲያጡት ሊመለሱ ሲያስቡ ዓልይ ተነሱና ዋሽተንም ተዋሽተንም አናውቅም፣ በማለት ሰይፋቸውን አውጥተው ጹሁፉን አምጭ አለበለዚያ አንገትሽን ነው የምቆርጠው ሲሏትና ማምረራቸውን ስታውቅ ከቁንጮዋ /ሹሩባዋ/ አውጥታ ሰጠቻቸው። እነሱም እሷን ለቀው ጽሁፉን ይዘው ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) መጡ። ነቢዩም (ﷺ) ሀጢብን በማስጠራት ይህን ጹሁፍ ታውቀዋለህ? ሲሉት አዎ አለ። ምን ሁነህ ነው ለዚህ ጥፋት የበቃኸው? ሲሉት፡- በጌታዬ ይሁንብኝ ከሰለምኩኝ አንድም ቀን አልከፈርኩም። አንድም ቀን አታልየም አላውቅም። እነሱንም ከተለየኋቸው ጀምሮ ወድጃቸው አላውቅም። ነገር ግን ከሙሃጅሮች ውስጥ በመካ ጠንካራ ዘመድ የሌለው ያለ እኔ ማንም የለም። እኔ ግን ባዕድ ነኝና ለቤተሰቦቼ ፈርቼ ከእነሱ ዘንድ ውለታ ያስቆጠረልኝ መስሎኝ ነው። አላህ በእነሱ ላይ ቁጣውን እንደሚያወርድ እጠብቃለሁኝና የእኔ ጹሁፍ ምንም አይጠቅማቸውም በማለት ምክንያቱን ሲያቀርብ ነቢዩም አዎ እውነቱን ነው፣ በማለት ምክኒያቱን ተቀበሉት። በዚህ ጊዜ ዑመር፡- ይህን ሙናፊቅ እንድገድለው ይፈቀድልኝ፣ ቢሉም ነቢዩም፡- ከበድር ሰዎች አንዱ ነው:: ስለበድር ሰዎች አላህ ከበድር በኋላ የፈለጉትን ቢሰሩ ምሬአቸዋለሁ ብሎ ከሆነ የምታውቀው ነገር አለህን? በማለት ከለከሉት። በዚህ ጊዜ ነበር ይህ አንቀጽ የወረደው:: (ዋሂዲ እና ሱዩጢ::) እናም አንቀፅ ከከሃዲዎች ጋር በምንም አይነት ቢሆን መወዳጀትን ይከለክላል።

[3] ከእነሱ ጋር ባላችሁ ፍቅር ምክኒያት የነቢዩን ወሬ ታደርሳላችሁ።

[4] ከመካ::

[5] እጃቸዉን በዱላና በመሳሰለው፤ምላሳቸዉን በስድብና በመሳሰለው

[6] ሐጢብ እንዳደረገው ሁሉ ለነሱ ብላችሁ የምትወዳጇቸው ልጆችም ሆኑ ዘመዶች የቂያማ ዕለት አይጠቅሟችሁም ። ይልቁንስ የሚጠቅማችሁ ከሃዲዎችን መጥላትና እነሱን መታገል ነው ።

[7] በመሀላችሁ ይለያል ። የጀነትን ሰዎች ጀነት፤ የእሳትን ሰዎች እሳት ያስገባል ።

[8] ከእናንተ ጋር አይደለንም ። እናንተም ከእኛ ጋር አይደላችሁም።

لَقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِيهِمۡ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَۚ
وَمَن يَتَوَلَّ فَإِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡغَنِيُّ ٱلۡحَمِيدُ ٦ ۞ عَسَى ٱللَّهُ أَن يَجۡعَلَ
بَيۡنَكُمۡ وَبَيۡنَ ٱلَّذِينَ عَادَيۡتُم مِّنۡهُم مَّوَدَّةٗۚ وَٱللَّهُ قَدِيرٞۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ
٧ لَّا يَنۡهَىٰكُمُ ٱللَّهُ عَنِ ٱلَّذِينَ لَمۡ يُقَٰتِلُوكُمۡ فِي ٱلدِّينِ وَلَمۡ يُخۡرِجُوكُم
مِّن دِيَٰرِكُمۡ أَن تَبَرُّوهُمۡ وَتُقۡسِطُوٓاْ إِلَيۡهِمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلۡمُقۡسِطِينَ
٨ إِنَّمَا يَنۡهَىٰكُمُ ٱللَّهُ عَنِ ٱلَّذِينَ قَٰتَلُوكُمۡ فِي ٱلدِّينِ وَأَخۡرَجُوكُم
مِّن دِيَٰرِكُمۡ وَظَٰهَرُواْ عَلَىٰٓ إِخۡرَاجِكُمۡ أَن تَوَلَّوۡهُمۡۚ وَمَن يَتَوَلَّهُمۡ فَأُوْلَٰٓئِكَ
هُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ٩ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا جَآءَكُمُ ٱلۡمُؤۡمِنَٰتُ
مُهَٰجِرَٰتٖ فَٱمۡتَحِنُوهُنَّۖ ٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِإِيمَٰنِهِنَّۖ فَإِنۡ عَلِمۡتُمُوهُنَّ مُؤۡمِنَٰتٖ
فَلَا تَرۡجِعُوهُنَّ إِلَى ٱلۡكُفَّارِۖ لَا هُنَّ حِلّٞ لَّهُمۡ وَلَا هُمۡ يَحِلُّونَ لَهُنَّۖ وَءَاتُوهُم
مَّآ أَنفَقُواْۚ وَلَا جُنَاحَ عَلَيۡكُمۡ أَن تَنكِحُوهُنَّ إِذَآ ءَاتَيۡتُمُوهُنَّ أُجُورَهُنَّۚ
وَلَا تُمۡسِكُواْ بِعِصَمِ ٱلۡكَوَافِرِ وَسۡـَٔلُواْ مَآ أَنفَقۡتُمۡ وَلۡيَسۡـَٔلُواْ مَآ أَنفَقُواْۚ
ذَٰلِكُمۡ حُكۡمُ ٱللَّهِ يَحۡكُمُ بَيۡنَكُمۡۚ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٞ ١٠ وَإِن فَاتَكُمۡ
شَيۡءٞ مِّنۡ أَزۡوَٰجِكُمۡ إِلَى ٱلۡكُفَّارِ فَعَاقَبۡتُمۡ فَـَٔاتُواْ ٱلَّذِينَ ذَهَبَتۡ
أَزۡوَٰجُهُم مِّثۡلَ مَآ أَنفَقُواْۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ ٱلَّذِيٓ أَنتُم بِهِۦ مُؤۡمِنُونَ ١١

አንድ ብቻ ሲሆን እስከምታምኑ ድረስ በእኛና በእናንተ መካከል ጠብና[2] ጥላቻ ዘውትር ተገለጿ::[3] ባሉ ጊዜ::[4] ኢብራሂም ለአባቱ፡- ለአንተ ከአላህ ቅጣት ምንም የማልጠቅምህ /የማላድንህ/ ስሆን ለአንተ በእርግጥ ምህረትን እለምንልሃለሁ ማለቱ ብቻ ሲቀር[5]:: ጌታችን ሆይ! በአንተ ላይ ተመካን:: ወደ አንተም ተመልሰን:: መመለሻም ወደ አንተ ብቻ ነው::[6]

5 ጌታችን ሆይ! ለእነዚያ ለካዱ ሰዎች መሞከሪያ አታድርገን። ለእኛ ምህረት አድርግልን[7]:: ጌታችን ሆይ! አንተ አሸናፊና ጥበበኛ ነህ።

6 ለእናንተ[8] አላህንና የመጨረሻዉን ቀን ለሚፈራ ሰው ሁሉ በእነርሱ መልካም መከተል አለላችሁ።[9] ፊቱን የሚያዞርም ሰው (ራሱን ይጎዳል):: አላህ ተብቃቂና ምስጉን ነውና።

7 አላህ በእናንተና በእነዚያ ከእነሱ ጋር በተጣላችሁት[10] ሰዎች መካከል መፋቀርን ሊያደርግ ይችላል:: አላህ መሀሪና አዛኝ ነው::

8 ለእነዚያ በሃይማኖት ላልተዋጓችሁ ከአገሮቻችሁም ላላወጧዋችሁ (ከሓዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደ እነርሱ ፍትህ ልትውሉላቸው አላህ አይከለክላችሁም :: አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና ::

9 አላህ የሚከለክላችሁ ከእነዚያ በሃይማኖት ሰበብ ከተዋጓችሁና ከቤቶቻችሁም ካወጡዋችሁ፤ እናንተንም በማውጣት ላይ የረዱትን እንዳትወዳጇቸው ብቻ ነው :: እነርሱን ወዳጅ የሚያደርጓቸውም ሰዎች እነዚያ እነርሱ በዳዮች ናቸው ::

10 እናንተ[11] ያመናችሁ ሆይ! ምእምናት ስደተኞች ሆነው በሚመጡበት ጊዜ (ለሃይማኖት ሲሉ መሰደዳቸውን) ፈትኑዋቸው[12]። አላህ በእምነታቸው ከእናንተ ይልቅ ዐዋቂ ነው ::[13] አማኞችም መሆናቸውን ብታውቁ ወደ ከሓዲዎች /ባሎቻቸው/ አትመልሷቸው ። እነርሱ (ሴቶች) ለእነርሱ /ለከሓዲ ወንዶች/ አይፈቀዱምና። እነርሱም /ከሓዲያን ወንዶች/ ለእነርሱ (ለአማኝ ሴቶች/ የተፈቀዱ አይደሉምና::[14]

---

1 በእምነታችሁ ወይም በተግባራችሁ ::
2 በዚሁ ከቀጠላችሁ::
3 ካመናችሁ ግን ጠቡ ወደ ፍቅር ይቀየራል::
4 መልካም መከተል አለቻችሁ::
5 የኢብራሒምን ተግባሮች ሁሉንም ተከተሉ:: ለአባቱ ያለውን ሲቀር:: በእሱማ አትከተሉት:: ምክኒያቱም እርሱንም ቢሆን የአላህ ጠላት መሆኑ ሲገለፅለት ከእሱ ንፁህ ሆነ:: ስለዚህ ለከሃዲዎች ምህረትን እንዳትጠይቁ::
6 ባለው ተከተሉት።
7 ሙጃሒድ ስለዚህ አንቀጽ ሲናገሩ በእጃችንም ሆነ ከአንተ ዘንድ በሆነ ቅጣት አየትቅጣን:: ምክንያቱም ከሃዲዎች፡- በእውነት ላይ ቢሆኑ ኑሮ ይህ አይደርስባቸዉም ነበር በማለት የበለጠ ይጠማሉና ::

---

8 **6ኛ ው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-** በዚህ ሱራ ላይ የመጀመሪያዋ አንቀፅ ስትወርድ ሙስሊሞች በካፊር ዘመዶቻቸው ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ስላደረባቸው ነው የወረደው :: (ዋሂዲ::)
9 ይህ መልካም አርአያ የሚሆነው ከአላህ ኸይር ለሚመኙ ብቻ ነው ::
10 ይህም የሚሆነው እምነቱን ተረድተው ሲሰልሙ ነው:: እናም ከመካ መከፈት በኋላ ኢስላምን ተቀብለው ከሙስሊሞች ጋር ፍቅርን መስርተዋል ነብዩም የአቡ ሱፍያንን ልጅ ኡሙ ሀቢባን አግብተዋል። ከአቡ ሱፍያን ጋር ፍቅር የመሰረቱት ግን መካ የተከፈተ ዕለት ኢስላምን ከተቀበለና ነብዩን መጥላት ካቆመ በኋላ ነበር ::
አቢሁረይራ ነብዩ ሲሞቱ እምነታቸውና የቀየሩትን ሰዎች ለመዋጋት የመጀመሪያ ጦር መዘዝ አቡሱፍያን ብንሐርብ ነበሩ የዚህም አንቀፅ መልዕክት ይህኑ የሚያመለክትው ብለዋል።
11 **10ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-** በነብዩና በመኮች መካከል የተካሄደው ከሁደይቢያ ስምምነች ነጥቦች መካከል አንዱ፡- ሰልሞ የመጣን ወደ ካፊሮች መመለስ የሚለው ስለ ነበር ስምምነቱ እንዳበቃ በዚያው ቦታ ላይ እያሉ ሱበይዓህ ቢንቱል ሀሪስ የተባለች ሴት ሰልማ ስትመጣ ካሃዲው ባሏ በስምምነቱ መሠረት ትመለስልኝ በማለቱ ነው :: (ዋሂዲ እና ሱዩጢ::)
12 የተሰደድነው አላህንና ነቢዩን ወደንና ዲኑን ፈልገን እንጂ ከባል ተጣልተን ወይ አገር መርጠን፤ ወይም ለዱንያ ፍለጋ አይደለም በማለት እንዲምሉ ይደረግ እና ከማሉ ነብዩ (ﷺ) ለባሎቻቸው መህሮቻቸውንና ለእሷ የከፈሉትን በመስጠት በእስልምናቸው እንዲቀጥሉ ያደርጉ ነበር ተብሏል።
13 ላይ ላዩን ከመፈተን በላይ የውስጡን ጉዳይ እናንተ አትጠየቁም::
14 ሙስሊም ሴት ለከሃዲ አትፈቀድምና። ሴት ልጅ

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ إِذَا جَآءَكَ ٱلْمُؤْمِنَٰتُ يُبَايِعْنَكَ عَلَىٰٓ أَن لَّا يُشْرِكْنَ
بِٱللَّهِ شَيْـًٔا وَلَا يَسْرِقْنَ وَلَا يَزْنِينَ وَلَا يَقْتُلْنَ أَوْلَٰدَهُنَّ وَلَا يَأْتِينَ
بِبُهْتَٰنٍ يَفْتَرِينَهُۥ بَيْنَ أَيْدِيهِنَّ وَأَرْجُلِهِنَّ وَلَا يَعْصِينَكَ
فِى مَعْرُوفٍ ۙ فَبَايِعْهُنَّ وَٱسْتَغْفِرْ لَهُنَّ ٱللَّهَ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ
١٢ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تَتَوَلَّوْا۟ قَوْمًا غَضِبَ ٱللَّهُ عَلَيْهِمْ
قَدْ يَئِسُوا۟ مِنَ ٱلْءَاخِرَةِ كَمَا يَئِسَ ٱلْكُفَّارُ مِنْ أَصْحَٰبِ ٱلْقُبُورِ ١٣

ያወጡትንም ገንዘብ (መህሩን) ስጧቸው።[1]
መህራቸውንም ከሰጣችኋቸው ብታገቡዋቸው
ኃጢዓት የለባችሁም። የካሓዲዎችንም
ሴቶች የጋብቻ ቃል ኪዳ ች አትያዙ።
ሆ ም እናንተ ያወጣችሁትን ገንዘብ ጠይቁ።
እነርሱም ያወጡትንም ይጠይቁ። ይህ
የአላህ ፍርድ ነውና። በመካከላችሁ
ይፈርዳል። አላህ ዐዋቂና ጥበበኛ ነው።
11 ከሚስቶቻችሁም[2] አንዳቸው ወደ
ከሓዲዎች ቢያመልጧችሁ ቀጥሎም
ብትዘሙቷባቸው[3] ለእነዚያ ሚስቶቻቸው
ለሄዱባቸው (ሰዎች) ያወጡትን ወጭ
ስጧቸው። ያንንም እናንተ በእርሱ
ያመናችሁበትን አላህን ፍሩት።
12 አንተ ነብዩ ሆይ! ምዕምናቶች በአላህ
ምንንም ላያጋሩ፤ ላይሰርቁም፤ ላያመነዝሩም፣
ለጆቻቸውን ላይገድሉም፣ በእጆቻቸውና
በእግሮቻቸው መካከልም የሚቀጣጥፉት
የሆነን ኃጢዓት ላያመጡ (ላይሠሩ)[4]፣
በበጎም ስራ ትእዛዝህን ላይጥሱ ቃል ኪዳን
ሊገቡልህ በመጡህ ጊዜ ኪዳን ተጋባቸው ።
ለእነርሱም አላህን ምህረት ለምንላቸው ።
አላህ በጣም መሓሪና አዛኝ ነውና ።[5]
13 እናንተ[6] ያመናችሁ ሆይ! አላህ በእነሱ
ላይ የተቆጣባቸውን ህዝቦች አትወዳጁ ።[7]
ከሓዲዎች ከመቃብር ሰዎች ተስፋ
እንደቆረጡ ሁሉ ከመጨረሻይቱም ዓለም
ምንዳ መኖር በእርግጥ ተስፋ ቆርጠዋል።[8]

سُورَةُ الصَّفِّ — ترتيبها ٦١ — آياتها ١٤

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

سَبَّحَ لِلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۖ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ
١ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لِمَ تَقُولُونَ مَا لَا تَفْعَلُونَ ٢
كَبُرَ مَقْتًا عِندَ ٱللَّهِ أَن تَقُولُوا۟ مَا لَا تَفْعَلُونَ ٣ إِنَّ
ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلَّذِينَ يُقَٰتِلُونَ فِى سَبِيلِهِۦ صَفًّا كَأَنَّهُم
بُنْيَٰنٌ مَّرْصُوصٌ ٤ وَإِذْ قَالَ مُوسَىٰ لِقَوْمِهِۦ يَٰقَوْمِ لِمَ
تُؤْذُونَنِى وَقَد تَّعْلَمُونَ أَنِّى رَسُولُ ٱللَّهِ إِلَيْكُمْ ۖ فَلَمَّا
زَاغُوٓا۟ أَزَاغَ ٱللَّهُ قُلُوبَهُمْ ۚ وَٱللَّهُ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْفَٰسِقِينَ ٥

## 61 ኛውምዕራፍ፡ የሰልፍ (ሱረቱ አስ-ሶፍ) ምዕራፍ ነው። አንቀጾቹ 14 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 በሰማያትና[9] በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ

በመሰደዷ ሳይሆን በመስለሟ ብቻ ከካፊር ባሏ ትለያለች።

1 ሻፊዒ ከባል ሌላ የሆነ ዘመድ እንድትመለስለት ከጠየቀ ካሳም ሆነ ሴትዩዋ አይሰጠውም ። ብለዋል ።

2 11ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-ከሰለመች በኋላ እምነቷን ቀይራ/ከፍራ/ አንድ ሰቂፋዊ ባገባችው ኡመልሐከም ቢንቱ አቢሱፍያን ምክንያት ነው ። ይህ አንቀጽ የወረደው በታሪኩ ውስጥ በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጊዜ ከሰለሙ የቁረይሽ ሴቶች የከፈረች ይህች ሴት ብቻ ናት ይባላል ። (ሱዩጢ።)

3 አሸንፋችሁ ንብረታቸዉን ብትቆጣጠሩ

4 ፈራዕ የተባለ ዓሊም አንዳንድ ሴቶች ከመንገድ ላይ የወደቀን ልጅ አንስተው ይህን ከአንተ የወለድነው ይሉ ስለነበር ነው። ሲሉ ኢብኑ ዓባስ ደግሞ አንዳንድ ሴቶች ሴት ሲወልዱ በወንድ የቀይሩ ስለነበር ነው ይህንን ህግ መደንገግ ያስፈለገው ብለዋል ።

5 ይህ ጉዳይ የተደረገው በፈትህ ቀን ነበር ። የመካ ሴቶች ወደ ነቢዩ መጥተው ሙባይዓ ለማድረግ ሲጠይቋቸው ይህን ዘርዘር ያዘለ የሙባይዓ አይነት አስተማሯቸው ።

6 **13ኛ ው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሀ.** አንዳንድ ችግረኛ ሙስሊሞች የሙስሊሞችን ሚስጥር ወደ አይሁዶች በማድረስ ከአይሁዶች አንዳንድ ጥቅማጥቅም ይፈልጉ ስለነበር ከዚህ ተብብራቸው እንዲቆጠቡ ነው ። (ዋሂዲ) አብዱላህ ቢን ዑመርና ዘይድ ኢብኑል ሀሪስ ከተወሰኑ አይሁዶች ጋር በነበራቸው መጠነኛ ፍቅር ምክንያት ነው ። (ሱዩጢ)

7 በዚህ አባባል ከሃዲ የተባለ ሁሉ ይጠቃለላል ሲሉ ሌሎች ደግሞ አይሆዶችን ብቻ ነው ብለዋል ።

8 ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ። 1.ትክክለኛ አማኞች አንዳንድ ጊዜ ስህተት ቢፈፅሙም ሊታለፉ እንደሚገባቸው፣ የበድር ዘማች ሰዎች ክብርና ትልቅነት ምን ያህል እንደሆነ፤ 2.ከአይሁድ ጋር ወዳጅነት መፍጠር፣ ሙስሊሞችን ወደ ጎን በመተው ከሐዲዎችን ወዳጅ አድርጎ መያዝና ማፍቀርም የተከለከለ መሆኑን እንገነዘባለን ። ከዚሁ ጋር በተያያዘም የሙስሊሞችን ምስጢር ለከሐዲዎች የሚያደርስ ቢሰግድም፣ ቢያምም በከፍተኛ አደጋ ላይ መሆኑን፤ ሙስሊም ከከሃዲ ጋር በሚኖረው ዝምድና በቂያማ ዕለት ምንም ፋይዳ እንደማያገኝ ያስተምረናል ። በኢስላም የተፈቀደውና የተከለከለው መውደድ ያለብንም ምን ምን እንደሆነ በግልጽ ተቀምጧል። ከሃዲዎች አመቺ አጋጣሚ ካገኙ ለሙስሊሞች ምንም ዓይነት ርህራሔ እንደማያደርጉላቸው የሚያሳይ ነጥብ እናገኛለን። 3.የፍትሃዊነትን አስፈላጊነት፣ የሙስሊሞችን መሪ ለመታዘዝ ቃል መግባትና በቃሉ መሰረት መሙላትም ግዴታ መሆኑን፤ 4.ሽርክና አብረው የተነሱት ወንጀሎች ሁሉ የተከለከሉ ስለመሆናቸው፤ 5.የተሰደደች ሴትን የእምነት ጥንካሬ መፈተን ግዴታ መሆኑንና በእምነቷ ትክክለኛ መሆንዋ ከታወቀ በኋላ ሴቲቱን ወደ ከሃዲው ባሏ መመለስ የተከለከለ ነው ።

9 **ከ1-2 ያሉ አንቀጾች የወረዱበት ምክንያት፡-**

وَإِذْ قَالَ عِيسَى ٱبْنُ مَرْيَمَ يَٰبَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ إِنِّى رَسُولُ ٱللَّهِ إِلَيْكُم مُّصَدِّقًا
لِّمَا بَيْنَ يَدَىَّ مِنَ ٱلتَّوْرَىٰةِ وَمُبَشِّرًۢا بِرَسُولٍ يَأْتِى مِنۢ بَعْدِى ٱسْمُهُۥٓ أَحْمَدُ ۖ فَلَمَّا
جَآءَهُم بِٱلْبَيِّنَٰتِ قَالُوا۟ هَٰذَا سِحْرٌ مُّبِينٌ ﴿٦﴾ وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنِ ٱفْتَرَىٰ
عَلَى ٱللَّهِ ٱلْكَذِبَ وَهُوَ يُدْعَىٰٓ إِلَى ٱلْإِسْلَٰمِ ۚ وَٱللَّهُ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلظَّٰلِمِينَ
﴿٧﴾ يُرِيدُونَ لِيُطْفِـُٔوا۟ نُورَ ٱللَّهِ بِأَفْوَٰهِهِمْ وَٱللَّهُ مُتِمُّ نُورِهِۦ وَلَوْ كَرِهَ
ٱلْكَٰفِرُونَ ﴿٨﴾ هُوَ ٱلَّذِىٓ أَرْسَلَ رَسُولَهُۥ بِٱلْهُدَىٰ وَدِينِ ٱلْحَقِّ لِيُظْهِرَهُۥ
عَلَى ٱلدِّينِ كُلِّهِۦ وَلَوْ كَرِهَ ٱلْمُشْرِكُونَ ﴿٩﴾ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ هَلْ أَدُلُّكُمْ
عَلَىٰ تِجَٰرَةٍ تُنجِيكُم مِّنْ عَذَابٍ أَلِيمٍ ﴿١٠﴾ تُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَتُجَٰهِدُونَ
فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ بِأَمْوَٰلِكُمْ وَأَنفُسِكُمْ ۚ ذَٰلِكُمْ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ ﴿١١﴾
يَغْفِرْ لَكُمْ ذُنُوبَكُمْ وَيُدْخِلْكُمْ جَنَّٰتٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ وَمَسَٰكِنَ
طَيِّبَةً فِى جَنَّٰتِ عَدْنٍ ۚ ذَٰلِكَ ٱلْفَوْزُ ٱلْعَظِيمُ ﴿١٢﴾ وَأُخْرَىٰ تُحِبُّونَهَا ۖ نَصْرٌ
مِّنَ ٱللَّهِ وَفَتْحٌ قَرِيبٌ ۗ وَبَشِّرِ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿١٣﴾ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ كُونُوٓا۟
أَنصَارَ ٱللَّهِ كَمَا قَالَ عِيسَى ٱبْنُ مَرْيَمَ لِلْحَوَارِيِّۦنَ مَنْ أَنصَارِىٓ إِلَى ٱللَّهِ ۖ
قَالَ ٱلْحَوَارِيُّونَ نَحْنُ أَنصَارُ ٱللَّهِ ۖ فَـَٔامَنَت طَّآئِفَةٌ مِّنۢ بَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ
وَكَفَرَت طَّآئِفَةٌ ۖ فَأَيَّدْنَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ عَلَىٰ عَدُوِّهِمْ فَأَصْبَحُوا۟ ظَٰهِرِينَ ﴿١٤﴾

አላህን አሞገሠ /አጠራ/፡፡ እርሱ አሸናፊና ጥበበኛ ነው፡፡

(2) (3) እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! የማትሰሩትን ነገር ለምን ትናገራላችሁ? የማትሰሩትን ነገር መናገራችሁ ከአላህ ዘንድ በመጠላት ተለቀ /እጅግ ከበደ/፡፡[1]

(4) አላህ እነዚያን ልክ እንደተለሰነ ግንብ የተሰለፉ ሆነው በመንገዱ /በሃይማኖቱ) የሚፋለሙትን ይወዳል[2]፡፡

(5) ሙሳም ለህዝቦቹ፡- ህዝቦቼ ሆይ! እኔ ወደ እናንተ የአላህ መልክተኛ መሆኔን እርግጥ የምታውቁ ስትሆኑ ለምን ታሰቃዩኛላችሁ ባለ ጊዜ የሆነዉን አስታውስ፡፡ ከእውነት በተዘነበሉ ጊዜ አላህ ልቦቻቸውን አዘነበለባቸው፡፡ አላህ አመፀኞችን ህዝቦች አያቀናም፡፡

(6) የመርየም ልጅ ዒሳም፡- የእስራኤል ልጆች ሆይ፤ እኔ ከተውራት በፊት ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልእክተኛ ስሙ አህመድ በሆነው የማበስር ስሆን ወደ እናንተ የተላክሁ የአላህ መልዕክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ የሆነዉን አስታውስ፡፡ ዒሳ /ሙሐመድ/ በግልጽ ታዓምራቶች ባመጣላቸው ጊዜ፡- ይህ ግልጽ ድግምት ነው አሉ[3]፡፡

(7) እርሱ ወደ ኢስላም የሚጠራ ሲሆን በአላህ ላይ ውሸትን ከቀጣጠፈ ሰውም ይበልጥ በደለኛ ማን ነው? አላህ በዳዮችን ህዝቦች አይመራም፡፡

(8) የአላህን ብርሃን በአፎቻቸው ሊያጠፉ ይሻሉ፡፡ አላህ ከሓዲዎች ቢጠሉም እንኳ ብርሃኑን ገላጭ ነው ፡፡

(9) አላህ ያ አጋሪዎች ቢጠሉም መልዕክተኛውን በመምሪያ መጽሐፍና በእውነተኛው ሃይማኖት /በኢስላም/ ከሃይማ ት ሁሉ በላይ ይፋ ሊያደርገው የላከ ነው፡፡

(10) ሙሐመድ ሆይ! እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ከአሳማሚ ቅጣት የምታድናችሁ የሆነችን ትርፋማ ንግድ ላመላክታችሁን? (በላቸው፡፡)

(11) (እርሷም) በአላህና በመልእክተኛው ታምናላችሁ፡፡ በአላህ መንገድ በገንዘቦቻችሁና በነፍሶቻችሁ ትታገላላችሁ፡፡ ይህ ተግባር የምታውቁ ከሆናችሁ ለእናንተ የተሻለ ነው፡፡

(12) ኃጢዓቶቻችሁን ይምራል፡፡ ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውንም ገነቶች ያገባችኋል፡፡ በመ ሪያ ገነቶችም በሚያማምሩ ቤቶች ውስጥ ያስቀምጣችኋል፡፡ ይህ ታላቅ ዕድል ነው፡፡

(13) ሌላይቱንም የምትወዷትን (ጸጋ ይሰጣችኋል፡፡ እርሷም)፡- ከአላህ የሆነ እርዳታና ቅርብ የሆነ የአገር መክፈት[4] ነው፡፡ ምዕምናንንም አብስር፡፡

(14) እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የመርየም ልጅ ዒሳ ለሀዋርያቱ፡- ወደ አላህ ረዳቴ ማንነው እንዳለና ሐዋርያቶቹም፡- እኛ የአላህ ረዳቶች ነን እንዳሉት የአላህ ረዳቶች ሁኑ በላቸው[5]፡፡ ከእስራኤልም ልጆች አንደኛዋ

---

ሀ-አብደላህ ቢን ሰላም የተባለ ሰሃቢይ ሲናገሩ አንድ ቀን የተወሰኑ ሰሃቦች በአንድ ተቀምጠን ከአላህ (ﷻ) ዘንድ ተወዳጅ ሥራ ምን እንደሆነ ብናውቅ እንሰራ ነበር በማለታቸው ነው ፡፡ (ዋሂዲ እና ሱዩጢ ፡፡)
ለ- አብደላህ ቢን ዐባስ የተባሉ ሰሃቢይ ሲናገሩ አንድ ቀን ጅሃድ ከመፈቀዱ በፊት ከተወሰኑ ሰሃቦች ጋር በአንድ ተቀምጠን ከአላህ (ﷻ) ዘንድ ተወዳጅ ሥራ ምን እንደሆነ ብናውቅና ብንሰራው ብለን ስንጠይቅና ጅሃድ መሆኑ ሲነገረን አንዳንዶቹ ስለከበዳቸው ነው ፡፡

[1] ኢብኑ ዓባስ ይህ ተግባር በነቢዩ ዘመን አንዳንድ ሰዎች ወደ አሳቸው እየመጡ በዚህ ሰይፌ ገደልኩ፤ እንዲህ አደረኩ እያሉ ያልሰሩትን ያወሩ ስለነበር ነው ፡፡

[2] ነቢዩ (ﷺ) ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ (የሁሉም ነገር ቁንጮ ኢስላም ነው፡፡ ቋሚው ምሰሶው ደግሞ ሶላት ነው ጉልላት ሻኛው ደግሞ ጂሀድ ነው) ብለዋል ፡፡

[3] የጂሃድ ሰዎችን እንደሚወድ ካስረዳ በኋላ ሙሳና ዒሳም ተውሂድ እንዳስተማሩና ጂሃድ እንዳደረጉ እነሱን እንቢ ያለ ሰው አደገኛ ቅጣት እንደደረሰበት አስተማረ ፡፡ የነቢዩ ኡመቶችም ይህን መሰል ተግባር ከፈፀሙ ተመሳሳይ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው ለማስተማር ነው ፡፡

[4] ቁረይሾችን አሸንፈው መካን መቆጣጠር ማለት ሊሆን እንደሚችል ሁሉ ዐጧእ የተባለው ዓሊም ሮምና ፋርስንም መቆጣጠር ሊሆን ይችላል ብለዋል፡፡

[5] ይህ ጉዳይ በተግባር ታይቷል ፡፡ ይኸውም አንሷሮች 70 ሰዎች ሆነው ከመዲና ወደ መካ መተው አቀባ ላይ ከነብዩ ጋር ተገቢውን ቃልኪዳን ገብተው ወደ መዲና በመውሰድ ኢስላምን ረድተዋል፡፡ ነብዩ (ﷺ) አቀባ ላይ ላገኟቸው 70 ሰዎች ‹‹ሃዋሪያት ለዒሳ ሰዎች ሃላፊዎች እንደሆኑ ሁሉ ሃላፊያችሁ የሚሆኑ አስራ ሁለት ሰዎችን ምረጡልኝ ብለው አስመረጡና

ጭፍራ አመነች። ሌላይቱም ጭፍራ ካደች። እነዚያን ያመኑትንም በጠላታቸው ላይ አበረታናቸው። አሸናፊዎችም ሆኑ።[1]

## 62 ኛው የጁሙዐ ምዕራፍ (ሱረቱ አል- ጁመዓህ) ነው።[2] አንቀጾቹ 11 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ ንጉሥ፤ ቅዱስ (ንፁህ)፤ አሸናፊና ጥበበኛ የሆነውን አላህን ያሞግሣል።

2 እርሱ ያ! ለመሃይማን (ዓረቦች)[3] አንቀጾችን (ቁርአንን) በእነርሱ ላይ የሚያነብላቸው፣ የሚያጠራቸውም፣ መጽሐፉንና ጥበብን የሚያስተምራቸውም የሆነን መልእክተኛ (ሙሐመድን) ከእነሱው ውስጥ የላከ ነው። እነርሱም ከእርሱ በፊት በግልጽ ስህተት ውስጥ ነበሩ ።

3 ከእነሱም ሌሎች ገና ያልተከተሏቸው[4] በሆኑት ላይ (የላከው ነው)። እርሱም አሸናፊና ጥበበኛ ነው ።

4 ይህ የአላህ ችሮታ ብቻ ነው። ለሚሻው ሰው ይሰጠዋል። አላህ የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው ።

5 የእነዚያ ተውራትን የተጫኑትና ከዚያም ያልተሸከሟት (ያልሰሩባት) ሰዎች ምሳሌ መጽሐፎችን እንደሚሸከም አህያ ብጤ ነው።[5] የእነዚያ በአላህ አንቀጾች ያስተባበሉት ህዝቦች ምሳሌ ከፋ ።[6] አላህ በደዮችን ህዝቦች አይመራም ።

6 ሙሀመድ ሆይ! እናንተ አይሁዳውያን ሆይ! /የሁዳ የሆናችሁ/ ሆይ! ከሰው ሁሉ በተለየ እናንተ ብቻ ለአላህ ወዳጆች ነን ብትሉና በዚህ አባባላችሁ እውነተኞች እንደሆናችሁ እስቲ ሞትን ተመኙ በላቸው።

7 እጆቻቸው[7] ባስቀደሙት ኃጢዓት ምክንያት በፍጹም አይመኙትም። አላህ በደዮችን ዐዋቂ ነው።

8 ሙሀመድ ሆይ! ያ ከእርሱ የምትሸሹት ሞት እርሱ በእርግጥ አግኛችሁ ነው[8]። ከዚያም ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ ወደ ሆነው ጌታ

سُورَةُ الجُمُعَةِ — آياتها ١١ — ترتيبها ٦٢

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

يُسَبِّحُ لِلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ ٱلۡمَلِكِ ٱلۡقُدُّوسِ ٱلۡعَزِيزِ
ٱلۡحَكِيمِ ١ هُوَ ٱلَّذِي بَعَثَ فِي ٱلۡأُمِّيِّـۧنَ رَسُولٗا مِّنۡهُمۡ يَتۡلُواْ
عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتِهِۦ وَيُزَكِّيهِمۡ وَيُعَلِّمُهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ وَإِن كَانُواْ
مِن قَبۡلُ لَفِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٖ ٢ وَءَاخَرِينَ مِنۡهُمۡ لَمَّا يَلۡحَقُواْ بِهِمۡۚ
وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٣ ذَٰلِكَ فَضۡلُ ٱللَّهِ يُؤۡتِيهِ مَن يَشَآءُۚ وَٱللَّهُ
ذُو ٱلۡفَضۡلِ ٱلۡعَظِيمِ ٤ مَثَلُ ٱلَّذِينَ حُمِّلُواْ ٱلتَّوۡرَىٰةَ ثُمَّ لَمۡ
يَحۡمِلُوهَا كَمَثَلِ ٱلۡحِمَارِ يَحۡمِلُ أَسۡفَارَۢاۚ بِئۡسَ مَثَلُ ٱلۡقَوۡمِ
ٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِۚ وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ٥
قُلۡ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ هَادُوٓاْ إِن زَعَمۡتُمۡ أَنَّكُمۡ أَوۡلِيَآءُ لِلَّهِ مِن
دُونِ ٱلنَّاسِ فَتَمَنَّوُاْ ٱلۡمَوۡتَ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ٦ وَلَا يَتَمَنَّوۡنَهُۥٓ
أَبَدَۢا بِمَا قَدَّمَتۡ أَيۡدِيهِمۡۚ وَٱللَّهُ عَلِيمُۢ بِٱلظَّٰلِمِينَ ٧ قُلۡ إِنَّ
ٱلۡمَوۡتَ ٱلَّذِي تَفِرُّونَ مِنۡهُ فَإِنَّهُۥ مُلَٰقِيكُمۡۖ ثُمَّ تُرَدُّونَ
إِلَىٰ عَٰلِمِ ٱلۡغَيۡبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ٨

---

ለተመራጮች እናንተ ሃዋሪያት ለዒሳ ሃላፊዎች እንደሆኑ ሁሉ እናንተም ለሕዝቦቻችሁ ሃላፊዎች ናችሁ። እኔም ለሕዝቦቼ ሃላፊ ነኝ ብለዋል ።›

1 **ከሱራው የምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።** 1.በኢስላም ቃልን ማፍረስና መዋሸት የተከለከለ ነው ። ውሸት ከሺርክና ኩፍር ቀጥሎ ከወንጀሎች ሁሉ አስከፊ መሆኑን፤ 2 ከወንጀል ወደ ወንጀል መሸጋገር አደገኛ ነው። በከፍተኛ ወንጀል ውስጥ የተዘፈቁ ሰዎች ለአሏህ (عَزَّ وَجَلَّ) ሂዳያ እንደማይታደሉ፤ 3.አይሁድ በዒሳ ከማስተባበላቸው በተጨማሪ በነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) በማስተባበል፤ ነሳራዎችም ነብዩ ዒሳን (عليه السلام) በመካድ፤ በእሳቸው /በዒሳ/ (عليه السلام) የተበሰረላቸውን ነብዩ ሙሐመድን (ﷺ) አናውቀም በማለት ለኩፍር እንደተዳረጉ፤ 4.ኢስላም የጅሃድን ትልቅነትና ለእሱም የአንድነትን አስፈላጊነት፣ በሐብትና በጉልበት የሚከፈሉ መስዋዕትነቶች በኢስላም የሚሰጣቸው ክብር ምን ያህል እንደሆነ እንማራለን።

2 ምዕራፉ በመዲና ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ።

3 መሃይማን የሚለው መፃፍ የሚችለትን ሆነ የማይችሉትን ዓረብ የሚያጠቃልል ሲሆን ብዙዎቹ መፃፍና ማንበብ የማይችሉ ስለ ነበሩ ነው በዚህ የተገለፁት ።

4 ያልተከተሏቸው ማለት ሲሆን እነሱም እስከ ዐለም ፍፃሜ ድረስ ኢስላምን የሚቀበሉ ሁሉ ናቸው። ቡኻሪና ሌሎችም ከአቡ ሁረይራ እንደዘገቡት (በነበዩ አጠገብ ተቀምጠን በነበርንበት ነው ይህ ሱራ የወረደው)። እናም እዚህ ቦታ ሲደርሱ አንድ ሰው ተነስቶ እኒህ እኛን ያልተከተሉን እነማን ናቸው? በማለት ሲጠይቃቸው እጆቻቸውን በሰልማኑል ፋሪሲ ላይ አስቀምጠው ሕይወቴ በእጁ በሆነበት ጌታ ይሁንብኝ እምነት ሱረያ ላይ እንኳን ቢሆን ከእነዚህ የሆኑ ሰዎች ያገኟታል።

5 ይህ ምሳሌ በተውራት የታዘዙትን ላልፈፀሙ አይሁዳዊያን የተሰጠ ምሳሌ ነው ።

6 ስለዚህ እንደእነሱ እንዳትሆኑ። ይህ ምሳሌ ነቢዩ ኹጥባ ላይ እያሉ ወደ ንግዱ ማህበረሰብ የሄዱትን አስመልክቶ የተሰጠ የማስጠንቀቂያ ምሳሌ ነው። ልክ እንደዚሁ በቦታው እያለም ኹጥባ /የማያዳማጥ ሁሉ ምሳሌው ነቢዩ እንዳሉት የጁሙዐ ዕለት ኢማሙ እየኸጠበ እያለ የተናገረ ሰው ምሳሌው መፅሐፎችን እንደሚሸከም አህያ ነው ። እሱን ዝም በል ያለ ሰው የጁሙዐ ሶላት የለዉም።

7 ይህም የሆነው አይሁዶች ከሰው ሁሉ የተለየ ክብር አለን ብለው ያምኑና ይናገሩ ስለ ነበር ይህ አባባል ዉሸት መሆኑን አስተማራቸው።

8 ፊት ለፊት መገኛኘታችሁ አይቀሬ ነው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا نُودِيَ لِلصَّلَوٰةِ مِن يَوۡمِ ٱلۡجُمُعَةِ
فَٱسۡعَوۡاْ إِلَىٰ ذِكۡرِ ٱللَّهِ وَذَرُواْ ٱلۡبَيۡعَۚ ذَٰلِكُمۡ خَيۡرٞ لَّكُمۡ إِن كُنتُمۡ
تَعۡلَمُونَ ٩ فَإِذَا قُضِيَتِ ٱلصَّلَوٰةُ فَٱنتَشِرُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ
وَٱبۡتَغُواْ مِن فَضۡلِ ٱللَّهِ وَٱذۡكُرُواْ ٱللَّهَ كَثِيرٗا لَّعَلَّكُمۡ تُفۡلِحُونَ
١٠ وَإِذَا رَأَوۡاْ تِجَٰرَةً أَوۡ لَهۡوًا ٱنفَضُّوٓاْ إِلَيۡهَا وَتَرَكُوكَ قَآئِمٗاۚ قُلۡ
مَا عِندَ ٱللَّهِ خَيۡرٞ مِّنَ ٱللَّهۡوِ وَمِنَ ٱلتِّجَٰرَةِۚ وَٱللَّهُ خَيۡرُ ٱلرَّٰزِقِينَ ١١

## سُورَةُ المُنَافِقُونَ

ترتيبها ٦٣ — آياتها ١١

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

إِذَا جَآءَكَ ٱلۡمُنَٰفِقُونَ قَالُواْ نَشۡهَدُ إِنَّكَ لَرَسُولُ ٱللَّهِۗ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ
إِنَّكَ لَرَسُولُهُۥ وَٱللَّهُ يَشۡهَدُ إِنَّ ٱلۡمُنَٰفِقِينَ لَكَٰذِبُونَ ١
ٱتَّخَذُوٓاْ أَيۡمَٰنَهُمۡ جُنَّةٗ فَصَدُّواْ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِۚ إِنَّهُمۡ سَآءَ مَا كَانُواْ
يَعۡمَلُونَ ٢ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ ءَامَنُواْ ثُمَّ كَفَرُواْ فَطُبِعَ عَلَىٰ قُلُوبِهِمۡ
فَهُمۡ لَا يَفۡقَهُونَ ٣ ۞ وَإِذَا رَأَيۡتَهُمۡ تُعۡجِبُكَ أَجۡسَامُهُمۡۖ
وَإِن يَقُولُواْ تَسۡمَعۡ لِقَوۡلِهِمۡۖ كَأَنَّهُمۡ خُشُبٞ مُّسَنَّدَةٞۖ يَحۡسَبُونَ كُلَّ
صَيۡحَةٍ عَلَيۡهِمۡۚ هُمُ ٱلۡعَدُوُّ فَٱحۡذَرۡهُمۡۚ قَٰتَلَهُمُ ٱللَّهُۖ أَنَّىٰ يُؤۡفَكُونَ ٤

(በቂያማ ዕለት) ተመላሾች ናችሁ:: ትሰሩትም የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል በላቸው::

9 እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በዐርብ ቀን ለስግደት ጥሪ[1] በተደረገ ጊዜ ወደ አላህ ማውሳት(ኹጥባ ሶላት) ሂዱ:: መሸጥንም ተዉ:: ይሃችሁ የምታውቁ ብትሆኑ ለእናንተ በጣም የተሻለ ነው።

10 ሶላቷ በተፈጸመች ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑና የአላህን ችሮታ ፈልጉ:: ልትድኑ ይከጀላልና አላህንም በብዙው አውሱ[2]::

11 ሙሀመድ ሆይ! ንግድን[3] ወይም ዛዛታን ባዩ ጊዜም ቆመህ የተዉህ ሲሆኑ ወደ እርሷ ይበተናሉ:: ከአላህ ዘንድ ያለው ከዛዛታም ከንግድም በላጭ ነው፤ አላህም ከሰጪዎች ሁሉ ይበልጥ ሲሳይን ሰጭ ነው በላቸው::[4]

## 63 ኛው ምዕራፍ የመናፍቃን ምዕራፍ (ሱረቱ አል-ሙናፊቁን) ነው::[5] አንቀጾቹ 11 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም እና አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 መናፍቃን በመጡህ /ወደ አንተ በመጡ/ ጊዜ፡- አንተ የአላህ መልዕክተኛ መሆንህን በእርግጥ (ምለን) እንመሰክራለን ይላቁ :: አላህም አንተ በእርግጥ መልክተኛው መሆንህን ያውቃል። አላህም መናፍቃን[6] ውሸታሞች መሆናቸውን ይመሰክራል።

2 መሐላዎቻቸውን ጋሻ አድርገው ያዙ:: ከአላህም መንገድ ከለከሉ:: እነሱ ይሰሩት የነበሩት ነገር ከፋ ::

3 ይህ እነሱ (በምላስ)፤ ያመኑ ከዚያም (በልብ) የካዱ በመሆናቸው ነው :: በልቦቻቸውም ላይ ታተመባቸው :: ስለዚህ እነሱ አያውቁም [7]::

4 ባየሃቸውም ጊዜ አካሎቻቸው (ግዙፍነታቸው) ያስደንቁሃል:: ቢናገሩም ንግግራቸውን[8] ታዳምጣለህ ::[9] እነርሱ ልክ

---

[1] ጥሪ ማለት ኢማሙ መንበር ላይ ሲወጣ የሚደረገውን አዛንን ስትሰሙ ማለት ነው :: ምክንያቱም በነብዩ ጊዜ ይህ ብቻ ነበር የነበረው አዛን የመጀመሪያው አዛን የተጀመረው ከተማዋ እየሰፋች በሄደችበት ጊዜ በኡስማን ኢብኑ አፋን ጊዜ ነበር ::

[2] በተለያዩ ስራዎች ላይም ሁናችሁ አላህን አስታውሱ ::

[3] **11ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሀ-** አንድ ሰው ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) መጥቶ(ግመሌን አስሬ በአላህ ልመካ ወይስ ልልቀቃትና በአላህ (عز وجل) ልመካ ሲላቸው ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) እሰራትና በአላህ ተመካ አሉት ::) (ቲርሚዚ) ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽና የነቢዩ ሀዲስ የሚያሳዩት ሰዎች በአላህ (عز وجل) መመካት ግዴታቸው ቢሆንም ራሳቸውን ለመቻል እንቅስቃሴ ማድረግ ከተወኩል ጋር ፈጽሞ አይቃረንም የሚለውን መልዕክት ያስተምራሉ :: ነቢያት ተቀጥረው ይሰሩ እንደነበር ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡበክርና ዑመርም ተቀጥረው ሠርተዋል :: እንዲያውም ኢስላም ሁለቱንም አጣምሮ መያዝን ነው አበክሮ የሚመክረው :: አንድ ቀን ከየመን የመጡ ሰዎች ዑመር ኢብኑልኸጣብ እነማን ናችሁ ብለው ጠይቀው በአላህ (عز وجل) ተመኪዎች ነን ስላሉዋቸው፡- እናንተ ሰነፎች ናችሁ :: በአላህ (عز وجل) ተመኪ ማለት ዘርን በምድር ላይ አሳርፎ በአላህ (عز وجل) የሚመካ ነው አሏቸው ::
ለ-የመዲና ሰዎች ከፍተኛ ረሃብና ድርቅ ስላጋጠማቸው ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በኹጥባ ላይ እያሉ የንግድ ግመሎች ወደ መዲና ከተማ ሲደርሱ:: አሥራ ሁለት ወንዶች ሰባት ሴቶች ብቻ ኹጥባ እያዳመጡ ሲቀሩ ሁሉም ጥለዋቸው በመሄዳቸው ነው ይህ አንቀጽ የወረደው :: (ዋሂዲ ና ሱዩጢ)

[4] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ::

1. የጁምአ ሶላት በሁሉም ሙስሊሞች ላይ ግዴታ ነው :: የጁምዐ አዛን በተሰማ ጊዜ ለሰላት ከሚደረግ ዝግጅት በቀር ሌላውን ነገር ሁሉ /መሸጥንም መቆፈርንም... ሌላ ሥራንም/ መተው ይገባል:: የጁምአ ቀን ኹጥባዎች ግዴታ መሆቸውና በሰዓቱ ተገኝቶ ማድመጡ አስፈላጊ ነው:: ኢማሙ ኹጥባ ላይ እያለ የተናገረ ሰው ምሳሌው «መፅሐፎችን እንደተሸከመ አህያ ማለት ነው፤ ነብዩ በኹጥባ ወቅት የተናገረን ሰው ዝምበል ያለ ሰው የጁምአ ሰላት የለውም/ ብለዋል::
2. የሥራን አስፈላጊነት በተመለከተ ሰዎች በአሏህ ብቻ ተመክተው እጃቸውን አጣጥፈው መቀመጥ እንደሌለባቸው እንማራለን::

[5] ምዕራፉ በመዲና ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው::

[6] ከልብ እንመሰክራለን በማለታቸው::

[7] ይህ አንቀፅ የወረደው አምነው በከፈሩ ሰዎች ምክንያት ነው::

[8] አንደበተ ርቱዕ በመሆናቸው::

[9] አብዱላህ ብን ኡበይ የተባለው የሙናፊቆች አለቃ አንደበተ ርቱእ፤ መልከ መልካምና ወፍራም ነበር ይባላል። እናም የእሱን ሁኔታ ለመግለፅ ነው ተብሏል።

وَإِذَا قِيلَ لَهُمْ تَعَالَوْا۟ يَسْتَغْفِرْ لَكُمْ رَسُولُ ٱللَّهِ لَوَّوْا۟ رُءُوسَهُمْ
وَرَأَيْتَهُمْ يَصُدُّونَ وَهُم مُّسْتَكْبِرُونَ ﴿٥﴾ سَوَآءٌ عَلَيْهِمْ
أَسْتَغْفَرْتَ لَهُمْ أَمْ لَمْ تَسْتَغْفِرْ لَهُمْ لَن يَغْفِرَ ٱللَّهُ لَهُمْ إِنَّ
ٱللَّهَ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْفَٰسِقِينَ ﴿٦﴾ هُمُ ٱلَّذِينَ يَقُولُونَ
لَا تُنفِقُوا۟ عَلَىٰ مَنْ عِندَ رَسُولِ ٱللَّهِ حَتَّىٰ يَنفَضُّوا۟ وَلِلَّهِ
خَزَآئِنُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَلَٰكِنَّ ٱلْمُنَٰفِقِينَ لَا يَفْقَهُونَ
﴿٧﴾ يَقُولُونَ لَئِن رَّجَعْنَآ إِلَى ٱلْمَدِينَةِ لَيُخْرِجَنَّ ٱلْأَعَزُّ
مِنْهَا ٱلْأَذَلَّ وَلِلَّهِ ٱلْعِزَّةُ وَلِرَسُولِهِۦ وَلِلْمُؤْمِنِينَ وَلَٰكِنَّ
ٱلْمُنَٰفِقِينَ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٨﴾ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تُلْهِكُمْ
أَمْوَٰلُكُمْ وَلَآ أَوْلَٰدُكُمْ عَن ذِكْرِ ٱللَّهِ وَمَن يَفْعَلْ
ذَٰلِكَ فَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْخَٰسِرُونَ ﴿٩﴾ وَأَنفِقُوا۟ مِن مَّا رَزَقْنَٰكُم
مِّن قَبْلِ أَن يَأْتِىَ أَحَدَكُمُ ٱلْمَوْتُ فَيَقُولَ رَبِّ لَوْلَآ أَخَّرْتَنِىٓ
إِلَىٰٓ أَجَلٍ قَرِيبٍ فَأَصَّدَّقَ وَأَكُن مِّنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿١٠﴾ وَلَن
يُؤَخِّرَ ٱللَّهُ نَفْسًا إِذَا جَآءَ أَجَلُهَا وَٱللَّهُ خَبِيرٌۢ بِمَا تَعْمَلُونَ ﴿١١﴾

## سُورَةُ التَّغَابُنِ

آياتها ١٨ — ترتيبها ٦٤

ወደ ግድግዳ የተጠጉ ግንዶችን ይመስላሉ[1] ። ጩኽትን ሁሉ በእነሱ ላይ ነው ብለው ያስባሉ ። እነርሱ ጠላቶች ናቸውና ተጠንቀቃቸው[2]። አላህ ይጋደላቸው[3]። ከእምነት) እንዴት ይመለሳሉ /ያፈገፍጋሉ/!።
5 ሙሐመድ ሆይ! ለእነሱም[4]፦ ኑ የአላህ መልእክተኛ ለእናንተ ምህረትን ይለምንላችኋል በተባሉ ጊዜ ራሶቻቸውን ያዞራቁ /ይነቀንቃሉ/(ለማፌዝ)። እነሱም ትዕቢተኞች ሆነው ሲሸሹ ታያቸዋለህ[5]።
6 ምህረትን[6] ብትለምንላቸውም ባትለምንላቸውም በእነሱ ላይ (ሁሉም) እኩል ነው ።[7] አላህ ለእነሱ በፍጹም አይምርም ።አላህ አመፀኛ[8] ህዝቦችን አይመራምና ።
7 እነሱ፦[9] ከአላህ መልዕክተኛ ዘንድ /አጠገብ/ ላሉት ሰዎች እስከሚበታተኑ ድረስ አትቀልቡ /አትስጡ/የሚሉ ናቸው ። የሰማያትና የምድር ድልቦችም የአላህ ናቸው ። ግን መናፍቃን አያውቁም ።
8 ወደ መዲና ብንመለስ አሸናፊው ወራዳውን በእርግጥ ከእርሷ ያወጣል ይላሉ[10]። አሸናፊነትም ለአላህ፣ ለመልክተኛውና ለምእምናን ነው ። ግን መናፍቃን አያውቁም ።
9 እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁ አላህን ከማስታወስ[11] አያታልሏችሁ /አያዘናጓችሁ/። ይህንንም የሚሰሩ[12] ሰዎች እነዚያ እነሱ ከሳሪዎች ናቸው ።
10 አንዳችሁንም ሞት ሳይመጣበትና፦ ጌታዬ ሆይ! እንድመጸውትና ከደጋጎቹም ሰዎች እንድሆን ጥቂት ጊዜ ብታቆየኝ ሮ እመኛለሁ ከማለቱ በፊት ከሰጠናችሁ ሲሳይ ለግሱ[13]።
11 ማንኛይቱንም ነፍስ (የሞት) ጊዜዋ በመጣባት ጊዜ አላህ በፍጹም አያቆያትም። አላህም በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው።[14]

---

1 ለይስሙላ በነብዩ አጠገብ ሲቀመጡ ምንም ስለማይጠቀሙና ስለማይረዱ ልክ እንደ እንጨት መሰላቸው ።
2 ምክንያቱም በአንተ ላይ የተሰማሩ የጠላቶችህ ሰላዮች ናቸውና።
3 አላህ ያጥፋቸው በሉ ማለትም ሊሆን ይችላል።
4 5ኛው አንቀጽ የወረደበት ምክንያት፦ አብደላህ ቢን ኡበይ፦ ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሂደህ የአላህን (عز وجل) ምህረት ቢጠይቁልህ ተብሎ ሲመከር አንገቱን እየወዘወዘ በማፌዙ ነው። (ሱዩጢ)
5 ምክኒያቱም እራሳቸዉን ትልቅ አድርገው ስለሚቆጥሩ ነው ።
6 6ኛው አንቀጽ የወረደበት ምክኒያት፦ በሱረቱ አት- ተውባ 80ኛ ቁጥር ላይ ያለው አንቀፅ ሲወርድና ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቢሆንም ከሰባ በላይ እጨምርለታለሁ በማለታቸው ይህ አንቀጽ ወረደና ቢጨመርለትም ምንም ጥቅም እንደሌለው የገለፀላቸው ። (ሱዩጢ)
7 በክህደታቸውና በኒፋቃቸው ላይ እስካሉ ድረስ ይህ ተግባርህ አይጠቅማቸዉም።
8 እንደ ሙናፊቆች ያሉት ።
9 አንቀጽ ፯ እና ፰ የወረዱበት ምክንያት፦
ዘይድ ኢብኑ አርቀም እንዳሉት ከሙናፊቆች የተወሰኑት አብረውን በነበሩበት ዘመቻ ላይ ሳለን አብደላህ ኢብኑ ዑበይ የሚባል የሙናፊቆች አለቃ ወደ መዲና ስንመለስ ክብር ያለው ክበረ ቢስን ከሀገሩ ያስወጣል ብሎ ሲናገር ስለሰማሁ ወዲያውኑ ለነብዩ (ﷺ) ሂጄ ነገርኳቸው ኢብኑ ዑበይ ግን አስጠርተው ሲጠይቁት ወላሂ አላልኩም በማለት ማለ በዚህ ጊዜ ዘመዶቼ ምን አስፈለገህ እና ነው ወደ ዚህ ችግር የገባኸው በማለት ወቀሱኝ እኔም ተመልሼ በቦታ አዝኘ እንቅልፍ አልወስድ ብሎኝ በመበሳጨት ላይ እያለሁ ጠዋቱኑ ነብዩ (ﷺ) አስጠሩኝ እና ፈገግ በማለት ደስ ይበላህ አላህ ምክንያትህን አውርዶላሃል እውነተኛነትህን አረጋግጦልሃል ብለዋል ።
10 ይህን ያለው አብዱላህ ብን ኡበይ የተባለው የሙናፊቆች አለቃ የነበረው ነው።
11 ኢስላማዊ ግዴታዎች አትዘንጋ ወይም ቁርአንን አትበል ማለት ሊሆን ይችላል ።
12 ለዱንያ ብለው ከአኼራ የሚዘናጉ ።
13 ከሰጠናችሁ ሲሳዮች ከፍላችሁ ስጡ ወይም ግዴታ የሆነባችሁን ዘካ ስጡ ማለት ነው ።
14 ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ
يُسَبِّحُ لِلَّهِ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ ۖ لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ ۖ
وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ ﴿١﴾ هُوَ الَّذِي خَلَقَكُمْ فَمِنكُمْ كَافِرٌ
وَمِنكُم مُّؤْمِنٌ ۚ وَاللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ ﴿٢﴾ خَلَقَ السَّمَاوَاتِ
وَالْأَرْضَ بِالْحَقِّ وَصَوَّرَكُمْ فَأَحْسَنَ صُوَرَكُمْ ۖ وَإِلَيْهِ الْمَصِيرُ ﴿٣﴾
يَعْلَمُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَيَعْلَمُ مَا تُسِرُّونَ وَمَا تُعْلِنُونَ ۚ وَاللَّهُ
عَلِيمٌ بِذَاتِ الصُّدُورِ ﴿٤﴾ أَلَمْ يَأْتِكُمْ نَبَأُ الَّذِينَ كَفَرُوا مِن قَبْلُ
فَذَاقُوا وَبَالَ أَمْرِهِمْ وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٥﴾ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُ كَانَت تَّأْتِيهِمْ
رُسُلُهُم بِالْبَيِّنَاتِ فَقَالُوا أَبَشَرٌ يَهْدُونَنَا فَكَفَرُوا وَتَوَلَّوا ۚ وَّاسْتَغْنَى
اللَّهُ ۚ وَاللَّهُ غَنِيٌّ حَمِيدٌ ﴿٦﴾ زَعَمَ الَّذِينَ كَفَرُوا أَن لَّن يُبْعَثُوا ۚ قُلْ بَلَىٰ وَرَبِّي
لَتُبْعَثُنَّ ثُمَّ لَتُنَبَّؤُنَّ بِمَا عَمِلْتُمْ ۚ وَذَٰلِكَ عَلَى اللَّهِ يَسِيرٌ ﴿٧﴾ فَآمِنُوا بِاللَّهِ
وَرَسُولِهِ وَالنُّورِ الَّذِي أَنزَلْنَا ۚ وَاللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ ﴿٨﴾ يَوْمَ
يَجْمَعُكُمْ لِيَوْمِ الْجَمْعِ ۖ ذَٰلِكَ يَوْمُ التَّغَابُنِ ۗ وَمَن يُؤْمِن بِاللَّهِ وَيَعْمَلْ
صَالِحًا يُكَفِّرْ عَنْهُ سَيِّئَاتِهِ وَيُدْخِلْهُ جَنَّاتٍ تَجْرِي مِن تَحْتِهَا
الْأَنْهَارُ خَالِدِينَ فِيهَا أَبَدًا ۚ ذَٰلِكَ الْفَوْزُ الْعَظِيمُ ﴿٩﴾

## 64 ኛው ሱራ (ሱረቱል አት-ተጋቡን) የመቆርጫው ምዕራፍ ነው ::[1] አንቀጾቹ 18 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህእና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 በሰማያት ውስጥም ሆነ በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ አላህን ያሞግሳል፤፡ ንግስናው የእርሱ ብቻ ነው። ምስጋናም ለእርሱ ብቻ ነው። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።.
2 እርሱ ያ የፈጠራችሁ ነው ። ከእናንተም መካከል ከሓዲ አለ። ከእናንተም መካከል አማኝ አለ። አላህም በምትሰሩት ሁሉ ተመልካች ነው ።
3 እርሱ ሰማያትንና ምድርን በእውነት ፈጠረ። ቀረፃችሁ። ቅርጻችሁንም አሳመረ። መመለሻችሁም ወደ እርሱ ብቻ ነው ።
4 በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለውን ሁሉ ያውቃል። የምትደብቁትንም ሆነ የምትገልጡትን ያውቃል። አላህ በልቦች ውስጥ ያለውን ሁሉ ዐዋቂ ነውና።
5 የእነዚያ ከአሁን በፊት የካዱትና የክህደታቸውን ቅጣት ቅመሱ የተባሉት ህዝቦች ወሬ አልመጣላችሁምን። ለእነሱም አሳማሚ ቅጣት አልለላቸው።
6 ይህ (ቅጣት) እርሱ መልእክተኞቻቸው በአስረጂዎች ይመጡባቸው ስለነበሩ፣ ሰዎችም ይመሩናልን? ስላሉና ስለካዱ፣ ከእምነት ስለ ዞሩም ነው። አላህ (ከእነሱ እምነት) ተብቃቃ። አላህ ተብቃቂና ምስጉን ነው።
7 ሙሐመድ ሆይ! እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች የማይቀሰቀሱ መሰላቸው። እንዴት አትቀሰቀሱም? በጌታዬ ይሁንብኝ ትቀሰቀሳላችሁ። ከዚያም ትፈፅሙት የነበረዉን ተግባራችሁን ትነገራላችሁ፣ ይህ (ተግባር) ለአላህ ቀላል ነው፣በላቸው ::
8 በአላህ፣ በመልዕክተኛውና በዚያ ባወረድነው ብርሃን እመኑም :: አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ዉስጥ አዋቂ ነዉና።
9 ይኸዉም ለመሰብሰቢያው ቀን የሚሰበስባችሁን ዕለት(አስታውሱ)[2]። ይህ ቀን የቁጭቱ ቀን ነው። በአላህ የሚያምንና መልካም ተግባር የፈፀመ ሰው ወንጀሉን ያብስለታል። ከስሮቿ ወንዞች የሚፈሱባት ጀነትም ለዘላለም ያስገባዋል። ይህ ታላቅ እድለኝነት ነው።

---

1-1 ከሚያምኑት ነገር ጋር የሚፃረርን የሚናገሩ መናፍቃን ሀሰተኞ መሆናቸውን፣ ከሃዲና ግፈኛ ሁሉን ነገር በራሱ ላይ አደገኛ አድርጎ እንደሚጠራጠር፣ በአፍና በቁመና ማማር ከመሸንገል መጠንቀቅ፤ እንዲሁም ወንጀል ላይ ከማዘውተር መጠንቀቅ አስፈላጊ መሆኑን፤
2 ትክክለኛ ክብር ለአሏህ (ﷻ) ለመልእክተኛው (ﷺ) እና ለአማኞች ብቻ መሆኑን፤
3.ለአስመሳዮች
4.የሙቶ መነሳትን ሐቅነት ማረጋገጥ፤
5. ሐጅ ማድረግ እየቻሉ የሚዘገዩ ሰዎች ተግባር ስህተት ስለመሆኑ፣ዘካን መስጠት ግዴታ መሆኑንና በሌሎችም የሰደቃ ዓይነቶች ላይ ግፊት ማሳደር አስፈላጊነትን እንማራለን።
[1] ምዕራፉ በመዲና ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ::

[2] ይህ ቀን የቂያማ ቀን ነው። በዚህ ቀንም ሥራ ከሰሪው፣ በዳይ ከተበዳይ፣ነብይ ከህዝቦቹ ጋር ሰዎች ከተፈጠሩበት አንስቶ እስከ ዐለም ፍፃሜ ያሉት በአንድ ሁነው የሚቀሰቀሱበት ቀን ነው ::

وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَكَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَآ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ
ٱلنَّارِ خَٰلِدِينَ فِيهَاۖ وَبِئۡسَ ٱلۡمَصِيرُ ١٠ مَآ أَصَابَ مِن
مُّصِيبَةٍ إِلَّا بِإِذۡنِ ٱللَّهِۗ وَمَن يُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ يَهۡدِ قَلۡبَهُۥۚ وَٱللَّهُ بِكُلِّ
شَيۡءٍ عَلِيمٞ ١١ وَأَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَۚ فَإِن
تَوَلَّيۡتُمۡ فَإِنَّمَا عَلَىٰ رَسُولِنَا ٱلۡبَلَٰغُ ٱلۡمُبِينُ ١٢ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ
إِلَّا هُوَۚ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلۡيَتَوَكَّلِ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ١٣ يَٰٓأَيُّهَا
ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِنَّ مِنۡ أَزۡوَٰجِكُمۡ وَأَوۡلَٰدِكُمۡ عَدُوّٗا
لَّكُمۡ فَٱحۡذَرُوهُمۡۚ وَإِن تَعۡفُواْ وَتَصۡفَحُواْ وَتَغۡفِرُواْ
فَإِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٌ ١٤ إِنَّمَآ أَمۡوَٰلُكُمۡ وَأَوۡلَٰدُكُمۡ
فِتۡنَةٞۚ وَٱللَّهُ عِندَهُۥٓ أَجۡرٌ عَظِيمٞ ١٥ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ مَا ٱسۡتَطَعۡتُمۡ
وَٱسۡمَعُواْ وَأَطِيعُواْ وَأَنفِقُواْ خَيۡرٗا لِّأَنفُسِكُمۡۗ وَمَن
يُوقَ شُحَّ نَفۡسِهِۦ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ١٦ إِن تُقۡرِضُواْ
ٱللَّهَ قَرۡضًا حَسَنٗا يُضَٰعِفۡهُ لَكُمۡ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡۚ وَٱللَّهُ شَكُورٌ
حَلِيمٌ ١٧ عَٰلِمُ ٱلۡغَيۡبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ١٨

ترتيبها ٦٥ — سُورَةُ الطَّلَاقِ — آياتها ١٢

10 እነዚያ በአላህ የካዱና በተአምሮቻችን
ያስተባበሉ የዝንታለም እሳት ባለቤቶች
ማለት እነሱ ናቸው። ጀሀነም መመለሻነቷ
ምን ይከፋ!
11 መከራ በአላህ ፈቃድ ቢሆን እንጂ
(ማንንም) አይነካም። በአላህ የሚያምን
ሰው አላህ ልቡን (ለትዕግስት)
ይመራዋል። አላህ ሁሉንም ነገር ዐዋቂ
ነው።
12 አላህን[1] ተገዙ ። መልዕክተኛውንም
ታዘዙ፤ ብትዞሩም (መልእክተኛውን
አትጎዱም ።) በመልዕክተኛውም ላይ
ያለበት ግልጽ ማድረስ ብቻ ነው።
13 አላህ ከእርሱ በቀር አምላክ የለም።
አማኞች በአላህ ይመኩ ።
14 እናንተ[2] ያመናችሁ ሆይ!
ከሚስቶቻችሁና ከልጆቻችሁ (ከአላህ
መንገድ በማስተጓጎል) ለእናንተ ጠላቶች
የሆኑ አሉ። ስለዚህ ተጠንቀቋቸው።
ይቅርታ ብታደርጉ፣ ብታልፏቸውም፣
ብትምሩዋቸውም፣ አላህ በጣም መሓሪና አዛኝ
ነው።
15 ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁ ለእናንተ
መፈተኛ ብቻ ናቸው። አላህም ከእርሱ
ዘንድ ታላቅ ምንዳ አለ።
16 አላህንም[3] የቻላችሁትን ያህል ፍቻት ።
ትዕዛዙን ስሙም ። ታዘዙም፤ ለግሱም፤
ለነፍሶቻችሁ መልካምን (ይሰጣችኋልና)፤
የነፍሱንም ንፍገት የሚጠበቅ ሰው እነዚያ
እነሱ ፍላጎታቸውን የሚያገኙ ናቸው ።
17 ለአላህ መልካም ብድርን ብታበድሩት
(ምንዳውን) ለእናንተ ይደራርበዋል።
ለእናንተም ይምራል። አላህ አመስጋኝና
ታጋሽ ነው ።
18 ስውሩንም ይፋውንም አዋቂ ኃያልና
ጥበበኛ ነው።

---

[1] ከሃዲዎች፡- ሙስሊሞች ትክክለኛ ቢሆኑ ኑሮ በዚህች ዐለምም ችግር ባላጋጠማቸው ነበር ስለ አሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው ።

[2] 14ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-

ሀ. በመካ አንዳንድ ሰዎች በሰለሙ ጊዜ ወይም ሰልሞ ሊሰደድ ሲል ቤተሰቦቹ ማለትም ሚስቱ ልጆቹ ያስቸግሩትና ያሳስቡት እንዲሁም እየወቀሱ ከስደት ያሳንፉት ስለነበርና ሙስሊም የሆነ ሰው የቤተሰብ ፍቅር ከአላህ ዲን እንዳያዘናጋው ለማስጠንቀቅ ነው። (ዋሂዲና ሱዩጢ።)

ለ. አውፍ ኢብኑ ማሊክ የተባለ ሷሃቢ ብዙ ንብረትና ቤተሰብ የነበረው ሲሆን ዘመቻ መሄድ ሲፈልግ ቤተሰቦቹ እየተላቀሱ ለማን ነው እኛን የምትተወን እያሉ ያሳንፉት ስለ ነበር ነውም ተብሏል። (ሱዩጢ።)

[3] 16ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት-፡

አላህን (ﷻ) በሚገባው ልክ ፍሩት የሚለው የቁርአን አንቀጽ ስትወርድ ሰዎች በኢባዳ ላይ ሲቆሙ እግራቸው እስከሚያብጥ፣ግንባራቸው እስከሚቆስል ለመተግበር ቢሞክሩም ሁኔታው አሳስቧቸው ያሉ ከአቅማቸው በላይ እንደማይገደዱ ለማሳወቅ ወረደ። (ሱዩጢ)

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ إِذَا طَلَّقۡتُمُ ٱلنِّسَآءَ فَطَلِّقُوهُنَّ لِعِدَّتِهِنَّ وَأَحۡصُواْ
ٱلۡعِدَّةَۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ رَبَّكُمۡۖ لَا تُخۡرِجُوهُنَّ مِنۢ بُيُوتِهِنَّ
وَلَا يَخۡرُجۡنَ إِلَّآ أَن يَأۡتِينَ بِفَٰحِشَةٖ مُّبَيِّنَةٖۚ وَتِلۡكَ حُدُودُ
ٱللَّهِۚ وَمَن يَتَعَدَّ حُدُودَ ٱللَّهِ فَقَدۡ ظَلَمَ نَفۡسَهُۥۚ لَا تَدۡرِي لَعَلَّ
ٱللَّهَ يُحۡدِثُ بَعۡدَ ذَٰلِكَ أَمۡرٗا ١ فَإِذَا بَلَغۡنَ أَجَلَهُنَّ فَأَمۡسِكُوهُنَّ
بِمَعۡرُوفٍ أَوۡ فَارِقُوهُنَّ بِمَعۡرُوفٖ وَأَشۡهِدُواْ ذَوَيۡ عَدۡلٖ مِّنكُمۡ
وَأَقِيمُواْ ٱلشَّهَٰدَةَ لِلَّهِۚ ذَٰلِكُمۡ يُوعَظُ بِهِۦ مَن كَانَ يُؤۡمِنُ
بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِۚ وَمَن يَتَّقِ ٱللَّهَ يَجۡعَل لَّهُۥ مَخۡرَجٗا ٢ وَيَرۡزُقۡهُ
مِنۡ حَيۡثُ لَا يَحۡتَسِبُۚ وَمَن يَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱللَّهِ فَهُوَ حَسۡبُهُۥٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ
بَٰلِغُ أَمۡرِهِۦۚ قَدۡ جَعَلَ ٱللَّهُ لِكُلِّ شَيۡءٖ قَدۡرٗا ٣ وَٱلَّٰٓـِٔي يَئِسۡنَ
مِنَ ٱلۡمَحِيضِ مِن نِّسَآئِكُمۡ إِنِ ٱرۡتَبۡتُمۡ فَعِدَّتُهُنَّ ثَلَٰثَةُ أَشۡهُرٖ
وَٱلَّٰٓـِٔي لَمۡ يَحِضۡنَۚ وَأُوْلَٰتُ ٱلۡأَحۡمَالِ أَجَلُهُنَّ أَن يَضَعۡنَ حَمۡلَهُنَّۚ
وَمَن يَتَّقِ ٱللَّهَ يَجۡعَل لَّهُۥ مِنۡ أَمۡرِهِۦ يُسۡرٗا ٤ ذَٰلِكَ أَمۡرُ ٱللَّهِ أَنزَلَهُۥٓ
إِلَيۡكُمۡۚ وَمَن يَتَّقِ ٱللَّهَ يُكَفِّرۡ عَنۡهُ سَيِّـَٔاتِهِۦ وَيُعۡظِمۡ لَهُۥٓ أَجۡرًا ٥

## 65 ኛው ምዕራፍ የፍች (ሱረቱ አጥ-ጠላቅ ነው::[1] የአንቀጾቹ ብዛት ፲፪ ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣምአዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 አንተ ነቢዩ ሆይ! ሴቶችን መፍታት ባሰባችሁ ጊዜ፤ ለዒዳቸው ፍቷቸው ፤ዓዳንም ቁጠሩ፤ ጌታችሁን አላህንም ፍሩ፤ ግልጽ የሆነችን ጠያፍ ካልሰሩ በስተቀር ከቤቶቻቸው አታውጡዋቸው፤ አይውጡም፤ ይህችም የአላህ ህግጋት ናት፤ የአላህንም ህግጋት የተላለፈ ሰው በእርግጥ ነፍሱን በደለ፤ ከዚህ ፍች በኋላ አላህ እንደገና የመማለስ ነገርን ምናልባት ያመጣ እንደሆነ አታውቅም።

2 ጊዜያቸውንም[2] ለመዳረስ በተቃረቡ ጊዜ በመልካም ያዙዋቸው፤ ወይም በመልካም ተለያዩዋቸው፤ ከናንተም ውስጥ ሁለት የትክክለኛነት ባለቤቶችን አስመስክሩ፤ ምስክርነትንም ለአላህ አስተካክሉ፤ ይሃችሁ በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን የሆነ ሰው ሁሉ በእርሱ ይገሠጽበታል፤ አላህንም የሚፈራ ሰው ለእርሱ መውጫን ያደርግለታል።

3 ከማያስበውም በኩል ሲሳይን ይሰጠዋል፣ በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው እርሱ በቂው ነው፤ አላህ ፈቃዱን አድራሽ ነው፤ አላህ ለነገሩ ሁሉ የተወሰነ ጊዜን በእርግጥ አድርጓል።

4 አሊያም[3] ከሴቶቻችሁ ከአደፍ ያቋረጡት (በዒዳቸው ህግ) ብትጠራጠሩ ዓዳቸው ሶስት ወር ነው፤ አለያም ገና አደፍን ያላዩት (ዒዳቸው እንደዚሁ ነው)፤ የእርግዝና ባለቤቶችም ጊዜያቸው እርጉዛቸውን መውለድ ነው፤ አላህንም የሚፈራ ሰው ከነገሩ ሁሉ ለእርሱ መግራትን ያደርግለታል።

5 ይህ የአላህ ፍርድ ነው፤ ወደ እናንተ አወረደው፣ አላህንም የሚፈራ ሰው ኃጢአቶቹን ከርሱ ይሰርይለታል:: ምንዳንም ለእርሱ ያተልቅለታል።

6 ከችሎታችሁ ከተቀመጣችሁበት ስፍራ አስቀምጧቸው:: በእነሱም ላይ ልታጣብቡ አትጉዷቸው፤ የእርግዝና ባለቤቶችም ቢሆኑ እርጉዛቸውን እስኪወልዱ ድረስ በእነሱ ላይ ቀልቡ፤ ለእናንተም (ልጆቻችሁን)

---

[1] ምዕራፉ በመዲና ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው::

[2] ከ2-3ያሉ አንቀፆች-የወረዱበት ምክንያት:- አውፍ ቢን ማሊክ ልጁ በጠላቶች ተማርካ ስለነበር እናቱ አዘነች:: ምን ይመክሩኛል? በማለት ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) ስለጠየቀ:- "ታገስ:: አላህን (ﷻ) ፍራ:: አንተም ሆንክ እናቱ ላሀውላ ወላቁወተ ኢላቢላህ የሚለውን አብዙ::" ብለውት ወደ ቤቱ ተመልሶ ለሚስቱ የተነገረውን ሲነግራት:- በጣም ጥሩ ነው የተባልነው፣ ብላ የተባሉትን ሲተገብሩ፤ ጠላት ተደናብሮ ባለበት፤ ልጃቸው አራት ሺህ ፍየሎችን ነድቶ ይዞ ስለ መጣ ነው:: (ዋሂዲ ና ሱዩጢ::)

[3] 4ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- በአልበቀራ 222ኛቁጥር ላይ ያለው አንቀፅ ሲወርድ ኻሊድ ቢን ዑመር ቢን አልጁምዐ ቢን ቀይስ አልአንሳሪ የተባለ ሰሃቢ ለነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) (የወር አበባ የማታይ አሮጊት፣ የወር አበባ ያላየች ህፃንና እርጉዝ ሴት እንዴት ሊሆን ነው ኢዳዋን የምትቆጥረው? በዚህ ህግ አልተጠቃለሉም እየተባለ በመዲና ሴቶች ዘንድ እየተወራ ነው) ብሎ ሲጠይቃቸው ነው ይህ አንቀጽ የወረደው :: (ዋሂዲ ና ሱዩጢ::)

أَسۡكِنُوهُنَّ مِنۡ حَيۡثُ سَكَنتُم مِّن وُجۡدِكُمۡ وَلَا تُضَآرُّوهُنَّ لِتُضَيِّقُواْ
عَلَيۡهِنَّۚ وَإِن كُنَّ أُوْلَٰتِ حَمۡلٖ فَأَنفِقُواْ عَلَيۡهِنَّ حَتَّىٰ يَضَعۡنَ حَمۡلَهُنَّۚ
فَإِنۡ أَرۡضَعۡنَ لَكُمۡ فَـَٔاتُوهُنَّ أُجُورَهُنَّ وَأۡتَمِرُواْ بَيۡنَكُم بِمَعۡرُوفٖۖ وَإِن
تَعَاسَرۡتُمۡ فَسَتُرۡضِعُ لَهُۥٓ أُخۡرَىٰ ٦ لِيُنفِقۡ ذُو سَعَةٖ مِّن سَعَتِهِۦۖ
وَمَن قُدِرَ عَلَيۡهِ رِزۡقُهُۥ فَلۡيُنفِقۡ مِمَّآ ءَاتَىٰهُ ٱللَّهُۚ لَا يُكَلِّفُ ٱللَّهُ نَفۡسًا
إِلَّا مَآ ءَاتَىٰهَاۚ سَيَجۡعَلُ ٱللَّهُ بَعۡدَ عُسۡرٖ يُسۡرٗا ٧ وَكَأَيِّن مِّن قَرۡيَةٍ
عَتَتۡ عَنۡ أَمۡرِ رَبِّهَا وَرُسُلِهِۦ فَحَاسَبۡنَٰهَا حِسَابٗا شَدِيدٗا وَعَذَّبۡنَٰهَا
عَذَابٗا نُّكۡرٗا ٨ فَذَاقَتۡ وَبَالَ أَمۡرِهَا وَكَانَ عَٰقِبَةُ أَمۡرِهَا خُسۡرًا ٩
أَعَدَّ ٱللَّهُ لَهُمۡ عَذَابٗا شَدِيدٗاۖ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ يَٰٓأُوْلِي ٱلۡأَلۡبَٰبِ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْۚ
قَدۡ أَنزَلَ ٱللَّهُ إِلَيۡكُمۡ ذِكۡرٗا ١٠ رَّسُولٗا يَتۡلُواْ عَلَيۡكُمۡ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ مُبَيِّنَٰتٖ
لِّيُخۡرِجَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ مِنَ ٱلظُّلُمَٰتِ إِلَى ٱلنُّورِۚ
وَمَن يُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ وَيَعۡمَلۡ صَٰلِحٗا يُدۡخِلۡهُ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا
ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدٗاۖ قَدۡ أَحۡسَنَ ٱللَّهُ لَهُۥ رِزۡقًا ١١ ٱللَّهُ ٱلَّذِي خَلَقَ
سَبۡعَ سَمَٰوَٰتٖ وَمِنَ ٱلۡأَرۡضِ مِثۡلَهُنَّ يَتَنَزَّلُ ٱلۡأَمۡرُ بَيۡنَهُنَّ لِتَعۡلَمُوٓاْ أَنَّ
ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ وَأَنَّ ٱللَّهَ قَدۡ أَحَاطَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عِلۡمَۢا ١٢

ቢያጠቡላችሁ ምንዳዎቻቸውን ስጧቸው። በመካከላችሁም በመልካም ነገር ተመካከሩ፤ ብትቸጋገሩም ለእርሱ ሌላ (ሴት) ታጠባለታለች ።

7 የችሎታ ባለቤት በችሎታው ልክ ይቀልብ፤ በእርሱም ላይ ሲሳዩ የተጠበበበት ሰው አላህ ከሰጠው ይስጥ ነፍስን የሰጣትን ያህል እንጅ አያስገድድም። አላህ ከችግር በኋላ ምቾትን በእርግጥ ያደርጋል ።

8 ከከተማም ከጌታዋ ትዕዛዝ ከመልክተኞቹም ያመጠች፣ ብርቱንም ቁጥጥር የተቆጣጠርናትና መጥፎንም ቅጣት የቀጣናት ብዙ ናት።

9 የነገርዋንም ቅጣት ቀመሰች። የነገርዋም መጨረሻ ኪሳራ ሆነ።

10 አላህ ለእነሱ ብርቱ ቅጣት አዘጋጀ፤ እናንተም የአእምሮ ባለ ቤቶች ሆይ፣ አላህን ፍሩ፤ አማኞች (ሆይ) ! አላህ ወደናንተ ግሣጼን በእርግጥ አወረደ፤ መልእክተኛን (ላከ)።

11 እነዚያን ያመኑትንና መልካሞችን የሰሩትን ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ያወጣ ዘንድ የአላህን አንቀጾች ገላጮች ሲሆኑ በናንተ ላይ የሚያነብላችሁን መልዕክልተኛ (ላከ)። በአላህም አንቀጾች የሚያምን፣ መልካምን ስራ የሚሰራም ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘለዓለም ዘውታሪዎች ሲሆን ያገባዋል፤ አላህ ለእርሱ ሲሳይን በእርግጥ አሳመረ።

12 አላህ ያ ሰባቱን ሰማያት የፈጠረ ነው፤ ከምድርም መሰላቸውን (ፈጥሯል)፤[1] በመካከላቸው ትእዛዙ ይወርዳል፤ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መሆኑን፣ አላህም በነገሩ ሁሉ በእውቀት ያካበበ መሆኑን ታውቁ ዘንድ ይህንን አሳወቃችሁ [2]፡

---

[1] ይህ አንቀፅ ሰማያትም ሆኑ ምድር ሰባት እንደሆኑ ከሚያመለክቱ አያሌ መረጃዎች አንዱ ነው። በሱረቱ አል ኢስራ ፬፬ኛው አንቀፅ በሱረቱል ሙልክ 3ኛ አንቀፅ በሱረቱ ኑህ 15 አንቀፅም የሰማይ ሰባትነት ተወስቷል። ከአንዱ ሰማይ እስከ ሁለት ሰማይ ከሁለት እስከ ሶስት ያለው እርቀት የአምስት መቶ አመት የሚያስኬድ መሆኑን የሰማይ ጉዟቸዉን በገለፁበት ሐዲስ ገልፀዋል ። ምድርን በተመለከተ ብዙ ልዩነት፤ ጭቅጭቅና ክርክር ያለበት ቢሆንም ኢብኑ ዐባስ (መሰላቸዉን) ማለት በቁጥርም ሆነ በአፈጣጠር በአጠቃላይ ሰማይን የሚመስል ማለት ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ በቁጥር ብቻ ነው እንጂ እርቀታቸዉን በተመለከተ እንደሽንኩርት ልጣጮች ድርብርብ ነው ያሉም አሉ ። ሰባት የመሆኑ ጉዳይ በቁርአን ባይገለፅም(በዚያ ስንዝር መሬትን የቀማ...) በሚለው ሐዲስና ነቢዩ ሙሳ (ጌታየ አንተን የምለምንበት ስጠኝ) ባሉበት ሐዲስ ተነግሯል። ስለዚህ ቁጥሩን ተቀብለን ሁኔታውን ለአላህ መስጠት ይኖርብናል ።

[2] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ።

1.ፍች መፈፀም ያለበት ለፍች በሚያበቃ ምክንያት ነው ፡ ፡ ፍችው መፈፀም ካለበት ሱናው ሴቷ ከወር አበባ እንደጠራችና የወሲብ ግንኙነት ሳይፈጸም በፊት መሆን ሲኖርበት፤የፍቺም ሱናው በአንድ መሆን እንዳለበት፤

2. ኢዳን መቁጠር ተገቢ ሲሆን፣ሴቷ በዝሙት ካልተጠረጠረች ወይም መጥፎ ባህሪያት ካላሳየች በስተቀር ከተፈታችበት ቤት ኢዳዋን ሳትጨርስ ማስወጣት ተገቢ አይደለም ። በሱናው መንገድ የተፈታችን ሴት ወደ ቀድሞ ኒካህ መመለስ የሚቻለው በኢዳዋ ዘመን ላይ እስካለች ሲሆን፣ መመለሱ ለማስቸገር ሳይሆን ባለፈው ተጸጽቶ ለመኖር መሆን አለበት ። በመፈታትም ሆነ በመመለስ ጊዜ ማስመስከር የግድ ነው ።

3.ኢዳህ ማለት ምን ማለት ነው;

ሀ- እርጉዝ ሳትሆን ባሏ የሞተባት አራት ወር ከአስር ቀን መቁጠር ያለባት መሆኑ

سُورَةُ التَّحْرِيمِ
ترتيبها ٦٦ — آياتها ١٢

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ لِمَ تُحَرِّمُ مَآ أَحَلَّ ٱللَّهُ لَكَ تَبْتَغِي مَرْضَاتَ أَزْوَٰجِكَ وَٱللَّهُ
غَفُورٌ رَّحِيمٌ ١ قَدْ فَرَضَ ٱللَّهُ لَكُمْ تَحِلَّةَ أَيْمَٰنِكُمْ وَٱللَّهُ مَوْلَىٰكُمْ
وَهُوَ ٱلْعَلِيمُ ٱلْحَكِيمُ ٢ وَإِذْ أَسَرَّ ٱلنَّبِيُّ إِلَىٰ بَعْضِ أَزْوَٰجِهِۦ حَدِيثًا
فَلَمَّا نَبَّأَتْ بِهِۦ وَأَظْهَرَهُ ٱللَّهُ عَلَيْهِ عَرَّفَ بَعْضَهُۥ وَأَعْرَضَ عَنۢ بَعْضٍ
فَلَمَّا نَبَّأَهَا بِهِۦ قَالَتْ مَنْ أَنۢبَأَكَ هَٰذَا قَالَ نَبَّأَنِيَ ٱلْعَلِيمُ ٱلْخَبِيرُ
٣ إِن تَتُوبَآ إِلَى ٱللَّهِ فَقَدْ صَغَتْ قُلُوبُكُمَا وَإِن تَظَٰهَرَا عَلَيْهِ
فَإِنَّ ٱللَّهَ هُوَ مَوْلَىٰهُ وَجِبْرِيلُ وَصَٰلِحُ ٱلْمُؤْمِنِينَ وَٱلْمَلَٰٓئِكَةُ
بَعْدَ ذَٰلِكَ ظَهِيرٌ ٤ عَسَىٰ رَبُّهُۥٓ إِن طَلَّقَكُنَّ أَن يُبْدِلَهُۥٓ أَزْوَٰجًا
خَيْرًا مِّنكُنَّ مُسْلِمَٰتٍ مُّؤْمِنَٰتٍ قَٰنِتَٰتٍ تَٰٓئِبَٰتٍ عَٰبِدَٰتٍ سَٰٓئِحَٰتٍ
ثَيِّبَٰتٍ وَأَبْكَارًا ٥ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ قُوٓا۟ أَنفُسَكُمْ وَأَهْلِيكُمْ
نَارًا وَقُودُهَا ٱلنَّاسُ وَٱلْحِجَارَةُ عَلَيْهَا مَلَٰٓئِكَةٌ غِلَاظٌ شِدَادٌ
لَّا يَعْصُونَ ٱللَّهَ مَآ أَمَرَهُمْ وَيَفْعَلُونَ مَا يُؤْمَرُونَ ٦ يَٰٓأَيُّهَا
ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لَا تَعْتَذِرُوا۟ ٱلْيَوْمَ إِنَّمَا تُجْزَوْنَ مَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ ٧

## 66 ኛው ምዕራፍ (ሱረቱ አት-ተህሪም) እርም የማድረግ ምዕራፍ ነው::[1] አንቀጾቹ 12 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 አንተ[2] ነቢዩ ሆይ! አላህ ለአንተ የፈቀደልህን ነገር ሚስቶችህ ማስወደድን የምትፈልግ ስትሆን (ባንተ ላይ) ለምን እርም ታደርጋለህ፤ አላህ እጅግ መሓሪና አዛኝ ነው።
2 አላህ ለእናንተ የመሓሎቻችሁን መፍቻ ደነገገላችሁ፤ አላህ ረዳታችሁ ነው:: እርሱም ዐዋቂና ጥበበኛው ነው።
3 ነቢዩ ከሚስቶቹ ወደ አንዷ ወሬን በመሰጠረች ጊዜ (አስታውስ)፤ እርሱንም በነገረችና አላህ እርሱን (ማውራቷን) ባሳወቀው ጊዜ ከፊሉን አስታወቀ፤ ከፊሉንም ተወ፤ በእርሱም ባወራት ጊዜ፡- ይህን ማን ነገረህ? አለች፤ አዋቂው፣ ውስጠ ዐዋቂው ነገረኝ አላት።
4 ወደ አላህ ብትመለሱ ልቦቻችሁ በእርግጥ ተዘንብለዋልና (ትስሰማላችሁ)። በእርሱ ላይ ብትረዳዱ ግን አላህ እና ጂብሪልም ከምእምናንም መልካሞቹ፣ እርሱ ረዳቶች ናቸው ከዚህም በኋላ መላዕክትቶች ረዳቶቹ ናቸው።
5 (ሁላችሁንም) ቢፈታችሁ ከናንተ የበለጡ ሚስቶችን እስላሞች፣ አማኞች፣ ታዛገሮች፣ ተጸጻቾች፣ (ለአላህ) ተገዢዎች፣ ጿሚዎች፣ ፈቶች፣ ደናግልም የሆኑትን ጌታው ሊለውጠው ይከጅላል።
6 እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ነፍሶቻችሁንና ቤተሰቦቻችሁን መቀጣጠያዋ ሰዎችና

ሰ- እርጉዝ ሆና ባሏ የሞተባት እሱ ከሞተ አስክትወልድ ብቻ መጠበቋ
ሐ- በህጻንነት ወይም በእርጅና ምክንያት የወር አበባ የማታይ ሴት ስትፈታ ሶስት ወራትን መቁጠር እንዳለባት ።
መ- የወር አበባ የምታይ ከሆነች ከተፈታችበት ጡሃራ ጀምሮ ሶስት ጠሃራ መቁጠር ያለባት መሆኑን ነው።
4.የፍቺ፣ የኢዳና የመመለስ ህግጋት ከአሏህ (ﷻ) መመሪያ የተሰጠባቸው እስላማዊ ህግጋት ናቸው ።
5.በፍች ዙሪያ የሴቷን ቀለብ በተመለከተ፤የመመለስ ዕድል ባለው መንገድ የተፈታች ሴት መኖሪያም ሆነ ቀለብ የወንዱ ግዴታ ነው ። ነገር ግን የመጨረሻ ፍች የተፈታች ሴት ቀለብም ሆነ መኖሪያ የሌላት ስትሆን ቀለብም ሆነ መኖሪያ የሚለው በራሱ በሰውየው አቅም የሚወሰን ነው ።

[1] ምዕራፉ በመዲና ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው::

[2] 1ኛው አንቀፅ-የወረደበት ምክንያት፡-
ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የልጅ እናታቸውን ማሪያን በአይሻ ቀን በሌላይቱ ሚስታቸው በሀፍሷ ቤት ይዘዋት ገብተው ሐፍሷ ስለአገኟቸው ተቆጥተው፡- ከሌሎች ሴቶች ቤት የማያደርጉትን እኔ ቤት ያደረጉት ስለናቁኝ ነው በማለት ሲያማርሩ፡- አይደለም ይህን ጉዳይ ለአኢሻህ አትንገሪያት። እሷም /ማርያም/ ከዛሬ በኋላ በእኔ ላይ እርም ናት ሲሏት፡- እሷ ሰራተኛ አይደለችም እንዴት ሀራም ትሆናለች ስትላቸው፡- በፍጹም ከዚህ በኋላ አልቀርባትም ባይሆን ለማንም አትንገሪ ብለዋት ሳለ ለአኢሻ ነገረቻቸው።
ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ይህንን ማድረጋቸውን በአኢሻ በኩል ሲሰሙ በዚህ ጊዜ ለአንድ ወር ወደ ሴቶቻቸው ላይቀርቡ ማሉና 29 ሌሊት ራቋቸው ። ከዚያም ይህ አንቀጽ ሁኔታው አግባብ እንዳልነበር ለማስተማር ይህ አንቀጽ ወረደ ። (ዋሂዲ እና ሱዩጢ ።)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ تُوبُوٓاْ إِلَى ٱللَّهِ تَوۡبَةٗ نَّصُوحًا عَسَىٰ رَبُّكُمۡ
أَن يُكَفِّرَ عَنكُمۡ سَيِّـَٔاتِكُمۡ وَيُدۡخِلَكُمۡ جَنَّـٰتٖ تَجۡرِي
مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ يَوۡمَ لَا يُخۡزِي ٱللَّهُ ٱلنَّبِيَّ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ
مَعَهُۥۖ نُورُهُمۡ يَسۡعَىٰ بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَبِأَيۡمَٰنِهِمۡ يَقُولُونَ رَبَّنَآ
أَتۡمِمۡ لَنَا نُورَنَا وَٱغۡفِرۡ لَنَآۖ إِنَّكَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ٨
يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ جَٰهِدِ ٱلۡكُفَّارَ وَٱلۡمُنَٰفِقِينَ وَٱغۡلُظۡ عَلَيۡهِمۡۚ
وَمَأۡوَىٰهُمۡ جَهَنَّمُۖ وَبِئۡسَ ٱلۡمَصِيرُ ٩ ضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلٗا
لِّلَّذِينَ كَفَرُواْ ٱمۡرَأَتَ نُوحٖ وَٱمۡرَأَتَ لُوطٖۖ كَانَتَا تَحۡتَ
عَبۡدَيۡنِ مِنۡ عِبَادِنَا صَٰلِحَيۡنِ فَخَانَتَاهُمَا فَلَمۡ يُغۡنِيَا عَنۡهُمَا
مِنَ ٱللَّهِ شَيۡـٔٗا وَقِيلَ ٱدۡخُلَا ٱلنَّارَ مَعَ ٱلدَّٰخِلِينَ ١٠
وَضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلٗا لِّلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱمۡرَأَتَ فِرۡعَوۡنَ إِذۡ
قَالَتۡ رَبِّ ٱبۡنِ لِي عِندَكَ بَيۡتٗا فِي ٱلۡجَنَّةِ وَنَجِّنِي مِن فِرۡعَوۡنَ
وَعَمَلِهِۦ وَنَجِّنِي مِنَ ٱلۡقَوۡمِ ٱلظَّـٰلِمِينَ ١١ وَمَرۡيَمَ ٱبۡنَتَ
عِمۡرَٰنَ ٱلَّتِيٓ أَحۡصَنَتۡ فَرۡجَهَا فَنَفَخۡنَا فِيهِ مِن رُّوحِنَا
وَصَدَّقَتۡ بِكَلِمَٰتِ رَبِّهَا وَكُتُبِهِۦ وَكَانَتۡ مِنَ ٱلۡقَٰنِتِينَ ١٢

ድንጊያዎች ከሆነች እሳት ጠብቁ፤ በእርሷ ላይ ጨካኝና ኃይለኛ የሆኑ መላእክት አሉ፤ አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጹም፤ የሚታዘዙትን ሁሉ ይሰራሉ።

(7) እናንተ የካዳችሁ ሆይ ዛሬ አታመካኙ፤ የምትመነዱት ያንን ትሰሩት የነበራችሁትን ብቻ ነው (ይባላሉ)።

(8) እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ንጹህ የሆነችን ጸጸት በመጸጸት ወደ አላህ ተመለሱ፤ ጌታችሁ ከእናንተ ኃጢአቶቻችሁን ሊሰርዝላችሁ፣ ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውንም ገነቶች ሊያስገባችሁ ይከጅላልና፤ አላህ ነቢዩን እነዚያንም ከእርሱ ጋር ያመኑትን በማያሳፍርበት ቀን ብርሃናቸው በፊቶቻቸውና በቀኞቻቸው የሚሮጥ ሲሆን፡- ጌታችን ሆይ! ብርሃናችንን ሙላልን፤ ለእኛ ምህረትም አድርግልን፤ አንተ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነህና ይላሉ።

(9) አንተ ነቢይ ሆይ! ከሓዲዎችንና መናፍቃንን ታገል፤ በእነሱም ላይ በርታ፤ መ ሪያቸውም ገሀነም ናት። ምን ትከፋም መመለሻ!

(10) አላህ ለእነዚያ ለካዱት ሰዎች የኑህን ሚስት እና የሉጥን ሚስት ምሳሌ አደረገ፤ ከባሮቻችን ከሆኑ ሁለት መልካም ባርያዎች ስር ነበሩ ከዱዋቸውም[1]፤ ከአላህም (ቅጣት ኑህና ሉጥ)ከሚስቶቻቸው ምንም አልገፈተሩላቸውም ከገቢዎችም ጋር እሳትን ግቡ ተባሉ።

(11) ለእነዚያ ለአመኑትም የፈርዖንን ሴት አላህ ምሳሌ አደረገ። ጌታዬ ሆይ! አንተ ዘንድ በገነት ውስጥ ለእኔ ቤትን ገንባልኝ፤ ከፈርዖንና ከስራውም አድነኝ፤ ከበደለኞች ህዝቦችም አድነኝ ባለች ጊዜ።

(12) የዒምራንን ልጅ መርየምንም ያችን ብልቷን የጠበቀችውን (ምሳሌ አደረገ)። በእርሷም ውስጥ ከመንፈሳችን ነፍፉን። በጌታዋ ቃላትና[2] በመጽሃፍቱም አረጋገጠች፤ ከታዛዦችም ነበረች[3]።

---

[1] የኑህ ሚስት ይህ ሰውየ እብድ ነው እያለች ለጠላቶቻቸው ትናገር እንደነበርና የሉጥ ሚስት ደግሞ አዳዲስ እንግዶች በመጡ ጊዜ ለግበረሰዶማውያን ትጠቁም እንደነበር በተፍሲር ምሁራን ዘንድ ተዘግቧል።

[2] ጅብሪል የነብዩ ዒሳን ማረገዝ ሊያበስራት በመጣ ጊዜ እኔ የጌታሽ መልዕክተኛ ነኝ ያለውን ቃል ማለት ነው ።

[3] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።
1.የነቢይነትን ሐቅነት ማረጋገጥ ፣
2.በአላህ (ﷻ) ዘንድ የነቢዩን ክብር ከፍተኛነትና ትልቅነት፣
3.በአላህ (ﷻ) ዘንድ የአቡበከርን ሲዲቅን ክብር ከፍተኛነት እንማራለን።
4. ሚስትንና ልጅን መንከባከብ እንደሚገባ፣ 5.ወንጀልን የሰራ ሁሉ በቶሎ አላህን (ﷻ) ይቅር መጠየቅ እንዳለበት፤
6. ከሃዲዎችን በጦር፡ ሙናፊቆችን በምላስ የመዋጋት ግዴታ፣
7. ከሃዲ በአኼራ በምንም አይነት ተጠቃሚ እንዳልሆነ፤
8.አማኝ በከሃዲ ዘመዱ ምክንያት በምንም እንደማይጐዳ እንማራለን ።

## 67 ኛው ምዕራፍ :- (ሱረቱ አል- ሙልክ) የንግሥና ምዕራፍ ነው::[1] አንቀጾቹ 30 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 ያ ንግሥና በእጁ የሆነው አምላክ ችሮታው በዛ:: እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው።

2 ያ የትኛችሁ ሥራው ይበልጥ ያማረ መሆኑን ሊሞክራችሁ ሞትንና ህይወትን የፈጠረ ነው። እርሱም አሸናፊና መሓሪ ነው።[2]

3 ያ ሰባቱን ሰማያት የተነባበሩ[3] ሆነው የፈጠረ ነው። በአልረሕማን አፈጣጠር ውስጥ ምንም /ቅንጣት ያህል /መዛነፍን /መቃረን/ መበላሸት/ አታይም። ዓይንህንም መልስ:: ከስንጥቆች አንዳችን ታያለህን?

4 ከዚያም ብዙ ጊዜ ዓይንህን መላልስ። ዓይንህ ተዋርዶ/ተናንሶ/፣ እርሱም የደከመ ሆ ወደ አንተ ይመለሳል።

5 ቅርቢቱን[4] ሰማይም በእርግጥ በመብራቶች /በከዋክብት/ አጌጥናት/:: ለሰይጣናትም መቀጥቀጫዎች አደረግናት[5]:: ለእነርሱም (ለሰይጣ ች) ተንቀልቃይ የእሳትን ቅጣት አዘጋጀንላቸው::

6 ለእነዚያም በጌታቸው ለካዱት የገሀነም ቅጣት አላቸው:: መመለሻይቱም (ገሀነም) ከፋች!

7 በውስጧ በተጣሉ ጊዜ እርሷ የምትፈላ ስትሆን ለእርሷ (እንደ አህያ) ማናፋትን ይሰማሉ::

8 ከቁጭቷ የተነሳ ልትቆራረጥ ትቀርባለች:: በውስጧ ጭፍሮች/ቡድኖች/ በተጣሉ ቁጥር ዘበኞቿ:- (ስለዚህ ቀን) አስፈራሪ(ነቢይ) አልመጣላችሁም ነበርን? በማለት ይጠይቋቸዋል።

9 አይደለም፣ በእርግጥ አስፈራሪ መጥቶልናል:: አስተባበልንም:: አላህም ምንንም አላወረደም:: እናንተ(አውርዷል ስትሉ)በትልቅ ስህተት ውስጥ እንጂ አይደላችሁም አልን ይላሉ።

10 የምንሰማ ወይም የምናስብ በነበርን ሮ የነዳጅ እሳት ጓዶች ባልሆን ነበር ይላሉ።

11 በኃጢአታቸውም ያምናሉ:: ለእሳት ጓዶችም (ከእዝነት) መራቅ ተገባቸው።

12 እነዚያ ጌታቸውን በሩቁ የሚፈሩ ለእነሱ ምህረትና ታላቅ ምንዳ አለላቸው።

سُورَةُ المُلْكِ

ترتيبها ٦٧ — آياتها ٣٠

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

تَبَٰرَكَ ٱلَّذِى بِيَدِهِ ٱلْمُلْكُ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ١ ٱلَّذِى خَلَقَ
ٱلْمَوْتَ وَٱلْحَيَوٰةَ لِيَبْلُوَكُمْ أَيُّكُمْ أَحْسَنُ عَمَلًا ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْغَفُورُ ٢
ٱلَّذِى خَلَقَ سَبْعَ سَمَٰوَٰتٍ طِبَاقًا ۖ مَّا تَرَىٰ فِى خَلْقِ ٱلرَّحْمَٰنِ مِن
تَفَٰوُتٍ ۖ فَٱرْجِعِ ٱلْبَصَرَ هَلْ تَرَىٰ مِن فُطُورٍ ٣ ثُمَّ ٱرْجِعِ ٱلْبَصَرَ كَرَّتَيْنِ
يَنقَلِبْ إِلَيْكَ ٱلْبَصَرُ خَاسِئًا وَهُوَ حَسِيرٌ ٤ وَلَقَدْ زَيَّنَّا ٱلسَّمَآءَ
ٱلدُّنْيَا بِمَصَٰبِيحَ وَجَعَلْنَٰهَا رُجُومًا لِّلشَّيَٰطِينِ ۖ وَأَعْتَدْنَا لَهُمْ عَذَابَ
ٱلسَّعِيرِ ٥ وَلِلَّذِينَ كَفَرُوا۟ بِرَبِّهِمْ عَذَابُ جَهَنَّمَ ۖ وَبِئْسَ ٱلْمَصِيرُ
٦ إِذَآ أُلْقُوا۟ فِيهَا سَمِعُوا۟ لَهَا شَهِيقًا وَهِىَ تَفُورُ ٧ تَكَادُ تَمَيَّزُ
مِنَ ٱلْغَيْظِ ۖ كُلَّمَآ أُلْقِىَ فِيهَا فَوْجٌ سَأَلَهُمْ خَزَنَتُهَآ أَلَمْ يَأْتِكُمْ نَذِيرٌ ٨
قَالُوا۟ بَلَىٰ قَدْ جَآءَنَا نَذِيرٌ فَكَذَّبْنَا وَقُلْنَا مَا نَزَّلَ ٱللَّهُ مِن شَىْءٍ إِنْ أَنتُمْ
إِلَّا فِى ضَلَٰلٍ كَبِيرٍ ٩ وَقَالُوا۟ لَوْ كُنَّا نَسْمَعُ أَوْ نَعْقِلُ مَا كُنَّا فِىٓ أَصْحَٰبِ
ٱلسَّعِيرِ ١٠ فَٱعْتَرَفُوا۟ بِذَنۢبِهِمْ فَسُحْقًا لِّأَصْحَٰبِ ٱلسَّعِيرِ ١١
إِنَّ ٱلَّذِينَ يَخْشَوْنَ رَبَّهُم بِٱلْغَيْبِ لَهُم مَّغْفِرَةٌ وَأَجْرٌ كَبِيرٌ ١٢

13 (ሰዎች[6] ሆይ!) ቃላችሁንም አመስጥ:: ወይም በእርሱ ጩሁ:: እርሱ በልቦች ውስጥ ያለን ሁሉ ዐዋቂ ነው።

14 የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀት ረቂቁ ውስጥ ዐዋቂው ሲሆን (ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን ?

15 እርሱ ያ ምድርን ለእናንተ የተገራች ያደረገላችሁ ነው:: በጋራዎቿና በመንገዶቿም ሂዱ:: ከሲሳዩም ብሉ:: (ኋላ) መመለሻችሁም ወደ እርሱ ብቻ ነው።

16 በሰማይ ውስጥ ያለን (ሰራዊት) በእናንተ ምድርን ቢያሰምጥባችሁ ወዲያውም እርሷ የምታረገርግ ብትሆን ትተማመናላችሁን? (አትፈሩምን?) ማስጠንቀቂያው እንዴት እንደሆነ ወደፊት ታውቃላችሁ ::

17 ወይም በሰማይ ውስጥ ያለን በእናንተ ላይ ጠጠርን ያዘለች ንፋስን ቢልክባችሁ ትተማመናላችሁን? አትፈሩምን?)

18 እነዚያ ከእናንተ በስተፊት የነበሩትም አስተባበሉ:: ጥላቻዬ እንዴት ነበር!

19 ከበላያቸው ሰልፍ ሰርተው ወዳሉ ወፎች

---

[1] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው::
[2] ሞት ማለት ሩህ/ነፍስ ከአካል መለየት ሲሆን ህይወት ማለት ነፍስ ከአካል ጋር መቆራኘት ነው::
[3] አንዱ በአንዱ ላይ ::
[4] ቀታዳ እንደሚሉት አላህ ከዋክብትን የፈጠረው ለሶስት ምክንያት ነው :: አንዱ ሰማይን ለማስጌጥ ሲሆን በዚህ አንቀጽ ተገልጿል:: ሁለተኛው ጥቅም በቀጣዩ አንቀጽ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ሦስተኛው ጥቅም ጊዜያትን ለመቁጠር አገልግሎት ስለሚውሉ ነው ::
[5] ይህ ሁለተኛው ጥቅም ነው ::

[6] 13ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት :- የመካ ከሃዲዎች እርስ በራሳቸው:- ድምጻችሁን ዝቅ አድርጋችሁ ተነጋገሩ:: የሙሐመድ ጌታ እንዳይሰማችሁ ይሉ ስለነበር ነው :: (ዋሂዲ::)

وَأَسِرُّواْ قَوۡلَكُمۡ أَوِ ٱجۡهَرُواْ بِهِۦٓۖ إِنَّهُۥ عَلِيمُۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ١٣ أَلَا
يَعۡلَمُ مَنۡ خَلَقَ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلۡخَبِيرُ ١٤ هُوَ ٱلَّذِي جَعَلَ لَكُمُ
ٱلۡأَرۡضَ ذَلُولٗا فَٱمۡشُواْ فِي مَنَاكِبِهَا وَكُلُواْ مِن رِّزۡقِهِۦۖ وَإِلَيۡهِ ٱلنُّشُورُ
١٥ ءَأَمِنتُم مَّن فِي ٱلسَّمَآءِ أَن يَخۡسِفَ بِكُمُ ٱلۡأَرۡضَ فَإِذَا هِيَ
تَمُورُ ١٦ أَمۡ أَمِنتُم مَّن فِي ٱلسَّمَآءِ أَن يُرۡسِلَ عَلَيۡكُمۡ حَاصِبٗاۖ
فَسَتَعۡلَمُونَ كَيۡفَ نَذِيرِ ١٧ وَلَقَدۡ كَذَّبَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡ فَكَيۡفَ
كَانَ نَكِيرِ ١٨ أَوَلَمۡ يَرَوۡاْ إِلَى ٱلطَّيۡرِ فَوۡقَهُمۡ صَٰٓفَّٰتٖ وَيَقۡبِضۡنَۚ مَا
يُمۡسِكُهُنَّ إِلَّا ٱلرَّحۡمَٰنُۚ إِنَّهُۥ بِكُلِّ شَيۡءِۭ بَصِيرٌ ١٩ أَمَّنۡ هَٰذَا ٱلَّذِي
هُوَ جُندٞ لَّكُمۡ يَنصُرُكُم مِّن دُونِ ٱلرَّحۡمَٰنِۚ إِنِ ٱلۡكَٰفِرُونَ إِلَّا فِي غُرُورٍ
٢٠ أَمَّنۡ هَٰذَا ٱلَّذِي يَرۡزُقُكُمۡ إِنۡ أَمۡسَكَ رِزۡقَهُۥۚ بَل لَّجُّواْ فِي عُتُوّٖ
وَنُفُورٍ ٢١ أَفَمَن يَمۡشِي مُكِبًّا عَلَىٰ وَجۡهِهِۦٓ أَهۡدَىٰٓ أَمَّن يَمۡشِي سَوِيًّا
عَلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ ٢٢ قُلۡ هُوَ ٱلَّذِيٓ أَنشَأَكُمۡ وَجَعَلَ لَكُمُ ٱلسَّمۡعَ
وَٱلۡأَبۡصَٰرَ وَٱلۡأَفۡـِٔدَةَۖ قَلِيلٗا مَّا تَشۡكُرُونَ ٢٣ قُلۡ هُوَ ٱلَّذِي ذَرَأَكُمۡ
فِي ٱلۡأَرۡضِ وَإِلَيۡهِ تُحۡشَرُونَ ٢٤ وَيَقُولُونَ مَتَىٰ هَٰذَا ٱلۡوَعۡدُ إِن كُنتُمۡ
صَٰدِقِينَ ٢٥ قُلۡ إِنَّمَا ٱلۡعِلۡمُ عِندَ ٱللَّهِ وَإِنَّمَآ أَنَا۠ نَذِيرٞ مُّبِينٞ ٢٦

አይመለከቱምን? ክንፎቻቸዉን ያጥፋሉ:: ከአልረህማን ሌላ የሚይዛቸው የለም:: እርሱ ሁሉን ነገር አዋቂ ነው::
20 በእውነት ያ እርሱ ከአልረህማን ሌላ የሚረዳችሁ ለእናንተ የሆነ ሰራዊት ማነው? ከሓዲዎች በመታለል ውስጥ እንጂ በሌላ ላይ አይደሉም::
21 ወይም ሲሳዩን ቢይዝባችሁ ያ ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማነው ? በእውነት እነርሱ በሞገድና በመደንበር ውስጥ ቸኩ /ፀኑ/::
22 በፊቱ ላይ ተደፍቶ የሚሄድ ሰው ይበልጥ የተቀና ነውን ? ወይስ በቀጥተኛ መንገድ ላይ ተስተካክሎ የሚሄድ?
23 እርሱ አላህ ያ የፈጠራችሁ፣ ለእናንተም መስሚያና ማያዎችን፣ ልቦችንም ያደረገላችሁ ነው:: ጥቂትንም አታመሰግኑምን በላቸው::
24 እርሱ ያ በምድር ላይ የበተናችሁ ነው:: ወደ እርሱም ትሰበሰባላችሁ በላቸው::
25 እውነተኞችም እንደሆናችሁ ይህ ቀጠሮ መቼ ነው ተፈፃሚ የሚሆነው ይላሉ::
26 እውቀቱ ከአላህ ዘንድ ብቻ ነው:: እኔ ግልጽ አስፈራሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው::
27 (ቅጣቱን) ቅርብ ሆ ባዩትም ጊዜ የእነዚያ የካዱት ሰዎች ፊቶች ይከፋሉ:: ይህ ያ በእርሱ ትከራከሩበት የነበራችሁት ነው ይባላሉም::
28 አያችሁን? (እስኪ ንግሩኝ?) አላህ ቢገድለኝ ከእኔ ጋር ያሉትንም (እንደዚሁ) ወይም (በማቆየት) ቢያዝንልን ከሓዲዎችን ከአሳማሚ ቅጣት የሚያድን ማን ነው? በላቸው::
29 እርሱ (እመኑበት የምላችሁ)አልረሕማን ነው:: (እኛ) በእርሱ አመንን:: በእርሱም ላይ ተጠጋን:: ወደ ፊትም በግልጽ መሳሳት ውስጥ የሆነው እርሱ ማን እንደሆነ በእርግጥ ታውቃላችሁ በላቸው::
30 አያችሁን (እስኪ ነግሩኝ?) ውሃችሁ ሠራጊ ቢሆን /ወደ መሬት ቢሰርግ/ ፈሳሽን ውሃ የሚያመጣላችሁ ማን ነው? በላቸው:: (አላህ የዓለማት ጌታ ያመጣዋል )[1]::

---

[1] **ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ::**
**1.** የአላህን (عَزَّ وَجَلَّ) ጌትነት ማረጋገጥ፣ **2.** የከዋክብትን የመፈጠር ምክንያትና ጥቅም፤ **3.** የሞቶ መነሳትን ሐቅነት ማረጋገጥ፣ **4.** ነቢያትን ማስተባበል ለከፍተኛ ቅጣት እንደሚጋብዝ:: **5.**የገሀነም ሰዎች የሚጋሩት አባባል፣ ዛሬ ያሉት ከሃዲዎች ምንነትና ኋላ ቀርነት፤
**6.**ከሃዲዎች አይሰሙም አያስቡም መባላቸው፣
**7.** የአላህ (عَزَّ وَجَلَّ) ብቸኛ ባለስልጣንነት፣ ይህን መግለጽ፣ ማወደስና በተሟላ መልኩ ማሞገስ ተገቢ መሆኑን
**8.** አላህ (عَزَّ وَجَلَّ) ሁሉን ነገር መፍጠር የሚችልና ሀቅ መሆኑን፤ **9.** ሞትና ሕይወትን የፈጠረበት ምክንያት የሰውን ልጅ ለመፈተን መሆኑን፤ **10.** መልካም ሥራ ማለት ለአላህ (عَزَّ وَجَلَّ) በፍጹምነት የተገበረ መሆኑን፤
**11.** አላህ (عَزَّ وَجَلَّ) ሰማይንና ምድርን ፈጥሮ አንድም ጉድለት አለመ የቱ ለመኖሩ የላቀ ማስረጃ መሆኑን፤
**12.** በገይብ ማመን በኢስላም ያለው ክብር፣
**13.** ርዝቅን ለመፈለግም ሆነ ለልዩ ልዩ ጥቅም በምድር ላይ መጓዝ ተገቢ ስለመሆኑና አላህ (عَزَّ وَجَلَّ) ምድርን ለዚህ ተስማሚ አድርጎ መፍጠሩን፣ **14.** የሙቶ መነሳትን ሐቅነትን በተለያዩ ማስረጃዎች ማረጋገጥ፣
**15.** የአላህ (عَزَّ وَجَلَّ) እውቀት በሚታዩና በሚሰሙ ነገሮች ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በልብ የተደበቀውን ሁሉ የሚያውቅ መሆኑን፤ **16.** ይህችን ምድር የተረጋጋች ያደረገ ጌታ አላህ (عَزَّ وَجَلَّ) ሲፈልግ ሊያንቀጠቅጣትም እንደሚችል፤ **17.** አላህ (عَزَّ وَجَلَّ) በሰማይ ላይ ያለ መሆኑን እንማራለን **18.** ከሃዲዎች ሁልጊዜም በመኮፈስ የሚኖሩ መሆናቸውን፣ **19.**ከሃዲ የተሳሳተና መንገድ የለቀቀ መሆኑን፣ **20.**አላህን (عَزَّ وَجَلَّ) ማመስገን እንዳለብን፤ **21.** አላህ (عَزَّ وَجَلَّ) የሰውን ልጅ በጥሩ አቋም እንደፈጠረው፣ አካሎችን እንደለገሰውና ሊያመሰግነው እንደሚገባ፤ **22.** አላህ (عَزَّ وَجَلَّ) ሰዎች በዚህች ምድር ላይ ፈጥሮ ሪዝቃቸውን በታትኖ በየድርሻቸው ከኖሩ በኋላ ወደ እሱው እንደሚሰበስባቸው፤ **23.** እነዚያ በዚህች ዓለም ሲኖሩ በሞቶ መነሳት ሲያፌዙ የኖሩ ሰዎች የቂያማን እውነት ሲመለከቱ ፊታቸው ከሰል እንደሚመስል፤ **24.** አላህ (عَزَّ وَجَلَّ) ከሃዲዎች እንደሚፈልጉትና እንደሚመኙት አማኞችን ቢያጠፋቸው ለከሃዲዎች ምንም አይነት ፋይዳ እንደሌለው፤ **25.** አማኝ የሆነ ሰው በየትኛውም አጋጣሚ ላይ ምንነቱን በይፋ ማንፀባረቅና አላህን (عَزَّ وَجَلَّ) ማመስገን እንዳለብን፤ **26.** ውሃ ሰዎች ከተለገሱት ዋና ዋና ፀጋዎች አንዱ መሆኑን፤ ይህንን ፀጋ የለገሰዉን አላህን (عَزَّ وَجَلَّ) ማመስገን እንደሚገባው፤
**27.**የአላህን (عَزَّ وَجَلَّ) ሕግ ለማያከብሩ ሰዎች ሁሉ ከዚህ

## 68 ኛው ምዕራፍ:- (ሱረቱ አል-ቀለም/የቀለም ምዕራፍ ነው፡፡[1] አንቀጾቹ 52 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 (ኑን)[2] በብዕር፣ በዚያም በሚጽፉት እምላለሁ።
2 (ሙሐመድ ሆይ!) አንተ በጌታህ ጸጋ የተጎናጸፍክ ስትሆን ዕብድ አይደለህም።[3]
3 ለአንተም (ከጌታህ) የማይቋረጥ ምንዳ ዋጋ በእርግጥ አልለህ።
4 አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ።[4]

فَلَمَّا رَأَوْهُ زُلْفَةً سِيٓـَٔتْ وُجُوهُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ وَقِيلَ هَٰذَا ٱلَّذِى
كُنتُم بِهِۦ تَدَّعُونَ ﴿٢٧﴾ قُلْ أَرَءَيْتُمْ إِنْ أَهْلَكَنِىَ ٱللَّهُ وَمَن مَّعِىَ
أَوْ رَحِمَنَا فَمَن يُجِيرُ ٱلْكَٰفِرِينَ مِنْ عَذَابٍ أَلِيمٍ ﴿٢٨﴾ قُلْ هُوَ
ٱلرَّحْمَٰنُ ءَامَنَّا بِهِۦ وَعَلَيْهِ تَوَكَّلْنَا ۖ فَسَتَعْلَمُونَ مَنْ هُوَ فِى ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ
﴿٢٩﴾ قُلْ أَرَءَيْتُمْ إِنْ أَصْبَحَ مَآؤُكُمْ غَوْرًا فَمَن يَأْتِيكُم بِمَآءٍ مَّعِينٍۭ ﴿٣٠﴾

سُورَةُ القَلَمِ
ترتيبها ٦٨ — آياتها ٥٢

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

نٓ ۚ وَٱلْقَلَمِ وَمَا يَسْطُرُونَ ﴿١﴾ مَآ أَنتَ بِنِعْمَةِ رَبِّكَ بِمَجْنُونٍ ﴿٢﴾
وَإِنَّ لَكَ لَأَجْرًا غَيْرَ مَمْنُونٍ ﴿٣﴾ وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ ﴿٤﴾
فَسَتُبْصِرُ وَيُبْصِرُونَ ﴿٥﴾ بِأَييِّكُمُ ٱلْمَفْتُونُ ﴿٦﴾ إِنَّ رَبَّكَ هُوَ
أَعْلَمُ بِمَن ضَلَّ عَن سَبِيلِهِۦ وَهُوَ أَعْلَمُ بِٱلْمُهْتَدِينَ ﴿٧﴾ فَلَا تُطِعِ
ٱلْمُكَذِّبِينَ ﴿٨﴾ وَدُّوا۟ لَوْ تُدْهِنُ فَيُدْهِنُونَ ﴿٩﴾ وَلَا تُطِعْ كُلَّ
حَلَّافٍ مَّهِينٍ ﴿١٠﴾ هَمَّازٍ مَّشَّآءٍۭ بِنَمِيمٍ ﴿١١﴾ مَّنَّاعٍ لِّلْخَيْرِ مُعْتَدٍ
أَثِيمٍ ﴿١٢﴾ عُتُلٍّۭ بَعْدَ ذَٰلِكَ زَنِيمٍ ﴿١٣﴾ أَن كَانَ ذَا مَالٍ وَبَنِينَ
﴿١٤﴾ إِذَا تُتْلَىٰ عَلَيْهِ ءَايَٰتُنَا قَالَ أَسَٰطِيرُ ٱلْأَوَّلِينَ ﴿١٥﴾

5 6 ወደፊትም ታያለህ፤ ያያሉም። ዕብደት በማንኛችሁ እንዳለ።
7 ጌታህ እርሱ ከመንገዱ የተሳሳተውን ሰው ዓዋቂ ነው። እርሱም ተመሪዎችን ዐዋቂ ነው።
8 ለአስተባባዮችም አትታዘዝ።
9 ብትመሳሰላቸውና ቢመሳሰሉህ ተመኙ፡፡
10 - 13 መሓለኛን፤ ወራዳን፤ ሰውን አነዋሪ፤ ነገር አሳባቂን፤ለበጎ ነገር በጣም ከልካይን፤ ወሰን አላፊን፤ ኃጢአተኛን፤ ልበ ደረቅን ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ የዘሙት ልጅን /ዲቃላን/ ሰው ሁሉ አትታዘዝ።[5]
14 የገንዘብና የልጆች ባለቤት በመሆኑ (ያስተባብላል)።
15 በእርሱ ላይ አንቀጾቻችን በሚነበቡ ጊዜ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ተረቶች ናቸው ይላል።
16 በአፍንጫው ላይ በእርግጥ (የሚነወርበት) ምልክት እናደርግበታለን።
17 እኛ የአትክልቲቱን[6] ባለቤቶች ማልደው

---

ተግባራቸው እንዲቆጠቡ ታሪክን በማጣቀስ ማስጠንቀቅ፣ **28.** እያንዳንዳችን ቀደም ሲሉ በጠፉ ሰዎች ታሪክ መማር እንዳለብን ማስታወስ፣ **29.**ከአላህ (ﷻ) ታምራት መካከል ችሎ ውን ቁልጭ አድርገው ከሚያሳዩን አያሌ ክስተቶች መካከል በራሪዎች መብረራቸውና በሱ ጥበቃ ብቻ በአየር ላይ መንሳፈፋቸው መሆኑን፣ **30.** ድል ከአላህ (ﷻ) ሌላ ይገኛል ማለት ቂልነት መሆኑን፤ **31.** መስጠትም ሆነ መንሳት የአላህ (ﷻ) ብቻ ስልጣን መሆኑን፤ **32.**አማኝ በቀጥተኛው መንገድ ላይ ቀጥ ብሎ በትክክል እንደሚጓዝ ሲመስል ከሃዲ ግን አንገቱን አቀርቅሮ እንደሚደናቀፍ መመሰሉ፤ **33.** ከሃዲዎች ለነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የነበራቸው ጥላቻ ምን ይመስል እንደነበር፣ **37.** በአላህ (ﷻ) ያመነ ሰው በአላህ (ﷻ) ላይ መመካት እንዳለበት፣ ሐቅን ለማሳወቅና ሐሰትን ለማክሸፈ መከራከር ተገቢ ስለ መሆኑ እንማራለን ፡፡

[1] ሱረቱአል-ቀለም ከሱረቱ ኢቅራእ በኋላና ከሱረተ-አል-ሙዘሚል በፊት በ28ኛነት በመካ የወረደ ሱራ ነው፥፥

[2] -ይህ ምዕራፍ በእነዚህ መሰል ፊደሎች ከሚጀመሩ የቁርአን ሀያ ዘጠኝ ምዕራፎች አንዱ ነው፡፡ እነሱም፡- ከሁለቱ አንጋፋ ከሆኑትና በመዲና ከወረዱት የላሚ ምዕራፍና ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ በስተቀር ሌሎች በእንዲህ አይነት ፊደላት የተጀመሩ ሁሉ በሙሉ በመካ የወረዱ ምዕራፎች ናቸው ፡፡ ይህም ሁኔታ የሚያሳየው የመካ ሰዎች በእንዲህ ያለ የአነጋገር ዜይቤ ቀደም ሲልም ይጠቀሙ እንደነበር ነው፡፡ እነዚሁም ሱራዎች ባለ አንድ ፊደል፣ባለ ሁለት ፊደል፣ ባለ ሶስት ፊደላት፣ ባለ አራትና ባለ አምስት ፊደላት ተብለው ይከፈላሉ ፡፡ እነዚህም የቁርአን ሱራዎች የተጀመረባቸው ፊደላት አስራ አራት ፊደላት ናቸው ፡፡ ይህም የዐረበኛውን ፊደል ጠቅላላ ብዛት የ28ቱን ፊደላት ግማሽ ቁጥር ይዟል ማለት ነው፡፡ ትርጉማቸዉን በተመለከተ ደግሞ የተፍሲር ሙሁራን በእነዚህ ዙሪያ ከሀያ በላይ የሆኑ አስተያቶችን የሰጡ ሲሆን፤ በብዙዎች ዘንድ የሚመረጠውና በብዙ ዐሊሞች ዘንድ ድጋፍ ያገኘው የእነዚህን ፊደላት ትክክለኛውን መልዕክት ማወቅ እንደማይቻልና ሆኖም ቁርአን ከአላህ (ﷻ) የወረደ መሆኑን ለማሳየት ነው የሚለዉን አባባል የመረጡ በመሆኑ እኔም ይህንኑ መርጫለሁ ፡፡ በየምዕራፎች መግቢያ ላይ ይህን አባባል መደጋገሙ አስፈላጊ ስለ ማይሆን ውድ አንባቢያን ልብ እንዲሉት በቅድሚያ ማሳሰብ አፈልጋለሁ፡፡

[3] ከምዕራፉ 2ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- መኮች ነቢዩ ሙሐመድን እንደ እብድ ይቆጥሯቸው ስለ ነበር ነው፡፡ (ሱዩጢ፡፡)

[4] የነቢዩ ሙሐመድ ስብእና በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አቻ የማይገኝለት ድንቅ ስብእና መሆኑን በማስረገጥ አላህ የሰጠው ምስክርነት በዚህ አንቀጽ ተመልክቷል። እናታችን አኢሻ የነብዩን ባህሪ ምን ይመስል እንደነበር ተጠይቀው ባህሪያቸው ቁርአን ነበር ብለዋል፡፡

[5] በነዚህ አናቅጽት እኩይ ባህሪው የተገለጸው ስብእና የነቢዩ ሙሐመድን ተልእኮ ለማደናቀፍ ብርቱ ጥረት ያደረገ ሲሆን በየዘመናቱም ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው እኩያን እስልምናን ለማጥቃት መሰሪ ተግባር ሲፈጽሙ ይስተዋላሉ፡፡

[6] ይህች አትክልት ከሰነዓ ከተማ ራቅ ብላ የምትገኝ ቦታ ላይ የነበረችና ባለቤቷ የአላህን ሀቅ በአግባቡ

سَنَسِمُهُۥ عَلَى ٱلۡخُرۡطُومِ ﴿١٦﴾ إِنَّا بَلَوۡنَٰهُمۡ كَمَا بَلَوۡنَآ أَصۡحَٰبَ ٱلۡجَنَّةِ إِذۡ أَقۡسَمُواْ
لَيَصۡرِمُنَّهَا مُصۡبِحِينَ ﴿١٧﴾ وَلَا يَسۡتَثۡنُونَ ﴿١٨﴾ فَطَافَ عَلَيۡهَا طَآئِفٞ مِّن رَّبِّكَ
وَهُمۡ نَآئِمُونَ ﴿١٩﴾ فَأَصۡبَحَتۡ كَٱلصَّرِيمِ ﴿٢٠﴾ فَتَنَادَوۡاْ مُصۡبِحِينَ ﴿٢١﴾ أَنِ
ٱغۡدُواْ عَلَىٰ حَرۡثِكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰرِمِينَ ﴿٢٢﴾ فَٱنطَلَقُواْ وَهُمۡ يَتَخَٰفَتُونَ ﴿٢٣﴾
أَن لَّا يَدۡخُلَنَّهَا ٱلۡيَوۡمَ عَلَيۡكُم مِّسۡكِينٞ ﴿٢٤﴾ وَغَدَوۡاْ عَلَىٰ حَرۡدٖ قَٰدِرِينَ ﴿٢٥﴾ فَلَمَّا
رَأَوۡهَا قَالُوٓاْ إِنَّا لَضَآلُّونَ ﴿٢٦﴾ بَلۡ نَحۡنُ مَحۡرُومُونَ ﴿٢٧﴾ قَالَ أَوۡسَطُهُمۡ أَلَمۡ أَقُل
لَّكُمۡ لَوۡلَا تُسَبِّحُونَ ﴿٢٨﴾ قَالُواْ سُبۡحَٰنَ رَبِّنَآ إِنَّا كُنَّا ظَٰلِمِينَ ﴿٢٩﴾ فَأَقۡبَلَ
بَعۡضُهُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٖ يَتَلَٰوَمُونَ ﴿٣٠﴾ قَالُواْ يَٰوَيۡلَنَآ إِنَّا كُنَّا طَٰغِينَ ﴿٣١﴾ عَسَىٰ
رَبُّنَآ أَن يُبۡدِلَنَا خَيۡرٗا مِّنۡهَآ إِنَّآ إِلَىٰ رَبِّنَا رَٰغِبُونَ ﴿٣٢﴾ كَذَٰلِكَ ٱلۡعَذَابُۖ وَلَعَذَابُ
ٱلۡأٓخِرَةِ أَكۡبَرُۚ لَوۡ كَانُواْ يَعۡلَمُونَ ﴿٣٣﴾ إِنَّ لِلۡمُتَّقِينَ عِندَ رَبِّهِمۡ جَنَّٰتِ ٱلنَّعِيمِ
﴿٣٤﴾ أَفَنَجۡعَلُ ٱلۡمُسۡلِمِينَ كَٱلۡمُجۡرِمِينَ ﴿٣٥﴾ مَا لَكُمۡ كَيۡفَ تَحۡكُمُونَ ﴿٣٦﴾ أَمۡ
لَكُمۡ كِتَٰبٞ فِيهِ تَدۡرُسُونَ ﴿٣٧﴾ إِنَّ لَكُمۡ فِيهِ لَمَا تَخَيَّرُونَ ﴿٣٨﴾ أَمۡ لَكُمۡ أَيۡمَٰنٌ
عَلَيۡنَا بَٰلِغَةٌ إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ إِنَّ لَكُمۡ لَمَا تَحۡكُمُونَ ﴿٣٩﴾ سَلۡهُمۡ أَيُّهُم
بِذَٰلِكَ زَعِيمٌ ﴿٤٠﴾ أَمۡ لَهُمۡ شُرَكَآءُ فَلۡيَأۡتُواْ بِشُرَكَآئِهِمۡ إِن كَانُواْ صَٰدِقِينَ ﴿٤١﴾
يَوۡمَ يُكۡشَفُ عَن سَاقٖ وَيُدۡعَوۡنَ إِلَى ٱلسُّجُودِ فَلَا يَسۡتَطِيعُونَ ﴿٤٢﴾

(ፍሬዋን) ሊለቅሟት በማሉ ጊዜ እንደሞከርን (የመካን ሰዎች) ሞከርናቸው::[1]
18 (በመሓላቸው) አያስቀሩምም።
19 እነርሱ የተኙ ሆነውም ሳሉ ከጌታህ
የሆነ ዟሪ በእርሷ ላይ ዞረባት።
20 እንደ ሌሊት ጨለማም የከሰለች ሆና
አነጋች (ከሰለች)።
21 ያነጉም ሆነው ተጠራሩ።
22 ቆራጮች እንደ ሆናችሁ ወደ
እርሻችሁ ላይ ማልዱ በማለት።
23 እነሱ የሚሾካሾኩ ሆነው ሄዱም።
24 ዛሬ በእናንተ ላይ ድሃ እንዳይገባት
በማለት።

25 (ድሆችን) በመከልከልም ላይ
(በሀሳባቸው) ቻዮች ሆነው ማለዱ።
26 (ተቃጥላ) ባዮዋትም ጊዜ፡- እኛ
በእርግጥ ተሳሳቾች ነን አሉ።
27 ይልቁንም እኛ የተከለከልን ነን አሉ።
28 ትክክለኛቸው /አስተዋያቸው/፡- ለእናንተ
አላህን ለምን አታጠሩም /አታወሱም/
አላልኳችሁም ነበር ? አለ።
29 ጌታችን ጥራት ይገባው፤ እኛ በዳዮች ነበርን
አሉ።
30 የሚወቃቀሱም ሆነው ከፊሎቻቸው
በከፊሉ ላይ መጡ። (እርስ በእርስ
ይወቃቀሱም ጀመር።)
31 ዋ! ጥፋታችን! እኛ ድንበር አላፊዎች
ነበርን፤ አሉ።
32 ጌታችን ከእርሷ የተሻለን (አትክልት)
ሊለውጠን ይከጅላል። እኛ ወደ ጌታችን
ከጀዮች ነን፤(አሉ)።
33 ቅጣቱ እንደዚሁ ነው። የመጨረሻይቱም
ዓለም ቅጣት ታላቅ ነው። የሚያውቁ
ቢሆኑ ሮ (በተጠነቀቁ ነበር)።
34 ለጥንቁቆች በጌታቸው ዘንድ
መጠቀሚያ ገነቶች አሏቸው።
35 ሙስሊሞችን እንደ ከሓዲዎች
እናደርጋለን? /አናደርግም/
36 ለእናንተ ምን(አስረጅ) አላችሁ?
እንዴት ትፈርዳላችሁ። /ምን ነካችሁ/
37 በእውነቱ ለእናንተ በእርሱ የምታጠኑበት
መጽሐፍ አላችሁን?
38 በውስጡ ለእናንተ የምትመርጡት
አላችሁ (የሚል)።
39 ወይስ ለእናንተ የምትፈርዱት አላችሁ
በማለት(ቃል ኪዳን የገባንላችሁ) እስከ
ትንሣኤ ቀን ደራሽ የሆኑ መሓላዎች
ለእናንተ በእኛ ላይ አሏችሁን?
40 በዚህ ማንኛቸው ተያዥ እንደ ሆነ
ጠይቃቸው።
41 ወይስ ለእነሱ (በፍርዳቸው ተስማሚ)
ተጋሪዎች አሏቸውን? እውነተኞችም
እንደሆኑ ተጋሪዎቻቸውን ያምጡ።
42 ባት[2] የሚገለፅበትን፣ (ከሓዲዎችም) ወደ
መስገድ የሚጥጠሩበትንና የማይችሉበትን
ቀን (አስታውስ)።
43 ዓይ ቻቸው የፈሩ፣ ውርደት
የምትሸፍናቸው ሲሆኑ (ወደ ስግደት
የሚጠሩበትን)። እነሱም (በምድረ ዓለም)
ደህና ሆነው ሳሉ ወደ ስግደት በእርግጥ
ይጠሩ ነበሩ።
44 (ሙሐመድ ሆይ!) በዚህም ንግግር
ከሚያስተባብሉት ሰዎች ጋር ተወኝ፤

---

የሚወታ ነበር ። እሱ ሲሞት የወረሱት ልጆቹ ግን ብዞዎቹ ስለሆንና ገንዘቡ ስለማይበቃን አባታችን ያለመዳቸውን ዲሆች ማስተናገድ አንችልም በማለታቸው ይህ ታሪክ ተፈጸመ።

[1] መሐላቸውን፡- የአላህ ፍቃድ ከተጨመረበት፣ በማለት አይናገሩም ነበር። ለድሆች ድርሻ ፋን አያስተርፉም ነበር ። ከአዝርእታቸው ለድሆች ድርሻ ባለማድረጋቸው ሐብታቸው ለጥፋት የተዳረገ ሰዎችን በምሳሌነት ያቀረበ አንቀጽ ነው ። ሰዎቹ በየመን አካባቢ የነበሩ የአንድ ባለጸጋ ልጆች ሲሆኑ በመካ ማሕበረሰብ ዘንድ ይታወቁ ነበር ። ሐብትን አላህ ለወደደው ነገር አለማዋል ለተመሳሳይ ጥፋት እንደሚዳርግ ያስተምራል ።

[2] አላህ ባቱን ይገልጣል ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሀዲስ ጌታችን ባቱን ይገልጣል ። ከዚያም ሴትም ሆነ ወንድ አማኝ ሱጁድ ሲያደርግ በዱንያ ሳለ ለይዩልኝና ለይስሙልኝ ሱጁድ ሲያደርግ የነበረ ሱጁድ ለማድረግ ሲሞክር ወገቡ መታጠፍ እምቢ ይለዋል ብለዋል ።

(ለእነሱ እኔ እበቃሃለሁ)። ከማያውቁት
ስፍራ አዘናግተን እንይዛቸዋለን።
45 እነርሱንም አዘገያለሁ። ዘዴዬ /ብቀላዬ/
ብርቱ ነውና።
46 (ሙሐመድ ሆይ!) ወይንስ በውነቱ
ዋጋን ትጠይቃቸዋለህን? ስለዚህ እነሱ
ከዕዳ የተከበዱ ናቸውን?
47 ወይስ ከእነሱ ዘንድ የሩቁ ምስጢር
ውቀት አልለን? ስለ ዚህ እነርሱ
ይጽፋሉን?
48 ለጌታህም ፍርድ ታገሥ (በመበሳጨትና
ባለ መታገሥ) እንደ ዓሣው ባለቤትም
(እንደ ዮናስ) አትሁን። እርሱ በጭንቀት
የተመላ ሆ (ጌታውን) በተጣራ ጊዜ።
49 ከጌታው የሆነ ጺጋ ባላገኘው ሮ
በምድረ በዳ ተወቃሽ ሆ በተጣለ ነበር።
50 ጌታውም (በነቢይነት) መረጠው።
ከደጋጎቹም አደረገው።
51 እነሆ እነዚያም የካዱት ሰዎች ቁርአኑን
በሰሙ ጊዜ በዓይ ቻቸው ሊጥሉህ
(ሊያጠፉህ) ይቃረባሉ፤ እርሱም በእርግጥ
እብድ ነው ይላሉ።
52 ግን እርሱ (ቁርአን) ለዓለማት
መገሠጫ እንጂ ሌላ አይደለም።[1]

خَٰشِعَةً أَبۡصَٰرُهُمۡ تَرۡهَقُهُمۡ ذِلَّةٞۖ وَقَدۡ كَانُواْ يُدۡعَوۡنَ إِلَى ٱلسُّجُودِ وَهُمۡ سَٰلِمُونَ
﴿٤٣﴾ فَذَرۡنِي وَمَن يُكَذِّبُ بِهَٰذَا ٱلۡحَدِيثِۖ سَنَسۡتَدۡرِجُهُم مِّنۡ حَيۡثُ
لَا يَعۡلَمُونَ ﴿٤٤﴾ وَأُمۡلِي لَهُمۡۚ إِنَّ كَيۡدِي مَتِينٌ ﴿٤٥﴾ أَمۡ تَسۡـَٔلُهُمۡ أَجۡرٗا فَهُم
مِّن مَّغۡرَمٖ مُّثۡقَلُونَ ﴿٤٦﴾ أَمۡ عِندَهُمُ ٱلۡغَيۡبُ فَهُمۡ يَكۡتُبُونَ ﴿٤٧﴾ فَٱصۡبِرۡ
لِحُكۡمِ رَبِّكَ وَلَا تَكُن كَصَاحِبِ ٱلۡحُوتِ إِذۡ نَادَىٰ وَهُوَ مَكۡظُومٞ ﴿٤٨﴾ لَّوۡلَآ
أَن تَدَٰرَكَهُۥ نِعۡمَةٞ مِّن رَّبِّهِۦ لَنُبِذَ بِٱلۡعَرَآءِ وَهُوَ مَذۡمُومٞ ﴿٤٩﴾ فَٱجۡتَبَٰهُ رَبُّهُۥ
فَجَعَلَهُۥ مِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿٥٠﴾ وَإِن يَكَادُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَيُزۡلِقُونَكَ بِأَبۡصَٰرِهِمۡ
لَمَّا سَمِعُواْ ٱلذِّكۡرَ وَيَقُولُونَ إِنَّهُۥ لَمَجۡنُونٞ ﴿٥١﴾ وَمَا هُوَ إِلَّا ذِكۡرٞ لِّلۡعَٰلَمِينَ ﴿٥٢﴾

## سُورَةُ الحَاقَّةِ

آياتها ٥٢ — ترتيبها ٦٩

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

ٱلۡحَآقَّةُ ﴿١﴾ مَا ٱلۡحَآقَّةُ ﴿٢﴾ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا ٱلۡحَآقَّةُ ﴿٣﴾ كَذَّبَتۡ ثَمُودُ
وَعَادُۢ بِٱلۡقَارِعَةِ ﴿٤﴾ فَأَمَّا ثَمُودُ فَأُهۡلِكُواْ بِٱلطَّاغِيَةِ ﴿٥﴾ وَأَمَّا
عَادٞ فَأُهۡلِكُواْ بِرِيحٖ صَرۡصَرٍ عَاتِيَةٖ ﴿٦﴾ سَخَّرَهَا عَلَيۡهِمۡ
سَبۡعَ لَيَالٖ وَثَمَٰنِيَةَ أَيَّامٍ حُسُومٗاۖ فَتَرَى ٱلۡقَوۡمَ فِيهَا صَرۡعَىٰ
كَأَنَّهُمۡ أَعۡجَازُ نَخۡلٍ خَاوِيَةٖ ﴿٧﴾ فَهَلۡ تَرَىٰ لَهُم مِّنۢ بَاقِيَةٖ ﴿٨﴾

## 69 ኛው ምዕራፍ (ሱረተል- ሐቀህ) የአረጋጋጭቱ ምእራፍ ነው።[2] አንቀፆቹ 52 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (ጀምራለሁ)።

1 እውነትን አረጋጋጪቱ (ትንሳኤ)።
2 አረጋጋጪቱ (እርሷ) ምንድን ናት!
3 አረጋጋጪቱም ምን እንደሆነች ምን
አሳወቀህ?
4 ሰሙድና ዓድ በቆርቋሪይቱ ትንሣኤ
ቀን[3] አስተባበሉ።

---

[1] ከምዕራፉ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፦
1. አላህ (ﷻ) በብዕርና በፅሁፍ ስለማለ በፈለገው ነገር እንደሚምል፣
2. የሁሉ መፃፊያ የሆነው ብዕር ትልቅነትና ክብር እንዳለው፤
3. ቀደርን ተቀብሎ ማመንና መማር አስፈላጊ መሆኑን፣
4. ከነቢዩ መልካም ባህሪየት በጥቂቱ፤
5. የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ባህሪ ሙሉ ነትን ማረጋገጥ፣
6. የቂያማ እለት ፍሬው ከገለባው፣ እውነት ከውሸት እንደሚለይ፤
7. በእነዚህ አንቀፆች ውስጥ የተወገዙትን መጥፎ ባህሪያት ማውገዝና ሰዎች እንዲርቋቸው ማድረግ፣
8. የገንዘብና የልጅ መብዛት ለኩራት ምክንያት መሆኑን ገልፆ ከዚህ መሰል ተግባር መጠንቀቅ እንዳለብን ማስታወስ፤
9. የአላህን (ﷻ) ታዐምሮችን ከማስተባበልና ከአስተባባዮች ጋር ከመመሳሰል መጠንቀቅ፤
10. ለሰው ልጆች በኸይርም ሆነ በሸር መፈተን ያለ ስለመሆኑ፤
11. የአላህ (ﷻ) ውለታዎች አለማመስገን እንደመካድ እንደሚቆጠር፤
12. ከእነኚህ ሰዎች ታሪክ ብዙ ቁም ነገሮችን እንደምንማር፣
13. ማንም ሰው ለወደፊቱ አንድ ሥራ ለመስራት ሲያስብ በአላህ (ﷻ)ፈቃድ ከሆነ ማለት እንደሚገባው፤
14. የአላህ (ﷻ) ችሎታ ከፍጡሮች ሁሉ ችሎታ በላይ መሆኑንና አላህ (ﷻ) ሊያደርገው ያሰበውን ነገር የማንም ምክክርና ጥንቃቄ ሊያድነው እንደማይችል፤
15. ከስህተት ታርሞ ከጥፋት መመለስ፣ መጸጸት በኢስላም ከፍተኛ ደረጃ እንዳለው፤
16. ትክክለኛና ምርጥ ሰው ማለት ሰዎችን ወደ አላህ (ﷻ) የሚጠራና በአላህ (ﷻ) የሚያስታውስ መሆኑን፤
17. አመፀኞች ከአማኞች ጋር በተግባርም ሆነ በምንዳ እንደማይስተካከሉ፣
18. አመጸኞችን ማውገዝ፤
19. የቂያማ ቀን ለካሃዲዎች የተዘጋጀው ችግርና መከራም ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ፣ ሁሉን ነገር ለአላህ (ﷻ) መስጠትና የሚወስደውን እርምጃ መጠባበቅ እንደሚገባ፣
20. ስለ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ትዕግስት፤
21. በዳዕዋ ሥራ ላይ ክፍያ መውሰድ ክልክል ስለመሆኑ፣
22. ለዳዕዋ ሥራ ትዕግስት አስፈላጊ ስለመሆኑ፣
23. ሙሽሪኮች ለነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የነበራቸው ጥላቻና ምቀኝነት፣

[2] 4 ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው።

[3] በዚህ የተሰየመችበት ምክኒያት በችግሯ የህዝቦችን ጆሮ ስለምትቆረቁር ነው።

وَجَآءَ فِرۡعَوۡنُ وَمَن قَبۡلَهُۥ وَٱلۡمُؤۡتَفِكَٰتُ بِٱلۡخَاطِئَةِ ﴿٩﴾ فَعَصَوۡاْ رَسُولَ
رَبِّهِمۡ فَأَخَذَهُمۡ أَخۡذَةٗ رَّابِيَةً ﴿١٠﴾ إِنَّا لَمَّا طَغَا ٱلۡمَآءُ حَمَلۡنَٰكُمۡ فِي ٱلۡجَارِيَةِ
﴿١١﴾ لِنَجۡعَلَهَا لَكُمۡ تَذۡكِرَةٗ وَتَعِيَهَآ أُذُنٞ وَٰعِيَةٞ ﴿١٢﴾ فَإِذَا نُفِخَ فِي ٱلصُّورِ
نَفۡخَةٞ وَٰحِدَةٞ ﴿١٣﴾ وَحُمِلَتِ ٱلۡأَرۡضُ وَٱلۡجِبَالُ فَدُكَّتَا دَكَّةٗ وَٰحِدَةٗ ﴿١٤﴾
فَيَوۡمَئِذٖ وَقَعَتِ ٱلۡوَاقِعَةُ ﴿١٥﴾ وَٱنشَقَّتِ ٱلسَّمَآءُ فَهِيَ يَوۡمَئِذٖ وَاهِيَةٞ
﴿١٦﴾ وَٱلۡمَلَكُ عَلَىٰٓ أَرۡجَآئِهَاۚ وَيَحۡمِلُ عَرۡشَ رَبِّكَ فَوۡقَهُمۡ يَوۡمَئِذٖ ثَمَٰنِيَةٞ
﴿١٧﴾ يَوۡمَئِذٖ تُعۡرَضُونَ لَا تَخۡفَىٰ مِنكُمۡ خَافِيَةٞ ﴿١٨﴾ فَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ
كِتَٰبَهُۥ بِيَمِينِهِۦ فَيَقُولُ هَآؤُمُ ٱقۡرَءُواْ كِتَٰبِيَهۡ ﴿١٩﴾ إِنِّي ظَنَنتُ أَنِّي مُلَٰقٍ
حِسَابِيَهۡ ﴿٢٠﴾ فَهُوَ فِي عِيشَةٖ رَّاضِيَةٖ ﴿٢١﴾ فِي جَنَّةٍ عَالِيَةٖ ﴿٢٢﴾
قُطُوفُهَا دَانِيَةٞ ﴿٢٣﴾ كُلُواْ وَٱشۡرَبُواْ هَنِيٓـَٔۢا بِمَآ أَسۡلَفۡتُمۡ فِي ٱلۡأَيَّامِ
ٱلۡخَالِيَةِ ﴿٢٤﴾ وَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ بِشِمَالِهِۦ فَيَقُولُ يَٰلَيۡتَنِي لَمۡ أُوتَ كِتَٰبِيَهۡ
﴿٢٥﴾ وَلَمۡ أَدۡرِ مَا حِسَابِيَهۡ ﴿٢٦﴾ يَٰلَيۡتَهَا كَانَتِ ٱلۡقَاضِيَةَ ﴿٢٧﴾ مَآ أَغۡنَىٰ
عَنِّي مَالِيَهۡۜ ﴿٢٨﴾ هَلَكَ عَنِّي سُلۡطَٰنِيَهۡ ﴿٢٩﴾ خُذُوهُ فَغُلُّوهُ ﴿٣٠﴾ ثُمَّ ٱلۡجَحِيمَ
صَلُّوهُ ﴿٣١﴾ ثُمَّ فِي سِلۡسِلَةٖ ذَرۡعُهَا سَبۡعُونَ ذِرَاعٗا فَٱسۡلُكُوهُ ﴿٣٢﴾ إِنَّهُۥ
كَانَ لَا يُؤۡمِنُ بِٱللَّهِ ٱلۡعَظِيمِ ﴿٣٣﴾ وَلَا يَحُضُّ عَلَىٰ طَعَامِ ٱلۡمِسۡكِينِ ﴿٣٤﴾

(5) ሰሙድማ[1]ወሰን በሌላት ጩኸት ተጠፉ፡፡
(6) ዓድማ [2]በኃይል በምትንሻሻ ብርቱ ነፋስ ተጠፉ።
(7) ተከታታይ በሆኑ ሰባት ሌሊቶችና ስምንት ቀናቶች ውስጥ በእነሱ ላይ ለቀቃት። ህዝቦችንም፤ በውስጧ የተጣሉ ሆነው ልክ ክፍት የሆኑ የበሰበሱ የዘንባባ ግንዶች መስለው ታያቸዋለህ።
(8) ለእነሱ ቀሪን [3]ታያለህን?
(9) ፈርዖን፤ከበፊቱ የነበሩትም ሰዎች፤ ተገልባጮቹም (የሉጥ ሰዎች) ከተሞች በኃጢአት[4] ፈፀሙ።
(10) የጌታቸውንም መልዕክተኛ ትእዛዝ ጣሱ፤ የበረታችንም ቅጣት ቀጣቸው[5]።
(11) እኛ ውሃው ባየለ ጊዜ በተንሻላይቱ /ተንሳፋፊይቱ/ ታንኳ ውስጥ[6] ጫንናችሁ።
(12) ይህንም ያደረግነው ለእናንተ መገሠጫ ልናደርጋትና አጥኚ የሆነችም ጆሮ ታጠናት ዘንድ ነው። በቀንዱ አንዲት መነፋት በተነፋች ጊዜ።
(14) ምድርና ጋራዎች (ከስፍራቸው) በተነሱና አንዲትን መሰባበር በተሰባበሩ /አንዲትን መዘርጋት በተዘረጋች/ጊዜ።
(15) በዚያ ቀን ኋኙቱ/ተከሳቿ/(ትንሣኤ) ትሆናለች።
(16) ሰማይም ትቀደዳለች ። ስለዚህ እርሷ በዚያ ቀን ደካማ ናት ።
(17) መላእክትም በየጫፎችዋ ላይ ይሆናሉ፡ ፡ የጌታህንም ዐርሽ በዚያ ቀን ስምንት (መላእክት) ከበላያቸው ይሸከማሉ።
(18) በዚያ ቀን ከእናንተ[7] ተደባቂ (ነገሮች) የማይደበቁ ሲሆኑ ትቀረባላችሁ።
(19) መጽሀፉን በቀኙ የተሰጠ ሰውማ (ለጓደኞቹ)፡- እንኩ መጽሐፌን አንብቡ ይላል።
(20) እኔ ምርመራዬን የምገናኝ መሆኔን አረጋገጥኩ፡፡
(21) እርሱም በተወደደች ኑሮ ውስጥ ይሆናል።
(22) በከፍተኛይቱ ገነት ውስጥ።
(23) ፍሬዎችዋ ቅርቦች የሆኑ።
(24) በአለፉት ቀናት ውስጥ (በምድረ ዓለም) ባስቀደማችሁት ምክንያት ብሉ፣ ጠጡም፡፡ (ይባላሉ፡፡)
(25) መጽሐፉን በግራው የተሰጠ ሰው ደግሞ ዋ ጥፋቴ ምነው መጽሐፌን ባልተሰጠሁ ይላል፡፡
(26) ምርመራዬንም ምን እንደሆነ ባላውቅሁ፡፡
(27) እርሷ (ሞት ህይወቴን) ምነው ፈጻሚ በሆነች፡፡
(28) ገንዘቤ ከእኔ ምንንም አላብቃቃኝ (አልጠቀመኝም)፡፡
(29) ኃይሌ /ስልጣኔ/ ከእኔ ላይ ጠፋ፡፡ (ይላል)
(30) ያዙት አትሰሩትም፡፡
(31) ከዚያም በእሳት ውስጥ አግቡት፡፡
(32) ከዚያም ርዝመቷ ሰባ ክንድ በሆነች ሰንሰለት ውስጥ አግቡት[8]፡፡
(33) እርሱ ታላቅ በሆነው አላህ አያምንም ነበርና፡፡
(34) ድሆችንም በማብላት ላይ አያግባባም /አያነሳሳም/ ነበርና፡፡
(35) ለእርሱም ዛሬ እዚህ ቦታ ዘመድም ሆነ ወገን የለውም፡፡
(36) ምግብም ከእሳት ሰዎች ቁስል እጣቢ (እኀር) በስተቀር የለውም፡፡
(37) ኃጢዓተኞች እንጂ ሌላ አይበላውም፤ (ይባላል)፡፡
(38) (39) በምታዩትም ነገር እምላለሁ፡፡

---

1 የነቢዩ ሷሊህ ህዝቦች ናቸው ፡፡
2 የነቢዩ ሁድ ህዝቦች፡ ናቸው፡:
3 ቡድን ወይም አንዲት ነፍስ ፡፡
4 ተግባሮች ወይም ስራዎች ሺርክና መሰል ወንጀሎችን፡፡
5 እሱም ሰፈራቸዉን በላያቸው ላይ መገልበጥና በላያቸው ላይ አሸዋ ማፍሰስ ነው ፡፡
6 እናንተ በአባቶቻችሁ ጀርባ ሁናችሁ ፡፡ በኑህ መርከብ አማካይነት ዝርያችሁን አተረፍን፡፡
7 አንድም ነገር፣ አካላችሁ፣ ተግባራችሁም ሆነ አንደበታችሁ አይደበቅም፡፡
8 ሱፍያን የተባሉት ዓሊም ይህ ሰንሰለት በአፍጋራው ገብቶ በአፉ እንዲወጣ ይደረጋል ብለዋል ፡፡

فَلَيْسَ لَهُ ٱلْيَوْمَ هَٰهُنَا حَمِيمٌ ﴿٣٥﴾ وَلَا طَعَامٌ إِلَّا مِنْ غِسْلِينٍ ﴿٣٦﴾ لَّا يَأْكُلُهُۥٓ
إِلَّا ٱلْخَٰطِـُٔونَ ﴿٣٧﴾ فَلَآ أُقْسِمُ بِمَا تُبْصِرُونَ ﴿٣٨﴾ وَمَا لَا تُبْصِرُونَ ﴿٣٩﴾
إِنَّهُۥ لَقَوْلُ رَسُولٍ كَرِيمٍ ﴿٤٠﴾ وَمَا هُوَ بِقَوْلِ شَاعِرٍ ۚ قَلِيلًا مَّا تُؤْمِنُونَ ﴿٤١﴾
وَلَا بِقَوْلِ كَاهِنٍ ۚ قَلِيلًا مَّا تَذَكَّرُونَ ﴿٤٢﴾ تَنزِيلٌ مِّن رَّبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٤٣﴾ وَلَوْ
تَقَوَّلَ عَلَيْنَا بَعْضَ ٱلْأَقَاوِيلِ ﴿٤٤﴾ لَأَخَذْنَا مِنْهُ بِٱلْيَمِينِ ﴿٤٥﴾ ثُمَّ لَقَطَعْنَا
مِنْهُ ٱلْوَتِينَ ﴿٤٦﴾ فَمَا مِنكُم مِّنْ أَحَدٍ عَنْهُ حَٰجِزِينَ ﴿٤٧﴾ وَإِنَّهُۥ لَتَذْكِرَةٌ
لِّلْمُتَّقِينَ ﴿٤٨﴾ وَإِنَّا لَنَعْلَمُ أَنَّ مِنكُم مُّكَذِّبِينَ ﴿٤٩﴾ وَإِنَّهُۥ لَحَسْرَةٌ عَلَى
ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٥٠﴾ وَإِنَّهُۥ لَحَقُّ ٱلْيَقِينِ ﴿٥١﴾ فَسَبِّحْ بِٱسْمِ رَبِّكَ ٱلْعَظِيمِ ﴿٥٢﴾

ترتيبها ٧٠ — سُورَةُ المَعَارِجِ — آياتها ٤٤

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

سَأَلَ سَآئِلٌۢ بِعَذَابٍ وَاقِعٍ ﴿١﴾ لِّلْكَٰفِرِينَ لَيْسَ لَهُۥ دَافِعٌ ﴿٢﴾ مِّنَ
ٱللَّهِ ذِى ٱلْمَعَارِجِ ﴿٣﴾ تَعْرُجُ ٱلْمَلَٰٓئِكَةُ وَٱلرُّوحُ إِلَيْهِ فِى
يَوْمٍ كَانَ مِقْدَارُهُۥ خَمْسِينَ أَلْفَ سَنَةٍ ﴿٤﴾ فَٱصْبِرْ صَبْرًا جَمِيلًا ﴿٥﴾
إِنَّهُمْ يَرَوْنَهُۥ بَعِيدًا ﴿٦﴾ وَنَرَىٰهُ قَرِيبًا ﴿٧﴾ يَوْمَ تَكُونُ ٱلسَّمَآءُ كَٱلْمُهْلِ
﴿٨﴾ وَتَكُونُ ٱلْجِبَالُ كَٱلْعِهْنِ ﴿٩﴾ وَلَا يَسْـَٔلُ حَمِيمٌ حَمِيمًا ﴿١٠﴾

በማታዩትም።
40 እርሱ (ቁርአን) የተከበረ መልዕክተኛ ቃል ነው።
41 እርሱም የባለቅኔ ቃል (ግጥም) አይደለም ጥቂትን ብቻ ታምናላችሁ።
42 የጠንቋይም ቃል አይደለም። ጥቂትን ብቻ ታስታውሳላችሁ።
43 ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው።
44 በእኛ ላይም ከፊልን ቃላት እንኳን (ያላልነውን) በቀጠፈ ሮ፤
45 በኃይል በቀጣነው ነበር።
46 ከዚያም ከእርሱ የልቡን ስር (የተንጠለጠለበትን ጅማት) በቆረጥን ነበር።
47 ከእናንተም ውስጥ ከእርሱ ላይ ከልካዮች ምንም አይ ሩም።
48 እርሱም (ቁርአን) ለጥንቁቆቹ መገሠጫ ነው።
49 እኛም ከእናንተ ውስጥ አስተባባዮች መ ራቸውን በእርግጥ እናውቃለን።
50 እርሱም (ቁርአን) በከሓዲዎቻ ላይ ጸጸት ነው።
51 እርሱም የተረጋገጠ እውነት ነው።
52 የታላቁን ጌታህንም ስም አወድስ።[1]

[1] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።
1. ሞቶ መነሳትን ማረጋገጥ፣

## 70 ኛው ሱራ፡-የመሰላሎች ምዕራፍ (ሱረቱ አል -መዓሪጅ ነው።[2]) አንቀጾቹ 44 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 ወዳቂ /ተከሳች/ ከሆነው ቅጣት ጠያቂ ጠየቀ።
2 በከሓዲዎች[3] ላይ (ወዳቂ ከሆነው)። ለእርሱ መላሽ የለውም።
3 የ(ሰማያት) መሰላሎች ባለቤት ከሆነው አላህ (መላሽ የለውም)።
4 መላዕክትና መንፈሱም ልኩ ሀምሳ ሺህ ዓመት በሆነ ቀን ውስጥ ወደ እርሱ ያርጋሉ (ይወጣሉ)።
5 መልካምንም ትእግስት ታገሥ።

2. እነኚህ ሕዝቦች ሞቶ መነሳትን ያምኑ እንዳልነበር፣
3. ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) ማስከፋትና ትዕዛዛቸውን መንቀፍ ለሁለቱም ዓለም ክስረት ዋና ምክንያት መሆኑን፤
4. ከማእበሉ ታሪክ ብዙ መማር እንዳለብን፣
5. ቁርአን ያለምንም ጥርጣሬ የአላህ ቃል መሆኑን፤
6. ይህች ዓለም አብቅቶ ሁለተኛው ዓለም እንዴት እንደሚጀመር በግልፅ ማሳየት፤
7.የቂያማው ቀንና የሚያስከትለው ጥፋት።
8. በአላህ (ﷻ) ፊት ለሒሳብ መቅረብ እንዳለ መግለፅና ሌሎችንም እንማራለን ።
9. ይህች ዱንያ የአኼራ ምርት መዝሪያ ስለ መሆንዋ የአኼራ ደስታ ከዚህች ዓለም ተግባር ጋር የተያያዘ መሆኑ፣
10. በትንሳኤ እለት ሰዎች የመልካም ተግባርና የመጥፎ ተግባር ባለቤቶች ተብለው ለሁለት እንደሚከፈሉ፤
11. አማኞች የሚያስደስቱ ነገሮችን ሁሉ ሲያገኙ ከሃዲዎች ደግሞ የሚያጋጥማቸው ሁሉ አስከፊና አስቃቂ መሆኑን፤
12. ከሞት የመነሳትን እውነትና አስፈላጊነትን ማረጋገጥ፣
13. ገንዘብ፣ ስልጣን፣ ዘመድና፣ ወዳጅ የሰው ልጅን ከምንም ሊከላከሉለት እንደማይችሉና የአኼራን ነጻነት ለማግኘት መልካም ተግባር እንደሚያስፈልገው፣
14.ክህደትንና ከሃዲዎችን ማውገዝ፣
15. ዘካንም ሆነ ሌላን ገንዘብ ነክ ሐቆችን በአግባቡ አለመወጣት ከፍተኛ ወንጀል ስለ መሆኑና ከአላህ (ﷻ) ዘንድ ሊያስከትለው የሚችለውን አደገኛ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤
16. አላህ (ﷻ) በፈለገው መማል እንደሚችልና ፍጡሮች ግን ያለ አላህ (ﷻ) በማንም መማል እንደማይችሉ፣
17.ወህይን /ራዕይንና/ ነቢይነትን ማረጋገጥና ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ባለቅኔና ጠንቋይ፣ ቁርአንም ቅኔ እንዳልሆኑ ማረጋገጥ፣
18. ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) በአላህ (ﷻ) ላይ መዋሸት እንደማይችሉ፣
19. ቁርአን ከአላህ (ﷻ) የወረደ፣ ለፈርሃዊያን ማስታወሻ፣ ለከሃዲዎች መፀፀቻ መሆኑን፣አላህን (ﷻ) ሁል ጊዜ ማጽዳት ተገቢ መሆኑን እንማራለን።

[2] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው።
[3] 1ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-ነድር ቢን አልሃሪስ፡-(ጌታየ ሆይ! ይህ እርሱ ከአንተ ዘንድ /የተወረደ/ እውነት እንደ ኾነ በእኛ ላይ ከሰማይ ድንጋዮችን አዝንብብን ወይም አሳማሚ ቅጣትን አምጣብን) ባለ ጊዜ ነው ። ይኸው የለመነውም ነገር በበድር እለት ወርዶለት ቀምሶታል ።

6 እነርሱ (ያንን ቀን) ሩቅ አድርገው ያዩታል።
7 እኛም ቅርብ ሆኖ እናየዋለን።
8 ሰማይ እንደ ዘይት አተላ በምትሆንበት ቀን።
9 ጋራዎችም በተለያዩ ቀለማት እንደ
ተነከረ ሱፍ (ንፋስ እንደበተነውና
እንደሚያበረው) በሚሆኑበት ቀን።
10 ዘመድም ዘመድን በማይጠይቅበት ቀን
(መላሽ የለውም) ።
11 (ዘመዶቻቸውን) ያዩዋቸዋል፤
አመፀኛው ከዚያ ቀን ስቃይ (ነፍሱን)
በልጆቹ ቤዛ ሊያደርግ ይመኛል።
12 በሚስቱም በወንድሙም ፤
13 በዚያችም በምታስጠጋው ጎሳው ፤
14 በምድርም ላይ ባለው ሁሉ (ሊበዥ)
ከዚያም ሊያድነው (ይመኛል)።
15 ይተው! እርሷ (እሳቲቱ) ለዟ (ነዲድ
እሳት) ናት።
16 የራስን ቅል ቆዳ የምትሞሽልቅ ስትሆን፤
17 (ከእምነት) የዞረንና የሸሸን ሰው (ወደ
እርሷ) ትጠራለች።
18 ገንዘብን የሰበሰበንና (ዘካውን ሳይሰጥ)
የቆጠረንም ( ትጠራለች)።
19 ሰው ቅጠ ቢስ ሆ ተፈጠረ።
20 ክፉ ነገር ባገኘው ጊዜ ብስጭተኛ፤
21 መልካምም ነገር (ድሎት) ባገኘው ጊዜ
ከልካይ (ሆኖ ተፈጠረ።)
22 ሰጋጆች ብቻ ሲቀሩ።
23 እነዚያ እነርሱ በስግደታቸው ላይ
ዘውታሪዎች የሆኑት።
24 እነዚያም በገንዘቦቻቸው ላይ የታወቀ
መብት ያለባቸው የሆኑት።
25 ለለማኝ ከልመና ለሚከለከልም
(መብት ያለባቸው የሆኑ)።
26 እነዚያም በፍርዱ ቀን እውነት
የሚሉት (የሚያረጋግጡት)።
27 እነዚያም እነሱ ከጌታቸው ቅጣት
ፈሪዎች የሆኑት።
28 የጌታቸው ቅጣት (መምጣቱም ሆነ
አለመምጣቱ) የማያስተማምን ነውና ።
29 እነዚያም እነሱ ብልቶቻቸውን
ጠባቂዎች የሆኑት።
30 በሚስቶቻቸው ወይም እጆቻቸው
በያዙዋቸው (ባሮች) ላይ ሲቀር ። እነሱ
(በነዚህ) የማይወቀሱ ናቸውና ።
31 ከዚያም ወዲያ የፈለገ ሰው እነዚያ
እነሱ ድንበር አላፊዎች ናቸው ።
32 እነዚያም እነሱ አደራዎቻቸውንና ቃል
ኪዳናቸውን ጠባቂዎች የሆኑት ።
33 እነዚያም እነሱ በምስክርነታቸው
ትክክለኞች የሆኑት ።
34 እነዚያም እነሱ በሶላቶቻቸው ላይ
የሚጠባበቁት ።
35 እነዚህ (ከዚህ በላይ የተወሱት ሁሉ)
በገነቶች ውስጥ የሚከበሩ ናቸው።
36 እነዚያ የካዱት ወደ አንተ በኩል
አንገቶቻቸውን መዝዘው የሚያተኩሩት

يُبَصَّرُونَهُمْ يَوَدُّ ٱلْمُجْرِمُ لَوْ يَفْتَدِى مِنْ عَذَابِ يَوْمِئِذٍ بِبَنِيهِ ﴿١١﴾
وَصَٰحِبَتِهِۦ وَأَخِيهِ ﴿١٢﴾ وَفَصِيلَتِهِ ٱلَّتِى تُـْٔوِيهِ ﴿١٣﴾ وَمَن فِى ٱلْأَرْضِ
جَمِيعًا ثُمَّ يُنجِيهِ ﴿١٤﴾ كَلَّآ ۖ إِنَّهَا لَظَىٰ ﴿١٥﴾ نَزَّاعَةً لِّلشَّوَىٰ ﴿١٦﴾ تَدْعُوا۟
مَنْ أَدْبَرَ وَتَوَلَّىٰ ﴿١٧﴾ وَجَمَعَ فَأَوْعَىٰٓ ﴿١٨﴾ ۞ إِنَّ ٱلْإِنسَٰنَ خُلِقَ هَلُوعًا
﴿١٩﴾ إِذَا مَسَّهُ ٱلشَّرُّ جَزُوعًا ﴿٢٠﴾ وَإِذَا مَسَّهُ ٱلْخَيْرُ مَنُوعًا ﴿٢١﴾ إِلَّا
ٱلْمُصَلِّينَ ﴿٢٢﴾ ٱلَّذِينَ هُمْ عَلَىٰ صَلَاتِهِمْ دَآئِمُونَ ﴿٢٣﴾ وَٱلَّذِينَ فِىٓ
أَمْوَٰلِهِمْ حَقٌّ مَّعْلُومٌ ﴿٢٤﴾ لِّلسَّآئِلِ وَٱلْمَحْرُومِ ﴿٢٥﴾ وَٱلَّذِينَ يُصَدِّقُونَ
بِيَوْمِ ٱلدِّينِ ﴿٢٦﴾ وَٱلَّذِينَ هُم مِّنْ عَذَابِ رَبِّهِم مُّشْفِقُونَ ﴿٢٧﴾ إِنَّ عَذَابَ
رَبِّهِمْ غَيْرُ مَأْمُونٍ ﴿٢٨﴾ وَٱلَّذِينَ هُمْ لِفُرُوجِهِمْ حَٰفِظُونَ ﴿٢٩﴾ إِلَّا عَلَىٰٓ
أَزْوَٰجِهِمْ أَوْ مَا مَلَكَتْ أَيْمَٰنُهُمْ فَإِنَّهُمْ غَيْرُ مَلُومِينَ ﴿٣٠﴾ فَمَنِ ٱبْتَغَىٰ وَرَآءَ
ذَٰلِكَ فَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْعَادُونَ ﴿٣١﴾ وَٱلَّذِينَ هُمْ لِأَمَٰنَٰتِهِمْ وَعَهْدِهِمْ رَٰعُونَ
﴿٣٢﴾ وَٱلَّذِينَ هُم بِشَهَٰدَٰتِهِمْ قَآئِمُونَ ﴿٣٣﴾ وَٱلَّذِينَ هُمْ عَلَىٰ صَلَاتِهِمْ يُحَافِظُونَ
﴿٣٤﴾ أُو۟لَٰٓئِكَ فِى جَنَّٰتٍ مُّكْرَمُونَ ﴿٣٥﴾ فَمَالِ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ قِبَلَكَ مُهْطِعِينَ
﴿٣٦﴾ عَنِ ٱلْيَمِينِ وَعَنِ ٱلشِّمَالِ عِزِينَ ﴿٣٧﴾ أَيَطْمَعُ كُلُّ ٱمْرِئٍ مِّنْهُمْ
أَن يُدْخَلَ جَنَّةَ نَعِيمٍ ﴿٣٨﴾ كَلَّآ ۖ إِنَّا خَلَقْنَٰهُم مِّمَّا يَعْلَمُونَ ﴿٣٩﴾

ምን አላቸው?
37 ከቀኝና ከግራ ክፍልፍል ጭፍሮች ሲሆኑ፤
38 ከእነሱ[1] እያንዳንዱ ሰው የጸጋይቱን
ገነት መግባትን ይከጅላልን ?
39 ይከልከል፤ በፍፁም እኛ ከሚያውቁት
ነገር[2] (ከፍቶት ጠብታ)ፈጠርናቸው ።
40 በምስራቆችና በምዕራቦች ጌታ
እምላለሁ፣ እኛ በእርግጥ ቻዮች ነን ።
41 ከነሱ የተሻለን በመለወጥ ላይ እኛም
ተሸናፊዎች አይደለንም ።
42 ያንንም የሚስፈራሩበትን ቀናቸውን
እስከሚገናኙ ድረስ ተዋቸው፤ ይዋኙ
ይጫወቱም።
43 ወደ ጣዖቶች እንደሚሽቀዳደሙ ሆነው

---

[1] ከ38-39 ያሉት አንቀፆች የወረዱበት ምክንያት፡- ካፊሮች በነብዩ ሙሀመድ ዙሪያ እየተሰበሰቡ የሚሉትን ይሰሙ፣ ያስተባብሉና ያፌዙ ሥለነበር፤ ብሎም ለሙስሊሞች፡- እነኝህ ጀነት ከገቡማ እኛም በይበልጥ ጀነት እንገባለን ይሉ ሥለነበር ነው ። (ዋሂድ።)

[2] አህመድ ኢብን ማእጃ በዘገቡት ሀዲስ እነዚያ የካዱ ወደ አንተ በኩል አንገቶቻቸውን መዘው ከሚለው አንቀፅ አንስቶ እስከ እዚህ አንቀፅ ድረስ ያሉትን አንብበው በእጃቸው ላይ ምራቅ ተፉ ጣታቸውንም እሷ ላይ አሳለፉ አሉም አላህ እንዲህ አለ የአደም ልጅ ከዚህ መሰል ፈጥሬህ እንዴት ነው የምታሸንፈኝ።

فَلَآ أُقۡسِمُ بِرَبِّ ٱلۡمَشَٰرِقِ وَٱلۡمَغَٰرِبِ إِنَّا لَقَٰدِرُونَ ﴿٤٠﴾ عَلَىٰٓ أَن نُّبَدِّلَ خَيۡرًا مِّنۡهُمۡ
وَمَا نَحۡنُ بِمَسۡبُوقِينَ ﴿٤١﴾ فَذَرۡهُمۡ يَخُوضُواْ وَيَلۡعَبُواْ حَتَّىٰ يُلَٰقُواْ يَوۡمَهُمُ ٱلَّذِى
يُوعَدُونَ ﴿٤٢﴾ يَوۡمَ يَخۡرُجُونَ مِنَ ٱلۡأَجۡدَاثِ سِرَاعًا كَأَنَّهُمۡ إِلَىٰ نُصُبٍ يُوفِضُونَ
﴿٤٣﴾ خَٰشِعَةً أَبۡصَٰرُهُمۡ تَرۡهَقُهُمۡ ذِلَّةٌ ذَٰلِكَ ٱلۡيَوۡمُ ٱلَّذِى كَانُواْ يُوعَدُونَ ﴿٤٤﴾

## سُورَةُ نُوحٍ

ترتيبها ٧١ — آياتها ٢٨

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

إِنَّآ أَرۡسَلۡنَا نُوحًا إِلَىٰ قَوۡمِهِۦٓ أَنۡ أَنذِرۡ قَوۡمَكَ مِن قَبۡلِ أَن يَأۡتِيَهُمۡ
عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿١﴾ قَالَ يَٰقَوۡمِ إِنِّى لَكُمۡ نَذِيرٌ مُّبِينٌ ﴿٢﴾ أَنِ ٱعۡبُدُواْ
ٱللَّهَ وَٱتَّقُوهُ وَأَطِيعُونِ ﴿٣﴾ يَغۡفِرۡ لَكُم مِّن ذُنُوبِكُمۡ وَيُؤَخِّرۡكُمۡ
إِلَىٰٓ أَجَلٍ مُّسَمًّىۚ إِنَّ أَجَلَ ٱللَّهِ إِذَا جَآءَ لَا يُؤَخَّرُۚ لَوۡ كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ
﴿٤﴾ قَالَ رَبِّ إِنِّى دَعَوۡتُ قَوۡمِى لَيۡلًا وَنَهَارًا ﴿٥﴾ فَلَمۡ يَزِدۡهُمۡ دُعَآءِىٓ إِلَّا
فِرَارًا ﴿٦﴾ وَإِنِّى كُلَّمَا دَعَوۡتُهُمۡ لِتَغۡفِرَ لَهُمۡ جَعَلُوٓاْ أَصَٰبِعَهُمۡ
فِىٓ ءَاذَانِهِمۡ وَٱسۡتَغۡشَوۡاْ ثِيَابَهُمۡ وَأَصَرُّواْ وَٱسۡتَكۡبَرُواْ ٱسۡتِكۡبَارًا
﴿٧﴾ ثُمَّ إِنِّى دَعَوۡتُهُمۡ جِهَارًا ﴿٨﴾ ثُمَّ إِنِّىٓ أَعۡلَنتُ لَهُمۡ وَأَسۡرَرۡتُ
لَهُمۡ إِسۡرَارًا ﴿٩﴾ فَقُلۡتُ ٱسۡتَغۡفِرُواْ رَبَّكُمۡ إِنَّهُۥ كَانَ غَفَّارًا ﴿١٠﴾

ከመቃብሮቻቸው ፈጥነው የሚወጡበትን
ቀን (እስከሚገናኙ ድረስ ተዋቸው) ።
(44) ዓይኖቻቸው ያፈሩ ሆነው፤ ውርደት
ትሸፍናቸዋለች። ይህ ቀን ያ ይስፈራሩበት
የነበሩት ነው።[1]

---

[1] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. የአላህ (ﷻ) ቅጣትን እንዲመጣ መለመን ክልክል መሆኑን፣
2. ለሁሉም ነገር ትዕግስት አስፈላጊ ስለመሆኑ፣
3. የሞቶ መነሳት ነገር ምንም ጥርጣሬ ሊገባው እንደማይችልና፤ በሱ ማመን አስፈላጊ ስለመሆኑ፣
4. የቂያማ ሁኔታ አሳሳቢ ስለመሆኑና ዘመድ ለዘመድ እንኳን የማይጠያየቅበት መሆኑን፣
5. የአላህን (ﷻ) ዒባዳ አለመተግበር ሊያስከትለው የሚችለው አደጋ ምን እንደሚመስል፤
6. ከሰዎች ባህሪያት መካከል አስከፊው ባህሪ ስግብግብነት ስለመሆኑ፣
7. የዚህ አስከፊ በሽታ መድሐኒት ምን እንደሆነ መጠቆም፣
8. እሱም ስምንት ነገሮች መሆናቸውን መግለፅ ስለመሆኑ፣
9. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱትን ትዕዛዛትና እርም የሆኑ ነገሮችን መተግበርና መቆጠብ፤
10. ስለ ዝሙት አስከፊነት ማስተማር፤
11. ስለ አማና እና አደራ ክብደት፤

## 71 ኛው ምዕራፍ:- የኖህ ምዕራፍ (ሱረቱ ኑህ) ነው።[2] አንቀጾቹ 28 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

(1) እኛ ኑሕን ህዝቦችህን አሳማሚ ቅጣት
ሳይመጣባቸው በፊት አስጠንቅቅ በማለት
ወደ ወገኖቹ ላክነው።[3]
(2) (እርሱም) አለ:- ህዝቦቼ ሆይ፤ እኔ
ለእናንተ ገላጭ የሆንኩ አስጠንቃቂ ነኝ ።
(3) አላህን ተገዙት። ፍሩትም። ታዘዙኝም ።
(በማለት አስጠንቃቂ ነኝ)።
(4) ለእናንተ ከኃጢአቶቻችሁ ይምራልና
እስከ ተወሰነ ጊዜም ያቆያችኋል። አላህ
(የወሰነው) ጊዜ በመጣ ወቅት አይቆይም።
የምታውቁ ብትሆኑ ኖሮ (በታዘዛችሁ ነበር)።
(5) (ስለተቃወሙትም) አለ :- ጌታዬ ሆይ!
እኔ በሌሊትም ሆነ በቀን ህዝቦቼን ጠራሁ።
(6) ጥሪየም መሸሽን እንጂ ሌላ
አልጨመረላቸውም።
(7) እኔም ለእነርሱ ትምራቸው ዘንድ (ወደ
እምነት) በጠራኋቸው ቁጥር ጣቶቻቸውን
በጆሮቻቸው ውስጥ አደረጉ። ልብሶቻቸውንም
ተከናነቡ። (በመጥፎ ሥራቸው ላይ)
ዘወተሩም። (ያለ ልክ) መኩራትንም ፍሩ።
(8) ከዚያም እኔ በግልፅ ጠራኋቸው።
(9) ከዚያም እኔ ለእነሱ ጥሪዬን ይፋ
አደረግኩ። ለእነሱም መመስጠርን መሰጠርኩ[4]፤
(10) አልኳቸውም:- ጌታችሁን ምህረትን
ለምኑት። እርሱ በጣም መሓሪ ነውና።
(11) በእናንተ ላይ ዝናምን ተከታታይ
አድርጎ ይልካል።
(12) በገንዘቦችና በልጆች ይለግሳችኋል፤

---

12. ስለ ምስክርነት ከፍተኛ ሀላፊነት መሆን ማስተማር፤
13. የሶላት ክብደት፤
14. ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) በመካ ሳሉ የነበሩበትን ሁኔታ መግለፅ፣
15. የሰው ልጅ ለጀነት የሚበቃው በእምነቱ በሥራው እንጂ አመጣጡማ ከሶስት ሰዎች በስተቀር ማለትም ከአደምና ሐዋ እንዲሁም ከኢሣ በስተቀር ከአፀያፊ ደካማ ፈሳሽ እንደሆነ መግለፅ፣
16. ስለ መጀመሪያ አፈጣጠራችን ማወቅ ለሁለተኛው ዓለም መኖር ማስረጃ እንደሚሆን፣
17. ሞቶ መነሳትን ያለማመንታት መቀበል እንዳለብን ማሳየት፣
18. የክህደት ሰዎች ኑሮ ላይ ላዩን ሲታይ ያማረና የሰመረ ቢመስልም ውስጡ የሚኮሰኩስና ውስብስብ መሆኑን፣
19. የነቢይነት ግዴታ መልዕክቱን ከማድረስ ያለፈ እንዳልሆነ፣
20. የትንሳኤ ዕለት ሰዎች ከቀብሮቻቸው እየተሯሯጡ እንደሚወጡና ለዚህ ቀን ቀደም ብሎ መዘጋጀቱ አስፈላጊ መሆኑን እንማራለን።

[2] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው።

[3] ኑህ የመጀመሪያ መልዕክተኛ እንደነበሩና ስንት ዘመን እንደቆዩ በሱረቱል ዐንከቡት አልፏል። ለ፱፻፶0 ዓመታት ጥሪ አድርገዋል።

[4] በየቤቶቻቸው እየሄዱ በግል ትምህርት ሰጥተዋቸዋል ማለት ነው።

يُرۡسِلِ ٱلسَّمَآءَ عَلَيۡكُم مِّدۡرَارٗا ﴿١١﴾ وَيُمۡدِدۡكُم بِأَمۡوَٰلٖ وَبَنِينَ وَيَجۡعَل
لَّكُمۡ جَنَّٰتٖ وَيَجۡعَل لَّكُمۡ أَنۡهَٰرٗا ﴿١٢﴾ مَّا لَكُمۡ لَا تَرۡجُونَ لِلَّهِ وَقَارٗا ﴿١٣﴾
وَقَدۡ خَلَقَكُمۡ أَطۡوَارًا ﴿١٤﴾ أَلَمۡ تَرَوۡاْ كَيۡفَ خَلَقَ ٱللَّهُ سَبۡعَ سَمَٰوَٰتٖ
طِبَاقٗا ﴿١٥﴾ وَجَعَلَ ٱلۡقَمَرَ فِيهِنَّ نُورٗا وَجَعَلَ ٱلشَّمۡسَ سِرَاجٗا ﴿١٦﴾
وَٱللَّهُ أَنۢبَتَكُم مِّنَ ٱلۡأَرۡضِ نَبَاتٗا ﴿١٧﴾ ثُمَّ يُعِيدُكُمۡ فِيهَا وَيُخۡرِجُكُمۡ
إِخۡرَاجٗا ﴿١٨﴾ وَٱللَّهُ جَعَلَ لَكُمُ ٱلۡأَرۡضَ بِسَاطٗا ﴿١٩﴾ لِّتَسۡلُكُواْ مِنۡهَا
سُبُلٗا فِجَاجٗا ﴿٢٠﴾ قَالَ نُوحٞ رَّبِّ إِنَّهُمۡ عَصَوۡنِي وَٱتَّبَعُواْ مَن لَّمۡ يَزِدۡهُ
مَالُهُۥ وَوَلَدُهُۥٓ إِلَّا خَسَارٗا ﴿٢١﴾ وَمَكَرُواْ مَكۡرٗا كُبَّارٗا ﴿٢٢﴾ وَقَالُواْ
لَا تَذَرُنَّ ءَالِهَتَكُمۡ وَلَا تَذَرُنَّ وَدّٗا وَلَا سُوَاعٗا وَلَا يَغُوثَ وَيَعُوقَ
وَنَسۡرٗا ﴿٢٣﴾ وَقَدۡ أَضَلُّواْ كَثِيرٗاۖ وَلَا تَزِدِ ٱلظَّٰلِمِينَ إِلَّا ضَلَٰلٗا ﴿٢٤﴾
مِّمَّا خَطِيٓـَٰٔتِهِمۡ أُغۡرِقُواْ فَأُدۡخِلُواْ نَارٗا فَلَمۡ يَجِدُواْ لَهُم مِّن دُونِ
ٱللَّهِ أَنصَارٗا ﴿٢٥﴾ وَقَالَ نُوحٞ رَّبِّ لَا تَذَرۡ عَلَى ٱلۡأَرۡضِ مِنَ ٱلۡكَٰفِرِينَ
دَيَّارًا ﴿٢٦﴾ إِنَّكَ إِن تَذَرۡهُمۡ يُضِلُّواْ عِبَادَكَ وَلَا يَلِدُوٓاْ إِلَّا فَاجِرٗا
كَفَّارٗا ﴿٢٧﴾ رَّبِّ ٱغۡفِرۡ لِي وَلِوَٰلِدَيَّ وَلِمَن دَخَلَ بَيۡتِيَ
مُؤۡمِنٗا وَلِلۡمُؤۡمِنِينَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتِۖ وَلَا تَزِدِ ٱلظَّٰلِمِينَ إِلَّا تَبَارَۢا ﴿٢٨﴾

ለእናንተም አትክልቶችን ያደርግላችኋል። ለናንተም ወንዞችን ያደርግላችኋል።
13 ለአላህ ተገቢዉን ልቅና የማትሰጡት ለእናንተ ምን አላችሁ?።
14 በልዩ ልዩ (በተለያዩ እርከ ች) ሁኔታዎች በእርግጥ የፈጠራችሁ ሲሆን።
15 አላህ ሰባትን ሰማያት አንዱ ከአንዱ በላይ ሲሆን እንዴት እንደፈጠረ አታዩምን ?
16 በውስጣቸውም ጨረቃን አብሪ አደረገ፡፡ ፀሐይንም ብርሃን አደረገ።
17 አላህም ከምድር ማብቀልን አበቀላችሁ።[1]
18 ከዚያም በውስጧ ይመልሳችኋል፡፡ ማውጣትንም ያወጣችኋል።
19 አላህ ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ አደረጋት።
20 ከእርሷ ሰፋፊዎችን መንገዶች ትገቡ ዘንድ።
21 ኑሕ አለ፡-ጌታዬ ሆይ! እነሱ አምመፁብኝ ገንዘቡና ልጁም ከጥፋት በስተቀር ያልጨመረለትን ሰው ተከተሉ።
22 ታላቅንም ተን ል የመከሩትን ሰዎች (ተከተሉ)።
23 (መሪዎች) አሉም፡- አምላ ቻችሁን አትተዉ፡፡ ወድንም፤ ሱዋዕንም፤ የጉስንም ፤ የዑቅንም ነስርንም አትተዉ፡[2]
24 በእርግጥ (እነዚህ መሪዎች ወይም ጣኦቶች) ብዙዎችን ሰዎች አሳሳቱ፡፡ ከሓዲዎችንም ጥመትን እንጂ ሌላን አትጨምርላቸው (አለ)።
25 በኃጢአቶቻቸው ምክንያት ተሰጠሙ፡፡ እሳትንም እንዲገቡ ተደረጉ፡፡ ለነሱም ከአላህ ሌላ የሆኑ ረዳቶችን አላገኙም።
26 ኑሕም አለ፡- ጌታዬ ሆይ! ከከሓዲዎች በምድር ላይ (በዐለም ላይ ወይም እሳቸው በተላኩባት ምድር) የሚኖርን እንድንም ሰው አትተው።
27 አንተ ብትተዋቸው ባሮችህን ያሳስታሉና፡፡ ኃጢአተኛ ከሓዲንም እንጂ ሌላን አይወልዱም።[3]
28 ጌታዬ ሆይ! ለእኔም ለወላጆቼም፣ ምዕምን ሆኖ በቤቴ ለገባም ሰው ሁሉ ለምእምናንና ለምእምናትም ምህረት አድርግ፡፡ ከሓዲዎችንም ከጥፋት በቀር አትጨምርላቸው! (አለ)[4]፡፡

---

[1] አባታችን አደምን ከመሬት አፈር በመፍጠርና እኛም ልጆች ከመሬት በሚበቅሉ ነገሮች በመኖራችን ነው ።

[2] እነዚህ ስሞች በአባታችን አደምና በኑህ ዘመን መካከል የነበሩ ስመጥር ሰዎች ናቸው፡፡ እኒህ ሰዎች ሲሞቱ ሐዉልታቸዉን ሰርተው በየ አምልኮ ቦታ ላይ አደረጉትና ዘመኑ ቆይቶ የእነሱን ማንነት የማያውቅ ትውልድ ሲፈጠር ዳቢሎስ፡- አባቶቻችሁ ያመልኩ የነበሩት እኒህን ሰዎች ነበርና እናንተም ይህኑ አርአያ ተከተሉ፣ ስላላቸው አመለኳቸው ። የጣኦት አምልኮ መነሻው ይህ ነበር ። ከዚያም እነዚሁ ጣኦቶች ወደ ዐረቡ ሀገር ደርሰው አንዳንድ ብሔሮች አመለኳቸው፡፡

[3] እዚህ ላይ ነቢዩ ኑህ ገይብን የማያውቁ ሆነው ሳለ ይህን አባባል እንዴት ደፍረው ለመናገር ቻሉ? ለጊዜው አላመኑም ማለት ወደፊት አያምኑም ማለት ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ መልሱ አሁን ካመኑት በስተቀር አያምኑልህም ከሚለው መልዕክት ስለተረዱት የሚለው ነው፡፡

[4] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡
1. ደእዋ ሲያደርጉ በራስ መጀመር አስፈላጊ ስለ መሆኑ፤ በዳዕዋ ሥራ ትክክለኛውን የዳዕዋ መንገድ መግለጽና ይፋ አድርጎ ማሳየት ተገቢ መሆኑን፤
2. ከሃዲዎች ለጣኦቶቻቸው የአምላክነት ስምና ማዕረግ እንደሚሰጧቸው፣ ይህም ድርጊት አጀማመሩ እንዴት እንደነበር፤
3. ከሃዲዎች ተውሒድንና ተውሒድ የያዙትን ሰዎች የሚጠሉ፣ ሴራና ተንኮለኝነት የሁል ጊዜ ተግባራቸው ስለ መሆኑ፤ 4. በከሃዲዎች ላይ ተስፋ ሲቆረጥ ዱዓ ማድረግ እንደሚፈቀድ፤ 5. ስሞታን ወደ አሏህ (ﷻ) ብቻ ማሰማት ተገቢ ነው፡፡ የአሏህን (ﷻ) ምህረት መጠየቅና ከወንጀሎች መቆጠብ የአሏህን (ﷻ) ረድኤትን ለመቀበል ዋና ምክንያት ይሆናል፡፡ 6. አነስተኛ ኑሮ ያላቸውና ድሆች ብዙ ጊዜ ሐብታሞችን እንደሚከተሉ፣ 7. የሰው ልጆች ለጥፋታቸው ምክንያት የሚሆነውን ወንጀል የሚሠሩት ራሳቸው መሆናቸዉንና ባለንበት ዘመንም የሰው ልጆችን እየቀሰፈ ያለው «ኤድስ»ም ሆነ ሌሎች መከራዎች መነሻቸው የእኛው ጥፋት እንደሆነ፤ 8. የአሏህ (ﷻ)ችሎታና ፀጋ ምን ያህል ሰፊና ጥልቅ እንደሆነ እንማራለን፡፡

ترتيبها ٧٢ سُورَةُ الجِنِّ آياتها ٢٨

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

قُلْ أُوحِيَ إِلَيَّ أَنَّهُ اسْتَمَعَ نَفَرٌ مِّنَ الْجِنِّ فَقَالُوا إِنَّا سَمِعْنَا قُرْآنًا
عَجَبًا (١) يَهْدِي إِلَى الرُّشْدِ فَآمَنَّا بِهِ ۖ وَلَن نُّشْرِكَ بِرَبِّنَا أَحَدًا (٢)
وَأَنَّهُ تَعَالَىٰ جَدُّ رَبِّنَا مَا اتَّخَذَ صَاحِبَةً وَلَا وَلَدًا (٣) وَأَنَّهُ كَانَ
يَقُولُ سَفِيهُنَا عَلَى اللَّهِ شَطَطًا (٤) وَأَنَّا ظَنَنَّا أَن لَّن تَقُولَ الْإِنسُ
وَالْجِنُّ عَلَى اللَّهِ كَذِبًا (٥) وَأَنَّهُ كَانَ رِجَالٌ مِّنَ الْإِنسِ يَعُوذُونَ بِرِجَالٍ
مِّنَ الْجِنِّ فَزَادُوهُمْ رَهَقًا (٦) وَأَنَّهُمْ ظَنُّوا كَمَا ظَنَنتُمْ أَن لَّن يَبْعَثَ
اللَّهُ أَحَدًا (٧) وَأَنَّا لَمَسْنَا السَّمَاءَ فَوَجَدْنَاهَا مُلِئَتْ حَرَسًا
شَدِيدًا وَشُهُبًا (٨) وَأَنَّا كُنَّا نَقْعُدُ مِنْهَا مَقَاعِدَ لِلسَّمْعِ ۖ فَمَن
يَسْتَمِعِ الْآنَ يَجِدْ لَهُ شِهَابًا رَّصَدًا (٩) وَأَنَّا لَا نَدْرِي أَشَرٌّ أُرِيدَ
بِمَن فِي الْأَرْضِ أَمْ أَرَادَ بِهِمْ رَبُّهُمْ رَشَدًا (١٠) وَأَنَّا مِنَّا الصَّالِحُونَ
وَمِنَّا دُونَ ذَٰلِكَ ۖ كُنَّا طَرَائِقَ قِدَدًا (١١) وَأَنَّا ظَنَنَّا أَن لَّن نُّعْجِزَ
اللَّهَ فِي الْأَرْضِ وَلَن نُّعْجِزَهُ هَرَبًا (١٢) وَأَنَّا لَمَّا سَمِعْنَا الْهُدَىٰ
آمَنَّا بِهِ ۖ فَمَن يُؤْمِن بِرَبِّهِ فَلَا يَخَافُ بَخْسًا وَلَا رَهَقًا (١٣)

## 72 ኛው ምእራፍ ሱረቱ አልጂን (የጋኔን ምዕራፍ) ነው::[1] አንቀጾቹ 28 ናቸው

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 (መሐመድ[2] ሆይ!)፡- እነሆ ከጂን የሆኑ
ጭፍሮች (ቁርአንን ከእኔ)አዳመጡ:: እኛ አስደናቂ የሆነን ቁርአን ሰማን አሉ ማለት ወደ እኔ ተወረደ በል።[3]
2 ወደ ቀጥታ መንገድ የሚመራን (ቁርአንን) ሰማን:: በእርሱም አመንን:: በጌታችንም አንድንም አናጋራም።
3 እነሆም የጌታችን ክብር ላቀ:: ሚስትንም ልጅንም አልያዘም::
4 እነሆ ቂላችን በአላህ ላይ ወሰን ያለፈን (ውሸት) ይናገር ነበር።
5 እኛም ሰዎችና ጋኔ ች በአላህ ላይ ውሸትን (ቃል) አይናገሩም ማለትን ጠረጠርን።[4]
6 እነሆም ከሰዎች የሆኑ ወንዶች በጋኔን ወንዶች ይጠበቁ ነበሩ[5]:: ኩራትንም ጨመሩዋቸው።
7 እነሱም አላህ አንድንም አይቀሰቅስም ማለትን እንደጠረጠራችሁ ጠረጠሩ።
8 እኛም ሰማይን (ለመድረስ) ፈለግን:: ብርቱ ጠባቂዎችንና ችቦዎችንም ተሞልታ አገኘናት።
9 እኛም ከእርሷ (ወሬን) ለማዳመጥ በመቀመጫዎች እንቀመጥ ነበርን:: አሁን ግን የሚያዳምጥ ለእርሱ ተጠባባቂ ችቦን ያገኛል።
10 እኛም፡- በምድር ውስጥ ባሉ ሰዎች ክፉ ተሽቷል? ወይስ በእነሱ ጌታቸው[6] ደግን ነገር(ቅናቻን) ሽቷል? ማለትን አናውቅም።
11 እኛም ከእኛ ውስጥ ደጎች አሉ:: ከእኛም ከዚህ ሌላ የሆኑ አሉ፡፤የተለያዩ መንገዶች (ባለ ቤቶች) ነበርን።
12 እኛም አላህን በምድር ውስጥ ፈጽሞ የማናቅተው፣ ሸሽተንም ፈጽሞ የማናመልጠው መሆናችንን አረጋገጥን።
13 እኛም መሪውን በሰማን ጊዜ በእርሱ አመንን፡፡ ፡በጌታውም የሚያምን ሰው መግጎደልንም መጭጨመርንም አይፈራም።
14 እኛም ከእኛ ውስጥ ሙስሊሞች አሉ:: ከእኛም ውስጥ በዳዮች አሉ:: የሰለሙም

---

[1] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው::

[2] 1ኛው አንቀጽ የወረደበት ምክኒያት፡-

ሀ. ሰህል ቢን አብደላህ የተባለ ሰሃቢ በዓድ ህዝቦች ሰፈር አጠገብ ነበር የሚኖረውና አንዲት የድንጋይ መንደር አይቼ ውስጧና በሮ የተበሳሱ የጂን መኖሪያ የሆነች ከተማ አግኝቼ ውስጧ ስገባ አንድ ጥሩ ባህሪ ያለው ሽማግሌ ወደ ካዕባ ዙሮ እየሰገደ አገኘሁት:: አንዲት ንፁህ ካቦርት ለብሶ ነበር :: በእሷ ተገርሜ ሰላም ስለው ሰላም መለሰልኝና፡- ሰህል ሆይ! የሰው አካል አይደለም ልብስን የሚያስረጀው :: ወንጀልና ሐራም መመገብ እንጅ :: ይህች ካቦርት በእኔ ላይ ሰባት መቶ አመቷ ነው :: ኢሣንም ሆነ ሙሐመድን ጎብኝቼባታለሁ አለኝ :: (ሱዩጢ::)

ለ. አንድ ቀን ሰይጣኖች እንደለመዱት ወደ ሰማይ ሊወጡ ሲያስቡ ተከልክለው ባሉበት ቀን አንዳች ነገር ቢፈጠር ነው ከሚል ተነሳስተው ምድርን ሲያስሱ ወደ ቆላማው ሀገር የተሰማራው ቡድን ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ዋዲ ነኽለህ በተባለው ቦታ ላይ ያሉ ሱብሂ የሰገዱ በቁርአን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እየሰገዱ ሲሰሙ እርስ በራሳቸው ይህ ነው የሰማዩን ዜና የዘጋባችሁ በማለት ወደ ዘመዶቻቸው ተመልሰው ነገሯቸው ይህንኑ አባባል አላህ (ﷻ) ለነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አወረደላቸው :: (ሱዩጢ::)

[3] ነቢዩ በዚህ ቀን ያነበቡት የቁርአን ሱራ ሱረቱል ዐለቅ እንደነበረ ይነገራል:: የጅን ነቢይ አልተላከም:: ነቢያት ሁሉ ሰዎች ናቸው::

[4] እናም ያሉንን የሺርክ ተግባር አምነን ተቀብለናቸው ነበር::

[5] አንዳንድ ዐረቦች በሆነ ቦታ ላይ ሲሰፍሩ በዚህ ቀየ አለቃ ከአካባቢው ተንኮለኛ ተንኮል እጠበቃለሁ እያሉ ይጠበቁ ነበር::

[6] ኢብኑ ዘይድ የተባለ ዓሊም ኢብሊስ እና በመከልከላችን አላህ ለምድር ሰዎች ሊቀጣቸው ፈልጎ ቢሆን ወይም መልዕክተኛ ሊልክላቸው አላወቅንም አለ::

وَأَنَّا مِنَّا الْمُسْلِمُونَ وَمِنَّا الْقَاسِطُونَ فَمَنْ أَسْلَمَ فَأُولَٰئِكَ
تَحَرَّوْا رَشَدًا ﴿١٤﴾ وَأَمَّا الْقَاسِطُونَ فَكَانُوا لِجَهَنَّمَ حَطَبًا ﴿١٥﴾
وَأَلَّوِ اسْتَقَامُوا عَلَى الطَّرِيقَةِ لَأَسْقَيْنَاهُم مَّاءً غَدَقًا ﴿١٦﴾ لِّنَفْتِنَهُمْ
فِيهِ ۚ وَمَن يُعْرِضْ عَن ذِكْرِ رَبِّهِ يَسْلُكْهُ عَذَابًا صَعَدًا ﴿١٧﴾ وَأَنَّ
الْمَسَاجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدْعُوا مَعَ اللَّهِ أَحَدًا ﴿١٨﴾ وَأَنَّهُ لَمَّا قَامَ عَبْدُ اللَّهِ
يَدْعُوهُ كَادُوا يَكُونُونَ عَلَيْهِ لِبَدًا ﴿١٩﴾ قُلْ إِنَّمَا أَدْعُو رَبِّي وَلَا أُشْرِكُ
بِهِ أَحَدًا ﴿٢٠﴾ قُلْ إِنِّي لَا أَمْلِكُ لَكُمْ ضَرًّا وَلَا رَشَدًا ﴿٢١﴾ قُلْ إِنِّي
لَن يُجِيرَنِي مِنَ اللَّهِ أَحَدٌ وَلَنْ أَجِدَ مِن دُونِهِ مُلْتَحَدًا ﴿٢٢﴾ إِلَّا بَلَاغًا
مِّنَ اللَّهِ وَرِسَالَاتِهِ ۚ وَمَن يَعْصِ اللَّهَ وَرَسُولَهُ فَإِنَّ لَهُ نَارَ جَهَنَّمَ
خَالِدِينَ فِيهَا أَبَدًا ﴿٢٣﴾ حَتَّىٰ إِذَا رَأَوْا مَا يُوعَدُونَ فَسَيَعْلَمُونَ
مَنْ أَضْعَفُ نَاصِرًا وَأَقَلُّ عَدَدًا ﴿٢٤﴾ قُلْ إِنْ أَدْرِي أَقَرِيبٌ
مَّا تُوعَدُونَ أَمْ يَجْعَلُ لَهُ رَبِّي أَمَدًا ﴿٢٥﴾ عَالِمُ الْغَيْبِ فَلَا
يُظْهِرُ عَلَىٰ غَيْبِهِ أَحَدًا ﴿٢٦﴾ إِلَّا مَنِ ارْتَضَىٰ مِن رَّسُولٍ فَإِنَّهُ
يَسْلُكُ مِن بَيْنِ يَدَيْهِ وَمِنْ خَلْفِهِ رَصَدًا ﴿٢٧﴾ لِّيَعْلَمَ أَن قَدْ أَبْلَغُوا
رِسَالَاتِ رَبِّهِمْ وَأَحَاطَ بِمَا لَدَيْهِمْ وَأَحْصَىٰ كُلَّ شَيْءٍ عَدَدًا ﴿٢٨﴾

ሰዎች እነዚያ ቅንን መንገድ መረጡ።[1]
(15) በዳዮችማ ለገሀነም ማገዶ ሆኑ።
(16) እነሆም[2] በመንገዲቱ ላይ ቀጥ ባሉ ሮ ብዙ ዝናምን ባጠጣናቸው ነበር።
(17) በእርሱ ልንሞክራቸው (ባጠጣናቸው ነበር) ጌታውን ከማስታወስ የሚያፈገፍግ ሰው አስቸጋሪን ቅጣት ያገባዋል።
(18) እነሆ[3] መስጊዶች የአላህ ብቻ ናቸው። (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ (ማለትም ተወረደልኝ)።
(19) እነሆም የአላህ ባሪያ (ሙሐመድ አላህን) የሚጠራው ሆ በተነሳ ጊዜ (ጋኔ ች) በእርሱ ላይ ድርብርቦች ሊሆኑ ቀረቡ።
(20) (ሙሐመድ ሆይ!) እኔ የማመልከው ጌታዬን ብቻ ነው። በእርሱም አንድንም አላጋራም በል።
(21) እኔ ለእናንተ ጉዳትንም ማቅናትንም አልችልም በል።
(22) እኔ[4] ከአላህ (ቅጣት) አንድም አያድነኝም። ከእርሱም ሌላ መጠጊያን አላገኝም በል።
(23) ከአላህ የሆነ ማድረስን መልክቶቹንም በስተቀር (አልችልም) ። አላህንና መልዕክተኛውንም የሚያምፅ ሰው ለእርሱ የገሀነም እሳት አለው። በውስጧ ዘላለም ዘውታሪዎች ሲሆኑ።
(24) የሚስፈራሩበትንም ባዩ ጊዜ ረዳተ ደካማ ቁጥሩም አነስተኛ የሆነው ማን እንደሆነ በእርግጥ ያውቃሉ።
(25) የምትስፈራሩበት ነገር ቅርብ ወይም ጌታዬ ለእርሱ የተወሰነ ጊዜን የሚያደርግለት (ሩቅ) መሆኑን አላውቅም በላቸው።
(26) (እርሱ) ሩቁን ምስጢር አዋቂ ነው፤ በምስጢሩም ላይ አንድንም አያሳውቅም።
(27) ከመልዕክተኛ[5] ለወደደው ቢሆን እንጂ (ለሌላ አይገልጽም)። ለእርሱም ከበስተፊቱም ከበስተኋላውም ጠባቂዎችን ያደርግለታል።
(28) ከእነሱ ዘንድ ባለው ነገር ዕውቀት የከበበና ነገሩንም ሁሉ በቁጥር ያጠቃለለ ሲሆን የጌታቸውን መልዕክቶች ያደረሱ መሆናቸውን ያውቅ ዘንድ (ጠባቂ ያደርጋል)።[6]

---

[1] በማለትም ተወረደልኝ።

[2] **16ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክኒያት፡-** ቁረይሾች ለሰባት አመት የተራብበትን ጊዜ ለማስ ወስ ነው። (ሱዩጢ።)

[3] 18ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-
ጂኖች ለነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ፍቀድልን መስጊድ መጥተን ከእርስዎ ጋር ጀመዓ እንስገድ ስለአሏቸው ነው ። (ሱዩጢ።)

[4] **22ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-** አንድ የጂን መሪ፡- ሙሐመድ አላህ (عزوجل) እንዲጠብቀው ነው የሚፈልገው ። እኔ ግን ልጠብቀው እችል ነበር ብሎ ስለተናገረ ነው ። (ሱዩጢ።)

[5] ለእነሱ የፈቀደውን ያህል በወህይ አማካኝነት ከሰው የተሰወረ ነገሮችን በማሳወቅ ተአምሮቻቸው እንደሆኑ ይታወቃል። ኮኮብ ቆጣሪ፤ ጠጠር ወርዋሪ፤ ወፍ አባራሪ መዳፍ አንባቢ እና መሰሎች አላህ ከመረጣቸው ገይብን ከሚያውቁ ሰዎች አይደሉም ብሎም በአላህ ላይ የሚቀጥፉ ከሃዲዎች ናቸው።

[6] **ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።**
1.በአላህ (عزوجل) መንገድ ቀጥ ማለት ወደ ጥሩ ነገር እንደሚያደርስ ፣ 2.ንብረት ፈታኝ መሆኑንና ከገንዘብ ፈተና ነፃ የሚወጡት ትንሽ ሰዎች መሆናቸውን፣ 3.ከአላህ (عزوجل) ሌላ ማንንም ከችግር ለመዳን መጥራት መማፀን ክልክል ቢሆንም ከአላህ (عزوجل) ሌላ ለሆነ ነገር መስገድ ግን የበለጠ አስከፊ ስለመሆኑ፣ 4.ኸይርም ሆነ ሸር፣ ቅንነትም ሆነ ጥመት በአላህ (عزوجل) እጅ እንጂ በማንም እጅ እንዳልሆነ፤ 5. አላህንና (عزوجل) ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) ማስከፋት ለዱንያም ሆነ ለአኺራ ቅጣት ዋና ምክንያት መሆኑ፣ 6. የውሃን አስፈላጊነትና አንገብጋቢነት፡ 7.ሰዎችም ሆኑ ጋኔኖች ኢስላምን ለማዳከም ከፍተኛ ሙከራ እንዳደረጉ፣ 8.ጥቅምም ሆነ ጉዳት በአላህ (عزوجل) እጅ ብቻ እንደሆነ፣ ሌላው ቀርቶ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) እንኳን ራሳቸውን ለማዳን እንደማይችሉ፣ 9. የአላህ (عزوجل) መልዕክተኛ ሃላፊነት መልዕክታቸውን ለህዝብ ማድረስ ብቻ እንደነበር፤ 10. መስጊዶች የአላህ (عزوجل) ቤቶች መሆናቸውን፤ 11. ገይብ የተባለ ነገርን ሁሉ ማወቅ የአላህ (عزوجل) ብቸኛ ስልጣን ስለ መሆኑ፣ 12.ለአንዳንድ ነቢያት ወይም መላኢካ አንዳንድ ገይቦችን እንደሚያሳውቃቸውና እሱም ከሰይጣን ተንኮሎች ሁሉ በተጠበቀ መልኩ መሆኑን፣ 13.የአላህ (عزوجل) እውቀት ሁሉን ያጠቃለለ ስለ መሆኑና ከእሱ

سُورَةُ المُزَّمِّل

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡمُزَّمِّلُ ﴿١﴾ قُمِ ٱلَّيۡلَ إِلَّا قَلِيلٗا ﴿٢﴾ نِّصۡفَهُۥٓ أَوِ ٱنقُصۡ مِنۡهُ قَلِيلًا
﴿٣﴾ أَوۡ زِدۡ عَلَيۡهِ وَرَتِّلِ ٱلۡقُرۡءَانَ تَرۡتِيلًا ﴿٤﴾ إِنَّا سَنُلۡقِي عَلَيۡكَ قَوۡلٗا
ثَقِيلًا ﴿٥﴾ إِنَّ نَاشِئَةَ ٱلَّيۡلِ هِيَ أَشَدُّ وَطۡـٔٗا وَأَقۡوَمُ قِيلًا ﴿٦﴾ إِنَّ لَكَ فِي
ٱلنَّهَارِ سَبۡحٗا طَوِيلٗا ﴿٧﴾ وَٱذۡكُرِ ٱسۡمَ رَبِّكَ وَتَبَتَّلۡ إِلَيۡهِ تَبۡتِيلٗا ﴿٨﴾
رَّبُّ ٱلۡمَشۡرِقِ وَٱلۡمَغۡرِبِ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ فَٱتَّخِذۡهُ وَكِيلٗا ﴿٩﴾ وَٱصۡبِرۡ
عَلَىٰ مَا يَقُولُونَ وَٱهۡجُرۡهُمۡ هَجۡرٗا جَمِيلٗا ﴿١٠﴾ وَذَرۡنِي وَٱلۡمُكَذِّبِينَ
أُوْلِي ٱلنَّعۡمَةِ وَمَهِّلۡهُمۡ قَلِيلًا ﴿١١﴾ إِنَّ لَدَيۡنَآ أَنكَالٗا وَجَحِيمٗا ﴿١٢﴾
وَطَعَامٗا ذَا غُصَّةٖ وَعَذَابًا أَلِيمٗا ﴿١٣﴾ يَوۡمَ تَرۡجُفُ ٱلۡأَرۡضُ وَٱلۡجِبَالُ
وَكَانَتِ ٱلۡجِبَالُ كَثِيبٗا مَّهِيلًا ﴿١٤﴾ إِنَّآ أَرۡسَلۡنَآ إِلَيۡكُمۡ رَسُولٗا شَٰهِدًا
عَلَيۡكُمۡ كَمَآ أَرۡسَلۡنَآ إِلَىٰ فِرۡعَوۡنَ رَسُولٗا ﴿١٥﴾ فَعَصَىٰ فِرۡعَوۡنُ ٱلرَّسُولَ
فَأَخَذۡنَٰهُ أَخۡذٗا وَبِيلٗا ﴿١٦﴾ فَكَيۡفَ تَتَّقُونَ إِن كَفَرۡتُمۡ يَوۡمٗا يَجۡعَلُ
ٱلۡوِلۡدَٰنَ شِيبًا ﴿١٧﴾ ٱلسَّمَآءُ مُنفَطِرُۢ بِهِۦۚ كَانَ وَعۡدُهُۥ مَفۡعُولًا ﴿١٨﴾
إِنَّ هَٰذِهِۦ تَذۡكِرَةٞۖ فَمَن شَآءَ ٱتَّخَذَ إِلَىٰ رَبِّهِۦ سَبِيلًا ﴿١٩﴾

## 73 ኛው ሱራ፡-የተከናናቢው ምዕራፍ።[1] (ሱረቱ አል-ሙዘሚል) አንቀጾቹ 20 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 አንተ[2] ተከናናቢው ሆይ።[3]
2 ሌሊቱን ሁሉ ጥቂት ሲቀር ቁም (ስገድ)።
3 ግማሹን (ቁም) ወይም ከእርሱ ጥቂትን ቀንስ።
4 ወይም በእርሱ ላይ ጨምር። ቁርአንንም በዝግታ ማንበብን አንብብ[4]።
5 እኛ በአንተ ላይ ከባድ ቃልን እንጥላለንና።
6 ሌሊት መነሳት እርሷ (ሕዋሳትንና ልብን) ለማስማማት በጣም ብርቱ ናት። ለማንበብም ትክክለኛ ናት።
7 ለአንተ በቀን ውስጥ ረዥም መዘዋወር አለህ።
8 የጌታህንም ስም አውሳ። ወደ እርሱም (መገዛት) መቋረጥን ተቋረጥ።
9 (እርሱም) የምስራቅና የምእራብ ጌታ ነው። ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። መጠጊያ አድርገህም ያዘው።
10 (ከሓዲዎች) በሚሉትም ላይ ታገሥ። መልካምንም መተው ተዋቸው።
11 የድሎት ባለቤቶችም ከሆኑት አስተባባዮች ጋር ተወኝ። ጥቂትንም ጊዜ አቆያቸው።
12 ከእኛ ዘንድ ከባድ ማሰሪያዎች፣ እሳትም አሉና።
13 የሚያንቅ ምግብም፣ አሳማሚ ቅጣትም (አለ)።
14 ምድርና ጋራዎች በሚርገፈገፉበት፣ ጋራዎችም ፈሳሽ የአሸዋ ክምር በሚሆኑበት ቀን።
15 እኛ በእናንተ ላይ መስካሪ መልእክተኛን ወደ እናንተ ላክን። ወደ ፈርዖን መልእክተኛን እንደላክን።
16 ፈርዖንም መልእክተኛውን አመፀ። ብርቱ መያዝንም ያዝነው።
17 ብትክዱ ልጆችን ሸበቶዎች የሚያደርገውን ቀን (ቅጣት) እንዴት ትጠበቃላችሁ !
18 ሰማዩ በእርሱ (በዚያ ቀን) ተሰንጣቂ ነው። ቀጠሮው ተፈፃሚ ነው።

እውቀት የሚሰወር አንድም ነገር አለመኖሩን፣ 14.ከአላህ (ﷻ) መልዕክተኞች በስተቀር ገይብን አውቃለሁ የሚሉ ሰዎች ሁሉ አባባላቸው ውድቅ እንደሆነ፤ 15.የነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) ነቢይነት ማረጋገጥና ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ለሰው ብቻ ሳይሆን ለጋኔንም መላካቸው 16. የቁርአንን ትልቅነትና የአላህ (ﷻ) ቃል መሆኑን መግለፅ፣ 17. ሽርክን አውግዞ ተውሂድን ማረጋገጥና ማሞገስ፣ 18. ሰዎች ሊዋሹ እንደሚችሉና ይህም እንደማይገባ፣ 19. ኢማን የሌለው ሰው ቂል ሊባል እንደሚችል፤ 20. የብዙ ሰዎች መንገድ መልቀቅ የሚፈጠረው በሚከተሉት አካል ላይ ከንቱ እምነት በማሳደር መሆኑን፤ 21. በጂን መጠበቅና መታገዝ ክልክል ከመሆኑም በላይ ወደ ሽርክ ሊያደርስ እንደሚችል፤ 22. ጂን የሚባል ፍጡር መኖሩንና ልክ እንደሰው የታዘዙና የተከለከሉ ስለ መሆናቸው፤ 23. በመላኢካና በጋኔን መካከል ያለውን ግልፅ ግንኙነት መግለፅና ማብራራት፣ 24. ከጋኔኖች መካከል በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ነቢይነት አማኞችና መልካም ሰሪዎች መኖራቸውን፣ 25. ልዩነትን ማስፋፋትና ስሜትን መከተል ተገቢ አለመሆኑ፣ 26.እውነትን መፈለግና ፍትሀዊነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ መጠቆም፣ 27.ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ተልከው ቁርአን መውረድ ከጀመረ በኋላ የጥንቆላ መስመሮች እንደተዘጉ፣ 28.ጂኖች ነቢዩ ሙሀመድን (ﷺ) ለማዳመጥ የነበራቸው ከፍተኛ ጉጉት፤ 29. ጂኖች ልክ እንደሰው ልጅ ብዙ አይነቶች እንደሆኑ፤ 30. አላህ (ﷻ) ሃያልና ማንም የማያመልጠው መሆኑን እንማራለን።

[1] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው።

[2] 1ኛው አንቀጽ የወረደበት ምክንያት፡-
ሀ/ ቁረይሾች ዳር-አል-ነድዋ በተባለው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተሰብስበው ስለ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)፡- ምን እንበል በሚል ተወያይተው የደረሱበት አቋም ለነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ስለ ደረሳቸው እና በልብሳቸው ተሸፋፍነው ሳሉ ነው። ሱዩጢ ።
ለ/ ነብዩ ሙሐመድ መጀመሪ ወህይ በወረደላቸው ጊዜ ደንግጠው ሸፍኑኝ ደርቡልኝ ብለው ስለነበር ይህንኑ ትዝታ ለማስታወስ ነው ።

[3] ነቢዩ መላኩ ጂብሪል መምጣት እንደጀመረ እየፈሩ ይከናነቡ ስለ ነበር ነው በዚህ አይነት ጥሪ የጠራቸው።

[4] ሙስሊምና አህመድ በዘገቡት ሀዲስ ሳዕድ ኢብኑ ሒሻም እናታችን አኢሻን የነብዩን የሌሊት ሶላት ንገረኝ ብለው ሲጠይቋቸው ይህን ምዕራፍ አታነብምን? አላቸው ሳዕድም አንብቢያለሁ አለ ከዚያም በመቀጠል አላህ የሌሊትን ሶላት በምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ግዳጅ አድርጎ ነብዩና ሰሃቦች ለአንድ አመት ከቆሙ በኋላ የምዕራፉን መጨረሻ በማውረድ አቀለለው ብለዋል ። ግዴታ የነበረው ሱና ሆኗል።

19 ይህቺ መገሰጫ ናት። (መዳንንም) የሻ /የፈለገ/ሰው ወደ ጌታው መንገድን ይይዛል።
20 አንተ ከሌሊቱ-[1] ሁለት እጅ ያነሰን፣ ግማሹንም፣ ሲሶውንም የምትቆም መሆንህን ጌታህ በእርግጥ ያውቃል። ከእነዚያም አብረውህ ካሉት ከፊሎች (የሚቆሙ መሆናቸውን ያውቃል)። አላህ ሌሊትንና ቀንን ይለካል። (ሌሊቱን) የማታዳርሱት መሆናችሁን ዐወቀ፤ በእናንተ ላይም (ወደ ማቃለል) ተመለሰላችሁ። ስለዚህ ከቁርአን (በስግደት) የተቻላችሁን አንብቡ። ከእናንተ ውስጥ በሽተኞች፣ ሌሎችም ከአላህ ችሮታ ለመፈለግ በምድር ላይ የሚጓዙ፣ ሌሎችም በአላህ መንገድ (ሃይማ ት) የሚጋደሉ እንደሚ ኑ ዐወቀ፣ (አቃለለላቸውም)። ከእርሱም የተቻላችሁን አንብቡ። ሶላትንም ስገዱ። ዘካንም ስጡ። ለአላህም መልካም ብድርን አበድሩ። ከመልካም ስራም ለነፍሶቻችሁ የምታስቀድሙትን ሁሉ እርሱ የተሻለና በምንዳም ታላቅ ሆ ከአላህ ዘንድ ታገኙታላችሁ። አላህን ምህረትን ለምኑት። አላህ በጣም መሓሪና አዛኝ ነውና [2]።

## 74 ኛው፡-የልብስ ደራቢው ምዕራፍ/።[3]
## (ሱረቱ አል-ሙደሲር ነው)
## አንቀጾች 56 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 አንተ[4] ልብስ ደራቢው ሆይ !

﴿ إِنَّ رَبَّكَ يَعْلَمُ أَنَّكَ تَقُومُ أَدْنَىٰ مِن ثُلُثَيِ ٱلَّيْلِ وَنِصْفَهُۥ وَثُلُثَهُۥ وَطَآئِفَةٌ
مِّنَ ٱلَّذِينَ مَعَكَ ۚ وَٱللَّهُ يُقَدِّرُ ٱلَّيْلَ وَٱلنَّهَارَ ۚ عَلِمَ أَن لَّن تُحْصُوهُ فَتَابَ
عَلَيْكُمْ ۖ فَٱقْرَءُوا۟ مَا تَيَسَّرَ مِنَ ٱلْقُرْءَانِ ۚ عَلِمَ أَن سَيَكُونُ مِنكُم مَّرْضَىٰ ۙ
وَءَاخَرُونَ يَضْرِبُونَ فِى ٱلْأَرْضِ يَبْتَغُونَ مِن فَضْلِ ٱللَّهِ ۙ وَءَاخَرُونَ
يُقَـٰتِلُونَ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ ۖ فَٱقْرَءُوا۟ مَا تَيَسَّرَ مِنْهُ ۚ وَأَقِيمُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُوا۟
ٱلزَّكَوٰةَ وَأَقْرِضُوا۟ ٱللَّهَ قَرْضًا حَسَنًا ۚ وَمَا تُقَدِّمُوا۟ لِأَنفُسِكُم مِّنْ خَيْرٍ تَجِدُوهُ
عِندَ ٱللَّهِ هُوَ خَيْرًا وَأَعْظَمَ أَجْرًا ۚ وَٱسْتَغْفِرُوا۟ ٱللَّهَ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌۢ ﴿٢٠﴾

## سُورَةُ المُدَّثِّرِ

ترتيبها ٧٤ — آياتها ٥٦

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَـٰنِ ٱلرَّحِيمِ

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلْمُدَّثِّرُ ﴿١﴾ قُمْ فَأَنذِرْ ﴿٢﴾ وَرَبَّكَ فَكَبِّرْ ﴿٣﴾ وَثِيَابَكَ فَطَهِّرْ ﴿٤﴾
وَٱلرُّجْزَ فَٱهْجُرْ ﴿٥﴾ وَلَا تَمْنُن تَسْتَكْثِرُ ﴿٦﴾ وَلِرَبِّكَ فَٱصْبِرْ ﴿٧﴾
فَإِذَا نُقِرَ فِى ٱلنَّاقُورِ ﴿٨﴾ فَذَٰلِكَ يَوْمَئِذٍ يَوْمٌ عَسِيرٌ ﴿٩﴾ عَلَى ٱلْكَـٰفِرِينَ
غَيْرُ يَسِيرٍ ﴿١٠﴾ ذَرْنِى وَمَنْ خَلَقْتُ وَحِيدًا ﴿١١﴾ وَجَعَلْتُ لَهُۥ مَالًا
مَّمْدُودًا ﴿١٢﴾ وَبَنِينَ شُهُودًا ﴿١٣﴾ وَمَهَّدتُّ لَهُۥ تَمْهِيدًا ﴿١٤﴾ ثُمَّ يَطْمَعُ
أَنْ أَزِيدَ ﴿١٥﴾ كَلَّآ ۖ إِنَّهُۥ كَانَ لِـَٔايَـٰتِنَا عَنِيدًا ﴿١٦﴾ سَأُرْهِقُهُۥ صَعُودًا ﴿١٧﴾

2 ተነሳና አስጠንቅቅ።
3 ጌታህን አክብር።
4 ልብስህን አጥራ።
5 ጣዖትን ራቅ።
6 ማብዛትንም የምትፈልግ ሆነህ አትለግስ።
7 ለጌታህም (ትእዛዝ) ታገሥ።
8 በቀንዱም በተነፋ ጊዜ (ነገሩ ይበረታል)።
9 ይህም (ጊዜ) ያ ቀን አስቸጋሪ ቀን ነው።
10 በከሓዲዎች ላይ ገር ያልሆነ ነው።
11 አንድ[5] ሆ ከፈጠርኩት ሰው ጋር

---

[1] 20ኛው አንቀጽ የወረደበት ምክኒያት፡- «አንተ ተከናናቢው ሆይ ሌሊቱን ሙሉ ጥቂት ሲቀር ቁም /ስገድ»የሚለው ሲወርድ አንድ አመት ሙሉ በሰላት ቁመው እግራቸው ሲያብጥና ሲቆሳስል ነው። (ሱዩጢ።)

[2] **ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።** **1.** የሌሊት ሰላት ለነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ግዴታ እንደነበርና ለሙስሊሞች አስፈላጊነቱን ማረጋገጥ፤ የመልካም ሰዎች ተግባር ስለመሆኑም መጠቆም፣ **2.** ቁርአንን ጭር ባለ ሌሊት ብሎም በጥሞና ማንበብ አስፈላጊ ስለ መሆኑ፣ **3.**የሌሊት ሰላት ከቀን ሰላት በአጅር የበለጠ መሆኑን፣ **4.**ስለ ሌሊት ሰላት ግፊት ማሳደር፤ **5.** በየትኛውም መልክ አላህን (عز وجل) መዘከር አስፈላጊ ስለ መሆኑ፣ **6.**በየትኛው ጊዜ ጉዳይን ለማውጣት በአላህ (عز وجل) ላይ መመካት ተገቢ ስለ መሆኑ፣ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ትዕግስት እንዲያደርጉ መታዘዛቸውንና አስተባባዮች ስለሚጠብቃቸው ቅጣት፤ **7.** ለሁሉም ነገር የትግስትን አስፈላጊነት፣ **8.** የነቢያትን (عليهم السلام) ሐቀኝነት ማረጋገጥና እነሱን ማስተባበል ለክፋ ቅጣት እንደሚዳርግ፣ **9.** የሙቶ መነሳትን እርግጠኝነት የተለያዩ ሁኔታዎችን በመጥቀስ ማረጋገጥ **10.** ነቢዩ ሙሐመድም (ﷺ) ሆነ ባልደረቦቻቸው ይሰሩት የነበረውን የለሊት ሰላት በቁርአን ታዘው እንደነበረ፣ **11.** የሌሊት ሰላት ግዴታነት መሻሩን መጠቆም፣ **12.** ሰላትን መስገድና ዘካን መስጠት ኢስላማዊ ግዴታ ስለመሆኑ፣ **13.** ከየትኛውም ዒባዳ ዘርፍ ከግዴታው በተጨማሪ መስራት በኢስላም አስፈላጊ ስለመሆኑ፣ **14.** የሰው ልጅ ወንጀል በሰራበት ጊዜ የአላህን (عز وجل) ምህረት ለሙስሊም መጠየቅ ግዴታ ስለ መሆኑና በሌላ ጊዜ ሱና ስለ መሆኑ ።

[3] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው።

[4] **1ኛ**ው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-
**ሀ.** ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አንድ ወር በሒራ ዋሻ ቆይተው ሲመለሱና ዋሻው ውስጥ ባሉበት ተጠርተው በቀኝ በግራ በፊት በኋላ ሲመለከቱ ምንም ሳያዩ ሁለተኛ ሲጠሩ ራሳቸውን ወደ ሰማይ ሲያነሱ ጅብሪልን በአየር ላይ ሁኖ አዩትና ደንግጠው ወደ ቤት በመሄድ ሸፍኑኝ ሸፍኑኝ አሉ። በዚህ ምክንያት ነበር የወረደው ። (ዋሂዲና ሱዩጢ።)
**ለ.** ቁረይሾች ዳር-አል-ነድዋ በተባለው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተሰብስበው ሰለ ሙሐመድ ምን እንበል በሚል ተወያይተው የደረሱበት አቋም ለነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ስለ ደረሳቸው እና በልብሳቸው ተሸፋፍነው ሳሉ ነው ። (ሱዩጢ።)

[5] **11ኛ**ው አንቀፅ የወረደበት ምክያት፡- ወሊድ ቢን ሙጊራህ ወደ ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) መጥቶ ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) የቁርአን አናቅፅ አንብበውለት ትንሽ

إِنَّهُۥ فَكَّرَ وَقَدَّرَ ﴿١٨﴾ فَقُتِلَ كَيْفَ قَدَّرَ ﴿١٩﴾ ثُمَّ قُتِلَ كَيْفَ قَدَّرَ ﴿٢٠﴾ ثُمَّ نَظَرَ
﴿٢١﴾ ثُمَّ عَبَسَ وَبَسَرَ ﴿٢٢﴾ ثُمَّ أَدْبَرَ وَٱسْتَكْبَرَ ﴿٢٣﴾ فَقَالَ إِنْ هَٰذَآ إِلَّا سِحْرٌ
يُؤْثَرُ ﴿٢٤﴾ إِنْ هَٰذَآ إِلَّا قَوْلُ ٱلْبَشَرِ ﴿٢٥﴾ سَأُصْلِيهِ سَقَرَ ﴿٢٦﴾ وَمَآ أَدْرَىٰكَ
مَا سَقَرُ ﴿٢٧﴾ لَا تُبْقِى وَلَا تَذَرُ ﴿٢٨﴾ لَوَّاحَةٌ لِّلْبَشَرِ ﴿٢٩﴾ عَلَيْهَا تِسْعَةَ عَشَرَ
﴿٣٠﴾ وَمَا جَعَلْنَآ أَصْحَٰبَ ٱلنَّارِ إِلَّا مَلَٰٓئِكَةً ۙ وَمَا جَعَلْنَا عِدَّتَهُمْ إِلَّا فِتْنَةً
لِّلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لِيَسْتَيْقِنَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ وَيَزْدَادَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ إِيمَٰنًا ۙ
وَلَا يَرْتَابَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ وَٱلْمُؤْمِنُونَ ۙ وَلِيَقُولَ ٱلَّذِينَ فِى قُلُوبِهِم مَّرَضٌ
وَٱلْكَٰفِرُونَ مَاذَآ أَرَادَ ٱللَّهُ بِهَٰذَا مَثَلًا ۚ كَذَٰلِكَ يُضِلُّ ٱللَّهُ مَن يَشَآءُ وَيَهْدِى
مَن يَشَآءُ ۚ وَمَا يَعْلَمُ جُنُودَ رَبِّكَ إِلَّا هُوَ ۚ وَمَا هِىَ إِلَّا ذِكْرَىٰ لِلْبَشَرِ ﴿٣١﴾ كَلَّا
وَٱلْقَمَرِ ﴿٣٢﴾ وَٱلَّيْلِ إِذْ أَدْبَرَ ﴿٣٣﴾ وَٱلصُّبْحِ إِذَآ أَسْفَرَ ﴿٣٤﴾ إِنَّهَا لَإِحْدَى
ٱلْكُبَرِ ﴿٣٥﴾ نَذِيرًا لِّلْبَشَرِ ﴿٣٦﴾ لِمَن شَآءَ مِنكُمْ أَن يَتَقَدَّمَ أَوْ يَتَأَخَّرَ ﴿٣٧﴾ كُلُّ
نَفْسٍۭ بِمَا كَسَبَتْ رَهِينَةٌ ﴿٣٨﴾ إِلَّآ أَصْحَٰبَ ٱلْيَمِينِ ﴿٣٩﴾ فِى جَنَّٰتٍ يَتَسَآءَلُونَ
﴿٤٠﴾ عَنِ ٱلْمُجْرِمِينَ ﴿٤١﴾ مَا سَلَكَكُمْ فِى سَقَرَ ﴿٤٢﴾ قَالُوا۟ لَمْ نَكُ مِنَ
ٱلْمُصَلِّينَ ﴿٤٣﴾ وَلَمْ نَكُ نُطْعِمُ ٱلْمِسْكِينَ ﴿٤٤﴾ وَكُنَّا نَخُوضُ مَعَ
ٱلْخَآئِضِينَ ﴿٤٥﴾ وَكُنَّا نُكَذِّبُ بِيَوْمِ ٱلدِّينِ ﴿٤٦﴾ حَتَّىٰٓ أَتَىٰنَا ٱلْيَقِينُ ﴿٤٧﴾

ተዎኝ እኔ እበቃሃለሁ።
12 ለእርሱም የተዘረጋን ገንዘብ (በዓይነቱ) ያደረግሁለት።
13 (በአደባባዩ) ተገኝ የሆኑ ወንዶች ልጆችንም።
14 ለእርሱም (ኑሮውን) መዘርጋትን የዘረጋሁለት (ከሆነ ሰው ጋር ተዎኝ)።
15 ከዚያም ልጨምርለት ይከጅላል።
16 ይከልከል፤ እርሱ ለአንቀጾቻችን በእርግጥ ተቃዋሚ ነበር።
17 በእርግጥ ችግርን አስገድደዋለሁ።
18 እርሱ (በቁርአን ነገር) አሰበ፤ ገመተም።
19 ተረገመ፤ እንዴት ገመተ !
20 ከዚያም ተረገመ። እንዴት ገመተ!
21 ከዚያም እንደገና (በቁርአኑ ነገር) ተመለከተ።
22 ከዚያም ፊቱን አጨፈገገ አ ማተረም።
23 ከዚያም (ከማመን) ዞ ራም።
24 አለም፡- ይህ (ከሌላ) የሚቀዳ ድግምት እንጅ ሌላ አይደለም።
25 ይህ የሰው ቃል እንጅ ሌላ አይደለም።
26 በሰቀር ውስጥ በእርግጥ አገባዋለሁ።

ለስለስ ያለ መስሎት ይኸው ክስተት ለአቡጀሕል ስለደረሰው በፍጥነት ወደ እሱ በመምጣት፡- አጐቴ ሆይ፣ ሰዎች ለአንተ ገንዘብ ሊሰጡህ እያሰባሰቡ ነው። ምክንያቱም ወደ ሙሐመድ አዘንብለሀል መባል ስለተሰማ ነው አለው ። (ሱዩጢ።)

27 ሰቀር ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ ?
28 (ያገኘችውን ሁሉ) አታስቀርም። አትተውምም።
29 ቆዳን በጣም አክሳይ ናት።
30 በእርሷም[1] ላይ አስራ ዘጠኝ (ዘበኞች) አሉባት[2]።
31 የእሳትን[3] ዘበኞች መላእክት እንጅ ሌላ አላደረግንም። ቁጥራቸውንም ለእነዚያ ለካዱት መፈተኛ እንጂ አላደረግንም። እነዚያ መጽሐፍን የተሰጡት እንዲያረጋግጡ፣ እነዚያም ያመኑት እምነትን እንዲጨምሩ፤ እነዚያም መጽሐፍን የተሰጡትና ምዕምና ቹ እንዳይጠራጠሩ፣ እነዚያም በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸው (መናፍቃን)፣ ከሓዲዎችም፡- አላህ በዚህ ቁጥር ምን ምሳሌ ሽቷል? እንዲሉ (እንጅ አላደረግንም)። እንደዚሁ አላህ የሚሻውን ያጠማል። የሚሻውንም ያቀናል። የጌታህንም ሰራዊት (ልክ) ከእርሱ በቀር ማንም አያውቅም። እርሷም (የሰቀር እሳት) ለሰዎች መገሠጫ እንጂ ሌላ አይደለችም።
32 (ከክሕደት) ይከልከሉ። በጨረቃ እምላለሁ።
33 በሌሊቱም በሄደ ጊዜ።
34 በንጋቱም ባበራ ጊዜ።
35 እርሷ (ሰቀር) ከታላላቆቸ (አደጋዎች) አንዷ ናት።
36 ለሰዎች አስፈሪ ስትሆን።
37 ከእናንተ (ወደ በጎ ነገር) መቅደምን ወይም ወደ ኋላ መቅረትን ለሻ ሰው (አስፈራሪ ስትሆን)።
38 ነፍስ ሁሉ በሰራችው ስራ ተያዥ ናት።
39 የቀኝ ባለቤቶች ብቻ ሲቀሩ።
40 (እነርሱ) በገነቶች ውስጥ ይጠያየቃሉ።
41 ከአመፀኞች ሁኔታ።
42 (ይሏቸዋልም)፡- በሰቀር ውስጥ ምን አገባችሁ?
43 (እነርሱም)ይላሉ፡- ከሰጋጆች አልነበርንም።
44 ለድሆችም የምናበላ አልነበርንም።
45 ከዘባራቂዎችም ጋር እንዘባርቅ ነበርን።
46 በፍርዱ ቀንም እናስተባብል ነበር።
47 እርግጠኛው (ሞት) እስከ መጣን ድረስ።
48 የአማላጆችም ምልጃ አትጠቅማቸውም።
49 ከግሣጼም /ከቁርአን/ የሚያፈገፍጉት እነርሱ ምን አላቸው ?
50 እነሱ ልክ ደንባሪዎች የሜዳ አህዮች ይመስላሉ።
51 ከአንበሳ የሸሹ።

[1] 30ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የተወሰኑ አይሁድ ወደ ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) በመምጣት የገሀነም ዘበኞች ስንት ናቸው ብለው በመጠየቅ ሲያፋጥጧቸው ነው ። (ሱዩጢ።)

[2] ነቢዩ የሚለዉን ሲያነቡ አንዳንድ ሰዎች ይህማ ትንሽ ቁጥር ነው። አሸንፈን ገነትን መውረስ እንችላለን ማለት ነው ሲሉ ነው።

[3] 31ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክኒያት፡- አቡጀህል አንድ ቀን ቁረይሽ ሙሐመድ እንደሚለው የአላህ (ﷻ) ሰራዊቶች በገሀነም ያሉት አሥራ ዘጠኝ ናቸው ይላል። እናንተ ደግሞ ብዙዎች ናችሁ። ለመሆኑ መቶ ሁናችሁ አንድን ማሸነፍ ያቅታችኋልን? በማለቱ ነው። (ሱዩጢ።)

52 ይልቁንም[1] ከእነርሱ እያንዳንዱ ሰው
የተዘረጉ ጽሁፎችን እንዲሰሰጥ ይፈልጋል።
53 ይከልከሉ። ይልቁንም የመጨረሻይቱን
ዓለም (ቅጣት) አይፈሩም።
54 ስለዚህ የሻ/የፈለገ/ ሰው ይገሠጽበታል።
55 አላህ ካልሻ/ካልፈለገ/ በስተቀር
አይገሠጹም። እርሱ (አላህ) የመፈራት
ባለቤት፤ የምህረትም ባለቤት ነው፡[2]፡

## 75 ኛው ምዕራፍ ፡ሱረቱል ቂያማህ[3]። የትንሳኤ ምእራፍ ነው) አንቀጾቹ 40 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም
አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።
1 (ነገሩ ከሓዲዎች እንደሚሉት)
አይደለም፤ በትንሳኤ ቀን እምላለሁ።
2 (ራሷን) ወቃሽ በሆነች ነፍስም
እምላለሁ፤ (በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ)።
3 ሰው[4] አጥንቶቹን አለመሰብሰባችንን ያስባልን?
4 አይደለም (እንዴታ)፤ ጣቶቹን ፊት
እንደ ነበሩ በማስተካከል ላይ ቻዮች

فَمَا تَنفَعُهُمۡ شَفَٰعَةُ ٱلشَّٰفِعِينَ ﴿٤٨﴾ فَمَا لَهُمۡ عَنِ ٱلتَّذۡكِرَةِ مُعۡرِضِينَ
﴿٤٩﴾ كَأَنَّهُمۡ حُمُرٞ مُّسۡتَنفِرَةٞ ﴿٥٠﴾ فَرَّتۡ مِن قَسۡوَرَةِۭ ﴿٥١﴾ بَلۡ يُرِيدُ
كُلُّ ٱمۡرِيٕٖ مِّنۡهُمۡ أَن يُؤۡتَىٰ صُحُفٗا مُّنَشَّرَةٗ ﴿٥٢﴾ كَلَّاۖ بَل لَّا يَخَافُونَ
ٱلۡأٓخِرَةَ ﴿٥٣﴾ كَلَّآ إِنَّهُۥ تَذۡكِرَةٞ ﴿٥٤﴾ فَمَن شَآءَ ذَكَرَهُۥ ﴿٥٥﴾
وَمَا يَذۡكُرُونَ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُۚ هُوَ أَهۡلُ ٱلتَّقۡوَىٰ وَأَهۡلُ ٱلۡمَغۡفِرَةِ ﴿٥٦﴾

ترتيبها ٧٥ — سُورَةُ القِيَامَةِ — آياتها ٤٠

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

لَآ أُقۡسِمُ بِيَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ ﴿١﴾ وَلَآ أُقۡسِمُ بِٱلنَّفۡسِ ٱللَّوَّامَةِ ﴿٢﴾ أَيَحۡسَبُ
ٱلۡإِنسَٰنُ أَلَّن نَّجۡمَعَ عِظَامَهُۥ ﴿٣﴾ بَلَىٰ قَٰدِرِينَ عَلَىٰٓ أَن نُّسَوِّيَ بَنَانَهُۥ ﴿٤﴾ بَلۡ
يُرِيدُ ٱلۡإِنسَٰنُ لِيَفۡجُرَ أَمَامَهُۥ ﴿٥﴾ يَسۡـَٔلُ أَيَّانَ يَوۡمُ ٱلۡقِيَٰمَةِ ﴿٦﴾ فَإِذَا بَرِقَ ٱلۡبَصَرُ
﴿٧﴾ وَخَسَفَ ٱلۡقَمَرُ ﴿٨﴾ وَجُمِعَ ٱلشَّمۡسُ وَٱلۡقَمَرُ ﴿٩﴾ يَقُولُ ٱلۡإِنسَٰنُ يَوۡمَئِذٍ
أَيۡنَ ٱلۡمَفَرُّ ﴿١٠﴾ كَلَّا لَا وَزَرَ ﴿١١﴾ إِلَىٰ رَبِّكَ يَوۡمَئِذٍ ٱلۡمُسۡتَقَرُّ ﴿١٢﴾ يُنَبَّؤُاْ ٱلۡإِنسَٰنُ
يَوۡمَئِذِۭ بِمَا قَدَّمَ وَأَخَّرَ ﴿١٣﴾ بَلِ ٱلۡإِنسَٰنُ عَلَىٰ نَفۡسِهِۦ بَصِيرَةٞ ﴿١٤﴾ وَلَوۡ أَلۡقَىٰ
مَعَاذِيرَهُۥ ﴿١٥﴾ لَا تُحَرِّكۡ بِهِۦ لِسَانَكَ لِتَعۡجَلَ بِهِۦٓ ﴿١٦﴾ إِنَّ عَلَيۡنَا جَمۡعَهُۥ
وَقُرۡءَانَهُۥ ﴿١٧﴾ فَإِذَا قَرَأۡنَٰهُ فَٱتَّبِعۡ قُرۡءَانَهُۥ ﴿١٨﴾ ثُمَّ إِنَّ عَلَيۡنَا بَيَانَهُۥ ﴿١٩﴾

ስንሆን እንሰበስባቸዋለን።
5 ይልቁን ሰው በፊቱ ባለው ነገር
(በትንሳኤ) ሊያስተባብል ይፈልጋል።
6 የትንሣዔው ቀን መቼ ነው?ሲል
ይጠይቃል።
7 ዓይንም በዋለለ ጊዜ።
8 ጨረቃም በጨለመ ጊዜ፤
9 ፀሐይና ጨረቃም በተሰበሰቡ ጊዜ፤
10 ሰው በዚያ ቀን መሸሻው የት ነው? ይላል።
11 ይከልከል፤ ምንም መጠጊያ የለም።
12 በዚያ ቀን መርጊያው ወደ ጌታህ ብቻ ነው።
13 ሰው በዚያ ቀን ባስቀደመውና
ባስቆየው ሁሉ ይነገራል።
14 በእርግጥ ሰው በነፍሱ ላይ አስረጅ ነው[5]።
15 ምክንያቶቹን ሁሉ ቢያመጣም እንኳ
አይሰማም።
16 በእርሱ[6] (በቁርዓን ንባብ) ልትቸኩል
ምላስህን በርሱ አታላውስ።
17 (በልብህ ውስጥ) መሰብሰቡና ማንበቡ
በኛ ላይ ነውና።

---

[1] 52ኛው አንቀጽ የወረደበት ምክንያት፡- መኮች ሙሐመድ የሚለው ትክክል ከሆነ በያንዳንዳችን ራስጌ ከእሳት ነፃ ናችሁ የሚል ጽሑፍ ያስልክልን በማለታቸው ነው። (ሱዩጢ።)

[2] **ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።** 1. ዳእዋ ከሙስሊም ባህሪያት አንዱ ስለመሆኑ፣ 2. በአላህ (ﷻ) ስሞችና ባህሪያት ዙሪያ ሊኖሩ የሚገባ ክብርና ግርማ ሞገስ፣ 3.ሙእሚን አካላቱም ይሁን ልብሱና ቦታው ንፁህ መሆን እንዳለበት፣ 4. ለሙስሊም ኩራት የማይገባው ስለ መሆኑ፣ 5.ለሙስሊም በምንም ነገር ላይ ትዕግስትን መላበስ እንደሚያስፈልገው፤ 6. ንብረትና ልጅ አላህ (ﷻ) የጠበቀው ሲቀር የኩራት መነሻዎች ስለ መሆናቸው፣ 7. የአላህን (ﷻ) ታአምሮች የሚክድ ሁሉ የከሃዲ ከሃዲ ስለመሆኑ፣ 8. የቁረይሾች ከሃዲ ወሊድ ብን ሙጊራህ ምን እንደሚደርስበት ማስተማር፣ 9. ገንዘብ ከአላህ (ﷻ) ፀጋዎች መካከል አንደኛው መሆኑና ማመስገኑ ተገቢ ስለ መሆኑ፤ 10. ልጆች የዚህች ዓለም ውበትና ጌጥ መሆናቸውን 11.እንደ ቁርአን ሁሉ ተውራትም ሆነ ኢንጂል እምነት የሚጨምር የሚቀንስ መሆኑን ማስተማራቸውን፣ 12.የገሃነም ዘበኞች ቁጥር ከአላህ (ﷻ) ሌላ ማንም እንደማያቃቸው፣ 13. ገሃነም ለሰዎች ማስፈራሪያ ስለ መሆኑ፣ 14.የገሀነም ዘበኞች ሃይለኛ መላዒኮች መሆናቸውን፤ 15. ከ38-55 ለገሀነም ከሚያበቁ ነገሮች መካከልና ከሐዲዎች እንደወገሸ አህያ እንደሚመስሉ ። 16. የትኛዋም ነፍስ በስራዋ እንደምትጠየቅ፣ 17. ከወንጀሎች ሁሉ ትልቁ ሶላት ማሳለፍና ዘካን መከልከል በውሸት ወሬ ውስጥ ራስን ማስገባትና ሙቶ መነሳትን አለማመን ስለመሆኑ፣ 18. በሺርክ ለሚሞቱ ሁሉ አሸማጋይ ሽማግሌ እንደሌላቸው፣ 19. የሰው ልጅ እምነት የመበላሸት መነሻው የእምነት ድክመት ስለመሆኑ፣ ኩራት የሚገባውና ወንጀልን መማር የሚችለው አንድ አላህ (ﷻ) ብቻ ስለ መሆኑ እንማራለን።

[3] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው።

[4] 3ኛው አንቀፅ-የወረደበት ምክኒየት፡- ዐምር ቢን ረቢይዓህ የተባለ ሰው ወደ ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) መጥቶ ቂያማ መቼ ነው? ሁኔታውስ እንዴት ነው? በማለት ጠየቃቸውና ዘርዝር አድርገው ሲነግሩት ያን ቀን ባየሁ ኖሮ አላምንህም ነበር ። ይህን አጥንት እስከሚሰበሰብ ድረስ ሲላቸው ነው ። ዋሂዲ።

[5] አካሎቹ ይመሰክሩበታል።

[6] **16ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-** ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ወህይ በሚወርድበት ጊዜ እንዳይጠፋቸው ለመደጋገም ምላሳቸውን ያንቀሳቅሱ ስለነበር ነው። ሱዩጢ ።

كَلَّا بَلْ تُحِبُّونَ ٱلْعَاجِلَةَ (٢٠) وَتَذَرُونَ ٱلْـَٔاخِرَةَ (٢١) وُجُوهٌ يَوْمَئِذٍ نَّاضِرَةٌ (٢٢)
إِلَىٰ رَبِّهَا نَاظِرَةٌ (٢٣) وَوُجُوهٌ يَوْمَئِذٍۭ بَاسِرَةٌ (٢٤) تَظُنُّ أَن يُفْعَلَ بِهَا فَاقِرَةٌ (٢٥)
كَلَّآ إِذَا بَلَغَتِ ٱلتَّرَاقِىَ (٢٦) وَقِيلَ مَنْ ۜ رَاقٍ (٢٧) وَظَنَّ أَنَّهُ ٱلْفِرَاقُ (٢٨) وَٱلْتَفَّتِ
ٱلسَّاقُ بِٱلسَّاقِ (٢٩) إِلَىٰ رَبِّكَ يَوْمَئِذٍ ٱلْمَسَاقُ (٣٠) فَلَا صَدَّقَ وَلَا صَلَّىٰ
(٣١) وَلَٰكِن كَذَّبَ وَتَوَلَّىٰ (٣٢) ثُمَّ ذَهَبَ إِلَىٰٓ أَهْلِهِۦ يَتَمَطَّىٰٓ (٣٣) أَوْلَىٰ لَكَ
فَأَوْلَىٰ (٣٤) ثُمَّ أَوْلَىٰ لَكَ فَأَوْلَىٰٓ (٣٥) أَيَحْسَبُ ٱلْإِنسَٰنُ أَن يُتْرَكَ سُدًى (٣٦)
أَلَمْ يَكُ نُطْفَةً مِّن مَّنِىٍّ يُمْنَىٰ (٣٧) ثُمَّ كَانَ عَلَقَةً فَخَلَقَ فَسَوَّىٰ (٣٨) فَجَعَلَ مِنْهُ
ٱلزَّوْجَيْنِ ٱلذَّكَرَ وَٱلْأُنثَىٰٓ (٣٩) أَلَيْسَ ذَٰلِكَ بِقَٰدِرٍ عَلَىٰٓ أَن يُحْـِۧىَ ٱلْمَوْتَىٰ (٤٠)

## سُورَةُ الإِنسَانِ

ترتيبها ٧٦ — آياتها ٣١

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

هَلْ أَتَىٰ عَلَى ٱلْإِنسَٰنِ حِينٌ مِّنَ ٱلدَّهْرِ لَمْ يَكُن شَيْـًٔا مَّذْكُورًا (١)
إِنَّا خَلَقْنَا ٱلْإِنسَٰنَ مِن نُّطْفَةٍ أَمْشَاجٍ نَّبْتَلِيهِ فَجَعَلْنَٰهُ سَمِيعًۢا
بَصِيرًا (٢) إِنَّا هَدَيْنَٰهُ ٱلسَّبِيلَ إِمَّا شَاكِرًا وَإِمَّا كَفُورًا (٣)
إِنَّآ أَعْتَدْنَا لِلْكَٰفِرِينَ سَلَٰسِلَا۟ وَأَغْلَٰلًا وَسَعِيرًا (٤) إِنَّ
ٱلْأَبْرَارَ يَشْرَبُونَ مِن كَأْسٍ كَانَ مِزَاجُهَا كَافُورًا (٥)

18 ባነበብነውም ጊዜ (ካለቀ በኋላ) ንባቡን ተከተል።
19 ከዚያም ማብራራት በእኛ ላይ ነው።
20 (ከመጣደፍ) ተከልከል፤ ይልቁንም ሰዎች ፈጣኒቱን ዓለም ትወዳላችሁ።
21 መጨረሻይቱንም (ዓለም) ትተዋላችሁ።
22 ፊቶች በዚያ ቀን አብሪዎች ናቸው።
23 ወደ ጌታቸው ተመልካቾች ናቸው።
24 ፊቶችም በዚያ ቀን ጨፍጋጊዎች ናቸው።
25 በነርሱምም ላይ ዐደጋ እንደሚሰራባቸው ያረጋግጣሉ፡፡
26 ንቁ! (ነፍስ) ወደ ጉረሮ በደረሰችና፤
27 አሻሪው ማነው? በተባለ ጊዜ፤
28 (ህመምተኛው) እርሱ (የሡፈረበት ነገር ከዚህ ዓለም) መለየት መሆኑን ባረጋገጠም ጊዜ፤
29 ባትም ከባት በተጣበቀች ጊዜ፤
30 በዚያ ቀን መነዳት ወደ ጌታህ (ፍርድ)ብቻ ነው።
31 አላመነምም ፤ አልሰገደምም።
32 ግን አስተባበለ፤ (ከእምነት) ዞረም።
33 ከዚያም እየተንጎማለለ ወደ ቤተሰቡ ሄደ።
34 የምትጠላውን[1] ነገር (አላህ) ያስከትልህ፤ ለአንተ ተገቢህም ነው።
35 ከዚያም ጥፋት ይጠጋህ። ለአንተ ተገቢህም ነው።
36 ሰው እንደፈለገ የሚኖር ልቅ /ስድ/ ሆኖ የሚተው ይመስለዋልን?
37 የሚፈስ ከሆነ የፍትወት ጠብታ አልነበረምን?
38 ከዚያም የረጋ ደም ሆነ (አላህ ሰው አድርጎ) ፈጠረውም፤ አስተካከለውም።
39 ከእርሱም ሁለት /ዓይነቶችን/ ወንድና ሴትን አደረገ።
40 ይህ (ጌታ) ሙታንን ሕያው በማድረግ ላይ ቻይ አይደለምን?[2]

## 76 ኛው ሱራ፡-የሰዎች ምዕራፍ (ሱረቱ አል- ኢንሳን) [3]፡፡ አንቀጾቹ 31 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 በሰው ላይ የሚታወስ ነገር ሳይሆን ከዘመናት የተወሰነ ጊዜ በእርግጥ አልፎበታል[4]።
2 እኛ ሰውን (በሕግጋት ግዳጅ) የምንሞክረው ስንሆን ቅልቅሎች /ዉሁድ/ ከሆኑ የፍትወት ጠብታ ፈጠርነው ፤ ሰሚ ተመልካችም አደረግነው።
3 እኛ ወይ አመስጋኝ ወይም ከሓዲ ሲሆን መንገዱን መራነው /ገለጽንለት/።
4 እኛ ለከሓዲዎች ሰንሰለቶችንና

---

[1] ከ34-35ያሉ አንቀፆች የወረዱበት፡- «በርሷም ላይ አስራ ዘጠኝ /ዘበኞች አሉባት» የሚለው ቁርአን ሲወርድ አቡጀህል መኮችን ሰብስቦ ያጥፋችሁ የአቡ ከብሻ ልጅ የጀሃነም ዘበኞች አስራ ዘጠኝ ናቸው ይላል እናንተ ብዙ ህዝቦች ናችሁ አስር አስሮች እንኳን አንድ አንዱን ማሸነፍ ያቅታችኋልን በማለት ስላፌዘ ነው ፡፡ (ሱዩጢ፡፡)

[2] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡
1. ሞቶ መነሳትን ማረጋገጥ፣
2. አላህ (ﷻ) ለሰው ልጅ የዋለውን ውለታ መዘርዘር፣
3. የሰዎች የጣት አሻራ መለያየት ከአላህ (ﷻ) ተአምራት መካከል አንዱና አስገራሚ መሆኑን፣
4. የሰው ልጅ በጀመረው ኸይር ስራ አጅር እንደሚያገኝ ሁሉ በመጥፎውም እንደሚጠየቅ፤
5. ስለ ቂያማ ቀን ትልቅነትና ክብደት
6. ነፍሶች ብዙ አይነት እንደሆኑ፡
7. አለማወቅ ምን ያህል ችግር እንዳለው፡
8. ዛሬ በአሻራና በምስክርነት እየተጠቀምንባት ያለችውን አትቀመ ማንሳቱ የሚያሳየውን ተዓምር፤
9. የሞት ሃቅነትና አምላጭ እንደሌለውና አስተማሪነቱን፣
10. የሙናፊቆች ምልክቶች በአላህና በመላክተኛው አለማመን ሰላትንና መሰል የዲን ምልክቶችን ችላ ማለት በቁርአን ሕግጋት መቀለድና ማፌዝ እንደሆነ፣
11. ኩራት የተጠላ አስከፊ ባህሪ መሆኑን፣
12. የሰው ልጅ የተፈጠረበት አላማ ያለው መሆኑን፣
13. የሰው ልጅን አመጣጥና አፈጣጠር በዝርዝር፣
14. በሰው ልጆች መካከል ፆታን መፍጠር ወንድና ሴት አድርጎ በመሐከላቸው ፍቅር እንደፈጠርና ዘር እንዲሰጣቸው፣
15. ለመጀመሪያ ጊዜ የፈጠረ ጌታ መልሶ መቀስቀስ እንደሚችል እንማራለን፡፡

[3] ምዕራፉ በመዲና ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው፡፡

[4] ወይም አላለፈበትምን?

እንዛዝላዎችን፣ እሳትንም አዘጋጅተናል።
5 በጎ አድራጊዎች መበረዣዋ ካፉር ከሆነች ጠጅ ይጠጣሉ።
6 ከእርሷ የአላህ ባሮች የሚጠጡላት፣ (ወደ ፈለጉበት) ማንቧቧትን የሚያንቧቧት ከሆነች ምንጭ (ይጠጣሉ)።
7 (ዛሬ) በስለታቸው ይሞላሉ፤ መከራው ተሰራጪ የሆነንም ቀን ይፈራሉ።
8 ምግብንም [1] ከመውደዳቸው ጋር ለድሃ፣ ለየቲም፣ ለምርኮኛና ለእስረኛ ያበላሉ።
9 የምናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብቻ ነው፤ ከእናንተ ዋጋንም ማመስገንንም አንፈልግም ።
10 እኛ (ፊትን) የሚያጨፈግግን ብርቱ ቀን ከጌታችን እንፈራለንና (ይላሉ።)
11 አላህም የዚያን ቀን ክፋት ጠበቃቸው፤ ፊታቸው ማማርንና መደሰትንም ገጠማቸው።
12 በመታገሳቸውም ገነትንና የሀር ልብስን መነዳቸው።
13 በውስጧ በባለ አጎበር አልጋዎች ላይ ተደጋፊዎች፣ በውስጧ ፀሀይንም ጨረቃንም /ሐሩርና ቁር አያዩም።
14 ዛፎቿም በእነሱ ላይ የቀረበች፣ ፍሬዎችዋም (ለለቃሚዎች) መገራትን የተገራች ስትሆን ገነትን መነዳቸው።
15 በእነሱም ላይ ከብር በሆኑ ዕቃዎች (ሳህ ች)፣ የብርጭቆዎች በሆኑ ኩባያዎችም ይዝዞርባቸዋል ።
16 መለካትን የለኳቸው በሆኑ የብር ብርጭቆዎች (ይዝዞርባቸዋል)።
17 በእርሷም መበረዣዋ ዘንጀቢል የሆነችን ጠጅ ይጠጣሉ።
18 በውስጧ ያለችውን ሰልሰቢል ተብላ የምትጠራውን ምንጭ።
19 በእነሱም ላይ (ባሉበት ሁኔታ) የሚዘወተሩ ወጣት ልጆች ይዘዋወራሉ፤ ባየሃቸው ጊዜ የተበተነ ሉል ናቸው ብለህ ታስባቸዋለህ።
20 እዚያም[2] በተመለከትክ ጊዜ ጸጋንና ታላቅ ንግስናን ታያለህ።

عَيۡنٗا يَشۡرَبُ بِهَا عِبَادُ ٱللَّهِ يُفَجِّرُونَهَا تَفۡجِيرٗا ﴿٦﴾ يُوفُونَ بِٱلنَّذۡرِ وَيَخَافُونَ
يَوۡمٗا كَانَ شَرُّهُۥ مُسۡتَطِيرٗا ﴿٧﴾ وَيُطۡعِمُونَ ٱلطَّعَامَ عَلَىٰ حُبِّهِۦ مِسۡكِينٗا
وَيَتِيمٗا وَأَسِيرًا ﴿٨﴾ إِنَّمَا نُطۡعِمُكُمۡ لِوَجۡهِ ٱللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنكُمۡ جَزَآءٗ وَلَا شُكُورًا
﴿٩﴾ إِنَّا نَخَافُ مِن رَّبِّنَا يَوۡمًا عَبُوسٗا قَمۡطَرِيرٗا ﴿١٠﴾ فَوَقَىٰهُمُ ٱللَّهُ شَرَّ ذَٰلِكَ
ٱلۡيَوۡمِ وَلَقَّىٰهُمۡ نَضۡرَةٗ وَسُرُورٗا ﴿١١﴾ وَجَزَىٰهُم بِمَا صَبَرُواْ جَنَّةٗ وَحَرِيرٗا
﴿١٢﴾ مُّتَّكِـِٔينَ فِيهَا عَلَى ٱلۡأَرَآئِكِۖ لَا يَرَوۡنَ فِيهَا شَمۡسٗا وَلَا زَمۡهَرِيرٗا ﴿١٣﴾
وَدَانِيَةً عَلَيۡهِمۡ ظِلَٰلُهَا وَذُلِّلَتۡ قُطُوفُهَا تَذۡلِيلٗا ﴿١٤﴾ وَيُطَافُ عَلَيۡهِم بِـَٔانِيَةٖ
مِّن فِضَّةٖ وَأَكۡوَابٖ كَانَتۡ قَوَارِيرَا۠ ﴿١٥﴾ قَوَارِيرَاْ مِن فِضَّةٖ قَدَّرُوهَا تَقۡدِيرٗا ﴿١٦﴾
وَيُسۡقَوۡنَ فِيهَا كَأۡسٗا كَانَ مِزَاجُهَا زَنجَبِيلًا ﴿١٧﴾ عَيۡنٗا فِيهَا تُسَمَّىٰ سَلۡسَبِيلٗا
﴿١٨﴾ ۞ وَيَطُوفُ عَلَيۡهِمۡ وِلۡدَٰنٞ مُّخَلَّدُونَ إِذَا رَأَيۡتَهُمۡ حَسِبۡتَهُمۡ لُؤۡلُؤٗا مَّنثُورٗا
﴿١٩﴾ وَإِذَا رَأَيۡتَ ثَمَّ رَأَيۡتَ نَعِيمٗا وَمُلۡكٗا كَبِيرًا ﴿٢٠﴾ عَٰلِيَهُمۡ ثِيَابُ سُندُسٍ
خُضۡرٞ وَإِسۡتَبۡرَقٞۖ وَحُلُّوٓاْ أَسَاوِرَ مِن فِضَّةٖ وَسَقَىٰهُمۡ رَبُّهُمۡ شَرَابٗا
طَهُورًا ﴿٢١﴾ إِنَّ هَٰذَا كَانَ لَكُمۡ جَزَآءٗ وَكَانَ سَعۡيُكُم مَّشۡكُورًا ﴿٢٢﴾ إِنَّا
نَحۡنُ نَزَّلۡنَا عَلَيۡكَ ٱلۡقُرۡءَانَ تَنزِيلٗا ﴿٢٣﴾ فَٱصۡبِرۡ لِحُكۡمِ رَبِّكَ وَلَا تُطِعۡ
مِنۡهُمۡ ءَاثِمًا أَوۡ كَفُورٗا ﴿٢٤﴾ وَٱذۡكُرِ ٱسۡمَ رَبِّكَ بُكۡرَةٗ وَأَصِيلٗا ﴿٢٥﴾

21 አረንጓዴዎች የሆኑ የቀጭን ሀር ልብሶችና ወፍራም ሀርም በላያቸው ላይ አለ። ከብር የሆኑ አንባሮችንም ይሸለማሉ፤ ጌታቸውም አጥሪ የሆነን መጠጥ ያጠጣቸዋል።
22 ይህ ለእናንተ ዋጋ ሆነ ። ስራችሁም ምስጉን ሆነ፤ (ይባላሉ)።
23 እኛ ቁርአንን ባንተ ላይ ማውረድን አወረድነው።
24 ለጌታህ[3] ፍርድ ታገሥ። ከእነሱም ኃጢአተኛን ወይም ከሓዲን አትታዘዝ።
25 የጌታህን ስም በጧትና ከቀትር በኋላ አውሳ።
26 ከሌሊቱም ለእርሱ ስገድ፤ በረጅም ሌሊትም አወድሰው።
27 እነዚህ ፈጣኒቱን /ይህችን/ ዓለም ይወዳሉ፤ ከባድ /አስቸጋሪ/ ቀንም በስተፊታቸው ሆ ይተዋሉ /ችላ ይላሉ/።
28 እኛ ፈጠርናቸው። መለያያቸውንም አጠነከርን። በሻን/በፈለግን/ ጊዜ መሰሎቻቸውን መለወጥን እንለውጣለን።
29 ይህቺ መገሰጫ ናት። የሻ/የፈለገ/ ሰው

[1] 8ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክኒያት፡-
ዓሊይ ቢን አቢጣሊብ ከአንድ ሐብታም ጋር ተቀጥረው ሰርተው የሰሩበትን ገብስ ይዘው መጥተው አንድ ሦስተኛ ውን ለራሳቸው ሰርተው ፤ሲበስል አንድ ድሃ መጥቶ ሲለምን ለእሱ ሰጡትና ሌላውን አንድ ስድስተኛ ሰራርተው ሲበስል አንድ የቲም ልጅ ሥለመጣ ለእሱ ሰጡትና ሦስተኛውን ሠርተው ሲበስል አንድ በጠላቶች ተይዞ የነበረ ምርኮኛ መጣና ለእሱ ቅድሚያ በመስጠት ራሳቸውን ከልክለው ስለአደሩ ነው። (ዋሂዲ)

[2] 20ኛው አንቀጽ-የወረደበት ምክንያት፡- ዑመር ነቢዩ ሙሀመድን (ﷺ) በሰሌን ላይ ተኝተው ጐናቸው ጎርቦ /ሰምበር አውጥቶ/ ሲያይዋቸው አለቀሱ። በዚህ ጊዜ፡- ለምን ታለቅሳለህ ብለው ሲጠይቋቸው የኪስራን፣ የሁርሙዝንና የሐበሻውን ንጉሶች ምቾትና እርሶ የአላህ (ﷻ) መላዕክተኛ ሁነው ሳለ በሰሌን ላይ መሆንዎን ሳይ ነው አሏቸው ። በዚህ ጊዜ ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ለእነሱ ይህች ዓለም ሁናላቸው ለእኛ ደግሞ አኺራ ቢሆን ደስ አይልህምን? በማለት ስለ መለሱላቸው ነው። (ዋሂዲ።)

[3] 24ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አቡጀህል፡- ሙሐመድ (ﷺ) ሲሰግድ ባየሁት ጊዜ ከአንገቱ ላይ ነው የምቆመው በማለቱ ነው ። (ሱዩጢ።)

وَمِنَ ٱلَّيۡلِ فَٱسۡجُدۡ لَهُۥ وَسَبِّحۡهُ لَيۡلٗا طَوِيلًا ﴿٢٦﴾ إِنَّ
هَٰٓؤُلَآءِ يُحِبُّونَ ٱلۡعَاجِلَةَ وَيَذَرُونَ وَرَآءَهُمۡ يَوۡمٗا ثَقِيلٗا ﴿٢٧﴾ نَّحۡنُ
خَلَقۡنَٰهُمۡ وَشَدَدۡنَآ أَسۡرَهُمۡۖ وَإِذَا شِئۡنَا بَدَّلۡنَآ أَمۡثَٰلَهُمۡ تَبۡدِيلًا
﴿٢٨﴾ إِنَّ هَٰذِهِۦ تَذۡكِرَةٞۖ فَمَن شَآءَ ٱتَّخَذَ إِلَىٰ رَبِّهِۦ سَبِيلٗا ﴿٢٩﴾
وَمَا تَشَآءُونَ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلِيمًا حَكِيمٗا ﴿٣٠﴾
يُدۡخِلُ مَن يَشَآءُ فِي رَحۡمَتِهِۦۚ وَٱلظَّٰلِمِينَ أَعَدَّ لَهُمۡ عَذَابًا أَلِيمَۢا ﴿٣١﴾

## سُورَةُ ٱلْمُرْسَلَاتِ

ترتيبها ٧٧ — آياتها ٥٠

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَٱلۡمُرۡسَلَٰتِ عُرۡفٗا ﴿١﴾ فَٱلۡعَٰصِفَٰتِ عَصۡفٗا ﴿٢﴾ وَٱلنَّٰشِرَٰتِ نَشۡرٗا ﴿٣﴾
فَٱلۡفَٰرِقَٰتِ فَرۡقٗا ﴿٤﴾ فَٱلۡمُلۡقِيَٰتِ ذِكۡرًا ﴿٥﴾ عُذۡرًا أَوۡ نُذۡرًا ﴿٦﴾ إِنَّمَا
تُوعَدُونَ لَوَٰقِعٞ ﴿٧﴾ فَإِذَا ٱلنُّجُومُ طُمِسَتۡ ﴿٨﴾ وَإِذَا ٱلسَّمَآءُ فُرِجَتۡ
﴿٩﴾ وَإِذَا ٱلۡجِبَالُ نُسِفَتۡ ﴿١٠﴾ وَإِذَا ٱلرُّسُلُ أُقِّتَتۡ ﴿١١﴾ لِأَيِّ يَوۡمٍ أُجِّلَتۡ
﴿١٢﴾ لِيَوۡمِ ٱلۡفَصۡلِ ﴿١٣﴾ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلۡفَصۡلِ ﴿١٤﴾ وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ
لِّلۡمُكَذِّبِينَ ﴿١٥﴾ أَلَمۡ نُهۡلِكِ ٱلۡأَوَّلِينَ ﴿١٦﴾ ثُمَّ نُتۡبِعُهُمُ ٱلۡأٓخِرِينَ
﴿١٧﴾ كَذَٰلِكَ نَفۡعَلُ بِٱلۡمُجۡرِمِينَ ﴿١٨﴾ وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ ﴿١٩﴾

ወደ ጌታው መንገድን ይይዛል።
30 አላህም ካልሻ በስተቀር አትሹም፤ አላህ ዐዋቂ ጥበበኛ ነውና።
31 የሚሻውን ሰው በእዝነ ቱውስጥ ያገባዋል፤ በዳዮችንም (ዝቶባቸዋል) ፤ ለእነሱ አሳማሚ ቅጣትን አዘጋጅቶላቸዋል፡፡[1]

## 77 ኛው ምዕራፍ፡-የተላኪዎች ምዕራፍ (ሱረቱ-አል ሙርሰላህ)[2] :: አንቀጾቹ 31 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 ተከታታይ ሆነው በተላኩት ፤
2 በኃይል መንፈስን ነፋሾች በሆኑትም ፤
3 መበተንን በታኝ በሆኑትም (ነፋሶች)፤
4 መለየትን[3] ለይዎች በሆኑትም ፤
5 6 ምክንያትን ለማስወገድ ወይም ለማስፈራራት መገሠጫን (ወደ ነቢያት) ጣይዎች በሆኑት መላእክት እምላለሁ።
7 ያ! የምትስፈራሩበት (ትንሣኤ) በእርግጥ ኗኝ ነው።
8 ከዋክብትም (ብርሃንዋን) በታበሰች ጊዜ።
9 ሰማይም በተከፈተች ጊዜ ፤
10 ጋራዎችም በተን ታኮቱ ጊዜ።
11 መልክተኞቹም ወቅት በተደረገላቸው ጊዜ።
12 ለየትኛው ቀን ተቀጠሩ (የሚባል ሲሆን) ፤
13 ለመለያው ቀን (በተባለ ጊዜ ፤ በፍጡሮች መካከል ይፈርዳል)።
14 የመለያውም ቀን ምን እንደሆነ ምን አሳወቀህ ?
15 ለአስተባባዮች በዚያ ቀን ወዮላቸው።
16 የፊተኞችን (ህዝቦች) አላጠፋንምን ?
17 ከዚያም የኋለኞችን እናስከትላቸዋለን።
18 በአመፀኞች ሁሉ እንደዚሁ ንሰራለን።

---

[1] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ::
1. የሰው ልጅ አባት የሆኑት አደምና ከዚም በኋላ የሚወለዱት ሰዎች አፈጣጠር ከአፈርና ከደካማ ፈሳሽ እንደሆነ በዝርዝር መጠቆምና የሰው ልጅ ምንም አቅም የሌለው ደካማ በመሆኑ በጌታው ላይ ሊያምጽ እንደማይገባው፣
2. ከአዕምሮ ጋር የመስሚያና የማያ አካሎች ለሰው ልጅ በጣም አስፈላጊ ስለመሆናቸው ፣
3. የሰው ልጅ ፊት ለፊቱ ሁለት መንገዶች እንዳሉትና የፈለገውን መርጦ መከተል እንደሚችል፣ የግል ምርጫው መሆኑን፣
4. ከአባታችን አደም (عليه السلام) በኋላ የመጣው ሕዝብ ከአባትና ከእናት ፈሳሽ መሆኑን፣
5. ስለትን መሙላት ግዴታ ስለመሆኑ፣
6. ስለቱ በወንጀል ካልሆነ በስተቀር፤
7. ችግረኛን መመገብና የቲምን መርዳት አስፈላጊ የጽድቅ ተግባር ስለ መሆኑ፤
8. የሞቶ መነሳትን ሐቅነት ማረጋገጥና እንድናምንበት ግፊት ማሳደር፣
9. በወርቅ ወይም በብር ዕቃነት ወይም በሌላ ነገሮች ላይ በዱንያ ለወንድ መጠቀም ክልክል ስለመሆኑ፣
10. ኸምርን መጠጣት በዱንያ የተከለከለ ስለመሆኑና በአኼራ ግን ይህን ስም የያዘ ጣፋጭ መጠጥ እንዳለ፤
11. መልካም ሰራተኞችን መያዝ ተፈላጊ ስለመሆኑ፣
12. ለወንድ ልጅ ሐርን መልበስ ክልክል መሆኑንና ለሴት የተፈቀደ መሆኑን፤
13. ከሃዲንና ወንጀለኛን በምንም መልኩ መታዘዝ እንደሌለብን፣
14. ሙዕሚን የሆነ ሰው በሰላትና በዚክር እንዲሁም በዱዓ መታገዝ እንዳለበት፣
15. የለሊት ሰላት አስፈላጊነትን መጠቆም፣
16. የአላህ (عز وجل) ፍላጎት ከፍላጎቶች ሁሉ በላይና ተቀዳሚ ስለመሆኑ፣
17. ቁርአን የአማኞች ማስታወሻ ስለ መሆኑ እንማራለን፡፡

[2] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው፡፡

[3] 48ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በእኒያ በበኒ ሰቂፎች ምክንያት ነው፡፡ (ሱዩጢ፡፡)

أَلَمۡ نَخۡلُقكُّم مِّن مَّآءٖ مَّهِينٖ (٢٠) فَجَعَلۡنَٰهُ فِي قَرَارٖ مَّكِينٍ (٢١) إِلَىٰ قَدَرٖ
مَّعۡلُومٖ (٢٢) فَقَدَرۡنَا فَنِعۡمَ ٱلۡقَٰدِرُونَ (٢٣) وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ (٢٤)
أَلَمۡ نَجۡعَلِ ٱلۡأَرۡضَ كِفَاتًا (٢٥) أَحۡيَآءٗ وَأَمۡوَٰتٗا (٢٦) وَجَعَلۡنَا فِيهَا رَوَٰسِيَ
شَٰمِخَٰتٖ وَأَسۡقَيۡنَٰكُم مَّآءٗ فُرَاتٗا (٢٧) وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ (٢٨)
ٱنطَلِقُوٓاْ إِلَىٰ مَا كُنتُم بِهِۦ تُكَذِّبُونَ (٢٩) ٱنطَلِقُوٓاْ إِلَىٰ ظِلّٖ ذِي ثَلَٰثِ
شُعَبٖ (٣٠) لَّا ظَلِيلٖ وَلَا يُغۡنِي مِنَ ٱللَّهَبِ (٣١) إِنَّهَا تَرۡمِي بِشَرَرٖ
كَٱلۡقَصۡرِ (٣٢) كَأَنَّهُۥ جِمَٰلَتٞ صُفۡرٞ (٣٣) وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ (٣٤)
هَٰذَا يَوۡمُ لَا يَنطِقُونَ (٣٥) وَلَا يُؤۡذَنُ لَهُمۡ فَيَعۡتَذِرُونَ (٣٦) وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ
لِّلۡمُكَذِّبِينَ (٣٧) هَٰذَا يَوۡمُ ٱلۡفَصۡلِۖ جَمَعۡنَٰكُمۡ وَٱلۡأَوَّلِينَ (٣٨) فَإِن كَانَ
لَكُمۡ كَيۡدٞ فَكِيدُونِ (٣٩) وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ (٤٠) إِنَّ ٱلۡمُتَّقِينَ فِي
ظِلَٰلٖ وَعُيُونٖ (٤١) وَفَوَٰكِهَ مِمَّا يَشۡتَهُونَ (٤٢) كُلُواْ وَٱشۡرَبُواْ هَنِيٓـَٔۢا
بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ (٤٣) إِنَّا كَذَٰلِكَ نَجۡزِي ٱلۡمُحۡسِنِينَ (٤٤) وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ
لِّلۡمُكَذِّبِينَ (٤٥) كُلُواْ وَتَمَتَّعُواْ قَلِيلًا إِنَّكُم مُّجۡرِمُونَ (٤٦) وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ
لِّلۡمُكَذِّبِينَ (٤٧) وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ ٱرۡكَعُواْ لَا يَرۡكَعُونَ (٤٨) وَيۡلٞ
يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ (٤٩) فَبِأَيِّ حَدِيثِۭ بَعۡدَهُۥ يُؤۡمِنُونَ (٥٠)

19 ለአስተባባዮች በዚያ ቀን ወዮላቸው።
20 ከደካማ ውሃ አልፈጠርናችሁምን ?
21 በተጠበቀ መርጊያ ውስጥም (በማህጸን) አደረግነው ፤
22 እስከ ታወቀ ገዜ ድረስ።
23 መጠንነውም፤ ምን ያማርንም መጣኞች ነን።
24 ላስተባባዮች በዚያ ቀን ወዮላቸው።
25 ምድርን ሰብሳቢ አላደረግናትምን ?
26 ህያውያን ሆናችሁ፣ ሙታንም ሆናችሁ።
27 በውስጧም ከፍተኛዎችን/ትላልቅ/ ተራራዎች አደረግን፤ ጣፋጭ ውሃንም አጠጣናችሁ።
28 ለአስተባባዮች በዚያ ቀን ወዮላቸው።
29 ወደ ዚያ በእርሱ ታስተባብሉ ወደ ነበራችሁት (ቅጣት) ሒዱ።
30 ባለ ሶስት ቅርንጫፎች ወደ ሆነው ጥላ ሒዱ።
31 ጥላም ያልሆነ ከእሳቱም ላንቃ የማያድን ወደ ሆነው ሒዱ።
32 እርሷ እንደ ታላላቅ ህንጻ የሆኑን ቃንቄዎች/ብልጭታዎች/ ትወረውራለች።
33 (ቃንቄውም) ልክ ዳለቻዎች ግመሎችን ይመስላል።
34 ለአስተባባዮች በዚያ ቀን ወዮላቸው።
35 ይህ የማይናገሩበት ቀን ነው።
36 ይቅርታም ይጠይቁ ዘንድ አይፈቀድላቸውም።
37 ለአስተባባዮች በዚያ ቀን ወዮላቸው።
38 ይህ የመለያው ቀን ነው። እናንተንም የፊተኞችንም ሰበሰብናችሁ።
39 ለእናንተም (ለማምለጥ) ብልሃት እንዳላችሁ ተተና ሉኝ።
40 ላስተባባዮች በዚያ ቀን ወዮላቸው።
41 42 ጥንቁቆች በጥላዎች፣ በምንጮችና በሚፈልጉትም የፍራፍሬ ዓይነቶች ውስጥ ናቸው።
43 ትሰሩት በነበራችሁት ዋጋ የምትደሰቱ ሆናችሁ ብሉ፤ ጠጡም፤ (ይባላሉ)።
44 እኛ እንደዚሁ መልካም ሰሪዎችን ሁሉ እንመነዳለን፤
45 ላስተባባዮች በዚያ ቀን ወዮላቸው።
46 ብሉ፤ ጥቂትንም (ጊዜ) ተጠቀሙ፤ እናንተ አመፀኞች ናችሁና።
47 ላስተባባዮች በዚያ ቀን ወዮላቸው።
48 ለነሱ ስገዱም በተባሉ ጊዜ አይሰግዱም፡፡
49 ላስተባባዮች በዚያ ቀን ወዮላቸው።
50 ከእርሱም ሌላ በየትኛው ንግግር ያምናሉ?[1]

---

[1] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1.ሞቶ መነሳትን በመሀላ አጠንክሮ ማረጋገጥ፣
2.ፍጡሮች ከአላህ (ﷻ) ሌላ በሆነ መማል ክልክል ቢሆንም አላህ (ﷻ) ግን በፈለገው መማል የሚችል መሆኑን በመላዒኮችና በነፍሶች በመማል መግለፁን፤
3.ሞቶ መነሳት እንዳለ ለማሳመን ብዙ ማስረጃዎች እንዳሉ፣
4. አላህ (ﷻ) ለፍጡሮቹ የዋለውን ከፍተኛ ውለታ በግልፅ ማሳየት፣
5.ብዙ ሰዎች አላህን (ﷻ) የማያመሰግኑ መሆኑን፣
6.ለካሐዲዎች የተገባው ዛቻ አስፈሪ መሆኑን፤
7. በገሀነም ቅጣት ክብደትና ክፋት መገረም፣
8.የቂያማ ቀን ጭንቅ ብርቱ ስለመሆኑ፣
9.ሞቶ መነሳትን በሰፊው ማስታወስ፣
10. የክህደት ቁንጮ በአላህ (ﷻ) ማስተባበል ስለመሆኑ፤
11. የአላህን (ﷻ) ፍራቻና መልካም ሥራን ትልቅነት በስፍራው ማንሳት፣
12. የቁርአን ዘገባ እውነተኛነት ለመካ ከሃዲዎች የዛተው ዛቻ በአጭር ጊዜ ሲፈፀም መታየቱ በቂ ስለመሆኑ፣
13.መስጊድ ሲገባ ሰዎች የሰገዱ ያገኘ ሰው ያለ ምንም ጥያቄ ከእነርሱ ጋር አብሮ መስገድ እንዳለበት እንማራለን፡፡

ترتيبها ٧٨ سُورَةُ النَّبَإِ آياتها ٤٠

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

عَمَّ يَتَسَآءَلُونَ ١ عَنِ ٱلنَّبَإِ ٱلۡعَظِيمِ ٢ ٱلَّذِي هُمۡ فِيهِ مُخۡتَلِفُونَ ٣
كَلَّا سَيَعۡلَمُونَ ٤ ثُمَّ كَلَّا سَيَعۡلَمُونَ ٥ أَلَمۡ نَجۡعَلِ ٱلۡأَرۡضَ مِهَٰدٗا ٦
وَٱلۡجِبَالَ أَوۡتَادٗا ٧ وَخَلَقۡنَٰكُمۡ أَزۡوَٰجٗا ٨ وَجَعَلۡنَا نَوۡمَكُمۡ سُبَاتٗا
٩ وَجَعَلۡنَا ٱلَّيۡلَ لِبَاسٗا ١٠ وَجَعَلۡنَا ٱلنَّهَارَ مَعَاشٗا ١١ وَبَنَيۡنَا
فَوۡقَكُمۡ سَبۡعٗا شِدَادٗا ١٢ وَجَعَلۡنَا سِرَاجٗا وَهَّاجٗا ١٣ وَأَنزَلۡنَا
مِنَ ٱلۡمُعۡصِرَٰتِ مَآءٗ ثَجَّاجٗا ١٤ لِّنُخۡرِجَ بِهِۦ حَبّٗا وَنَبَاتٗا ١٥ وَجَنَّٰتٍ
أَلۡفَافًا ١٦ إِنَّ يَوۡمَ ٱلۡفَصۡلِ كَانَ مِيقَٰتٗا ١٧ يَوۡمَ يُنفَخُ فِي ٱلصُّورِ
فَتَأۡتُونَ أَفۡوَاجٗا ١٨ وَفُتِحَتِ ٱلسَّمَآءُ فَكَانَتۡ أَبۡوَٰبٗا ١٩ وَسُيِّرَتِ
ٱلۡجِبَالُ فَكَانَتۡ سَرَابًا ٢٠ إِنَّ جَهَنَّمَ كَانَتۡ مِرۡصَادٗا ٢١ لِّلطَّٰغِينَ
مَـَٔابٗا ٢٢ لَّٰبِثِينَ فِيهَآ أَحۡقَابٗا ٢٣ لَّا يَذُوقُونَ فِيهَا بَرۡدٗا وَلَا شَرَابًا
٢٤ إِلَّا حَمِيمٗا وَغَسَّاقٗا ٢٥ جَزَآءٗ وِفَاقًا ٢٦ إِنَّهُمۡ كَانُواْ
لَا يَرۡجُونَ حِسَابٗا ٢٧ وَكَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا كِذَّابٗا ٢٨ وَكُلَّ شَيۡءٍ
أَحۡصَيۡنَٰهُ كِتَٰبٗا ٢٩ فَذُوقُواْ فَلَن نَّزِيدَكُمۡ إِلَّا عَذَابًا ٣٠

## 78 ኛው ምእራፍ፡ የዜናው ምዕራፍ ነው:: (ሱረቱ አን-ነበእ)[1] አንቀጾቹ 40 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 ከምን[2] ነገር ይጠያየቃሉ?
2 3 ከዚያ እነርሱ በእርሱ የተለያዩበት (የተወዛገቡበት) ከሆነው ከታላቁ ዜና (ይጠያየቃሉ) ::
4 5 ጉዳዩ እነሱ እንደሚሉት አይደለም:: ወደፊት ያውቃሉ ::
6 ምድርን እንደ ፍራሽ (የምትመች) አላደረግንምን?
7 መሬት እንዳ ረገርግ ጋራዎችንም ችካሎች አድርገናል::[3]
8 ብዙ ዓይነቶች አርገን ፈጠርናችሁ።
9 እንቅልፋችሁንም ዕረፍት አደረግን።
10 ሌሊቱንም ልባስ አደረግን::
11 ቀኑንም (ለኑሮ )መስሪያ፣ ለጉዳይ መከወኛ አደረግን ::
12 ከበላያችሁም ሰባትን ብርቱዎች (ሰማያት) ገነባን ::
13 አንጸባራቂ ብርሃንንም (ፀሐይን) አደረግንላችሁ
14 - 16 ከአረገዙት ደመናዎችም በእርሱ ህልንና ቅጠላ ቅጠልን፣ የተቆላለፉ አትክልቶችንም እናወጣ ዘንድ የሚንቧቧ ውሃን አደረግን::
17 የመለያው ቀን የተወሰነ ጊዜ ነው።
18 በቀንዱ በሚነፋበትና የተለያዩ ጭፍሮች ሆናችሁ በምትመጡ ቀን ነው።
19 ሰማይም በምትከፈትና (ባለ) ብዙ ደጃፎችም በምትሆንበት ቀን::
20 ጋራዎችም በሚነዱበት (እንደ) ሲራብዱም በሚሆኑበት (ቀን) ነው።
21 ገሀነም -ለከሃዲያን- መጠባበቂያ ኬላ (ስፍራ) ናት ::
22 ለህግ (ለወሰን) ተላላፊዎች መመለሻ ስትሆን።
23 በውስጧ ብዙ ዘመናትን ነዋሪዎች ሲሆኑ።
24 25 ሙቅ (የፈላ) ውሃንና እዥን እንጂ በውስጧ ቀዝቃዜንም፣መጠጥንም አይቀምሱም (አያገኙም) ::
26 ተስማሚን (ፍትሃዊን) /ተመጣጣኝን/ ምንዳ ይመነዳሉ።
27 እነሱ ምርመራን የማይፈሩ ነበሩና። (ተጠያቂ እንደሚሆኑ ቅንጣት አይጠብቁም ነበርና)
28 በአንቀጾቻችንም ማስተባበልን አስተባበሉና ::
29 ነገሩንም ሁሉ (በመዝገብ ውስጥ) የተጻፈ ሲሆን አጠቃለልነው ::
30 (የተግባራችሁን) ውጤት ቅመሱም፤ ቅጣትንም እንጅ (ሌላን) አንጨምራችሁም (ይባላሉ) (እንላቸዋለን) ::
31 ለጥንቁቆቹ (አላህን ለሚፈሩ) መዳኛ ስፍራ አላቸው ::
32 አትክልቶችና ወይ ችም ::
33 በእድሜ እኩያዎች የሆኑ ጡተ ጉችማዎችም።
34 በወይን ጠጅ የተሞሉ ብርጭቆዎችም።
35 በውስጧ ትርፍ ቃልንም፣

[1] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው :: ከሱረቱል ማዓሪጅ በኋላና ከሱረቱ አናዚዓት በፊት በ80ኛነት ደረጃ በመካ የወረደ ሱራ ነው :: ሰረቱ ዐምማ- ሱረቱ የተሳአሉን፣ ሱረቱ አልሙዕሶራት በመባልም ይታወቃል።-

[2] ከ1-2 ያሉት አንቀፆች የወረዱበት ምክንያት፡- ነቢዩ ሙህመድ (ﷺ) በተላኩበት ዘመን ካፊሮች ስለሞቶ መነሳት ጉዳይ በየቦታው በሰፊው ይወያዩበት ስለነበር ነው:: (ሱዩጢ።)

[3] በቁርአን ውስጥ ካሉ ሳይንሳዊ ተዓምራት ስለተራራዎች የተነገረው ሚስጥር አንዱ ነው :: እሱም ዛሬ ሳይንቲስቶች በዝርዝር ያስቀመጡትን ከ1420 አመት በፊት ማውሳቱ ይህ ቁርአን ከአላህ (ﷻ) የመጣ እንጂ የሰው ልጆች ስራ አለመሆኑን ያመለክታል :: ተራራዎች ወደ መሬት ውስጥ የጠለቁ ስሮች እንዳሏቸውና ለምድረ ገፅ መረጋጋትና ሚዛን መጠበቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ቁርአን ገልጿል ሳይንስም አረጋግጧል።

ማስዋሸትንም አይሰሙም ::
36 ከጌታህ የሆነን ምንዳ፣ በቂ ስጦታን (ተሰጡ)።
37 የሰማያትና የምድር፣ በመካከላቸውም ያለው ሁሉ ጌታና በጣም አዛኝ ከሆነው (ተመነዱ)፤ ከእርሱ ጋር መነጋገርን አይችሉም (አይደፍሩም) ።
38 መንፈሱ (ጂብሪል) እና መላእክቶችም የተሰለፉ ሆነው በሚቆሙ ቀን አል-ረሕማን ለእርሱ የፈቀደለትና ትክክለኛን ቃል ያለ ቢሆን እንጅ (መነጋገርን አይችሉም)፤ (አይደፍሩም) ።
39 ያ! መከሰቱ የተረጋገጠ ቀን ነው። የከጀለ ሰው ወደ ጌታው (በመልካም ተግባር) መመለስን ይይዛል ።
40 እኛ ሰው ሁሉ እጆቹ ያስቀደሙትን በሚያይበትና ከሓዲውም፡- ዋ ምኞቴ ምንነው አፈር በሆንኩ (ባልተቀሰቀስኩኝ) በሚልበት ቀን ቅርብ የሆነን ቅጣት አስጠነቀቅናችሁ።[1]

## 79 ኛው ሱራ፡-የአውጪዎች ምዕራፍ (ሱረቱ-አን-ናዚዓት) [2]። አንቀጾቹ 46 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (ጀምራለሁ)።

1 በኃይል[3] አውጪዎች በሆኑት እምላለሁ።

إِنَّ لِلْمُتَّقِينَ مَفَازًا (٣١) حَدَآئِقَ وَأَعْنَٰبًا (٣٢) وَكَوَاعِبَ أَتْرَابًا (٣٣) وَكَأْسًا
دِهَاقًا (٣٤) لَّا يَسْمَعُونَ فِيهَا لَغْوًا وَلَا كِذَّٰبًا (٣٥) جَزَآءً مِّن رَّبِّكَ عَطَآءً
حِسَابًا (٣٦) رَّبِّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا ٱلرَّحْمَٰنِ لَا يَمْلِكُونَ
مِنْهُ خِطَابًا (٣٧) يَوْمَ يَقُومُ ٱلرُّوحُ وَٱلْمَلَٰٓئِكَةُ صَفًّا لَّا يَتَكَلَّمُونَ
إِلَّا مَنْ أَذِنَ لَهُ ٱلرَّحْمَٰنُ وَقَالَ صَوَابًا (٣٨) ذَٰلِكَ ٱلْيَوْمُ ٱلْحَقُّ فَمَن
شَآءَ ٱتَّخَذَ إِلَىٰ رَبِّهِۦ مَـَٔابًا (٣٩) إِنَّآ أَنذَرْنَٰكُمْ عَذَابًا قَرِيبًا يَوْمَ
يَنظُرُ ٱلْمَرْءُ مَا قَدَّمَتْ يَدَاهُ وَيَقُولُ ٱلْكَافِرُ يَٰلَيْتَنِى كُنتُ تُرَٰبًۢا (٤٠)

سُورَةُ النَّازِعَاتِ — ترتيبها ٧٩ — آياتها ٤٦

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَٱلنَّٰزِعَٰتِ غَرْقًا (١) وَٱلنَّٰشِطَٰتِ نَشْطًا (٢) وَٱلسَّٰبِحَٰتِ سَبْحًا
(٣) فَٱلسَّٰبِقَٰتِ سَبْقًا (٤) فَٱلْمُدَبِّرَٰتِ أَمْرًا (٥) يَوْمَ تَرْجُفُ ٱلرَّاجِفَةُ
(٦) تَتْبَعُهَا ٱلرَّادِفَةُ (٧) قُلُوبٌ يَوْمَئِذٍ وَاجِفَةٌ (٨) أَبْصَٰرُهَا
خَٰشِعَةٌ (٩) يَقُولُونَ أَءِنَّا لَمَرْدُودُونَ فِى ٱلْحَافِرَةِ (١٠) أَءِذَا كُنَّا
عِظَٰمًا نَّخِرَةً (١١) قَالُوا۟ تِلْكَ إِذًا كَرَّةٌ خَاسِرَةٌ (١٢) فَإِنَّمَا هِىَ زَجْرَةٌ
وَٰحِدَةٌ (١٣) فَإِذَا هُم بِٱلسَّاهِرَةِ (١٤) هَلْ أَتَىٰكَ حَدِيثُ مُوسَىٰٓ (١٥)

2 በቀስታ መምዘዝንም መዛገሮች በሆኑት እምላለሁ።
3 መዋኘትንም ዋኚዎች በሆኑት እምላለሁ።
4 መቅደምንም ቀዳሚዎች በሆኑት እምላለሁ።
5 ነገርንም አስተናባሪዎች በሆኑት (መላእክት) እምላለሁ፤(በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ)።
6 ተርገፍጋፊይቱ (ምድር)በምትርገፈገፍበት ቀን፤
7 ለጣቂይቱ/ተከታይቱ/ የምትከተላት ስትሆን (ትቀሰቀሳላችሁ)።
8 በዚያ ቀን ልቦች ተሸባሪዎች ናቸው።
9 ዓይ ቻቸው ተዋራጆች (አቀርቃሪዎች) ናቸው።
10 እኛ ወደ መጀመሪያይቱ ሁኔታ ተመላሾች ነን? ይላሉ።
11 የበሰበሱ አጥንቶች በሆንን ጊዜ (እንቀሰቀሳለን?)
12 ይህች ያን ጊዜ ባለ ከሳራ መመለስ ናት ይላሉ።

---

[1] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።
1.የአላህ (ﷻ) ተአምሮችን ለማስተዋል ግፊት ማሳደር፣
2. ሰዎች የተጨቃጨቁበት የነበረውን የቂያማ ዕለት አይቀሬ መሆኑን ማረጋገጥ፣
3.ዛሬ ሠዎች የተጠራጠሩት ያለው የቂያማ ቀን ጉዳይ የሰው ልጆች ከሞቱበት እለት ጀምሮ የሚያረጋግጡት ጉዳይ መሆኑን፣
4. ግፈኛነትን በግልፅ ማውገዝ፣
5.የሰው ልጆች ተግባር ደግም ይሁን መጥፎ የሚመዘገብ መሆኑን፣
6.የቂያማ ቀን ቅጣት ለከሀዲች ዘላለማዊ መሆኑን፣
7. የፈራሀያን ክብርና ደረጃ ምን እንደሆነ ማሣወቅ፣
8. ስለጀነት አጠር ያለችና ውብ የሆነች ማብራሪያና አጓጊ መግለጫ፣
9. ውሸት እና አሉባልታ ንግግር አስቀያሚነታቸውን በግልፅ ማስረዳት፣
10. የቂያማ ዕለት ሁኔታዎች በጣም ከባድ እንደሆኑና ያስተባበሉት ሁሉ የሚጠብቃቸው እጅግ አስከፊ ቅጣት እንደሆነ፣
11. መልካም ስራዎችን እንዲሠሩ ግፊት ማሳደርና ከመጥፎ እንዲታቀቡ ማስጠንቀቅን፡-
12. ከአላህ ፊት መላዒኮች እንኳን ቢሆኑ ያለፍቃዱ መናገር እንደማይችሉ፤
13. የአላህን ተአምራት ማስተዋል አስፈላጊ መሆኑንና ይህም አላህን እንድንፈራው እንድንገዛውና እንድናመሰግነው እንደሚያደርገን፤ 14-አላህን የፈሩ በፍርዱ ዕለት ክብርና ደረጃቸው ከፍ ያለ መሆኑንና ስለ ጀነት ውበትና ማራኪነት እንማራለን።
[2] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው።
[3] ከ10-12 ያሉት አንቀፆች የወረዱበት ምክንያት፡- «እኛ ወደ መጀመሪያይቱ ሁነታ ተመላሾች ነን» የሚለው የቁርአን አንቀጽ ሲወርድ መኮች ከሞትን በኋላ የምንቀሰቀስ ከሆነማ ከሰርን በማለታቸው ነው ። (ሱዩጢ።)

إِذْ نَادَىٰهُ رَبُّهُۥ بِٱلْوَادِ ٱلْمُقَدَّسِ طُوًى ﴿١٦﴾ ٱذْهَبْ إِلَىٰ فِرْعَوْنَ إِنَّهُۥ طَغَىٰ ﴿١٧﴾
فَقُلْ هَل لَّكَ إِلَىٰٓ أَن تَزَكَّىٰ ﴿١٨﴾ وَأَهْدِيَكَ إِلَىٰ رَبِّكَ فَتَخْشَىٰ ﴿١٩﴾ فَأَرَىٰهُ
ٱلْـَٔايَةَ ٱلْكُبْرَىٰ ﴿٢٠﴾ فَكَذَّبَ وَعَصَىٰ ﴿٢١﴾ ثُمَّ أَدْبَرَ يَسْعَىٰ ﴿٢٢﴾ فَحَشَرَ
فَنَادَىٰ ﴿٢٣﴾ فَقَالَ أَنَا۠ رَبُّكُمُ ٱلْأَعْلَىٰ ﴿٢٤﴾ فَأَخَذَهُ ٱللَّهُ نَكَالَ ٱلْـَٔاخِرَةِ وَٱلْأُولَىٰٓ
﴿٢٥﴾ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَعِبْرَةً لِّمَن يَخْشَىٰٓ ﴿٢٦﴾ ءَأَنتُمْ أَشَدُّ خَلْقًا أَمِ ٱلسَّمَآءُ ۚ بَنَىٰهَا
﴿٢٧﴾ رَفَعَ سَمْكَهَا فَسَوَّىٰهَا ﴿٢٨﴾ وَأَغْطَشَ لَيْلَهَا وَأَخْرَجَ ضُحَىٰهَا ﴿٢٩﴾
وَٱلْأَرْضَ بَعْدَ ذَٰلِكَ دَحَىٰهَآ ﴿٣٠﴾ أَخْرَجَ مِنْهَا مَآءَهَا وَمَرْعَىٰهَا ﴿٣١﴾
وَٱلْجِبَالَ أَرْسَىٰهَا ﴿٣٢﴾ مَتَـٰعًا لَّكُمْ وَلِأَنْعَـٰمِكُمْ ﴿٣٣﴾ فَإِذَا جَآءَتِ ٱلطَّآمَّةُ
ٱلْكُبْرَىٰ ﴿٣٤﴾ يَوْمَ يَتَذَكَّرُ ٱلْإِنسَـٰنُ مَا سَعَىٰ ﴿٣٥﴾ وَبُرِّزَتِ ٱلْجَحِيمُ
لِمَن يَرَىٰ ﴿٣٦﴾ فَأَمَّا مَن طَغَىٰ ﴿٣٧﴾ وَءَاثَرَ ٱلْحَيَوٰةَ ٱلدُّنْيَا ﴿٣٨﴾ فَإِنَّ ٱلْجَحِيمَ
هِىَ ٱلْمَأْوَىٰ ﴿٣٩﴾ وَأَمَّا مَنْ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ وَنَهَى ٱلنَّفْسَ عَنِ ٱلْهَوَىٰ
﴿٤٠﴾ فَإِنَّ ٱلْجَنَّةَ هِىَ ٱلْمَأْوَىٰ ﴿٤١﴾ يَسْـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلسَّاعَةِ أَيَّانَ مُرْسَىٰهَا
﴿٤٢﴾ فِيمَ أَنتَ مِن ذِكْرَىٰهَآ ﴿٤٣﴾ إِلَىٰ رَبِّكَ مُنتَهَىٰهَآ ﴿٤٤﴾ إِنَّمَآ أَنتَ مُنذِرُ
مَن يَخْشَىٰهَا ﴿٤٥﴾ كَأَنَّهُمْ يَوْمَ يَرَوْنَهَا لَمْ يَلْبَثُوٓا۟ إِلَّا عَشِيَّةً أَوْ ضُحَىٰهَا ﴿٤٦﴾

ترتيبها ٨٠ — سُورَةُ عَبَسَ — آياتها ٤٢

13 እርሷ አንዲት ጩኸት ብቻ ናት::
14 ወዲያዉኑ እንቅልፍ በሌለባት ቦታ ላይ ይሆናሉ::
15 የሙሳ ወሬ መጣልህን?
16 ጌታው በተቀደሰው ሸለቆ በጡዋ በጠራው ጊዜ
17 ወደ ፊርዖን ሒድ፤ ወሰን አልፏልና::
18 ራስህን ለማጥራት ትመኛለህን? በለውም::
19 ጌታህን ትፈራ ዘንድ ልመራህ፤ (መንገ-ድ አለህን?) አለው።
20 (ሙሳ ለፊርዖን)ታላቂቱንም ታምር አሳየው::
21 ፊርዖውንም ሙሳን አስተባበለም፤ አመፀም።
22 ከዚያም (ለማጥፋት) የሚተጋ ሆ ዞረ።
23 (ሰራዊቶቹን) ሰበሰበም፤ ተጣራም።
24 እኔ ታላቁ ጌታችሁ ነኝ አለም።
25 አላህም በኋለኛይቱና በፊተኛይቱ (ቃል) ቅጣት ያዘው።
26 በዚህ ውስጥ አላህን ለሚፈራ ሰው ሁሉ በእርግጥ መገምገሚያና ማስጠንቀቂያ አለበት።
27 ባፈጣጠር እናንተ ይበልጥ የበረታችሁ ናችሁን? ወይንስ ሰማይ ? (አላህ) ገነባት፥፥
28 ከፍታዋን አጎነ፤ አስተካከላትም።
29 ሌሊቷንም አጨለመ ፤ ቀንዋንም ግልፅ አደረገ።
30 ምድርንም ከዚህ በኋላ ዘረጋት።
31 ውሃዋንና ግጦሿን ከርሷ አወጣ።
32 ጋራዎችንም አደላደላቸው።/ቸከላቸው/::
33 ለእናንተና ለእንስሳዎቻችሁ መጣቀሚያ ይሆን ዘንድ (ይህን አደረገ።)
34 ታላቂቱም መዐት በመጣች ጊዜ፤
35 ሰው ሁሉ የሰራውን በሚያስታውስበት ቀን፥
36 ገሀነምም ለሚያይ ሰው በተገለጠች ጊዜ የካደ ሰውማ፣
38 ቅርቢቱንም ህይወት የመረጠ ፥
39 በእርግጥ ጀሀነም መ ሪያው ናት።
40 በጌታው ፊት መቆምን የፈራና ነፍሱንም ከዝንባሌዋ የከለከለ ሰውማ፥
41 በእርግጥ ገነት መ ሪያው ናት።[1]
42 ከሞት መነሻዋ ሰዓት መቼ ም ንደምትከሰት ይጠይቁሃል
43 ስለመሆኑ አንተ ስለዚያች እለት ምን ውቀት ይኖርሃል?
44 የ ርሷ ጉዳይ የሚመለሰው ወደ ጌ ህ ብቻ ነው::
45 አንተ ያለብህ ለሚፈራት ሰው ከወዲሁ ማስጠንቀቅ ነው::
46 እነርሱ የሚያዩዋት ቀን የአንዲትን ቀን ምሽት ወይም ረፋዷን እንጅ ያልቆዩ ይመስላሉ::

## 80 ኛው ምዕራፍ:- የማጨፍገግ ምዕራፍ ነው::[2] (ሱራህ ዐበሰ)

---

[1] ከሱራው ከ ምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ::
1.አላህ (ﷻ) በፈለገው መማል የሚችል መሆኑን እና ሰ-ዎች ግን ከአላህ (ﷻ) ሌላ ለመማል እንደማይችሉ፣
2.የሙዕሚን ሩህ እና የካፊር ሩህ አወጣጥና ሞት እንኳን ልዩነት እንዳለው፣
3. አስተማሪ የሆነ ሰው አላማውን ለማሣካት ትግስት እንደሚያስፈልገው፣
4.ነቢዩላህ ሙሣ ከጌታቸው ጋር በቀጥታ እንደተነጋገሩ፣
5. የሰው ልጅ ሕይወት ከክስረት ልትፀዳ የምትችለው በኢስላም ብቻ መሆኑ፣
6. አላህን (ﷻ) መፍራት ሣያውቁት እንደማይገኝ፣
7.ተዓምሮችን ማየት ማመንን በቁርጠኝነት እንደሚያስከትል ፣
8. የጌትነትን ስልጣን የሚቀናቀን ሁሉ ኢምንትም ብትሆን የሚጠብቀው ቅጣት አስከፊ መሆኑን፣
9. ፊርኦን አምባገነን እንደነበርና ውድቀቱ ምን ይመስል እንደነበር፣
10. አላህ (ﷻ) ለሰው ልጆች የዋለው ውለታ ምን ያህል አያሌ እንደሆነ፣
11.ግዙፍ ነገሮች ለጥቃቅን ነገሮች ማስረጃ ስለ መሆናቸው፤
12. እንደዚሁም ብዙ ነገሮች ለጥቂቶች ማስረጃ መሆናቸው፣
13. የሰው ልጆች በቂያማ እለት የጀነት ሰዎችና የገሀነም ሰዎች በሚባል ለሁለት እንደሚከፈሉ፣ 14. ስለ ቂያማ እለትና ስለተሰወሩ ነገሮች የሚያውቅ አንድ አላህ (ﷻ) እንጂ ሌላ እንደሌለ፣
15. የትንሣኤ ዕለት መከራ አንዱ ሌላውን እንደሚያስረሳ፤ የሰው ልጅ ሕይወት ከክስረት ልትፀዳ የምትችለው በኢስላም ብቻ እንደሆነ እንማራለን::

[2] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ
عَبَسَ وَتَوَلَّىٰٓ ﴿١﴾ أَن جَآءَهُ ٱلْأَعْمَىٰ ﴿٢﴾ وَمَا يُدْرِيكَ لَعَلَّهُۥ يَزَّكَّىٰٓ ﴿٣﴾ أَوْ
يَذَّكَّرُ فَتَنفَعَهُ ٱلذِّكْرَىٰٓ ﴿٤﴾ أَمَّا مَنِ ٱسْتَغْنَىٰ ﴿٥﴾ فَأَنتَ لَهُۥ تَصَدَّىٰ ﴿٦﴾
وَمَا عَلَيْكَ أَلَّا يَزَّكَّىٰ ﴿٧﴾ وَأَمَّا مَن جَآءَكَ يَسْعَىٰ ﴿٨﴾ وَهُوَ يَخْشَىٰ ﴿٩﴾ فَأَنتَ
عَنْهُ تَلَهَّىٰ ﴿١٠﴾ كَلَّآ إِنَّهَا تَذْكِرَةٌ ﴿١١﴾ فَمَن شَآءَ ذَكَرَهُۥ ﴿١٢﴾ فِى صُحُفٍ مُّكَرَّمَةٍ
﴿١٣﴾ مَّرْفُوعَةٍ مُّطَهَّرَةٍۭ ﴿١٤﴾ بِأَيْدِى سَفَرَةٍ ﴿١٥﴾ كِرَامٍۭ بَرَرَةٍ ﴿١٦﴾ قُتِلَ ٱلْإِنسَٰنُ
مَآ أَكْفَرَهُۥ ﴿١٧﴾ مِنْ أَىِّ شَىْءٍ خَلَقَهُۥ ﴿١٨﴾ مِن نُّطْفَةٍ خَلَقَهُۥ فَقَدَّرَهُۥ ﴿١٩﴾ ثُمَّ
ٱلسَّبِيلَ يَسَّرَهُۥ ﴿٢٠﴾ ثُمَّ أَمَاتَهُۥ فَأَقْبَرَهُۥ ﴿٢١﴾ ثُمَّ إِذَا شَآءَ أَنشَرَهُۥ ﴿٢٢﴾ كَلَّا لَمَّا
يَقْضِ مَآ أَمَرَهُۥ ﴿٢٣﴾ فَلْيَنظُرِ ٱلْإِنسَٰنُ إِلَىٰ طَعَامِهِۦٓ ﴿٢٤﴾ أَنَّا صَبَبْنَا ٱلْمَآءَ صَبًّا
﴿٢٥﴾ ثُمَّ شَقَقْنَا ٱلْأَرْضَ شَقًّا ﴿٢٦﴾ فَأَنۢبَتْنَا فِيهَا حَبًّا ﴿٢٧﴾ وَعِنَبًا وَقَضْبًا ﴿٢٨﴾
وَزَيْتُونًا وَنَخْلًا ﴿٢٩﴾ وَحَدَآئِقَ غُلْبًا ﴿٣٠﴾ وَفَٰكِهَةً وَأَبًّا ﴿٣١﴾ مَّتَٰعًا لَّكُمْ
وَلِأَنْعَٰمِكُمْ ﴿٣٢﴾ فَإِذَا جَآءَتِ ٱلصَّآخَّةُ ﴿٣٣﴾ يَوْمَ يَفِرُّ ٱلْمَرْءُ مِنْ أَخِيهِ ﴿٣٤﴾
وَأُمِّهِۦ وَأَبِيهِ ﴿٣٥﴾ وَصَٰحِبَتِهِۦ وَبَنِيهِ ﴿٣٦﴾ لِكُلِّ ٱمْرِئٍ مِّنْهُمْ يَوْمَئِذٍ شَأْنٌ
يُغْنِيهِ ﴿٣٧﴾ وُجُوهٌ يَوْمَئِذٍ مُّسْفِرَةٌ ﴿٣٨﴾ ضَاحِكَةٌ مُّسْتَبْشِرَةٌ ﴿٣٩﴾ وَوُجُوهٌ
يَوْمَئِذٍ عَلَيْهَا غَبَرَةٌ ﴿٤٠﴾ تَرْهَقُهَا قَتَرَةٌ ﴿٤١﴾ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْكَفَرَةُ ٱلْفَجَرَةُ ﴿٤٢﴾

## አንቀጾቹ 42 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

(1) (2) አይነ[1] ስውሩ ወደ እርሱ ስለ
መጣ፥፥ (ሙሐመድ) ፊቱን አጨፈገገና ዞረ፤
(3) (ሙሐመድ ሆይ) ምን ያሳውቅሃል? ምን አልባትም ይህ ሰው ከአንተ በሚሰማው ምክር (ከኃጢአቶቹ) ሊጥራራ ይከጀላል።
(4) ወይም ሊገሠጽና፥ ግሣጼይቱም ልትጠቅመው (ይከጀላል)፡፡
(5) (6) (ከአላህ) የተብቃቃውን ሰውማ አንተ ለእርሱ (ለእምነተ ቢሱ) ትዘጋጃለህ፡፡
(7) ባይጥራራ[2] (ባያምን) ባንተ ላይ ምንም የሌለብህ ስትሆን፤
(8) (9) (10) ያ፡ እየገሰገሰ የመጣው ሰው፤ እርሱ (አላህን) የሚፈራ ሲሆን፤ አንተ ከእርሱ ትዘዘናጋለህ።
(11) ተከልከል፤ እርሷ ማስገንዘቢያ ናት።
(12) የሻም ሰው (ቁርአኑን) ያስታውሰዋል።
(13) በተከበሩ ጽሁፎች ውስጥ ነው።
(14) ከፍ በተደረገች፤ ንጹህም በተደረገች (ጽሁፍ ውስጥ ነው)።
(15) በጸሀፊዎች (መላእክት) እጆች (ንጹህ የተደረገች)።
(16) የተከበሩና ታዛገሮች በሆኑት (ጸሀፊዎች እጆች)።
(17) ሰው ተረገመ፡፡ ምን ከሓዲ አደረገው?
(18) (ጌታው) ከምን ነገር ፈጠረው? (አያስብምን?)
(19) ከፍትወት ጠብታ ፈጠረው ፤ መጠነውም።
(20) ከዚያም (መውጫ) መንገዱን አገራው።
(21) ከዚያም ገደለው፤ እንዲቀበርም አደረገው፤
(22) ከዚያም ማንሳቱን በሻ ጊዜ ያነሳዋል።
(23) በእውነት ያንን (ጌታው) ያዘዘውን ገና አልፈጸመም።
(24) ሰውም ወደ ምግቡ ይመልከት፤
(25) እኛ ውሃን ማንቧቧትን ያንቧቧን መሆናችንን፤
(26) ከዚያም ምድርን (በደካማ ቡቃያ) መሰንጠቅን የሰነጠቅን ፤
(27) በውስጧም እህልን ያበቀልን ፤
(28) ወይንንም፤ እርጥብ ሳርንም ፤
(29) የዘይት ወይራንም ዘንባባንም፤
(30) ጭፍቆች አትክልቶችንም ፤
(31) ፍራፍሬንም ገለባንም (ያበቀልን መሆናችንን ይመልከት)።
(32) ለእናንተም ለእንስሶቻችሁም መጠቀሚያ ይሆን ዘንድ(ይህን ሠራን)።
(33) አደንቋሪይቱ[3] መከራ በመጣች ጊዜ፥
(34) ሰው ከወንሙ በሚሸሽበት ቀን ፥
(35) ከናቱም ከአባቱም ፥
(36) ከሚስቱም ከልጁም፥
(37) ከእነሱ ለየሰው ሁሉ በዚያ ቀን (ከሌላው) የሚያብቃቃው ሁኔታ አለው።
(38) ፊቶች በእዚያ ቀን አብሪዎች ናቸው።
(39) ሳቂዎችም ተደሳቾችም ናቸው።
(40) ፊቶችም በእዚያ ቀን በላያቸው ላይ ትቢያ አልለባቸው፤
(41) ጥቁረት ትሸፍናቸዋለች ፤
(42) እነዚያ እነርሱ ከሓዲዎችና አመጠኞች ናቸው[4]።

---

[1] ከ 1-2ኛ ያሉ አንቀፆች የወረዱበት ምክንያት፡- ›ዓብደላህ ብን ኡሚ መክቱም የተባሉ አይነ-ሠውር ሱሃቢ ለመማር ጓግተው ወደ ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ሲመጡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የመካ አዛውንቶችን ያነጋገሩ ስለ ነበር ለጊዜው እሱን ማናገር ባለመፈለጋቸውና ፊታቸውን በማዞራቸው ነው። (ዋሂዲ እና ሱዩጢ።)

[2] 7ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክናየት፡- ሱረቱ አን-ነጅም በወረደ ጊዜ ኡትበት ኢብኑ አቢለሃብ በነጅም ጌታ እክጃለሁ በማለቱ ነው ። (ሱዩጢ)

[3] ከ33-42 ስለ ቂያማ ቀንና ዝናዋ የሚያወሱ አናቅጽ ናቸው፡፡

[4] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡
1. ስለ ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ትልቅነት፣
2. ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) በዚህ ወቀሳ ሳይቀየሙ ባለታሪኩን ይሰጡት የነበረው ክብር የሳቸውን ትልቅነት እንደሚያሳይ ፣
3. ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ወቀሳውን ሳይቀንሱና ሳያስተካክሉ ለሕዝብ ጆሮ ማብቃታቸው ታማኝነታቸውን በግልጽ አንደሚያሳይ፣

سُورَةُ التَّكۡوِيرِ
آياتها ٢٩ — ترتيبها ٨١

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

إِذَا ٱلشَّمۡسُ كُوِّرَتۡ ١ وَإِذَا ٱلنُّجُومُ ٱنكَدَرَتۡ ٢ وَإِذَا ٱلۡجِبَالُ
سُيِّرَتۡ ٣ وَإِذَا ٱلۡعِشَارُ عُطِّلَتۡ ٤ وَإِذَا ٱلۡوُحُوشُ حُشِرَتۡ
٥ وَإِذَا ٱلۡبِحَارُ سُجِّرَتۡ ٦ وَإِذَا ٱلنُّفُوسُ زُوِّجَتۡ ٧ وَإِذَا
ٱلۡمَوۡءُۥدَةُ سُئِلَتۡ ٨ بِأَيِّ ذَنۢبٖ قُتِلَتۡ ٩ وَإِذَا ٱلصُّحُفُ نُشِرَتۡ
١٠ وَإِذَا ٱلسَّمَآءُ كُشِطَتۡ ١١ وَإِذَا ٱلۡجَحِيمُ سُعِّرَتۡ ١٢ وَإِذَا ٱلۡجَنَّةُ
أُزۡلِفَتۡ ١٣ عَلِمَتۡ نَفۡسٞ مَّآ أَحۡضَرَتۡ ١٤ فَلَآ أُقۡسِمُ بِٱلۡخُنَّسِ ١٥
ٱلۡجَوَارِ ٱلۡكُنَّسِ ١٦ وَٱلَّيۡلِ إِذَا عَسۡعَسَ ١٧ وَٱلصُّبۡحِ إِذَا تَنَفَّسَ ١٨
إِنَّهُۥ لَقَوۡلُ رَسُولٖ كَرِيمٖ ١٩ ذِي قُوَّةٍ عِندَ ذِي ٱلۡعَرۡشِ مَكِينٖ ٢٠ مُّطَاعٖ
ثَمَّ أَمِينٖ ٢١ وَمَا صَاحِبُكُم بِمَجۡنُونٖ ٢٢ وَلَقَدۡ رَءَاهُ بِٱلۡأُفُقِ ٱلۡمُبِينِ
٢٣ وَمَا هُوَ عَلَى ٱلۡغَيۡبِ بِضَنِينٖ ٢٤ وَمَا هُوَ بِقَوۡلِ شَيۡطَٰنٖ رَّجِيمٖ ٢٥
فَأَيۡنَ تَذۡهَبُونَ ٢٦ إِنۡ هُوَ إِلَّا ذِكۡرٞ لِّلۡعَٰلَمِينَ ٢٧ لِمَن شَآءَ مِنكُمۡ أَن
يَسۡتَقِيمَ ٢٨ وَمَا تَشَآءُونَ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٢٩

سُورَةُ الانفطار
آياتها ٢٩ — ترتيبها ٨٢

## 81 ኛው ምዕራፍ፡- የመጠቅለል ምዕራፍ ነው[1]፡፡ (ሱራህ አት-ተክዊር) አንቀጾቹ 29 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)፡፡

1 ፀሐይ በተጠቀለለች ጊዜ፤
2 ከዋክብትም በረገፉ ጊዜ፤
3 ተራራዎች በተናዱ ጊዜ፤
4 የዐሥር ወር እርጉዝ ግመሎች (ያለጠባቂ) በተተዉ ጊዜ ፤
5 እንስሳትም ሁሉ በተሰበሰቡ ጊዜ፤
6 ባህሮችም በተቃጠሉ ጊዜ፤
7 ነፍሶችም (ከየአካሎቻቸው) በተቆራኙ ጊዜ፤
8 ከነሕይወቷ የተቀበረችውም ሴት ልጅ በተጠየቀች ጊዜ፤
9 በምን ወንጀል እንደተገደለች ፤
10 ጽሑፎችም በተዘረጉ ጊዜ ፤
11 ሰማይም በተገሸለጠች ጊዜ ፤
12 ገሀነምም በተነደደች ጊዜ ፤
13 ገነትም በተቀረበች ጊዜ ፤
14 ነፍስ ሁሉ (ከሥራ) ያቀረበችውን ታውቃለች ፤
15 ተመላሾችም በሆኑት እምላለሁ፡፡
16 ሂያጆች ገቢዎች በሆኑት (ከዋክብት)፡፡
17 በሌሊቱም (ጨለማውን) በጠነሰሰ ጊዜ ፤
18 በንጋቱም (በብርሃን) በተነፈሰ ጊዜ (እምላለሁ)፡፡
19 እርሱ (ቁርአን) የክቡር መልዕክተኛ ቃል ነው፡፡
20 የኃይል ባለቤት፣ ከዙፋኑ ባለቤት ዘንድ ባለሟል የሆነ ፤
21 በዚያ ስፍራ ትዕዛዙ ተሰሚ ታማኝ የሆነ (መልክተኛ ቃል) ነው፡፡
22 ነቢያችሁም በፍጹም እብድ አይደለም፡፡
23 በግልጹ አድማስም በእርግጥ አይቶታል፡፡
24 እርሱም በሩቁ ወሬ ላይ ሰሳች (ንፉግ) አይደለም፡፡
25 እርሱም (ቁርአን) የርጉም ሰይጣን ቃል አይደለም፡፡
26 ታዲያ ወዴት ትሄዳላችሁ ?
27 እርሱ የዓለማት መገሠጫ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡
28 ከእናንተ ቀጥተኛ ሰው መሆንን ለፈለገ ሰው (መገሠጫ ነው)፡፡
29 የዓለማት[2] ጌታ አላህ ካልሻ አትሹም፡፡[3]

---

4.በእነዚህ አንቀፆች የአላህን (ﷻ) ችሎታ፣ ጥልቅ ዕውቀት፣ አስደናቂ ጥበብና ትልቅነት መመልከት፣
5.ሥራ ሰሪውን እንደሚያመለክት ሁሉ ፍጡሮችም በራሳቸው ፈጣሪ እንዳላቸውና ሁሉን ቻይነቱን አዋቂነቱን አለመረዳታቸው የሚገርም መሆኑን፣
6.የሰው ልጅ እድሜውን ሙሉ ቢሰግድና ቢፆም የአላህን (ﷻ) ሐቅ በትክክል እንደማይወጣ፣
7.የቂያማ ቀን መከራ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ፣
8.የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ሲኖር ያልተወጣቸው ግዴታዎች በዚያኛው ዓለም ምን ያህል ሊያስቸግሩት እንደሚችሉ፣ 9. ከትንሳዔ አስደንጋጭነት የተነሳ ወዳጅ ከወዳጁ የሚርቅበት ሌላው ቀርቶ ወንድም ከወንድሙ፣ ልጅ ከወላጆቹ ወዘተ የሚሸሽበት ቀን መሆኑን፣ 10. የኢማን ውጤት የቂያማ እለት በፊት ላይ እንደሚያበራና አማኞች እንደሚደሰቱ ሁሉ የኩፍርም ውጤት እንደዚሁ በፊት ላይ ከሰል ሆኖ የካህዲያን ፊት በፍርሃት እንደሚጠቁር እንማራለን፡፡

[1] ምዕራፉ፡- በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው፡፡

---

[2] 29ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- «ከእናንተ ቀጥተኛ መሆንን ለሻ ሰው» የሚለው የቁርአን አንቀጽ ሲወርድ እነ አቡ ጅህል ይህማ እኛ እንደፈለግነው ነው ማለት ነው ብንፈልግ እንስተካከላለን ባንፈልግ ግን እንተዋለን በማለታቸው ነው፡፡

[3] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡
1.ሞቶ መነሳትና ሒሳብ መኖሩ ቅንጣት ያህል የማያጠራጥር እንደሆነ ፣
2.ስለ ቂያማ መነሻና መድረሻ ሰፊ ማብራሪያ፣
3.ገነት የዓማኞች ማረፊያ መሆኑዋን በማውሳት ገሀነም ደግሞ የአጋሪዎች መኖሪያ መሆኑዋን በመጥቀስ በኢማንና በመልካም ሥራ ላይ ግፊት ማሳደር፣
4.ከሽርክና ከወንጀል ማስፈራራትና ማስጠንቀቅ፣
5.በአላህ ስሞቹና በባህሪያቱ መማል እንደሚፈቀድ፣

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ
إِذَا ٱلسَّمَآءُ ٱنفَطَرَتۡ ﴿١﴾ وَإِذَا ٱلۡكَوَاكِبُ ٱنتَثَرَتۡ ﴿٢﴾ وَإِذَا ٱلۡبِحَارُ
فُجِّرَتۡ ﴿٣﴾ وَإِذَا ٱلۡقُبُورُ بُعۡثِرَتۡ ﴿٤﴾ عَلِمَتۡ نَفۡسٞ مَّا قَدَّمَتۡ
وَأَخَّرَتۡ ﴿٥﴾ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ مَا غَرَّكَ بِرَبِّكَ ٱلۡكَرِيمِ ﴿٦﴾ ٱلَّذِي
خَلَقَكَ فَسَوَّىٰكَ فَعَدَلَكَ ﴿٧﴾ فِيٓ أَيِّ صُورَةٖ مَّا شَآءَ رَكَّبَكَ ﴿٨﴾
كَلَّا بَلۡ تُكَذِّبُونَ بِٱلدِّينِ ﴿٩﴾ وَإِنَّ عَلَيۡكُمۡ لَحَٰفِظِينَ ﴿١٠﴾ كِرَامٗا
كَٰتِبِينَ ﴿١١﴾ يَعۡلَمُونَ مَا تَفۡعَلُونَ ﴿١٢﴾ إِنَّ ٱلۡأَبۡرَارَ لَفِي نَعِيمٖ ﴿١٣﴾ وَإِنَّ
ٱلۡفُجَّارَ لَفِي جَحِيمٖ ﴿١٤﴾ يَصۡلَوۡنَهَا يَوۡمَ ٱلدِّينِ ﴿١٥﴾ وَمَا هُمۡ عَنۡهَا بِغَآئِبِينَ
﴿١٦﴾ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ ﴿١٧﴾ ثُمَّ مَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ
﴿١٨﴾ يَوۡمَ لَا تَمۡلِكُ نَفۡسٞ لِّنَفۡسٖ شَيۡـٔٗاۖ وَٱلۡأَمۡرُ يَوۡمَئِذٖ لِّلَّهِ ﴿١٩﴾

## سُورَةُ المُطَفِّفِينَ

ترتيبها ٨٣ — آياتها ٣٦

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ
وَيۡلٞ لِّلۡمُطَفِّفِينَ ﴿١﴾ ٱلَّذِينَ إِذَا ٱكۡتَالُواْ عَلَى ٱلنَّاسِ يَسۡتَوۡفُونَ ﴿٢﴾
وَإِذَا كَالُوهُمۡ أَو وَّزَنُوهُمۡ يُخۡسِرُونَ ﴿٣﴾ أَلَا يَظُنُّ أُوْلَٰٓئِكَ أَنَّهُم
مَّبۡعُوثُونَ ﴿٤﴾ لِيَوۡمٍ عَظِيمٖ ﴿٥﴾ يَوۡمَ يَقُومُ ٱلنَّاسُ لِرَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿٦﴾

## 82 ኛው ምዕራፍ:-የመሰንጠቅ ምዕራፍ ነው::[1] (ሱረቱ አል-ኢንፊጧር) አንቀጾቹ 29 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 ሰማይ በተሰነጠቀች ጊዜ ፤
2 ከዋክብትም ተበታትነው በወደቁ ጊዜ፤
3 ባህሮችም በተከፈቱና በተደበላለቁ ጊዜ፤
4 መቃብሮችም በተገለባበጡና (ሙታን) በተነሱ ጊዜ፤
5 ማንኛይቱም ነፍስ ያስቀደመችውንና ያቆየችውን ታውቃለች።
6 አንተ[2] ሰው ሆይ! በቸሩ ጌታህ ምን አታለለህ?
7 በዚያ በፈጠረህ፤ አካለ ሙሉም ባደረገህ፣ ባስተካከለህም።
8 በማንኛውም በሻው ቅርጽ በገጣጠመህ (ጌታህ ምን አታለለህ)።
9 ተከልከሉ፤ በእውነቱ በፍርዱ ቀን ታስተባብላላችሁ።
10 በናንተ ላይ ተጠባባቂዎች ያሉባችሁ ስትሆኑ፤
11 የተከበሩ ጸሐፊዎች የሆኑ (ተጠባባቂዎች) ፤
12 የምትሰሩትን ሁሉ የሚያውቁ ፤
13 እውነተኞቹ አማኞች በእርግጥ በገነት ውስጥ ናቸው።
14 ከሓዲዎቹም በእርግጥ በገሀነም ውስጥ ናቸው።
15 በፍርዱ ቀን ይገቧታል።
16 እነርሱም ከእርሷ ራቂዎች አይደሉም።
17 የፍርዱ ቀን ምን እንደሆነ ምን አሳወቀህ ?
18 ከዚያም የፍርዱ ቀን ምን እንደሆነ ምን አሳወቀህ ?
19 (እርሱ) ማንኛይቱም ነፍስ ለሌላይቱ ነፍስ ምንም ማድረግ የማትችልበት ቀን ነው። ነገሩም ሁሉ በዚያ ቀን ለአላህ ብቻ ነው።[3]

## 83 ኛው ምዕራፍ:-የሰላቢዎች ምዕራፍ ነው:: (ሱራቱ አል-ሙጦፊፊን) አንቀጾቹ 36 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 ለሰላቢዎች[4] ወዮላቸው ፤
2 ለነዚያ ከሰዎች ባስሰፈሩ ጊዜ የሚያስሞሉ ፤
3 ለነሱም (ለሰዎች) በሰፈሩ ወይም በመዘኑላቸው ጊዜ ፤ የሚያጎሉ (ለሆኑት)።
4 እነዚያ እነሱ ተቀስቃሾች መሆናቸውን

---

6. ወህይና ነቢይነት እውነት መሆኑን፤ ቁርአን የአላህ ቃል ነቢዩ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን፣
7.የመላኩ ጅብሪል ባህሪያትን ማስታወስ፣
8. ነቢዩ (ﷺ) አጋሪዎች ከሚሏቸው ሁሉ የፀዱ መሆናቸውን መግለፅ፣
9. የሰው ልጆችን ፍላጐት የአላህ (ﷻ) ፍላጐት እንደሚቀድምና እሱ ያልሻው ነገር እንደማይከሰት እንማራለን ::

[1] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው::
[2] 6ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:-
በኡበይ ቢን ኽለፍ ምክንያት ነው :: (ሱዩጢ ::)
[3] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ::
1.የመጀመሪያውን መንፋት የሚቀድሙ ልዩ ልዩ ክስተቶች እንዳሉ፣
2.መጥፎ ነገርን መጀመር ምን እንደሚያስከትል፣
3. እያንዳንዱ ሰው ጋር ሁለት መላይኮች እንዳሉና መልካም ሥራውም ሆነ መጥፎ ሥራው እንደሚፃፍ፣
4.የሰው ልጆች ለሁለት እንደሚከፈሉ የጀነት ወይም የገሀነም መሆኑን፣
5.የቂያማ ዕለት የሰው ልጆችን የማንም ሽምግልናና ወዳጅነት ከአላህ (ﷻ) ፈቃድ ውጭ የማይጠቅማቸው መሆኑን፤
6.የእያንዳንዱን ሰው መጥፎም ሆነ በጐ ሥራ የሚመዘግቡ ሁለት መላይኮች ከሁሉም ሰው ዘንድ አሉ:: የሰው ልጆችም ለሁለት ይከፈላሉ:: የጀነት ወይም የጀሀነም በመባል::
[4] 1ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:-
ነቢዩ (ﷺ) ወደ መዲና በተሰደዱ ጊዜ የመዲና ሰዎች በስፍር፣ በሚዛን ማጭበርበር የታወቁ ነበሩና እነሱን ለማረም ነው:: (ዋሂዲ እና ሱዩጢ::)

كَلَّآ إِنَّ كِتَٰبَ ٱلْفُجَّارِ لَفِى سِجِّينٍ ﴿٧﴾ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا سِجِّينٌ ﴿٨﴾ كِتَٰبٌ
مَّرْقُومٌ ﴿٩﴾ وَيْلٌ يَوْمَئِذٍ لِّلْمُكَذِّبِينَ ﴿١٠﴾ ٱلَّذِينَ يُكَذِّبُونَ بِيَوْمِ ٱلدِّينِ ﴿١١﴾
وَمَا يُكَذِّبُ بِهِۦٓ إِلَّا كُلُّ مُعْتَدٍ أَثِيمٍ ﴿١٢﴾ إِذَا تُتْلَىٰ عَلَيْهِ ءَايَٰتُنَا قَالَ أَسَٰطِيرُ
ٱلْأَوَّلِينَ ﴿١٣﴾ كَلَّا ۖ بَلْ ۜ رَانَ عَلَىٰ قُلُوبِهِم مَّا كَانُوا۟ يَكْسِبُونَ ﴿١٤﴾ كَلَّآ إِنَّهُمْ
عَن رَّبِّهِمْ يَوْمَئِذٍ لَّمَحْجُوبُونَ ﴿١٥﴾ ثُمَّ إِنَّهُمْ لَصَالُوا۟ ٱلْجَحِيمِ ﴿١٦﴾ ثُمَّ يُقَالُ
هَٰذَا ٱلَّذِى كُنتُم بِهِۦ تُكَذِّبُونَ ﴿١٧﴾ كَلَّآ إِنَّ كِتَٰبَ ٱلْأَبْرَارِ لَفِى عِلِّيِّينَ
﴿١٨﴾ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا عِلِّيُّونَ ﴿١٩﴾ كِتَٰبٌ مَّرْقُومٌ ﴿٢٠﴾ يَشْهَدُهُ ٱلْمُقَرَّبُونَ
﴿٢١﴾ إِنَّ ٱلْأَبْرَارَ لَفِى نَعِيمٍ ﴿٢٢﴾ عَلَى ٱلْأَرَآئِكِ يَنظُرُونَ ﴿٢٣﴾ تَعْرِفُ فِى
وُجُوهِهِمْ نَضْرَةَ ٱلنَّعِيمِ ﴿٢٤﴾ يُسْقَوْنَ مِن رَّحِيقٍ مَّخْتُومٍ ﴿٢٥﴾
خِتَٰمُهُۥ مِسْكٌ ۚ وَفِى ذَٰلِكَ فَلْيَتَنَافَسِ ٱلْمُتَنَٰفِسُونَ ﴿٢٦﴾ وَمِزَاجُهُۥ
مِن تَسْنِيمٍ ﴿٢٧﴾ عَيْنًا يَشْرَبُ بِهَا ٱلْمُقَرَّبُونَ ﴿٢٨﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ
أَجْرَمُوا۟ كَانُوا۟ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ يَضْحَكُونَ ﴿٢٩﴾ وَإِذَا مَرُّوا۟ بِهِمْ
يَتَغَامَزُونَ ﴿٣٠﴾ وَإِذَا ٱنقَلَبُوٓا۟ إِلَىٰٓ أَهْلِهِمُ ٱنقَلَبُوا۟ فَكِهِينَ ﴿٣١﴾
وَإِذَا رَأَوْهُمْ قَالُوٓا۟ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ لَضَآلُّونَ ﴿٣٢﴾ وَمَآ أُرْسِلُوا۟ عَلَيْهِمْ
حَٰفِظِينَ ﴿٣٣﴾ فَٱلْيَوْمَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ مِنَ ٱلْكُفَّارِ يَضْحَكُونَ ﴿٣٤﴾

አያውቁምን?
5 በታላቁ ቀን ፤
6 ሰዎች ሁሉ ለዓለማት ጌታ (ፍርድ) በሚቆሙበት ቀን (ተቀስቃሾች መሆናቸውን)።
7 በውነት የከሓዲዎቸ (የሰላቢዎቸ) መጽሐፍ በእርግጥ በሲጂን ውስጥ ነው።
8 ሲጂንም ምን እንደሆነ ምን አሳወቀህ?
9 የታተመ መጽሐፍ ነው።
10 ለአስተባባዮች በዚያ ቀን ወዮላቸው።
11 ለእነዚያ በፍርዱ ቀን ለሚያስተባብሉት።
12 በእርሱም ወሰን አላፊ ኃጢአተኛ ሁሉ እንጂ ሌላ አያስተባብልም።
13 አንቀጾቻችን በእርሱ ላይ በተነበቡ ጊዜ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ተረቶች ናቸው ይላል።
14 ይከልከሉ፤ ይልቁንም በልቦቻቸው ላይ ይሰሩት የነበሩት (ኃጢአት) ደገደገባቸው፤
15 ይከልከሉ፤ እነሱ በዚያ ቀን ከጌታቸው (ማየት) ተጋራጆች ናቸው።
16 ከዚያም እነርሱ በእርግጥ ገሀነምን ገቢዎች ናቸው።
17 ከዚያም ይህ ያ በእርሱ ታስተባብሉበት የነበራችሁት ነው ይባላል።
18 በእውነቱ የውነተኞቹ ምእምናን መጽሀፍ በዒሊዮን ውስጥ ነው።
19 ዒሊዮንም ምን እንደሆነ ምን አሳነሳ?
20 የታተመ መጽሀፍ ነው።
21 ባለሟልዎቹ ይጣዱታል።
22 እውነተኞች ምዕምናን በእርግጥ በ-ድሎት (ገነት) ውስጥ ናቸው።
23 በባለ አጎበር አልጋዎቹ ላይ ሆነው ይመለከታሉ።
24 በፊቶቻቸው ላይ የድሎትን ውበት ታውቃለህ።
25 ተጣርቶ ከታተመ ጠጅ ይጠጣሉ።
26 ማተሚያው ሚስክ ከሆነ። በዚህም ተሽቀዳዳሚዎች ይሽቀዳደሙ።
27 መበረዣውም ከተስኒም ነው።
28 ባለሟሎቹ ከእርሷ የሚጠጡላት ምንጭ ናት።
29 እነዚያ ያምመጡት በእነዚያ ባመኑት በእርግጥ ይስቁ ነበሩ።
30 በእነሱም ላይ ባለፉ ጊዜ ይጠቃቀሱ ነበር።
31 ወደ ቤተሰቦቻቸውም በተመለሱ ጊዜ (በመሳለቃቸው) ተደሳቾች ሆነው ይመለሱ ነበር።
32 ባዩዋቸውም ጊዜ፡- እነዚህ በእርግጥ ተሳሳቾች ናቸው ይሉ ነበር።
33 በእነሱ ላይ ተጠባባቂዎች ተደርገው ያልተላኩ ሲሆኑ።
34 ዛሬ (በትንሳዔ ቀን) እነዚያ ያመኑት በከሓዲዎቸ ይስቃሉ።
35 በባለ አጎበር አልጋዎች ላይ ሆነው የሚመለከቱ ሲሆኑ (ይስቃሉ)፤
36 ከሓዲዎች ይሰሩት የነበሩትን (ዋጋ) ተመነዱን ? (ይላሉ)።[1]

---

[1] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።
1.በሚዛንም ሆነ በሥፍር ማታለል ክልክል መሆኑን፣
2.የአብራሮች መዝገብና ምንዳቸው ምን እንደሚመስል፤
3.ከሞት በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ መነሳት የማይቀር ሐቅ ትክክለኛ መሆኑን፣
4.ያመፀኞች መዝገብ ከሰባት ምድር በታች እንደሆነ፣
5.በአላህ (ﷻ) በተዓምሮቹና በሞቶ መነሳት የሚያስተባብሉ ሁሉ ከፍተኛ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው፣
6.በወንጀል ላይ ከመዘውተር ማስጠንቀቅና ንሰሐ አለመግባት ቀልብን እንደሚያጠቁር አበክሮ መምከር፣
7.አላህን (ﷻ) አውነተኞች አማኞች በአኺራ የሚያዩት መሆኑን ማረጋገጥና ከሃዲያን ግን ጌታቸውን ማየት እንደማይችሉ፣

عَلَى ٱلۡأَرَآئِكِ يَنظُرُونَ ٣٥ هَلۡ ثُوِّبَ ٱلۡكُفَّارُ مَا كَانُواْ يَفۡعَلُونَ ٣٦

ترتيبها ٨٤ سُورَةُ الانشِقَاق آياتها ٢٥

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

إِذَا ٱلسَّمَآءُ ٱنشَقَّتۡ ١ وَأَذِنَتۡ لِرَبِّهَا وَحُقَّتۡ ٢ وَإِذَا ٱلۡأَرۡضُ مُدَّتۡ
٣ وَأَلۡقَتۡ مَا فِيهَا وَتَخَلَّتۡ ٤ وَأَذِنَتۡ لِرَبِّهَا وَحُقَّتۡ ٥ يَٰٓأَيُّهَا
ٱلۡإِنسَٰنُ إِنَّكَ كَادِحٌ إِلَىٰ رَبِّكَ كَدۡحٗا فَمُلَٰقِيهِ ٦ فَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ
كِتَٰبَهُۥ بِيَمِينِهِۦ ٧ فَسَوۡفَ يُحَاسَبُ حِسَابٗا يَسِيرٗا ٨ وَيَنقَلِبُ
إِلَىٰٓ أَهۡلِهِۦ مَسۡرُورٗا ٩ وَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ وَرَآءَ ظَهۡرِهِۦ ١٠ فَسَوۡفَ
يَدۡعُواْ ثُبُورٗا ١١ وَيَصۡلَىٰ سَعِيرًا ١٢ إِنَّهُۥ كَانَ فِيٓ أَهۡلِهِۦ مَسۡرُورًا ١٣
إِنَّهُۥ ظَنَّ أَن لَّن يَحُورَ ١٤ بَلَىٰٓۚ إِنَّ رَبَّهُۥ كَانَ بِهِۦ بَصِيرٗا ١٥ فَلَآ أُقۡسِمُ
بِٱلشَّفَقِ ١٦ وَٱلَّيۡلِ وَمَا وَسَقَ ١٧ وَٱلۡقَمَرِ إِذَا ٱتَّسَقَ ١٨
لَتَرۡكَبُنَّ طَبَقًا عَن طَبَقٖ ١٩ فَمَا لَهُمۡ لَا يُؤۡمِنُونَ ٢٠ وَإِذَا قُرِئَ
عَلَيۡهِمُ ٱلۡقُرۡءَانُ لَا يَسۡجُدُونَ ۩ ٢١ بَلِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يُكَذِّبُونَ
٢٢ وَٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِمَا يُوعُونَ ٢٣ فَبَشِّرۡهُم بِعَذَابٍ أَلِيمٍ ٢٤
إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَهُمۡ أَجۡرٌ غَيۡرُ مَمۡنُونِۭ ٢٥

## 84 ኛው ምዕራፍ:- የመቀደዱ ምዕራፍ (ሱረቱ አል-ኢንሺቃቅ ነው[1]) አንቀጾቹ 25 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 ሰማይ በተቀደደች/በተሰነጠቀች/ጊዜ፤
2 ለጌታዋም (ትዕዛዝ) በሰማች ጊዜ፤ (ልትሰማ) ተገባትም፤
3 ምድርም በተለጠጠች ጊዜ፤
4 በውስጧ ያለውንም ሁሉ በጣለችና ባዶ በሆነች ጊዜ ፤
5 ለጌታዋም በሰማች ጊዜ (መስማት) ተገባትም፤ (ሰው ሁሉ ስራውን ይገናኛል)፤
6 አንተ ሰው ሆይ፤ አንተ ጌታህን (በሞት) እስከምትገናኝ ድረስ ልፋትን ለፊ ነህ፤ ተገናኚውም ነህ።
7-9 መጽሐፉን በቀኙ እጅ የተሰጠ ሰው በእርግጥ ቀላልን ምርመራ ይመረመራል፤ ወደ ቤተሰቦቹም ተደሳች ሆ በደስታ ይመለሳል።
10 መጽሐፉን በጀርባው በኩል የተሰጠ ሰው፤
11 (ዋ! ጥፋቴ በማለት) ጥፋትን በእርግጥ ይጠራል።
12 የተጋጋመች እሳትንም ይገባል።
13 እርሱ በቤተሰቡ ውስጥ ተደሳች፣
14 እርሱም (ወደ አላህ) እንደማይመለስ ያስብ ነበርና።።
15 አይደለም (ይመለሳል)፤ ጌታው በርሱ (መመለስ) ዐዋቂ ነበር፤ (ነውም)።
16 አትካዱ ፤ በውጋገኑ ፣ እምላለሁ።
17 በሌሊቱም በሰበሰበውም ሁሉ፤
18 በጨረቃውም በሞላ ጊዜ (እምላለሁ) ።
19 ከሁኔታ በኋላ ወደ ሌላ ሁኔታ ትለዋወጣላችሁ፤ (ከአንድ እርከን ወደ ሌላ እርከን ትሸጋገራላችሁ።)
20 የማያምኑት ለእነርሱ ምን አላቸው? (ለምን አያምኑም?)
21 በእነሱ ላይ ቁርአን በተነበበ ጊዜ የማይሰግዱት (ለእነርሱ ምን አላቸው? /ለምን አይሰግዱም?)
22 በእርግጡ እነዚያ የካዱት (በትንሣኤ) ያስተባብላሉ።
23 አላህም (በልቦቻቸው) የሚቆጥሩትን ዐዋቂ ነው።
24 (መሐመድ ሆይ፣) በአሳማሚ ቅጣትም አብስራቸው።
25 ግን እነዚያ ያመኑና መልካሞችን የሠሩ ለእነሱ የማይቋረጥ ምንዳ አላቸው።[2]

---

8.ፈራህያንን ማሞገስና በጀነት ያዘጋጀላቸውን በምሳሌ አድርጎ መግለፅ ፣
9.የጀነትን ፀጋ ለማግኘት መልካም ሥራን ማብዛት እንደሚያስፈልግ በይፋ ማሳመን፣
10.በአላህ (ﷻ) ላይ ማመፅን ማውገዝና ማንቋሸሽ፣
11.የኢስላም ዳዕዋ ሲጀመር በመካ ሙስሊሞች ላይ ስለደረሰባቸው ስቃይና መከራ መግለጫ በጥቂቱ፣
12.ሙዕሚኖች በጀነት ሁነው ሙሽሪኮችን በገሀነም ውስጥ ሲሰቃዩ እንደሚያይዋቸው፣
13.አላህ (ﷻ) ወዳጆቹን እንደሚያስከብርና ጠላቶቹን እንደሚያዋርድ የሚሉት ናቸው።።

[1] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው።።

[2] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።።
1. የሞቶ መነሳትን ነገር ሐቅነት ማረጋገጥ፣
2.የሰው ልጅ ከጌታው ጋር መገናኘቱ አይቀሬ መሆኑን በግልፅ ማስረዳት፣
3.በአላህ (ﷻ) የሚያምኑና አላህን በአግባቡ የሚፈሩ ሁሉ ገር ምርመራ እንደሚመረመሩ፣
4.በሱ ያላመነነና መልካም ሥራ የሌለው ምርመራው ከባድ እንደሚሆንበት፣
5.በዱንያ መደሰትና በስሜት መሳብ ያለማመን ምልክት መሆኑን፣
6. የሰው ልጅ ከአንዱ ሁኔታ ወደ ሌላ ሁኔታ እየተዘዋወረ ጀነት ወይም ጀሀነም እስከሚደርስ እንደሚጓዝ፣

ترتيبها ٨٥ | سُورَةُ البُرُوجِ | آياتها ٢٢

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَٱلسَّمَآءِ ذَاتِ ٱلۡبُرُوجِ ١ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡمَوۡعُودِ ٢ وَشَاهِدٖ وَمَشۡهُودٖ
٣ قُتِلَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡأُخۡدُودِ ٤ ٱلنَّارِ ذَاتِ ٱلۡوَقُودِ ٥ إِذۡ هُمۡ عَلَيۡهَا
قُعُودٞ ٦ وَهُمۡ عَلَىٰ مَا يَفۡعَلُونَ بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ شُهُودٞ ٧ وَمَا نَقَمُواْ
مِنۡهُمۡ إِلَّآ أَن يُؤۡمِنُواْ بِٱللَّهِ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡحَمِيدِ ٨ ٱلَّذِي لَهُۥ مُلۡكُ
ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ ٩ إِنَّ ٱلَّذِينَ
فَتَنُواْ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتِ ثُمَّ لَمۡ يَتُوبُواْ فَلَهُمۡ عَذَابُ جَهَنَّمَ وَلَهُمۡ
عَذَابُ ٱلۡحَرِيقِ ١٠ إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَهُمۡ
جَنَّٰتٞ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُۚ ذَٰلِكَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡكَبِيرُ ١١ إِنَّ بَطۡشَ
رَبِّكَ لَشَدِيدٌ ١٢ إِنَّهُۥ هُوَ يُبۡدِئُ وَيُعِيدُ ١٣ وَهُوَ ٱلۡغَفُورُ ٱلۡوَدُودُ ١٤
ذُو ٱلۡعَرۡشِ ٱلۡمَجِيدُ ١٥ فَعَّالٞ لِّمَا يُرِيدُ ١٦ هَلۡ أَتَىٰكَ حَدِيثُ ٱلۡجُنُودِ
١٧ فِرۡعَوۡنَ وَثَمُودَ ١٨ بَلِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فِي تَكۡذِيبٖ ١٩ وَٱللَّهُ مِن
وَرَآئِهِم مُّحِيطُۢ ٢٠ بَلۡ هُوَ قُرۡءَانٞ مَّجِيدٞ ٢١ فِي لَوۡحٖ مَّحۡفُوظِۭ ٢٢

ترتيبها ٨٦ | سُورَةُ الطَّارِقِ | آياتها ١٧

## 85 ኛው ምዕራፍ:- የቡሩጆች ምዕራፍ ነው::[1] (ሱረቱ አል- ቡሩጅ) አንቀጾቹ 22 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1-3 የቡሩጆች ባለቤት በሆነችው ሰማይ፣ በተቀጠረው ቀንም፤ በተጣጅና በሚጣዱትም /መስካሪና በሚመሰከርበት/ (እምላለሁ)።
4 የጉድቡ ባለቤቶች ተረገሙ ፤
5 የማገዶ ባለቤት የሆነችው እሳት (ባለቤቶች)።
6 7 እነርሱ (በምእምና ች ላይ የሚሰሩትን ለመመልከት) በእርሷ (አፋፍ) ላይ ተቀማጮች በሆኑ ጊዜ፤ (ተረገሙ።)
8 ከእነሱም በአሸናፊውና በምስጉኑ (ጌታ) ማመናቸውን እንጂ ሌላን ምንንም
አልጠሉም።
9 በዚያ የሰማያትና የምድር ንግስና ለእርሱ ብቻ በሆነው (አላህ ማመናቸውን።) አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ መስካሪ ነው።
10 እነዚያ ምዕምናንንና ምእምናትን ያሰቃዩ ከዚያም ያልተጸጸቱ ለእነርሱ የገሀነም ቅጣት አላቸው። ለእነሱም የመቃጠሉ ስቃይ አላቸው።
11 እነዚያ ያመኑና መልካም ስራዎችንም የሰሩ ለእነሱ ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች አሏቸው ፤ ይህ ታላቅ ማግኘት ነው።
12 የጌታህ በኃይል መያዝ ብርቱ ነው።
13 እነሆ እርሱ መፍጠርን ይጀምራል፤ ይመልሳልም።
14 እርሱም ምህረተ ብዙ፣ ወዳድ ነው።
15 የዙፋኑ ባለቤት የላቀው ነው።
16 የሚሻውን ሁሉ ሰሪ ነው።
17 የሰራዊቶቹ ወሬ መጣልህን።
18 የፊርዖንና የሰሙድ (ወሬ)።
19 በእውነት እነዚያ የካዱት በማስተባበል ውስጥ ናቸው።
20 አላህም በዙሪያቸው (በዕውቀቱ) ከባቢ ነው።
21 ይልቁንም እርሱ የከበረ ቁርአን ነው።
22 የተጠበቀ በሆነ ሰሌዳ ውስጥ ነው።[2]

## 86 ኛው ሱራ የሌሊት መጪው ምዕራፍ ነው።[3] (ሱረቱ አጥ- ጧሪቅ) አንቀጾቹ 17 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 በሰማዩ[4]፣ በሌሊት መጪውም እምላለሁ።

---

7.በአላህ (ﷻ) አለማመን በጣም የሚገርም ተግባር መሆኑን፣
8.አላህ (ﷻ) የሰው ልጅ የተነገረውንና የሰራውን ብቻ ሳይሆን በልቡ ያሰበውንም የሚያውቅ መሆኑን፤

[1] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው።

[2] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።
1.ስለሞቶ መነሳት ሐቅነትና ሁሉም በአላህ (ﷻ) ፊት እንደሚቀርቡ፣ 2.የዓረፋና የጁመዓ ቀናትን ክብር ማሳወቅ፣ 3.ሰዎች በዚህ ዓለም ሲኖሩ ለሚገጥማቸው ችግር ትዕግስት ካደረጉ የሚጠብቃቸው ምንዳ ጀነት መሆኑን፣ 4.የአማኞችንም ሆነ የከሃዲዎች ምንዳ በማውሳት ለኸይር ማግባባት ከመጥፎ መከልከል፣
5.ግፈኞች በዚህች ዓለምም ሆነ በሁለተኛው ዓለም እንደሚቀጡ መዛቱ፣
6.ያለፉ ሰዎችን ታሪክ የማውሳትን ጥቅም ማፅናናት መሆኑን መግለፅ፣ 7.ሰዎች በአላህ (ﷻ) ቁጥጥር ሥር መሆናቸው፣ 8.የቁርአንን ትልቅነትና ለውሃል መህፉዝ የተባለ አንድ ዓለም እንዳለ ማረጋገጥ፣ 9.ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) እና ባልደረቦቻቸውን እንደዚሁም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ያሉ ተከታዩቻቸውን የአላህ ድል እንደማይለያቸው፤ 10.ዐርሽ የሚባል ፍጡር እንዳለ፤ 11.ከሃዲዎች ምንም ዓይነት ተአምር ከክህደት እንደማይመልሳቸው እንማራለን።

[3] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ።

[4] ከ1-3ኛው ያሉ አንቀፆች የወረዱበት ምክንያት:-
የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አጎት አቡጣሊብ ቂጣና ወተት ይዞ ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አጠገብ መጥቶ ባለበት አንድ ኮከብ ወደቀ ከዚያም አጠገባቸው የነበረውን እሳት ሞላው እሱም ይህ ነገር ምንድን ነው ብሎ ሲጠይቅ ይህ የተውረወረ ነው ከአላህ (ﷻ)

2 የሌሊት መጪውም ምን እንደሆነ ምን
አሳወቀህ?
3 ጨለማን ሰንጣቂ ከብ ነው።
4 ነፍስ ሁሉ በእርሷ ላይ ጠባቂ ያለባት
እንጂ ሌላ አይደለችም።
5 ሰውም[1] ከምን እንደተፈጠረ
ይመልከት።
6 ከተስፈንጣሪ ውሃ /የዘር ፈሳሽ/
ተፈጠረ።
7 ከጀርባና ከእርግብግቢቶች መካከል
የሚወጣ ከሆነ የዘር ፈሳሽ (ውሃ)።
8 እርሱ (አላህ) እርሱን /ሰውን/
በመመለሱ ላይ በእርግጥ ቻይ ነው።
9 ምስጥሮች በሚገለጹበት ቀን።
10 ለእርሱም (ለሰው) ምንም ኃይልና ረዳት
አይ ረውም።
11 የመመለስ ባለቤት (ዝናባማ) በሆነችው
ሰማይም (እምላለሁ)።
12 (በበቃይ) የመሰንጠቅ ባለቤት በሆነችው
ምድርም ፤
13 እርሱ (ቁርአን፣ እውነትን ከውሸት)
የሚለይ ቃል ነው።
14 እርሱም ቀልድ አይደለም።
15 እነርሱ በእርግጥ ተን ልን ይሠራሉ።
16 (እኔ) ተን ልንም እመልሳለሁ፤
/ይሸርባሉ አመክናለሁ/
17 ከሓዲዎችንም ቀን ስጣቸው። ጥቂትን
ጊዜ አቆያቸው/ታገሳቸው/።[2]

## 87 ኛው የአል-አዕላ ሱራ ነው።
## (ሱረቱ አል-አዕላ)
## አንቀጾቹ 19 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም
አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 ከሁሉ በላይ የሆነውን ጌታህን ስም
አውሳ /አጥራ/ /አሞግሥ/።
2 የዚያን (ሁሉንነገር) የፈጠረውን
ያስተካከለውንም፤
3 የዚያንም የወሰነውን(ለተፈጠረለት ነገር)
የመራውንም፤
4 የዚያንም ግጦሽን (ለምለም አርጎ)

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَٱلسَّمَآءِ وَٱلطَّارِقِ ١ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا ٱلطَّارِقُ ٢ ٱلنَّجۡمُ ٱلثَّاقِبُ ٣ إِن كُلُّ
نَفۡسٖ لَّمَّا عَلَيۡهَا حَافِظٞ ٤ فَلۡيَنظُرِ ٱلۡإِنسَٰنُ مِمَّ خُلِقَ ٥ خُلِقَ مِن مَّآءٖ
دَافِقٖ ٦ يَخۡرُجُ مِنۢ بَيۡنِ ٱلصُّلۡبِ وَٱلتَّرَآئِبِ ٧ إِنَّهُۥ عَلَىٰ رَجۡعِهِۦ لَقَادِرٞ ٨
يَوۡمَ تُبۡلَى ٱلسَّرَآئِرُ ٩ فَمَا لَهُۥ مِن قُوَّةٖ وَلَا نَاصِرٖ ١٠ وَٱلسَّمَآءِ ذَاتِ ٱلرَّجۡعِ ١١
وَٱلۡأَرۡضِ ذَاتِ ٱلصَّدۡعِ ١٢ إِنَّهُۥ لَقَوۡلٞ فَصۡلٞ ١٣ وَمَا هُوَ بِٱلۡهَزۡلِ ١٤ إِنَّهُمۡ
يَكِيدُونَ كَيۡدٗا ١٥ وَأَكِيدُ كَيۡدٗا ١٦ فَمَهِّلِ ٱلۡكَٰفِرِينَ أَمۡهِلۡهُمۡ رُوَيۡدَۢا ١٧

ترتيبها ٨٧ — سُورَةُ الأَعۡلَى — آياتها ١٩

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

سَبِّحِ ٱسۡمَ رَبِّكَ ٱلۡأَعۡلَى ١ ٱلَّذِي خَلَقَ فَسَوَّىٰ ٢ وَٱلَّذِي قَدَّرَ فَهَدَىٰ
٣ وَٱلَّذِيٓ أَخۡرَجَ ٱلۡمَرۡعَىٰ ٤ فَجَعَلَهُۥ غُثَآءً أَحۡوَىٰ ٥ سَنُقۡرِئُكَ
فَلَا تَنسَىٰٓ ٦ إِلَّا مَا شَآءَ ٱللَّهُۚ إِنَّهُۥ يَعۡلَمُ ٱلۡجَهۡرَ وَمَا يَخۡفَىٰ ٧ وَنُيَسِّرُكَ
لِلۡيُسۡرَىٰ ٨ فَذَكِّرۡ إِن نَّفَعَتِ ٱلذِّكۡرَىٰ ٩ سَيَذَّكَّرُ مَن يَخۡشَىٰ ١٠
وَيَتَجَنَّبُهَا ٱلۡأَشۡقَى ١١ ٱلَّذِي يَصۡلَى ٱلنَّارَ ٱلۡكُبۡرَىٰ ١٢ ثُمَّ لَا يَمُوتُ
فِيهَا وَلَا يَحۡيَىٰ ١٣ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن تَزَكَّىٰ ١٤ وَذَكَرَ ٱسۡمَ رَبِّهِۦ فَصَلَّىٰ ١٥

ያወጣውን፤ ያበቀለውን፤
5 ከዚያም ደረቅና ጥቁር ያደረገውንም
(አምላክ ስም አሞግሥ።)
6 (ቁርአንን)[3] በእርግጥ እናስነብብሃለን፤
አትረሳምም፤
7 አላህ ከሻው ነገር በስተቀር፤ እርሱ
ግልጹንም የሚሸሸገውንም ሁሉ ያውቃልና።
8 ለገሪቱም (ህግጋት/ እስላምን ትከተል
ዘንድ) እናገራሃለን።
9 ግሣጼይቱ ብትጠቅም (ሰዎችን) ገሥጽም።
10 አላህን የሚፈራ ሰው በእርግጥ ይገሠጻል።
11 መናጢውም ይርቃታል፤
12 ያ፣ ታላቂቱን እሳት የሚገባው፤
13 ከዚያም በእርሷ ውስጥ አይሞትም፣
ህያውም አይሆንም።
14 የተጥራራ ሰው በእርግጥ ዳነ።
15 የጌታውንም ስም ያወሳና የሰገደ።
16 ይልቁንም ቅርቢቱን ህይወት
ትመርጣላችሁ፤
17 መጨረሻይቱ (ህይወት) በላጭም፣
ዘውታሪም ስትሆን።

---

ታምራቶች አንዱ ነው ሲሉት በጣም ስለተገረመ ነው። ዋሂዲ።

[1] ከ5-10ያሉ አንቀፆች የወረዱበት ምክንያት:- አቡል አሹድ የተባለ ሰውዬ በቆዳ ላይ ይቆምና ከዚህ እኔን የገፈተረ ይህን ያህል ሽልማት ሰጠዋለሁ ያለ ከመፈከሩም አልፎ (ሙሐመድ የገሀነም ዘበኞች አሥራ ዘጠኝ ናቸው ይላልና እናንተ ለዘጠኞቹ ሁኑ እንጂ እኔ አሥሮችን ብቃቸው አለሁ) ይል ስለ ነበር ነው። (ሱዩጢ።)

[2] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። 1.የሙቶ መነሳትን ሐቅነት ማረጋገጥ፣ 2.የሰዎች ተግባራት ሁሉ ቀድሞውኑ የተመዘገቡ ስለ መሆናቸው፣ 3.የሰው ልጅ ከተስፈንጣሪ ፈሳሽ እንደመጣ ማስተማር፣ 4.መጥፎን በውስጥ ደብቆ ተቃራኒውን ይፋ ከማውጣት ማስጠንቀቅ፤ 5.የሰው ልጅ የትንሳኤ ዕለት ራሱን መርዳት እንደማይችልና ሌላ ረዳት እንደማያገኝ እንማራለን።

[3] 6ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ጀብሪል ወህይ ይዞ በሚመጣበት ጊዜ እንዳይረሱት ይጣደፉ ስለነበር ነው። (ሱዩጢ።)

بَلْ تُؤْثِرُونَ ٱلْحَيَوٰةَ ٱلدُّنْيَا ﴿١٦﴾ وَٱلْـَٔاخِرَةُ خَيْرٌ وَأَبْقَىٰٓ ﴿١٧﴾ إِنَّ
هَٰذَا لَفِى ٱلصُّحُفِ ٱلْأُولَىٰ ﴿١٨﴾ صُحُفِ إِبْرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ ﴿١٩﴾

## سُورَةُ الغَاشِيَةِ
ترتيبها ٨٨ — آياتها ٢٦

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

هَلْ أَتَىٰكَ حَدِيثُ ٱلْغَٰشِيَةِ ﴿١﴾ وُجُوهٌ يَوْمَئِذٍ خَٰشِعَةٌ ﴿٢﴾
عَامِلَةٌ نَّاصِبَةٌ ﴿٣﴾ تَصْلَىٰ نَارًا حَامِيَةً ﴿٤﴾ تُسْقَىٰ مِنْ عَيْنٍ ءَانِيَةٍ ﴿٥﴾
لَّيْسَ لَهُمْ طَعَامٌ إِلَّا مِن ضَرِيعٍ ﴿٦﴾ لَّا يُسْمِنُ وَلَا يُغْنِى مِن جُوعٍ ﴿٧﴾
وُجُوهٌ يَوْمَئِذٍ نَّاعِمَةٌ ﴿٨﴾ لِّسَعْيِهَا رَاضِيَةٌ ﴿٩﴾ فِى جَنَّةٍ عَالِيَةٍ ﴿١٠﴾
لَّا تَسْمَعُ فِيهَا لَٰغِيَةً ﴿١١﴾ فِيهَا عَيْنٌ جَارِيَةٌ ﴿١٢﴾ فِيهَا سُرُرٌ مَّرْفُوعَةٌ ﴿١٣﴾
وَأَكْوَابٌ مَّوْضُوعَةٌ ﴿١٤﴾ وَنَمَارِقُ مَصْفُوفَةٌ ﴿١٥﴾ وَزَرَابِىُّ مَبْثُوثَةٌ ﴿١٦﴾
أَفَلَا يَنظُرُونَ إِلَى ٱلْإِبِلِ كَيْفَ خُلِقَتْ ﴿١٧﴾ وَإِلَى ٱلسَّمَآءِ كَيْفَ
رُفِعَتْ ﴿١٨﴾ وَإِلَى ٱلْجِبَالِ كَيْفَ نُصِبَتْ ﴿١٩﴾ وَإِلَى ٱلْأَرْضِ كَيْفَ
سُطِحَتْ ﴿٢٠﴾ فَذَكِّرْ إِنَّمَآ أَنتَ مُذَكِّرٌ ﴿٢١﴾ لَّسْتَ عَلَيْهِم
بِمُصَيْطِرٍ ﴿٢٢﴾ إِلَّا مَن تَوَلَّىٰ وَكَفَرَ ﴿٢٣﴾ فَيُعَذِّبُهُ ٱللَّهُ ٱلْعَذَابَ
ٱلْأَكْبَرَ ﴿٢٤﴾ إِنَّ إِلَيْنَآ إِيَابَهُمْ ﴿٢٥﴾ ثُمَّ إِنَّ عَلَيْنَا حِسَابَهُم ﴿٢٦﴾

18 ይህ በፊተኞቹ መፀሐፍት ዉስጥ የሰፈረ ነው።
19 በኢብራሂምና በሙሳ መጽሀፍት ዉስጥ።[1]

## 88 ኛው ሱራ፡-የሼፋኙቱ ምዕራፍ ነው።[2] (ሱረቱ አል-ጋሺየህ) አንቀጾቹ 26 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 የሸፋኙቱ (ትንሣዔ) ወሬ መጣልህን?
2 በዚያ ቀን የከሐዲያን ፊቶች ተዋራጆች ናቸው፤
3 ሰሪዎች ለፊዎች ናቸው።
4 የምታቃጥልን እሳት ይገባሉ።
5 በጣም ከፈላች ምንጭም ይጋታሉ።
6 ዶሪዕ ከሚባል (እሾሃም) ዛፍ እንጂ
ሌላ ምግብ የላቸውም ፤
7 አካል የማያሰባ፣ ከረኃብም የማያብቃቃ
ከሆነው።
8 የአማኒያን ፊቶች በዚያ ቀን
ተቀማጣዮች ናቸው።
9 በስራቸው ተደሳቾች ናቸው ፤
10 በከፍተኛ ገነት ውስጥ ናቸው።
11 በውስጧ ውድቅን ነገር አይሰሙም።
12 በውስጧ ፈሳሾች ምንጮች አሉ።
13 በውስጧ ከፍ የተደረጉ አልጋዎች አሉ።
14 በተርታ የተ ሩ ብርጭቆዎችም፤
15 የተደረደሩ መከዳዎችም፤
16 የተነጠፉ ስጋጃዎችም (አሉ)።
17 (ከሓዲዎች)[3] ግመል እንዴት
እንደተፈጠረች[4] አይመለከቱምን?
18 ሰማይም እንዴት ከፍ እንደ ተደረገች !
19 ተራራዎችም እንዴት እንደ ተቸከሉ !
20 ምድርም እንዴት እንደተዘረጋች
(አይመለከቱምን?!)
21 አስታውስም። አንተ አስታዋሽ ብቻ
ነህና።
22 በነሱ ላይ ተሿሚ (አስገዳጅ)
አይደለህም ፤
23 ግን (ከእውነት) የዞረና የካደ ሰው፤
24 አላህ ታላቁን ቅጣት ይቀጣዋል።
25 መመለሻቸው ወደ እኛ ብቻ ነው።
26 ምርመራቸውም በእኛ ላይ ብቻ ነው።[5]

## 89 ኛው ምዕራፍ፡-የጎህ ምዕራፍ ነው።[6] (ሱረቱ አል-ፈጅር) አንቀጾቹ 30 ናቸው።

---

[1] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። **1.**አላህን (ﷻ) በዛቱ ማጥራት ግዴታ እንደሆነ ሁሉ ስሙንም ማጥራት ግዴታ መሆኑን፣ **2.**ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) የማይረሱ መሆናቸው፣ **3.**ስገር ነገር ሁሉ የተገራላቸው መሆኑን፣ **4.**በዘካ፣ በዚክርና በሶላት ላይ ከፍተኛ ግፊት ማድረግ፣ **5.**ዱንያን አጣጥሎ አኺራን ማሞገስ፣ **6.**የሰማያዊ መፀሐፍት መልዕክት በአንድ መስማማት ሁሉም ከአንድ አላህ (ﷻ) የመጡ መሆናቸውን ማመልከቱ፤ **7.**የሰማያዊ እምነቶች አጠቃላይ ይዘትና መሰረታዊ ባህሪ አንድ መሆኑን፤ በየትኛዉም ዘመን የተነሱ ነቢያት ያስተላልፉት የነበረው መለዕክት ተመሳሳይ መሆኑን እንማራለን።

[2] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው።

[3] 17ኛው አንቀፅ- የወረደበት ምክንያት፡-
አላህ (ﷻ) የጀነትን ፀጋዎች በቁርአን ሲናገር ከሃዲዎች በጉዳዩ ስለተረገሙ ነው። (ሱዩጢ።)

[4] ግመል ከእንሰሳዎች ሁሉ አያሌ ጥቅም ያላትና በተለይ ለዐረቦች ሕይወት ከምግባቸው፣ ከልብሳቸው፣ ከጉዟቸውና ከሌላዉም የዕለት ከዕለት እንቅስቃሲያቸው ጋር የተያያዘች ናት።

[5] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።
**1.**ስለ ሞቶ መነሳትና ስለ ምንዳ፣
**2.**ስለ ቂያማ ቀንና ከስሞች አንዱ ጋሺያህ መባሉ፣
**3.**ጀነት ውስጥ ልፋት እንደሌለ ሁሉ ገሀነም ውስጥ ከፍተኛ ልፋት መኖሩን፣
**4.**የሰዎችን ስሜት ክፉኛ ከሚጎዱ ነገሮች መካከል ትክክል ያልሆኑ ወሬዎች ይገኙበታል፣
**5.**ሞቶ መነሳት ያለ መሆኑን፣
**6.**ወደ አላህ (ﷻ) ጥሪ የሚያደርግ ሰው ሃላፊነቱ ማስተማር ብቻ መሆኑ፣ የሰዎች መጨረሻ ማንም ይሁን ማን ወደ አላህ (ﷻ) መሆኑን፤ በተጨማሪም ከአንቀፆቹ ስለሞቶ መነሳትና ስለምንዳ ንማራለን።

[6] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

(1)-(4) በጎህ[1]፤ በዐሥር ሌሊቶች[2]፤ በጥንዱም[3] በነጠላውም፤ በሌሊቱም በሚሄድ ጊዜ እምላለሁ፤

(5) በዚህ (መሐላ) ለባለ አእምሮ ታላቅ መሐላ አለበትን?

(6) (7) ጌታህ በዓድ ህዝቦች ላይ እንዴት እንደሠራ አላወቅክምን? በኢረም፣ በባለ ረዣዥሚቱ አዕማድ፤

(8) በዚያች ብጤዋ በአገሮች ውስጥ ያልተፈጠረ በሆነችው፤

(9) በነዚያ በሸለቆውም ቋጥኝን የቆረጡ በሆኑት፤ በሰሙዶች፤

(10) ባለ ችካሎች (ባለብዙ ሰራዊት) በሆነው በፊርዖንም፤

(11) በእነዚያ በአገሮች ላይ ግፍ የሰሩ፤

(12) በእርሷም ውስጥ ጥፋትን ያበዙ በሆኑት (እንዴት እንደሰራ አታውቅምን?)

(13) በነሱ ላይም ጌታህ የቅጣትን አለንጋ አወረደባቸው ።

(14) ጌታህ በመጠባበቂያ ላይ ነውና ።

(15) የሰው ልጅ ጌታው በሞከረው ጊዜ ባከበረውና ባጣቀመውም (ጊዜ) ጌታዬ አከበረኝ (አበለጠኝ)ይላል።

(16) በሞከረውና በርሱ ላይ ሲሳዩን ባጠበበበት ጊዜ እንዲሁ ጌታዬ አሳነሰኝ ይላል።

(17) ተከልከሉ ይልቁንም የቲምን አታከብሩም፤

(18) ድሃንም በማብላት አትተዛዘዙም፤

(19) የውርስንም ገንዘብ ያለአግባብ ትበላላችሁ፤

(20) ገንዘብንም አለቅጥ ትወዳላችሁ፤

(21) ተዉ ታቀቡ፤ ምድር በተን ታ ተች ጊዜ፤

(22) መላዕክትም በሰልፍ ሆነው ጌታህ በመጣ ጊዜ፤

(23) ገሀነምም በዚያ ቀን በተመጣች ጊዜ በዚያ ቀን ሰው (ጥፋቱን) ይገነዘባል?

(24) ወይ እኔ! ምነው በህይወቴ (መልካምን ስራ) ባስቀደምኩ ሮ ይላል።

(25) በዚያ ቀንም የርሱን አቀጣጥ አንድም አይቀጣም ።

(26) የእርሱንም አስተሳሰር አንድም አያስርም ።

سُورَةُ الفَجۡرِ — آياتها ٣٠ — ترتيبها ٨٩

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَٱلۡفَجۡرِ ١ وَلَيَالٍ عَشۡرٖ ٢ وَٱلشَّفۡعِ وَٱلۡوَتۡرِ ٣ وَٱلَّيۡلِ إِذَا يَسۡرِ
٤ هَلۡ فِي ذَٰلِكَ قَسَمٞ لِّذِي حِجۡرٍ ٥ أَلَمۡ تَرَ كَيۡفَ فَعَلَ رَبُّكَ بِعَادٍ
٦ إِرَمَ ذَاتِ ٱلۡعِمَادِ ٧ ٱلَّتِي لَمۡ يُخۡلَقۡ مِثۡلُهَا فِي ٱلۡبِلَٰدِ ٨
وَثَمُودَ ٱلَّذِينَ جَابُواْ ٱلصَّخۡرَ بِٱلۡوَادِ ٩ وَفِرۡعَوۡنَ ذِي ٱلۡأَوۡتَادِ ١٠
ٱلَّذِينَ طَغَوۡاْ فِي ٱلۡبِلَٰدِ ١١ فَأَكۡثَرُواْ فِيهَا ٱلۡفَسَادَ ١٢ فَصَبَّ
عَلَيۡهِمۡ رَبُّكَ سَوۡطَ عَذَابٍ ١٣ إِنَّ رَبَّكَ لَبِٱلۡمِرۡصَادِ ١٤ فَأَمَّا
ٱلۡإِنسَٰنُ إِذَا مَا ٱبۡتَلَىٰهُ رَبُّهُۥ فَأَكۡرَمَهُۥ وَنَعَّمَهُۥ فَيَقُولُ رَبِّيٓ أَكۡرَمَنِ
١٥ وَأَمَّآ إِذَا مَا ٱبۡتَلَىٰهُ فَقَدَرَ عَلَيۡهِ رِزۡقَهُۥ فَيَقُولُ رَبِّيٓ أَهَٰنَنِ ١٦
كَلَّاۖ بَل لَّا تُكۡرِمُونَ ٱلۡيَتِيمَ ١٧ وَلَا تَحَٰٓضُّونَ عَلَىٰ طَعَامِ
ٱلۡمِسۡكِينِ ١٨ وَتَأۡكُلُونَ ٱلتُّرَاثَ أَكۡلٗا لَّمّٗا ١٩
وَتُحِبُّونَ ٱلۡمَالَ حُبّٗا جَمّٗا ٢٠ كَلَّآ إِذَا دُكَّتِ ٱلۡأَرۡضُ دَكّٗا
دَكّٗا ٢١ وَجَآءَ رَبُّكَ وَٱلۡمَلَكُ صَفّٗا صَفّٗا ٢٢ وَجِاْيٓءَ يَوۡمَئِذِۭ
بِجَهَنَّمَۚ يَوۡمَئِذٖ يَتَذَكَّرُ ٱلۡإِنسَٰنُ وَأَنَّىٰ لَهُ ٱلذِّكۡرَىٰ ٢٣

(27)-(30) (ለአመነች ነፍስም)[4]:- አንቺ የረካሺው ነፍስ ሆይ! ወዳጅ፣ ተወዳጅ ሆነሽ ወደ ጌታሽ ተመለሺ። ከባሮቼም ጋር ተቀላቀይ። ገነቴንም ግቢ /ውረሺ/ (ትባላለች)።[5]

## 90ኛው ሱራ፡- የሀገር ምዕራፍ ነው፡፡[6]
## (ሱረቱ አል-በለድ)
## አንቀጾቹ 20 ናቸው፡፡

---

[1] የሱብህ ሶላት ወይም ንጋቱ እራሱ ማለት ነው ፡፡

[2] የዙልሒጃህ ወይም የሙሐረም ወይም የረመዷን አስር ቀኖች ማለት ሊሆን ይችላል ፡፡

[3] በነዚህ አባባሎች ትርጉም ላይ ከሀያ በላይ ልዩነቶች ያሉበት ሲሆን በጥንዱም[3]፤ ፉጡር ሁሉ ማለትን ይመርጣሉ። ብዙ ዑለሞች ምክኒያቱም ፉጡር ተብሎ ጥንድ ያልሆነ አንድም የለምና ፡፡ በነጠላውም አላህ (ﷻ) ማለት ነው። ምክናቱም በሁሉ ነገር ብቸኛ አምላክ እሱ ብቻ ነዉና ፡፡

[4] 27ኛው አንቀፅ-የወረደበት ምክንያት፡- በሐምዛ ወይም በዑስማን ምክንያት ነው የወረደው ፡፡ (ሱዩጢ፡፡)

[5] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡
**1.** ከዙልሂጃ ወር መጀመሪያ ላይ ያሉትን አስር ቀናቶች ክብር፣
**2.** አላህ (ﷻ) አመፀኞችን ማጥፋቱ ሙቶ መነሳትንና ምንዳ ከፋይነቱን የሚያረጋግጥ መሆኑን፣ **3.** አላህ (ﷻ) ባሮቹን የሚጠባበቅ በመሆኑ ከስህተት ራሳቸውን እንዲጠብቁ ማስጠንቀቁ፣
**4.** የቲሞችን ማክበር ግዴታ መሆኑን እና ረሀብተኛን ማብላት ተገቢ ስለመሆኑ፣
**5.** ውርስ በአግባቡ መሰጠት ግዴታ መሆኑ፣
**6.** የሰው ልጆችን መብት እስከመተላለፍ የሚያደርስ የገንዘብ ፍቅር መጥፎ መሆኑን እንማራለን፡፡

[6] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ፡፡

يَقُولُ يَٰلَيۡتَنِي قَدَّمۡتُ لِحَيَاتِي ﴿٢٤﴾ فَيَوۡمَئِذٖ لَّا يُعَذِّبُ عَذَابَهُۥٓ أَحَدٞ ﴿٢٥﴾
وَلَا يُوثِقُ وَثَاقَهُۥٓ أَحَدٞ ﴿٢٦﴾ يَٰٓأَيَّتُهَا ٱلنَّفۡسُ ٱلۡمُطۡمَئِنَّةُ ﴿٢٧﴾ ٱرۡجِعِيٓ
إِلَىٰ رَبِّكِ رَاضِيَةٗ مَّرۡضِيَّةٗ ﴿٢٨﴾ فَٱدۡخُلِي فِي عِبَٰدِي ﴿٢٩﴾ وَٱدۡخُلِي جَنَّتِي ﴿٣٠﴾

## سُورَةُ البَلَدِ

ترتيبها ٩٠ — آياتها ٢٠

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

لَآ أُقۡسِمُ بِهَٰذَا ٱلۡبَلَدِ ﴿١﴾ وَأَنتَ حِلُّۢ بِهَٰذَا ٱلۡبَلَدِ ﴿٢﴾ وَوَالِدٖ وَمَا وَلَدَ
﴿٣﴾ لَقَدۡ خَلَقۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ فِي كَبَدٍ ﴿٤﴾ أَيَحۡسَبُ أَن لَّن يَقۡدِرَ عَلَيۡهِ
أَحَدٞ ﴿٥﴾ يَقُولُ أَهۡلَكۡتُ مَالٗا لُّبَدًا ﴿٦﴾ أَيَحۡسَبُ أَن لَّمۡ يَرَهُۥٓ أَحَدٌ
﴿٧﴾ أَلَمۡ نَجۡعَل لَّهُۥ عَيۡنَيۡنِ ﴿٨﴾ وَلِسَانٗا وَشَفَتَيۡنِ ﴿٩﴾ وَهَدَيۡنَٰهُ
ٱلنَّجۡدَيۡنِ ﴿١٠﴾ فَلَا ٱقۡتَحَمَ ٱلۡعَقَبَةَ ﴿١١﴾ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا ٱلۡعَقَبَةُ ﴿١٢﴾
فَكُّ رَقَبَةٍ ﴿١٣﴾ أَوۡ إِطۡعَٰمٞ فِي يَوۡمٖ ذِي مَسۡغَبَةٖ ﴿١٤﴾ يَتِيمٗا ذَا مَقۡرَبَةٍ
﴿١٥﴾ أَوۡ مِسۡكِينٗا ذَا مَتۡرَبَةٖ ﴿١٦﴾ ثُمَّ كَانَ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَتَوَاصَوۡاْ
بِٱلصَّبۡرِ وَتَوَاصَوۡاْ بِٱلۡمَرۡحَمَةِ ﴿١٧﴾ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡمَيۡمَنَةِ ﴿١٨﴾ وَٱلَّذِينَ
كَفَرُواْ بِـَٔايَٰتِنَا هُمۡ أَصۡحَٰبُ ٱلۡمَشۡـَٔمَةِ ﴿١٩﴾ عَلَيۡهِمۡ نَارٞ مُّؤۡصَدَةُۢ ﴿٢٠﴾

## سُورَةُ الشَّمۡسِ

ترتيبها ٩١ — آياتها ١٥

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም እና አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 (መሀመድ ሆይ!) በዚህ አገር (በመካ) እምላለሁ፤[1]
2 አንተ በዚህ አገር ሰፋሪ ስትሆን ፤
3 በወላጂም በወለዳቸውም ሰዎች (በአዳምና በዘሮቹ ሁሉ) እምላለለሁ ።
4 ሰውን ሁሉ በእርግጥ በልፋት ውስጥ ሆ ፈጠርነው፤
5 በርሱ ላይ አንድም አካል የማይችል መሆኑን ይጠረጥራልን?
6 ብዙን ገንዘብ አጠፋሁ ይላል፤
7 አንድም ያላየው መሆኑን ያስባልን?
8 ለእርሱ ሁለት ዓይ ችን አላደረግንለትምን?
9 አንድ ምላስንና ሁለት ከንፈሮችንም ፤
10 ሁለትን መንገዶች አልመራነውምን?
11 ዓቀበቲቱንም አልወጣም።
12 ዓቀበቲቱም (መውጣቷ) ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ?
13 (እርሱ) ጫንቃን[2] መልቀቅ ነው ።

[1] ወላጅ ማለት እዚህ አባታችን አደምን ነው ። ልጆች የተባሉት ደግሞ ዘሮቹ ማለት ነው የሚለው ተፍሲር የተሻለ በመሆኑ እኔም ይህንኑ መርጫለሁ ።
[2] ባሪያን ነፃ ማውጣት ማለት ነው ።

14 ወይም የረኃብ ባለቤት በሆነ ቀን (ረሀብተኛን) ማብላት ፤
15 የዝምድና ባለቤት የሆነን የቲም፤
16 ወይም የዐፈር ባለቤት የሆነን ማብላት ነው።
17 ከዚያም ከነዚያ ከአመኑትና በመታገሥ አደራ ከተባባሉት ሰዎች ጋር መሆን ነው።
18 እነዚያ (ይህንን የፈፀሙ) የቀኝ ጓዶች/ የስኬት ባለቤቶች/ናቸው።
19 እነዚያም በአንቀጾቻችን የካዱ እነሱ የግራ ጓዶች/ እድለ ቢሶች/ ናቸው።
20 በእነሱ ላይ የተዘጋች እሳት አለች።[3]

## 91ኛው፡-የፀሐይ ምዕራፍ ነው።[4](ሱረቱ አሽ-ሽምስ) አንቀጾቹ 15 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 - 8 በፀሐይና በብርሃኗ፣ በጨረቃም በተከተላት ጊዜ፤ በቀንም (ፀሐይን) በገለጻት ጊዜ፤ በሌሊቱም /ፀሐይን/ በሸፈናት ጊዜ፤ በሰማይ እና በገነባትም በምድር እና በዘረጋትም፤ በነፍስም ባስተካከላትም፤ አመጥዋንና ፍርሃትዋንም ባሳወቃት (አምላክ) እምላለሁ፤[5]
9 (ከኃጢአት) ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ ።
10 (በኃጢአት) የሸፈናትም ሰው በእውነት አፈረ /ከሰረ/ ።
11 ሠሙድ ወሰን በማለፍዋ አስተባበለች፤
12 ጠማማዋ በተንቀሳቀሰ ጊዜ።
13 ለእነሱም የአላህ መልዕክተኛ (ሷሊህ)፡- የአላህን ግመልና የመጠጥ ተራዋንም (ተጠንቀቁ) አላቸው።
14 አስተባበሉትም፤ ወጓትም፤ በኀጢአታቸውም ምክንያት ጌታቸው (ቅጣትን) በእነርሱ ላይ ደመደመባቸው፤ አስተካከላትም።
15 (አላህ) ፍፃሜዋንም (የምታስከትለውን) አይፈራም።[6]

[3] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ። ✸ስለመካና ስለነቢዩ መሐመድ (ﷺ) ክብር፣ ✸አደምና መልካም ዝርያዎቹ ያላቸዉ ክብር፣ ✸ የሰው ልጅ ከተወለደ ጀምሮ እስከሚሞት የማያርፍ እና ከዚያም በአኼራ ጀነት ገብቶ እስከሚያርፍ ወይም እሳት ገብቶ ለዘላለም እስከሚቀጣ ድረስ የማያባራበት ወይም ልፋቱ የማያቆም መሆኑን፣ ✸ሰዎች ንብረታቸውን በወንጀል ከማውጣት ለኸይር ስራ እንዲያውሉት ግፊት ማሣደር፣ 5.የቂያማ ቀን ተራራ ሊታለፍ የሚችለው በኢማንና በመልካም ስራ እና ፊሰቢሊላህ ገንዘብን በማውጣትና በኸይር በመመካከር ብቻ መሆኑን፣ ✸ የአላህን እና የረሱልን ህግ ለመጣስ የደፈሩ ሰዎች ፀፀታቸው ምን ያህል ብርቱ እንደሚሆን መግለፅ፣ ✸ በእምነት የፀናች ነፍስ ስትሞት ቀብር ስትቀሰቀስ እና መዝገቦች ሲበተኑ ምን ያህል ደስተኛ እንደምትሆን ማብሰር፤ ✸ የቁሳዊነት ርእዮት አዲስ እንዳልሆነና ከ1400 አመት በፊት የነበሩት የመካ ከሃዲች ማቴሪያሊስቶች እንደነበሩ እንማራለን።
[4] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ።
[5] አላህ እያንዳንዳቸው በቂ የሆኑትን ሰባት ልዩልዩ ተዐምሮችን አውስቶ ነፍሱን ያጠራ ሰው ነፃ መሆኑን ያቆሸሻት ደግሞ እንደሚከስር አስተምሯል ። ይህም የሚያመለክተው ነፍስን መንከባከብ ምን ያህል አንገብጋቢና አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑን ነው።
[6] **ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።** ✸..መለኮታዊ

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَٱلشَّمۡسِ وَضُحَىٰهَا ﴿١﴾ وَٱلۡقَمَرِ إِذَا تَلَىٰهَا ﴿٢﴾ وَٱلنَّهَارِ إِذَا جَلَّىٰهَا ﴿٣﴾
وَٱلَّيۡلِ إِذَا يَغۡشَىٰهَا ﴿٤﴾ وَٱلسَّمَآءِ وَمَا بَنَىٰهَا ﴿٥﴾ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا طَحَىٰهَا
﴿٦﴾ وَنَفۡسٖ وَمَا سَوَّىٰهَا ﴿٧﴾ فَأَلۡهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقۡوَىٰهَا ﴿٨﴾ قَدۡ
أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ﴿٩﴾ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ﴿١٠﴾ كَذَّبَتۡ ثَمُودُ
بِطَغۡوَىٰهَآ ﴿١١﴾ إِذِ ٱنۢبَعَثَ أَشۡقَىٰهَا ﴿١٢﴾ فَقَالَ لَهُمۡ رَسُولُ ٱللَّهِ
نَاقَةَ ٱللَّهِ وَسُقۡيَٰهَا ﴿١٣﴾ فَكَذَّبُوهُ فَعَقَرُوهَا فَدَمۡدَمَ
عَلَيۡهِمۡ رَبُّهُم بِذَنۢبِهِمۡ فَسَوَّىٰهَا ﴿١٤﴾ وَلَا يَخَافُ عُقۡبَٰهَا ﴿١٥﴾

آياتها ٢١ — سُورَةُ اللَّيۡلِ — ترتيبها ٩٢

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَٱلَّيۡلِ إِذَا يَغۡشَىٰ ﴿١﴾ وَٱلنَّهَارِ إِذَا تَجَلَّىٰ ﴿٢﴾ وَمَا خَلَقَ ٱلذَّكَرَ وَٱلۡأُنثَىٰٓ ﴿٣﴾
إِنَّ سَعۡيَكُمۡ لَشَتَّىٰ ﴿٤﴾ فَأَمَّا مَنۡ أَعۡطَىٰ وَٱتَّقَىٰ ﴿٥﴾ وَصَدَّقَ بِٱلۡحُسۡنَىٰ ﴿٦﴾
فَسَنُيَسِّرُهُۥ لِلۡيُسۡرَىٰ ﴿٧﴾ وَأَمَّا مَنۢ بَخِلَ وَٱسۡتَغۡنَىٰ ﴿٨﴾ وَكَذَّبَ بِٱلۡحُسۡنَىٰ
﴿٩﴾ فَسَنُيَسِّرُهُۥ لِلۡعُسۡرَىٰ ﴿١٠﴾ وَمَا يُغۡنِي عَنۡهُ مَالُهُۥٓ إِذَا تَرَدَّىٰٓ ﴿١١﴾ إِنَّ عَلَيۡنَا
لَلۡهُدَىٰ ﴿١٢﴾ وَإِنَّ لَنَا لَلۡأٓخِرَةَ وَٱلۡأُولَىٰ ﴿١٣﴾ فَأَنذَرۡتُكُمۡ نَارٗا تَلَظَّىٰ ﴿١٤﴾

## 92ኛው ሱራ፡-የሌሊት ምዕራፍ ነው[1]:: (ሱረቱ አል-ለይል)አንቀጾቹ 21ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1-3 በሌሊቱ[2] (በጨለማው) በሚሸፍን ጊዜ፤ በቀንም በተገለጸ ጊዜ፤ ወንድና ሴትን በፈጠረውም[3](አምላክ) እምላለሁ፤

4 ስራችሁ በእርግጥ የተለያየ ነው።

5-7 የሰጠ[4] ሰው እና ጌታውን የፈራም፤ በመልካሚቱም (እምነት) ያረጋገጠ ፤ለገሪቱ ስራ እናዘጋጀዋለን፤ /እናገራዋለን/።

8-11 የሰሰተ ሰው እና የተብቃቃም (በራሱ የተመካ)፤ በመልካሚቱ (እምነት) ያስተባበለም፤ ለክፉይቱ ሥራ

---

ሀያልነቱን የገለፀባቸውን ሁኔታዎች ማየት፣ ✸የሰው ልጅ ነፃ የሚወጣበትን ቀና መንገድና የሚከስርበትን የጥፋት ጉዞ መግለፅ፣ 3.በኢማንና በመልካም ሰራዎች ግፊት ማሳደር እና በአንፃሩም ከሽርክና ከመጥፎ ሰራዎች ማስፈራራት፣ ✸ የሰው ልጅ ከጀሀነም እሳት ነፃ ሆኖ ጀነት የመግባት ዕድሉ ራሱን ከወንጀሎች በማፅዳት መሆኑንና የመክሰሩ ምክንያት ደግሞ ራሱን በሽርክና በወንጀል ማቆሸሹ መሆኑን፣ ✸ በመጥፎ ነገር መስረፅና መግባት አደገኛ መሆኑ ማስጠንቀቅ፣ ✸ከሀዲዎች የነቢያትን መልዕክት ማስተባበል የተለመደ መሆኑን በማውሳት ነቢዩን ማፅናናት፣ ✸ ቁረይሾች የፈፀመት ሽርክና የዋሉት ግፍ መጨረሻ አስከፊ መሆኑን እንማራለን ።

[1] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ።

[2] ከ1-21ኛው አንቀፅ -የወረዱበት ምክንያት፡-
አንድ ሰውዬ የተምር አትክልት ነበረው ። ከዛፎቹ አንዷ ቅርንጫፍ በድሃው ሰው ቤት ተንዘርፋ ነበር። ባለ ሃብቱ ለመልቀም ሲፈልግ አንዳንድ ፍሬዎች በድሀው ግቢ ሲወድቁ የድሀው ሰውዬ ልጆች ሲለቅሙና ሲበሉ ሰውየው ወርዶ ይቀማቸው ነበር። ከዚህም አልፎ በአፋቸው ውስጥ ያስገቡትንም ሳይቀር እንኳን ጣቱን አስገብቶ ያስተፋቸው ነበርና ከዕለታት አንድ ቀን ድሃው ሰውዬ ይህን ችግር ለነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) በዝርዝር ሲያስረዳቸው ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ወደ ሰውየው በመሄድ ወደ ሰውየው ግቢ የገባችውን የተምር ዛፍ ሰጠተኸን የጀነት የተምር ዛፍ ቢሰጥህ ቢሉት እኔ ብዙ የተምር እግሮች አሉኝ ነገር ግን እንደዚህች የሚጣፍጥ ፍሬ ያላት ባለማግኘቴ ለማንም አልሰጥም አላቸው ። ከዚያ ሰውዬው ወደ አቡ ደህዳህ ሄደና ነቢዩን እንደሚሰማና እንደሚያከብራቸው ስለአወቀ ነገረው ። አቡዳህዳህም ለነቢዩ ሄዶ ለእሱ የሰጡትን ለኔ ይሰጡኛል ከሱ ልውሰዳት ሲላቸው አዎ አሉት ። በዚህ ጊዜ ወደ ባለተምሩ ሄደና በዋጋ መደራደር ሲጀምር ሙሃመድ እኮ በጀነት የተምር ዛፍ ሰጥቶኝ ነበር እንቢ ብየው ነው ሲለው መሸጥ ትፈልጋለህ አለው እሱም በፍፁም ከመጠን በላይ የሚያጓጓ ዋጋ ካልተሰጠሁ በስተቀር አለው። ስንት ማለት ነው በማለት ጠየቀው አርባ የቴምር እግር ነዋ አለው። መለስ አድርጐ በጣም አስወደድከው ብሎ ካሰበበት በኋላ በል በዚሁ ዋጋ ተቀብያለሁና አስመስክርልኝ በማለት ሲጠይቀው ነው ።

[3] በሴትና በወንድም እምላለሁ ተብሏል ።
ሴትና ወንድ ማድረግ ከታላላቅ ተዐምሮችና ከሰዎች አቅም በላይ ከሆኑት ነገሮች ነው ። ወንድና ሴት መሆን በባለጡትና ማሕፀን ባለቤቶች መዋለድ /መዳቀል የሚፈጠረው ወንድ ከሴት ጋር በምታደርገው ግንኙነትና ከሁለቱም ፆታዎች ከሚፈጠሩ ፈሳሾች ነው ። አላህ እንዲህ አለ (እኛ ሰውን (በሕግ ግዳጅ) የምንሞክረው ስንሆን ቅልቅሎች /ዉሁድ/ ከሆኑ ፍትወት ጠብታ ፈጠርነው፤ ሰሚ ተመልካችም አደረግነው።76/2 ወንድና ሴት በማድረግ ረገድ ወንዱም ሆነ ሴት ሚና /ምርጫ/ የላቸዉም። በትክክል ከቁርአን አናቅፅ አስተምህሮቶች የምንረዳው ነገር ቢኖር እናት ማብቀያ ማሳ በመሆኗ (ሴቶቻችሁ ለናንተ እርሻ ናቸው ። እናም እርሻችሁን በፈለጋችሁት ሁኔታ እረሱ።)2/223 ስለሆነም ሴቷ መዝሪያ ቦታ ከመሆን ሌላ ምንም ሚና የላትም። ወንዱም ቢሆን ሴት ወይም ወንድ ለመሆን የሚያበቁት ማዕድኖች እሱ ጋር ያሉ ቢሆንም የፈለገዉን መስጠት የሚያስችል አቅም የለዉም። ማለትም ወንዱ የተሸከመው የመዳቀያ ማዕድን በ23ና በ24 የሚከፈል 47--ሲሆን ሴቷ ግን በ24በ24 የሚከፈል 48- ነው ። አላህ ፅንሱን ወንድ ሊያደርገው ሲፈልግ የወንዱን 23ና የሴቲቱን 24 በማገናኘት እንዲፀነስ ያደርጋል ። አላህ ፅንሱን ሴት ሊያደርገው ሲፈልግ ደግሞ የወንዱን 24ና የሴቲቱን 24 በማገናኘት እንዲፀነስ ያደርጋል ። ስለዚህ ወንድና ሴት ማድረጉ ብቸኛው ስልጣን የአላህ ነው ። ቁርአን እንዲህ አለ (የሰማያትና የምድር ንግስና የአላህ ነው። የሚሻውን ይፈጥራል፤ ለሚሻው ሰው ሴቶችን ልጆች ይሰጣል፤ ለሚሻውም ሰው ወንዶችን ይሰጣል ። ወይም ወንዶችና ሴቶች አድርጎ ያጠናዳቸዋል፤ የሚሻውንም ሰው መካን ያደረገዋል። እርሱ ዐዋቂና ቻይ ነውና) 42/49,50

[4] ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አቡበከር ሰባት በስቃይ ላይ የነበሩ ባሮችን ገዝተው ነፃ ባወጡ ጊዜ አባታቸው አቡ ቁሃፋ ልጄ ሆይ! ሁል ጊዜ ድሃ ባሮችን ነፃ ስታወጣ እመለከታለሁ ምነው ጠንካራ ባሮችን ነፃ አታወጣም ነበር ሲሏቸው ። እኔኮ የምፈልገው አላህ (ﷻ) ዘንድ የሚገኘውን አጅር ነው በማለታቸው ነው ። (ሱዩጠ ..።)

لَا يَصۡلَىٰهَآ إِلَّا ٱلۡأَشۡقَى ١٥ ٱلَّذِي كَذَّبَ وَتَوَلَّىٰ ١٦ وَسَيُجَنَّبُهَا
ٱلۡأَتۡقَى ١٧ ٱلَّذِي يُؤۡتِي مَالَهُۥ يَتَزَكَّىٰ ١٨ وَمَا لِأَحَدٍ عِندَهُۥ مِن
نِّعۡمَةٖ تُجۡزَىٰٓ ١٩ إِلَّا ٱبۡتِغَآءَ وَجۡهِ رَبِّهِ ٱلۡأَعۡلَىٰ ٢٠ وَلَسَوۡفَ يَرۡضَىٰ ٢١

ترتيبها ٩٣ — سُورَةُ الضُّحَىٰ — آياتها ١١

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَٱلضُّحَىٰ ١ وَٱلَّيۡلِ إِذَا سَجَىٰ ٢ مَا وَدَّعَكَ رَبُّكَ وَمَا قَلَىٰ ٣
وَلَلۡأٓخِرَةُ خَيۡرٞ لَّكَ مِنَ ٱلۡأُولَىٰ ٤ وَلَسَوۡفَ يُعۡطِيكَ رَبُّكَ
فَتَرۡضَىٰٓ ٥ أَلَمۡ يَجِدۡكَ يَتِيمٗا فَـَٔاوَىٰ ٦ وَوَجَدَكَ ضَآلّٗا
فَهَدَىٰ ٧ وَوَجَدَكَ عَآئِلٗا فَأَغۡنَىٰ ٨ فَأَمَّا ٱلۡيَتِيمَ فَلَا تَقۡهَرۡ
٩ وَأَمَّا ٱلسَّآئِلَ فَلَا تَنۡهَرۡ ١٠ وَأَمَّا بِنِعۡمَةِ رَبِّكَ فَحَدِّثۡ ١١

ترتيبها ٩٤ — سُورَةُ الشَّرۡحِ — آياتها ٨

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

أَلَمۡ نَشۡرَحۡ لَكَ صَدۡرَكَ ١ وَوَضَعۡنَا عَنكَ وِزۡرَكَ ٢ ٱلَّذِيٓ
أَنقَضَ ظَهۡرَكَ ٣ وَرَفَعۡنَا لَكَ ذِكۡرَكَ ٤ فَإِنَّ مَعَ ٱلۡعُسۡرِ يُسۡرًا ٥ إِنَّ
مَعَ ٱلۡعُسۡرِ يُسۡرٗا ٦ فَإِذَا فَرَغۡتَ فَٱنصَبۡ ٧ وَإِلَىٰ رَبِّكَ فَٱرۡغَبۡ ٨

እናዘጋጀዋለን፡፡ በወደቀም ጊዜ ገንዘቡ ከእርሱ ምንም አይጠቅመውም፡፡
12 ቅኑን መንገ መግለጽ በኛ ላይ ሃላፊነት አለብን።
13 መጨረሻይቱም መጀመሪያይቱም ዓለም የእኛ ናቸው።
14 - 16 ከዚያ ጠማማ፣ ያስተባበለና ከትዕዛዝ የሸሸ እድለቢስ በስተቀር የማይገባባትን የምትንቀለቀል እሳት አስጠነቀቅኳችሁ፡፡
17 18 ያ የሚጥራራ ሆ ገንዘቡን (ለሰዎች) የሚሰጠው፣ አላህን በጣም ፈሪውም በእርግጥ ይርቃታል፡፡
19 ለአንድም ሰው ከእርሱ ዘንድ የምትመለስ ውለታ የለችም።
20 ግን የታላቁን ጌታውን ውዴታ ለመፈለግ (ይህንን ሠራ)።
21 ወደፊትም በእርግጥ ይደሰታል፡፡[1]

## 93 ኛው ምዕራፍ፡- የረፋድ ምዕራፍ ነው፡፡[2] (ሱረቱ አድ-ዱሃ) አንቀጾቹ 11 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 2 በረፋዱ[3]፤ በሌሊቱም ጸጥ ባለ ጊዜ፤ እምላለሁ።
3 (መሀመድ ሆይ!) ጌታህ አላሰናበተህም[4]፤ አልጠላህምም።
4 መጨረሻይቱም[5] ዓለም ከመጀመሪያይቱ ይልቅ ለአንተ በላጭ ናት።
5 ጌታህ ወደ ፊት (ብዙ ስጦታ) በእርግጥ ይሰጥሃል። ትደሰታለህም።
6 የቲም ሆነህ አላገኘህምና አላስጠጋህምን? (አስጠግቶሃል)።
7 የሳትክም ሆነህ አገኘህና መራህ።
8 ደሃም ሆነህ አገኘህና አከበረህ።
9 የቲምን አትጨቁን።
10 ለማኝንም አትገላምጥ።
11 የጌታህንም ጸጋ ግለጽ፤[6]

## 94 ኛው ሱራ፡-የልብ መስፋት ምዕራፍ፡፡[7](ሱረቱ አሽ-ሽርህ) አንቀጾቹ 8 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 (መሀመድ ሆይ![8]) ልብህን ለአንተ

---

[1] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ 1.የአላህን (ﷻ) ትልቅነትና ግርማ ሞገስ መግለፅ፣ 2.የሰው ልጅ ለተፈጠረለት ነገር የገራ መሆኑን እና ስለቀደር ግልፅ አስተምሮ፣ 3.ለኸይር ስራ መታደል ከአላህ (ﷻ) መሻት ጋር ከሰው ልጆች ፍላጐትና ጉጉት ላይ የተመሠረተ መሆኑን እና ለመጥፎ ስራም መጋለጥ እንዲሁ፣ 4.የሰው ልጆች ቀና መንገዶችን እንዲከተሉ ለማድረግ የተሟሉ ሁኔታዎችን እንዳመቻቸው፣ 5.ዱንያም ሆነ አኼራ የአላህ (ﷻ) ብቸኛ ስልጣን መሆናቸውና ሁለቱም መጠየቅ ያለባቸው ከሡ ብቻ መሆኑን፣ 6.የአቡበከር ስዲቅን ክብርና በጀነት መበሠር እንማራለን፡፡

[2] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው፡፡

[3] ከ1-3ኛው አንቀፅ የወረዱበት ምክንያት፡-
ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) አንድ ሌሊት ወይም ሁለት ሌሊት ታመው ከመኝታ ሳይነሱ በመቅረታቸው (ኡሙ ጀሚል) የተባለች የአቡ-ለሃብ ባለቤት ወደ ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) መጥታ ለማናደድ፡- ሙሃመድ ሆይ፣ ሰይጣንህ ተወህ፣ አሰናበተህ እንዴ? በማለቷ እና እናታችን ኸዲጃም በበኩላቸው ወህይ በመዘግየቱ አዝነው አላህ (ﷻ) ለምን ወህይ አላወረደሎትም በማለት በሀዘኔታ ተሞልተው ጠይቀዋቸው ስለነበር ለሁለቱም መልስ ይሆን ዘንድ ነው ፡፡ (ዋሂዲ እና ሱዩጢ፡፡)

[4] አልተወህም ማለትም ሊሆን ይችላል፡፡

[5] 4ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) የቲም ሆነው ሳሉ ያስጠጋቸው ከሳቸው በኋላ ለሚኖሩ ተከታዩቻቸው ህዝቦች የሚያጋጥማቸውን ድል እና ድል አንድ በአንድ ስላሳያቸው በመደሰታቸው ነው ፡፡ (ሱዩጢ ፡፡)

[6] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፡፡ 1.ዱንያ ከጭንቀትና ችግር ሁልግዜም ነፃ የማትሆን መሆንዋን፣ 2.የነቢዩ ሙሀመድ ﷺ ክብርና ማዕረግ ከፍ ያለ መሆኑን፣ 3.የሰው ልጅ በችግር ጊዜ ትዕግስት እንዲኖረውና በደስታ ጊዜም አላህን እንዲያመሰግን፤ 4.የሰው ልጅ ቀደም ሲል የነበረበትን ችግርም ተድላ ዘወር ብሎ ማስታወስ ተገቢ መሆኑን፣ 5.የሰው ልጅ ይህን ሁሉ ፀጋ ለለገሠው ጌታው አላህ (ﷻ) ምሥጋና ማድረስ ግዴታው መሆኑን እንማራለን፡፡

[7] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው፡፡

[8] 1ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ካፊሮች

አላሰፋንልህምን-(አስፍተንልሃል)፤
2 ሸክምህን አወረድንልህ፡፡
3 ያንን ጀርባህን ያከበደውን (ሸክምህን)፡፡
4 መወሳትህንም ከፍ አደረግንልህ፤
5 ከችግርም ጋር በእርግጥ ምቾት አለለ፡፡
6 ከችግር ጋር በእርግጥ ምቾት አለለ፡፡
7 በጨረስክም ጊዜ ልፋ፣ (ቀጥል)፤ (የጀመርከውን ጥሩ ስራ በጨረስክ ጊዜ ሌላ ጥሩ ስራ ቀጥል፤ ወይም አስከትል፡፡)
8 ወደ ጌታህም ብቻም ከጅል፡፡[1]/[2]

## 95 ኛው ሱራ፡-የበለስ ምዕራፍ ነው፡፡[3](ሱረቱ አት-ቲን)፡፡ አንቀጾቹ 8 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)፡፡

1 በበለስና በዘይቱን ፤
2 በሲኒን ተራራም ፤
3 በዚህ በፀጥተኛው /ፀጥታ በነገሰበት/ አገርም (እምላለሁ)፡፡
4 ሰውን[4] በጣም በአማረ አቋም ላይ ፈጠርነው፡፡
5 ከዚያም[5] (ከፊሉን) ከዝቅተኞች ሁሉ በታች አርገን መለስነው፡፡
6 ግን እነዚያ ያመኑት፣ መልካሞችንም የሰሩት ለነሱ የማይቋረጥ ምንዳ አላቸው፡፡
7 ታዲያ ከዚህ በኋላ በፍርዱ ምን አስተባባይ አደረገህ?
8 አላህ ከፈራጆች ሁሉ ይበልጥ ፈራጅ አይደለምን?[6]

## سُورَةُ التِّين

ترتيبها ٩٥ — آياتها ٨

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَٱلتِّينِ وَٱلزَّيْتُونِ ﴿١﴾ وَطُورِ سِينِينَ ﴿٢﴾ وَهَٰذَا ٱلْبَلَدِ ٱلْأَمِينِ ﴿٣﴾
لَقَدْ خَلَقْنَا ٱلْإِنسَٰنَ فِىٓ أَحْسَنِ تَقْوِيمٍ ﴿٤﴾ ثُمَّ رَدَدْنَٰهُ أَسْفَلَ سَٰفِلِينَ
﴿٥﴾ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ فَلَهُمْ أَجْرٌ غَيْرُ مَمْنُونٍ ﴿٦﴾
فَمَا يُكَذِّبُكَ بَعْدُ بِٱلدِّينِ ﴿٧﴾ أَلَيْسَ ٱللَّهُ بِأَحْكَمِ ٱلْحَٰكِمِينَ ﴿٨﴾

## سُورَةُ العَلَق

ترتيبها ٩٦ — آياتها ١٩

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

ٱقْرَأْ بِٱسْمِ رَبِّكَ ٱلَّذِى خَلَقَ ﴿١﴾ خَلَقَ ٱلْإِنسَٰنَ مِنْ عَلَقٍ ﴿٢﴾ ٱقْرَأْ وَرَبُّكَ
ٱلْأَكْرَمُ ﴿٣﴾ ٱلَّذِى عَلَّمَ بِٱلْقَلَمِ ﴿٤﴾ عَلَّمَ ٱلْإِنسَٰنَ مَا لَمْ يَعْلَمْ ﴿٥﴾ كَلَّآ إِنَّ
ٱلْإِنسَٰنَ لَيَطْغَىٰٓ ﴿٦﴾ أَن رَّءَاهُ ٱسْتَغْنَىٰٓ ﴿٧﴾ إِنَّ إِلَىٰ رَبِّكَ ٱلرُّجْعَىٰٓ ﴿٨﴾ أَرَءَيْتَ
ٱلَّذِى يَنْهَىٰ ﴿٩﴾ عَبْدًا إِذَا صَلَّىٰٓ ﴿١٠﴾ أَرَءَيْتَ إِن كَانَ عَلَى ٱلْهُدَىٰٓ ﴿١١﴾ أَوْ أَمَرَ
بِٱلتَّقْوَىٰٓ ﴿١٢﴾ أَرَءَيْتَ إِن كَذَّبَ وَتَوَلَّىٰٓ ﴿١٣﴾ أَلَمْ يَعْلَم بِأَنَّ ٱللَّهَ يَرَىٰ ﴿١٤﴾ كَلَّا لَئِن
لَّمْ يَنتَهِ لَنَسْفَعًۢا بِٱلنَّاصِيَةِ ﴿١٥﴾ نَاصِيَةٍ كَٰذِبَةٍ خَاطِئَةٍ ﴿١٦﴾ فَلْيَدْعُ نَادِيَهُۥ
﴿١٧﴾ سَنَدْعُ ٱلزَّبَانِيَةَ ﴿١٨﴾ كَلَّا لَا تُطِعْهُ وَٱسْجُدْ وَٱقْتَرِب ۩ ﴿١٩﴾

## 96 ኛው ምዕራፍ የረጋ ደም ምዕራፍ/ ሱረቱ አል- ዓለቅ/ ነው ፡፡ [7]

---

ሙስሊሞችን በድህነት ሲያነውሯቸው ነው፡፡ (ሱዩጢ፡፡)

[1] ከሶላት በኋላ ዱዓ አድርግ ለማለት ወይም ፈርድ ስትጨርስ ሱና ስራ ማለት ነው በሚል ልዩ ነቶች ቢነገሩም ትክክለኛው ግን ጊዜህን ለዱንያህ ወይም ለአኺራህ በሚጠቅም ነገር ላይ አዉል ማለት ነው የሚለው ነው ፡፡

[2] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ 1.አላህ (ﷻ) ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) ልባቸውን በመክፈት ወንጀላቸውን መማሩና ክብራቸውን ከፍ ማድረጉ፣ 2.የሙዕሚን ልብ ለዲን መከፈቱና ችግሮችን ለመሸከም መታደሉ ትልቅ ፀጋ መሆኑ፣ 3.ሁልጊዜ ከችግር በስተኋላ የነገሮች መቃለል እንዳለ ማስተማር፣ 4.ዱንያ ከጭንቀትና ችግር ሁልጊዜም ነፃ አትሆንም ፡፡ የሰው ልጅም በችግር ጊዜ ትዕግስት እንዲኖረውና በደስታ ጊዜም አላህን ሊያመሰግን ይገባዋል ፡፡ ቀደም ሲልም የነበረበትን ችግርም ሆነ ተድላ ዘወር ብሎ ማስተዋል አለበት ፡፡ ይህን ሁሉ ፀጋ ለለገሰው ጌታው አላህ (ﷻ) ምስጋና ማድረስ ግዴታው ነው፡፡
5.ከላይ ከተቀመጡት ነጥቦች በተጨማሪም የነብዩ መሐመድ ክብርና ማዕረግ ከፍ ያለ መሆኑን፤ የሙዕሚን ሕይወት ሁልጊዜም ሥራ፣ ዒባዳ፣ ጂሃድ እንጂ ቀልድ የሌለበት መሆኑን እንማራለን ፡፡

[3] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ፡፡

[4] አንዳንድ ዐሊሞች ሰው በማለት እዚህ ቦታ ላይ የተፈለገው ሙቶ መነሳትን የካደ እንደ ወሊድ ብን ሙጊራህ ያሉትን ከህዲ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ የሰውን ዘር በሙሉ ነው የተፈለገው ይላሉ ፡፡

[5] 5ኛው አንቀጽ የወረደበት ምክንያት፡- በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጊዜ የጃጁ ሽማግሌዎች ስለነበሩ ስለነሱ ሲጠየቁ ነው ፡፡ (ሱዩጢ ፡፡)

[6] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፡፡ 1.የዘይቱንና የቲን ዛፎች፤ የጡሩሲና፤ የመካ አካባቢዎች ያላቸውን ክብር፣ 2.አላህ (ﷻ) የሰውን ልጅ ባማረ ስብዕና፣ በተሻለ ቅርጽና ይዘት በመፍጠር የዋለለትን ውለታ ማስታወስ፣ 3.የሰው ልጅ የቱንም ያህል ቢዋብና ቢያምር ሄዶ ሄዶ ማርጀቱና መጃጀቱ እንደማይቀር፤ 4.የሰው ልጅ ሲያረጅና ከእንቅስቃሴ ሲቋረጥ በወጣትነቱ ይሰራው የነበረው መልካም ተግባር አጅር እንደሚቀጥልለት፤ 5.በፍትህ ከአላህ (ﷻ) የበለጠ ማንም እንደሌለ እንማራለን፡፡

[7] ሱረቱ አል -ዓለቅ በመጀመሪያ ደረጃ በ1ኛ በመካ የወረደ ሱራ ነው፡፡ ይህ ሱራ ሱረቱ ኢቅረእ፣ ሱረቱ ኢቅረእ ቢስሚረቢክ፣ ሱረቱ ኢቅረእ ውልዓለቅ ሱረቱል-ቀለም በመባል ይታወቃል፥፥
ይህ ሱራ ከቁርአን ሱራዎች ሁሉ በመጀመሪያ የወረደ ቢሆንም ማንበብና መማር አስፈላጊ መሆኑንም አበክሮ ያስተምራል ፡፡ በተጨማሪም ያ ሰውን ከዚያ ደካማ ከሆነ ፈሳሽ የፈጠረ ጌታ አላህ መማሪያና መግባቢያ የሆነውን መፃፍና እንዲሁም ያላወቃቸውን ነገሮች እንደሚያስተምረው ያስገነዝባል ፡፡ ሱራው ሐብትና ጉልበት የአላህን ሕግ እንዲጥስ ከሚገፋፉ ነገሮች መካከል መሆናቸውንና ሁሉም ወደ አላህ እንደሚመለስ አስታውስና ከአላህ መንገድ እንቅፋት የሆኑን ሁሉ በማስፈራራት ቅንጥ ቅንጣቸውን በመያዝ ወደ ገሀነም ሊያወርዳቸው እንደሚችል አስፍራርቶ ምንም መረዳት እንደማይቻል

## አንቀጾቹ 19 ናቸው::

### በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም

መክሮ የአላህን ሕግ ለማያስከብሩ ሁሉ አመፀኞችን እንዳይታዘዙ ጥሪ በማስተላለፍ መልዕክቱን ያጠቃልላል::

ወህይ (መለኮታዊ ራዕይ)፡-ስለ ቅዱስ ቁርአን ጥናታዊ ትምህርት ስንጀምር መጀመሪያ የምናነሳው ነጥብ ይህ ይሆናል:: የቁርአንን አመጣጥ ለማወቅ «ወህይ» የሚገለጽበትን መንገድ ማወቅ ያስፈልጋል :: ጌታ አላህ ከነቢያት ጋራ በስንት ዓይነት መንገድ ነው የሚገናኘው? በዚህ ጉዳይስ ቁርአን ምን ያስተምራል? እንግዲህ ሙስሊሞች እንደሚያምኑትም ሆነ ቅዱስ ቁርአን እንደሚያስተምረው መለኮታዊ ራዕይ «ወህይ» መገለጫ መንገዶቹ ሶስት ብቻ እንደሆኑ ነው :: አምላካችን አላህ ከነቢያቱ ጋራ የሚገናኘው በሶስት መንገዶች ብቻ ነው:: ከእነዚህ መንገዶች ውጪ ከአላህ ጋር መገናኘት ለሰው ተገቢው አይደለም:: እነዚህም ሶስት መንገዶች በአንድ የቅዱስ ቁርአን አያት ውስጥ እንዲህ በሚለው ቃል ተጠቃለዋል፡- «ለሰውም አላህ በራዕይ ወይም ከግርዶ ወዲያ ወይም መልክተኛን (መልአክን) የሚልክና በፈቃዱ የሚሻውን ነገር የሚያወርድለት ቢሆን እንጂ (በጋሀድ) ሊያናግረው ተገቢው አይደለም :: እርሱ የበላይ ጥበበኛ ነውና» አል- ሹራ 51 በዚህ የቅዱስ ቁርአን ጥቅስ መሰረት መለኮታዊ ራዕይ መገለጫ መንገዶቹ ሶስት ብቻ ሆነው እናገኛቸዋለን:: እነሱም፡- በራዕይ «ኢልሳ ወህየን» ይህ ማለት ጌታ አላህ ያን ለነብይነት ወይም ለረሱልነት የመረጠውን ግለሰብ መላኢካን ሳይልክለት ወይም ቀጥታ ቃሉን ሳያሰማው ነገር ግን ያ ነቢይ በንቃተ ህሊና እያለ አላህ በልቡ አንድን ነገር ይጥልለታል ወይም ያስታውቀዋል :: ካልሆነም ያ ነቢይ ተኝቶ እያለ አላህ በህልም መልክትን ያስተላልፍለታል:: በዚህ መንገድ የተገለጸ መለኮታዊ ራዕይን እንደ ምሳሌ ብንመለከት የነቢዩላህ ኢብራሂምን ታሪክ ማየት ይቻላል :: ጌታ አላህ ነቢዩላህ ኢብራሂምን ልጃቸውን ኢስማዒልን እንዲያርዱ ማዘዙን ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው:: ታዲያ ይህ የጌታችን ትዕዛዝ ወደ ኢብራሂም የመጣው በየትኛው መንገድ ነው? ይህ ትዕዛዝ የመጣው በህልማቸው ነው:: ቅዱስ ቁርአን እንዲህ ይላል፡- «ታጋሽ በሆነ ወጣትም ልጅ አበሰርነው:: ከርሱ ጋርም ለስራ በደረሰ ጊዜ ልጄ ሆይ እኔ በህልሜ የማርድህ ኾኜ አያለሁ ተመልከትም ምን ትላለህ? አለው አባቴ ሆይ! የታዘዝከውን ስራ አላህ ቢሻ ከታጋሾቹ ኾኜ ታገኘኛለህ አለ::» አል ሷፍፋት 102 ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት የሀዲስ ሰንሰለት ውስጥ ዓኢሻ እንዲህ ብለዋል «ነቢዩ መለኮታዊውን ራዕይ ማየት የጀመሩት በእንቅልፍ በሚያዩት እውነተኛ ህልም አማካይነት ነበር» 2.ከመጋረጃ በስተጀርባ፡- ይህ ማለት ደግሞ ለነቢይነት የተመረጠው ግለሰብ አላህን ሳያይ ነገር ግን ያለ ማንም አገናኝ በቀጥታ የአላህን ንግግር እየሰማ መልእክት የሚቀበልበት መንገድ ነው :: ለዚህ አይነት መለኮታዊ ራዕይ መገለፅ አይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን ነቢዩላህ ሙሳ ናቸው :: ጌታ አላህ በተደጋጋሚ ብዙ ጊዜ ቃሉን እያሰማ ለሳቸው መልዕክቱን አስተላልፏል:: ማስረጃዎቹን እነሆ፡- «ሙሳም ለቀጠሮአችን በመጣና ጌታውም ባነጋገረው ጊዜ፡- ጌታዬ ሆይ! (ነፍስህን) አሳየኝ ወደ አንተ እመለከታለሁና አለ...» አል አዕራፍ 143 «...አላህም ሙሳን ማነጋገርን አነጋገረው» አል -ኒሳዕ 164 «የሙሳም ወሬ በእርግጥ መጥቶሀል:: እሳትን ባየና ለቤተሰቦቹ፡- (እዚህ) ቆዩ እኔ እሳትን አየሁ ። ከእርሷ ችቦን ላመጣላችሁ ወይም እሳቲቱ ዘንድ መሪን ላገኝ እከጅላለሁ ባለ ጊዜ (አስታውስ) :: በመጣትም ጊዜ፡- ሙሳ ሆይ፣ በማለት ተጠራ:: እኔ ጌታህ ነኝ መጫሚያዎችህንም አውልቅ አንተ በተቀደሰው ሸለቆ በጡዋ ነህና::» ጧሀ 11-14 «በመጣትም ጊዜ ከሸለቆው ቀኝ ዳርቻ ከዛፊቱ በኩል በተባረከችው ስፍራ ውስጥ፡- ሙሳ ሆይ! እኔ የአለማት ጌታ አላህ ነኝ በማለት ተጠራ» አል- ቀሶስ 30 ነቢያችንም (ﷺ)) ለይለተል ኢስራዕ ወል ሚዕራጅ (በለሊት ጉዞና በሰማይ እርገት) በወጡበት ጊዜ ያለማንም ዋሲጣነት (አገናኝነት) ጌታቸውን አነጋግረውታል:: አምስት ወቅት ሰላትንም ተቀብለው የመጡት ያዚያን ጊዜ ነው::

3. መላዕክትን በመላክ (አው ዩርሲለ ረሱላ) ይሄኛው ደግሞ ያ ለነቢይነት የተመረጠው ግለሰብ ቀጥታ የአላህን ቃል ሳይሰማ ነገር ግን በመላኢካው (ጅብሪል) አማካይነት ከአላህ መልክት የሚቀበልበት መንገድ ነው :: ይህ ደግሞ ሙሉው ቁርዓን የወረደበት መንገድ ነው :: 114ቱም ሱራዎች 6236ቱም አያዎች በጅብሪል አማካይነት የወረዱ ናቸው :: እሱም ነብዩ በንቃተ ህሊናቸው እያሉ ነው :: «እርሱ (ቁርአን) የክቡር መልክተኛ ቃል ነው :: የሀይል ባለቤት ዘንድ ባለሟል የሆነ:: በዚያ ስፍራ ትዕዛዝ ተሰሚ እማኝ የሆነ (መልክተኛ ቃል) ነው ::» አል- ተክዊር 19-21 ይህ የቁርዓን አያ «ቁርአኑ» የጂብሪል ቃል እንደሆነ ነው የሚናገረው:: በእርግጠኝነት ግን ቁርዓን የአላህ ቃል ነው:: አል- ተውባህ

6 የጅብሪል ቃል የተባለበት ምክንያት ከጌታ አላህ ዘንድ ተቀብሎ በእማኝነት በማድረሱ ነው:: «እርሱ (ቁርአን) የተከበረ መልክተኛ ቃል ነው::» አል- ሃቃህ 40 እዚህ ጋር ደግሞ «ቁርዓን» የነቢዩ ቃል ተብሏል :: የሳቸው ቃል የተባለበት ምክንያት ደግሞ ከጅብሪል ተቀብለው ያለምንም ማጉደል ለተከታዮቻቸው ስላደረሱት ነው እንጂ ቁርአን የጅብሪልም ሆነ የነብዩ ቃል አይደለም :: በጥቅሉ መለኮታዊ ራዕይ መገለጫ መንገዶቹ ሶስት ብቻ እንደሆኑ ነው የምንረዳው ::

ዋናው ጉዳያችን ግን ስለ ቁርአን ማወቅ ስለሆነ ቁርዓን ደግሞ የወረደው በሶስተኛው መንገድ «በጅብሪል አማካኝነት» በመሆኑ ጅብሪል ከነቢዩ ዘንድ ቁርአንን ይዞ ሲመጣ በምን ዓይነት ሁኔታ ነበር የሚመጣው የሚለውን ለማወቅ ደግሞ ቀጥሎ ያሉት ነጥቦችን እንከታተል:: ጅብሪል ሶስት ዓይነት ባህሪዎች «መገለጫ መንገዶች» አሉት :: ከነዚህ ከሶስቱ ግን ቁርዓንን ይዞ የሚመጣው በአንደኛው ባህሪ ብቻ ነበር:: እነሱም፡-

1.ሲልሲለቱል ጀረስ «በቃጭል ድምጽ» እሜቴ አኢሻ፡- ሀሪስ ኢብኑ ሂሻም ነቢዩን፡- ወህይ እንዴት ነበር የሚመጣሎት? ሲላቸው እሳቸውም፡- አንዳንድ ጊዜ ልክ እንደ ቃጭል ድምጽ ይመጣልኛል አንዳንዴም መላኢካው በሰው አምሳል ይገለጽልኛል ብለው መመለሳቸውን ተናግራለች» ቡኻሪ የዘገበው :: ኢማሙ ሲዩጢ«ሲልሲለቱል ጀረስ» የሚለውን ቃል ሲያብራሩ፡- የመላኢካው የክንፉ እንቅስቃሴ ድምጽ ነው ብለዋል ::

2.«በሰው መመሰል» «....አንዳንዴም መላኢካው ለእኔ በሰው አምሳል ይገለጽልኛል» ብለው መመለሳቸውን እሜቴ አኢሻ ተናግራለች» ቡኻሪ የዘገበው :: ሌሎች የሀዲስ ዘገባዎችም ጅብሪል የሚመስልበት ሰው (ሰሀባ) «ዲሂየተል ከለቢ» መሆኑን ያስረዳሉ :: አንዳንድ ኡለማዎች ይህ መላኢካ በዚህ ሰሀባ ለምን እንደተመሰለ ምክንያቱን ሲያስረዱ፡- ዲሂየተል ከለቢ ከሰሀቦች ሁሉ በጣም ቆንጆ ስለነበረ ይህ መንፈሳዊ አካል የሆነው መላኢካ በእሱ መመሰሉ የተገባ ነው ብለዋል :: 3.አላ□ ሀይአቱል ሀቂቃ«ተፈጥሮአዊ በሆነ ቅርጹ» ጃቢር ኢብኑ አብዱላህ ባወራው ሀዲስ አቢሰለማ ኢብኑ አብዱራህማን፡- ጃቢር ኢብኑ አቢዲላህን ከቁርዓን መጀመሪያ የወረደው የትኛው ነው ብዬ ጠየቅኩት:: ጃቢርም «ያ አዩኸል ሙደሲር» ወይም «ኢቅራእ ቢስሚ ረቢከ» ነው :: እንደውም ነቢዩ የነገሩንን እነግራችኋለሁ:: ነቢዩም፡- እኔ ሂራዕን ኅበኘሁኝ:: ጉብኝቴን እንደጨረስኩ ወጣሁ :: ከዚያም ወደ ፊቴ ወደ ኋላዬ ወደ ቀኝና ወደ ግራዬ ተመለከትኩ:: ከዚያም ወደ ሰማይ ተመለከትኩ :: የዚያን ጊዜ ከዚህ በፊት አይቸው የነበረውን መላኢካ ተመለከትኩት :: እንቅጥቃጤም ይዞኝ ወደ ቤት በመምጣት እንዲሸፋፍኑኝ አዘዝኩ :: የዚያን ጊዜ «ያ አዩሀል ሙደሲር» የሚለው ወረደ ::

ኡለማኦች እንደተስማሙበት ደግሞ ነቢዩ ጅብሪልን በተፈጥሮ ቅርጹ ለርሱ 600 ክንፍ ያለው ሆኖ 2 ጊዜ አይተውታል ::

አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 በዚያ[1] (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም አንብብ።
2 ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)።[2]
3 አንብብ። ጌታህ በጣም ቸር ነው።
4 ያ በብዕር ያስተማረ ።
5 ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ነው።
6 በእውነት ሰው ወሰንን ያልፋል።
7 ራሱን የተብቃቃ (ባለ ሀብት) ሆ በማየቱ።
8 መመለሻ ወደ ጌታህ ብቻ ነው።
9 (መሀመድ ሆይ!)[3] ያንን የሚከለክለውን አየህን?
10 ባሪያን በሰገደ ጊዜ ፤
11 ንገረኝ (ተከልካዩ) በትክክለኛ መንገድ ላይ ቢሆን፤
12 ወይም (ፈጣሪውን) በመፍራት ቢያዝ፤
13 አየህን? ንገረኝ (ከልካዩ) ቢያስተባብልና (ከእምነት) ቢሸሽ፤
14 አላህ የሚያይ መሆኑን አያውቅምን?
15 ይታቀብ፤ ባይከለከል አናቱን ይዘን እንጎትተዋለን።
16 ውሸታም ስህተተኛ የሆነችውን አናቱን።
17 ሸንጎውንም[4] ይጥራ፤
18 (እኛም) ዘበኞቻችንን እንጠራለን።
19 ይታቀብ፤ (መሐመድ ሆይ! ይህን ለሚል ከሀዲ) አትታዘዘው፤ ስገድም፤ (ወደ አላህ) ተቃረብም[5]።

سُورَةُ القَدْرِ
آياتها ٥ — ترتيبها ٩٧

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

إِنَّآ أَنزَلۡنَٰهُ فِي لَيۡلَةِ ٱلۡقَدۡرِ ﴿١﴾ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا لَيۡلَةُ ٱلۡقَدۡرِ ﴿٢﴾
لَيۡلَةُ ٱلۡقَدۡرِ خَيۡرٞ مِّنۡ أَلۡفِ شَهۡرٖ ﴿٣﴾ تَنَزَّلُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ وَٱلرُّوحُ
فِيهَا بِإِذۡنِ رَبِّهِم مِّن كُلِّ أَمۡرٖ ﴿٤﴾ سَلَٰمٌ هِيَ حَتَّىٰ مَطۡلَعِ ٱلۡفَجۡرِ ﴿٥﴾

سُورَةُ البَيِّنَةِ
آياتها ٨ — ترتيبها ٩٨

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

لَمۡ يَكُنِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنۡ أَهۡلِ ٱلۡكِتَٰبِ وَٱلۡمُشۡرِكِينَ مُنفَكِّينَ
حَتَّىٰ تَأۡتِيَهُمُ ٱلۡبَيِّنَةُ ﴿١﴾ رَسُولٞ مِّنَ ٱللَّهِ يَتۡلُواْ صُحُفٗا مُّطَهَّرَةٗ ﴿٢﴾
فِيهَا كُتُبٞ قَيِّمَةٞ ﴿٣﴾ وَمَا تَفَرَّقَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ إِلَّا مِنۢ
بَعۡدِ مَا جَآءَتۡهُمُ ٱلۡبَيِّنَةُ ﴿٤﴾ وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مُخۡلِصِينَ
لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ وَيُقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُواْ ٱلزَّكَوٰةَۚ وَذَٰلِكَ دِينُ
ٱلۡقَيِّمَةِ ﴿٥﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنۡ أَهۡلِ ٱلۡكِتَٰبِ وَٱلۡمُشۡرِكِينَ
فِي نَارِ جَهَنَّمَ خَٰلِدِينَ فِيهَآۚ أُوْلَٰٓئِكَ هُمۡ شَرُّ ٱلۡبَرِيَّةِ ﴿٦﴾ إِنَّ
ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ أُوْلَٰٓئِكَ هُمۡ خَيۡرُ ٱلۡبَرِيَّةِ ﴿٧﴾

## 97 ኛው ምዕራፍ የመወሰኛው ምዕራፍ ነው።(ሱረቱ አል-ቀደር) አንቀጾቹ 5 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 እኛ[6] (ቁርአኑን) በመወሰኛይቱ (በተላቀችው) ሌሊት ውስጥ አወረድነው[7]።

---

[1] 1ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-አንድ ቀን አቡ ጀህል፡- ሙሐመድ በፊታችሁ ፊቱን በአፈር ያጨማልቃል (ይሰግዳል) ተባለ ። በላትና በዑዛ ይሁንብኝ ይህን ሲያደርግ ካየሁት ከአንገቱ ላይ ቁሜ ፊቱን በአፈር እለውሰዋለሁ በማለቱ ነው ። (ሱዩጢ፡፡)

[2] እዚህ ላይ ለማሳሳብ የምፈልገው የሰው ልጅ አራት መኖሪያ ቦታዎች እንዳሉት ሲሆን፡- እነሱም፡-
1.በእናቱ ሆድ. 2.በዱንያ ዐለም› 3.በበርዘኽና
4.በመጨረሻም ጀነት ወይም ጀሀነም ነው።

[3] 9ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-
ነብዩ ሙሀመድ (ﷺ) እየሰገዱ ባሉበት ወቅት አቡጀህል ወደ እሳቸው መጥቶ ስለ ከለከላቸው ነው። (ሱዩጢ ።)

[4] 17ኛው አንቀጽ-የወረደበት ምክንያት፡- ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) እየሰገዱ ባሉበት አቡጀህል መጥቶ ይህን ነገር ተው አላልኩህም? ሲላቸው ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ስለተቆጡት በዚህ አገር አንድም ከእኔ የተሻለ ቡድን ያለው እንደሌለ ታውቃለህ። እንዴት ደፍረህ ትናገረኛለህ? ስላላቸው ነው። (ሱዩጢ።)

[5] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። 1.ስለ ወህይ አጀማመርና የነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ)) ነቢይነት እንዴት እንደተከሰተና እንዴት እንደተጀመረ፣ 2.መልካም የተባለን ሁሉ በአላህ (ﷻ) ስም የመጀመር አጅር። 3.በመሐፀን ውስጥ የሰው ልጅ ሺል እድገትን በተመለከተ መግለጫ፣ 4.የአላህ (ﷻ) ቸርነት ከሁሉ የበለጠ መሆኑን፣ 5.ስለ መፃፍና ስለ መፃፊያ በዚያ በጨለማ ዘመን ማስታወሱና ክብር የሚገባው መሆኑን መጠቆም፣ 6.አላህ (ﷻ) የሰውን ልጅ የማያውቀውን በማሳወቁ የዋለለትን ከፍተኛ ውለታ ማስታወስና ማመስገን እንደሚገባው፣ 7. የሰው ልጅ ባህሪ ኢማን ከሌለው ምን እንደሚመስል፣ 8.አላህ (ﷻ) መልእክተኛውን መሐመድ (ﷺ)) እንደሚረዳ ቃል መግባቱን፣ 9-ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)) ከሁሉ በበለጠ ያስቃያቸው የነበረውንና የዚህች ኡመት ፈርዑን ነው ያሉት አቡጀህልን አላህ (ﷻ) እርግማን ያወረደበት መሆኑን በግልፅ እንማራለን።

[6] 1ኛው አንቀጽ የወረደበት ምክንያት፡-
ነቢዩ ሙሀመድ አንድ ሺህ ወር ለጅሃድ መሣሪያ የተሸከመ ሰው ታሪክ ስላወሩና ሰሃቦች በዚህ ሰውዬ ተግባርና ኸይር ስለቀኑ እናንተም የዚህን ሰውዬ እድል የምታገኙበት አለ ለማለት ነው ። (ሱዩጢ ።)

[7] ሙሉው ቁርአን የወረደው በነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ)) የነቢይነት እድሜ በ23 አመት ዉስጥ መሆኑ የታወቀ ሐቅ ነው ። ይህ አንቀጽ ደግሞ የምታስተምረው ቁርአን በለይለተል ቀድር መሆኑን ነዉና ሁለቱን ቁርአናዊ አናቅፅ እንዴት ማጣጣም ይቻላል ቢባል መልሱ እንደሚከተለው ነው ። ቁርአን በዚህች ሌሊት ከለውሐል መህፉዝ በአጠቃላይ ወደ ሰማዩ ዱንያ በአንድ ገዜ የወረደ ሲሆን በዚያው ዕለት የመጀመሪያይቱ ሱራ ወደ ምድር ወረደ ማለት እንጂ

2 መወሰኛይቱም (የተላቀችው) ሌሊት ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ?
3 መወሰኛይቱ የተላቀችው ሌሊት ከሺሕ ወር በላጭ ናት፡፡
4 በእርሷ ውስጥ መላእክትና መንፈሱ በጌታቸው ፈቃድ ከነገሮች[1] ሁሉ ይዘው ይወርዳሉ፡፡
5 እርሷ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሰላም ብቻ ናት፡፡[2]/[3]

## 98 ኛው ሱራ የግልፅ አስረጂዋ ምዕራፍ ነው፡፡(ሱረቱ አል-በዪናህ) አንቀጾቹ 8 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)፡፡

1 እነዚያ ከመጽሐፉ ባለቤቶችና ከአጋሪዎቸ የካዱት ግልጹ አስረጅ እስከ መጣላቸው ድረስ (ከነበሩበት ላይ) ተወጋጆች አልነበሩም፡፡[4]
2 (አስረጅውም) ከአላህ የሆነ መልእክተኛ፣ የተጥራሩ መጽሐፎች የሚያነብ ነው፡፡
3 በውስጧ ቀጥተኛ የሆኑ ጽሁፎች ያሉባት የሆነችን፡፡
4 እነዚያ መጽሀፉን የተሰጡ ሰዎች ግልጽ አስረጅ ከመጣላቸው በኋላ እንጅ አልተለያዩም፡፡
5 አላህን ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ ቀጥተኞች ሆነው ሊግገዙት፣ ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ፣ ዘካንም ሊሰጡ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆኑ (ተለያዩ)፡፡ ይህም የቀጥተኛይቱ (ሃይማ ት) ድንጋጌ ነው፡፡
6 እነዚያ ከመጽሐፉ ሰዎችና ከአጋሪዎችም የካዱት በውስጧ ዘውታሪዎች ሲሆኑ በገሀነም እሳት ውስጥ ናቸው፡፡ እነዚያ እነሱ ከፍጥረት ሁሉ ኳፉዎች/መጥፎዎች/ናቸው፡፡
7 እነዚያ ያመኑና መልካሞችንም የሰሩ እነሱ ከፍጥረት ሁሉ በላጭ/ምርጦች/ናቸው፡፡
8 በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው የመ ሪያ ገነቶች ናቸው፡፡ በውስጣቸው ለዘልዓለም ዘውታሪዎች ሲሆኑ (ይገቡባቸዋል)፡፡ አላህ ከነሱ (ስራቸውን) ወደደ፡፡ ከርሱም (ምንዳውን) ወደዱ፡፡ ይህ ጌታውን ለፈራ ሰው ነው፡፡[5]

## 99ኛው ምዕራፍ የመሬት መንቀጥቀጥ ምዕራፍ(ሱረቱ አዝ-ዘልዘለህ)ነው፡፡[6] አንቀጾቹ 8 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)፡፡

1 ምድር (በኃይል) መንቀጥቀጥን በተንቀጠቀጠች ጊዜ፤
2 ምድር ሸክሞችዋን ባወጣችም ጊዜ፤
3 ሰውም ምን ሆነች ባለ ጊዜ፤
4 በዚያ ቀን ወሬዎችዋን ትናገራለች፡፡
5 ጌታህ ለእርሷ በማሳወቁ ምክንያት፡፡
6 በዚያ ቀን ሰዎች ስራዎቻቸውን እንዲያዩ ይደረጉ ዘንድ (እንደየስራቸው) የተበታተኑ ሆነው (ከመቆሚያው ስፍራ) ይመለሳሉ፤

---

ሁሉም ቁርአን በአንድ ቀን ወደመሬት ወረደ ማለት አይደለም በማለት ነው ፡፡

[1] ትዕዛዛትም ማለት ይቻላል፡

[2] . ይህችን ሌሊት ለይቶ ለማወቅ የተደረገው ሙከራ ሁሉ ዉጤታማ አልሆነም ፡፡
ምክንያቱም 21ኛዋ/23ኛዋ /25ኛ 27ኛዋ/29ኛዋ ናት በሚል የተፍሲር ሙሁራን የተለያዩ ሲሆን ለእያንዳንዱ አባባል ማስረጃ ለማቅረብ ሙከራ አድርገዋል ፡፡ ሆኖም በብዙሃኖች ዘንድ የተደገፈውና ማስረጃዉም ጠንካራው አባባል 27ኛዋ ወይም 21ኛዋ ሌሊት ናት የሚሉት ናቸው ፡፡

[3] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ 1. ስለ ወህይና ስለ ነቢይነት ግልፅ አስተምህሮት፣ 2.የቀዷና የቀደርን ጉዳይ በግልፅ ማሳየት፣ 3.የለይለተል ቀድር ክብርና በእሷ ውስጥ የሚሠሩ በጎ ተግባራት አጅር በሌላው ጊዜ ከሚሰሩ ነገሮች ያላቸው ብልጫ ምን ያህል እንደሆነ፣ 4.ቁርአን መውረድ የጀመረው በረመዷን ወር መሆኑን፣ 5.ስለ ለይለተል ቀድር ክብር፣
6.ቁርአንን መቅራትና መስማት ያለውን ከፍተኛ ምንዳ እንማራለን፡፡

[4] ይህ አባባል ክህደት ከመጽሐፍ ሰዎችም ሆነ ከአጋሪዎች ዘንድ እንዳለ ያሳያል፡፡

[5] ከሱራው ከ ምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፡፡
1.ኢስላም በመጣበት ዘመን የነበሩት ልዩ ልዩ እምነቶች እውነት ከውሸት የተደባለቀባቸው እንደነበር፣
2.የመፅሐፍ ባለቤቶች የነቢዩን መላክ በተስፋ ይጠብቁት እንደነበርና ሲላኩ ግን ከፊሎች አምነው ከፊሎች እንደካዱ፣ 3.የመፀሐፍ ባለቤቶች በመፀሐፋቸው ከታዘዙት መካከል ሽርክንና ኩፍርን ወደ ጐን በመተው አላህን (ﷻ) በብቸኝነት እንዲያመልኩ፣ ሰላት እንዲሰግዱና ዘካ እንዲሠጡ ሲሆን ይህንኑ ተግብሩ ሲባሉ እንደ አመፁ፣
4.ትክክለኛው እምነትና ነፃ የሚያወጣው መንገድ አላህን (ﷻ) በብቸኝነት ማምለክና ሰላት መስገድ፣ዘካ መስጠት መሆኑን፣ 5. የካደ ሰው ቅጣቱ ከሁሉ የከፋ መሆኑን፣ 6.እስላምን የተቀበለ ምንዳው ጀነት እንደሆነ፣ 7.አላህን (ﷻ) መፍራት ምን ያህል መልካም ስነምግባር እንደሆነ፣ 8.ካፊሮች ከከብቶችና ከእንስሳዎች በታች መሆናቸዉን እንማራለን፡፡

[6] ሱረቱአዝ-ዘልዘለህ ከሱረቱ አን- ኒሣእ በላይና ከሱራህ አል- ሐዲድ በፊት በ94ኛ ተራ ቁጥር በመካ የወረደ ነው፡፡ ይህ ሱራ ሱረቱ አዚልዛልና ሱረቱ ኢዛዙልዚለት ይባላል፡፡

መግቢያ፡- ይህ ሱራ ስለ ቂያማ ቀን ጠቅላላ ሁኔታ አውስቶ በተለይ መሬት እንደምትንቀጥቀጥ በውስጧ ያሉት ማዕድናትም ሆነ የተቀበሩባት ሰዎች ከውስጧ እንደሚወጡ፣ የሰው ልጅ በሚያጋጥመው ድንገተኛ ጉዳይ በመደናገጥ ራሱን እንደሚጠይቅ፣ ሰዎችም ከየቀብራቸው እንደሚቀሰቀሱ ያስታዉሳል፡፡ ይህ ሱራ በወረደ ጊዜ አቡበክር በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አጠገብ ተቀምጠው እየተመገቡ ነበርና፡- የሰራሁትን ኢምንት እንኳን ተንኮል ተመልካች ነኝ፣ በማለት ማልቀስ ሲጀምሩ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)፡- ምን አስለቀሰህ? በማለት ሲጠይቋቸው ይህች ሱራ ናት ያስለቀሰችኝ በማለት መለሱ፡፡ በዚህ ጊዜ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡበክር እነዚያ በዚች ዐለም የሚያስከፉህ ነገሮችን አላየህም ፡፡ እነሱ እኮ የጥቃቅን መጥፎ ስራ ዉጤቶች ናቸው፡ ፡ አቡበክር እናንተ የማትሳሳቱና የማትወነጀሉ ብትሆኑ ኑሮ አላህ (ﷻ) እየተሳሳቱና እየወነጀሉ ይቅርታ የሚለምኑት ህዝቦች ሊፈጥር ይቺል ነበር አሏቸው፡፡ (በከፊሉ ጦበራኒ፤ በይሀቂ፤ ኢብኑአቢሓቲም ከአነስ ዘገበዉታል፡)

7 የብናኝ[1] ክብደት[2] ያክልም መልካምን የሠራ ሰው ያየዋል /ያገኘዋል/።
8 የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሠራ ሰው ያየዋል/ያገኘዋል/።[3]/[4]

## 100ኛው ሱራ የሯጮች ምዕራፍ/ ሱረቱ አል-ዓዲያት)ነው።[5] አንቀጾቹ 11ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 እያለከለኩ[6] ሩዋጮች በሆኑ (ፈረሶች)።
2 (በሸ ናቸው) እያጋጩ እሳትን አውጪዎች በሆኑትም (ፈረሶች)፤
3 በማለዳ ወራሪዎች በሆኑትም (ፈረሶች)፤
4 በእርሱ አቧራን በቀሰቀሱትም (ፈረሶች)፤
5 በ(ጠላት) ክቢ መካከል በርሱ (በጧት) በተጋፈጡትም (ፈረሶች) እምላለሁ።

جَزَآؤُهُمۡ عِندَ رَبِّهِمۡ جَنَّٰتُ عَدۡنٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ
فِيهَآ أَبَدٗاۖ رَّضِيَ ٱللَّهُ عَنۡهُمۡ وَرَضُواْ عَنۡهُۚ ذَٰلِكَ لِمَنۡ خَشِيَ رَبَّهُۥ ٨

ترتيبها ٩٩ — سُورَةُ الزَّلْزَلَةِ — آياتها ٨

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

إِذَا زُلۡزِلَتِ ٱلۡأَرۡضُ زِلۡزَالَهَا ١ وَأَخۡرَجَتِ ٱلۡأَرۡضُ أَثۡقَالَهَا
٢ وَقَالَ ٱلۡإِنسَٰنُ مَا لَهَا ٣ يَوۡمَئِذٖ تُحَدِّثُ أَخۡبَارَهَا ٤
بِأَنَّ رَبَّكَ أَوۡحَىٰ لَهَا ٥ يَوۡمَئِذٖ يَصۡدُرُ ٱلنَّاسُ أَشۡتَاتٗا
لِّيُرَوۡاْ أَعۡمَٰلَهُمۡ ٦ فَمَن يَعۡمَلۡ مِثۡقَالَ ذَرَّةٍ خَيۡرٗا
يَرَهُۥ ٧ وَمَن يَعۡمَلۡ مِثۡقَالَ ذَرَّةٖ شَرّٗا يَرَهُۥ ٨

ترتيبها ١٠٠ — سُورَةُ العَادِيَاتِ — آياتها ١١

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَٱلۡعَٰدِيَٰتِ ضَبۡحٗا ١ فَٱلۡمُورِيَٰتِ قَدۡحٗا ٢ فَٱلۡمُغِيرَٰتِ صُبۡحٗا
٣ فَأَثَرۡنَ بِهِۦ نَقۡعٗا ٤ فَوَسَطۡنَ بِهِۦ جَمۡعًا ٥ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ
لِرَبِّهِۦ لَكَنُودٞ ٦ وَإِنَّهُۥ عَلَىٰ ذَٰلِكَ لَشَهِيدٞ ٧ وَإِنَّهُۥ لِحُبِّ
ٱلۡخَيۡرِ لَشَدِيدٌ ٨ ۞ أَفَلَا يَعۡلَمُ إِذَا بُعۡثِرَ مَا فِي ٱلۡقُبُورِ ٩

6 ሰው ለጌታው ብርቱ ከሓዲ ነው።
7 እርሱም በዚያ ላይ መስካሪ ነው።[7]
8 እርሱም ገንዘብን በመውደድ በጣም ብርቱ ነው።
9 (ሰው) በመቃብሮች ያሉት (ሙታን) በተቀሰቀሱ ጊዜ፤ ምን እንደሚከሰት አያውቅምን?
10 በልቦች ውስጥ ያለውም ሁሉ በተገለጸ ጊዜ (እንዴት እንደሚሆን)፤
11 ጌታቸው በዚያ ቀን በእነሱ (ነገር) በእርግጥ ውስጠ ዐዋቂ ነው።[8]

---

[1] ከ7-8ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-
ሙቃቲል የተባሉ ዐሊም በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)) ዘመን ሁለት ሙስሊሞች ነበሩ ። እናም አንደኛው ትንሽ ነገርን በመስጠት አጅር የማያገኙ ስለሚመስለው የምወደዉን ነገር ስሰጥ ነዉ እንጂ በአንድ ቴምር፤በቁራሽ ቂጣ ምን አጅር ሊገኝ ነው እያለ ሲንቅ፤ ሌላኛው ደግሞ በአንፃሩ በጥቃቅን ወንጀሎች ማለትም፡- አንድ ጊዜ በመዋሼት፤አንድ ጊዜ አጅነቢይ ፆታ" በማየት፤ አንድ ጊዜ በማማት እንደማይቀጣ" ከቶዉንም የአላህ (ﷻ) ቅጣት በታላላቅ ወንጀሎች ብቻ የተገደበ ይመስለው ስለ ነበር ነው። (ሱዩጢ።) ሌሎች ደግሞ የመካ ካፊሮች የምርመራው ቀን መቼ ነው እያሉ ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) ይጠይቁ ስለ ነበር ነው ይላሉ።

[2] ቀደምት ዐሊሞች ዘራ ማለት የጎመንዘር ፍሬና የአቧራ ብናኝ ይሉን ነበር። ይህም የሆነው በእነሱ ጊዜ የነበረ አነስተኛ ነገር ይመሰል የነበረው በነዚህ ነገሮች ስለነበረ ነው። አሁን ግን ብዙ ጥቃቅን ነገሮች(አተሞች) ተገኝተዋል። በጣም ዘመናዊ በሆኑ ማጉሊያዎች እንኳን መታየት ያልቻሉና መኖራቸው ግን የተረጋገጠ ብዙ ነገሮች አሉ ።

[3] መልካም ስራ ሽርክ ካላበላሸው ኢምንትም ይሁን ጠቃሚ ነው። መጥፎ ስራ ደግሞ የአላህ ምህረት ካልተቸረው ኢምንትም ቢሆን ጎጅ ነው ። ስለዚህ መልካም ስራንም ሆነ ክፉ ስራን ማናናቅ የሙእሚን ባህሪ አይደለም።

[4] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ። 1.ሞቶ መነሳትንና የትኛዉም ተግባር ተገቢ ምንዳ እንዳለው፣ 2.የዚህን ዓለም ለውጥ መምጣት አይቀሬ መሆኑን በግልፅ ማስቀመጥ፣ 3.የመሬት መናገር ከአላህ (ﷻ) ተዐምራት አንዱ መሆኑን፣ 4.ኸይር ሥራ ምንም ብታንስ ጠቃሚ መሆንዋንና መጥፎ ሥራም እንዲሁ ምንም ያህል ቢያንስ ጉጂ መሆኑን፣ 5.የካፊር በጐ ሥራ የሚጠቀመው በዚህች ዓለም እንጂ በአኺራ እንደማይጠቀመው፤ 6.መጥፎን ተግባርን (የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሠራ ሰው ያየዋል /ያገኘዋል/) ስላለ ማየቱ ቀርቶ ካለፈ በኋላ ስለ እሱ ማስታወሱ እንኳን ቅጣት መሆኑን እንማራለን ።

[5] ሱረቱአል- ዓዲያት ከሱረቱል አስር ቀጥላ ከሱረቱ አልከውሰር በፊት በ14ኛ በብዙ ዐሊሞች ዘንድ በመካ የወረደ ሱራ ነው ። አንዳንድ ዐሊሞች ደግሞ ሱራው የወረደው በመዲና ነው ብለዋል። ማስረጃው የሚደግፈዉና የሚመረጠዉም ይህው አባባል ነው ። ይህ ሱራ ሱረቱ ወልዓዲያት በመባልም ይታወቃል፡

[6] 1ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-
ነቢዩ (ﷺ)) በሙንዚር ቢን ዓምር የሚመራ አንድ ቡድን ወደ ኪናና ቢሔር ልከው ስለ ዘገየ እና ወሬአቸው ስለ ጠፋ ሙናፊቆች፡- ሁሉም አለቁ እኮ ብለው ስለአወሩ ነው። (ዋሂዲ እና ሱዩጢ ።)

[7] ይህ አንቀፅ የሰው ልጅ ክህደቱን በራሱ ይመሰክራል ማለትን ሲያመለክት (እነዚያ እነሱ ሥራን የሚያሳምሩ የሚመስላቸው ሲሆኑ በቅርቢቱ ህይወት ሥራቸው የጠፋባቸው ናቸው። 18/104 (እነርሱም ቅኑን መንገድ የተመራን ነን ብለው ያስባሉ።) 7/30 የሚሉት ደግሞ የዚህን ተቃራኒ ያመለክታሉ ። ሁለቱን እንዴት ማስማማት እንዳለበት ሲያብራሩ ሁኔታው እንደሚመሰክር ነው ማለት ነው። የሰው ልጅ በራሱ ላይ የሚመሰክረው ። በነፍሶቻቸውም ላይ እነርሱ ካሓዲች የነበሩ መሆናቸውን መሰከሩ።) 6/130 (በየኃጢአታቸውም ያምናሉ። ለእሳት ጓዶችም (ከእዝነት) መራቅ ተገባቸው።) 67/11 እንዳለው ሁሉ የቂያማ ዕለት መሆኑን ነው።

[8] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። 1.ለጂሃድ ሰዎችን መገፋፋትና ለራስም መዘጋጀት እንደሚያስፈልግ፣

وَحُصِّلَ مَا فِي ٱلصُّدُورِ ﴿١٠﴾ إِنَّ رَبَّهُم بِهِمْ يَوْمَئِذٍ لَّخَبِيرٌۢ ﴿١١﴾

ترتيبها ١٠١ — سُورَةُ القَارِعَةِ — آياتها ١١

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

ٱلْقَارِعَةُ ﴿١﴾ مَا ٱلْقَارِعَةُ ﴿٢﴾ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا ٱلْقَارِعَةُ
﴿٣﴾ يَوْمَ يَكُونُ ٱلنَّاسُ كَٱلْفَرَاشِ ٱلْمَبْثُوثِ ﴿٤﴾
وَتَكُونُ ٱلْجِبَالُ كَٱلْعِهْنِ ٱلْمَنفُوشِ ﴿٥﴾ فَأَمَّا
مَن ثَقُلَتْ مَوَٰزِينُهُۥ ﴿٦﴾ فَهُوَ فِي عِيشَةٍ رَّاضِيَةٍ
﴿٧﴾ وَأَمَّا مَنْ خَفَّتْ مَوَٰزِينُهُۥ ﴿٨﴾ فَأُمُّهُۥ هَاوِيَةٌ
﴿٩﴾ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا هِيَهْ ﴿١٠﴾ نَارٌ حَامِيَةٌۢ ﴿١١﴾

ترتيبها ١٠٢ — سُورَةُ التَّكَاثُرِ — آياتها ٨

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

أَلْهَىٰكُمُ ٱلتَّكَاثُرُ ﴿١﴾ حَتَّىٰ زُرْتُمُ ٱلْمَقَابِرَ ﴿٢﴾ كَلَّا سَوْفَ
تَعْلَمُونَ ﴿٣﴾ ثُمَّ كَلَّا سَوْفَ تَعْلَمُونَ ﴿٤﴾ كَلَّا لَوْ تَعْلَمُونَ
عِلْمَ ٱلْيَقِينِ ﴿٥﴾ لَتَرَوُنَّ ٱلْجَحِيمَ ﴿٦﴾ ثُمَّ لَتَرَوُنَّهَا
عَيْنَ ٱلْيَقِينِ ﴿٧﴾ ثُمَّ لَتُسْـَٔلُنَّ يَوْمَئِذٍ عَنِ ٱلنَّعِيمِ ﴿٨﴾

## 101 ኛው ሱራ፡ የቆርቋሪይቱ ምዕራፍ/ ሱረተ (ሱረቱ አል-ቃሪዐህ) ነው: [1] አንቀጾቹ 11 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

(1) ቆርቋሪይቱ (ጩኸት) ፤
(2) ምን አስደናቂ ቆርቋሪ ናት!
(3) ቆርቋሪይቱም ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ?
(4) ሰዎች እንደ ተበታተነ ቢራ ቢሮ (ወይም ኩብኩባ) በሚሆኑበት ቀን ፤
(5) ጋራዎችም እንደ ተነደፈ ሱፍ በሚሆኑበት (ቀን ልቦችን በድንጋጤ ትቆረቆራለች)።
(6) (7) ሚዛ ቹ የከበዱለት ሰው እርሱ በምትወደድ ኑሮ ውስጥ ይሆናል።
(8) (9) ሚዛ ቹ የቀለሉበት ሰው፤ ደግሞ መ ሪያው[2] ሃዊያህ ናት።
(10) ስለ እርሷ ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ?
(11) (እርሷ) በጣም ተኳሳ እሳት ናት።[3]

## 102 ኛው ሱራ በብዛት የመፎካከር ምዕራፍ/(ሱረቱ አት-ተካሱር)ነው:: [4]አንቀጾቹ 8 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

(1) (2) (በዚህች[5] ዓለም ፀጋዎች) ብዛት መፎካከር (ጌታችሁን ከመገዛት) አዘናጋችሁ፤ መቃብሮችን እስከ ጎበኛችሁ ድረስ።
(3) ተከልከሉ /ታቀቡ/፤ ወደፊት (ውጤቱን) ታውቃላችሁ፤
(4) ከዚያም[6] ተከልከሉ፣ ወደ ፊት ታውቃላችሁ።
(5) በእውነቱ (የሚጠብቃችሁን) እርግጠኛ ዕውቀትን ብታውቁ ሮ (ባልዘነጋችሁ ነበር)።

---

2.የሰው ልጅ እምነት ከሌለው አላህ ለዋለለት ውለታና ለለገሰለት ፀጋ ከሃዲ ስለመሆኑ፣ 3.የሰው ልጅ ካላመነ በስተቀር ገንዘብን በጣም ከሚገባው በላይ እንደሚወድ፣ 4.ሞቶ መነሳትና ምንዳ ያለ መሆኑን ማረጋገጥን እንማራለን::

[1] ሱረቱ አልቃሪዐህ ከሱረቱ ቁረይሽ በኋላና ከሱረቱ አልቂያመህ በፊት በመካ በ30ኛ የወረደ ሱራ ነው ። የሰዎችን ፊት የሚለዋውጠውን የገሀነምን ቅጣት ክብደት በማውሳት ጀምሮ ሰዎችም ሆኑ ጋኔኖች በዚያን ጊዜ ምን እንደሚሆኑ አውስቷል። ሰዎች የስራቸው ዋጋ ሲሰጣቸው ምን እንደሚጠብቃቸው በማውሳት መልዕክቱን ያጠቃልላል።
ሱራው በጣም አስደንጋጭ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ቀን ዑመር ብን ዐብዱ-ል ዐዚዝ ሰምተውት አእምሯቸዉን እስከሚስቱ ድረስ ሙሉ ሌሊት እያለቀሱና ወይኔ (ሰዎች እንደ ተበታተነ ቢራ ቢሮ (ወይም ኩብኩባ) በሚሆኑበት ቀን፤ ጋራዎችም እንደ ተነደፈ ሱፍ በሚሆኑበት (ቀን) ምን ይበጀኝ ይሆን እያሉ አነጉ ይባላል ።

[2] ይህ አባባል ሶስት ተፍሲር አለው። አንደኛው ኡም የሚለውቃል አናቱ፤ ጭንቅላቱ፤ ማለት ሲሆን ይህም ማለት በአናቱ ተዘቅዝቆ በእሳት ዉስጥ ይወረወራል ማለት ሲሆን፤ ሁለተኛው እናቱ በሀዘን ወዳቂናት ማለት ነውም ተብሏል። ሶስተኛው ኡም ማለት እናት ማለት ቢሆንም ገሀነም የዘንት አለም መኖሪያው በመሆኗ እንደእናቱ መቆጠሯን ያመለክታል የሚለው ነው።

[3] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው:: 1.ሞቶ መነሳትና የምንዳ ቀንን ማረጋገጥ፣ 2.የቂያማ ቀን ሚዛን እንዳለና መልካም ስራም ሆነ መጥፎ እንደሚመዘን፤ 3.ከቂያማ ዕለት ሰቆቃ ድንጋጤ ማስጠንቀቅ፣ 4.ሥራ-ችን እንደሚመዘንና ምንዳውም በዚሁ መሠረት እንደሚሆን፣ 5.ሰዎች የቂያማ ዕለት ሁለት ቡድን እንደሚሆኑና አንዱ የጀነት ሲሆን ሌላኛው የገሀነም እንደሚሆን፤ 6.መልካም ስራዉና መጥፎ ተግባሩ እኩል የሆነበት ሰው ምን እንደሚሆን በዚህች ሱራ ዉስጥ ግልፅ ባይሆንም በሱረቱል-አዕራፍ ላይ በጀነትና በጀሀነም መካከል እንደሚሆኑ ተገልጧል፤ 7.ጀሀነም እሳት ብትሆን ወንጀለኞች ሌላ መጠጊያ ስለሌላቸው እሷኑ እንደእናት ያደረገባቸው መሆኑን እንማራለን ።

[4] በአብዛኛ ዐሊሞች ዘንድ በመካ የወረደ ሱራ ነው ። ሌሎች ደግሞ በመዲና የወረደ ሱራ ነው ተብሏል ። ይህ ሱራ ሱረቱ አልሃኩምና ሱረቱ አልመቅበረህ ይባላል። የአንቀፆቹ ብዛት ስምንት ናቸው።

[5] **ይህ ምዕራፍ የወረደበት ምክንያት፡-** ሁለት የቁረይሽ ብሔሮች ማለትም፡- በኒ ዓብድመናፍ እና በኒ ሰህም በተባሉ ብሔሮች መካከል የነበረው የእርስ በእርስ የዘር ፉክክር በተመለከተ ነው ። (ዋሂዲ።)

[6] ታላቁ ዐሊም ሐሰኑ-ልበስሪ ተደጋጋሚ ዛቻ ነው ብለዉታል። ኢብኑ ዐባስ ደግሞ የመጀመሪያው የቀብርን ቅጣት ሲያመለክት ሁለተኛው ደግሞ የአኼራዉን ቅጣት ነው የሚያመለክተው ብለዋል።

6 ገሀነምን በእርግጥ ታያላችሁ፡፡
7 ከዚያም እርግጠኛን ማየት ታዩዋታላችሁ፤
8 ከዚያም ከድሎታችሁ ሁሉ በዚያ ቀን ትጠየቃላችሁ፡፡ [1]/[2]

## 103 ኛው ሱራ፡- የጊዚያት ምዕራፍ (ሱረቱ አል-ዓስር) ነው፡፡[3] አንቀጾቹ 3 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም እና አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)፡፡

1 በጊዜ እምላለሁ፤
2 ሰው ሁሉ በእርግጥ በኪሳራ ውስጥ ነው፡፡
3 እነዚያ ያመኑና መልካሞችን የሰሩ፤ በእውነትም[4] አደራ የተባባሉት፤ በመታገሥም አደራ የተባባሉ[5] ብቻ ሲቀሩ፡፡[6]

---

[1] ዑመር ብን-ልኸጣብ አንድ ቀን፡- ከየትኛው ፀጋ ነው የምንጠየቀው? ከሀገራችን ተባረን ንብረታችንን ተዘርፈን፣ ብለው ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሲጠይቁ ከፀሐይና ከብርድ የሚከላከሉላችሁ የግድግዳ፤ የዛፍና የድንኳን ጥላዎችስ? በጠራራ ሰአት የምትጠጡት ቀዝቃዛ ዉሃስ በማለት መለሱላቸው ፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በቤቱ ሰላም ያደረ፤ ሰውነቱ ጤና የሆነና የዕለት ቀለብ ያለው ዱንያ ተጠቃላ ገባችለት ብለዋል፡፡

[2] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ 1.ግዴታውን የማይወጡለት ገንዘብ አደገኛነት፣ 2.ስለ ቀብር ቅጣት መኖር ማረጋገጥ፣ 3.ስለ ቀብር ጉብኚት አስፈላጊነት መጠቆም፤ 4.ሞቶ መነሳትና ከዚያም የሥራን ዋጋ ማግኘት ያለ መሆኑን፣ 5. አላህ (ﷻ) ለሰጠው ውለታ ሁሉ መጠየቁ የማይቀር ሐቅ መሆኑን እንማራለን፡፡

[3] ሱረቱ አል-ዓስር ከሱረቱ አልኢንሺራሕ በኋላ ከሱረቱ አልዓዲያት በፊት 13ኛ ሆኖ በአብዛኞቹ ዓሊሞች ዘንድ በመካ የወረደ ሱራ ነው ፡፡ ይህ ሱራ ሱረቱ ወልአስር በመባልም ይታወቃል ፡፡

[4] እውነት የሚለው ቃል ቁርአን ወይም ኸይር ነገር ሁሉ ማለት ነው ተብሏል ፡፡ በእውነት ነገር ላይ አደራ መባባል የነቢያት መንገድም አደራቸዉም ነው፡፡ አላህ (ለናንተ ከሃይማኖት ያንን በርሱ ኑህን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ ፤ ያንንም ወዳንተ ያወረድነውን ያንንም በርሱ ኢብራሂምን ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ በርሱም አትለያዩ ማለትን (ደነገግን) በአጋሪዎቹ ላይ ያ ወደርሱ የምትጠራቸው ነገር ከበዳቸው ፤ አላህ የሚሻውን ሰው ወደርሱ እምነት ይመርጣል የሚመለስንም ሰው ወደርሱ ይመራል፡፡))42/13፡፡ በዲን ላይ አደራ መባባል የነቢያት ፈለግ ነው፡፡ አላህ እንዲህም አለ (በእርሷም (በህግጋቲቱ) ኢብራሂም ልጆቹን አዘዘ፡፡ ያዕቁብም (እንደዚሁ ልጆቹን አዘዘ)፡፡ ልጆቼ ሆይ! አላህ ለእናንተ ሀይማኖትን መረጠ፡፡ ስለዚህ እናንተ ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጂ አትሙቱ (አላቸው) 2/132

[5] ትዕግስት ለሁሉም አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይም ለመልካም ሰሪዎች በይበልጥ ሰዎችን ለማስተማር ለሚያስቡ ሁሉ ለስራቸው መቃናት አስፈላጊው ነገር ትዕግስት ነው፡፡ ሉቅማን ለልጃቸው ከለገሱት ምክር መካከል የሚከተለው አባባል ነበረበት (ልጄ ሆይ ሶላትን አስተካክለህ ስገድ በበጎ ነገርም እዘዝ ከሚጠላም ሁሉ ከልክል፡፡ በሚያገኝህም መከራ ላይ ታገስ፡፡)

[6] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፡፡ 1.የከሃዲ መጨረሻው ዘላለማዊ ክስረት መሆኑን፣ 2.በአላህ (ﷻ) ያመኑና መልካም የሰሩ ሰዎች ክብርና ትልቅነት ምን እንደሆነ፣ 3.በእውነትና በትዕግስት ለሐቅ መትጋትና መከራከር ግዴታ መሆኑን፤ 4.ሰዎችን ለማስተማር የሚንቀሳቀስ ሰው እውነቱን ሊደብቃቸው እንደማይገባ፤ 5.--ሰዎችን ለማስተማር የሚንቀሳቀስ ሰው ብዙ ችግር ሊያጋጥሙት እንደሚችሉና ከወዲሁ የመንፈስ ዝግጅት አድርጎ ሊጠብቃቸው እንደሚገባ፤ 6.-ሐቅን የሚፈልግ ሰው ሁሉ በትዕግስት መጠበቅ እንደሚገባው እንማራለን ፡፡

سُورَةُ العَصۡرِ — ترتيبها ١٠٣ — آياتها ٣

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَٱلۡعَصۡرِ ١ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَفِي خُسۡرٍ ٢ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ
وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَتَوَاصَوۡاْ بِٱلۡحَقِّ وَتَوَاصَوۡاْ بِٱلصَّبۡرِ ٣

سُورَةُ الهُمَزَةِ — ترتيبها ١٠٤ — آياتها ٩

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَيۡلٞ لِّكُلِّ هُمَزَةٖ لُّمَزَةٍ ١ ٱلَّذِي جَمَعَ مَالٗا وَعَدَّدَهُۥ ٢
يَحۡسَبُ أَنَّ مَالَهُۥٓ أَخۡلَدَهُۥ ٣ كَلَّاۖ لَيُنۢبَذَنَّ فِي ٱلۡحُطَمَةِ ٤
وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا ٱلۡحُطَمَةُ ٥ نَارُ ٱللَّهِ ٱلۡمُوقَدَةُ ٦ ٱلَّتِي تَطَّلِعُ
عَلَى ٱلۡأَفۡـِٔدَةِ ٧ إِنَّهَا عَلَيۡهِم مُّؤۡصَدَةٞ ٨ فِي عَمَدٖ مُّمَدَّدَةِۭ ٩

سُورَةُ الفِيلِ — ترتيبها ١٠٥ — آياتها ٥

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

أَلَمۡ تَرَ كَيۡفَ فَعَلَ رَبُّكَ بِأَصۡحَٰبِ ٱلۡفِيلِ ١ أَلَمۡ يَجۡعَلۡ كَيۡدَهُمۡ
فِي تَضۡلِيلٖ ٢ وَأَرۡسَلَ عَلَيۡهِمۡ طَيۡرًا أَبَابِيلَ ٣ تَرۡمِيهِم
بِحِجَارَةٖ مِّن سِجِّيلٖ ٤ فَجَعَلَهُمۡ كَعَصۡفٖ مَّأۡكُولِۭ ٥

## 104 ኛው ሱራ ፡-የሀሜተኛ ምዕራፍ ነው፡፡[7] (ሱረቱ አል-ሁመዛህ) አንቀጾቹ 9 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)፡፡

1 ለሐሚተኛ፣[8] ለዘላፊ፣ አሽሟጣጭ ሁሉ ወዮለት፡፡
2 ለእዚያ ገንዘብን የሰበሰበና የቆጣጠረው (ያደለበውም) ለሆነ (ወዮለት)፡፡
3 ገንዘቡ የሚያዘወትረው መሆኑን ያስባል፡፡
4 ይከልከል /ይታቀብ/፤ በሰባሪይቱ (አውዳሚቱ) (እሳት) ውስጥ በእርግጥ ይጣላል፡፡

---

[7] ይህ ሱራ ሱረቱ ወይሉ ሊኩሉ ሁመዛህና ሱረቱ አል-ሁሰጦመህ በመባልም ይታወቃል ፡፡ አንቀጾቹ ዘጠኝ ናቸው ፡፡

[8] ይህ ሱራ የወረደበት ምክንያት፡-ብዛት ያላቸው አሊሞች፡- ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) ሲወጡና ሲገቡ ያስቸግራቸው በነበረው በኡበይ ብን ኸለፍ ምክንያት ነው የወረደው ሲሉ፤ አንዳንዶች አሊሞች ደግሞ በአኽነስ ኢብኑ ሸሪቅ ምክንያት ነው የሚሉም አሉ፡፡ (ሱዩጢ፡፡)

سُورَةُ قُرَيۡشٍ
آياتها ٤ — ترتيبها ١٠٦

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

لِإِيلَٰفِ قُرَيۡشٍ ١ إِۦلَٰفِهِمۡ رِحۡلَةَ ٱلشِّتَآءِ وَٱلصَّيۡفِ
٢ فَلۡيَعۡبُدُواْ رَبَّ هَٰذَا ٱلۡبَيۡتِ ٣ ٱلَّذِيٓ أَطۡعَمَهُم
مِّن جُوعٖ وَءَامَنَهُم مِّنۡ خَوۡفِۭ ٤

سُورَةُ المَاعُونَ
آياتها ٧ — ترتيبها ١٠٧

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

أَرَءَيۡتَ ٱلَّذِي يُكَذِّبُ بِٱلدِّينِ ١ فَذَٰلِكَ ٱلَّذِي
يَدُعُّ ٱلۡيَتِيمَ ٢ وَلَا يَحُضُّ عَلَىٰ طَعَامِ ٱلۡمِسۡكِينِ ٣
فَوَيۡلٞ لِّلۡمُصَلِّينَ ٤ ٱلَّذِينَ هُمۡ عَن صَلَاتِهِمۡ سَاهُونَ
٥ ٱلَّذِينَ هُمۡ يُرَآءُونَ ٦ وَيَمۡنَعُونَ ٱلۡمَاعُونَ ٧

سُورَةُ الكَوۡثَرِ
آياتها ٣ — ترتيبها ١٠٨

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

إِنَّآ أَعۡطَيۡنَٰكَ ٱلۡكَوۡثَرَ ١ فَصَلِّ لِرَبِّكَ وَٱنۡحَرۡ ٢
إِنَّ شَانِئَكَ هُوَ ٱلۡأَبۡتَرُ ٣

5 ሰባሪይቱም ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ?
6 የተነደደችው የአላህ እሳት ናት ።
7 ያቺ በልቦች ላይ የምትዘልቅ የሆነችው።
8 9 እርሷ በእርግጥ በእነርሱ ላይ
በተዘረጋች አዕማ ውስጥ የተዘጋች ናት።[1]

## 105 ኛው ሱራ የዝሆኑ ምዕራፍ ነው። (ሱረቱ አል-ፊል)[2]/ አንቀጾቹ 5 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህእና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 (ሙሐመድ[3] ሆይ!) በዝሆኑ ባለቤቶች ላይ
ጌታህ[4] እንዴት እንደሠራ አላወቅህምን?
2 ተንኮላቸውን በጥፋት ውስጥ (ከንቱ)
አላደረገምን?
3 በነሱ ላይ መንጎች የሆኑን ወፎች ላከ።
4 ከተጠበሰ ጭቃ በሆነ ደንጊያ
የምትወረውርባቸው የሆነችን (አዕዋፍ)።
5 ቅጠሉ እንደ ተበላ አዝመራም አደረጋቸው።[5]

## 106 ኛው ሱራ የቁረይሾች ምዕራፍ ነው[6]። (ሱረቱ ቁረይሽ) አንቀጾቹ 4 ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 ቁረይሽን ለማላመድ(ባለ ዝሆ ቹን አጠፋ)።
2 ክረምትንና የበጋን ወራት ጉዞዎች
ሊያላምዳቸው (ይህንን ሠራ) ።
3 ስለዚህ የዚህን ቤት (የካዕባን) ጌታ
ይግገዙ /ያምልኩ/።
4 ያንን ከርኃብ ያበላቸውን፣ ከፍርሃትም
ያዳናቸውን (ጌታ ያምልኩ)።[7]

## 107 ኛው ሱራ :- የእቃ መዋዋስ ምዕራፍ[8] ነው። (ሱረቱ አል-ማዑን)አንቀጾቹ 7 ናቸው።

---

[1] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። **1.**ሞቶ መነሳትና ለሰሩት ምንዳ ማግኘት አይቀሬ መሆኑን፣ **2.**ሰዎችን ሐሜትና ነገር ማዋሳድን ማውገዝ፣ **3.**በንብረት የሚመኩ ሁሉ ጠንካራ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው፣ **4.**የገሀነም ቅጣት ምን ያህል ብርቱ መሆኑንና የገባባትን ሁሉ እንደምታም እንማራለን ።

[2] ይህ ሱራ ሱረቱ አለምተራ በመባልም ይታወቃል ። **መግቢያ:-** ሱራው የተከበረውን ቤት ካዕባን ለማፍረስ ተዘጋጅቶ ሂዶ የነበረውን ኢትዮጵያዊ ወራሪ ቡድን የደረሠበትን ታሪክና አስተምህሮት ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) እንዲያስታውሱ ያስተምራል። አላህ (عز وجل) የእሱን ህግጋትና ደንብ የሚያልፉ ሰዎች ሁሉ ተመሣሣይ እርምጃዎች እንደሚወሰድባቸውም ያስተምራል።

[3] **ይህ ሱራ የወረደበት ምክንያት፡-** ካዕባን ሊያፈርሱ ወደ መካ ተጉዘው የነበሩትን ኢትዮጵያዊያን ሀይል እንዴት እንደመለሰላቸውና ካዕባን ቀደም ሲልም እንዴት እንደ ተንከባከበው የሚያሳየውን ታሪክ ለመኮች ለማስታወስ ነው ። ዋሂዲ ።

[4] አላህ በአብረሀም አልአሽረም መሪነት ወደ መካ በመሄድ ከዕባን ለማፍረስ በሞከሩ ጊዜ የሆነዉን ማለት ነው ።

[5] **ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎች የሚከተሉት ናቸው ።** **1.**የታሪክን አስተማሪነት በሰፊው መገንዘብ፤ **2.**አንድን ታሪክ በተለይ በሰዎች ዘንድ የታወቀ ከሆነ በአጭሩ መጥቀስ እንደሚቻል፤ **3.**ነቢዩ (ﷺ) የቁረይሽ ከሃዲ-ዎች በሚያደደርሱባቸው ችግርና ስቃይ እንዳይበሳጩ ማፅናናት፣ አላህ (عز وجل) ከዕባን እንደጠበቀ ሁሉ ነቢዩ ሙሀመድንም (ﷺ) ሆነ ኢስላምን ከፈለገው ሀይል እንደሚጠብቀው፤ **4.**ሙስሊሞች ላይ ስቃይ ሲፈፅሙ ቁረይሾች የአላህን (عز وجل) ሃይልና ቅጣት እንዲያስ ውሱ ማድረግና መጋበዝ፣ **5.**አላህ (عز وجل) ጠቅላላ ሃይሉን ማሳየትና ማሳወቅ፤ **6.**በምድር ላይ ጉልበት አለኝ ሀብት አለኝ ስልጣን አለኝ ብሎ የሚደነፋ ሁሉ በአላህ (عز وجل) ዘንድ ቅንጣት ያህል እንደማይከብድ እንማራለን።

[6] ሱረቱል ቁረይሽ ። ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ።

[7] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ። **1.**ጥበበኛና ርህሩህ የሆነው ጌታ አላህ (عز وجل) ቅንብር ምን ምን እንደሚመስል በግልጽ ማየት፣ **2.**አላህ (عز وجل) ለቁረይሾች የዋለው ታላላቅ ፀጋና እሱን ባለማመስገናቸው ያጋጠማቸው ችግር ምን እንደሆነ ማየት፣ **3.**አላህን (عز وجل) በብቸኝነት ማምለክ ግዴታ ስለመሆኑ፣ **4.**የአላህ (عز وجل) ፀጋዎችን ማመስገን ግዴታ ስለመሆኑ፣ **5.**በቂ ምግብና የተሟላ ሰላም ማስገኘት የአንድ ገዢ መገለጫ ሲሆን ይህንንም ያለአላህ (عز وجل) ማንም ሊያደርገው እንደማይችል እንማራለን።

[8] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

(1) (ሙሐመድ[1] ሆይ!) ያንን በምርመራው የሚያስተባብለውን አየህን ?/ (ዐወቅከውን ?)
(2) ይህም[2] ያ የቲምን በኃይል የሚገፈትረው፤
(3) ያንም በማብላት ላይ ለራሱ ይቅርና ሌሎችን የማያግባባው (የማያነሳሳ) ሰው ነው።
(4) ወዮላቸው ለሰጋጆች ፤
(5) ለእነዚያ እነሱ ከሰግደታቸው ዘንጊዎች[3] ለሆኑት ፤(ሰጋጆች)።
(6) ለእነዚያ እነሱ ይውልኝ ባዮች ለሆኑት ፤
(7) የዕቃ ትውስትንም (ሰዎችን) የሚከለክሉ ለሆኑት (ወዮላቸው)።[4]

## 108 ኛው የበጎ ነገሮች ምዕራፍ)[5] (ሱረቱ አል-ከውሰር)አንቀጾቹ 3ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

(1) (ሙሐመድ ሆይ!) እኛ በጣም ብዙ በጎ ነገሮችን ሰጠንህ /ለገስንህ/።
(2) ስለዚህ ለጌታህ በፈፀምናት ስገድ (በስሙ) ብቻ ሠዋም።
(3) የሚጠላህ እርሱ በእርግጥ (ዘሩ)የተቆረጠ ነው።[6]

## 109 ው ሱራ፡- የከሃዲዎች ምዕራፍ።[7] : (ሱረቱ አል-ካፊሩን)አንቀጾቹ 6ናቸው።

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

(1) (ሙሐመድ ሆይ!)[8] ለካሓዲያን በላቸው ፡- -እናንተ ከሓዲዎች ሆይ ፤
(2) ያንን የምትግገዙትን (ጣዖት አሁን) አልግገዛም።
(3) እናንተም እኔ የምግገዛውን (አምላክ አሁን) ተገገርዎች አይደላችሁም [9]።
(4) እኔም ያንን የተገዛችሁትን (ወደፊት) ተገገር አይደለሁም።
(5) እናንተም እኔ የምግገዛውን (ወደፊት) ተገገርዎች አይደላችሁም።
(6) እናንተ የራሳችሁ ሃይማ ት አላችሁ፤ እኔም የራሴ ሃይማ ት አለኝ።[10]

## 110 ኛው ምዕራፍ የዕርዳታው ምዕራፍ (ሱረቱ አን-ነስር) ነው።[11] አንቀጾቹ 3 ናቸው።

---

[1] **ከ1-4 የወረበት ምክንያት፡-** ዓስ ቢን ዋኢል በተባለ መካዊ ግለሰብ ምክንያት ነው ። ዋሂዲ።፡

[2] 2ኛው አንቀፅ-የወረደበት ምክናየት፡-አቡሱፍያን ቢን ሐርብ በየሳምንቱ ሁለት ግመሎች እያረደ ያበላ ነበርና ከዕለታት አንድ ቀን አንድ የቲም መጥቶ ሲለምነው በቁጣ ስለ ገለመጠው እና በዱላ ስላ ባረረው ነው።

[3] .የዚህን አንቀጽ ትርጉም በተመለከተ ሁለት ዋና ዋና አባባሎች ያሉ ሲሆኑ፡- የተመረጡው ጊዜዋን የሚያሳልፉ ማለት እንደሆነና ከብነ ዐባስ የተ ዘገበው ነው ።

[4] ከሱራው ከ ምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። **1.**ሞቶ መነሳት ያለና ሓቅ መሆኑን ማረጋገጥ፣ **2.**በሞቶ መነሳት የማያምን ሁሉ እርጉም መሆኑን፣ **3.**የየቲሞችን ንብረት የሚበሉና እነሱን በመናቅ የሚገፋተሩ ሁሉ በአላህ ዘንድ አደገኛ ቅጣት የሚጠብቃቸው መሆኑን፣ **4.**ቁሳቁሶችን አለማዋስና መከልከል ከሙናፊቆች ባህሪ አንዱ መሆኑን፣ **5.**አላህን (ﷻ) የካዱና ሞቶ መነሳት የለም ለሚሉ ካሃዲዎች የተሰጠው ከፍተኛ ዛቻ፣ በሰላት የሚዘናጉና ጊዜዋን የማይጠብቁ መጥፎ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው እንማራለን ።

[5] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ።

[6] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። **1.**አላህ (ﷻ) ለመልክተኛው ሙሐመድ (ﷺ) የሰጠው ማዕረግና ክብር፣ **2.**በአምልኮ በተለይም በሰላትና በእርድ ዙሪያ ለአላህ (ﷻ) ሊኖር የሚገባ ፍፁምነት፣ **3.**በግፈኞች ላይ ዱዓ ማድረግ ተገቢ መሆኑን፤ **4.**ነቢዩን መጥላት ለከፋ ችግር እንደሚያጋልጥ ሁሉ እሳቸዉን መውደድም ለመልካም እድል እንደሚያበቃ፤ **5.**ዱዓቶችን የሚጠሉና በመጥፎ የሚያስቡ ሁሉ መጨረሻቸው እንደማያምር፤ ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) የጠላ ሁሉ ቆራጣ መሆኑን እንማራለን ።

[7] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ። ሱረቱል ካፊሩን ከሱረቱ-ልማኡን በኋላና ከሱረተል ፊል በፊት በ18ኛ ተራቁጥር ላይ በመካ የወረደ ሱራ ነው። ይህ ሱራ ሱረቱ አስ-ሳፊረህ ሱረቱ -ኢኽላስ ሱረቱ አል-ዒባዳህ ሱረቱ አል-ሙቀሽቂሻህ ሱረቱ አዲንም ትባላለች ።
አንቀጾቿ በሁሉም አሊሞች ዘንድ ስስት ናቸው ።
**መግቢያ፡-** አላህ (ﷻ) በዚህ ሱራ ውስጥ ካፊሮች ነቢዩ መሐመድ (ﷺ) ጋር ያደርጉት የነበረውን እውነታዊ ድርድር ተስፋ እንዲቆርጡና መቼውንም ቢሆን ወደ እነሡ እምነት እንደማይገቡ ለአንድ አፍታም ቢሆን ከእነሱ ጋር እንደማይስማሙ በግልፅ ያውጃል።

[8] ሱራው የወረደበት ምክንያት፡-
የተወሰኑ-አልአስወድ ኢብኑ አብዱል ሙጠለብ፤ ወሊድ ብን ሙጊራህ፤ኡመየት ብንኸለፍ አል-ዓሲ-ብን ዋኢል-ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጋር በጦዋፍ ላይ ተገናኝተው ገንዘብ ከፈለክ እንሰብስብልህ ሴት ከፈለክ የፈለካትን ምረጥና እንዳርህ ስልጣን ከፈለክ እናንግስህ ብቻ አምላካችንን ተውልን እንስማማ በዚህ ካልተስማማህ ደግሞ አንድ ዓመት ያንተን ጌታ በሌላ ዓመት ደግሞ የእኛን ጌታ አብረን እንገዛ በማለት ለድርድር ሲቀርቡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጌታዬ የሚለኝን እጠባበቃለሁ በማለታቸው ነው። ጦበሪ፤ ዋሂዲ፤ እና ሱዩጢ ።

[9] ይህ አባባል ለእነዚያ (እነዚያ የጌታህ ቃል የተረጋገጠባቸው ታምራት ሁሉ ብትመጣላቸውም አሳማሚን ቅጣት እስከሚያዩ ድረስ አያምኑም ። የተባሉትንና ለተወሰኑት የከሃዲ ቡድኖች ካልሆነ በስተቀር ወይም ማንኛዉም ከሃዲ ከመስለሙ በፊት ተብሎ መረዳት ነው ያለበት ።

[10] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ። **1.**ኢማን ማለት በጣዖት ያላመነ ከሃዲ ማለት በጣዖት አምኖ በአላህ (ﷻ) የካደ መሆኑን በማስተማር ቀደርን ማስተማር ፣ **2.**አላህ (ﷻ) ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የካሃዲዎችን አስተሳሰብ እንዳይቀበሉ የወሰደው ሃላፊነት ፣ **3.**በኩፍር ሰዎችና በኢማን ሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባው ወሳኝ ሐሳብ በእምነት ጉዳይ ላይ ለምንም ተብሎ በሺርክ ላይ መደራደር እንደማይቻል፤ በእውነቱ ላይ መድረስ ካልተቻለ ሁሉም የየራሱን ይዞ ለጊዜው መቀጠል ለአፍታም ቢሆን ከኩፍር ጋር መደራደር እንደማይቻል እንማራለን።

[11] ምዕራፉ በመዲና ከወረዱት አጫጭር ምዕራፎች አንዱ ነው። ሱረቱ -ነስር- ከሱረቱ -ተውባ በኋላ በ114ኛ ተራ ቁጥር ላይ በመዲና የወረደ ሱራ ነው።

سُورَةُ الكَافِرُونَ
ترتيبها ١٠٩ — آياتها ٦

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

قُلۡ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡكَٰفِرُونَ ١ لَآ أَعۡبُدُ مَا تَعۡبُدُونَ ٢
وَلَآ أَنتُمۡ عَٰبِدُونَ مَآ أَعۡبُدُ ٣ وَلَآ أَنَا۠ عَابِدٞ مَّا عَبَدتُّمۡ ٤
وَلَآ أَنتُمۡ عَٰبِدُونَ مَآ أَعۡبُدُ ٥ لَكُمۡ دِينُكُمۡ وَلِيَ دِينِ ٦

سُورَةُ النَّصۡرِ
ترتيبها ١١٠ — آياتها ٣

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

إِذَا جَآءَ نَصۡرُ ٱللَّهِ وَٱلۡفَتۡحُ ١ وَرَأَيۡتَ ٱلنَّاسَ
يَدۡخُلُونَ فِي دِينِ ٱللَّهِ أَفۡوَاجٗا ٢ فَسَبِّحۡ بِحَمۡدِ رَبِّكَ
وَٱسۡتَغۡفِرۡهُۚ إِنَّهُۥ كَانَ تَوَّابَۢا ٣

سُورَةُ المَسَدِ
ترتيبها ١١١ — آياتها ٥

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

تَبَّتۡ يَدَآ أَبِي لَهَبٖ وَتَبَّ ١ مَآ أَغۡنَىٰ عَنۡهُ مَالُهُۥ وَمَا
كَسَبَ ٢ سَيَصۡلَىٰ نَارٗا ذَاتَ لَهَبٖ ٣ وَٱمۡرَأَتُهُۥ
حَمَّالَةَ ٱلۡحَطَبِ ٤ فِي جِيدِهَا حَبۡلٞ مِّن مَّسَدِۭ ٥

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም
አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 (ሙሐመድ[1] ሆይ!) የአላህ እርዳታና
(መካን) መክፈት በመጣ ጊዜ፤
2 ሰዎችም ጭፍሮች እየሆኑ ወደ አላህ
ሃይማ ት ውስጥ ሲገቡ ባየህ ጊዜ፤
3 ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው።
ምህረትንም ለምነው፤ እርሱ ጸጸትን በጣም
ተቀባይ ነውና።[2]

## 111 ኛው ምዕራፍ የመንቀልቀል ምዕራፍ[3] (ሱረቱ አል-መሰድ) ነው:: አንቀጾቹ 5 ናቸው::

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም
አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

1 የአቡ[4] ለሀብ ሁለት እጆች[5] ከሰሩ/

---

ይህ ሱራ ሱራህ ኢዛጃአ ነስሩላህ፣ ሱራህ አል-ፈትህ፣ ሱራህ አት-ተውዲዕ፣ በመባልም ይታወቃል። ይዘቱን በተመለከተ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)) የአላህ (ﷻ) ድል ሲመጣና ሰዎች ወደ ኢስላም በቡድን በቡድን እየሆኑ ሲገቡ ካዩ አላህን (ﷻ) ከማጥራት ጋር እንዲያመሰግኑትና ለራሳቸውም ሆነ ለአማኞች ከአላህ (ﷻ) ምህረትን እንዲለምኑ ሱራው ያስተምራል :: ብዙ የዐረብ ህዝቦች ኢስላምን ለመቀበል የመካን በድል መከፈት በጉጉት ይጠባበቁ ነበር:: መሐመድ በሕዝቦቹ ላይ ድልን ከተቀዳጀ እውነተኛ የአላህ ነቢይ ነው ይሉም ነበር :: አላህ (ﷻ) ሙስሊሞችን ለድል አብቅቷቸው መካን ሲከፍቱ ሰዎች በነቂስ ኢስላምን ተቀበሉ:: እናም ሁለት ዓመት ባልሞላጊዜ ዉስጥ ዐረቢያ
በኢስላም ስር አደረች::

1 ይህ ሱራ የወረደበት ምክንያት:-ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ከሁነይን ዘመቻ ሲመለሱ ነው :: (ዋሂዲና ሱዩጢ ::) .ይህ ሱራ ከወረደ በኋላ ነቢዩ (ﷺ) በሩኩዐቸዉም ሆነ በሱጁዳቸው ላይ:- ሱብሀነከላሁመ ረበና ወቢሀምዲከ አላሁመ ግፊርሊ የሚለዉን ዱዓ በብዛት ይሉ ነበር:: (ቡኻሪና ሙስሊም::)

2 ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው :: 1.የአላህን (ﷻ) ፀጋ ባገኘን ቁጥር ልናመሰግነውና ልናጠራው እንደሚገባን፣ 2.ድል ከአላህ (ﷻ) እንጂ በጉልበትም ሆነ በሀብት እንዳልሆነ፤
3.ኢስላም የተስፋፋው በውድ እንጂ በግድና በሐይል አለመሆኑን፣ 4.የሰው ልጅ የቱንም ያህል ትልቅ/ወንጀለኛ ቢሆን ከአላህ (ﷻ) ምህረትን መጠየቅ እንደሚገባውና ከአላህ (ﷻ) ምህረት ተስፋ መቁረጥ እንደሌለበት፤
5.በሙስሊሙ ዘንድ መሪ የሆነ ሰው ተከታዩን በየጊዜው መገምገም፤ 6.የዚህ ዲን ድል ቀጣይነት ያለውና ዓለምን እንደሚያጥለቀልቀው፤ 7.የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) እድሜ ማለቁን ማመላከቷን እንማራለን ::

3 ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው :: ሱረቱ-አቢ- ለሀብ /የአቡለሀብ ምዕራፍ/ ሱረቱ-ተበት እና ሱረቱ አል- መሰድ (የጭረቱ ምዕራፍ) ይባላል :: ሱረቱል መሰድ ከሱረቱል-ፋቲሃ በኋላና ከሱረቱ አትተክዊር በፊት በ6ኛ ተራ ቁጥር ላይ በመካ የወረደ ነው ::
ሱራው የአቡ ለሀብን መጥፋትና ንብረቱም ሆነ ዝናውን እንዲሁም ወገኑ ከአላህ ቅጣት የማያድነው መሆኑን ገልጾ በመጥፎ ስራ ተባብራ የነበረችው ኡሙ ጀሚል የምትባል አንዳይና ባለቤቱ የመጨረሻዋ እጣ ፈንታዋ ገሀነም እሳት ውስጥ መማገድ መሆኑን ያመለክታል ::

4 ይህ ሱራ የወረደበት ምክኒያት:- ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)) አንድ ቀን ወደ ሶፋ ጋራ ወጥተው እያንዳንዱን ብሔር ጠርተው ሲሰበሰቡላቸው (ጠላት ሊወራቹሁ ከዚህ ጋራ ጀርባ ነው ብየ ብነግራችሁ አታምኑኝምን? ብለው ሲጠይቋቸው እነሱም:- እንዴት አናምንህም? ዋሺተህ አታውቅ፣ ሲሏቸው:- እንግዲያውስ እኔ እናንተን ከጀሃነም ለማስፈራትና ለማስጠንቀቅ የተላኩኝ መልክተኛ ነኝ አሉ። አቡለሃብ:- ያጥፋህ፣ ለዚህ ነው የሰበሰብከን? በማለት ሲያዋርዳቸው እና ኡሙ ጀሚል የተባለችው ባለቤቱ ነቢዩን (ﷺ) ለመጉዳት ታደርጋቸው የነበሩትን አፀያፊ ተግባራት አስመልክቶ ነበር:: (ዋሂዲ እና ሱዩጢ::)

5 .እጆቹ ጠፉ ማለት፤- ራሱ ጠፋ ማለት ነው :: ምክንያቱም ዐረቦች የአንድን ሰው ክስረትና ዉድቀት ለማመልክት በዚህ መሰል አገላለጽ ይጠቀማሉ :: ይህ ሱራ በወረደበት ጊዜ አቡ ለሀብ በህይወት ነበር :: እርሱ በህይወት እያለ ስለ ፍጻሜው ተነገረው :: አንተ ወደፊት ካፊር ሆነህ ትሞታለህ የመንቀልቀል ባለቤት የሆነችንም እሳት ትገባለህ ሚስትህም ካሃዲ ስትሆን እንጨት በጀርበዋ የተሸከመች ሆና ትከተልሀለች ተባለ :: አቡ ለሀብ በዚህች የቁርአን ጥቅስ ብቻ ሙስሊሞችን ከመንገድ ላሳስት ቢል ይችል ነበር :: ሶሀቦች በተሰበሰቡበት ሄዶ እንዲህ በማለት:- ስሙ እናንተ ሰዎች ሆይ! እናንተ ነቢይ ነው ብላችሁ የምታምኑበት ሙሐመድ እኔ ወደፊት ካፊር ሆኜ እንደምሞት ተናግሯል:: እኔ ግን ከናንተ

ጠፉ/፡፡ እርሱም ከሰረ/ጠፋ/፡፡
2 ገንዘቡና ያም ያፈራው ሁሉ ምንም አልጠቀመውም፡፡[1]
3 የመንቀልቀል ባለቤት የሆነችን እሳት በእርግጥ ይገባል፡፡
4 ሚስቱም (ትገባለች) እንጨት ተሸካሚ ስትሆን፤
5 በአንገቷ ላይ /ዙረያ/ የጭረት ገመድ ያለባት ስትሆን፤(ትገባለች)[2]

## 112 ኛው የፍፁምነት ምዕራፍ [3] (ሱረቱ አል-ኢኽላስ) ነው፡፡አንቀጾቹ 4 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)፡፡

1 እርሱ አላህ አንድ ነው፡፡
2 አላህ (የሁሉ ነገር) መጠጊያ ነው ፡፡ [4]

سُورَةُ الإِخْلَاصِ
ترتيبها ١١٢ — آياتها ٤

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

قُلۡ هُوَ ٱللَّهُ أَحَدٌ ١ ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ ٢ لَمۡ يَلِدۡ
وَلَمۡ يُولَدۡ ٣ وَلَمۡ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدُۢ ٤

سُورَةُ الفَلَقِ
ترتيبها ١١٣ — آياتها ٥

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

قُلۡ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلۡفَلَقِ ١ مِن شَرِّ مَا خَلَقَ ٢ وَمِن
شَرِّ غَاسِقٍ إِذَا وَقَبَ ٣ وَمِن شَرِّ ٱلنَّفَّٰثَٰتِ فِي
ٱلۡعُقَدِ ٤ وَمِن شَرِّ حَاسِدٍ إِذَا حَسَدَ ٥

سُورَةُ النَّاسِ
ترتيبها ١١٤ — آياتها ٦

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

قُلۡ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلنَّاسِ ١ مَلِكِ ٱلنَّاسِ ٢ إِلَٰهِ
ٱلنَّاسِ ٣ مِن شَرِّ ٱلۡوَسۡوَاسِ ٱلۡخَنَّاسِ ٤ ٱلَّذِي
يُوَسۡوِسُ فِي صُدُورِ ٱلنَّاسِ ٥
مِنَ ٱلۡجِنَّةِ وَٱلنَّاسِ ٦

3 አልወለደም ፤ አልተወለደምም፡፡
4 ለእርሱ አንድም ብጤ[5] የለውም በል ፡፡[6]

---

ፊት «አሽሀዱ አንላ ኢላሀ ኢለላህ ወአሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉላህ» ብዬ ሙስሊምነቴን እመሰክራለሁ፤ በማለት ሳያምን በመናፍቅነት መናገር ይችል ነበር፡፡ አምላካችን አላህ ግን ይህ አስተሳሰብ እንኳ በአቡ-ለሀብ አዕምሮ ከቶውንም ሊመጣ እንደማይችል ስለሚያውቅ ተናገረ ፡፡ ይህ ክስተት ቁርአን የእያንዳንዱን ሰው የወደፊት እጣ ፈንታ ከሚያውቀው አምላክ ዘንድ የወረደ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

1 .ምን ጠቀመው ለማለትም ሊሆን ይችላል፡፡

2 ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ 1.አቡለሐብን በማጥፋትና ተንኮሉን መና በማስቀረት የአላህን (ﷻ) የበላይነት ማረጋገጥ፣ 2.የሰው ልጅ ገንዘቡም ሆነ ልጁ ከአላህ (ﷻ) ቁጣ ቅንጣት ያህል እንደማያድኑት፣ 3.አማኒያንን ማንገላታት ክልክል መሆኑን፣ 4.በኢስላም በዘር፤ በወገን መዳን አለመኖሩን ፡፡ የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አጐት የሆነው አቡለሐብ እሳት መግባቱን በግልፅ እንደሚያሳይ፤ 5.ቁርአን የአላህ (ﷻ) ቃል መሆኑንና የትንቢቱን ታዐማኒነት በግልፅ ማየት፤ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የአጎታቸዉን የአቡ ለሀብንና የባለቤቱን አለመስለም በሙሉ አንደበት መናገራቸው ትክክለኛ ነቢይነታቸዉን በግልጽ እንደሚያመለክት፡፡

3 ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው፡፡ ሱረቱል- ኢኽላስ ከሱረቱ አን-ናስ በኋላና ከሱረቱ አን-ነጅም በፊት በ22ኛ በመካ የወረደ ነው፡፡ ሱረቱ አስ-ሰመድ ሱረቱ አት-ተፍሪድ፤ ሱረቱ አት-ጅሪድ፤ ሱረተ አን-ነጃህ፤ ሱረቱ አል-ዊላያህ ፤ ሱረቱ አን-ኒስባህ፤ ሱረቱ አል-ማዕሪፋህ፣ ሱረቱ አል-ጀማል፣ ሱረቱ አል-መህዶር፣ ሱረቱ አል-ማዓዳህ፣ ሱረቱ አል-ሙነፊረህ፣ ሱረቱ አል-መዘኪራህ፣ ሱረቱ አን-ኑር፣ ሱረቱ አል-አማን፣ ሱረቱ አሽ-ሻፊያ፣ ሱረቱ ቁልሁወላሁ አሐድ፤ ሱረቱ አት-ተውሂድ፣ ሱረቱ አል-አሳስ፣ ሱረቱ አል-ሙቀሽቂሻህ በመባልም ይታወቃል፡፡ የመካ ሰዎች ሙሐመድ ሆይ! የጌታህን ዘር ንገረኝ በማለት ሲጠይቋቸው ነው የወረደው፡፡

4 ሶመድ ማለት ሁሉን ማድረግ ስለሚችል ለሁሉ ነገር የሚፈለግ ማለት ሲሆን ኢብኑ አባስ ‹‹ሶመድ ማላት የአለቆቹ ሁሉ አለቃ የታላቆች ሁሉ ታላቅ የታጋሾች ሁሉ ታጋሽ፤ የሀብታሞች ሁሉ ሀብታም፤ የአሸናፊዎች ሁሉ አሸናፊ የአዋቂዎች ሁሉ አዋቂ፤ የጥበበዩች ሁሉ የበላይ ጥበበኛ ማለት ነው›› ብለዋል ይህ ደግሞ ለአንድ አላህ እንጂ ለማንም አይሟላም ፡፡

.ይህ አንቀፅ ለሶስቱም ቡድኖች ማለትም፡- መላዒኮች የአላህ (ﷻ) ሴት ልጆች ናቸው ፡፡ የሚሉትን የዐረብ አጋሪዎች፤ ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው ለሚሉት አይሁድና መሲሕ የአላህ ልጅ ነው ለሚሉት ነሷራዎች በአንድ መልስ ይሰጣል ፡፡

5 ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ይህን ሱራ በሱብሂ፤ በመግሪብ፤ በጠዋፍና በዊትር የሱና ሰላቶች ላይ አዘውትረው ያነቡት እንደነበር በብዙ ሀዲስ ተዘግቧል፡፡ ሙስሊሞችም ይህን አይነት ሱና በማስታወስ ሊተገብሩት ይገባል ፡፡

6 ይህ ሱራ- የወረደበትን ምክንያት በተመለከተ ሁለት ዘገባ የተዘገበ ሲሆን፡- 1-የተወሰኑ ሙሽሪኮች ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) መጥተው (ሙሐመድ ሆይ! አላህ መላዒካን ከብርሃን፤ አደምን ከጭቃ፤ ኢብሊስን ከእሳት፤ ሰማይን ከጭስ፤ እና ምድርን ከዉሀ አረፋት ፈጠረ፡፡ እስቲ ጌታህን ከምን እንደተፈጠረ ግለጥልን? ከምንድን ነው የተሰራው? ከወርቅ ወይስ ከብር ወይስ ከንሀስ? ይበላል ወይስ ይጠጣልን? ብለው በመጠየቃቸው ነው ይህ ሱራ የወረደው ፡፡ (ዋሂዲ፤ ሱዩጢ፤ አህመድ ና ቲርሚዚ፡፡) 2-ሌሎች እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ ዉስን አይሁዶች በከዕብ ቢን አሽረፍ መሪነት ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)) መጥተው ይህ የምናየው ነገር

## 113 ኛው ምዕራፍ ፡-የተፈልቃቂው ምዕራፍ [1](ሱረቱ አል-ፈለቅ) ነው፡፡አንቀጾቹ ፭ ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

(1) በተፈልቃቂው ጎህ/ /በአልፈለቅ[2]/ ጌታ፤
(2) ከፈጠረው ፍጡር ሁሉ ክፋት።
(3) ከሌሊትም ክፋት፣ በጨለመ ጊዜ፤
(4) በተቋጠሩ (ክሮች) ላይ ተፊዎች ከሆኑት (ደጋሚ)[3] ሴቶች ክፋት፤[4]
(5) ከምቀኛም ክፋት፣ በተመቀኘ ጊዜ እጠበቃለሁ በል።

---

ሁሉ የአላህ (عز وجل) ፍጡር ነው፡፡ አላህን (عز وجل) ራሱን ማን ፈጠረው? እስቲ ንገረን በማለት ሲጠይቋቸው ነቢዩ በጣም ተቆጥተው ሳሉ መላኩ ጂብሪል መጥቶ አረጋጋቸውና ለጥያቄያቸው መልስም ይህችን ሱራ አወረደላቸው ብለዋል፡፡ ይህ አባባል ግን ሱራው በመዲና መውረዱን ነው የሚያሳየው ፡፡
ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡
1. አላህን (عز وجل) በስሞቹና በባህሪያቱ ማወቅ እንደሚገባ ፣
2. የአላህን (عز وجل) አንድነትና የነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) ነቢይነት ማረጋገጥ ፣
3. ለፈጣሪ ልጅ ፤ሚስት ፤እሱን መሰል ቢጤ አለው ማለት መሠረተ ቢስ አባባል መሆኑን ፣
4. አላህ (عز وجل) ብቻውን ሊመለክ የሚገባው ብቸኛ አምላክ መሆኑን፤ በአጠቃላይ የአላህን አንድነትና የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ ይገባል፡፡ አላህ (عز وجل) ብቻውን ሊመለክ የሚገባው ሥልጣኑን መጋፋት የሚችል ሌላ ተጋሪ የሌለው ብቸኛ አምላክ ነው፡፡

[1] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው፡፡ ይህ ሱራ እና- 114ኛው ሱራ በአንድ ሱረቱል ሙዓዊዘተይን ይባላሉ፡፡ ሱረቱል ሙዓዊዘተይን ከሱረቱል ፊል በኋላ በ20ኛ እና በ21ኛ ሁነው በመካ በአንድ ግዜ የወረዱ ሱራዎች ናቸው ፡፡

[2] .ንጋት፣ ፍጡራን ፡፡

[3] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡
1. የሰው ልጅ ሊከላከለው ከማይችለው ነገር ሁሉ በአላህ (عز وجل) ብቻ መጠበቅ ግዴታ መሆኑን፣
2. ለድግምት ወይም ለሌላ ተንኮል በገመዶችም ሆነ በክር መትፋት ክልክል መሆኑን፣
3. ምቀኝነት የተከለከለ አደገኛ የማህበራዊ በሽታ መሆኑን፤
4. ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ተደግሞባቸው እንደነበር፤
5. ሩቅያ በሚደረግበትም ጊዜ መትፋቱ ምንም የሌለበት መሆኑን፣ እናታችን ዓኢሻ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቱፍታ ሲያደርጉ ይተፉ ነበር በማለት ስለዘገቡ እንደሚፈቀድ፤

[4] ሴቶችን ብቻ የማውሳቱ ሚስጥር በብዛት ይህን አይነት ተግባር የሚሰሩት እነሱ በመሆናቸው ነው ፡፡

## 114 ኛው ምዕራፍ፡-የሰዎች ምዕራፍ (ሱረቱ አን-ናስ) [5]፡፡ ነው፡፡አንቀጾቹ 6 ናቸው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

(1) በሰዎች ሁሉ ፈጣሪ (ጌታ) እጠበቃለሁ፡፡[6]
(2) የሰዎች ሁሉ ንጉስ በሆነው፡፤
(3) የሰዎች ሁሉ አምላክ[7] በሆነው ፡፡-
(4) ብቅ እልም ባይ ከሆነው ጎትጓች (ሰይጣን) ክፋት፡፡[8]
(5) ከዚያ በሰዎች ልቦች ውስጥ የሚጎተጉት ከሆነው፤
(6) ከጋኔ□ችም ሆነ ከሰዎችም ሰይጣናት እጠበቃለሁ በል[9]፡፡[10]

---

[5] ምዕራፉ በመካ ከወረዱት ምዕራፎች አንዱ ነው ፡፡ ሱረቱ አል-ናስ ከሱረቱል ፈለቅ በኋላ በ21ኛ ተራ ላይ ነው የወረደው ፡፡
በዚህ ሱራ ውስጥ አላህ (عز وجل) ነቢዩ መሐመድን (ﷺ) ከተለያዩ ችግሮች ለመጠበቅና ለመከላከል በአላህ (عز وجل) እንዲጠበቁ፣ ወደ አላህ (عز وجل) እንዲጠጉ ከማዘዙም በላይ ሰይጣን ከላይ ተደብቆ ሰዎችን በስሜታቸው በኩል እየገባ ሊጎተጉታቸው እንደሚችል ያስተምራል፡፡

[6] ረብ፡- የፉጡራንን ጉዳዩች አስተናባሪ፤የበላይ ገዥና ተቆጣጣሪ ማለት ነው ፡፡

[7] ኢላህ፡- በትክክል ሊመለክ የሚገባው ብቸኛ አምላክ ማለት ነው፡፡

[8] እነዚህ ሁለቱ የሰይጣን ባህሪዎች ላይላዩን ሲመለከቷቸው ይቃረናሉ፡፡ ብቅ እልም የሚለው ባህሪው የሚጠፋ መሆኑን ሲያመለክት ጎትጓች የሚለው ግን የማይለቅ፣ ጧት ማታ የሚወተዉት ማለትን ያመለክታል ፡፡ ስለዚህ ሁለቱም በተለያዩ ሰዐታትና በተለያዩ ግለሰቦች ላይ የሚከሰቱ ናቸው ብሎ ማስማማት ይቻላል ፡፡ ሰዎች ሲዘናጉ ሰይጣን ያጠቃቸዋል፣ ይወሰውሳቸዋል ፡፡ አላህን ሲያስታውሱ ደግሞ ከእነርሱ ይሸሻል ፡፡ ኢብኑ አባስ ማኛውም ሰው ሲወለድ ጎትጓተ ሰይጣን አብሮት አለ ፡፡ አላህን ሲያስታውስ ይደበቃል፡፡ ሲዘናጋ ይጎተጉተዋል ብለዋል ፡፡

[9] .እነዚህ ሶስቱ ተከታታይ የመጨረሻ ሱራዎች ነቢዩ ሙሐመድ ሊተኙ ሲሉ በመዳፋቸው ላይ በመቅራት ትንሽ ትንሽ በምራቃቸው በማርጠብ ፊታቸዉንና የደረሱበትን አካላቸዉን ያብሱ እንደነበር በቡኻሪ ተዘግቧል፡፡ እንደዚሁም ከአምስቱ የፈርድ ሶላቶች በኋላ ያነቧቸው እንደነበር፣ (አቡዳዉድና ነሳኢ ዘግበዋል፡፡)

[10] ከሱራው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፡፡
1. እያንዳንዱ ሰው መጥፎ ድርጊት እንዲፈጽም ከሚያደርገው ሰይጣንም ሆነ አሳሳች ሰው መጠበቅ አለበት ፡፡ ከዚህ መሰሉ ችግር መጠበቅ የሚቻለውም በአንድ አላህ (عز وجل) ብቻ ነው፡፡ መወስወስ /ማሳሳት/ በሰይጣን ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በእርጉም ሰዎችም ሊፈፀም ይችላል፡፡ ሰይጣንም ሆነ ተንኮለኛ ሰው ሰውን ሊያሳስቱ የሚችሉት ከአላህ (عز وجل) በተዘናጋበት ጊዜ ነው፡፡
2. የአላህ (عز وجل)/ ብቸኛ አምላክነት ለማወቅ ፈጣሪነቱንና ንጉስነቱን ማወቅ፣ ፈጣሪነቱም ቅንጣት ታህል ሳይጠራጠሩ ማረጋገጥ እንደሚገባና ሰይጣን የሚባል እርኩስ መንፈስ መኖሩን ማወቅ እንዳለብን እንማራለን፡፡

# ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ ጥያቄዎች

**1** **ሙስሊም እምነቱን ከየት ነው የሚወስደው ?** ከአላህ (ﷻ) ቁርአንና ከዚያ በቁርአን ከመለኮታዊ ራዕይ እንጂ- “ከስሜት አይናገርም ” ﴿وَمَا يَنطِقُ عَنِ ٱلۡهَوَىٰٓ ٣ إِنۡ هُوَ إِلَّا وَحۡيٞ يُوحَىٰ﴾ 53:3 ከተባሉት- ከታላቁ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ትክክለኛ ሐዲስ ነው:: እነዚህንም የእምነት ምንጮች ሱሃቦችና ቀደምት ዐሊሞች በተረዱበት መንገድ ይረዳል::

**2** **በአንድ ነገር ላይ የአቋም ልዩነት ሲኖረንና ሣንግባባ ስንቀር ወደ ምን እንመለሳለን?**
ወደ ትክክለኛው የሸሪዐ መረጃ እንመለሳለን:: በጉዳያችንም የመጨረሻና የበላይ ወሳኝ የሚሆነው የአላህ (ﷺ) ቁርአንና የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሱና ብቻ ናቸው:: አላህ (ﷺ) እንዲህ አለ (በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ከሆናችሁ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልዕክተኛው መልሱት::)
ነቢዩ (ﷺ) ማሊክ በሞጦእ በዘገቡት ሐዲስ (አጥብቃችሁ ከያዛችኋቸው የማትሳሳቱባቸውን ሁለት ነገሮች በመሀከለችሁ ትቻለሁ :: እነሱም የአላህ /ቁርአን/ እና የነብዩ ሱና ናቸው::) ብለዋል::

**3** **ከእሳት የሚድነው ቡድን የትኛው ቡድን ነው ?** ነቢዩ (ﷺ) አህመድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ :- «ህዝቦቼ ሰባ ሶሰት ቡድን ሁነው ይከፈላሉ :: አንዷ ብቻ ስትቀር ሁሉም የእሳት ናቸው” ሲሉ:- «እነሱ እነማን ናቸው?” ተብለው ሲጠየቁ-እኔና ባልደረቦቼ አሁን ያለንበትን መንገድ የተከተሉ ቡድኖች ብቻ ናቸው» ብለዋል ::
ስለዚህ እውነት ማለት ነቢዩና ባልደረቦቻቸው የነበሩበትን ፈለግ መከተል ብቻ ነው:: ከእሳት ነፃነት የምትፈልግና ስራህ ተቀባይነት እንዲኖረዉ ካሰብክ የሰለፎችን መንገድ ብቻ ተከተል እንጂ በዲን ዉስጥ አዲስ ነገርን አትጨምር ::

**4** **መልካም ተግባራትን በአላህ ዘንድ ተቀባይ የሚያደርጉት መስፈርቶች ስንት ናቸው? ተቀባይነት እንዲኖረውየሚከተሉት ያስፈልጋሉ::** 1) በአላህ (عز وجل) መኖርና በአንድነቱ ማመን ሲሆን፤ በአላህ (عز وجل) የሚያጋራ ሰው ስራዉ መቸውም ቢሆን ተቀባይነት የለዉም:: 2) ፍፁምነት ሲሆን እሱም ስራን ለአላህ (عز وجل) ፊት ብቻ አስቦ መስራት ማለት ነው:: 3) በተግባሩ ሂደት የነቢዩ (ﷺ) አሰራርን መከተል ሲሆን፤ ይህም ማለት አላህ በደነገገው ድንጋጌ መሰረት አላህን ማምለክና የአምልኮ ተግባራቱን ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በተገበሩትና ባስተማሩት መሰረት መፈፀም ነው :: ስራ ተቀባይነት ሊኖረዉ ከነዚህ መስፈርቶች አንዱን እንኳን ቢያጣ ተቀባይነት የለዉም :: አላህ (عز وجل) እንዲህ አለ (ወደ ሰሩት ስራም እንገባለን:: ከዚያም የተበተነ ትቢያ እናደርገዋለን::)

**5** **የሃይማኖት ደረጃዎች ስንት ናቸው?** የሐይማኖት ደረጃዎች ሶስት ናቸው :: እነሱም ኢስላም : ኢማንና ኢህሳን ይባላሉ ::

**6** **ኢስላም ምንድን ነው? ማዕዘናቱስ ስንት ናቸው?** ኢስላም ማለት አላህን (عز وجل) በብቸኝነት መታዘዝና ለሱ ብቻ መገዛት፤ በመመሪያው መመራት፤ እንዲሁም ከባዕድ አምልኮና ከጣዖት አምላኪዎች ነፃ መሆን ነው:: ማዕዘናቱን በተመለከተ ነቢዩ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ:- “ኢስላም በአምስት ማዕዘናት ላይ ነው የተገነባው:: እነሱም ከአላህ (ﷻ) በስተቀር በእዉነት የሚመለክ ማንም የለም፤ ሙሐመድ (ﷺ) የአላህ (عز وجل) መልዕክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር፤ ሶላትን ደንቡን ጠብቆ መስገድ፤ ዘካን መስጠት፤ የአላህን ቤት መጎብኘት/ሀጅ ማድረግ/ ና የረመዷንን ወር መፆም ናቸው” ብለዋል ::

**7** **ኢማን ምን ማለት ነው? ማዕዘናቱስ ስንት ናቸው?** ኢማን ማለት በልብ ማመን፤ በምላስ መናገርና በአካል መተግበር ነው:: እሱም በመልካም ስራ ምክኒያት ይጨምራል:: በወንጀልም ይቀንሳል:: አላህ (ﷻ):- ከእምነታቸው ላይ እምነትን ሊጨምር ያወረደ ነው::” ማለቱ እምነት/ኢማን የመጨመርና የመቀነስ ባህሪ ያለው መሆኑን ያሳያል :: ነቢዩም (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ:- “ኢማን ከሰባ ሶስት እስከ ሰባ ዘጠኝ የሚሆኑ ቅርንጫፎች አሉት :: ግዙፉና ዋናው ላኢላሀ ኢለሏህ ማለት ሲሆን አነስተኛው ደግሞ ከመንገድ ላይ ሰዎችን የሚያስቸግርን ነገር ማንሳት ነው:: ሀያእ/ አይነ አፋርነት ከኢማን ቅርንጫፎች አንዱ ነው ::” በማለት የኢማንን ዘርፌ ብዙነት ጠቁመዋል::አላህም (መልካም ሥራዎች ሀጢአቶችን ያስወግዳሉና) ብሏል::

ማንም ሰው በራሱ ላይ መልካም በሰራ ጊዜ ሲነቃቃ በወንጀል ሲሆንም ሲዳከምና ሲሳነፍ በግልጽ ይመለከታል፡፡

የኢማን ማዕዘናቱ ስድስት ናቸው ። እነሱም ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ፡- "በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጻሕፍቱ በመልዕክተኞቹ ፣ በመጨረሻው ቀንና በቀደር ክፍም ሆነ ደጉ ከአላህ መሆኑን ማመን ናቸው" ብለዋል፡፡

8 የላኢላሀ ኢለሏህ ትርጉም ምንድን ነው? አምልኮ ለሱ ብቻ መሆኑን ማፅደቅና የአምላክነት ስልጣንን ከአላህ ሌላ ከሆነ አካል ሁሉ ማንሳት /መግፈፍ/ ነው፡፡

9 አላህ (ﷻ) ከኛ ጋር ነውን ? አዎ ! አላህ (ﷻ) ከኛ ጋር ነው፡፡ ሆኖም ከኛ ጋር ነው ሲባል በዛቱ /በአካሉ/ ማለት ሳይሆን፤ በእውቀቱ፤ በመስማቱ፤ በማየቱ፤ በመጠበቁ፤ እውቀቱ በማካበቡ፤ በችሎታውና በፍላጎቱ ከኛ ጋር ነው ማለት ነው፡፡ ዛቱ ግን የፍጡሮችን ዛት ፈፅሞ አይደባለቅም፡፡ የትኛዉም ፍጡር ቢሆን በሱ ላይ እውቀቱ አያካብብም፡፡ ስለዚህ በዛቱ ከእኛ ጋር ነው አይባልም፡፡

10 አላህ (ﷻ) በአይን ይታያልን? ወደ ቂብላ የሚሰግዱ ሙስሊሞች ሁሉ አላህ በዚህ ዐለም እንደማይታይና አማኞች በመህሸር ቀንና በጀነት እንደሚያዩት ተስማምተዋል፡፡ አላህ በቁርአን (ፊቶች በዚያ ቀን አብሪዎች፡ ወደ ጌታቸው ተመልካቾች ናቸው) ብሏል፡፡ 75:22-23

11 የአላህን ስሞችና ባህሪያት ማወቁ ጥቅሙ ምንድን ነው ? አላህ የሰው ልጅ በአንደኛ ደረጃ እንዲያውቀው ግዴታ ያደረገው ነገር እሱን ማወቅን ነው፡፡ ምክኒያቱም ሰዎች ካወቁት በትክክል ይታዘዙታል፡፡ አላህ (ﷻ) እንዲህ በቁርአን ላይ (ከአላህ በስተቀር የእውነት አምላክ አለመኖሩን እወቅ ለወንልህም ምህረትን ለምን) አለ፡፡ 47:190 አላህን (ﷻ) በርህሩህነቱ ማውሳት በሱ ራህመት ላይ ከፍተኛ ተስፋ እንዲኖረን ያደርገናል፡፡ በበቀለኝነቱ ማውሳቱም ከሱ ቅጣትና ቁጣ ፍርሃት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ፀጋን በመቸር ብቸኛ መሆኑን ማውሳትም እንድናመሰግነዉ ያደርገናል፡፡ በአጠቃላይ በአላህ (ﷻ) ስሞችና ባህሪያት የመገዛቱ ጥቅም እሷን ማወቅ፤ መልዕክቷን መረዳትና በሷም መስራት ነው፡፡ ከአላህ (ﷻ) ስሞችና ባህሪያት መካከል የሰው ልጅ የሚገለፅበትና የሚወደስበት አለ፡፡ እሱም ዕውቀት፤ እዝነትና ፍትህን ይመስል ነው፡፡ ከመካከሉም ሰዉ በእነሱ ከተገለፀበት የሚወገዝበት አለ፡፡ እሱም አምላክነትንና ኩራትን ይመስል ነው፡፡ የሰው ልጅ የሚገለፅበትና የሚመስገንበት ብሎም የሚታዘዝበት አላህ (ﷻ) ግን የማይገለፅበት ባህሪ አለ፡፡ እሱም አገልጋይነት፤ ድህነት፤ ከጃይነት፤ የበታችነት፤ ልመናና የመሣሰሉትን ነው ። አላህ (ﷻ) ዘንድ በጣም የተወደደ ማለት አላህ (ﷻ) የሚወደውን ባህሪ የተላበሰ ሰው ነው ። የተጠላ ማለት ደግሞ እሱ በሚጠላቸው ባህሪያት የተገለፀ ነው፡፡

12 የአላህ ስሞች ምን ምን ናቸው? አላህ (ﷻ) በቁርአን (ለአላህ መልካም ስሞች አሉት፡ ፡ እናም (ስትጸልዩ) በነርሱ ጥሩት አለ፡፡ 7:180 ነቢዩም ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «ለአላህ ዘጠና ዘጠኝ ለመቶ አንድ የጎደለው ስሞች አሉት፡፡ እነሱን በቃሉ የሐፈዛቸውና የተገበራቸው ጀነት ይገባል» ብለዋል፡፡

እነሱን በቃሉ የሐፈዛቸው የሚለው

አንደኛ:- ቃላቸውንና ቁጥራቸውን መሀፈዝ፤

ሁለተኛ:- ትርጉማቸውንና መልዕክታቸውን ማወቅ በሱም ማመን ነው ። ለምሳሌ (አልሐኪሙ) ጥበበኛው ስንል ሁለንተናዊ ጉዳዩቻችንን ለአላህ መስጠት አለብን ማለት ነው ። ምክንያቱም ሁሉም ነገር የሚሆነው በጥበቡ ብቻ ነውና ።

(አልቅዱስ) ንፁሁ ስንል አላህ ከሁሉም ነውርና ጉድለት የፀዳ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በቀልባችን እናስታውሳለን ።

ሶስተኛ:- አላህን በነዚህ ስሞች መለመን ነው ። እሱም ሁለት ክፍል አለው፡፡

ሀ/ የማሞገስና የአምልኮ ልመና ሲሆን:

ለ/ ጥያቄ አዘል ልመና ነው፡፡ ቁርአንንና ትክክለኛ ሐዲሶችን የተከታከለ ሰው ሁሉንም ማግኘት ይችላል፡፡ እነርሱም፡-

| ስም | | መልዕክቱ |
|---|---|---|
| አላህ (አምላክ:) | الله | በፍጡሩ ዘንድ በብቸኝነት ሊመለክ፤ ለሰገድለት፤ ሊተናነሱለት፤ ዝቅ ሊሉለት የሚገባው አምላክ ማለት ነው። |
| አረህማን | الرحمن | (በጣም አዛኝ) እዝነቱ ሰፊና ሁሉን ፍጡር የሚያዳርስ መሆኑን የሚያመለክት ስም ነው።ይ ህ ስም ለአላህ ብቻ እንጂ ማንም የማይጠራበት ብቸኛው ስሙ ነው። |
| አርረሂም | الرحيم | (በጣም ሩህሩህ) በጣም ሩህሩህ):አማኞችን በዚህ አለም ወደ ኢስላም በመም ራት በዚያኛው ዐለም ም ጀነትን በመስጠት የሚያዝንላቸው ማለት ነው፡ |
| -አል-ዐፉው | العفو | ይቅር ባይ፤የሚያስቀጣ ወንጀል የሰራን ሰው ቅጣቱን ትቶ ጭራሽ የሚሽርለት ። |
| አል-ገፉሩ | الغفور | መሐሪ ፤ወንጀሎችን የሚደብቅ፤ በአጥፊው ላይ የማይቆጣ፤ በህዝብ ፊት የማያዋርድ ፤ |
| አል-ገፋር | الغفار | ምህረት ለሚጠይቁ ሁሉ ምህረቱ ሰፊ፤የሰፊ ምህረት ባለቤት |
| አል-ረኡፉ | الرؤوف | በዚህ ዐለም ለሁሉ አዛኝ፤ በአኺራ ደግሞ ለአማኞች ብቻ አዛኝ፤ |
| አል-ሐሊሙ | الحليم | (በጣም ታጋሽ፤ ለመቅጣት የማይቸኩል ፤ለሚጠይቁት ይቅር ባይ፤ |
| አል-ተዋቡ | التواب | ንስሃን ተቀባይ፤ ባሮቹን ወደ እሱ እንዲመለሱ የሚያደርግና ይቅርታቸዉን የሚቀበል፤ |
| አል-ሲቲሩ | الستير | ሸፋኝ፤የባሮቹን ነዉር የሚደበቅ ፤የራሳቸው ገመና እንዲደበቁ የሌሎችንም ነዉር እንዲደብቁ የሚወድ ማለት ነው፤ |
| አል-ገኒዩ | الغني | ሀብታሙ፤ፍጡሮች በጠቅላላ የሚከጅሉት እሱ ግን ከማንም ምንም የማይከጅል ፤ |
| አል-ከሪሙ | الكريم | ቸሩታው ሰፊ፤ የፈለገዉን ለፈለገው በፈለገው ጊዜ የሚሰጥ፤ |
| አል-አክረሙ | الأكرم | በጣምቸሩ፤ በቸሮታው ወደር የሌለው። |
| አል-ወሃቡ | الوهاب | ሰጪ/ሲሳይ ለጋሽ/፤ ስጦታው ብዙ ፤ ለስጦታው ክፍያ የማየጠይቅ፤ ሳይጠየቅ የሚሰጥ፡ |
| አል-ጀዋዱ | الجواد | ቸር፤ ቸሮታው ሰፊ፤ በተለይ ለአማኞች በሰፊ ሰጪ፤ |
| አል-ወዱዱ | الودود | አማኞቹ የሚወዱት ፤እንዲወዱትም ምህረቱን የሚቸራቸው፡ ተወዳጅ/ለወዳጆቹ ወዳድ/ሰው እንዲወዳቸው የሚያደርግ፤ |
| አል-ሙዕጢ | المعطي | ሰጪ፤ለፈለገው ሰው በፈለገው መልኩ በፈለገበት ሰዐት የሻዉን ያህል የሚሰጥ፤ |
| አል-ዋሲዑ | الواسع | ቸሮታው ሰፊ፤በሁለንተናው ሰፊ ማንም ስለ እሱ ቢናገር ባህሪዉን ተናግሮ የማይጨርሰው፤ ስልጣኑ ሰፊ፤ምህረተ ብዙ፤ |
| አል-ሙህሲኑ | المحسن | ለፍጡሩቹ በጎ ዋይ)፤ ዛቱ ፤ ባህሪያቱ፤ ስሞቹና ተግባራቱ መልካም የሆኑ፤ |
| አል-ራዚቁ | الرازق | መጋቢ፤ፍጡሮችን ሁሉ የሚመግብ፤አለምን ከመፍጠሩ በፊት የፍጡሮችን ሁሉ ርዝቅ የወሰነ፤ |
| አል-ረዛቁ | الرزاق | ሲበዛ ለጋስ፤ ሳይጠየቁት የሚሰጥ ፤እያጠፉ እንኳን የሚመግብና የሚያስመች፤ |
| አል-ለጢፉ | اللطيف | ዉሰጥ አዋቂ ፤ምስጥሮችን ሁሉ የሚያውቅ፤ምንም ነገር የማይሰወረው፤ ባሮቹ ሁሉ ባላሰቡት መንገድ የሚመግባቸው፤ |
| አል-ኸቢሩ | الخبير | ዉስጠ አዋቂ፤ የነገራትን ሁሉ ዉስጠ ሚስጥሩን ሳይቀር የሚያውቅ፤ |
| አል-ፈታሁ | الفتاح | የሚከፍት /ድልን አጎናፃፊ፤ ከትሩፋት ካዝናው ለፈለጋቸው በፈለገው መጠን ና ሰዐት የሚሰጥ፤ |
| አል-ዐሊሙ | العليم | አዋቂ፤ የተደበቁንም ሆነ ይፋ የሆነዉን ፤ ያለፈዉም፤ የአሁኑንና መጪዉን፤አንድም ሳይሰወረው ሁሉንም የሚያውቅ፤ |
| አል-በሩ | البر | ደግ ሰሪ፤ ስጦታው ተቆጥሮ የማልቅ፤ቃሉን አክባሪ፤ባሪያዉን ጠባቂ፤ የባሪያዉን ተግባር ትኒሽም ብትሆን የማይንቅ፤ |

| | | |
|---|---|---|
| አል-ሐኪሙ | الْحَكِيْم | ጥበበኛ፤ ሁሉን ነገር በተስማሚው ቦታ የሚያስቀምጥ፤ በመስተናበሩ ላይ ቅንጣት ያህል እንከን የማይታይበት፤ |
| አል-ሐከሙ | الْحَكَم | በህዝቦች መካከል ፍትህ ሰጪ ፤ማንንም የማይበድል፤ |
| አል-ሻኪሩ | الشَّاكِر | አመስጋኝ፤ ታዛዥ ባሪያዉን የሚያመሰግን፤ የሚያሞግስ፤ ብታንስም ለተግባራችን ተገቢ ምንዳ ከፋይ፤ ለአመሰገኑት ባሪያዎች በዱንያ በመጨመር በአኺራ ምንዳቸዉን በማበባ የሚክስ፤ |
| አል-ሸኩሩ | الشَّكُوْر | ዉለታን መላሽ፤ በትኒሽ ተግባር ብዙ የሚሰጥ የሚመነዳ፤ |
| አል-ጀሚሉ | الْجَمِيْل | መልካሙ፤ የዛቱ ፤ የባህሪያቱ የስሞቹና የተግባሩ ዉበት ወደር የሌለው፤ |
| አል-መጂዱ | الْمَجِيْد | ለጋስ፤ ኩሩው ፤ ታላቁ፤ |
| አል-ወሊዩ | الْوَلِي | ወዳጅ፤ የባሮቹ ረዳት፤ የፍጡሮቹን ጉዳይ በብቸኝነት አስተናባሪ፤ |
| አል-ሐሚዱ | الْحَمِيْد | ምስጉኑ፤በባህሪያቱ፤ በስሞቹና በተግባራቱ ምስጉን ፤በችግርም ቀን ሆነ በደስታ የሚመሰገን፤ ሁልጊዜም መመስገን የሚገባው፤ |
| አል-መውላ | الْمَوْلَى | ወዳጅ/ረዳት/ንጉስ/ድጋፍ ሰጪ፤ |
| አል-ነሲሩ | النَّصِيْر | ድልን ሰጪ፤ የፈለገዉን አካለ በፈለገው ጊዜ በፈለገው መልኩ የሚረዳ፤ እሱ የረዳዉን ማንም አያሸንፈዉም ፤እሱ ያልረዳዉን ማንም የሚረዳው የለም፤ |
| አል-ሰሚዑ | السَّمِيْع | ሰሚ፤ ምስጥሮቹንም ይፋዎችን የሚያውቅ ቋንቋዎችን ሁሉ የሚሰማ፤ ድበቅነት የማያመልጠው፤ |
| አል-በሲሩ | الْبَصِيْر | ተመልካችነቱን ርቀት፤ የመጠን ማነስ የማይገድበው፤ ሁሉን የሚመለከት፤ |
| አል-ሸሂዱ | الشَّهِيْد | ፍጡሮችን ተከታታይ፤ ለራሱ አንድነትና ፍትሃዊነት በራሱ የመሰከረ፤ ለአማኞች ትክክለኛ እምነት የመሰከረ፤ ለነብያትም ሆነ ለመላይኮች የሚመሰክርላቸው)፤ |
| አል-ረቂቡ | الرَّقِيْب | የፍጡሮችን ተግባራት ተጠባባቂ፤ ስራቸዉን መዝጋቢ፤ |
| አል-ረፊቁ | الرَّفِيْق | በተግባሩ አዛኝ፤ፍጡሮችን እዝነት በተሞላበት የሚንከባከብ፤ የማይችሉትን ከአቅማቸው በላይ የማያስገድዳቸው፤ |
| አል-ቀሪቡ | الْقَرِيْب | ለሁሉም በእውቀቱ በችሎታው በእርዳታና በእንክብከካቤው ቅርብ፤ |
| አል-ሙጂቡ | الْمُجِيْب | ጥሪን መላሽ /ዱዓን ተቀባዩ፤ |
| አል-ሙቂቱ | الْمُقِيْت | ርዝቅን ፈጣሪና ለየባለቤቱ በአግባቡ አድራሽ፤በትክክል ቀላቢ፤ |
| አል-ሐሲቡ | الْحَسِيْب | የሁሉ ተሳሳቢ፤የሁሉ ተቆጣጣሪ፤ |
| አልሙእሚኑ | الْمُؤْمِن | ለሁሉ ፀጥታን ፤ደህንነትን ሰጭ፤ |
| አል-መናኑ | الْمَنَّان | ለጋስ፤ችሮታው ሰፊ፤ሰጪ፤ |
| አል-ጦይቡ | الطَّيِّب | ጥሩው፤ንፁሁ፤ ጥሩን እንጂ የማይበል፤ |
| አል-ሻፊ | الشَّافِي | ፈዋሽ፤ልብንም ሆነ አካልን፤ |
| አል-ሐፊዙ | الْحَفِيْظ | በችሎታው ሁሉን ጠባባቂ |
| አል-ወኪሉ | الْوَكِيْل | የፉጡሩ ተወካይ፤ |
| አል-ኸላቁ | الْخَلَّاق | ፈጣሪ፤በመፍጠር ላይ ያለ፤ |
| አል-ኻሊቁ | الْخَالِق | ያለ ተመሳሳይ ዐለምን ፈጣሪ፤ |
| አል-ባሪኡ | الْبَارِئ | ከምንም ያስገኘ ፈጣሪ፤ |
| አል-ሙሶውሩ | الْمُصَوِّر | ለሻው ነገር የሻዉን ቅርፅ ሰጪ፤ |
| አል-ረቡ | الرَّب | የሁሉ ጌታ/ (የሁሉ ተንከባካቢ)፤ |
| አልዐዚሙ | الْعَظِيْم | የታላቆች ሁሉ ታላቅ |
| አል-ቃሂሩ | الْقَاهِر | ሁሉን አሸናፊ፤የሁሉ በላይ፤ |
| አል-ቀሃሩ | الْقَهَّار | ሁሉን በሃይል አሸናፊ፤ |
| አልሙሀይሚኑ | الْمُهَيْمِن | የባሮቹ ጠባቂ፤የሚመሰክርባቸው፤ቋሚያቸው፤ |
| አል-ዐዚዙ | الْعَزِيْز | ሁሉን አሸናፊ፤ከሁሉም የማይፈልግ፤ |
| አል-ጀባሩ | الْجَبَّار | ሁሉንም በቁጥጥሩ ስር የሚያደርግ ሀያል/፤ ለተጎዱ ሁሉ ጠጋኝ፤ድሃን |

| | | |
|---|---|---|
| | | አክባሪ፤ችግረኛን ጠጋኝ፤ |
| አል-መተከቢሩ | المتكبر | ኩሩው፤ከማይሆኑ ነገሮች ራሱን ከፍ አድራጊው ፤ |
| አል-ከቢሩ | الكبير | በዛቱ፤ በባህሪያቱና በተግባሩም ትልቅ፤ |
| (አል-ሐይዩ) | الحيي | መከበር ያለባቸዉን ነገሮች አክባሪ፤ |
| አል-ሐዩ | الحي | ሁልጊዜም ህያው፤ ዝንታለም ኗሪ፤ መጀመሪያ የሌለው መጨረሻም የሌለው፤ |
| አል-ቀዩሙ | القيوم | ራሱን ቻይ)፤በራሱ የተብቃቃ፤ |
| አል-ዋሪሱ | الوارث | ወራሽ/ብቻዉን ቀሪ፤ |
| አል-ደያኑ | الديان | ፍጡሮችን ሁሉ አስጎብዳጅ፤አሸናፊ፤ |
| አል-መሊኩ | الملك | የሁሉ ንጉስ)፤ንጉስ |
| አል-ማሊኩ | المالك | የሁሉ ንጉስ)፤ንጉስ |
| አል-መሊኩ | المليك | የሁሉ ንጉስ፤ |
| አል-ሱቡሁ | السبوح | ከጉድለት ሁሉ የጠራው፤ |
| አልቁዱሱ | القدوس | (ከጉድለት ሁሉ የጠራ)፡ |
| አሰላሙ | السلام | ከእንከን ሁሉ ነፃ የሆነ፤የሰላም ባለቤት፤ |
| አል-ሐቁ | الحق | በጌትነቱ ምንም ጥርጣሬ የሌለበት፤ እውነቱ፤ |
| አል-ሙቢኑ | المبين | ግልፅ፤ ሁሉን ነገር ግልፅ አድራጊ፤ |
| አል-ቀዊዩ | القوي | (ሁሉን ነገር በማድረግ ሀይለ ብርቱ)፤ |
| አል-መቲኑ | المتين | (የማይሰለቸው እጅግ ብርቱ)፤ |
| አል-ቃዲሩ | القادر | (ምንም የማይሳነው ሁሉን ቻይ)፤ |
| አል-ቀዲሩ | القدير | (በነገሮች ላይ በጣም ቻይ)፤ |
| አልሙቅተድሩ | المقتدر | (ሁሉን ነገር ለማድረግ የሙሉ ችሎታ ባለቤት) |
| አል-ዐሊዩ | العلي | በሁሉ ነገር በዛትም ሆነ በስልጣን፤ የሁሉ የበላይ፤ |
| አል-አዕላ | الأعلى | በሁሉ ነገር በዛትም ሆነ በስልጣን፤ የሁሉ የበላይ፤ |
| አል-ሙተዓሊ | المتعال | በሁሉም ላይ የላቀ)ሁሉም ለሱ የሚተናነስለት፤፤ |
| አል-ሙቀዲሙ | المقدم | የፈለገዉን አስቀዳሚ/የሚያቀርብ)፤ |
| አል-ሙአኺሩ | المؤخر | የፈለገዉን አዘግይ/የሚያርቅ) |
| አል-ሙሰዒሩ | المسعر | የሁሉን ዋጋ አውጪ)፤ |
| አል-ቃቢዱ | القابض | ሩህን የሚወስድ፤ ከፋጡሩ ሲሳይን ያዠ) |
| አል-ባሲጡ | الباسط | ለባሮቹ ሲሳይን የሚዘረጋ፤ ለአጥፊዎቹ የይቅርታ እጁን የሚዘረጋ፤ |
| አል-አወሉ | الأول | ፊት የነበረ/የመጀመሪያ)፤ከፊቱ ምንም ያልነበረ፤ |
| አል-አኺሩ | الآخر | ሁሉም ሲያልቅ ኗላ ቀሪ/ መጨረሻ የሌለው፤ |
| አል-ዟህሩ | الظاهر | ለሁሉ ግልፅ፤ ከሁሉ በላይ ማንም የማይበልጠው)፤ሁሉንም አሸናፊ፤ |
| አል-ባጢኑ | الباطن | በዚህ ዐለም ከሰዎች እይታ ስዉር የሆነ፤ |
| አል-ዊትሩ | الوتر | አጋር የሌለው ብቸኛው ጌታ፤ |
| አል-ሰይዱ | السيد | ጌትነቱ ምሉዕ የሆነው ጌታ፤ የሁሉም ፍጡር ንጉስ፤ |
| አልሶመዱ | الصمد | ሁሉን አስጠጊ፡ ሁሉን መጋቢ፤ ሁሉም የሚከጅለው፤ |
| አል-ዋሂዱ | الواحد | በሁሉም ነገር አንዱ፤ |
| አል-አሀዱ | الأحد | አጋር የሌለው ብቸኛ፤ |
| አል-ኢላሁ | الإله | እውነተኛው ብቸኛ አምላክ፤ |

**13** **በአላህ (ﷻ) ስሞችና በባህሪያቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው ?** የአላህ (ﷻ) ስሞችና ባህሪያቱ በነሱ በኢስቲዓዛ/ በአላህ በመጠበቅ/ ና በእነሱም በመማል በመፈቀዱ ላይ ሁለቱም የጋራ ተልዕኮ ሲኖራቸዉ እንዲሁ በመሐከላቸው ብዙ ልዩነቶችም አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ዋናዋናዋቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

**1ኛው፡-**በባህሪያቱ ሣይሆን በስሙ አላህን ማምለክና መለመን የሚቻል ሲሆን በስሙ አላህን ማምለክ ሲባል ለምሳሌ አብዱልከሪም የቸሩ ጌታ ባሪያ ዐብዱሏህ/ የአላህ ባሪያ፤ ዐብዱረህማን /የረህማን ባሪያ/፤ ብሎ መሰየም ይቻላል፡፡ በባህሪያቱ ግን ለምሳሌ ከረም

/ልግስና/ በሚለዉ ባህሪዉ /ዐብዱልከሪም / የልግስና ባሪያ/ ተብሎ መሰየም ግን አይቻልም:: በዱዓም ያከሪም ብሎ አላህን መለመን የሚቻል ሲሆን -ያከረመ አሏህ(ﷻ) ብሎ መለመን ግን አይቻልም::

2ኛው -ከአላህ (ﷻ) ስሞች ባህሪ ይወሰዳል: ለምሳሌ አር-ረህማን/አዛኝ ከሚለው ስሙ ረህመህ /እዝነት የሚለዉን ባህሪ እንወስዳለን:: ባህሪያቱ ግን ከነቢዩ የተሰሙ ካልሆኑ በስተቀር ቋንቋን መሰረት አድርጎ ስሞች አይመሰረቱም:: ለምሳሌ ኢስቲዋእ/መደላደል/ከሚለው ስርወ ቃል ወስደን ከአላህ (ﷻ) ስሞች አንዱ ሙስተዊ/ተደላዳዩ/ ነው ማለት አይቻልም::

3ኛው- የአላህ ሥራዎች ከነቢዩ የተሰሙ ካልሆኑ በስተቀር ቋንቋን መሰረት አድርጎ ስሞች አይመሰረቱም:: ለምሳሌ ከአላህ ተግባሮች መካከል ቁጣ አንዱ ነው:: ስለሆነም ቁጣ ከሚለው ስርዎ ቃል ወስደን ከአላህ (ﷻ) ስሞች አንዱ ተቆጭ ነው ማለት አይቻልም:: ባህሪያቱ ግን ከተግባሮቹ ቀጥታ ይወሰዳሉ:: ለምሳሌ ቁጣ የሚለዉን ባህሪ ለአላህ አለው እንላለን:: ምክኒያቱም ቁጣ ከተግባሮቹ መካከል አንዱ ነዉና::

14 በመላኢኮች ማመን ማለት ምን ማለት ነው? መላኢኮች የተባሉ ፍጡሮች በመኖራቸውና አላህ (ﷻ) ጥራት የተገባውን ጌታ ሊገዙትና ትዕዛዙን ሊተገብሩ የተፈጠሩ ናቸዉ ብሎ ማመን ነዉ። አላህ በቁርአን "(መላእክት) የተከበሩ ባሮች ናቸው:: በንግግር አይቀሙትም (ያላለውን አይሉም)፤ እነሱም በትእዛዙ መሰረት ይሰራሉ::) ይላል::

ስለመላዕክት በነሱ ማመን ሲባል ብዙ ነገሮችን ያጠቃልላል:: 1-መኖራቸዉን ማመን፤ 2-ስማቸዉን ያወቅናቸዉን እንደጂብሪል ያሉትን ከነስማቸው ማመን፤ 3-ከባህሪያቸው ያወቅነዉንና እነሱ የተለዩበትን ግዙፍነታቸዉን ይመስል ለይቶ ማወቅ፤ 4-ያወቅነዉንና እነሱ የተለዩበትን ተግባር ለምሳሌ እንደሞት መላኢካ ያለዉን ከነተግባሩ ለይቶ ማመንና ማወቅ ነው::

15 ቁርአን ምንድን ነው? ቁርአን የአላህ (ﷻ) ቃል ነው:: እሱን በማንበብ ብቻ እንኳን የአላህ (ﷻ) አምልኮ ይገለፅበታል:: እሱ ዘንድ ወርዶ ወደሱ ይመለሳል:: በፊደሉም ሆነ በድምፅ ተናግሮታል:: ቁርአን መልአኩ ጂብሪል ከአላህ (ﷻ) ሰምቶት ከዚያም ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አድርሶታል:: ቁርአን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰማያዊ መፅሐፍት ሁሉ የአላህ (ﷻ) ቃል ናቸው::

16 ሀዲስን ትተን በቁርአን ብቻ መብቃቃት ይቻላልን ? - አይቻልም:: ምክንያቱም አላህ (ﷻ) ራሱ ሀዲስን እንድንይዝ (መልዕክተኛው የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ።) በማለት አዟልና:: ሀዲስ ደግሞ የቁርአን ማብራሪያ ነው:: የኢስላም ህግጋቱም ሆነ ስርአተ ዝርዝሩ ለምሳሌ :-የሶላትን አሰጋገድ ዝርዝረ ስርአቱን ይመስል ያለ ሐዲስ አይታወቅም:: ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድና አቡ ዳዉድ በዘገቡት ሐዲስ (አዋጅ ! ቁርአንና መሰሉን ተሰጥቻለሁ :: አዋጅ! አንዳንድ የጠገቡ ሰዎች በትራሳቸው ላይ ተደግፌው ይህን ቁርአን ብቻ ያዙ :: እሱ ሀላል ያደረገላችሁን ብቻ ሐላል በሉ:: ሐራም ያደረገባችሁንም ብቻ ሀራም በሉ ለማለት ይቀርባሉ) ብለዋል::

17 በነቢያት ማመን ማለት ምን ማለት ነው ? አላህ (ﷻ) ለየህዝቦች ወደሱ የሚጠሩና እሱ የብቸኛ አምልኮት ባለቤት መሆኑንና ከሱ ሌላ ማንም ሊመለክ የማይገባው መሆኑን የሚያስተምሩ አማኞችና እዉነተኞች የተከበሩ ቀናኢዎች ፈሪሃ አላህ ያደረባቸዉን ነቢያትን ልኳል:: እነሱም የተላኩበትን በትክክል አድርሰዋል:: እነሱም ከፍጡሩ ሁሉ ምርጦች ናቸው:: በአላህ (ﷻ) ከማጋራትም ከተወለዱበት ጊዜ አንስቶ እስከለተሞታቸው ድረስ የፀዱ ናቸው ብሎ በቁርጠኝነት ማመን ነው::

18 በቂያማ ቀን የሚኖሩት የሸፈዓ /የሽምግልና/ምልጃ/ አይነቶች ስንት ናቸው ?

የሽምግልና አይነቶች ብዙ ናቸው::
አንደኛውና ዋናው - ታላቁ ሽምግልና- የሚባለው ነው::
እርሱም ሰዎች ሀምሳ ሺህ አመት ሙሉ ዉሳኔ እንዲሰጣቸው ሲጠባበቁ ከቆዩ በኋላ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጌታቸዉን ለምነው ለዉሳኔ የሚያበቁበት የሽምግልና ሂደት ነው:: ይህ ለነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ብቻ የተሰጠ ማዕረግ ነው:: ይህም ያ! አላህ ቃል የገባላቸው - ምስጉኑ ቦታ የተባለው ነው::
ሁለተኛው ሽምግልና የጀነትን በር ለማስከፈት የሚደረገው ሽምግልና ሲሆን ለዚህም የመጀመሪያ ጠያቂው ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ናቸው፡፡ ከሕዝቦችም ሁሉ የመጀመሪያ ገቢዎች የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ኡመቶች ናቸዉ::
ሦስተኛው ሽምግልና እሳት እንዲገቡ የተወሰነባቸውን ሰዎች እሳት እንዳይገቡ ለመለመን የሚደረገው ሽምግልና ነው::
አራተኛው ሽምግልና ከሙስሊሞች መካከል በወንጀል ወደ እሳት ገብተው ያሉትን ሰዎች ከእሳት ለማስወጣት የሚደረገው ሽምግልና ነው::
አምስተኛው ሽምግልና፡- ጀነት የገቡ ሰዎች በጀነት ዉስጥ የደረጃ እድገትን እንዲሰጣቸዉ የሚደረገው ሽምግልና ነው:: በነዚህ በመጨረሻ በተወሱት በሶስቶቹ የሽምግልና አይነቶች ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ግንባር ቀደም ቢሆኑም ለሳቸው ብቻ የተለየ አይደለም:: ከሳቸው ቀጥሎ ነቢያት፤ መላኢኮች፤ ሳሊህ ሰዎችና የኢስላም ሰማዕታት /ሸሂዶች/ ይከተላሉ::
ስድስተኛው ሽምግልና ፡-ሰዎች ያለምንም ጥያቄና ምርመራ ጀነት እንዲገቡ የሚደረገው የሽምግልና ሂደት ነው::
ሰባተኛው ሽምግልና፡- አላህ የአንዳንድ ከሃዲዎችን ቅጣት እንዲያቃልል የሚደረገው ሽምግልና ነው:: ይህም ለነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የአጎታቸዉ የአቡጧሊብን ቅጣት ለማቃለል ብቻ የሚያደርጉት በመሆኑ ለእሳቸው ብቻ የተለየ ነው::
ስምንተኛው ፡-ከዚያም አላህ (ﷻ) ተውሒድ ኖሮዋቸው የሞቱና ወደ እሳት ገብተው የነበሩ ቁጥራቸውን እሱ ብቻ የሚያውቃቸውን ብዙ ሰዋችን ያለማንም ሽምግልና/አማላጅ/ ያወጣና ጀነት ያስገባቸዋል::

19 በህይወት ካሉ ሰዎች እገዛንም ሆነ ሽምግልና መጠየቅ ይቻላልን ? አዎን፡፡ ሁለቱም ይቻላል:: ኢስላም ሌላን በመርዳት ላይ ቁርአን (በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ) ሲል አስፈላጊነቱን በግልፅ አስተምሯል:: ነቢዩ ሙሐመድም (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «የሰው ልጅ ወንድሙን እስከረዳ ድረስ አላህ ይረዳዋል» ብለዋል:: ሽምግልና በኢስላም ትልቅ ምንዳ ያለው ተግባር ነው:: ቁርአን (መልካም መታደግን የሚታደግ/ ሽምግልናን የሚሸመግል/ ሰው ለሱ ከርሷ ድርሻ ይኖረዋል) ብሏል፡፡) ብሏል:: ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ (ለቸገራቸው ሰዎች ሽምግሉ ምንዳ አላችሁና) ብለዋል፡፡ ይህም የሚሆነው ከዚህ በታች ያሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ሲያሟሉ ብቻ ነው:: እነሱም:-

(1) ለሽምግልናውም የሚጠየቀዉ ሕይወት ካለው ሰው እንጂ ከሞተ ሰዉ እርዳታ መጠየቅ አይቻልም:: ምክኒያቱም የሞተ ሰው የሚለምነውን ሰው መርዳቱ ቀርቶ አይስማምና:: ቁርአን ‹‹ብትጠሩዋቸው ጥሪያችሁን አይሰሙም፤ ቢሰሙም ኖሮ ለእናንተ አይመልሱላችሁም:: በትንሳኤም ቀን እነርሱን በአላህ ማጋራታችሁን ይክዳሉ::›› አለ:: ይህ በመሆኑም ከመርዳት አኳያም ለሰው መርዳቱ ቀርቶ ራሱን መርዳት ያልቻለ ነገር ሁሉ ሌላን ይረዳል ተብሎ አይታሰብምና ነው::
የሰው ልጅ ሲሞት ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) (የሰው ልጅ ሲሞት ከሶስት ነገሮች በስተቀር ስራው ይቆማል ፡፡ እነሱም ቀጣይነት ያለው ሶደቃ፤ለሰዎች ጥቅም የሚሰጥ እውቀት እና ዱዓ

ከሚያያደርግ ልጅ በኩል የሚያደርስ ጥቅም ሲቀር) በማሰት ካከተመሩት
(2) አሸማጋዩ የተሸምጋዩን ቋንቋ ማወቅ መረዳት ከቻለ ነው::
(3) አሸማጋዩ በቅርብ ያለ ከሆነ ነው::
(4) የሚጠየቀዉ ነገር በሰዎች አቅም ሊፈፀም የሚቻል ነገር ከሆነ ፤
(5) የሚጠይቀው ጉዳይ በዱንያ ጉዳይ ላይ ብቻ ያተኮረ ከሆነ ከሆነና
(6) ለሌላ አካል ጉዳት የሌለው ነገር ሲሆን ብቻ ነው::

20 ተወሱል/ ወደ አላህ መቃረብ/ መጠጋት/ ስንት ክፍል አለው ? ተወሱል ሁለት ክፍል አለው:: አንደኛው ክፍል የሚፈቀደው ክፍል ሲሆን:- እሱም በሶስት ተከፍሎ ይታያል::
(1) በአላህ (ﷻ) ስሞችና ባህሪያት መወሰል/ወደ አላህ መቃረብ/፤
(2) በራስ መልካም ስራ መወሰል ሲሆን፤ ምሳሌውም የነዚያ ሶስት የዋሻ ሰዎችን ታሪክን ይመስል ነው:: (3) ጉዳዩን በሚሰማና በህይወት ባለ ከአላህ (ﷻ) ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው ተስፋ በሚጣልበት ሙስሊም ሷሊህ/በጎ ሰዉ/ ዱዓ መወሰል ናቸው::
ሁለተኛው የተወሱል አይነት የሚከለከለው ተወሱል ሲሆን ፡-እሱም ለሁለት ይከፈላል::
(1) በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ወይም በወሊይ ክብርና ግርማ ሞገስ መወሰል ነው:: ለምሳሌ ጌታየ ሆይ! በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ክብር ይሁንብህ ወይም በሁሴን ክብር ይሁንብህ ብሎ እንደመጠየቅ ነው:: የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ክብር ትልቅ መሆኑ አሌ የማይባል ሐቅ ነው:: እንደዚሁም የሷሊሆች ክብር የማይካድ ሀቅ ነው:: ሆኖም ከኛ የበለጠ ለኸይር ይጓጉ የነበሩት እኒያ የነቢዩ ሶሃቦች እንኳን ምድር ደርቃ ተጨንቀው በነበሩበት ጊዜ አጠገባቸው ቀብር ያዉም የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) መቃብር እያለ በሱ ሳይሆን የተወሰሉት በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)አጎት በሆኑት በዐባስ ብን አብዱልሙጠሊብ ዱዓዕ ነበር::
2) በነቢይ ወይም በወሊይ ምሎ ጌታውን መለመን ነው:: ለምሳሌ ጌታየ ሆይ ! በወዳጅህ እገሌ በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ወይም በእገሌ ላይ ሀቅ ይሁንብህና ይህን እጠይቅሃለሁ ማለት ነው:: ምክኒያቱም በፍጡርም መማል የተከለከለ ነው:: በተጨማሪም ፍጡር መታዘዝ ብቻ እንጂ በፈጣሪው ላይ የማዘዝ ምንም መብት የለዉምና ነው::

21 በመጨረሻ ቀን ማመን ማለት ምን ማለት ነው? የመጨረሻው ቀን የማይቀር መሆኑን ማመን ሲሆን በዚሁም ዉስጥ የሚጠቃለሉትን ማለትም ሞትና ከዚያም ቀጥለው የሚመጡትን የቀብር ፈተና/ ቅጣት እና ድሎቱ በቀንድ መነፋት፤ ሰዎች በጌታቸው ፊት ለጥያቄ መቆማቸው ፤የመዝገቦች መበተን፤ ሚዛን መቀመጡ፤ ሲራጥ መኖሩ፤ ሀውድና ሸፋዐህ መኖራቸውንና ከዚያም የሰዎች መጨረሻ ወደ ጀነት ወይም ወደ እሳት መሆኑን አምኖ መቀበል ማለት ነው፡፡

22 የቂያማ ታላላቅ ምልክቶች ምን ምን ናቸው? ነቢዩ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ቂያማ ከፊት ለፊቷ አስር ታላላቅ ነገሮችን ሳታዩ አትከሰትም:: ከነዚህም ጭስን፤ ደጃልን፤ ላሚን፤ ፀሐይ በምዕራብ መውጣቷን፤ የመርየም ልጅ ነብዩ የዒሳ መውረድን፤ የዕጁጅና መዕጁጅን፤መውጣት ሶስት የመሬት ስምጠትን፤ ማለትም አንዱ በምስራቅ፤ አንዱ በምዕራብና አንዱ ደግሞ በዐረቡ ደሴት የሚከሰቱትን የመሬት ስምጠቶች የመጨረሻው ከየመን ተነስ ሰዎችን ወደ መሰብሰቢያቸው የምትነዳዉን እሳት) ጠቅሰዋል::

23 በሰው ልጅ ህይወት ዉስጥ የምታልፈው ታላቋ ፈተና የትኛዋ ናት ? ነቢዩ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ኣደም ከተፈጠረ አንስቶ እስከ ቂያማ ቀን መከሰት ድረስ ከደጃል መምጣትቸ የበለጠ የከፋ ነገር የለም) ብለዋል፡፡ ደጃል ከኣደም ልጆች አንዱ ሲሆን በዐለም ፍፃሜ አካባቢ የሚመጣ ሐሰተኛ ሰው ነው:: በአይኖቹ መካካል (ك ف ر) ከፈረ/ካደ/ የሚል ተፅፎበታል: ይህንንም አማኞች ሁሉም ያነቡታል:: ቀኝ አይኑ ሸውራራ ነው:: አይኖቹ ጣፊ የሆነ ወይን ይመስላሉ:: በመጀመሪያ ሲመጣ መልካም ሰው በመምሰል ለማሳሳት ይሞክራል ፡፡ ከዚያም ነቢይ ነኝ ይላል፡ ከዚያም አምላክ ነኝ ይላል::

ወደ ሰዎች ይመጣና ጥሪ ማድረግ ይጀምራል፡፡ ሰዎች ግን ፍፁም አይቀበሉትም፡፡ ሰበካዉን ያስተባብላሉ:: ከዚያም እሱም ትቷቸዉ ይሄዳል:: ንብረቶቻቸው ግን በገዛ ፍቃዳቸው እሱን ይከተሉታል ፡፡ በዚህም ሰዎች ምንም የሌላቸው ድሆች ይሆናሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ወደሱ ይመጣሉ፡፡ እንደገና ይሰብካቸዋል:: የሚቀበሉት ይቀበሉታል፤ ያምኑበታልም:: ከዚህ በኋላ ሰማይን ያዝዛትና ዝናብ ታዘንባለች:: ምድርንም ያዝዛትና ታበቅላለች:: ወደ ህዝቡ እሳትና ዉሃን ይዞ ብቅ ይላል፡፡ እሳቱ ቀዝቃዛ ዉሃ ነው:: ዉሃው ደግሞ የሚያቃጥል እሳት ነው:: ማንኛዉም አማኝ የሆነ ሰዉ ሁል ጊዜም በሶላቱ መጨረሻ/አተ-ተሒያቱን ካነበበ በኋላ አላህን ከሱ እንዲጠብቀዉ ሊማፀነዉ ይገባል:: ያገኘው ሰው በሱ ላይ የከህፍን ምዕራፍ መግቢያ ያንብበበት:: ከተቻለም በሱ ላለመፈተን አጠገቡ ከመድረስ ይቆጠብ::

ነቢዩ (ﷺ) አህመድና አቡዳዉድ በዘገቡት ሐዲስ (የደጃልን መምጣት የሰማ ሰው ከሱ ይራቅ በጌታየ ይሁንብኝ እራሱን አማኝ ነኝ ብሎ የሚተማመን ሰው እንኳን ሳይቀር እሱ በሚረጨው ማሳሳቻ ሳይታሰብ ተከታዩ ይሆናል::) ብለዋል፡፡ በምድር ላይ የሚቆየው አርባ ቀን ብቻ ነው:: የመጀመሪያዋ ቀን እንደ አንድ አመት፤ ሁለተኛዋ ቀን እንደ አንድ ወር፤ ሶስተኛዋ ቀን ደግሞ እንደ አንድ ሳምንት ሌሎች ቀናቶች እንደ ተለመዱት የዱኒያ ቀኖቻችን ናቸው:: ከመካና ከመዲና ሌላ ያሉ ሀገራትን በሙሉ አንድም ሳይቀር ያስሳቸዋል:: ከዚያም ነቢዩ ዒሳ ይወርዱና ይገድሉታል::

**24** በአሁኑ ሰዓት ጀነትና እሳት ተፈጥረው ይገኛሉን ? አዎን ሁለቱም ተፈጥረው ይገኛሉ፡፡ አላህ (ﷻ) ሰዎችን ከመፍጠሩ በፊት ነው እነሱን የፈጠራቸው:: ሁለቱም ምንጊዜም አሉ አይጠፉም:: አላህ (ﷻ) በችሮታው ለጀነት ሰዎችን ፈጥሯል:: ለእሳትም በፍትሃዊነቱ ሰዎችን እንደዚሁ ፈጥሯል:: ሁሉም ሰው ለተፈጠረለት ነገር የተገራ ነው::

**25** በቀደር ማመን ማለት ምን ማለት ነው ? ሁሉም ነገር መጥፎም ሆነ በጎው ሊሆን የሚችለው በአላህ (ﷻ) እውቀት ብቻ መሆኑን አላህ (ﷻ) የሻዉን ሰሪ መሆኑን በቁርጠኝነት ማመን ነው:: ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድና አቡዳዉድ በዘገቡት ሐዲስ (አላህ የሰማይንም ሆነ የምድርን ፍጡራን ቢቀጣ ኑሮ ሁሉንም ለእነሱ በዳይ ሣይሆን በቀጣቸዉ ነበር:: ቢያዝንላቸውም ኖሮ እዝነቱ ከተግባራቸው የተሻለ ነው:: የኡሁድን ጋራ የሚያህል ወርቅ ለጂሃድ ብትሰጥ እንኳን በቀደር ካላመንክ ጴና ያገኘህ ነገር ሁሉ ሊያመልጥህ ይችል እንዳልነበረ፤ ያመለጠህ ነገር ሁሉ ደግሞ ሊያጋጥምህ የሚችል እንዳልነበር በትክክል እስካላወቅክ ድረስ ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት የለህም:: ከዚህ ሌላ በሆነ እምነት ላይ ሆነህ ብትሞት እሳት ገባህ) ብለዋል፡፡

በቀደር ማመን አራት ዋና ዋና ነገሮችን ያጠቃልላል:: 1) አላህ (ﷻ) የሁሉን ነገር ዝርዝር ጉዳይ ኢምንት እንኳን ሳይቀር ያውቃል ብሎ ማመን፤ 2) ይህን ሁሉ በለውሀል መህፉዝ ቀድሞ ፅፎታል ብሎ ማመን፤ ነቢዩ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ስለዚሁ ሲናገሩ (አላህ የፍጡሮችን ዉሳኔ የፃፈው ሰማይንና ምድርን ከመፍጠሩ ከሀምሳ ሺህ አመት በፊት ነበር) ብለዋል:: 3) የአላህን ፍላጎት ማንም የማይመልሰው ሀይሉንም ማንም የማያሸንፈውና እሱ የፈለገውን የሚፈፀም ያልፈለገው የማይፈፅም መሆኑን ማመን 4) አላህ (ﷻ) ሁሉን ነገር የፈጠረ፤ ከእርሱ ሌላ ያለው ሁሉ የተፈጠረ መሆኑን ማመን ነው፤

**26** ፍጡር ነገሮችን በራሱ የመምረጥ አቅምና ፍላጎት አለዉን? አዎን፡፡ የሰው ልጅ የራሱ የሆነ ነፃ ፍላጎትና ምርጫ አለው:: ሆኖም ከአላህ ምርጫና ፍላጎት አይወጣም፡፡ አላህ እንዲህ አለ (የዓለማት ጌታ አላህ ካልሻ በስተቀር ምንንም አትሹም፡፡) ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ስሩ፡፡ ሁሉም ለተፈጠረለት ነገር የተገራ ነውና) ብለዋል:: አላህ ጥሩን ከመጥፎ ልንለይበት አዕምሮ፤ጆሮና አይንን ሰጠን:: ለመሆኑ ትክክለኛ አዕምሮ ያለው ሰው አውቆ ሰርቆ አላህ (ﷻ) ሽቶብኝ ነው ማለቱ

ያስኬዳልን? ቢልስ ማን ይቀበለዋል! እንዲያዉም ይህን የሰማው አካል ስልጣን ያለው ከሆነ ባዩን ሰዉ ይቀጣዉና ከቅጣቱ ከጠየቀዉ ቅጣቱንም አላህ (ﷻ) ነዉ የሻብህ ሲል ይመልስለታል:: ለጥፋት በቀደር ማመካኜት ፈፅሞ አይቻልም:: አያዋጣምም:: ይህ ራሱ ማስተባበል ነው የሚሆነው:: አላህ (ﷻ) (እነዚያ ያጋሩት አላህ በሻ ኖሮ እኛም ሆንን አባቶቻችን ባላጋራን ነበር:: አንዳችን ነገርም ባላደረግን ነበር ይላሉ፡፡ ልክ እንደዚሁ (እነዚህ እንደዋሹ ሁሉ) እነዚያ ከበፊታቸው የነበሩት ሰዎችም ብርቱ ቅጣታችንን እስኪቀምሱ ድረስ አስተባበሉ፡፡) ብሏል፡

**27** **ኢህሳን ማለት ምን ማለት ነው?** ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (መልካም ስራ ምንድን ነው ብሎ ለጠየቃቸው ሲመልሱ (አላህን እንደም የው ሆነህ መገዛት ነው፡፡ አንተ የምታየው ባትሆን እሱ ያይሃል) ብለዋል:: እሱም ከኢስላም ሃይማኖት ከሶስቱ ደረጃዎች ከፍተኛው ደረጃ ነው::

**28** **የተውሂድ ክፍሎች ስንት ናቸው?** የተውሂድ ክፍሎች ሶስት ናቸው፡፡ እነሱም:-

**1ኛው-** አላህን በጌትነት አንድ መሆኑን ማወቅ ሲሆን እሱም አላህን (ﷻ) በድርጊቶቹ ማለትም በመፍጠር፤ በመመገብ፤ በማዳንና በመሳሰሉት አንድ ማድረግ ነው:: ይህን ክፍል ከሃዲዎችም ሳይቀሩ ያምኑበት ነበር::

**2ኛው-** አላህን በማምለክ/ በአምልኮት/ አንድ ማድረግ ሲሆን:- ይኸዉም አላህ (ﷻ)ን በአጠቃላይ አምልኮ ተግባራት፤ በሶላት፤ በስለት፤ በሰደቃና በመሳሰሉት አንድ ማድረግ ነው:: ለዚህ ሲባልም ነው ነቢያት በዋናነት በየጊዜው ወደህዝቦች የተላኩትና መፅሐፍትም የተወረዱት፡፡

**3ኛው-** አላህን በስሙና በባህሪያቱ አንድ አድርጎ መገዛት ሲሆን እሱም አላህና መልዕክተኛው ለአላህ (ﷻ) ያፀደቋቸዉን መልካም ስሞችና ሙሉዕ ባህሪያትን ያለምንም ለውጥና ከትክክለኛ ትርጉማቸው ያለማዛባት ያለማቀናነስና እንዲህ ነው ብሎ ባለመግለፅና ከፍጡር ጋር ባለማመሳሰል ማመን ነው::

**29** **ወሊይ ማን ነው?** አላህን (ﷻ) የሚፈራ በጎና አማኝ ሰው ነው፡፡ አላህ (ﷻ) በቁርአኑ (ንቁ! /አዋጅ/ የአላህ ወዳጆች ምንም ፍርሃት የለባቸውም፡፡ በምንም አያዝኑምም) ብሏል:: ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (የእኔ ወዳጅ አላህና መልካም ሰዎች ናቸው) ብለዋል፡፡

**30** **ስለ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ባልደረቦች ያለብን ግዴታ ምንድን ነው?** እነሱን መውደድ፤ አላህም (ﷻ) ተግባራቸዉን እንዲወድላቸው መለመን፤ ምላሳችንንም ሆነ ልቦናችንን ለእነሱ ማፅዳት፤ ገድላቸውንና ደረጃቸውን ማውሳት፤ ስህተቶቻቸዉንና በመሀከላቸው የተፈጠረዉን አለመግባባት ከማውሳት መቆጠብ፤ እነሱም ሰዎች ናቸዉና ከስህተት የተጠበቁ አይደሉም፡፡ ከመሐከላቸው መረጃ እውነትን ለማግኘት ጥረት ያደረጉ ናቸዉ፤ ከመሐከላቸው ትክክለኛዉን መረጃ ያገኘ ሰው ሁለት አጅር ሲኖረው ለተሳሳተው ክፍል ደግሞ አንድ አጅር አለው፡፡ የተሳሳቱት ሊማሩ ይችላሉ:: ቢሳሳቱም እንኳን ስህተታቸዉን ሊያስወግድ የሚችል ታላላቅ መልካም ሥራዎች አሏቸው፡፡ በመሐከላቸው ይበላለጣሉ ፡፡ዋናዋቻቸው አስሮች ናቸው፡፡ እነሱም አቡበክር ፤ ከዚያም ዑመር ፤ ከዚያም ዑስማን፤ ከዚያም ዐሊየ፤ ከዚያም ጦልሐ ህ ፤ ከዚያም ዙበይር ፤ ከዚያም ዐብዱረህማን ብን ዐውፍ ፤ ከዚያም ሰዕድ ብን አቢ ወቃስ ፤ ከዚያም ሰዒድ ብን ዘይድ ፤ ከዚያም አቡ ዐበይደት ብን ጀራህ ናቸው፡፡ ፤ ከዚያም ሌሎች ለኢስላም ሲሉ ከመካ ወደ መዲና የተሰደዱት ናቸው፡፡ ከዚያም የበድር ዘማቾች ናቸው፡፡ ከዚያ በበድር ዘመቻ ዕለት ያልተሳተፉ የመዲና ሙስሊሞች ናቸው፡፡ ከዚያ ከነብዩ ጋር መገናኘት የበቁት ሱሃቦች ናቸው፡፡

ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ባልደረቦቼን

አትስደቡብኝ፡፡ ህይወቴ በእጁ በሆነው ጌታ ይሁንብኝ ከመሐከላችሁ አንዱ የኡሁድን ተራራ ያህል ወርቅ ቢሰጥ እንኳን የእነሱን ቁና ብሎም ግማሹን አይስተካከልም) ጦበራኒ በዘገቡት ሐዲስም (ሶሃቦቸን የሰደበ ሰው በእሱ ላይ የአላህ፤ የመላይኮች እና የሰዎች እረፍግማን ይውረድበት) ብለዋል፡፡

31 ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) ከተሰጡት ደረጃ በላይ በሙገሳ ማጋነን ይፈቀድልናልን? ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ከፍጡሮች ሁሉ የላቁ ስለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የለዉም፡ ፡ ሆኖም ስናወድሳቸው ክርስቲያኖች ነቢዩ ዒሳን ሲያሞግሱ ከተገቢው በላይ እንደሚያሞግሷቸው እንደሚያልቋቸው ሁሉ እኛም ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) ከሚገባቸው ደረጃ በላይ አናወድስም፡፡ ምክኒያቱም ራሳቸው ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ (ክርስቲያኖች የመርየምን ልጅ ዒሳን ሲያሞግሱ ከተገቢው በላይ እንዳላቁት ሁሉ እኔንም ከተገቢው በላይ አታልቁኝ፡፡ ይልቁንስ እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፡፡ እናም የአላህ ባሪያና መልዕክተኛ በሉኝ) በማለት ስለከለከሉን ነው፡፡

32 እውነት የመፅሐፍ ሰዎች አማኞች ይባላሉን ? አይሁድ፤ክርስቲያንና ሌሎችም ባለ ሀይማኖቶች መነሻ መሰረት ባለው ሀይማኖት የሚያምኑ ቢሆንም በኢስላም እይታ ከሃዲዎች ናቸው። ምክኒያቱም ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ከተላኩ በኋላ ሁሉም የግል እምነቱን ትቶ እሳቸውን በመከተል ያልሰለመ ሰው ‹‹ ከእርሱ ተቀባይ የለውም። ጀርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ አንዱ ነው፡፡›› የእነርሱን ክህደት ያላመነ ወይም በእምነታቸዉ ብልሹነት የተጠራጠረ ሁሉ ራሱ ከሃዲ ነው። ምክኒያቱም ከሃዲ መሆናቸዉን የገለፀዉን የአላህን እና የነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) ዉሳኔ ተቃውሟልና ነው፡ ፡ ስለዚህ ጉዳይ አላህ (ከአህዛቦቹ በእርሱ የሚክድ ሰው እሳት መመለሻው ናት፡) ብሏል። ነብዩ በሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ሕይወቴ በእጁ በሆነው ጌታ ይሁንብኝ ከዚህች ኡመትም ሆነ ከአይሁድ ውይም ከክርስቲያን የእኔን መላክ ሰምቶ ካላመን የእሳት ነው» ብሏል።

33 ከሃዲዎችን ያለምንም ጥፋት መበደል ይፈቀዳልን ? ፍትሀዊነት ግዴታ ነው አላህ በቁርአን ‹‹አላህ በማስተካከል /በፍትህ/ በማሳመር /በመልካምሥራ/ና ለዘመድ በመስጠት ያዛል ከአስከፊ /ጸያፍ ነገር/ ከማመንዘር) ከሚጠላ ነገር ሁሉ ከመበደልም ይከለክላል። ትገነዘቡ ዘንድ ይገሥጻችኋል፡፡›› ብሏል ፡፡ መበደል ክልክል ነው። ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (አላህ እንዲህ አለ ግፍ መስራትን በራሴ ላይ እርም አድርጊያለሁ። በእናንተም ላይ እንዲሁ እርም አድርጊያለሁ።እናም እርስ በእርስ አትበዳደሉ፡፡) ብለዋል። የተበደለ ሰው የቂያማ ዕለት ከበዳዩ ይካሳል። ነብዩ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ድሃ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? አሉ። ሶሃቦችም እኛ ዘንድ ድሃ ማለት ብርና እቃ የሌለው ማለት ነው አሏቸው። ነብዩ ግን በእኔ ኡመቶች ዘንድ ድሃ ማለት የቂያማ ዕለት ሶላት ሰግዶ ፆም ፆሞ ዘካም ሰጥቶ በሌላ በኩል ደግሞ አንዱን ሰድቦ፤ የአንዱን ስም አጉድፎ፤ የአንዱን ገንዘብ በልቶ የሌላውን ደም አፍስሶ፤ ሌላውን ደብድቦ የሚመጣ ከዚያም ለዚህም ለዚያም ከበጎ ተግባሩ እየተነሳ ይሰጠውና ከፍሎ ሳይጨርስ መልካም ተግባሩ ሲያልቅ ከተበዳዩች ወንጀላቸው ተነስቶ በእሱ ወንጀል ላይ ተጨምሮ ወደ እሳት የሚወረውረው ሰው ነው›› ብለዋል መካካስ በእንስሳዎች መካከልም አለ።

34 ቢድዓ ምንድን ነው ? ኢብኑ ረጀብ የተባሉ ዐሊም (ቢድዐ ማለት የተፈለገው በሸሪኣ አንድም መሰረትና መነሻ የሌለዉ ማለት ነው፡፡ በሸሪዕ መሰረት ያለዉ ነገር ከሆነ ግን ከቋንቋ አኳያ ቢድዐ ሊባል ቢችልም በሸሪዐ ግን ቢድዐ አይባልም፡፡) ብለዋል።

35 ቢድዐ በኢስላም መልካምና መጥፎ ተብሎ ለሁለት ይከፈላልን ? ቢድዓ በኢስላማዊ ትርጉሙ በሸሪዐ መሰረት ሳይኖረው አዲስ የተፈጠረ ነገር ማለት ነዉና ቢድዐ አስቀያሚና የተወገዘ ለመሆኑ አያሌ የቁርአን አንቀፆችና የሀዲስ ዘገባዎች አሉ፡፡

ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ትዕዛዛችን የሌለበትን ነገር የሠራ ሰው ተግባሩ ወደ እርሱ ተመላሽ ይሆናል/ዉድቅ ነው) ብለዋል፡፡ እንዲሁም ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (አዲስ ፈጠራ ሁሉ ቢድዐ ነው፡፡ ቢድዐ ሁሉ ደግሞ ጥሜት ነው) ብለዋል፡፡

ኢማሙ ማሊክ ስለ ኢስላማዊ የቢድዐ ትርጉም ሲናገሩ (በኢስላም ቢድዐን ፈጥሮ መልካም ናት ብሎ ያሰበ ሰው ሙሐመድ በተልዕኮው ላይ ክህደት ፈፅሟል እንዳለ ይቆጠራል) ብለዋል፡፡ ምክኒያቱም አላህ (ዛሬ ሃይማኖታችሁን ሞላሁላችሁ፡፡ ፀጋዬንም በናንተ ላይ ሞላሁ፡፡ ኢስላምንም ከሃይማኖት ለናንተ ወደድኩ) ብሏልና፡፡ ቢድዐን ከቋንቋዊ ትርጉሙ አኳያ-በሸሪዐው መሰረት የሚያሞግሱ አንዳንድ ሀዲሶች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (በኢስላም ዉስጥ መልካም ሱናን የጀመረ ሰው እሱ በሰራዉም ሆነ ከእሱ በኋላ እሱን ተከትለው በሰሩት ሰዎች ቁጥር ልክ ምንዳ አለው፡፡ ይኸዉም ከእነሱ ምንዳ ምንም ሳይቀነስባቸው ነው) የሚለው አንዱ ነው፡፡ በዚሁ ትርጉም ሙሰረ ተም የከሊፋ ዑመር ነቢዩ ያን ግዜታ እንዳይሆን በመፍራት ለሶስት ቀን ብቻ ሰግደዉ ትተዉት የነበረዉን የተራዊህ ጀመዓ ሶላትን እንደገና መጀመርን አከሞልክተው (ምንኛ ያማረች ቢድዓ ናት፡፡) ያሉተም ተወስቷል፡፡

**36** የንፍቅና አይነቶች ስንት ናቸው? የንፍቅና አይነቶች ሁለት ናቸው፡፡

1)እምነታዊ ትልቁ ንፍቅና/ ሲሆን እሱም ክህደትን በዉስጥ ደብቆ እምነትን በአፍ መናገርና ከሰዎች መመሳሰል ነው፡፡ ይህ አይነቱ ንፍቅና ከኢስላም ያስወጣል፡፡ በዚሁ አቋሙ ፀንቶ የሞተ ሰውም በክህደት ላይ ሞተ ይባላል፡፡ አላህ (መናፍቃን በርግጥ ከእሳት በታችኛው አዘቅት ውስጥ ናቸው) ብሏል፡፡

ከመናፊቆች ባህሪያት መካከል አላህንና አማኞችን ማታለል፣ በአማኞች ላይ ማፌዝ፣ በሙስሊሞች ላይ ከሃዲዎችን ማስተባበር፣ በሚሰሩት መልካም ስራ ሁሉ የዱንያን ጥቅም መፈለግ ናቸው፡፡

2) ድርጊታዊ ንፍቅና (አነስተኛው ንፍቅና) ሲሆን ይህም ከኢስላም ባያወጣም በተዉባ ካልተመለሰ/ንስሃ ካልተገባ/ በስተቀር ወደ ከፍተኛው ንፍቅና እንዳያደርስ የሚያሰጋ ነው፡፡ ከዚህ ንፍቅና ባለቤት ባህሪያት መካከል ዉሸታምነት፣ ቀጠሮ ማፍረስ፣ ሲከራከር መዋሸት፣ ቃል ገብቶ በቃሉ አለመሙላትና አማናን /አደራን/ መክዳት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ለዚህም ነበር የነብዩ ሶሃቦች ከዚህኛው የንፍቅና ክፍል በጣም ይፈሩ የነበሩ ኢብኑ አቢሙላይካ ሰላሳ የነብዩ ሶሃቦችን አግኝቻለሁ፡፡ ሁሉም ንፍቅናን በራሳቸው ላይ ይፈሩ ነበር ብለዋል፡፡ ኢብራሂሙ ተይሚ ተግባሬን በንግግሬ ላይ አነፃፅሬ አላውቅም አስተባባይ እንዳልሆን እየፈራሁ እንጂ ብለዋል፡፡ ሐሰኑል በስሪ ‹‹ንፍቅናን የሚፈራ ሁሉ አማኝ ነው ምንም የለብኝም የሚል ደግሞ ሙናፊቅ ነው›› ብለዋል፡፡ ዑመር ሑዘይፋህን በአላህ ስም እጠይቅሀለሁ እኔን ከሙናፊቆች አንዱ እንደሆንኩኝ ነግረውሃልን? ብለው ጠየቋቸው ፈፅሞ ከእንተበላይ ማንም አላመሰግንም›› ብለዋል

**37** አላህ (ﷻ) ዘንድ ትልቁ ወንጀል ምንድነው ? አላህ (ﷻ) ዘንድ ትልቁ ወንጀል በአላህ (ﷻ) ማጋራት ነው፡፡ አላህ (ﷻ) በቁርአን እንዲህ አለ (ማጋራት በርግጥ ታላቅ በደል ነው፡፡) ነቢዩ ሙሐመድም (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (የወን ጀሎች ሁሉ ትልቁ ወንጀል ምንድን ነው? ተብለው ሲጠየቁ (የፈጠረህ ሆኖ ሣለ በጌታህ አጋር ማድረግ ነው) ብለዋል፡፡

**38** የማጋራት አይነቶች ስንት ናቸው ? የማጋራት አይነቶች ሁለት ናቸው፡፡

1ኛዉ)ትልቁ ማጋራት ሲሆን እሱም ከኢስላም የሚያወጣና ቁርአን (አላህ በርሱ ማጋራትን ፈጽሞ አይምርም::)[1] ሲል የተናገረበት ነው፡፡ እሱም አራት ክፍሎች አሉት፡፡ ሀ) የዱዓና የልመና ማጋራት/ሽርክ/ልዲባዳ ለ) በኒያ፤ በሐሳብና በፍላጎት ማጋራት፤ ለምሳሌ መልካም ሥራን ከአላህ ውጪ ለሆነለሌላ አካል መሥራት፤ ሐ) የመታዘዝ ማጋራት ሺርክል ጧዓህ ምሣሌ አላህ (ﷻ)ሐላል ያደረገዉን ነገር ሐራም፤ ሐራም ያደረገዉን ነገር ሐላል የሚያደርጉ ሰዎችን መታዘዝና አሚን ብሎመቀበል ማለት ነው፡ ፡ መ) የማፍቀር ማጋራት ሺርኩልሙሐበሩ ሲሆን እሱም አንድን ነገር ልክ እንደ አላህ (ﷻ) አድርጎ መውደድ ነው::

2ኛዉ) ትንሹ ማጋራት ሺርክልአስገሮ ሲሆን ይህ አይነቱ ማጋራት የሰራዉን ሰው ከኢስላም አያወጣዉም፡፡ ይህም ለሁለት የሚከፈል ሲሆን፤ 1-ግልጽ የወጣ ለምሣሌ ከአላህ ዉጭ በሌላ መማል[2]፤ አንተና አላህ የሻዉ ይሆናል ወይም አንተና አላህ ባትኖሩልኝ ኖሮ እያሉ አላህን ከሰዉ እኩል ማድረግ እንዲሁም አላህን ዘንግቶ በሰበቦች ለምሣሌ በጦር መከላከያ ልብስ፡ የሰዉ ዓይንን ፈርቶ አንገት ላይ በሚንጠለጠሉ ነገሮች፤ በገድና በአድባር በሌሎችም በነገሮች ሙሉ በሙሉ መተማመንን ይመስል ነዉ:: ሌላዉ ድብቁ ማጋራት የሚባለው ሲሆን ለእዩልኝ ለስሙልኝ ብሎ ነገሮችን ማሰብ ማቀድና መስራት ነው፡፡

39 በትልቁ ማጋራትና በትንሹ ማጋራት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

በመሀከላቸው ካሉ ልዩነቶች መካከል ትልቁን ማጋራት የፈፀመ ሰው በዚሁ በዱንያ እያለ ከኢስላም የወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፤ በአኺራም በገሀነም ዉስጥ እንደሚዘወትር ብይን ይሰጠዋል፡፡ ትንሹን ሽርክ የፈፀመ ሰው ግን ከኢስላም እንደወጣ አይቆጠርም፡፡ በገሀነምም ውስጥ አይዘወትርም፡፡ ትልቁ ማጋራት መልካም ስራዎችን ሁሉ ሲያበላሽ፤ ትንሹ ግን ከእሱ ጋር ግንኙነት ያለዉን ስራ ብቻ ነው የሚያበላሸው፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር አለ፡፡ እሱም ትንሹ ሽርክ ሰዉየው ንስሃ እስካልገባ ድረስ እንደ ትልቁ ሽርክ ሁሉ አይማርም? ወይንስ እሱም እንደሌሎች ታላላቅ ወንጀሎች በአላህ (ﷻ) ፍቃድ ስር የሚጠቃለል ነው በሚለው ላይ የዑለማዖች የአቋም ልዩነት አለ። ይህም ጉዳዩ በጣም አስጊ ነውና ሰዎች አጥብቀው ሊርቁት ይገባል፡፡

40 እነኚህን ሳይከሰቱ በፊት መከላከያቸዉ ምንድን ነዉ ? ከተከሰቱ በኋላስ ማበሥ አሊያም መሰረዝ የሚቻለዉ እንዴት ነው? ከታይታ/ እዩልኝ ለመጠበቅ ሥራን የአላህን (ﷻ) ዉዴታ ፈልጎ መስራት ሲሆን ትንሹን ሪያዕ ግን በዱዓም መከላከል ይቻላል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድም (ﷺ) አህመድ. በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ አሉ (ሰዎች ሆይ ይህን ሽርክን ተጠንቀቁ፡፡ ምክኒያቱም እሱ ከጩጫን የጨለማ ጉዞ በላይ የተደበቀ ነው፡፡ ከጨጪን ጉዞ የተደበቀ ሆኖ ባለበት ሁኔታ እንዴት ነው የምንጠነቀቀው ? ተብለውም ሲጠየቁ (አላሁመ ኢና ነዑዙ ቢከ ርን አን ኑሽሪከ ቢከ ሸይአን ዕለሙሁ ወነስተግፌሩከ ሊማላነዕለሙሁ በሉ) ብለዋል፡፡ ከአላህ (ﷻ) ሌላ በሆነ አካል የማለ ሰው ማካካሻውን ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (በላትና በዑዛ የማለ ሰው ላኢላሀ ኢለሏህ ይበል) በማለት አስተምረዋል፡፡ ስለ ተጦዩር /መጥፎ ገድ እምነት/ እና ማካካሻዉንም በተመለከተ ነቢዩ አህመድ በዘገቡት ሐዲስ

---

[1] እነሆ ! በአላህ የሚ ያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ፡፡ መኖሪያውም እሳት ናት፡ ፡ ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም:: አል-ማኢዳህ 72....ባጋሩም ኖሮ ይሠሩት የነበረው ሁሉ ከነሱ በታበሰ ነበር:: አል-አንዓም88 .ወ፱ አንተም ወደእነዚያም ካንተ በፊት ወደነበሩትም በእርግጥ ተወርዷል ብታጋራ ስራህ በእርግጥ ይታበሳል፡ በእርግጥም ከከሣሪዎች ትሆናለህ፥፥ አዝ-ዙመር 65

[2] -ምሳሌ በእናት፤ በአባት፤ በልጅ በባል፤በሸኽ ፤በነቢያት ....

(ከአሰበው መጥፎ ግድ የመለሰው ሰው በአላህ አጋራ፡፡) ያሉ ሲሆን የዚህ ማካካሻዉ ምንድነው ብለው ሲጠይቋቸው (አላሁመ ላኸይረ ኢላ ኸይሩከ ወላ ጠይረ ኢላ ጦይሩከ ወላ ኢላሀ ገይሩከ) ማለት እንደሆነ አስተምረዋል፡፡

**41** በአላህ መካድ ሲባል ስንት ዓይነት አለው ? ሁለት ናቸዉ፡፡

1) ከኢስላም የሚያስወጣ ክህደት ሲሆን እሱም ራሱ አምስት ክፍል አሉት፡፡ እነሱም፡- ሀ) የማስተባበል ክህደት ፤ ለ) እዉነትን እያወቁናየሚፈፀም የትዕቢት ክህደት፤ ሐ) የመጠራጠር ክህደት፤ መ) የመተው /እውነትን ያለመቀበል/ ክህደትና፤ ሠ) የንፍቅና ክህደት ናቸው፡፡

2- ትኒሹ መካድነው፡፡ ሲባል ይህዉም የወንጀል ክህደት ሲሆን ባለቤቱን ከኢስላም አያስወጣዉም፡፡ ምሳሌውም ሙስሊምን እንደ መግደልና የመሳሰለው ነው፡፡

**42** በኢስላም ስለት መሳል እንዴት ይታያል? ስለት ነቢዩ ሙሐመድ (عَزَّ وَجَلَّ) ስለከለከሉና እሱ ምንም ፋይዳ የለዉም ስላሉ ስለቱ ለአላህ እንኳን ቢሆን መሳሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለት ከአላህ ሌላ ለምሳሌ ለቀብር ፤ ለወልይና ለመሳሰሉት ከሆነ ደግሞ ከናካቴው ስለቱ የተከለከለ ነው፡፡ የተገባዉን ቃልም መሙላት አይፈቀድም፡፡ ስለዚህ ስለት በኢስላም ተቀባይነት የሌለዉና ዋጋ ቢስ ድርጊት ነው፡፡

**43** ወደ ጠንቋይ ወይም አውቃለሁ ባይ ዘንድ መሔድ ኢስላማዊ ብያኔዉ ምንድነው ? ይህ ተግባር ክልክል ነው፡፡ እነሱ የሩቅ ዕዉቀት አለን በሚሉት ሳያምን እራሱን ለመጥቀም ብሎ ወደነሱ የሄደ ሰው ነቢዩ ሙሐመድ (صلى الله عليه وآله وسلم) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ወደ ጠንቋይ ወይም አውቃለሁ ባይ ዘንድ የሄደና የሆነ ነገር የጠየቀው ሰው የአርባ ቀን ሶላቱ ተቀባይነት የለውም) ብለዋል፡፡ ወደ እነሱ ሂዶ እነሱ ገይብን/ የተሰወሩ ነገሮችን እናውቃለን የሩቅ እውቀቱ አለን የሚሉትን ያመነና የተቀበለ ሰው ደግሞ በነቢዩ ሙሐመድ ዲን/ሃይማኖት የካደ ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (صلى الله عليه وآله وسلم) አቡዳዉድ በዘገቡት ሐዲስ (ወደ ጠንቋይ ወይም አውቃለሀ ባይ ዘንድ የሄደና የሚለውን ያመነው በሙሐመድ ላይ በተወረደው ቁርአን ክዷል) ብለዋል፡፡

**44-** ዝናብን በኮከብ መለመን እንደ ማጋራት የሚቆጠረዉ መቸ ነዉ ? ከአላህ (عَزَّ وَجَلَّ) ፍቃድ ዉጭ ኮከቦች ዝናብን የማምጣት አቅም አላቸው ብሎ ያመነና ዝናብን የማዝነብን ስልጣን ለኮከቦች የሰጠ ሰው ትልቅ የሽርክ ተግባር የፈፀመ ነው፡፡ ኮከቦች በአላህ (عَزَّ وَجَلَّ) ፍቃድ ላይ ተፅዕኖ አላቸው ወይም ስልጣኑን ለመጋራት አቅም አላቸው ብሎ ያመነ ሰው ፤ አላህ (عَزَّ وَجَلَّ) ለዝናብ መምጣት ምክኒያት አድርጓል ብሎ ያመነና አላህ የዝናብ መምጫን ምልክት ይህ ኮከብ ሲመጣ አድርጎታል ብሎ ያመነ ሰው በተጨባጭም ሆነ ከሸሪዕ እንዲሁም ከትክክለኛ አዕምሮ መረጃ ያለው አባባል ባለመሆኑ ክልክልና ከትንሹ ሽርክ የሚመደብ ነዉ፡፡ አመትን በወራቶች በመከፋፈል በኮከቦች ለያይቶ ማወቅና የዝናቡን መምጫ ወቅት በእሱ ለመረዳት መሞከር በኢስላም ምንም ችግር የለበትም፡፡

**45** ለሙስሊም መሪዎች ያለብን ግዴታ ምንድነው? በክፉም ሆነ በደጉ እነሱን መታዘዝ ግዴታ ነው፡፡ አጠፉ ተብሎ በእነሱ ላይ ማመፅ አይፈቀድም፡፡ /መራገምም አይገባም፡፡ ከመታዘዝ አናፈነግጥም፡፡ ከቶዉንም በመልካምና ገር ነገር ላይ እንዲውሉ በጤናና ቀናዉን መንገድ እንዲይዙ ዱዓ እናደርግላቸዋለን፡፡ በወንጀል እስካላዘዙን ድረስ እነሱን መታዘዝ አላህን (ﷻ) እንደ መታዘዝ ነው፡፡ በወንጀል ቢያዙን ግን ለነሱ መታዘዝ አይገባም፡፡ ነቢዩ (صلى الله عليه وآله وسلم) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ለመሪህ ትሰማለህ ትታዘዛለህ፡፡ ብትገረፍም ንብረትህ ቢወሰድብህም የሚሉህን ስማ፣ ያዘዙህን ታዘዝ) ብለዋል፡፡

**46** አላህ (ﷻ) ባዘዘባቸዉና በከለከላቸዉ ነገሮች ዉስጥ ያለዉ ጥበብ ምክኒያቱ ምን

**እንደሆነ መጠየቅ ይፈቀዳልን?** አዎን፣ ከማመንም ሆነ ከመሥራት ጋር ሳያያይዙ ጥበቡን ማወቁ ይበልጥ ለመርካትና በኢማን ለመጨመር ከሆነ መጠየቁ ችግር የለዉም። ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ እጅ መስጠትና ፈልፍሎ አለመጠየቅ እንደ ሰሃቦች ሁሉ የሙሉ አምልኮትና ኢማን ዉጤት ነዉና የተሻለዉ ይህ ነዉ።

**47 አላህ (عزّ وجلّ) (ከመልካም ነገር የሚያገኝህ ከአላህ ችሮታ ነው። ከመከራም የሚደርስብህ ከራስህ (ጥፋት የተነሳ ነው) ማለቱ ምን ማለት ነው?** እዚህ ላይ መልካም የተባለው ፀጋ ማለት ሲሆን መጥፎ በማለት የተፈለገው ደግሞ ችግሮችና ፈተናዎች ማለት ነው፡፡ እናም ሁሉም ከአላህ (عزّ وجلّ) የተወሰኑ ነገሮች ናቸው፡፡ መልካም ነገርን እሱ ያሣመረዉ የሱ ትሩፋቱ ነዉና ወደ አላህ (عزّ وجلّ) እናስጠጋለን፡ መጥፎዉን ደግሞ እሱዉ እራሱ ለሚያውቀው ጥበቡ የፈጠረዉ ነው፡ በጥበቦቹ መልካምነቱ ይገለፃል፡፡ አላህ መጥፎን ነገር ፈፅሞ አይሰራም፡፡ ተግባሩ ሁሉ መልካም ነዉ፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) **(ኸይር/መልካም ነገር የተባለ ሁሉ በእጆችህ ነው መጥፎዉ ወዳንተ አይደለም)** ብለዋል፡፡ የሰዎች ተግባር ከመተግበራቸው አንፃር ታይቶ የእነሱ ተግባር ነው ቢባልም ከመፍጠር አኳያ ሲታይ ደግሞ የአላህ ፈጠራ ነው፡፡ አላህ (عزّ وجلّ) (ያ! የሰጠ ሰው እና ጌታውን የፈራ በበጎይቱም እምነት ያረጋገጠ ለገሪቱ ስራ እናዘጋጀዋለን /እናገራዋለን/። ያ! የሰሰተ ሰው እና የተብቃቃዉ (በራሱ የተመካ)፤ በበጎይቱም እምነት ያስተባበለ፤ ለመከራ ሥራ እናዘጋጀዋለን /እናገራዋለን።) ብሏል።

**48 እገሌ ሰማዕት/ሸሂድ/ ነው ወይም ሰማዕት/ሸሂድ ሆነ/ ማለት ይፈቀዳልን?** ከሙስሊሞች መካከል ለአንድ ሰው ለይቶ ሰማዕትነትን መበየን /ሰማዕት ነው ማለት የጀነት ነው ከማለት የተለየ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሱና አቋም አራማጆች ነቢዩ (ﷺ) የጀነት ነው ወይም የእሳት ነው ያሉት ሰው ሲቀር አንድን ሰው ለይቶ የጀነት ነው ወይም የእሳት ነው ማለት አንችልም፡፡ ምክኒያቱም የዉስጥ አዋቂዉ አላህ ነዉና፡፡ ያ ሰዉ በምን ላይ እንደሞተ እዉቀቱም የለንምና፡፡ የሰው ልጅ ደግሞ ኻቲማዉ/መጨረሻዉ ነው የሚታየው፡፡ የሰዉን ኒያም የሚያውቀዉ አንድ አላህ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም መልካምን ለሰራ መልካምን ስንመኝ፤ መጥፎን ለሰራ ደግሞ ቅጣትን እንፈራለታለን፡፡

**49 አንድን ሙስሊም የሆነን ሰው ለይቶ ከሃዲ ነው ማለት ይቻላልን ?** ለዚህ የሚያበቃው ተግባር በገሃድ እስካልታየና ምክኒያቶች እስካልተወገዱ ድረስ በክህደት፤ በሽርክም ሆነ በንፍቅና አንድን ሙስሊም የሆነን ሰው መግለፅ ክልክል ነው። የሰዉ ዉስጡን ለአላህ ብቻ እንተዋለን።

**50 ጦዋፍን ከከዕባ በቀር በሌላ ቦታ ማድረግ ይቻላልን?** በምድር ላይ ከተከበረው ከአላህ ቤት ከከዕባ ሌላ አንድም መሬት እንዲጦወፍ የሚፈቀድበት ቦታ የለም። የትኛዉንም ቦታ ምንም ያህል ክብር ቢኖረው ከመካ ጋር ማወዳደር አይቻልም። ከከዕባ በቀር ሌላን ቦታ በአክብሮት መልክ የጦወፈ ሰው አላህን (ﷻ) የከለከለውን ነገር በመፈፀም ወንጅሏል።

# የልብ ተግባራት

አላህ ልብን ንጉስ አድርጎ ፈጠረና ሌሎች አካላትን የሱ ሰራዊት አደረጋቸው:: ንጉሱ ካማረ ሰራዊቱም ማማሩ አይቀርም:: ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ « በየአካላችን ውስጥ አንዲት ልማጭ ስጋ አለች:: እሷ ካማረች አካላችን ሁሉ ያምራል:: እሷ ከተበላሸች አካላችን ሁሉ ይበላሻል :: እሷም ልብ ናት » ብለዋል:: ልብ የእምነትና የአላህ ፍራቻ ወይም የክህደት የንፍቅናና የሺርክ ቦታ ነው:: ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ {ወደ ልባቸው እያመለከቱ ‹‹ተቅዋ የአላህ ፍራቻ ቦታው እዚህ ውስጥ ነው } ብለዋል::

- ኢማን ማለት በውስጥ የሚታመን፤ በአንደበት የሚነገርና በአካል የሚተገበር ነው:: እናም ልብ ከውስጥ አረጋግጦ ያምናል:: ከዚያም የምስክርነት ቃሉን ምላስ እንዲናገር ያደርጋል:: ከዚያም ልብ ውስጣዊ ስራውን ማለትም አላህን ማፈቀር፤ እሱኑ መፍራት፤ ከሱው ተስፋ ማድረግንና የመሳሰሉትን ውስጣዊ ተግባራት ያከናውናል::ምላስ በዚክር ና በቁርአን ይንቀሳቀሳል:: አካላት በሩኩዕ፤ በሱጁድና በሌሎችም ውጫዊ መልካም ተግባራት ይውላሉ:: አካል ሁልጊዜም የ;ልብ ተከታይ ነው:: በልብ ያለ ነገር ሁሉ በሆነ ነገር ሳይም ቢሆን በአካል ላይ በግልፅ መንፀባረቁ አይቀርም::

- የልብ ተግባራት የሚባሉት ከልብ ጋራ በከፍተኛ ደረጃ ትስስር ያላቸውን ነገሮች ሁሉ ናቸው:: ከልብ ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎች በአላህ ማመን ነው:: በተጨማሪም ለአላህ የሚያሳይ ልባዊ ፍቅር፤ ፍራቻ፤ በሱ ላይ ተስፋ ማሳደር፤ ወደ እርሱ መመለስ፤ በእሱ ላይ ብቻ መመካት፤ ለእሱ ብሎ መታገስ ፤ በእሱ እርግጠኛ መሆን ኹሹዕ እና መሰሎች ተግባራት የሚሉት ናቸው::

- የልብ ተግባራት የሆኑ ነገሮች ሁሉ ተቃራኒዎቻቸው የልብ በሺታዎች ናቸው:: ለምሳሌ የፍፁምነት ተቃራኒው የዩይኝ/ልታይባይነት/ ነው ፤ የእርግጠኝነት ተቃራኒው መጠራጠር ነው:: የውዴታ ተቃራኒው ጥላቻ ነው፤ወ.ዘ.ተ :: ልቦቻችንን ችላ ካልናቸውና መንከባከብ ከተውቸው ወንጀሎች ይረባረቡባቸውና ድራሻቸውን ያጠፏቸዋል::

ነብዩ ቲርሚዚ በዘገቡተ ሐዲስ ‹‹ የሰው ልጅ አንዲት ስህተት ሲፈፅም በልቡ ላይ ነጥብ ትቀመጣለች :: ከዚያም ወደ አላህ ከተመለሰና የአላህን ምህረት ከጠየቀ ትፀዳለች:: ከደገመ ግን ይጨምርበታል:: ከዚያም ከደጋገመው ነጥቡም ይጨምርበታል:: ይኼው ሂደት እሷ እስከምትቆጣጠረው ድረስ ይቀጥላል:: ይህም ያ ቁርአን (ይከልከሉ፤ ይልቁንም በልቦቻቸው ላይ ይሰሩት የነበሩት (ኃጢአት) ደገደገባቸው፤› በማለት የጠቀሰው ራን የተባለው ነው›› ብለዋል::

ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስም ‹‹ፊትናዎች በልቦናዎች ላይ እንደሰሌን ገመዶች አንዳንድ እያሉ በልቦናዎች ላይ ያርፋሉ:: እሺ አሚን ብሎ የተቀበላቸው ልብ ዉሰጥ ጥቁር ነጥብ ሁነው ይቀመጣሉ:: እንቢ አልቀበልም ባለ ልብ ውስጥ ደግሞ ነጭ ሆነው ይቀመጣሉ:: በሁለት ልቦች ላይ እስከምትሆን ድረስ ፦ በነጭ ልብ ላይ እንደ ሶፋ ጋራ ጠንካራ ወይም እንደ ብር ንፁህ በመሆን ምድርና ሰማይ እስካሉ ድረስ በየትኛውም ፊትና ጉዳት ሊደረስበት የማይችል:: ሌላው አመዳማ ጥቁር እንደ ተዘቀዘቀ የውሃ ኩባያ ሆኑ ጥሩንና መጥፎ ሳይ ለይ በስሜቱ የሚሰጠው ብቻ ተቀባይ እስከሚሆን ድረስ ›› ብለዋል::

- ልባዊ አምልኮቶችን ማውቅ አካላዊ ተግባራትን ከማወቅ የበለጠ በማንም ሰው ላይ ግዴታ ይሆናል:: ምክንያቱም ልባዊ አምልኮቶች ዋናዋናዎቹ ሲሆኑ አካላዊ አምልኮቶች ደግሞ የእነሱ ቅርንጫፎች፤ለእነሱ ማሙያዎች ና የእነሱ ውጤቶች በመሆናቸው ነው:: ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ አላህ ወደ አካላችሁም ሆነ ወደ ንብረታችሁ አይመለከትም :: ግና ወደ ልቦቻችሁና ተግባራችሁ ይመለከታል›› ብለዋል:: ልብ የእውቀት ማጠራቀሚያ እና የምርምር ማካሄጃ ቦታ ነው:: ለዚህም ነው በአላህ ዘንድ በሰዎች መካከል ማበላለጥ የሚቻለው በልቡ ውስጥ በሰረፀ ኢማንና ኢኽላስ መሰረት የሆነው:: ሐሰኑ-ልበከሪ « በጌታየ እምላለሁ አቡበክር ሰዎችን በሶላትም ሆነ በፆም

አልቀደማቸውም:: አቡበክር ከሰዋች የበለጠው በልቡ ውስጥ በሰረፀው ብርቱ እምነት ብቻ ነው::) ብለዋል::

◗ የልብ ተግባራት ከአካላት ተግባራት በብዙ ምክንያቶች ይበልጣሉ:: 1) የልብ አምልኮ ሲበላሽ የአካልን አምልኮ ያበላሻል:: ምሳሌዉም ለዩልኝ መስራትን ይመስል ነው:: 2) የልብ ተግባራት ዋና መሰረት ነው:: በሙሆኑም በልብ ሳያከቡት በድንገት የተከሰተ እንቅስቃሴም ሆነ ንግግር በአላህ ዘንድ አያስጠይቅም:: 3) የልብ ተግባራት በጀነት ውስጥ ከፍተኛ ማዕረግን የምታስገኝ በመሆና ለምሳሌ ዙሁድን ይመስል ነው:: 4) የልብ ተግባራት ከአካል ተግባራት ይበልጥ ከባድ በመሆናቸው ነው:: ኢብኑል-ሙንከዲር «ራሴን ለማስተካከል አርባ አመት ጥሬ /ለፍቼ/ ነው የተስተካከለችልኝ» ብለዋል:: 5) የልብ ተግባራት ውጤታቸው ሲታይ በጣም የሚያምር በመሆኑ ነው:: ለምሳሌ የአላህን ውዴታን ይመስል ነው:: 6) ምንዳቸውም ከፍተኛ በመሆኑ ነው:: አቡ ደርዳእ ‹‹ አንዷት ሰዐት መመራመር /ማሰብ / ሌሊቱን ሙሉ ቆሞ ከማደር ይበልጣል» ብለዋል:: 7) የልብ ተግባራት ለአካል እንቅስቃሴዎች ሁሉ ቀስቃሽ በመሆኗዋ ነው:: 8) የልብ ተግባራት የአካል ተግባራት ዋጋን ከፍ ያደርጋል ያሳንሳልም አለበለዚያም ዋጋ ያሳጣልና ነው:: ለዚህ ምሳሌው ኹሹዕ ነው:: 9) የልብ ተግባሩ በአካል ከሚሰሩ አምልኮቶች አንዳንድ ጊዜ የምትተካቸው በመሆናቸው ነው:: ለምሳሌ ገንዘብ ሳይኖረው ሰደቃ ማሰብን ይመስል ነው:: 10) የልብ ተግባራት የምንዳው ግዝፈት ድንበር የሌለው መሆኑ ነው:: ለምሳሌ ትግስት 11) ማንም ሰው አካል ተግባሩን ቢያቆም ወይም ቢያቅተው ፅንኳኑ ምንዳው ቀጣይ በመሆኑ ነው:: 12) ከአካል ተግባራት በፊትና አብሮም መሆን በመቻሉ የሚሉት ናቸው::

◗ <u>ልብ አካል ገና ወደ ተግባር ሳይገባ በፊት በብዙ ሁኔታ ዋች ላይ ያልፋል:: እነሱም:-</u>

1) ለመጀመሪያ ጊዜ በአዕምሮ ዉስጥ ውል ማለት፤2) ስለ ጉዳዩ በቋሚነት ማሰብ፤
3) ጉዳዩን ላድርግ አላድርግ እያሉ በጭንቅላት ዉስጥ ማመላለስ:፤4) ጉዳዩን ወደ መተግበር መዘንበል፤ 5)ጉዳዩን ለመፈፀም በቁርጥ መወሰን በሚሉት የሚያልፍ ሲሆን፤ የመጀመሪያዎቹ ሶስቶች በኸይር ከሆነ አጅር የላቸውም ፡፡ በወንጀልም ከሆነ አያስጠይቅም::

አራተኛው በመልካም ነገር ከሆነ አንዷት ሐሰና ሲያሰጥ፤ በመጥፎ ነገር ከሆነ ደግሞ ምንም አይፃፍበትም:: ግን ይኸው አድጎ ወደ ውሳኔ ከበቃና ለመልካም ከሆነ ምንዳ አሉው:: በጥፋት ላይም ከሆነ ባይተገብረውም እንኳን ወንጀለኛ ይሆናል:: አላህ « እነዚያ በነዚያ ባመኑት ሰዎች ውስጥ መጥፎ ወሬ ንድትስፋፋ የሚወዱ ለእነሱ በቅርቢቱም በመጨረሻይቱም ዓለም አሳማሚ ቅጣት አላቸው አላህም ያውቃል፡፡ ፅናንተ ግን አታውቁም » ብሏል::

ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ «ሁለት ሙስሊሞች በጦራቸው ከተገባበዙ ገዳዩ ግለሰብም ሆነ ተገዳዩ ግለሰብ የእሳት ናቸው:: ሲሉ ገዳይስ እሺ ሟች ምን ሆኖ ነው አልኳቸውና እሱም ቢሆን ወንድሙን ለመግደል ጓጉቶ ነበርና ነው» ብለዋል::

ወንጀልን ለመተግበር ከወሰነ በኋላ ሳይተገብረው ከቀረ በአራት አይነት ይከፈላል ::

1) አላህን ፈርቶ የተወው ከሆነ ምንዳ አለው:: 2) ሰዎችን ፈርቶ የተወው ከሆነ መተው የነበረበት ለአላህ ብሎ ሲሆን ለሰዎች ብሎ በመተው ወንጀለኛ ይሆናል:: 3) ሁኔዎታች አልመቻችለት ብሎ የተወውም ከሆነ ለመስራት በመወሰኑ ይጠየቃል:: 4) ሁኔታዎችን ሁሉ ተግብሮ ተግባሩ ሳይሳካለት ከቀረም በትክክል ፅንደፈፀመው ተደርጎ ይጠየቅበታል:: ምክንያቱም ለመፈፀም የሚያበቁት ምክንያቶቹን ፈፅሞ ዋናውን ለመፈፀም አቅም አጥቶ መደናቀፍ ከላይ በተጠቀሰው ሐዲስ እንደተረዳነው ሁሉ ልክ እንደፈፀመው ይጠየቅበታል:: ተግባር ከውሳኔው ጋር ከሆነ ተግባሩ ቢቀድም ቢዘገይ ይጠየቅበታል::

መጥፎ ተግባር ፈፅሞ ወደፊትም ባመቸው ቀን ራሱ ያንኑ ተግባር ለማድረግ ከወሰነ ባይተገብረውም በተግባሩ ላይ ፅንደዘወተረ ይቆጠራል::

## ከልብ ተግባራት መካከል የተወሰኑት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው::

**እነሱም:-** ኒያ /ማሰብ/፣ መመኘት፣ መፈለግ ማለት ሲሆን:: የትኛውም ተግባር ያለ ንያ ብቃት ተቀባይነትም የለውም:: ነብዩ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «ተግባራት ሁሉ ያለ ንያ ብቃት የላቸውም:: ሰዋች የሚመነዱት ጿንደንያቸው ነው » ብለዋል::

ኢብኑ ሙባረክ (በኒያ የተነሳ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርሱ አነስተኛ ተግባራት ጿንዳሉ ሁሉ ጿንደዚሁም በኒያ የተነሳ ዋጋ የሚያጡ አያሌ ተግባራት አሉ) ብለዋል::

ፉዶይል «አላህ ከአንተ የሚፈልገው ኒያህን ነው:: እናም ኒያህ ለአላህ ከሆነ ኢኽላስ ይባላል:: ከዚህ ሌላ ከሆነ ግን የዩልኝ ፣ንፍቅና ሌላ ሌላም ይባላል:: » ብለዋል

ጠቃሚ ምክር ዓሊሞች ሲቀሩ ሰዎች ሁሉም ጠፍተዋል:: ተግባሪዎች ሲቀሩ ዓሊሞች ሁሉ ጠፍተዋል:: ፍፁማውያን ሲቀሩ ተግባሪዎች ሁሉም ጠፍተዋል:: ስለዚህ አላህን ለመገዛት ለፈለገ ሰው ሁሉ የመጀመሪያው ተግባር ኒያን መማር ነው:: ከዚያም ፍፁምነትን በትክክል በመረዳትና በማወቅ ኒያን ማስተካከል ነው:: ያለ ኒያ ተግባር አጉል ልፋት ነው:: ያለፍፁምነት ኒያ ማድረግም ይውልኝ ነው:: ጿምነት ሳይኖር ፍፁምነት ደግሞ ዋጋ ቢስ ነው::

ተግባራት ሶ ስት አይነት ናቸው:: 1) ወንጀሎች ናቸው:: ጿናም ኒያ ወንጀልን ወደ መልካም አምልኮ ተግባርነት አይቀይርም:: ከቶውንም መጥፎ ኒያ ከተጨመረበት ቅጣቱ ጿጥፍ ድርብ ይሆናል:: 2) የተፈቀዱ ነገሮች ናቸው:: የትኛውም የተፈቀደ ተግባር አንድ አይነት ወይም የተለያየ ኒያ ሊኖረው ይችላል:: ጿናም ከታሰበበት ወደ ኢባዳ ሊቀየር ይችላል ማለት ነው:: 3) አምልኮቶች ናቸው:: ጿነዚህ ተግባራት ለብቃታቸውም ሆነ አጅራቸውን ለማብዛት ኒያ የግድ ያስፈልጋቸዋል [1]::

አንድ ሰው በተግባሩ ለዩልኝ ካሰበ ተግባሩ ወንጀል ይሆንበታል:: ብሎም ወደ መለስተኛ ሺርክነት ደረጃም ይደርሳል:: እንደሁኔታው ከዚያም አልፎ ወደ ከፍተኛ ሺርክ ሊያድግ ይችላል::

እሱም ለሶስት ይከፈላል:: 1. በመጀመሪያ ለሰው ብሎ መስራት ሲሆን ይህ ተግባር ሺርክ ነው:: በዚህ እሳቤ የፈፀመው ኢባዳውም ባጢል ነው::

2.ተግባሩ ለአላህ ሆኖ የዩልኝ ስሜቱ ኋላ የመጣበት ከሆኑ የተግባሩ መጨረሻ" በመጀመሪያው ላይ ያልተመሰረተ ከሆነ ለምሳሌ ሰደቃን ይመስል መጀመሪያው ልክ ነው መጨረሻው ግን ባጢል ነው:: የተግባሩ መጨረሻው ከመነሻው ጋር የተያያዘ ከሆነ በሁለት መልክ ይታያል::

ሀ. የዩልኝን ከተከላከለ በተግባሩ ላይ ምንም ተፅዕኖ አያደርግበትም፡፡

ለ. ዩዩልኝን በደስታ ተቀብሎ የሚያስተናግድ ከሆነ ግን ተግባሩ ዋጋ ቢስ ውድቅ ነው::

3. ልታይ ባይነቱ ከተግባሩ በኋላ የተከሰተ ከሆነ ይህ አይነቱ ኒያ ምንም አይነት ተፅዕኖ አያሳድርም:: በተግባሩም ላይ ሆነ በተገበረው ላይ ጿዚህ ላይ ብዙ ልታይ ባይነትን

---

[1] ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹አንዲትን መልካም ተግባር ለመፈፀም ያሰበና ያልተገበረ ሰው አንዲት ሙሉ ሐሰና ይፅፍለታል። አስቦት ከተገበረው ደግሞ ከአስር እስከ ሰባት መቶና ከዚያም የበለጠ እጥፍ ድርብ ሆኖ ሊፅፍት ይችላል። መጥፎ ነገር አስቦ ሳይተገብር የቀረ ሰው አንዲት ሙሉ ሐሰና ይፅፍለታል። አስቦ ከተገበረው ደግሞ አንዲት ሙሉ ወንጀል አድርጎ ይመዘገብለታል›› ብለዋል።

ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስም ‹‹የዚህች ኡመት ምሳሌያቸው እንደ አራት ሰዎች ናቸው። አንዱ አላህ ገንዘብና እውቀት ሰጥቶት በእውቀቱ የሚሰራ ገንዘቡንም በአላህ መንገድ ላይ የሚያወጣው ነው። ሁለተኛው እውቀትን ሰጥቶት ገንዘብ ያልሰጠው ነው። ይህ ሰው እንደዚህ ሰው ገንዘብ በነበረኝ ልክ እንደ እሱ ነበር የምሰራበት የሚል ነው። አሉና ሁለቱም በምንዳ እኩል ናቸው ብለዋል። ሌላው ገንዘብ ሰጥቶት እውቀት የሌለውና ገንዘቡን ባልሆነ ቦታ የሚያውል ነው። አራተኛው እውቀትም ሆነ ገንዘብ ያልተሰጠው ግን ገንዘብ በነበረኝ ልክ አንድ ሶስተኛው ነበር የምበትነው እያለ የሚመኝ ነው። አሉና እነዚህ ሁለቱም በቅጣት እኩል ናቸው›› ብለዋል።

በዚህ ሐዲስ የተማርነው ሁለተኛው እና አራተኛው ሰዎች እንደ አንደኛውና እንደ ሶስተኛው በነበረን ብለው በማሰባቸው ብቻ ተሳክቶላቸው እንደተገበሩት አንደኛውና ሶስተኛው እኩል ተመነዱ። ኢብኑ ረጀብ የተባሉ ዓሊም በምንዳ እኩል ናቸው የሚለው በዋናው ክፍያ እንጂ በሚጨምረው ጉዳይ የተገበሩት ብቻ የሚለዩ መሆናቸውን ያመለክታል›› ብለዋል።

የሚመለከቱ ጉዳዩች አሉና ሁሉም ሙስሊም አውቋቸው ሊጠነቀቃቸው ይገባል፡፡
መልካም ስራውን ሲፈፅም ያሰበው የዚህች ዓለምን ደስታ ለማግኘት ብቻ ከሆነ ምንዳውም ሆነ ቅጣቱ በኒያው ልክ ነው፡፡
**እሱም በሶስት ይከፈላል፡፡ 1)** ለዚህ ተግባር ያነሳሳው ዱንያዊ ጆሳቤ ብቻ የሆነ ሲሆን ይኸውም ለገንዘብ ብቻ ብሎ ሶላት እንደሚያሰግድ ሰው ሲሆን ይህ ሰው ምንም አይነት ምንዳ የለውም ወንጀል ብቻ ነው የሚያከማቸው፡፡ ነብዩ አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ «የአላህ ፊት ከሚፈልጉበት ትምህርቶች ውስጥ የዱንያን ጥቅም ብቻ ጆሳቤ አድርጎ የተማረ ሰው የቂያማ ዕለት የጀነትን ሺታ ጆንኳን አያገኝም፡፡ **2)** ለአላህና ለዱንያ ለጥቅም ብሎ የሰራ ሰው ጆምነቱም ሆነ ኢኽላሱ የጎደለ ሰው ነው፡፡ የዚህም ምሳሌው ሐጂን ሲተገብር ንግድ አብሮ የነየተ ሰው ነው፡፡ የዚህ ሰውየ ምንዳው በኢኽላሱ ልክ ነው፡፡ **3)** ለአላህ ብቻ ብሎ ሰርቶ ለኑሮው የሚሆን ክፍያ የሚቀበል ሲሆን ይህ አይነቱ በተቀበለበት ደመወዝ ምክንያት በአኼራ ከሚያገኘው ምንም አይጎልበትም፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ **«ክፍያ ከተቀበላችሁባቸው ነገሮች ሁሉ ዋናው የአላህ መፅሐፍ /ቁርአን ነው»** ብለዋል፡፡
**ተግባራቸውን በፍፁምነት የሚያሰሩ ሰዎች የተለያዩ ደረጃዎች አሏቸው፡፡ 1)**ዝቅተኛው ሲሆን ይኸውም ተግባሩን የሚፈፅመው ምንዳ ለማግኘትና ከቅጣት ነፃ ለማውጣት ብሎ የሚተገብር ነው፡፡ **2)** መካከለኛው ነው አላህን ለማመስገንና ትዕዛዙን ለማክበር ብሎ የሚፈፅመው ነው፡፡ **3)** ከፍተኛው ሲሆን እሱም ተግባሩን ለአላህ ውዴታና ክብር ብሎ የሚሰራ ሲሆን ይህ የሲዲቆች[1] ደረጃ ነው፡፡
◗ **ተውባህ** /ንስሃ መግባት/ሁልጊዜም ግዴታ ነው፡፡ በስህተቶች ላይ መውደቅ የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ባህሪ ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ « **የአደም ልጅ ሁሉ ተሳሳች ነው ከተሳሳቾች ሁሉ የበለጠ ደግሞ ንስሃ ገቢዎች ናቸው** » ብለዋል፡፡
ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስም **«ባትወነጀሉ ኖሮ አናንተን አጥፍቶ ጆያጠፉ ከዚያ የአላህን ምህረት ጆየጠየቁ የሚምራቸው ሕዝቦች ይፈጥር ነበር»** ብለዋል፡፡
ንስሃን ማዘግየትና በወንጀል ላይ መቆየት ወንጀል ነው፡፡ ሰይጣን የሰውን ልጅ ከሰባት አንቅፋቶች በአንዱ ማደናቀፍ ይፈልጋል፡፡ በአንዱ ሲያቅተው ወደሌላው ይተላለፋል፡፡
**1)** የሺርክና የክህደት ጆንቅፋት፤**2)**ይህ ካልተሳካ በጆምነቱ ውስጥ ያልሆነ ነገር በማስገባትና ነብዩንና ባልደረቦቻቸውን መንገድ እንዳይከተል በማድረግ፤ **3)** ይህን ካልቻለ ታላላቅ ወንጀሎች በማሰራት፤ **4)** ይህን ካልሆነለት ትናንሽ ወንጀሎችን በማሰራት፤ **5)**ይህን ካልቻለ የተፈቀዱ ነገሮችን በማስበዛት፤ **6)** በዚህ ካልተሳካለት በላጭ ነገሮችን በማስተው ዝቅተኛ አጅር ያላቸውን በማሰራት፤ **7)** በዚህ ካልተሳካለት የሰውንም ሆነ የሰይጣንን ጋኒኖች በሱ ላይ በማሰማራት ነው፡፡
**ወንጀሎች ብዙ አይነቶች ናቸው፡፡ 1.** ታላላቅ ወንጀሎች ሲሆኑ ጆነሱም ዱንያዊ ቅጣት/ ለምሳሌ ግርፋት ግድያ ወይም በአኺራ ጆንደሚያስቀጣ ዛቻ፤ ቁጣ ጆርግማን ወይም ጆምነት የለውም የተባለበት ጉዳይ ነው፡፡
**2.** ትናንሽ ወንጀሎች ሲሆን እነሱም በአንደኛው ከተጠቀሱት በታች የሆኑት ናቸው ፡፡
**ጆዚህ ላይ ትናንሽ ወንጀሎችን ወደ ከፍተኛው ወንጀሎች የሚያደርሱ ብዙ ምክንያቶች**

---

[1] አላህ‹-እነሱ እነዚህ በዱካዬ ላይ ያሉ ናቸው፡፡ ጌታዬ ሆይ! ትወድልኝ ዘንድ ወደ አንተ ቸኮልኩ አለ፡፡በማለት-›ሙሳ የተጣደፉበት ምክንያት የአላህን ትዕዛዝ ለሞፌፀም ብቻ ሳይሆን ውዴታውን ለማግኘት ነበር፡፡ ለወላጆች መልካም መዋልን የዚሁ ተመሳሳይ ነው፡፡
**ዝቅተኛው** የወላጆችን ሀቀ መርገጥ ቅጣት ጆንዳያገኘውና የወላጆቹን ማከያሰተ አጅር ለማግኘት ብሎ ወላጆቹን የሚንከባከብ ነው ፡፡
**መካከለኛ**ው ደግሞ የአላህን ትዕዛዝ ለማክበርና ያሳደጉበትን ለአንተ መገኙት ውለታ ለመመለስ ብሎ ወላጆቹን የሚንከባከብ ነው፡፡
**ከፍተኛው** ደግሞ የአላህን ትዕዛዝ ለማክበርና ነብዩ ለማክበር ብሎ የሚንከባከብ ነው፡፡

አሉ፡፡ ዋናዋናቹ በጥቃቅን ወንጀሎች ላይ መዘወተር፤ እነሱን መደጋገም እነሱን አቃሎ ማየት በወንጀሉ መኩራራት ወይም ወንጅሉን ግልፅ አድርጎ በይፋ በአደባባይ መስራት ነው፡፡ ከሁሉም ወንጀሎች ተውባ ማድረግ ይቻላል፡፡ ፀሐይ በመግቢዋ እስካልወጣች ወይም የተውበተኛው ሩህ ጣረሞት ላይ እስካልሆነች ድረስ ተውባ ማድረግ ይቻላል፡፡ የትክክለኛ ተውበት ባለቤት ምንዳው ወንጀሉ ሰማይ ቢደርስ ወደ ደረጃ መቀየር ነው፡፡ ተውባ ተቀባይነት እንዲኖረው ወሣኝ መስፈርቶች አሉ፡፡ እነሱም፡- 1) ወንጀልን መተው. 2)ባለፈው ነገር መፀፀት 3) ወደፊት ላለመመለስ ቁርጥ ዉሳኔ ማድረግ ሲሆን ወንጀሉ ከፍጡር ጋር የተያያዘ ከሆነ ደግሞ የሰዎችን ንብረት መመለስ ግድ ይላል[1]፡፡ ከሁሉም ወንጀሎች ተዉባ ማድረግ የሚፈለግና የተፈቀደ ነው፡፡ ፀሐይ በመግቢያዋ እስከምትወጣ ወይም ሩህ ጉሮሮን እስከምትተናነቅ ድረስ የተውባ በሩ ክፍት ነው፡፡ የቶበተ ሰው ተዉበቱ ትክክለኛ ከሆነ ወንጀሉ ከብዛቱ አንፃር ሰማይ ቢደርስም እንኳን መጥፎ ሥራዉ ወደ መልካም ነገር ይለወጥለታል፡፡

ሰዎች ወደ አላህ ንስሃ ከመግባት አኳያ አራት አይነት ናቸው፡፡ 1) እስከመጨረሻድረስ ቶብቶ የሚቀጥልና ሰዎች ሊጠነቀቁት ካማይችሉት ትቃቅን ስህተቶች በስተቀር ወደ ነበረበትም ሆነ ወደ ሌላ ወንጀል የማይመለስ ነው፡፡ ይህተግባር ኢስቲቃማ ይባላል፡፡ ይህን የፈፀመ ሰዎም ትክክለኛ ንስሃ የገባ ይባላል፡፡ ይህ አይነት አቋም ያላት ነፍስ የተረጋጋች ነፍስ ትባላለች፡፡ 2)መሰረታዊ የአምልኮ ተግባሮችን እየፈፀመ ሆን ብሎ ሳይሆን በልዩ ልዩ ወንጀሎች ይዘፈቃል፡፡ ሆኖም በተሳሳተ ቁጥር እራሱን ይወቅሳል፡ ፡ ይህ አይነት አቋም ያላት ነፍስ ራሷን ወቃሽ ትባላለች፡፡ 3) የተወሰነ ጊዜ ቶብቶ ና ቀጥ ብሎ ከጊዜ በኋላ በአንዳንድ ወነወጀሎች ላይ ይወድቃል፡፡በጥቂት ወንጀሎች ላይ ቢጠቃም ብዙ ወንጀሎችን ተቋቁሞ ያልፋል፡፡ ወንጀሎችንም እንፈፀመ ይፀፀታል ወደፊት ላለመመለስ ቃል ይገባል፡፡ ይህ አይነት ነፍስ ደግሞ ተጠያቂነት ያላት ነፍስ ትባላለች፡፡ ይህ አይነቱ ሰው በማዘግየቱና ነገ ዛሬ በማለቱ መጨረሻው አደጋ ነው፡፡ ምክናየቱም ሳይቶበብት ሊሞት ይችላልና ነው፡፡ የተግባሮች ምንነት የሚወሰነው ከመጨረሳው አኳያ ነዉና ነው፡፡ 4)የተወሰነ እድሜዉን ቶብቶ ከዚያ በኋላ በልዩልዩ ወንጀሎች ስጥ የሚዘፈቅ ነው፡፡ ከዚያም በስህተቱ የማይፀፀትና በጥፋቱ የማያምን ነው፡፡ ይህ አይነት ነፍስ ያለው ሰው ባለመጥፎ ነፍስ ይባላል፡፡

◗ <u>ሲድቅ እውነተኝነት</u> ይህ ተግባር የተግባሮች ሁሉ ምንጭ ነው፡፡ ሲድቅ የሚለው በስድስት ነገሮች ሊታይ ችላል፡፡ 1)በአንደበት ላይ፤ 2)በአስተሳሰብ ላይ፤ 3)በዉሳኔ ላይ፤ 4)ቃል በመፈፀም ጊዜ፤ 5)በተግባር ጊዜ ይህ ተግባሩ ከዉስጡ ጋር መጣጣሙ ነው፡፡ ይህ ምሳሌው በሶላት ዉስጥ የሚታየው ኹሹዕ ነው፤ 6)የዲን ተግባራትን በሙሉ በመተግበር እውነተኛ መሆን ነው፡፡ይህ ደረጃ የደረጃዎች ሁሉ ከፍተኛው ነው፡፡ ምሳሌዉም አላህን በመፍራት፤ተስፋ በማድረግ፤በማክበር፤ችላ በማለት፤ቀደርን አሚን ብሎ በመቀበል፤በአላህ በመመካት፤ በመውደድና በሌሎችም ልባዊ ተግባራት ሁሉ ናቸው፡፡ እናም በእነዚህ ሁሉ እውነተኛ የሆነ ሰው ትክክለኛው እውነተኛ ማለት እሱ ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (እውነተኛ ሁኑ እውነተኝነት ወደ መልካም ተግባር ይመራል፡፡ መልካም ተግባር ደግሞወደ ጀነት ያደርሳል፡፡ የሰው ልጅ አላህ ዘንድ በእውነተኝነት

---

1 አህመድ በዘገቡት ሐዲስ መዝገቦች አላህ ዘንድ ሶስት ናቸው፡፡
አንደኛው አላህ ምንም ዋጋ የ ማይሰጠው፤
ሁለተኛው አላህ አንድንም ነገር የማይተውለት፤
ሶስተኛው ደግሞ ፈፅሞ የማይምርው ናቸው፡፡ ያ ! የማይምርው ወንጀል በአላህ ማጋራት ነው፡፡ ምንም ዋጋ የማሰጠው ደግሞ በሱና በፔጣሬው መካከል ያለ ወንጀል ነው ምክንያቱም አላህ ከፈለገ ሊምረውና ሊያልፈው ስለሚችል፡፡ ትንሽም የማይተውለት ወንጀል ደግሞ ፍጡሮች እርስ በራሳቸው በፍጡሮች መካከል የሚበዳደሉት ነው፡፡

እስከሚፃፍ ድረስ እውነትን ከማፈላለግና ከመናገር አያቋርጥም፡፡)
እውነቱ የተደባለቀበት ሰው ከዚያም በትክክል የፈለገ ብዙዉን ጊዜ አላህ ይሰጠዋል፡፡ ባይደርሰበትም አላህ ይቅር ይለዋል፡፡ የዚህተቃራኔው ዉሼት ነው፡፡ ዉሼት በመጀመሪያ ጊዜ በምላስ ላይ ነው የሚንፀባረቀው ፡፡ከዚያም የምላስን ተግባር እንዳበላሸ ሁሉ ወደ መላ አካሉ ይሰራጭና ተግባራቱን ሁሉ ያበላሻል፡፡ ከዚያም ሁሉ ተግባሩ ሁሉ የተበላሸ ይሆናል፡፡

**መውደድ:-** አላህን፤ ነብዩን፤ ሙእሚን ወንድሞቹን በመውደድ የእምነት ጣዕም ይገኛል። ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ « ሶስት ነገሮች በውስጡ ያሉለት በእነሱ የእምነትን ጣዕም አግኝቷል። አላህና መልዕክተኛውን ከእነሱ ውጪ ከሆነ ሁሉ አብልጦ መውደድ፤ ሰውን ሲወድ ለአላህ ብቻ ብሎ መውደድ አላህ ከክህደት ነፃ ካዳረገው በኋላ ወደ ክህደት መመለስን ወደ እሳት እንደመወርወር ያህል መጥላት ነው። » ብለዋል። የውዴታ አትክልት በልቡ የተከለና የዘራ ከዚያም በኢኽላስና ነብዩን መከተል ውሃ ያጠጣህ እንደሆነ የፍሬ አይነቶችን ታፈራለች ፡፡ በአላህ ፈቃድሞ በየጊዜው ፍሬ ትሰጣለች። ማፍቀር አራት አይነት አለው። 1) አላህን መውደድህ ነው፡፡ እሱም የእምነትህ ዋና መሰረት ነው፡፡ 2)ለአላህ ብሎ መውደድና ለአላህ ብሎ መጥላት ነው፡፡ ይህም ግዴታ ነው፡፡[1] 3) ከአላህ ጋር መውደድ ነው፡፡ ይኸውም ከአላህ ጋር ሌላን ማጋራት ነው፡፡ ይህም አጋሪዎች አምላኮቻቸውን መውደዳቸውን ይመስል ነው፡፡ ይህ ክፍል የሺርክ ዋናው ምንጭ ነው፡፡ 4) የተፈጥሮ ማፍቀር ነው፡፡ እሱም አባቶች ልጆቻቸውን፤ ልጆች አባቶቻቸውን፤ ባል ሚስቱን፤ ሚስት ባሏን ፤ሰዎች ምፋብን መውደድ ይመስል ነው፡፡ ይህ ክፍል የተፈቀደ ነው፡፡ አላህ እንዲወድህ ዱኝያን ችላ በል ፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ኢብኑ ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ «ዱኝያን ችላ በል አላህ ይወድሀልና» ብለዋል።

**ተወኩል:-** የሚፈልጉትን ለማግኘት ከጠሉት ለመጠበቅ በአላህ ከማመንና ምክንያቶችን ሁሉ ከፈፀሙ በኋላ ወደ አላህ መጠጋትና በአላህ ላይ መመካት ነው። ልብን ወደ አላህ አለማስጠጋት ተውሂድን ይነካል። ምክንቶችን አለመፈፀሙ ደግሞ

---

[1] ከወላዕና ከበራዕ አንፃር ሰዎች ለሶስት ይከፈላሉ፡፡ ሀ-ያለምንም ጥላቻ በንፁህ መውደድ ሲሆን፡- እነሱም ንፀህ አማኞች፤ነቢያት፤ፃድቃን ሲሆኑ የእነዚህም ግንባር ቀደም ነቢዩ ሙሐመድ፤ሚስቶቻቸው፤ ሴት ልጆቻቸውና ባልደረቦቻቸው ናቸው፡፡ ለ-ፈፅሞ የማይወደዱና ብሎም ከእነሱ ነፃ መሆን አስፈላጊ የሚሆንበት ነው፡፡ እነሱም ከመፅሐፍ ባለቤቶች መካከል፤አጋሪዎች፤ ሙናፊቃንና ከሃዲዎች ናቸው፡፡ ሐ-በአንድ በኩል ሲወደድ በሌላ በኩል ደግሞ የሚጠላ አካል አለ፡፡ እሱም በልዩ ልዩ ስህተቶች ዉስጥ የተዘፈቁ አማኞች ሲሆኑ ባላቸው መሰረታዊ እምነት መጠን ሲወደዱ በፈፀሙት ስህተት መጠንም ይጠላሉ፡፡

ከሃዲዎችን መውደድ ማለት ደግሞ:- ለሁለት ይከፈላል፡፡

1-ከኢስላም የሚያወጣ መውደድ ሲሆን፡- እሱም፡- ከሃዲዎችን -ሙስሊሞችን-እንዲያጠቁ መርዳት፤ወይም ከሃዲዎችን ከሃዲዎች ናቸው አለማለት፤ወይም በእነሱ ክህደት ላይ ግልፅ አቋም አለመውሰድና መጠራጠርን የመሳሰለው ነው፡፡

2- ከዚህ በታች የሆኑ ታላላቅ ወንጀሎች፤ክልክልና የተጠሉ ነገሮች ሲሆኑ፡-ይህዉም፡-ከሃዲዎችን በበአላቸው ላይ በመገኘት መጋራት፤ ለበዐሉ እንኳን አደረሳችሁ ማለት፤ወይም በልዩ ልዩ ተግባሮች ላይ ከእነሱ ጋር መመሳሰል ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ጦረኛ ያልሆኑት ከሃዲዎች ከሙስሊሞች ጋር የሚደረጉት መልካም ማህበራዊ ትብብሮችና ከሃዲዎችን መጥላት በሚለው መሰረታዊ ነጥብ መካከል በብዙ ሰዎች ላይ የተደበላለቀ ስዕል ይፈጥራል፡፡ ሆኖም ለዚህ አይነቱ መዘረቅ በመሀከላቸው ያለዉን ልዩነት በደንብ ለይቶ ማየት ያስፈልጋል፡፡ የዉስጥ ፍቅር ሳይኖር ከእነሱ ጋር መልካም ማህበራዊ ህይወት መመስረት፤ ከእነሱም መካከል ለችግረኞች ማዘን፤ለእነሱ በመተናነስ ሳይሆን አንደበትን ማለስለስ፡፡ አላህ በቁርአን እንዲህ (ለእነዚያ በሃይማ ት ላልተዋጓችሁ ከአገሮቻችሁም ላላስወጧችሁ ከሓዲዎች መልካም ብትውሉላቸውና ወደ እነርሱ ፍትህ ልትውሉላቸው አላህ አይከለክላችሁም፡፡) ያለበት ነጥብ ነው፡፡

እነሱን መጥላትና አለመውደድን በተመለከተ ደግሞ አላህ እንዲህ አለ (እናንተ ያመናችሁ ሰውች ሆይ !ጠላቶቼንና ጠላቶቻችሁን ወዳጆች አድርጋችሁ አትያዙ፡፡ የመጣላችሁን እምነት የካዱ ሲሆኑ ውዴታን ለእነሱ ታደርሳላችሁ።) በማለት ያዘዘው ነው፡፡ ይኸዉም ነቢዩ ሙሐመድ ከመዲና አይሁዶች ጋር እንዳደረጉት ስምምነት አይነት እነሱን ከመጥላት ጋር ፍትሃዊ ሁነው መኖር ይቻላል፡፡

የአእምሮ ችግር መኖሩን ያመለክታል፡፡ የተወኩል ቦታው ስዓቱ ከተግባሩ በፊት ነው፡፡ ተወኩል የየቂን ውጤት ነው፡፡ ክፍሎቹ ሶስት ናቸው፡፡

1) ግዴታ የሆነው ተወኩል አላህ ብቻ በሚችለው ነገር ላይ ለምሳሌ በሺተኛን ከማዳን ይመስል በአላህ መጠጋት፡፡

2) የተከለከለው ለሁለት ይከፈላል እሱም ፡- ሀ) ታላቅ ሺርክ ውስጥ የሚገባው ሲሆን እሱም ሁሉን ነገር በምክንያቶች ላይ ብቻ ማያያዙን ምክንያቶች ብቻቸውን ውጤት ያመጣሉ ብሎ ማመን ነው[1]፡፡ ለ) አነስተኛው ሺርክ ሲሆን እሱም ቀልቡን ምክንያት ከመሆን አልፎ ሌላን ነገር ሊያደርግ ይችላል፡፡ ብሎ ማመን ነው፡፡

3) የሚፈቀደው የተወኩል አይነቶች ሲሆኑ አንድ ሰው ሌላውን ማድረግ በሚችለው ነገር ላይ ለምሳሌ መሸጥ መግዛት በመሳሰሉ ነገሮች መወከልና ነው፡፡ ሆኖም በአላህ ላይ ከዚያም በአንተ ተመካሁ አይባልም፡፡ በዚህ ተግባር ላይ ወክየሃለሁ ነው የሚባለው፡፡

**ሹክር ፡-** ነብዩ አህመድ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ በልቶ የሚያመሰግን ፆሞ እንደሚታገስ ነው፡፡ ብለዋል፡፡ ልቦና ውስጥ ከእምነትህ ማመስገን ማለት የአላህ ውለታ በሰዎች ምላስ ላይ በማመስገንና በአካላቸው ላይ በአምልኮ ሲገለፁ መታየቱ ነው፡፡ እናም ምስጋና በልብ፤ ምላስና በአካል የሚገለፅ ከፍተኛ ተግባር ነው፡፡

**ትዕግስት:-** ትዕግስት ማለት የደረሰበትን ችግር ከአላህ ሌላ ለማንም አካል ስሞታን አለማቅረብ ነው፡፡ ‹‹ ታጋሾች መንዳቸውን የሚሰሰጡት ያለግምት ነው ›› ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ለመታገስ የተጣጣረ አላህ ትግስት ይሰጠዋል፡፡ ማንም ሰው ከትግስት የበለጠና የሰፋ የተሰጠ የለም፡፡ ዑመር በምንም ነገር ስፈተን አላህ አራት ፀጋዎችን ይሰጠኛል፡፡ በዲኒየ ላይ አለመሆኑ፤ በጣም የከበደና ከአቅም በላይ አለመሆኑ፤ አሚን ብየ እንድቀበል መደረጉ፡፡ ከአላህ ምንዳ ተስፋ እንዲደረግለት ማድረጉ ነው፡፡

ትዕግስት ብዙ ደረጃ አለው፡፡

ዝቅተኛው እሱም የደረሰውን እየጠሉ ማሰሞትን መተው ነው፡፡

---

[1] ምክንቶያቶችን መስራት ከተወኩል ጋር ይቃረናሉን ይህ ጉዳይ ብዙ ክፍል አለው ፡፡

1-ያለነበረን ጥቅም ለማስገኜት የሚፈፀም ምክንያት ሲሆን ይኸዉም ለሶስት ይከፈላል፡፡ ሀ)አስተማማኝ ምክንያት ሲሆን ለምሳሌ ልጅ ለመውለድ ማግባትን ይመስል ነው፡፡ይህን አይነት ምክናየት መተው በአላህ መመካት ሳይሆን እብደት ነው፡፡ ለ)እርግጠኛ ያልሆኑ ምክናየቶች ሲሆኑ ለማሳሌ በበረሃ የሚጓዝ ስንቅን መያዝን ይመስል ነው፡፡ ይህን አይነት ምክናየት መተዉ የተወኩል አካል አይደለም፡፡ከቶዉንም ስንቅ መያዙ ታዞበታል፡፡ምክንያቱም ነቢዩ በጉዟቸው ላይ ስንቅ ይይዙ፤ ወደ መዲናም ሲሄዱ መሪ ተከራይተው ነበርና ነው፡፡ ሐ)በግልፅ ሳይተማመኑበት ዉስጥዉስጡን ወደ ምክናየቱ የሚያስጠጋ የሚያስመስል ምክንያት አለ፡፡ ምሳሌውም ሀብት ለማግኜት የሚደረጉ ረቂቅ እቅዶችን ይመስል ነው፡፡ይህም ቢሆን ከተወኩል አይወጣም፡፡ እንዴዉም አለመስራት ከተወኩል ጋር ምንም ግንኙነት የለዉም፡፡ዑመር ብን አልኸጧብ በአላህ የሚመካ ያ! አዝርዕቱን መሬትላይ በትኖለዉጤቱ በአላህ ላይ የሚመካ ነው፡፡)ብለዋል፡፡

2)ያለን ነገር ለመጠበቅ የሚፈፀም ምክንየት ነው፡፡ለምሳሌንፁህ ገንዘብ ያገኜ ሰው ይህ ገንዘብ በማስቀመጡ ከተወኩል አይወጣም፡፡በተለይም ቤተሰብ ካለው፡፡ምክንያቱም ነቢዩቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የበኒ ነዲርን ቴምር ሺጠው ለቤተሰቦቻቸው የአንድ አመት ቀለብ ያስቀምጡ ነበርና፡፡

3)ያልተከሰተን ችግር ለመከላከል የሚፈፀም ምክንያት ነው፡፡ተወኩል ለማድረግ ሊከላከሉ የሚችሉ ምክነየቱችን መተው ቅድመ ሁኔታ አይደለም፡፡ ምሳሌው የጦር ልብስ መልበስን፤ግመልንማሰርና ከዚያም በአላህ መመካትይመስል ነው፡፤

4)የተከሰተን ችግር ለማስወገድ የሚፈፀሙ ምክንየቶችን ይመስል ነው፡፡ ይህም ሶስት ክፍል አለው፡፤ ሀ)አስተማማኝ የሆነ ለምሳሌ ጥምን ለመቁረጥ ዉሃን መጠጣት ይነቱን ይመስል ነው፡፡ይህ አይነቱን ምክናየት መተው በአላህ መመካት አይደለም፡፡ ለ) ችግሩን ለማስወገድ የሚጠረጠር የሆነን ነገር መጠቀም ለምሳሌ ዋገምትንና መሰሉን የህክምና ምክናየቶችን መጠቀም ነው፡፡ ይህ አይነት ምክናየት መጠቀም በአላህ ከመመካት ጋር አይጋጭም፡፡ ነቢዩ ታክመዋል ሌላዉንም እንዲታከም አዝዘዋል፡፡ ሐ) መከላከሉእርግጠኛ ያለሆነን ነገር መውሰድ ነው፡፡ ለምሳሌ በጤናላይ ያለ ሰው መከላከያ ክትባትን መውሰድ ይመስል ነው፡፡ ይህን አይነት ተግባር መጠቀም በአላህ የመመካትን ምሉዕነት ይፃረራል ፡፡

መካካለኛው ደግሞ የደረሰበትን ነገር አሚን ብሎ ተቀብሎ አለማስሞት ነው።
ከፍተኛው የትግስት ክፍል በደረሰበት ችግር ላይ ከማስሞት ይልቅ አልሐምዱሊላህ ብሎ አላህን ማመስገን ነው። ተበድሎ በበዳዩ ላይ ዱዓ ያደረገበት ሰው በራሱ ስለተበቀለ ታገሰ አይባልም። ትዕግስት ሁለት ዓይነት ነው።
1. አካላዊ ትዕግስት ሲሆን እዚህ ላይ ስለዚህ ክፍል በሰፊው ማውሳት አንፈልግም
2. ስሜትንና የግል ፍላጎትን በማሸነፍ የሚደረገው መንፈሳዊ ትግስትን ነው[1]።
የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ኑሮው ውስጥ የሚያጋጥሙት ችግሮች ከሁለቱ አንዱ ነው።
ሀ) ስሜቱን [2]የሚስማማ ሲሆን ይህን ለመውጣት የአላህን ሐቅ ጠብቆ፤ አላህን አመስግኖ፤ ከእሱ ትእዛዝ ውጪ እንዳይሆን ተጠንቀቀ ለመፈፀም መታገስ ሲሆን ክፍሉ ግን ግዴታው የግዴታዎቹን ለመወጣት የሚያስችለውን ያህል ነው።
ለ) ከስሜት ጋር የሚጣረስ ሲሆን ይህም ለሶስት ይከፈላል። 1. በአላህ ኢባዳ ላይ የሚደረገው ትዕግስት ሲሆን ከዚህ ክፍሉ ግዴታው የግዴታዎቹን መወጣት የሚያስችለውን ያህል ነው። የሚወደደው ደግሞ ይህ ውሳኔዎች ላይ የሚወዱትን ለመተግበር የሚያስችለው የትግዕስትን ክፍል ነው። 2. አላህ ከከለከላቸው ነገሮች መታገስ ነው ከዚህም ክፍል ግዴታ የሚሆነው የተከለከሉትን መተው ሲሆን የሚወደደው የሚጠሉትን መተው ነው። 3. በአላህ ውሳኔዎች ላይ የሚደረገው ትግዕስት ነው። ከዚህም ክፍል ግዴታው ምላስን ከማማረር መቆጠብንና ልቦናን ከመቃወምና ከመጥላት መከልከልና አካላትን ደግሞ አላህ የማይወዳቸውን ሙሾ ማልቀስ አንገትዩን መቅደድና ደረትን መምታት ከመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ መቆጠብ ነው። ከዚህ ክፍል የሚወደደው የአላህን ውሳኔ በልቡ አሚን ብሎ መቀበል ነው።
ወሳኝ ጥያቄ የትኛው ይበልጣል ሐብታም ሆኖ የሚያመሰግን ወይንስ ደሃ ሆኖ የታገሰ ሐብታምም? ሐብታም ገንዘቡን ለኸይር ካዋለው ወይም ለዚሁ ጉዳይ ካስቀመጠው ከታጋሹ ድሃ ይበልጣል። ብዙውን ገንዘቡን በተፈቀዱ ነገሮች የሚያውል ከሆነ ደግሞ ታጋሹ ድሃ ይበልጣል። ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹እየበላ የሚያመሰግን እንደ ታጋሽ ፆመኛ ነው ›› ብለዋል።

▶ **ሪዷ፡-**ሪዷ ማለት ባገኘው ነገር ወዶ መቀበል ሲሆን ተግባሩ ከተከሰተ በኋላ ነው። የአላህ ውሳኔ ወዶ መቀበል ከከፍተኛ ደረጃዎች መካከል አንዱ ነው። ይህም የሚሆነው ለአላህ ከፍተኛ ፍቅርና በእሱ ላይ ጠንካራ ተወኩል ሲኖረው ነው። የደረሰበትን ችግር እንዲያነሳለት አላህን መለመን ከሪዷ ጋር አይቃረንም

▶ **ኹሹዕ፡-**ኹሹዕ ማለት ማክበር ዝቅ ማለት መተናነስ የሚለውን ይተካል። ሁዘይፍ የንፈቅናን መተናነስ ተጠንቀቁ ሲሉ ይህ ማለት ምን ማለት ነው ብለው ጠየቋቸው ዕሳቸውም ሲመልሱ አካሉን ስትመለከቱ የፈራ የሚመስል ውስጡ ግን የማይፈራ ነው። ሁዘይፍ በሌለ ጊዜም ለመጀመሪያ ከዲናችሁ የምታጡት ነገር ኹሹዕ ነው። ብለዋል።
ኹሹዕ የሚያስፈልገው የአምልኮ ተግባር ሁሉ ምንዳው በኹሹዑ ልክ ነው። ለምሳሌ ሶላት። ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሶላት የሚሰግድ ሰው (ከሶላቱ ግማሹን፤ አራተኛውን፤ አምስተኛው. …አስረኛውን እንጂ የለውም።) ብለዋል። ከቶውንም ጭራሽ ኹሹዕ በማጣቱ ምንም የማይኖረው አለ።

▶ **ተስፈኙነት ማለት፡-** የአላህን ረህመት ስፋት መመልከት ነው። ተቃራኒው ደግሞ ተስፋ መቁረጥ ነው። በተስፈኙነት ላይ ሆኖ አምልኮ መስራት በስጋት ላይ ሁኖ ከመስራት

---

[1] -ይህ ክፍል ከሆድና ከስሜት ፍላጎት መታገስ ከሆነ ንፅህና ይባላል። በጦርነት ላይ የሚያይል ፅናት ከሆነ ጀግንነት ይባላል።
ቁጣን በመቆጣጠር ላይ ከሆነ ደግሞ መቻል ይባላል። ጉዳዮችን በመደበቅ ከሆነ ሚስጠርኙነት ይባላል። የተትረፈረፈ ኖሮን በመተው ከሆነ ዙህድ ይባላል። በትኒሽ ነገር ላይ መታገስ ከሆነ መብቃቃት ይባላል።

ጰጅጉን ይበልጣል:: ምክንያቱ በአላህ ላይ መልካም ጥርጣሬ ስለሚጨምር ነው:: አላህ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «ጰኔ ባሪያየ በጠረጠረብኝ ላይ ነኝ» ብሏል:: ተስፈኘነት ሁለት ደረጃ አለው:: ከፍተኛው አምልኮትን ሲተገብር የአላህን መልካም ምንዳ በመመኘት የሚተገብር ሲሆን እናታችን አኢሻ ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ «እነዚያም የሚሰጡትን ነገር ሁሉ እነርሱ ወደ ጌታቸው ተመላሾች መሆናቸውን ልቦቻቸው የሚፈሩ ሆነው የሚሰጡ ናቸው *» ያለውን ቁርአናዊ ቃል ጰኒያ ጰየሰረቁ፣ ጰየዞሞቱ እና ኸምር ጰየጠጡ አላህን የሚፈሩ ሰዎች ማለት ነውን? አሏቸው:: ነብዩም አይደለም:: የሲዲቅ ልጅ ነገር ግን ጰኒያ ጰየሰገዱ ጰየፆሙ ጰየሰደቁ በዚህም ላይ አላህ አይቀበለንም ብለው ስጋት ያለባቸው ማለት ነው:: «እነዚያ በመልካም ስራዎች ይጣደፋሉ፣ እነሱም ለርሷ ቀደሚዎች ናቸው:: » ብለዋል:: ጰኛው ደግሞ ወንጀል ፈፅሞ ወደ አላህ ንስሀ ገብቶ የአላህን ምህረት የሚመኝ ነው ያ በወንጀል ጰንደተዘፈቀ የአላህን ጰዝነት ተስፋ የሚያደርግ ሰው ግን ከንቱ ምኞት ላይ ነው ያለው:: የመጀመሪያው የሚመሰገን ሲሆን ሁለተኛው ግን የተወገዘ ተግባር ነው:: ሙጰሚን መልካም ጰየሰራ አላህን ይፈራል ሙናፊቅ ግን ክፉ ተግባር ጰየፈፀመም ከምን ስጋትም የለውም::

**ኸውፍ መስጋት፡-** የሚጠላው ነገር ጰንዳይደርስበት የሚጨነቅ ሰው በስጋት ላይ ያለ ይባላል:: ጰርግጠኛ ከሆነ ነገር ከሆነ ደግሞ ፍርሃት ይባላል:: ይህ ባህሪ የተስፈኘነት ባህሪ ተቃራኒ አይደለም ጰንዲያውም ይበልጥ በማነሳሳት ተስፈኘነት ጰንዲያጠናክር ይገፋፋል:: ተስፈኘነት ደግሞ በማግባባት በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው:: ጰናም ሁለቱም በአንድ ሲገናኙ የተሟሉ ይሆናሉ::

ኢብኑል-ቀይም ልብ ወደ አላህ በሚያደርገው ጉዞ ልክ ጰንደ ወፍ ነው:: ውዴታ አንደ ጭንቅላት ስትሆን ስጋትና ተስፈኘነት ደግሞ ክንፎቹ ናቸው:: ስጋት በልብ ውስጥ ካለ በውስጡ ያሉቱን ስሜቶች ያቃጥላቸዋል:: የዱኒያ ፍቅርንም ያባርራል:: ግዴታ ሆነው ስጋት ግዴታን ለመስራትና የተከለከሉ ነገሮችን ለመተው የሚያስችል ያህሉ ነው::

የሚወደደው ስጋት ደግሞ የሚወደዱ ነገሮችን ለመተግበርና የተጠሉ ነገሮችን ለመተው የሚያስችል ያህሉ ነው:: ስጋት ብዙ ክፍሎች አሉት:: 1) ውስጣዊና አምልኮ ስጋት አለ ጰሱም ለአንድ አላህ ብቻ መሆን አለበት:: ይህ አይነቱን ስጋት ከአላህ ሌላ ለሆነ ለምሳሌ ለአማልክቶች የሚያደርጉትን መንፈሳዊ ፍርሀትን ይመስል ከፍተኛ ሺርክ ነው:: 2}የተከለከለው ስጋት ሲሆን ይኸውም ሰዎችን ፈርቶ አላህ ያዘዘውን መተው ወይም የከለከለውን መስራት ነው:: 3) የተፈቀደ ስጋት ሲሆን እሱም በተፈጥሮ የሚያስፈራን ነገር ለምሳሌ አንበሳ፣ ነብር፣ ተኩላ እና ውሻ መፍራት ይመስል ነው::

**ዙሁድ ችላ ማለት** ዙህድ/ ዝህድና ጰየተባለ በተለምዶ የሚነገርለት ኢስላማዊ ተግባር ነው:: ይኸውም አንዳንድን ነገር ጰየፈለጉት ወደ ተሻለ ነገር ስሜትን ማዞር ነው:: ብለው የቋንቋ ሰዎች ይፈቱታል:: ዝህድና በዚህ ዓለም ልብንም ሆነ አካልን ጰረፍት ይሰጣል:: ዱኒያ በጣም መመኘት ጭንቀትንና ሐዘንን ያስከትላል:: የዱኒያ ፍቅር የስህተቶች ሁሉ ቁንጮ ነው:: ዱኒያን መጥላት ደግሞ የአምልኮት ሁሉ ዋና ነው:: ዱኒያን ችላ ማለት ከልብ አውጥቶ ለጰሷ አለመጨነቅ ጰንጂ ቀልብህ ጰያሰባት ከአጅህ ማውጣት አይደለም:: ይህ አይነቱ ዝህድና የማህይማን ዝህድና ነው:: ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በዘገቡት ሐዲስ «መልካም ገንዘብ ለመልካም ሰው ምን ያምር ነው» ብለዋል::

ድሃ ከገንዘብ ጋር አምስት ሁኔታዎች አሉት:: 1) በገንዘብ ምክንያት የሚመጣባቸውን ችግር በመፍራት ከገንዘብ የሚሸሽ ሲሆን ይህ አይነቱ ዛሂድ ይባላል:: 2) በማግኘቱ የማይደሰት በማጣቱ የማይከፋ ራዲ /ወደ ተቀባይ/ ይባላል:: 3) ማግኘቱ ያስደስተዋል ለማግኘት በጣም የሚሯሯጥ ከመጥላት በደስታ የሚቀበል ልፋት ከጠየቀ ግን ብዙውም በሱ የማይጨነቅ ክፍል አለ ይህም አይነት ሰው ቃኒዕ /የተብቃቃ/ ይባላል:: 4) አቅቶት ጰንጂ ለማግኘት ጧት ማታ የሚጥር አለ ይህ አይነቱ ስግብግብ ይባላል:: 5) ገንዘብ ለማግኘት ግዴታው የሆነ ጰንደ ርሀብተኛ፣ ጰንደ ታረዘ ይመስል ይህ አይነቱ የተቸገረ ይባላል::

## በአብደላህና በዐብዱ ነቢይ መካከል የተደረገ ለስላሳና አስተማሪ ዉይይት።

**ዐብደላህ**[1]የሚባል ሰው **ዐብዱነቢይ**[2]ከሚባል ሰው ጋር ተገናኝቶ ይህን ስሙን (ዐብዱ ነቢይን) ለራሱ በውስጡ በማዉገዝ አንድ ሰዉ እንዴት ከአላህ በቀር ለሌላ ባሪያ ይሆናል በማለት አብዱነቢን -ለመሆኑ አንተ ከአላህ (ﷻ) ሌላ የሆነን ታመልካለህ ማለት ነዉን ? በማለት ጠየቀው።

**ዐብዱነቢይ:-** ፈፅሞ! ከአላህ ሌላ ማንንም አላመልክም። እኔ እኮ ሙስሊም ነኝ፡፡ አላህን ብቻ ነው የምገዛው /የማመልከዉ/ አለው።

**ዐብደላህ:-** ታዲያ ይህ ክርስቲያኖች ገብረ እየሱስ እንደሚሉት የመሰለ ስም ምንድን ነው ? የእነሱስ አይገርምም፤ ምክኒያቱም ነቢዩ ዒሳን ያመልካሉና ነው፡፡ ስምህን የሰማና ትርጉሙን ያወቀ ሰው የመጀመሪያ ግንዛቤው ነቢዩን እንደምትገዛ ነው፡፡ ነገር ግን ሙስሊሞች ስለነቢዩ ያላቸዉ እምነት ይህ እንዳልሆነ ይታወቃል፡ እንዲያዉም በዚህ ዙሪያ የአንድ ሙስሊም ግዴታ ሙሐመድ የአላህ (ﷺ) መልዕክተኛና አገልጋይ ናቸው ብሎ መመስከሩ ነው በማለት አስረዳው፡፡

**ዐብዱነቢይ:-** ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) እኮ የሰዋች ሁሉ ምርጥና የነቢያትም ሁሉ በላጭ ናቸው፡፡ እኛም በዚህ ስም የምንጠራው ከአላህ (ﷻ) ዘንድ ባላቸው ትልቅነትና በክብራቸው በረካን ለማግኘትና ወደ አላህም ለመቃረብ ብለን ነው፡፡ በዚህም የሳቸዉን ሽምግልና/ሽፈዓ/ እንጌልጋለን። እናም አይግረምህ፡፡ ወንድሜ ስሙ ዐብዱልሁሴን ነው፡፡ የአባቴ ስም ደግሞ ዐብዱረሱል ነው፡ በዚህ ዓይነቶቹ ስሞች መጠራት አዲስ ሳይሆን ከድሮም ጀምሮ የነበረና በሰዎች ዘንድም የተስፋፋ ነው፡ አባቶቻችንንም በዚሁ ላይ ነው ያገኘናቸው፡ብዙ አታካብድ። ጉዳዩ ቀላል ነው። ዲናችንም ገር ነው፡፡

**ዐብደላህ:-** ይህማ ከመጀመሪያዉም የባሰ በጣም ፀያፍ ነገር ነው፡፡ ይኸዉም ከአላህ (ﷻ) ሌላ ሰዎች የማይችሉትን፣ ነቢዩም ይሁኑ ሌሎች ታላላቅና ሷሊህ ሰዎችን ሀሰንና ሁሴንን ስጡኝ ብሎ መለመን ከነሱ መፈለግ የታዘዝንበትን ተውሂድ የሚፃረርና የላኢላህ ኢለሏህን ትርጉም የሚያዛባ ነዉ፡፡ በዚህ ዓይነቱ ስም መሰየም አደገኛነቱ ምን ያህል እንደሆነ ታውቅ ዘንድ አንዳንድ ጥያቄዎችን አነሣልሃለሁ፡፡ አላማዬ ሁሉ እውነቱን ማሳየትና መከተል፣ ዉሸትን ግልፅ ማድረግና መራቅ ነዉ። መመካታችንም በአላህ ነዉ። ከዚያ በፊት ግን (የአማኞች ቃል ወደ አላህና ወደ መልዕክተኛው በመካከላቸው ሊፈር በተጠሩ ጊዜ ሰማን ታዘዝንም ማለት ብቻ ነው። 23:51) የሚለውን እና (በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ከሆናችሁ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልዕክተኛው መልሱት። 4:59) የሚሉትን ቁርአናዊ አንቀፆች ላስታዉስህ እወዳለሁ፡፡

አላህን በብቸኝነት እንደምታመልክና ላኢላህ ኢለሏህ በማለት እንደምትመሰክር ነግረኸኛል። ነገር ግን ትርጉሙን ልትነግረኝ ትችላለህን?

**ዐብዱነቢይ:-** ተውሂድ ማለት በአላህ (ﷻ) መኖር ማመን፤ ሰማይንና ምድርን የፈጠረው፤የሚገድለውና የሚያኖረው በአጠቃላይም በዐለም ላይ እንቅስቃሴችን የሚቆጣጠረዉ፤ ሲሣይን የሚለግሰዉ፤ አዋቂና ቻይ እሱ ነው ብሎ ማመን ነዋ!

**ዐብደላህ:-** ይህ ብቻ ተውሂድ የሚባል በነበረማ ፈርዖንና ህዝቦቹ፤ አቡጀህልና ሌሎችም አማኞች ናቸዉ በተባሉ ነበር፡፡ ምክኒያቱም እነሱም ሆኑ ሌሎች አጋሪዎች ይህንን ሁኔታ አይክዱም ነበርና፡፡ ያ ጌትነትን ይሞግት የነበረው ፈርዖን እንኳን ሳይቀር በዉስጡ የአላህን (ﷻ) መኖር ጠንቅቆ ያምን ነበር፡፡ ማስረጃዬም ቁርአን (ነፍሶቻቸውም ያረጋገጧት ሲሆኑ ለበደልና ለኩራት በርሷ ካዱ (27:14) ያለዉ ነዉ፡

---

[1] ትርጉሙ የአላህ ባሪያ ፤ አገልጋይ ማለት ነዉ።
[2] ትርጉሙ የነቢዩ ባሪያ ፤ አገልጋይ ማለት ነዉ።

ይህም እዉነት በስምጠቱ ጊዜ በይፋ ታይቷል፡፡ ነብያት የተላኩበት፤ መፅሐፍት የተወረደበት፤ ቁረይሾችም የተወጉበት የተዉሂድ እውነታው ግን አላህን በአምልኮ ብቸኛ ማድረግ ላይ ነው፡፡ አምልኮ ማለት ደግሞ አላህ የሚወዳቸውን ነገሮች ዉስጣዊም ሆኑ ዉጫዊ ተግባሮችና ንግግሮችን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ በ- ላኢላህ ኢለሏህ- ዉስጥ ኢላህ ማለት አምልኮ የሚገባው ብቸኛ አምላክ ማለት ነው፡፡

ዐብደላህ:- እኒያ መጀመሪያቸዉ ነቢዩ ኑህ የሆኑት ነቢያት በምድር ላይ ለምን እንደተላኩ ታውቃለህን?

ዐብዱነቢይ:- አዎን- አጋሪዎችን ወደ አላህ አምልኮ ለመጥራትና በሱ የሚያጋሩትን ሁሉ እንዲተው ነው፡፡

ዐብደላህ:- የኑህ ህዝቦች ወደ ሽርክ ለመግባታቸዉ ምክኒያቱ ምን እንደሆነ ታዉቃለህን ?

ዐብዱ ነቢይ:- ይህንስ አላውቅም፡፡

ዐብደላህ:- ወድ፤ ሱዋዕ፤ የጉስ፤ የዑቅንና ነስር የተባሉትን መልካም የአላህ ሰዎች ከተገቢው በላይ በማላቃቸዉ ነበር አላህ ኑህን የላከባቸዉ፡፡

ዐብዱነቢይ:- እነዚህ ሁሉ የአምባገነን ከሃዲ ስሞች ሳይሆኑ የመልካም ሰዎች ስሞች ነበሩ ነው የምትለኝ ?

ዐብደላህ:- አዎን፡፡ እኒህ ስሞች የመልካም ሰዎች መጠሪያ ስም ነበሩ። ኋላ ላይ የኑህ ሰዎች አምላክ አድርገው ያዟቸውና ዐረቦችም ተከትሏቸው፡፡ የዚህም ማስረጃው ከኢብን አባስ እንደተላለፈዉ (ቀደም ሲል በነብዩ ኑህ ዘመን የነበሩ አማልክት በአረቦችም ዘንድ ተመለኩ፡ -ወድ-ን ደውመተልጀንደል አካባቢ የከልብ ጎሳዎች፤ ሱዋዕን ሁዘይሎች፤ የጉስን ሙራድ ከዚያም የበኒ ጉጠይፎች ሰበዕ አካባቢ፤ የዑቅን የሀምዳኖች፤ ነስርን ሂምየሮችና የዚልኪላዕ ቤተሰቦች አማልክቶቻቸዉ አደረጉ፡፡ እኒህ ስሞች ከኑህ ህዝቦች መካከል የነበሩ ደጋግ ሰዎች ነበሩ፡፡ ሲሞቱ ሰይጣን ለህዝቦቻቸው በቦታቸዉ ላይ ሀዉልት ትከሉላቸውና ሀዉልቱን በስማቸው ጥሩት በማለት ሹክ አላቸው፡፡ ህዝቦቹም ያላቸዉን ፈጸሙ:: ግን አልተመለኩም፡፡ ይህን ታሪክ የሚያውቁ ትውልዶች አልቀው እውቀት ሲጠፋ መመለክ ጀመሩ) ብለዋል::

ዐብዱነቢይ:- ይህ የሚገርም ነገር ነው፡፡

ዐብደላህ:- ከዚህ የበለጠ የሚገርም ነገር ልንገርህን ? እሱም ነቢዩ ሙሐመድ የተላኩበት ሕዝብ ምህረትን የሚለምኑ፤ አምልኮቶችን የሚፈፅሙ፡ ጠዋፍ የሚያደርጉ፤ በሶፋና በመርዋ መካከል የአምልኮት ሩጫ የሚፈፅሙ፤ ሐጅ የሚያደርጉና ሰደቃ የሚሰጡ ነገር ግን አንዳንድ ፍጡሮችን መላይኮችን፤ ነብዩ ዒሳንና ሌሎችንም ሷሊህ ሰዎችን ወደ አላህ ያቃርቡናል በሚል በአላህና በእነርሱ መካከል የሚያስገቡ ህዝቦች ነበሩ:: እነዚህን ህዝቦች የአባታቸዉን የነቢየላህ ኢብራሂምን መንገድ እንዲያድሱላቸውና ይህ አይነቱ አምልኮት የሚገባዉ ለአንድ ፈጣሪ፤ ለብቸኛው ሲሣይን ለጋሽ፤ ሰባቱ ሰማያትና በዉስጣቸው ያሉት ሰባቱ ምድርና በዉስጣቸው ያለው ሁሉ አገልጋዩና በቁጥጥሩ ስር የሆነው የአላህ ብቸኛ መብት መሆኑን እና ሌላዉ ቀርቶ የሚገዟቸዉ አማልክቶቻቸው እራሳቸው በአላህ ቁጥጥር ስር መሆናቸዉን ያምኑ እንደነበር ለማስረዳት ነበር የተላኩት፡፡

ዐብዱነቢይ:- ይህ በእዉነቱ በጣም አደገኛ ነገር ነው፡፡ ለመሆኑ ለዚህ ምን ማስረጃ አለዉ?

ዐብደላህ:- መረጃዎች ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል (ሙሐመድ ሆይ!) ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማን ነው ? መስሚያችንና ማያችንስ የፈጠረ ማን ነው? ከሙትም ህያውን የሚያወጣ ከህያውም ሙትን የሚያወጣሥ ማን ነው? ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብርስ ማን ነው? በላቸው፡ አላህ ነው ይሉሃል:: ታዲያ (ለምን ታጋራላችሁ ?):: ታዲያ አትፈሩትምን? በላቸው:: (10:31)

ሌላዉ (ምርና በውስጧ ያለው ሁሉ የማን ነው ? የምታውቁ ብትሆኑ (ንገሩኝ) በላቸው::. በእርግጥ የአላህ ነው ይሉሃል፤ ታዲያ አትገሠጹምን? በላቸው::. የሰባቱ

ሰማያት ጌታ የታላቁ ዐርሽ ጌታ ማን ነው? በላቸው:. በእርግጥ አላህ ነው ይሉሃል፣ እንግዲያዉስ አትፈሩትምን? በላቸው:. የነገሩ ሁሉ ግዛት በእጁ የሆነ እርሱ የሚጠብቅ በርሱ ላይ የማይጠበቅ ማን ነው? የምታውቁ እንደሆናችሁ (መልሱልኝ)፣ በላቸው (23፡84-91) ሙሽሪኮች በሀጅ ጊዜ (ለበይክላሁመ ለበየከ ለበይከ ላሽሪከለከ ለበይከ) - ጌታችን ሆይ ! ጥሪህን ተቀብለን መጣን! ጌታችን ሆይ! አጋር የለህም ሁሉም ግዛት ያንተ ነዉ- ይሉ ነበር፡፡ የቁረይሽ ሙሽሪኮች የአላህን የጌትነት ተዉሂድ/ተዉሂድ አሩቡቢያን/ መቀበላቸዉ ብቻ ሙስሊሞች አላደረጋቸዉም፡፡ መላኢኮችን ደጋግ ሰዎችንና ነቢያትን ተጣርተን በነሱ አማላጅነት ወደ አላህ እንጠጋለን በማለታቸዉ ይህ ነዉ ከሙስሊሞች ጋር ጦርነት ዉስጥ እንዲገቡ ያደረጋቸዉ፡፡ ስለዚህም ዱዓዕ: ስለት: መስዋዕት: እገዛን መጠየቅ በአጠቃላይ ማንኛዉም የአምልኮ ተግባራት ሁሉ ለአላህና ወደ አላህ ብቻ ሊሆን ይገባል የምንለዉ፡፡

ዐብዱነቢይ:- በአላህ መኖር ማረጋገጥ እሱ የነገሮች ሁሉ አስተናባሪ መሆኑን ማመን ተውሂድ ካልሆነ ታዲያ የተዉሂድ ትርጉሙ ምንድነው ?

ዐብደላህ:- ነቢያት የተላኩበት፣ አጋሪዎች የካዱት እንቢ ያሉት ተውሂድ (አላህን በብቸኝነቱ ማምለክ ማንኛዉንም ከላይ የተጠቀሱትን የአምልኮ ተግባራት ሁሉ ለሱ ብቻ ማድረግ ነዉ፡፡ ላኢላሀ ኢለላህ ማለትማ ቃሉን ብቻ መናገር ሣይሆን በተግባርም አላህን ብቻ ማምለክና ወደሱ መጠጋት ነዉ፡፡

ዐብዱነቢይ:- አጋሪ የመካ ሰዎች ስለ ላኢላህ ኢለሏህ ከዘመኑ አብዛኞቹ ሙስሊሞች በበለጠ ያውቃሉ ማለትህ ነውን?

ዐብደላህ:- አዎን፡፣ ይህዉ ነው አሳዛኙና ተጨባጩም ነገር፡፡ የመካ ከሃዲዎች ነብዩ ላኢለሀ ኢለሏህ በሉ ሲሏቸው አምልኮን ለአላህ ብቻ አድርጋችሁ ሌላዉን ተዉ ማለት እንደፈለጉ በትክክል ያውቁ ነበር፡፡ ምክንያቱም ላኢለሀ ኢለሏህ በሉ ባሏቸው ጊዜ (አማልክቶችን አንድ አምላክ አደረጋቸውን? ይህ በእጅጉ የሚገርም ነገር ነው አሉ) (38፡5) በማለት ነበር የመለሱት፡፡ ነገር ግን በተቃራኒዉ ብቸኛዉ የዓለም አስተናባሪ አላህ መሆኑን ያዉቁ ነበር: እዚህ ላይ የሚገርመው ነገር በዛሬዉ ዘመን እኒያ መህይማን የተረዱትን ያህል ያልተረዳ ሙስሊም ነኝ ባይ መኖሩ ነው፡፡ አንዳንዱ መልዕክቷ ምን እንደሆነ ባያውቅም በምላሱ መናገሩ ብቻ የሚበቃው የሚመስለው አለ፡፡ ሻል ያለው ደግሞ የሚፈጥር፣ የሚለግስ: ሁሉን ነገር የሚያስተናብር ያለ እርሱ ማንም የለም ማለት ነው ብሎ ያስባል፡፡ ታዲያ በላኢላህ ኢለሏህ ትርጉም የቁረይሽ ጃሂሎች የበለጧቸው ሰዎች ምን ተስፋ አላቸው !

ዐብዱነቢይ:- እኔ እኮ በአላህ አላጋራም፡፡ የሚፈጥር፣ የሚመግብ፣ ሁሉን ነገር የሚያስተናብር ያለ እርሱ ማንም የለም ብየ አምናለሁ፡፡ እንኳንስ ዐሊ፣ ሁሰይን፣ ዐብዱልቃድር.. ሌሎችም ሁሉ ይቅርና ነብዩ ሙሐመድም (ﷺ) ቢሆኑ ለራሳቸው መጥቀምም ሆነ መጉዳት አይችሉም ብየ አምናለሁ፡፡ ነገር ግን እኔ ሀጢዓተኛ ነኝ፡፡ ሷሊሆች ደግሞ ከአላህ ዘንድ ክብር አላቸው እናም ከአላህ ዘንድ እንዲሸመግሉኝ/እንዲያማልዱኝ ነው የምጠይቃቸው፡፡

ዐብደላህ:- ለዚህ ጥያቄህ ያለፈውን መልስ ነው የምመልስልህ፡፡ እሱም ነብዩ የተዋጓቸው ሰዎች አሁን አንተ ያልከዉን ሁሉ ያምኑበት ነበር፡፡ ጣዖቶቻቸው ምንም እንደማይ ጠቅሟቸዉ እንደማይጎዷቸዉ ያዉቃሉ: የሚፈልጉት በአላህ ዘንድ ባላቸዉ ክብር እንዲያማልዷቸዉ ነዉ፡፡ መረጃዉም ከላይ ተጠቅሷል፡፡

ዐብዱነቢይ:- የተጠቀሱት አንቀፆች የወረዱት በጣኦት አምላኪዎች ምክኒያት ነው፡፡ ታዲያ ነቢያትንና ሷሊሆችን እንዴት እንደ ጣኦት እንመለከታቸዋለን?

አብደላህ:- ጣኦቶቹ የተሰየሙት በአንዳንድ መልካም ሰዎች ስም መሆኑን አይተናል፡፡ ለምሳሌ በኑህ ህዝቦች ዉስጥ የነበረዉ ዐይነት፡፡ አጋሪዎችም ከነሱ ይፈልጉት የነበረዉ ነገር ከአላህ ዘንድ ባላቸው ክብርና ማዕረግ ተጠቅመዉ እንዲያሸማግሏቸዉ ነዉ፡፡ ለዚህ መረጃው አላህ እንዲህ አለ (እነዚያ ከርሱ ሌላ ጣዖታትን ረዳቶች አድርገው የያዙት

ሰዎች ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጂ ለሌላ አንገዛቸውም [1]ይላሉ፡፡ (39፡3)
ነቢያትንና ወሊዩችን እንዴት ጣኦት እንመለከታቸዋለን ላልከው ደግሞ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በተላኩላቸው ከሐዲዎች መካከል አላህ (እነዚያ እነርሱ የሚገዟቸው ማንኛቸውም (ወደ አላህ) በጣም ቀራቢያቸው ወደ ጌታቸው መቃረቢያን (ሥራ) ይፈልጋሉ፡፡ እዝነቱንም ይከጅላሉ፡፡ ቅጣቱንም ይፈራሉ፡፡ የጌታህ ቅጣት የሚፈራ ነውና፡፡ (17፡57) በማለት የጠቀሳቸው ወሊዩችን የሚያመልኩ ክፍሎች ነበሩ፡ ከመሀከላቸዉም ዒሳንና እናታቸዉን የሚያመልኩ ሰዎች ነበሩ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አላህ ሲናገር (ሁሉንም በሚሰበስባቸውና ከዚያም ለመላዕክቶች እነዚህ እናንተን ይገዙ ነበሩን ? በሚላቸው ቀን የሚሆነውን አስታውስ፡፡ (34፡40) ከነርሱም መካከል መላኢኮችን የሚያመልኩ ነበሩ፡፡ አላህም (ሁሉንም በሚሰበስባቸውና ከዚያም ለመላእክቶች እነዚህ እናንተን ይገዙ ነበሩን ? በሚላቸው ቀን የሚሆነውን አስታውስ፡፡ (5፡116) አለ፡፡
እነዚህንና ሌሎችን የቁርአን አንቀፆች በጥሞና ብናስተዉል ማንኛዉም ጣዖትን በአምልኮ ያሰበ ሁሉ መላኢካ ነቢያትንም ሆነ ደጋግ የአላህ ሰዎችን ካሰበዉ ሰዉ ጋር እኩል ተመሣሣይ ወንጀለኛ መሆኑን ነዉ፡፡
ዐብዱነቢይ፡- ቢሆንም ከሃዲዎች ከጣዖቶቻቸዉ ጥቅምን ይፈልጋሉ፡፡ እኔ ግን የሚጠቅመዉም ሆነ የሚጎዳዉ አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ ብቻ ነዉ ብዬ አምናለሁ፡ የምፈልገዉም ከአላህ ዘንድ እንዲያማልዱኝ ብቻ ነዉ፡፡
ዐብደላህ፡- ይህ ራሱ ከከሃዲዎች አባባል ጋር ተመሣሣይ ነው፡፡ ቁርአን (ከአላህ ሌላ የማይጎዳቸውንና የማይጠቅማቸውን ይገዛሉ፡፡ እነዚህ ከአላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው ይላሉ፡፡ (10፡18) አለ፡፡
ዐብዱነቢይ፡- እኔ ግን መቸም ቢሆን ከአላህ ሌላ አላመልክም፡፡ ወደ እነሱ መጠጋትና እነሱን መለመን አምልኮ አይደለም፡፡
ዐብደላህ፡- እስቲ ልጠይቅህ ፤ ለመሆኑ አላህ (ﷻ) (አላህን- ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ አጥሪዎች ቀጥተኞች ሆነው ሊገዙት ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ፤ ዘካንም ሊሰጡ እንጂ አልታዘዙም፡፡) (98፡5) እንዳለው በፍፁምነት እንድታመልከው ግዴታ እንዳደረገብህ ታምናለህን ?
ዐብዱነቢይ፡- አዎን፡ ይህ ነገር በኔም ላይ ግዴታ ነው፡፡
ዐብደላህ፡- እኔ ከአንተ የምጠይቀው ነገር ቢኖር ይህ ግዴታ የሆነብህ ነገር ምን እንደሆነ እንድትገልፅልኝ ነው፡፡
ዐብዱነቢይ፡- በጥያቄህ ምን ማለት እንደፈለክ አልገባኝምና እስቲ አብራራልኝ
ዐብደላህ ፡- እሺ አዳምጠኝ፡ አላህ (ﷻ) (ጌታችሁን ተናንሳችሁና ተዋርዳችሁ በድብቅ ለምኑት (ጥሩት)፡ እርሱ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና፡» (7፡55) ብሏል፡፡ ስለሆነም ዱዓ የአምልኮ አካል ነው ወይንስ አይደለም ?
ዐብዱነቢይ፡- በርግጥም ዱዓ ከአምልኮት መሠረቶች ነዉ:: ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) (ዱዓ አምልኮት ነው) ብለዋል፡፡
ዐብደላህ፡- ዱዓዕ የአላህ (ﷻ) አምልኮት መሆኑን አምነህ ከተቀበልክና ከዚያም አላህን ቀንም ሆነ ሌሊት ፈርተህና ተስፋ አድርገህ ከጠራህ እንዲሁም በሌላ በኩል ለየትኛዉም ችግርህ ብለህ ሌላን አካል ማለትም ነቢይም ይሁን መላኢካን ወይም በቀብር ያለን ወሊይ ከጠራህ በአላህ (ﷻ) አጋራህን ወይንስ አላጋራህም ?
ዐብዱነቢይ ፡- አዎን በርግጥ ይህማ ትክክለኛና ግልፅ የሆነ ነገር ነዉ፡፡
ዐብደላህ ፡- ሌላም ምሳሌ ላምጣልህ እሱም (ስለዚህ ለጌታህ በፍፁምነት ስገድ (በስሙ)

---

[1]- በዚህ አባባል ግን እነሱን ይገዙ እንደነበር እንረዳለን፡፡ እናም ይህ አባባል ከተወሱል ጋር ተመሳሳይነት እንደሌለው እንገነዘባለን፡፡

ብቻም ሠዋ /እረድ/:: የሚለዉን የአላህን (ﷻ) ቃል ካወቅክና ይህን ትዕዛዙን ተቀብለህ ለእሱ ብቻ ካረድክ ይህ ተግባርህ ለአላህ (ﷻ) አምልኮ ነው ወይንስ አይደለም ?

ዐብዱነቢይ፡- በርግጥም ይህ አምልኮ ነው፡፡

ዐብደላህ፡- ከአላህ (ﷻ) ሌላ ለሆነ ፍጡር ጅን፡ ነቢይም ይሁን ወሊይ ካረድክለት በዚህ ተግባር በአላህ አጋርተሃል ወይንስ አላጋራህም ?..

ዐብዱ ነቢይ፡- አዎን፡ ይህ ያለምንም ጥርጥር ሽርክ ነው፡፡

ዐብደላህ ፡- በዱዓም ሆነ በእርድም ምሣሌ ሰጥቸሃለሁ፡፡ ይህንንም ያደረግኩት ዱዓ ከንግግራዊ የአምልኮ ተግባሮች ዋናው ስለሆነና እርድ ደግሞ ከድርጊታዊ አምልኮቶች ዋናው ስለሆነ ነው፡፡ አምልኮት በእነዚህ ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡ ከዚህ የሰፋና ብዙ ቁም ነገሮችን ያካተተ ስለት፡ መሀላ፡ ኢስቲዓዛ/ መጠበቅ/፡ እገዛን መጠየቅና ሌሎችንም የአምልኮት አይነቶች የሚያጠቃልል ነው፡ ቁርአን የወረደባቸው አጋሪዎች መላኢኮችን ላትንና ኡዛን እንዲሁም ሷሊህ ሰዋችን ያመልኩ አልነበረምን ?

ዐብዱነቢይ፡- አዎን፡ እነሱማ ይህን ሁሉ ያደርጉ ነበር፡፡

ዐብደላህ፡- ታዲያ የነሱ አምልኮ በዱዓ፤ በእርድ፤ ጠብቁን ብሎ በመማፀን፤ በእርዳታ ጥየቃ፡ ወደነሱ በመሸሽ እንጂ በምን ይመስልሃል? እነሱ የአላህ (ﷻ) ባሮች እንደሆኑና በሱ ቁጥጥርም ስር እንዳሉ አላህ (ﷻ) ሁሉን የሚያስተናብር ጌታ እንደሆነና እነሱን የሚጠሩት ያሸማግሏቸዉ ዘንድ ብቻ እንደነበር ግልፅ አደል እንዴ !

ዐብዱነቢይ፡- የነቢዩን (ﷺ) ሸፋዓ /ሽምግልና/ ትቃወማለህን ?

ዐብደላህ፡- ፈፅሞ አልቃወምም፡፡ አልክድምም፡ በአባቴም በእናቴም ፊዳ ይሁኑላቸዉ እላለሁ፡፡ ሽምግልናቸዉንም ከአላህ (ﷻ) እመኛለሁ፡ ነገር ግን ሽምግልና/ምልጃ/ የአላህ (ﷻ) ብቻ ስልጣን ነው፡፡ አላህ (ﷻ) እንዳለዉም (ሸፈኣ/ምልጃ/ ሁሉ የአላህ ብቻ ነው፡፡ (39:34) ምልጃ ከአላህ ፍቃድ በኋላ እንጂ አትሆንም፡፡ አላህ (ያ ! እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጂ የሚያማልድ ማን ነው? (2:255) [1] አለ፡፡

አላህ (ﷻ) ምልጃን ተዉሂድ ካላቸዉ ብቻ እንጂ ሰዋች አይቀበልም፡፡ ቁርአን (ለወደደው ሰው ብቻ እንጂ ለሌላው አያማልዱም (21:28) አለ፡፡

በሌላ አንቀፅም (ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይነት የለውም፡፡ (3:85) አለ፡፡ ከላይ እንዳየነዉ ሽምግልና ሁሉ የአላህ (ﷻ) ብቻ እና ሊሆን የሚችለዉም ከእሱ ፍቃድ በኋላ መሆኑን እንዲሁም ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አላህ (ﷻ) ላልፈቀደው ሰው የማይሸመግሉ እንደሆነና፤ ምልጃ የሚፈቀደዉም ተውሂድ ላላቸው ሰዎች ብቻ መሆኑን ተረድተናል:: እንግዲያዉስ ምልጃ ሁሉ የአላህ ብቻ መሆኑን ካወቅን (አላሁመ ላተህሪምኒ ሽፋዐተሁ፤ አላሁመ ሸፊዕሁ ፊየ) (ጌታችን ሆይ !የነቢዩን ሽምግልና አትከልክለኝ አላህ ሆይ! እሱን ለኔ ሽምጋይ አድርግ/...እና በመሳሰለው ዱዓዕ የነቢዩን ሽምግልና ከአላህ (ﷻ) ከራሱ እንጠይቃለን፡፡

ዐብዱ ነቢይ፡- ከማንኛዉም አካል እሱ ያልተሰጠዉንና የማይችለዉን ጉዳይ መጠየቅ እንደሌለብን ተስማምተናል፡፡ ነቢዩ (ﷺ)ደግሞ ሸፋዐ ተሰጥቷቸዋል፡፡ከተሰጣቸው ደግሞ መልከዉታል/ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ነገር ከነቢዩ መጠየቅ ሽርክ ሊሆን አይገባም፡፡

ዐብደላህ፡- አዎን፡ አላህ (ﷻ) ባይከለክልህ ኑሮ ይህ አባባል ትክክል ነበር፡፡ ግን አላህ

---

[1] ምልጃን በተመለከተ ብዙ አናቅፅ አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል (ምልጃ መላውም የአላህ ብቻ ነው፤ የሰማያትና የምድር ስልጣን የርሱ ብቻ ነው፤ ከዚያም ወደርሱ ትመለሳላችሁ፤ በላቸው)፡፡ አዝ-ዙመር4422. (እነዚያን ከአላህ ሌላ አማልክት ብላችሁ የምታሰስቧቸውን ጥሩ፤ በሰማያትም በምድርም ውስጥ የብናኝ ክብደት ያክል ምንንም አይችሉም፡፡ ለነርሱም በሁለቱም ውስጥ ምንም ሽርክና የላቸውም ከነርሱም ለርሱ ምንም አጋር የለውም» በላቸው፡፡23. ሰበእ እነዚህንና መሰል የቁርአን አንቀፆች በማሰባሰብ የምንረዳው ነገር ቢኖር ምልጃ የተባለ ሁሉ ስልጣኑ የአላህ ብቻ መሆኑን እሱም ተቀባይነት ያለውና ተቀባይነት የሌለው ተብሎ ለሁለት እንደሚከፈል ነው፡፡

(ﷻ) (እነሆ መስጊዶች የአላህ ብቻ ናቸው፡ (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድም አትገዙ/አትጥሩ፡፡) (72፡18) ብሏል፡፡ ሸፈዐን መጠየቅ ዱዓ ነው፡፡ ለነቢዩ ሸፈዓን የሰጠዉም አላህ ነው፡፡ ከእሱ ሌላ ከማንም እንዳትጠይቅ የከለከለህም አላህ (ﷻ) ራሱ ነው፡፡ እንደዚሁም ብዙዎች ለምሳሌ መላኢኮች፤ በልጅነት የሞቱ ህፃናትና ሌሎችም የአላህ ወዳጆች ሸፈዓ ተሰጥቷቸዋል፡ ስለሆነም ተሰጥተዋልና ሸፈዓን ከእነሱ እጠይቃለሁ ልትል ነዉን? ይህን ካልክ ደግሞ ልክ አላህ (ﷻ) በቁርአን እንዳወሳው ሷሊሆችን ወደ ማምለኩ ተራመድክ ማለት ነው፡፡ አይደለም ካልክ ደግሞ አላህ ሸፈዓን ሰጥቶታልና ከተሰጠዉ ሰዉ እፈልጋለሁ የሚለዉ አባባልህ ዋጋ አጣ ማለት ነው፡፡

ዐብዱነቢይ፡ እኔ አሁንም ቢሆን በአላህ (ﷻ) ማንንም ምንንም አላጋራም፡፡ ወደ ሷሊሆች መጠጋት ደግሞ ሽርክ አይደለም፡፡

ዐብደላህ፡- አላህ ሽርክን ከዝሙት በበለጠ እንደከለከለና እንደማይምረውም ታምናለህ?

ዐብዱነቢይ፡- አዎ እኔም በዚህ አምናለሁ፡፡ ይህም በአላህ (ﷻ) ቁርአን ዉስጥ በግልፅ የተቀመጠ ነገር ነው፡፡

ዐብደላህ፡- አንተ አሁን አላህ ከከለከለዉ ሽርክ ንጹህ እንደሆንክ ነው የምታምነው፡ አልሰራሁትም /የለሁበትም ብለህ የምትክደዉ የሽርክ አይነት የትኛዉ ነው ?

ዐብዱነቢይ፡- ሽርክ ማለት እኔ እንደማውቀው ከሆነ ጣኦት ማምለክ ነው፡፡ እሱም ሲባል እነሱን መለመን፤ ከእነሱ መፍራትና መሰል ተግባር ነው፡፡

ዐብደላህ፡- ጣኦት አምልኮ ማለት ምን ማለት ነው?

ለመሆኑ እነዚያ ቁረይሾች/የመካ ሰዎች/ ይማፀኗቸዉ የነበሩተ ድንጋዮች ፤እንጨቶችና ዛፎች ይፈጥራሉ፤ ይሰጣሉ፤ የሰዉን ጉዳይ ተከታትለው የሚያወጡለት ናቸው ብለው የሚያምኑ ይመስሉሃልን ? በርግጥ የእነሱ እምነት አንተ እንዳልከው አይደለም፡፡

ዐብዱነቢይ፡- እኔም እንደሱ የማምን አይደለሁም፡፡ ብሎም ዛፍን፤ ድንጋይን፤ ቀብርን የተማፀነ ወይም ለእነሱ ያረደና እነሱ ወደ አላህ (ﷻ) ያቃርቡኛል፤ ችግሬንም አላህ (ﷻ) በእነሱ በረከት ይከላከልልኛል ብሎ ያመነ ሰውን... ይህን ነዉ እኔ የባዕድ አምልኮ የምለው።

ዐብደላህ፡- ልክ ነህ፡፡ ሆኖም ግን ይህ በየዶሪሁ፤ በየ ድንጋይ፤ በየ ግንቦች ዘንድ የምትሰሩት የእናንተ ተግባር ነው፡፡ እንደዚሁም ሽርክ ማለት ታቦትን ማምለክ ነው ያልከው ይህ ተግባር ብቻ ነው ማለትህ በሷሊሆች ላይ መመካት እነሱን መጥራት ሽርክ አይሆንም ማለትህ ነው ?

ዐብዱነቢይ፡- ይህን ነው እኔም ማለት የፈለኩት፡፡

ዐብደላህ፡- እንግዲያዉስ ታዲያ አንተ ከነዚያ በወሊዩች ላይ መመካትን፤ በመላኢኮች ላይ መንጠልጠልን የሚከለክሉትንና ይህን የሰራንም የሚያከፍሩትን አያሌ የቁርኣን አንቀፆች ምን ትላቸዋለህ?

ዐብዱነቢይ፡- እነዚያ መላይካንና ነቢያትን የተጣሩ ሰዎች በዚህ ምክኒያት ሳይሆን የከፈሩት መላኢኮች የአላህ ሴት ልጆች ናቸው፤ አል-መሲህ የአላህ ወንድ ልጅ ነው በማለታቸው ነው፡፡ እኛ ግን ዐብዱልቃድር የአላህ ወንድ ልጅ ነው፤ ዘይነብ የአላህ (ﷻ) ሴት ልጅ ናት አላልንም፡፡

ዐብደላህ፡- ለአላህ (ﷻ) ልጅ አለው ማለት ራሱን የቻለ ክህደት ነው፡፡ አላህ (ﷻ)እንዲህ አለ (ሙሐመድ ሆይ!) እርሱ አላህ አንድ ነው። አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው።[1] አልወለደም፤ አልተወለደምም። (112፡1-3)

አህድ /አንድ/ ማለት አምሣያ የሌለው ማለት ሲሆን፡ ሶመድ ማለት ደግሞ የሁሉ

---

[1].ይህ አንቀፅ ለሶስቱም የተሳሳቱ ቡድኖች ማለትም፡ መላኢኮች የአላህ ሴት ልጆች ናቸው፡፡ የሚሉትን የዐረብ አጋሪዎች ፤ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው ለሚሉት አይሁድና መሲሕ የአላህ ልጅ ነው የሚሉትን ነሷራዎች በቂና የማያዳግም መልስ ይሰጣል፡፡

መጠጊያ ማለት ነው፡፡ ይህን እውነታ የካደ ሰው የአንቀጿን መጨረሻ ባይክድ እንኳን ይከፍራል፡፡ አላህ (ﷻ) (አላህ ምንም ልጅን አልያዘም (አልወለደም)፡ ከርሱም ጋር አንድም አምላክ የለም፡፡ ያን ጊዜ (ሌላ አምላክ በነበረ) አምላክ ሁሉ በፈጠረው ነገር በተለየ ነበር፡፡ ከፊላቸውም በከፊሉ ላይ በላቀ ነበር አለ፡፡) (23፡91) በሁለቱ ክህደቶች መካከል ልዩነት አለ፡፡ ለዚህ መረጃው እነዚያ ላትን የተገዙ ሰዎች (መልካም ሰዎች የነበሩ ሲሆን) የአላህ (ﷻ) ልጅ አላደረጉትም:: እኒያ ጂኖችን በመገዛት የከፈሩት ሰዎችም የአላህ (ﷻ) ልጆች አላደረጓቸዉም ነበር፡ እንደዚሁም አራቱም የፊቅህ መዘህቦች ስለ ሙርተድ /ከሃይማኖቱ ስለተመለሰ ሰዉ/ በፃፉበት ርዕስ ላይ ለአላህ (ﷻ) ልጅ አለው ያለ ሰው ይከፍራል (ሙርተድ/ከእምነት ወጥቷል) ብለዋል፡፡ በአላህ (ﷻ) ካጋራ (ሙርተድ ነው)ብለዋል። በሁለቱ መካከል ልዩነት አላደረጉም፡፡

ዐብዱነቢይ፡- አላህ (ﷻ) ግን (ንቁ! /አዋጅ/ የአላህ ወዳጆች ምንም ፍርሃት የለባቸውም፡፡ በምንም ነገር አያዝኑምም፡፡ 10፡62 ) ይላል፡፡

ዐብደላህ፡- እኛም ይህ አባባል እዉነት ነዉ እንላለን፡፡ ሆኖም ወሊዮች አይመለኩም አይጠሩም፡፡ እኛ እኮ እየተቃወምን ያለነው መመለካቸዉንና ከአላህ (ﷻ) ጋር አጋር መደረጋቸዉን ነው፡፡ ከዚህ በተረፈ እነሱን መውደድ፤ ተግባራቸዉን መከተል፤ ከራማቸዉን ማመንና መቀበል ግዴታ ነው፡፡ ከራማቸዉን የሚክዱ የቢድዐ ሰዎች ናቸው፡፡ ትክክለኛው የአላህ (ﷻ) ዲን በሁለት ጫፎች መካከል፤ በሁለት ጥሜቶች መካከል፤ በሁለት ባጢሎች መካከል ያለ ብቸኛ ሐቅ ነው፡፡

ዐብዱ ነቢይ፡- እነዚያ ቁርአን የወረደባቸው ሰዎች ላኢላሀ ኢለሏህ አይሉም፡ ነቢዩን ያስተባብላሉ፤ ሙቶ መነሳትን ይክዳሉ:: ቁርአንንም ያስተባብላሉ። ድግምትም ነው ይሉታል፡፡ እኛ ግን በአላህ (ﷻ) እናምናለን፤ በነቢዩም በቁርአንም በሙቶ መነሳትም፡፡ ደግሞም እንሰግዳለን፡፡ እንፆማለን:: እንዴት እንደ እነሱ ታደርጉናላችሁ?

ዐብደላህ፡- ነገር ግን አንድ ሰው ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) በአንድ ነገር ተቀብሏቸው በሌላ ነገር ካስተባበላቸው ወደ ኢስላም የገባ ላለመሆኑ በዐሊሞች መካከል ምንም የአቋም ልዩነት የለም፡፡ በግማሽ ቁርአን አምኖ በግማሹ የካደ ሰው ለምሳሌ በተውሂድ አምኖ በሶላት የካደ ወይም በሶላት አምኖ ዘካን የካደ ወይም በዚህ ሁሉ አምኖ ፆምን ብቻ የካደ ወይም በዚህ ሁሉ አምኖ ሐጅን ብቻ የካደ ሰውም እንደዚሁ ነው፡፡ በነቢዩ ሙሐመድም (ﷺ) ዘመን ሰዎች ለሐጅ ፀሎት ብቻ አንታዘዝም በማለታቸው (ለአላህ ከሰዎች መካከል ወደርሱ መሄድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ ነዉ፡ የካደ ሰው ግን (እራሱን እንጂ ማንንም አይጎዳም) አላህ ከአለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው፡፡ (3፡97) የሚለዉን የቁርአን አንቀፅ አወረደ፡፡ ሙቶ መነሳትን ብቻ ያስተባበለ ሰው በሁሉም ዐሊሞች አባበል ይከፍራል፡፡ እንደዚሁም አላህ (ﷻ) በቁርአን በግማሽ አምኖ በግማሽ የካደን ሰው ትክክለኛ ከሃዲ ማለት እሱ እንደሆነ ተናግሯል፡፡ ኢስላምን በሙሉ መያዝ እንዳለብንም አዟል፡፡ አንዱን ይዞ ሌላዉን የተወ ሰውም ይከፍራል፡፡ ለመሆኑ አንተ ግማሹን አምኖ በግማሹ የካደ ሰው እንደሚከፍር ታምናለህን ?

ዐብዱነቢይ፡- አዎን፡ በዚህ አምናለሁ:: ይህም በቁርአን ዉስጥ በግልፅ ተቀምጧል፡፡

ዐብደላህ፡- ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) በአንድ ነገር ተቀብሎ የሶላትን ግዴታነት የካደ ወይም ሙቶ መነሳት ሲቀር በሌላው ያመነ ሰው ቁርአንም እንደተናገረው በሁሉም ዐሊሞች ዘንድ ከሀዲ ነው:: ህይወቱም ሆነ ንብረቱ ዋስትና የለዉም ብለህ የምታምን ከሆንክ ተውሂድ አላህ ግዴታ ካደረጋቸው ነገሮች ሁሉ ማለትም ከሶላት፣ ከዘካ፣ ከሐጅ እንኳን ሳይቀር የበለጠ መሆኑን ተገንዘብ፡፡ ታዲያ የሰው ልጅ እነዚህን ነገሮች ሲክድ እየተገበራቸው እንኳን ቢሆን ከሀዲ መሆኑ የታወቀ ሆኖ ሣለ ያ የነቢያት ሁሉ ዋና ተልዕኮ የሆነዉን ተውሂድን ሲክድ እንዴት አይከፍርም ይባላል ! በጣም የሚገርም

ድንቁርና ነው፡፡ እንደዚሁም የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ባልደረቦች በኒ ሐኒፋዎችን በየማማ ላይ ሲዘምቱባቸው ላኢላሀ ኢለሏህ ሙሐመድ ረሱለሏህ ብለው የምስክርነት ቃል የሰጡ፣ የሚሰግዱና አዛን የሚያደርጉ መሆናቸዉን እያወቁ ነበር፡፡

**ዐብዱነቢይ፡-** እነሱ ግን ሙሰይሊማ ነቢይ ነው ይሉ ነበር:: እኛ ግን ከነቢዩ በኋላ ነቢይ አለ ብለን አናምንም፡፡

**ዐብደላህ፡-** እናንተ ግን ዐሊይን፤ ዐብዱልቃድርን ወይም ሌሎችንም ነቢያት ይሁኑ መላኢኮችን የሰማይና የምድር ፈጣሪ ደረጃ ትሰጧቸዋላችሁ፡፡ እነሱን ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ደረጃ ያቀረበ እንኳን ሲከፍር ወደ አላህ (ﷻ) ደረጃ ያሳደገ ሰው በይበልጥ ነው የሚከፍረው፡፡ እንደዚሁም እኒያ ዐሊይ በእሳት ያቃጠሏቸው ሰዎቸ ሁሉም ሙስሊሞች ነን የሚሉና የዐሊይ ባልደረቦች፣ ከሱሃቦችም የተማሩ ነበሩ:: ነገር ግን እናንተ አሁን በዐብዱልቃድር ላይ እንዳላችሁ እምነት አይነት በዐሊይ አመኑ:: እነዚህን ሰዎች እንዲገደሉ ሶሐቦች ሁሉ ተስማምተዋል። ለመሆኑ ሰሃቦች ሙስሊሞችን በማክፈር ይስማማሉ ብለህ ታስባለህን ! ወይንስ በነ ሰይድና መሰሎቹ ማመን የማይጎዳ በዐሊይ ማመን የሚጎዳ መሰለህ ?

**እንደዚሁም** ቀደምት ከሃዲዎች የከፈሩት ሽርክን በነቢዩ፤ በቁርአን፤ በሙቶ መነሳት ስላስተባበሉ ከሆነ የፊቅህ ምሁራን በየመዝሀባቸው 'የሙርተድ ክፍል' ብለው ለይተው የፃፉት ርዕስና በዚያው ዉስጥም በዙ ነገሮችን እያንዳንዳቸው የሚያከፍሩ ብለው ያወሷቸው በጣም ጥቃቅን ነገሮች እንኳን ሳይቀሩ ለምሳሌ በልቡ ሳያምንበት በድንገት የሚናገራት አላህን (ﷻ) የምታስቀይም ቃልን ይመስል ምንድን ነው ትላለህ? እንደዚሁም አላህ (ﷻ) እንዲህ አለ (አታመካኙ፤ ከእምነታችሁ በኋላ በእርግጥ ክዳችኋል፡፡ ከእናንተ አንዷን ቡድን ብንምር ሌላዋን ቡድን ግን ሀጢአተኞች በመሆናቸው እንቀጣለን::)

እኒያ (ከእምነታችሁ በኋላ በእርግጥ ክዳችኋል፡፡) በማለት ካመኑ በኋላ ከሃዲ ሆነዋል የተባሉት እኮ ከነቢዩ ሙሐመድ ጋር በተቡክ ዘመቻ ላይ ሁነው በቀልድ ያልሆነ ነገር ስለተናገሩ ብቻ ነው፡፡ እንደዚሁም አላህ (ﷻ) ስለ እነዚያ የኢስራኢል ልጆች ሙስሊሞች አዋቂዎችና መልካም ሰዎች ከመሆናቸው ጋር ለሙሳ (የእስራኤልን ልጆች ባህሩን አሻገርናቸው ለነርሱ በሆኑ ጣኦታት (መገዛት) ላይ በሚዘወትሩ ህዝቦች ላይ አለፉም፡፡ ሙሳ ሆይ:- ለሰዋቹ አማልክት እንዳሉዋቸው ሁሉ ለእኛም አምላክን አድርግልን አሉት:: <እናንተ የምትሳሳቱ ህዝቦች ናችሁ አላቸው:: (7፡138) ልብ እንበል። ከሶሐቦች መካከል አንዳንዶቸ ነቢዩ ሙሐመድን (ለእነሱ ዛቱ አንዋጥ እንዳላቸው ሁሉ ለእኛም ይኑረን) ባሏቸው ጊዜ ነቢዩ ሙሐመድም (ﷺ):- «ይህ አባባል ልክ እንደበኒ ኢስራኢሎች አባባል ነው» ማለታቸው እንደዚሁ ነው፡፡

**ዐብዱነቢይ፡-** ታዲያ በኒ ኢስራኢሎችም ሆኑ ነቢዩ ሙሐመድንም (ﷺ) ዛቱ አንዋጥ የጠየቁት ሰዎች መች ከፈሩ ተባለ፡፡

**ዐብደላህ፡-** ለዚህ መልሱ - በኒ ኢስራኢሎችም ሆኑ ነቢዩን (ﷺ) የጠየቁ ሰዎች ተግባሩን ጠየቁ እንጂ አልፈፀሙትም:: ፈፅመዉት ቢሆን ኖሮ ግን ይከፍሩ ነበር፡ እነዚያ ነቢዩ (ﷺ) የከለከሏቸዉም እሺ ብለው ባይቀበሏቸውና ዛቱ እንዋጥን ይዘዉ ቢሆን ኑሮ ይከፍሩ ነበር፡፡

**ዐብዱነቢይ፡** ሌላም ያልገባኝ ነገር አለ፡ እሱም የኡሳመህ ብን ዘይድ ታሪክ ነው፡ ላኢላሀ ኢለሏህ ያለን ሰው ገድሎ ነቢዩ (ﷺ) (እንዴ! ላኢላሀ ኢለሏህ ካለ በኋላ ገደልከው! ፡ቡኻሪ) በማለትያወገዙበት ታሪክ ነው፡፡ እንደዚሁም ሙስሊም (ሰዎች ላኢላሀ ኢለሏህ እስኪሉ ድረስ እንድዋጋቸው ታዝዣለሁ) በማለት የዘገቡት ሐዲስ ነው፡፡ በእነዚህ ሐዲሶችና አንተ ባልከኝ መካከል እንዴት ላስማማ እንደምችል እስቲ ጠቁመኝ?

**ዐብደላህ፡-** ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አይሁዶችን የተዋጓቸውና የማረኳቸው ላኢላኢለሏህ

እያሉ ነው፡ የነቢዩ ባልደረቦችም በኒሐኒፋዎችን ጦር ያዘመቱባቸው ላኢላኢለሏህ ሙሐመድ ረሱሉሏህ እያሉና እየሰገዱ ነው፡፡ እንደዚሁም እነዚያ ዐሊይ ብን አቢጧሊብ በሳት ያነደደ‍ቿቸው ላኢላኢለሏህ ሙሐመድ ረሱሉሏህ የሚሉና የሚሰግዱ ነበሩ፡፡ አንተም ብትሆን ሙቶ መነሳትን ያስተባበለ ሰው ላኢላኢለሏህ ሙሐመድ ረሱሉሏህ ቢልም እንደሚከፍርና መግደሉም እንደሚበቃ የኢስላምን መሰረት አንዷን እንኳን የካደ ቢናገራትም ከሃዲ እንደሚሆን እና ቢሰግድም እንደሚገደል ታምናለህ፡፡ ታዲያ ቅርንጫፍን ነገር በመተው ላኢላኢለሏህ ማለቱ ሳትፈይደው እንዴት ዋና የነቢያት ተልዕኮ የሆነዉን ተውሂድን ለካደ ሰው ትፈይደዋለች፡፡ ምናልባትም የእነዚህን ሐዲሶች መልዕክት በደንብ አልተረዳህም ይሆናል፡፡

የኡሳመህ ብን ዘይድ ሐዲስ የተባለው እሱ የገደለው ላኢላኢለሏህ ያለን ሰው ቢሆንም ያለው ለራሱና ለንብረቱ ፈርቶ እንጂ ከልቡ አይደለም በሚል ጥርጣሬ ነው፡ ፡ ኢስላምን የተናገረ ሰው ተቃራኒዋን ካልፈፀመ በስተቀር የተከበረ ነው፡፡ ቁርአን እንዲህ አለ (እናንተ ያመናችሁ ሆይ ! ነገረኛ ወሬን ቢያመጣለቸሁ በስህተት ላይ ኾናችሁ ህዝቦችን እንዳትጎዱና በሠራችሁት ነገር ላይ ተጸጻቾች እንዳትኾኑ አረጋግጡ፡፡) (4:94) ብሏል፡፡ አንቀጿ የምታስተምረው ቁምነገር ላኢላኢለሏህን የሚፃረር ነገር እስካልታየበት ድረሰ አንድን ሰዉ ከመግደል መታቀብን ነው፡ ይህማ ባይሆን ኑሮ ' አረጋግጡ ' የሚለው ቃል ምንም አይነት ጥቅም ባልነበረው፡፡

እንደዚሁም ሁለተኛው ሐዲስ ፍቺዉ ተውሂድን ይፋ አድርጎ የሚታይ ሰው ተቃራኒዉን በይፋ እስካልፈፀመ ድረስ እንደዚሁ የተከበረ መሆኑን ነው፡፡ ለእነዚህም መረጃው ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)ቡኻሪ በዘገቡት (ላኢላህ ኢለሏህ ካለ በኋላ ገደልከው !) የሚለዉ ሐዲስና ሙስሊም የዘገቡት ደግሞ (ሰዎች ላኢላህ ኢለሏህ እስኪሉ ድረስ እንድዋጋቸው ታዝዣለሁ) ያሉት ሐዲስ ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ያገኙ ሶሃቦች ሳይቀሩ የእነሱን የዒባዳ ጥንካሬ ባዩ ጊዜ ራሳቸዉን ዝቅ አድርገው የሚለከቱተን ትምህርትንም ከእነሱ የወሰዱት ኸዋሪጆች ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ (ባገኛችኋቸው ቦታ ሁሉ ግደሏቸው) ያሉ ናቸው፡፡ እናም ላኢላኢለሏህ፣ የዒባዳ መብዛትና ሙስሊም ነኝ ማለት የኢስላምን ህግ በተቃረኑ ጊዜ ከመገደል አላስጣላቸዉም፡፡

ዐብዱነቢይ፡- ሰዎች በቂያማ እለት በአደም፣ በኑህ፣ በኢብራሂም፣ በሙሳ፣ በዒሳ ይማፀኑና ሁሉም አንችልም ብለዋቸው ከዚያም በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ይማፀናሉ፡፡ ይህ ታዲያ በሰዎች መማፀን የሚፈቀድ መሆኑን አያመለክትምን ?

ዐብደላህ፡- ይህ እውነትን ከሐሰት ጋር ማደበላለቅ ነው የሚባለው፡ ህይወት ባለውና አጠገብህ ባለ በሚሰማና ቻይ በሆነ ሰዉ እርዳታን መጠየቅ አላህ (ﷻ) እንዳለዉ (ያ ከወገኑ የሆነው ሰው በዚያ ከጠላቱ በሆነው ሰው ላይ ተማፀነዉ /እርዳታን ጠየቀው፡፡ (28:15) እንዳለው ሁሉ አንቃወመዉም፡ ይህም ማንኛዉም ሰዉ በጠላቱ ላይ በሚችለዉ ነገር እንዲያግዙት እንደሚማፀነዉ ማለት ነው፡፡ እኛ የምንቃወመዉ ኢስቲጋሳ ያን በየ መቃብሩ ላይ የሚደረገዉን ወይም ሰዎች በሌሉበት ቦታ በመንፈስ ድረሱልን እየተባለ የሚደረገዉንና ከአላህ (ﷻ) ሌላ ማንም በማይችለው ጉዳይ የሆነዉን ነው፡፡ ሰዎች የቂያማ ዕለት በመህሸር ከመቆም ጭንቀት ለመገላገል ምርመራቸዉ ተፋጥኖ ወደ ጀነት ይሄዱ ዘንድ አላህን (ﷻ) እንዲጠይቁላቸዉ ነቢያትን ይማፀናሉ፡ ይህ አይነቱ መማፀን በዚህ ዐለምም የተፈቀደ ነው፡ ይህም ማለት ከሚሰማህ ሰው ዘንድ ሂደህ ችግርህን ነግረህ አላህን (ﷻ) እንዲለምንልህ መጠየቅ ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በህይወት እያሉ ሰሃቦችም ይህን ይጠይቋቸው ነበር፡፡ ከሞቱ በኋላ ግን በቀብር ላይ ቁመው የጠየቁበት አንድም ቀን አልነበረም፡ ከቶዉንም ሰለፎች በቀብር አጠገብ ሁኖ አላህን (ﷻ) መለመንን ከልክለዋል፡፡

ዐብዱነቢይ፡- ነብዩ ኢብራሂም እሳት ላይ በተጣሉ ጊዜ በአየር ላይ እያሉ ጂብሪል ጉዳይ አለህን ? ብሎ ሲጠይቃቸው እሣቸዉም ' ካንተ ከሆነ ፈፅሞ ' ብለዉታል፡፡

በጂብሪል መታገዝ የማይሆን ቢሆን ኑሮ ይህን አይነቱን ጥያቄ ባለቀረበላቸው ነበር፡ ይህንንስ ምን ትላለህ ?

ዐብደላህ፡- ይህችም ከዚያችኛዋ ተመሳሳይ የሆነች ማሳሳቻ ናት፡፡ የተዘገበው አባባልም ትክክል አይደለም፡ ትክክልነቱን ብንቀበልም ጂብሪል የጠየቀው በአቅሙ ያለዉን ነገር ነው ምክኒያቱም ጂብሪል አላህ (ﷻ) (ሀይለ ብርቱ የሆነው መልዐክ አስተማረው (53፡5) እንዳለው ነዉ::

አላህ የኢብራሂምን እሳትና በዙሪያዋ ያለዉን ምድር ጭምር እንዲያነሳና በምስራቅ ወይም በምዕራብ እንዲጥለው ፈቅዶለት ቢሆን ኑሮ ባላቃተው ነበር፡፡ ይህ ማለት አንድ ሀብታም ለአንድ ድሃ ገንዘብ እንዲሰጠውና ችግሩን እንዲወጣበት ጠይቆት በትዕግስት ምንም አይደለም መመፃደቅ የሌለበትን የአላህ (ﷻ) ትሩፋት እጠብቃለሁ ብሎ እንቢ እንዳለው ነው፡፡ታዲያ ይህ አሁን እየተሰራ ካለው ሽርክና ሰዎችን ከማምለክ ጋር ምን ያመሣስለዋል ?

ወንድሜ አንድ ልታውቀው የሚገባ ነገር አለ፡፡ እሱም ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የተላኩባቸዉ ሰዎች ሽርካቸዉ አሁን ካለው የሽርክ ተግባር በሶስት ምክኒያቶች የተሻለ ነው፡፡

አንደኛ፡- እነዚያ ቀደምት ሰዎች ከአላህ (ﷻ) ጋር ያጋሩት የነበረው በድሎት ጊዜ ነበረ፡፡ በችግር ጊዜ ግን ቁርአን እንዳለው (በመርከቦች ውስጥ በተሳፈሩ ጊዜም አላህን መገዛትን ለርሱ ብቻ ያጠሩ ኾነው ይጠሩታል፡ ወደ የብስ (በማውጣት) ባዳናቸው ጊዜ ግን ወዲያዉኑ እነርሱ (ጣዖትን) በርሱ ያጋራሉ:: (29፡65) (እንደ ጥላዎች የሆነ ማእበል በሸፈናቸው ጊዜ ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ ያጠሩ ሆነው አላህን ይጠሩታል፡፡ ወደ የብስ ባዳናቸው ጊዜ ግን ከነሱ መካከል ትክክለኛም አለ፤ (ከነሱም የሚክድ አለ)፡ በአንቀጾቻችንም አታላይና ከዳተኛ የሆነ ሁሉ እንጂ ሌላው አይክድም፡፡ (31፡32)

እኒያ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጦር ያዘመቱባቸው አጋሪዎች በድሎት ጊዜ አላህንና (ﷻ) ሌሎችንም አማልክቶች ይጠሩ ነበር፡፡ በችግር ጊዜ ግን እኒያን አማልክቶቻቸዉን ረስተው አላህን ብቻ የሙጥኝ ብለው ይለምናሉ፡፡ የዘመኑ አጋሪዎች ግን በደስታም ጊዜ ሆነ በችግር ጊዜ ከአላህ ዉጭ የሆነዉን ሌላን አካል ይጠራሉ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ! ሁሰይን ሆይ! ይላሉ፡፡ ነገር ግን ይህን የሚያውቅ ማን አለ?

ሁለተኛ፡- ቀደምት አጋሪዎች ከአላህ (ﷻ) ጋር ያጋሩት የነበረው ወደ አላህ (ﷻ) ቅርበት አላቸዉ የሚሉትን አካሎች ነቢይ፤ ወሊይ፤ መላኢካ፤ ወይም ቢያንስ አላህን (ﷻ) ብቻ የሚታዘዝና የማይፃረርን ድንጋይና ዛፍን ነበር፡፡ የዘመኑ ሰዎች ግን ከአላህ (ﷻ) ጋር የሚያጋሩት የለየላቸዉን አመፀኞችን ነው፡፡

ሶስተኛ፡ በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ዘመን የነበሩት አጋሪዎች ችግር በአምልኮታዊ ተውሂድ ላይ ሲሆን:: የዘመኑ አጋሪዎች ግን ብዞዎቹ በጌትነቱም ጭምር ሽርክ አድርገዋል፡፡

እናም ለምሳሌ - በተለምዶ የሚታወቁትን በሞትና በህይወት ጉዳይ ላይ ሣይቀር ስልጣን ለሚያመልኩት ሰጥተዋል፡፡

ቢሆንም ካለፉው ዉይይትአንድ ልንረዳው የምንችለውንና በጣም ጠቃሚ የሆነን ጉዳይ በመጥቀስ ሐሳቤን ማጠቃለል እፈልጋለሁ፡፡ እሱም ተውሂድ ማለት በልብ ማመን፤ በምላስ መናገርና በአካል መተግበር መሆኑ አማራጭ የሌለው ነው፡፡ አንድ ሰዉ ከእነዚህ መሰረታዊ ነገሮች አንዱንም ቢያጎድል ሙስሊም አይባልም፡፡ ስለዚህ ተውሂድን አውቆ ባይሰራበት ልክ እንደ ፈርዐውንና ኢብሊስ ሁሉ እንቢተኛ ከሃዲ ነው፡፡ ይህ ነገር ብዙዎች የሚሳሳቱበትና‘ ይህ ጉዳይ ሐቅ ነው፡፡ ነገር ግን አንችለዉም፡ በአገራችን ይህ ነገር ይከብዳል፤ ከእነሱ ጋር ከመመሳሰል ውጪ አማራጭ የለንም የሚሉት ነው፡፡ አብዛኞቹ የኩፍር መሪዎች እዉነትን ላለመቀበል ሰበብ አያጡም፡፡ (በአላህ አንቀጾች ጥቂትን ዋጋ ገዙ፡፡ ከመንገዱም አገዱ:: እነርሱ

ይሰሩት የነበሩት ሥራም  እጅግ በጣም ከፉ::) ይላል አላህ። ተውሂድን ሣያውቀዉና በልቡም ሣያምንበት አንድ ሰዉ ላይ ላዩን ብቻ በሱ የሚሠራ ቢሆን ይህ ሰው ከንፁህ ካሃዲም የባሰ ሙናፊቅ ነው፡፡ አላህ (መናፍቃን በርግጥ ከእሣት በታችኛው አዘቅት ውስጥ ናቸው፡፡) ብሏል። ይህን ጉዳይ በትክክል ካስተዋልከው በሰዎች አንደበት ላይ በግልፅ ታገኘዋለህ፡፡ ምክኒያቱም ስንት ሰው አለ እውነትን አውቆ ሣለ የማይተገበር፡ ዱኒያው እንዳይጎድልበት ብሎ ለምሳሌ እንደ ቃሩን፤ ወይም ክብሩ እንዳይነካበት እንደ ሃማን ወይም ስልጣኑን እንዳይጋሩት ብሎ እንደ ፈርዐውን ያሉትን ማለት ነዉ፡፡ ከዉስጥ ሣይሆን ላይ ላዩን ብቻ የሚሰራም ለምሳሌ ሙናፊቆችን ይመስል አለ፡፡ በምን እንደሚያምን ሲጠየቅ ጭራሽ አያውቀዉም፡፡

በዚሁ ዙሪያ ሁለት የቁርአን አንቀፆችን ማወቅ ያስፈልግሃል፡፡

አንደኛው አንቀፅ፡ ያ ከላይ ያለፈው “ ምክኒያቶችን አትደርድሩ:: ካመናችሁ በኃላ ክዳችኋል ..” የሚለው አንቀፅ ሲሆን  እኒያ ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጋር ወደ ሩም የዘመቱ ሰዎች በቀልድ አስመስለው በተናገሯት አንዲት ቃል ብቻ ለክህደት መብቃታቸዉን ትረዳለህ፡፡  ይህንን ካወቅክ  ንብረቱ እንዳይጠፋበት፤ ወይም ክብሩን ላለማጣት፤ ወይም ከሰው ጋር ለመኖር ብሎ በክህደት መስመር መጓዝ እየቀለዱ ከመናገር የበለጠ ነው፡፡ ምክኒያቱም የሚቀልድ ሰው አብዛኛዉን ጊዜ ሰዎችን ለማሳቅ በሚል ይናገራል እንጂ በልቡ አስቦበት ላይሆን ይችላል፡፡ ያ ከሰዉ ፈርቶም ሆነ ከነሱ ከጅሎ ክህደትን የሚናገር ወይም የሚፈፅም ሰው ግን:- (ሰይጣን (እንዳትለግሱ) በድህነት ያስፈራራችኋል፡ በእኩይ ነገርም ያዛችኋል፡፡ (2፡268) በማለት ቃል የገባዉን አፀናለት፡፡ እንዲህ አለ፡- (ያ ሸይጣን ነው፡ ወዳጆቹን (የአላህን) ያስፈራራል፡) የሚለዉን ዛቻ አረጋገጠለት፡ (አትፍሯቸው ፡ ምዕምናን ከሆናችሁ እኔን ብቻ ፍሩኝ::[1]) የሚለዉን የአላህን ግሣፄ አልፈራም፡፡ አላህ እንዲህ (አላህ ከርሱ የሆነን ምህረትና ችሮታን ይቀጥራችኋል፡፡ አላህ ችሮታው ሰፊና አዋቂ ነው::) በማለት የገባዉን ቃልኪዳኑን አላመነም፡፡ ታዲያ እንዲህ አይነት ባህሪ ያለው ሰው የአላህ ወዳጅ መሆን ነው የሚችለው ወይስ የሰይጣን ?

ሁለተኛው አንቀፅ ደግሞ አላህ (ﷻ) (ከእምነቱ በኋላ በአላህ የካደ ሰው (ብርቱ ቅጣት አለለት)  ልቡ በእምነት የረካ ኾኖ(በክሕደት ቃል  መናገር) የተገደደ ሰው ብቻ ሲቀር:: ግን ልባቸውን ለክሕደት የከፈቱ ሰዎች ከአላህ ቁጣ አለባቸው፡ ለእነርሱም አሣማሚ ቅጣት አለ:: (6፡106) የሚለው ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው አላህ (ﷻ)) በልቡ እምነቱን አጠንክሮ ይዞ ሣለ የተገደደን ሰዉ ብቻ ሲቀር የሌላ የማንንም ምክኒያት እንዳልተቀበለ ነዉ፡፡ ፈርቶ ወይም በአንድ ነገር ተስፋ አድርጎ ወይም ሊመሳሳል ብሎ አሊያም ለሀገር ለጎሣ ለዘመዱ ብሎ ወይም ለንብረት ለገንዘቡ ብሎ ወይም በቀልድ አስመስሎ ወይም ለሌላ ምክኒያት ብሎ የሰራ ሰው ከፍሯል ማለት ነዉ፡ አንቀጿ የተገደደን ሰዉ ብቻ ነዉ የምትመለከተዉ:: የሰው ልጅ የሚገደደዉ በመናገርና በመተግበር ብቻ እንጂ በልብ በሚያዘዉ እምነቱ ማንም አይገደድም፡፡ አላህ (ﷻ) (ይህ ቅጣት እነሱ ቅርቢቱን ሕይወት ከመጨረሻይቱ በመምረጣቸው

---

[1] -ከምዕራፉ ከአንቀፅ 172-175 ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋናዋናዎቹ፡-

1)የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጓዶች (ሰሀባች)  ከሌሎች ሰዎች በተለየ መልኩ የተሰጣቸውን ታላቅ ክብር፣

2)አላህ (عز وجل) በቂያችን ነው በእርሱም መመካት አማረ» (ሀስቡነላህ ወኒዕመል ወኪል) በማለት በችግር ጊዜ አላህን ማስታወስና በርሱ መመካት  እጅግ ተወዳጅና አጅሩም (ምንዳውም) የበዛና የነቢያት ፈለግ መሆኑን፣ሰይጣን ሙስሊሞችን ለማስፈራራትና ለማርበትበት መጠነ ሰፊ ሙከራችን እንደሚያደርግ፤

3)ከሁለት አስቸጋሪ ነገሮች መካከል አንድን ከመፈጸም አማራጭ ከጠፋ አነስተኛውን (ቀለል ያለውን) ጥፋት መፈጸም ተገቢ ነው፡፡ እንዲሁም ከሁለት ጥቅሞች በአንዱ ላይ የተማረጠ ሰው የበለጠውን መምረጥ እንዳለበት፤ሠራተኛን በአገልግሎት ልጅን መዳርም እንኳን ቢሆን መከራየት እንደሚቻል እንማራለን፡፡

ምክንያትና አላህ ከሓዲዎችን ሕዝቦች የማያቀና በመኾኑ ነው:: (16፡107) አለ። እዚህም እንደተመለከተዉ የቅጣቱ ምክኒያት እምነት ሳይሆን የዱንያ ፍላጎትም አብሮ ስለነበረበትና ዱንያን ከዲን ስላስቀደሙ መሆኑን ነው የሚያመለክተው፡፡ አላህ ሁሉን አዋቂ ነዉ።

ከዚህ በኋላ አላህ (ﷻ) ቀናዉን መንገድ ይምራህና የነበርክበትን ትተህ ወደ ጌታህ የምትመለስበት ጊዜ የቀረበ ይመስለኛል፡፡ ምክኒያቱም ጉዳዩ እንደሰማህው ሁሉ በጣም ከባድና አደገኛ ነገር ነውና፡፡

ዐብዱነቢይ፡- አላህን ምህረቱን እለምነዋለሁ፡ ወደ እሱም ተውባ አደርጋለሁ፡፡ በአላህ ብቸኛ አምላክነትና ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ በመሆናቸው እመሰክራለሁ፡፡ ከአላህ ሌላ አመልክ በነበርኩት ሁሉ ክጃለሁ፡፡ አላህም (ﷻ) ላለፈው ይቅር እንዲለኝ፣ በእዝነቱና በትሩፋቱ እንዲንከባከበኝ፣ እሰከለተ ሞቴ ድረስ በትክክለኛው እምነት ላይ እንዲያፀናኝ እለምነዋለሁ፡፡ አንተንም በዚህ ምክርህ ከተገቢው በላይ ምንዳህን እንዲሰጥህ እለምነዋለሁ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ስሜንም ወደ ዐብዱረህማን የቀየርኩና በዉስጤም የነበረዉን ባዕድ እምነት የተውኩኝ መሆኔን ልነግርህ እወዳለሁ፡፡ ሆኖም አንድ የመጨረሻ ጥያቄ አለኝ:: እሱም ብዙ ሰዎች የሚሳሳቱባቸውን ነገሮች አለፍ አለፍ ብለህ ብትጠቁመኝ ብየ ነው፡፡

ዐብደላህ፡- ምንም ችግር የለውም:: ብቻ ጆሮህን ስጠኝና በደንብ አዳምጠኝ፡፡ ፊትናን የሚቀሰቅሱና ትርጉማቸዉ አሻሚ የሆኑ በቁርአንም ሆነ በሐዲስ ሰዎች በተለያዩበት ጉዳይ ላይ ኺላፍን ተከትሎ መሄድ ይቅርብህ፡፡ ምክኒያቱም ትክክለኛዉን ፍች ከአላህ (ﷻ) በስተቀር ማንም አያውቀዉምና፡፡ መለያህ የእኒያ የትክለኛ አዋቂዎች (ሁሉንም አምነንበታል ሁሉም ከአላህ ነው (3፡7) የሚሉት ይሁን፣ ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት የነቢዩ ሐዲስ (የሚያጠራጥርህን ነገር ተዉና ወደ ማያጠራጥርህ ነገር ተመለስ) የሚለዉና እንዲሁም ሙስሊም የዘገቡት የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሐዲስ (ወንጀል ማለት በልብህ ዉስጥ የተመላለሰብህ እና ሰዎችም እንዳያውቁብህ የምትደብቀው ነገር ነው) የሚለዉ እና አህመድ የዘገቡት (ሶስት ጊዜ ዉስጥህን ጠይቅ ፡ ዉስጥህን ጠይቅ ካሉ በኋላ- መልካም ነገር ማለት ነፍስ የረጋችበት ነው፡፡ ወንጀል ማለት ደግሞ በልብህ ዉስጥ የተመላለሰብህ ነው ፡ ሰዎች ቢጠይቁህም ቢነግሩህም) ያሉት መለያህ ይሁን፡፡

✸ ስሜትህን አትከተል፡፡ አላህ (ﷻ) እንዲህ አለ (ስሜቱን አምላኩ አድርጎ የያዘዉን አየህን!)

✸ ለግለሰቦችና ለተለያዩ አስተሳሰቦች ወገንተኛ አትሁን፣ ምክኒያቱም ዉድ ንብረት የሆነውን 'እውነትን' ፈትሸህ ከማወቅ እንቅፋት ይሆንብሐልና፡፡ አላህ እንዲህ አለ:- (ለነርሱም አላህ ያወረደውን ተከተሉ በተባሉ ጊዜ አይደለም አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘ ንበትን ነገር እንከተላለን ይላሉ:: አባቶቻቸው ምንም የማያውቁና (ወደ እውነት) የማይመሩም ቢሆኑ (ይከተሏቸዋልን?))

✸ ከካሃዲዎች ጋር መመሳሰል ይቅርብህ:: ምክኒያቱም የችግሩ ሁሉ መንሰኤ እሱ ነዉና፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡዳዉድ በዘገቡት ሐዲስ (ከሰዎች ጋር የተመሳሰለ ሁሉ ከነሱው ነው)ብለዋል፡፡

✸ ከአላህ (ﷻ)ሌላ በማንም አትመካ (በአላህ ላይ የሚመካ ሰው እርሱ በቂው ነው ፤ 63፡3)

✸ አላህን በሚያስቆጣ ጉዳይ ላይ ማንንም አትታዘዝ፡፡ ነቢዩ ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ. (ፈጣሪን ባለመታዘዝ ፍጡርን መታዘዝ የለም) ብለዋል፡፡

✸ በአላህ (ﷻ) ላይ መጥፎ ጥርጣሬን ተጠንቀቅ፡፡ ምክኒያቱም አላህ (ﷻ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሰል ቁድስ (እኔ ባሪያዬ በጠረጠረኝ ዘንድ ነኝ) ብሏልና፡፡

✸ የተለያዩ ችግሮች ሲከሰቱብህ ወይም ገና ሳይከሰቱ በፊት አደጋን ለመከላከል

ብለህ ገመዶችንና የተለያዩ ቀለበቶችን ከማንጠልጠል ተጠንቀቅ፡፡

✱ ለአይነናስ /የሰዉ ዐይን/መከላከያ ብለህ ሂርዝን ከማንጠልጠል ተጠንቀቅ:: ምክኒያቱም ይህ ተግባር ሽርክ ነዉና፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ (አንድን ነገር ያንጠለጠለ ሰው ወደዚያዉ ነገር ይተዋል/) ብለዋል፡፡

✱ በድንጋዮች፣ በዛፎች፣ በተለያዩ ቅርሳ ቅርሶችና ግንቦች ተበሩክ ማድረግ ይቅርብህ:: ይህ ነገር ሽርክ ነዉና፡፡

✱ በየትኛዉም ነገር ገድን መተንበይ ይቅርብህ:: ሽርክ ነዉና፡፡ ነቢዩ አቡዳዉድ. በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ (ጢየራህ/ በወፎች ገድን ማየት/ ሽርክ ነው፡፡ ጢየራህ ሽርክ ነው፡፡ ጢየራህ ሽርክ ነው፡፡) ሶስት ጊዜ በማለት አስጠንቅቀዋልና፡፡

✱ እነዚያን የሩቅ ዕዉቀት አለን የሚሉትን መተተኞችና ኮከብ ቆጣሪዎችን በዚህም በመታገዝ የሰዎችን የወደፊት ዕጣ ፈንታ እናውቃለን የሚሉትን አትመን:: ይህ ከሽርክ ነዉና፡፡ ከአላህ በስተቀር ገይብን / የሩቅ ሚስጢርን / አዋቂ ማንም የለም፡፡

✱ የዝናብ መምጣትን ከኮከብ ጋር አታያይዘው:: ይህ ተግባር ሽርክ ነዉና፡፡ ምክኒያቱም ዝናብ ከአላህ ጋር ብቻ ነው መያያዝ ያለበት፡፡

✱ ከአላህ በስተቀር በማንም አትማል:: ምክኒያቱም ሽርክ ነዉና፡፡ ነቢዩ ሙሐመደ (ﷺ). አህመድ በዘገቡት ሐዲስ (ከአላህ ሌላ በሆነ የማለ ሰው አላህን ክዷል ወይም በአላህ አጋርቷል፡፡) ይህም በነቢዩ፡ በአማና፡ በክብር፣ በህይወት፡ በቃልኪዳንና በመሣሠሉት መማልን ያጠቃልላል፡፡

✱ ዘመንን፣ ንፋስን፣ ፀሐይን፣ ብርድን፣ ሙቀትን፣ ከመሳደብ ተጠንቀቅ:: ምክኒያቱም ይህ ማለት ፈጣሪያቸዉን መስደብ ነዉና፡፡

✱ ችግር ሲያጋጥምህ እንዲህ በሆን ኖሮ ከማለት ተጠንቀቅ ይህ አባባል የሰይጣንን መንገድ ይከፍታልና፡፡ የአላህን ዉሳኔም መቃረን ነዉና፡፡ ይልቁንም አላህ (ﷻ) ወሰነ የሻዉንም ሰራ በል፡፡

✱ መቃብሮችን መስጂዶች አታድርጓቸው፡፡ ቀብር ካለበት መስጊድ ዉስጥ አይሰገድምና፡፡ ነቢዩ ሙሐመደ (ﷺ) ቡኻሪ እናታችን ዓኢሻን ዋቢ በመጥቀስ በዘገቡት ሐዲስ በሰከራተል መውት እያጣጣሩ ባሉበት (አይሁድና ነሳራዎችን አላህ እርግማኑን ያዉርድባቸው፡፡ የነብያቶቻቸዉን መቃብር መስገጃ አድርገው ይዘዋልና፡ ፡) አሉ። ዓኢሻህ በመቀጠል:- (ይህ ማሰጠንቀቂያ ባይኖር ኑሮ ቀብራቸዉን ግልፅ ቦታ ባደረጉት ነበር) ብለዋል፡፡ በተጨማሪም አቡ ዐዋነህ በዘገቡት ሐዲስ (ከእናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦች የነብያቶቻቸዉንና የመልካም ሰዎቻቸዉን መቃብር መስጊድ ያደርጉት ነበር፡፡ ስለዚህ መቃብሮችን መስገጃ አታድርጓቸው:: ከዚህ ተግባር እከለክላችኋለሁ፡፡) ብለዋል።

✱ በነቢዩም ሆነ በሌሎች መልካም ሰዎች በዛታቸው መወሰል/ ወደ አላህ መቃረብ/ይበቃል ብለው የሌለ ሀዲስ በነቢዩ ላይ የሚቀጥፉትን ሰዎች ሰበካና የሐሰት ሐዲስ አትቀበል። ከነዚህም መካከል (በክብሬ ተወሰሉ/ ወደ አላህ ተቃረቡ/የእኔ ክብር አላህ ዘንድ ትልቅ ነዉና) (ችግሮች ሲያይልባችሁ በተቀበሩት ላይ ሙጥኝ በሉ) (ከአላህ በየወሊዮች መቃብር ላይ የባለ ጉዳዮችን ችግር የሚፈታ መላኢካ ይመድባል) (ማንም ሰው በድንጋይ እንኳን መልካም ንያ ካሣደረ ይጠቅመዋል) የሚሉት እና ሌሎችም ናቸው፡፡

✱ ሐይማኖታዊ በዐላት የሚባሉትን ለምሳሌ የነቢዩ መውሊድ በዐል፣ የኢሰራእና ሚዕራጅ፣ የሸዕባን አስራ አምስት ቀንና ሌሎችንም ከማክበር ተጠንቀቅ፡፡ ምክኒያቱም ከነቢዩም ሆነ ከኛ በበለጠ ነቢዩን ይወዷቸዉና ያከብሯቸው ከነበሩት ሰሀቦች ምንም አይነት መረጃ የሌላቸው ነገሮች ናቸዉና፡፡ ይህ ተግባር ኸይር ቢሆን ኖሮ እነሱ ይቀድሙን ነበርና፡፡

## ላኢላሀ ኢለሏህ /ከአሏህ በቀር በእውነት ሊገዙት የሚገባ አምላክ የለም/ ብሎ ስለመመስከር፡፡

(የጀነት በር ቁልፍ ላኢላሀ ኢለሏህ እንደሆነች ተወስቷል) ነገር ግን በምላሱ ብቻ የተናገራት ሰው ሁሉ ጀነት ትከፈትለት ይሆን ? አንደኛው ላኢላሀኢለሏ ይህቺ የምስክርነት ቃል ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን ታጠቃለላለች፡፡ አንደኛደኛው ላኢለሀ የሚለው ቃል ሲሆን ይኸውም ትክክለኛ አምላክነት ከአላህ ሌላ ከሆነ ሁሉ መግፋፍ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ኢለሏህ የሚለው ቃል ሲሆን እሱም ትክክለኛ አምላክነትን ለአላህ ብቻ መስጠት ነው፡፡ አላህ በቁርአን « ኢብራሂም ለአባቱና ለወገኖቹ፣ ያለዉን አውሳላቸው፣ እኔ ከምታመልኩት ነገር ሁሉ፣ ገለልተኛና የፀዳሁ ነኝ፣ ያየፈጠረኝ ሲቀር እሱም በእርግጥ ቀናዉን መንገድ ይመራኛል። » እናም አላህን መገዛት ብቻ በቂ አይደለም፡፡ አምልኮት ለእሱ ብቻ አምልኮት የአላህን ብቸኝነት ማመንና ከሽርክና ከባለቤቱ ነፃ ካልተሆነ በስተቀር ፍይዳ የለውም፡፡ ወህብ ብን ሙነቢህ (ላኢላሀ ኢለሏህ የጀነት ቁልፍ አይደለችምን? ) ተብለዉ ሲጠየቁ እንዴ ! ናት እንጂ:: ነገር ግን ቁልፍ የተባለ ሁሉ ጥርስ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ ጥርስ ያለው ቁልፍ ይዘህ ከመጣህ ይከፈትልሃል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን አይከፈትልህም፡፡) ብለዋል።

የዚህን ቁልፍ ጥርሶች የሚያመላክቱ ብዙ ሐዲሶች ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ተዘግበዋል፡፡ ለምሳሌ ከእነዚህም መካከል (በፍፁምነት ከልቡ..) እርግጠኛ ሆኖ...) (ከልቡ እውነተኛ ሆኖ... ላኢላሀ ኢለሏህ ያለ ሰው ጀነት ይገባል፡፡) የሚለውን የሐዲስ አባባል በጥሞና ብንመለከት ጀነት ለመግባት ፍቺዋን አውቆ ትዕዛዟን የተገበረና እስከ እለተ ሞቱ ድረስ በእሷ ላይ የፀና ከሆነ ብቻ እንደሆነ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከእነዚህና በዚህ ዙሪያ ከተዘገቡ ማስረጃዎች በመነሣት ሙሰሊም ምሁራን ላኢላሀ ኢለሏህ ያላትን ሰዉ ጠቅማ የጀነት በር መክፈቻ ትሆን ዘንድ ሊሟሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና መወገድ ያለባቸው እንቅፋቶች እንዳሉ ለመረዳት ችለዋል፡፡ እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎችም የቁልፉ ጥርሶች ናቸው፡፡ እነሱም፡-

❶ **እውቀት/አል-ኢልም/፡-** ምክኒያቱም እያንዳንዱ ቃል የራሷ የሆነ ትርጉም አላት፡፡ እናም የላኢላሀ ኢለሏህን ትርጉም በትክክል መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ትርጉሟም አምላክነትን ከአላህ ሌላ ከሆነ ሁሉ ሰርዛ ለእርሱ ብቻ ማፅደቅ ነው፡፡ በእውነት በአግባቡ በትክክል ሊመለክ የሚገባው ከአላህ ሌላ ማንም የለም ማለት ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ (እነዚያም ከአላህ ሌላ የሚገዟቸው እነሱ ትክክለኛዉን የሚያውቁ ሆነው[1] በእውነት ከመሰከሩት ክፍሎች በስተቀር ምልጃን አይችሉም) (43፡86) ነቢዩ ሙሐመድም (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (በትክክል የሚመለክ ከአላህ ሌላ የሌለ መሆኑን እያወቀ የሞተ ሰው ጀነት ይገባል ብለዋል፡፡)

❷ **እርግጠኝነት/አል-የቂን/ይህም** ማለት መልዕክቷን በትክክልና ያለምንም ጥርጣሬ መቀበል ነው፡፡ አላህ (ﷻ) አማኞችን ሲገልፅ (እውነተኞቹ ምእምናን እነዚያ በአላህና በመልዕክተኛው ያመኑትና ከዚያም ያልተጠራጠሩት፤ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ ላይ የታገሉት ናቸው:: እነዚያ እነርሱ እውነተኞቹ ናቸው::) (49፡15) ብሏል፡፡ ስለዚህ ዉሥጣችን ሳይቀበል በምላስ መናገሩ ብቻ አይጠቅምም፡ ይህ ከሆነም ንፍቅና ነው የሚሆነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) (አሽሀዱ አንላ ኢላሀ ኢለሏህ (በትክክል የሚመለክ ከአላህ (ﷻ) ሌላ የለም ፡ ሙሐመድ ረሱሉላህ የአላህ (ﷻ)መልዕክተኛ ናቸው ብየ እመሰክራለሁ፡፡ በእነዚህ በሁለቱ ሳይጠራጠር ከአላህ (ﷻ) ጋር መገናኘት የቻለ ሰው ጀነት ገባ) ብለዋል ፡ሙስሊም ዘግበዉታል።.

❸ **መቀበል /አልቀቡል/፡-** ላኢላሀ ኢለላህን ካወቅህና ካረጋገጥክ ለዚህ ማረጋገጥህ ዉጤት ሊኖርህ ይገባል፡፡ ይህዉም ይህች የምስክር ቃል ግዴታ አድርጋ የያዘችዉን በልብም ሆነ በምላስም መተግበርና መቀበል ነው፡፡ የተውሂድን ጥሪ

---

[1] -ሰዎች መመስከር ያለባቸው በሚያውቁት እንጂ በማያውቁት ነገር ፈፅሞ መናገር እንደሌለባቸው፡፡

በትዕቢትም ሆነ በሞገደኝነት ወይም በምቀኝነት የተቃወመና ያልተቀበለ ከሃዲ ነው፡ ፡ አላህ (ﷻ) በትዕቢት የተቃወሙትን ሰዎች (እነርሱ ከአላህ ሌላ አምላክ የለም በተባሉ ጊዜ ይኮሩ ነበሩ፡፡) (37፡35) በማለት ገልጿቸዋል፡፡

❹ መታዘዝ /አእጣዓህ/ይህም የሚረጋገጠው አላህ (ﷻ) የደነገገዉን በመተግበርና የከለከለዉን በመተው ነው፡፡ አላህ (ﷻ) እንዲህ አለ (መልካም ሰሪ ሆኖ ፊቱን ወደ አላህ የሚሰጥ ሰው ጠንካራ ገመድ በእርግጥ ጨበጠ፡፡ የነገሩ ሁሉ ፍጻሜ ወደ አላህ ነው፡፡) (31፡22)

❺ እውነተኝነት/አስ- ስድቅ/፡- ይህም ማለት ሲናገራት እዉነተኛ ሆኖ ዉሸትን ተፃርሮ መሆን አለበት፡ ልቡ እያስተባበለ በምላሱ ብቻ የሚናገራት ሙናፊቅ ይሆናል፡፡ ቁርአን ሙናፊቆችን ሲያወግዝ እንዲህ ይላል (...በልቦቻቸው ውስጥ የሌለውን ነገር በምላሶቻቸው ይናገራሉ፡) (48፡11)

❻ መውደድ/አል-መሃባህ/፡- የምስክርነት ቃሏን፣ መልዕክቷንና በሷ የሚሰሩትን ሰዎች መውደድ ተገቢ ነው። አንድ ሰዉ ጌታዉን የመውደዱ ምልክት ስሜቱ ከሚወደውና አላህ (ﷻ) ከሚወደው የአላህን (ﷻ) ዉዴታ ማስቀደም፤ የአላህን (ﷻ) ወዳጆች ወዳጁ ማድረግ፤ ጠላቶቹን ጠላቱ ማድረግ፤ ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) መከተልና መመሪያቸዉን ማክበር ነው፡፡

❼ ፍፁምነት/አልኢኽላስ/የምስክር ቃሏን ሲናገርም ሆነ በእሷ ሲሰራ ለአላህ ብቻ የማድረግ ስሜት/መኖር ነው፡፡ አላህ (ﷻ) እንዲህ አለ (አላህ ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ ወደ ቀጥተኞች መንገድ የተዘነበሉ ሆነው ሊገዙት ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ፣ ዘካንም ሊሰጡ እንጂ አልታዘዙም። ይህም የቀጥተኞይቱ (ሃይማኖት) ድንጋጌ ነው።) (98፡5) ነቢዩ ሙሐመድም (ﷺ) አላህ የእሱን ዉዴታ ፈልጎ በፍፁምነት ላኢላሀ ኢለሏህን የተናገረን ሰው እሳት በሱ ላይ እርም አድርጓል) ብለዋል፡፡ ከእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎችም ጋር እስከ ዕለተ ሞት ድረስ በእሷ ላይ መፅናት ያስፈልጋል፡፡

## ሙሐመድ ረሱሉላህ – ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር

የሞተ ሰው በቀብር ዉስጥ ይፈተናል:: ስለ ሶስት ነገሮችም ይጠየቃል:: ሁሉንም ከመለሰ ነፃ ይወጣል:: ካልመለሰ ግን ይጠፋል / ይከስራል:: ከነዚህ ጥያቄች መካከል ነቢይህ ማን ነው ? የሚለው ጥያቄ ይገኝበታል:: ይህን ጥያቄ በዱንያ ላይ ሳለ መስፈርቶቹን አሟልቶ የነበረ ሰውና አላህ በቀብር ዉሰጥ ፅናቱን ሰጥቶት ልጅም ሆነ ገንዘብ በማይጠቅምበት በዚያ ቀን እንድትጠቅመው ያደረገለት ሰው ካልሆነ በስተቀር ለትክክለኛው መልስ ሁሉም ሰዉ አይታደልም:: እነዚህ መስፈርቶችም፡-

❶ ነቢዩ ሙሐመድ ያዘዙትን መታዘዝ ነው፡፡ ይህም ሲባል አላህ (-መልዕክተኛውን የሚታዘዝ ሰው ሁሉ በርግጥ አላህን ታዘዘ፡፡ ከትዕዛዝም የሸሸ ሰው (አያሳስብህ):: በርሱ ላይ ጠባቂ አድርገን አልላክንህምና:: (4፡80) ሌላዉ ደግሞ (ሙሐመድ ሆይ! አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ እኔን ተከተሉኝ:: አላህ ይወዳችኋል፡፡ ሀጢአቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና:: አላህ መሓሪና አዛኝ ነው- በላቸው:: (3፡31) በማለት እሳቸዉን እንድንታዘዝ ስላዘዘን ነው፡፡ ያለምንም ገደብ ጀነት መግባት ያለምንም ገደብ እሳቸዉን በመታዘዝ የሚገኝ እድል ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ (ህዝቦቼ ሁሉ እንቢ ያለ ሲቀር - ጀነት ይገባሉ አሉ፡፡ ሶሃቦችም - የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ማን ነው እንቢ የሚለው! - ሲሏቸው ‘ የታዘዘኝ ሰው ጀነት ይገባል:: ያልታዘዘኝ ደግሞ እንቢ አለ፡፡) ብለዋል፡፡ ነቢዩን እወዳለሁ የሚል ሰው ሁሉ እሳቸዉን መታዘዝ ግዴታው ነው፡፡ ምክኒያቱም መታዘዝ የመውደድ ዉጤት ነዉና፡፡ እሳቸዉን ሳይታዘዝና ሳይከተል እወዳቸዋለሁ በማለት የሚሞግት ሰው ሙግቱ የሐሰት ነው፡፡

❷ የተናገሩትን ሁሉ እዉነት ነዉ ብሎ ማመን:: ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)

ከተዘገቡ ነገሮች አንድን ነገር በልብወለዱ ወይም በስሜቱ ተገፋፍቶ ያስተባበለ ሰው አላህንና መልዕክተኛዉን አስተባብሏል፡፡ ምክኒያቱም ነቢዩ ከስህተትና ከዉሸት የፀዱ ናቸዉና፡፡ አላህ እንዲህ አለ (ከልብወለድ አይናገርም ፡ እርሱ /ቁርአን / ከአላህ የተወረደለት እንጂ ሌላ አይደለም፡፡) (53፡3)

❸ እሣቸዉ የከለከሉትንና ያስጠነቀቁትን መራቅ፡፡ ይህዉም ከወንጀሎች ሁሉ ታላቁ ከተባለው ከሽርክ አንስቶ በታላላቅ ወንጀሎች አልፎ እስከ ጥቃቅን ወንጀሎች ድረስ ያሉትን መራቅ ነው፡፡ ማንኛዉም ሙስሊም ለነቢዩ ባለው ዉዴታ ልክ እምነቱ ይጨምራል፡፡ እምነቱ በጨመረው ልክም አላህ መልካም ስራዎችን ያስወድደዋል፡፡ መጥፎ ተግባሮችን ያስጠላዋል፡፡

❹ አላህን በሳቸው አማካኝነት በተደነገገው የሸሪዓ ህግ መሰረት ብቻ እንጂ አለማምለክ ነው፡፡ አምልኮትን በተመለከተ የቅድሚያ መሰረቱ መከልከል ነው፡፡ እናም ነቢዩ (ﷺ) ባስተማሩት መሰረት እንጂ አላህን ማምለክ አይገባም፡፡ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ነቢዩ (ትዕዛዛችን የሌለበትን ስራ የሰራ ሰው ስራው ዉድቅ ነው) ብለዋል፡፡

ጠቃሚ ነገር፡- ነቢዩንና (ﷺ) እሣቸዉ ያመጡትን ሁሉ መውደድ ግዴታ ነዉ፡ ነቢዩ ይዘዉ ከመጡት ነገር አንዱን እንኳን የጠላ ከሀዲ ነዉ፡፡ ደግሞም መውደድ ብቻዉን በቂ አይደለም:: ከሁሉ ነገር ከራስህ ጭምር አስበልጠህ ነቢዩን መውደድ አለብህ፡፡ ምክንያቱም አንድን ነገር የወደደ ሰው ከሁሉም ያስቀድመዋልና፡፡ የእሱን ፍላጎትም ከፍላጎቶች ሁሉ ያስቀድማል፡፡ እናም ትክክለኛ የነቢዩ ወዳጅ ማለት የዚሁ ምልክት በላዩ ላይ የሚታይበት ሰው ነው፡፡ ይህም ሲባል በሁሉ ነገር እሳቸዉን መከተል፤ ፈለጋቸውን መተግበር፤ ንግግራቸዉንም ሆነ ተግባራቸዉን መከተል፤ የከለከሉትን መከልከል ፤ በችግርም ጊዜ ሆነ በድሎት በድካምም ጊዜ ሆነ በጥንካሬ የእሳቸዉን ስነ ምግባር መላበስ ነው፡፡ ምክኒያቱም መከተልና መታዘዝ የዉዴታ ዉጤት ነዉና፡፡ ያለ እነሱ ዉዴታ ተአማኒነት የለዉም፡፡

ነቢዩን (ﷺ) መውደድ ብዙ ምልክቶች አሉት፡፡ ከብዙ በጥቂቱ፡ 1- በብዛት እሳቸዉን ማውሳትና በእሳቸው ላይ ሶለዋት ማውረድ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድን ነገር የወደደ ሰው በብዛት ያነሳዋልና፡፡ 2- ከእርሳቸው ጋር ለመገናኘት መናፈቅ/መጓጓት ነው፡፡ ምክንያቱም የወደደ ሰው የወደደዉን ለማግኘት ይጓጓልና፡፡ 3- እሳቸዉን ማክበርና ስማቸው ሲወሳ በተገቢዉ መልኩ ማላቅ ነው፡፡ ኢስሃቅ የተባለ ዐሊም (የነብዩ ባልደረቦች ነብዩ ከሞቱ በኋላ ስማቸው እንኳን ሲወሳ ሰዉነታቸው ይንቀጠቀጥና ያለቅሱ ነበር፡) ብለዋል። 4- የጠላቸዉን መጥላት፡ የተጣላቸዉን መጣላት፣ ሱናቸዉን የሚንቅን፣ የሙናፊቆችንና የቢድዓ ሰዎች መሸሽ ነው፡፡ 5- ነብዩ የወደዷቸዉን ቤተሰቦቻቸውን፣ ሚስቶቻቸዉን፣ የሙሃጂርና የአንሷር ጓደኞቻቸዉን መውደድ፣ የጠላቸዉን ወይንም የሰደባቸዉን መጥላት ነው፡፡ 6- በመልካም ስነ ምግባራቸው መቀረፅ፡፡ ዓኢሻህ እንዳሉት የነብዩ ስነምግባር ቁርአን ነበር፡ ይህም ማለት ከቁርአን መመሪያ ዝንፍ የማይሉ ነበሩ ማለት ነው፡፡

የነብዩን (ﷺ) ባህሪን በተመለከተ ነብዩ የጀግኖች ሁሉ ጀግና ነበሩ፡ ይበልጥ ጀግና የሚሆኑት ደግሞ በጦርነት ላይ ነዉ፡፡ የቸሮች ሁሉ የበላይ ቸርም ነበሩ፡፡ ይበልጥ ይቸሩ /ይለግሱ/ የነበረውም በረመዷን ዉስጥ ነበር፡፡ ለሰው ደግ ከሚያስቡ ሰዎች ሁሉ ደግ አሳቢ ነበሩ፡፡ ከቻዮች /ታጋሾች/ ሁሉ ቻይም ነበሩ፡፡ አንድም ቀን እንኳን ለራሳቸው ተበቅለው አያውቁም፡፡ በአላህ ዲን ላይ ወደር የለሽ ጠንካራ ነበሩ፡፡ ከግርማ ሞገሳቸው ጋር ራሳቸዉን ዝቅ አድራጊ ነበሩ ፡፡ ከጫጉላ ሙሽራ የበለጠ አይን አፋርና ሰው አክባሪም ነበሩ፡፡ ለቤተሰባቸው በደግነታቸዉ በላጭ፡ ለፍጥረታትም ከፍጡሩ ሁሉ አዛኝ ነበሩ፡፡ ሌሎችም ያልተዳሰሱ ብዙ መልካም ባህሪያት አሏቸው፡፡

# ስለ ጠሃራ /ንፅህና /በኢስላም

ሶላት ከኢስላም ማዕዘናት ሁለተኛው ነው:: እናም ሶላት ያለ ንፅህና ዋጋ የለዉም ። ንፅህና በዉሃ ወይም በአፈር እንጂ በሌላ ነገር አይሆንም::

የዉሃ አይነቶች ሁለት ናቸው:: እነሱም፡-

1)ንፁህ ዉሃ የሚባለው ሲሆን:- እርሱም ለራሱ ንፁህ ሆኖ ሌላዉንም ነገር ማፅዳት የሚችል ዉሃ ነው:: ከራሱ ንፅህና አልፎ ሌላን ማፅዳት የሚችል ዉሃ ማለት ደግሞ የተፈጥሮ ባህሪዉን ያልለቀቀ የዉቅያኖስ፤ የጉድጓድ፤ የምንጭና የጅረት ዉሃዎች ማለት ነው:: ይህ አይነቱ ዉሃም ሀደስን[1] ያነሳል፡፡ ቆሻሻን ያስወግዳል::

2)የተነጀሰ ዉሃ ሲሆን:- እሱም ጥቂት ከሆነ ነጃሳ ነገር የተደባለቀበት ሲሆን ብዙ ከሆነ ግን ጣዕሙ ወይም መልኩ ወይም ሽታው በነጃሳው የተለወጠ ዉሃ ነው::

ማሳሰቢያ: ብዙ ዉሓ የሚነጀሰው ነጃሳው ከባህሪያቶቹ መካከል አንዱን ማለትም መልኩ ወይም ጣዕሙ ወይም ሽታው ሲቀየር ነው:: ጥቂት ዉሃ ደግሞ ነጃሳው ከሱ ጋር በመደባለቁ ብቻ ይነጀሳል:: ዉሃ ብዙ የሚባለው ከሁለት ቁልለት/ ከሁለት መቶ አስር ሊትር / የበለጠ እንደሆነ ነው::

ዕቃች: ከወርቅና ከብር ሌላ በሆነ ንፁህ ዕቃዎቹ ሁሉ መጠቀም ይፈቀዳል:: በሁለቱም/ጠሃራን /ንፅህናን ማግኘት ወንጀል ቢኖረዉም ይቻላል:: መነጀሳቸው ያልተረጋገጡ/ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችን/ የካፊሮችን እቃቻቸዉንና ልብሶቻቸውን መጠቀም ይፈቀዳል::

የበክት ቆዳ ሁሉም ነጃሳ ነው:: የበከተ ማለት ለሁለት ይከፈላል :: 1) በምንም መልኩ ስጋው የማይበላና 2) ስጋው የሚበላም ሆኖ ሣይታ ረድ የሞተ ሲሆን:: ስጋው የሚበላ ሆኖ የበከተ ቆዳው ከተነከረ ለፈሣሽ ሣይሆን ለደረቅ ነገር ብቻ በሱ መጠቀም ይፈቀዳል::

ኢስቲንጃእ፡- በሁለቱ መፀዳጃዎች በኩል የሚወጡ ነገሮችን ማስወገድ ነው:: ይህም ተግባር በዉሃ ከሆነ ኢሰቲንጃእ ሲባል በድንጋይ ወይም በወረቀት ከሆነ ደግሞ ኢስቲጅማር ይባላል:: በሁለተኛው ላይ ከዚህ የሚከተሉት ሁኔታች ሊሟሉ ይገባል:: ኢሰቲጅማር የሚደረግበት ነገር ንፁህ፤ የተፈቀደ፤ የሚያፀዳ / ነጃሣን ማስወገድ የሚችል/ መሆንና የሚበላ ነገር አለመሆን ይኖርበታል።

ኢስቲጅማር በሶስትና ከዚያም በላይ በሆኑ ድንጋዮች ይሆናል:: ከሁለቱ በአንዱ መንገድ የወጣን ሁሉ በዉሃ ወይም በድንጋይና መሰል ነገሮች ማስወገድ ግዴታ ነው::

የሚፀዳዳ ሰው በመፀዳጃ ቦታ ላይ ከአስፈላጊ ሰዐት በላይ መዘግየት፤ በዉሃ መውረጃ ላይ ወይም በመንገድ፤ ወይም ለሰዎች አገልግሎት በሚሰጥ ጥላ ላይ፤ ወይም ከምታፈራ ዛፍ ስር መፀዳዳትና በሜዳ ላይ ሲፀዳዳ ወደ ከዕባ መዞሩ ክልክል ነው::

ለሚፀዳዳ ሰው የአላህ ስም ያለበትን ነገር ይዞ ወደ መፀዳጃ ቤት መግባት፤ እየተፀዳዳ ባለበት ቦታ ላይ መነጋገር፣ በቦይና መሰል ነገሮች ላይ መሽናትን የመፀዳጃ አካሉን በቀኝ እጁ መንካት፤ በቤተ መፀዳጃ ዉስጥ ሆኖ ወደ ቂብላ መዞር ይጠላል:: ለችግር ጊዜ ግን ይህ ሁሉ ይፈቀዳል:: የሚፀዳዳ ሰው በትጥበትም ሆነ በማበስ ጊዜ በነጠላ ቁጥር ማድረጉ ይወደዳል:: በዉሃና በድንጋይ ማድረግና ሁለቱን በአንድ መሰብሰቡ የተመረጠ ነው::

ሲዋክ ፡- እንደ አራክ ዛፍ ባለ ለስላሳ እንጨት ጥርስን መፋቅ ሱና ነው:: በተለይም ወደ ሶላት ለመግባት ባሰቡ ጊዜ፤ ቁርአንን ሊቀሩ ሲያስቡ፤ በዉዱእ ጊዜ አፍን ከመጉመጥመጥ በፊት፤ ከዕንቅልፍ ሲነሱ፤ ወደ መስጊድና ወደ ቤት ሲገባ፤ የአፍ ጠረን /ሽታ/ ሲለወጥና በመሳሰሉት ጊዜ ሲዋክ መጠቀም ይወደዳል:: በሲዋክም ጊዜ ሆነ በንፅህና ጊዜ በቀኝ በኩል ባለ አካል መጀመርና የማይወደዱ ነገሮችን ለማስወገድ ደግሞ በግራ እጅ መጠቀም ሱና ነው::

ዉዱእ:- ግዴታዎቹ -: 1ኛው፡- ፊትን መታጠብ ሲሆን፤ መጉመጥመጥና በአፍንጫ

---

[1] -ዉዱእ የሚያስፈቱ ነገሮች ያጋጠመው ሰው ሐደስ ያለበት ይባላል፡፡

ዉሃን መውሰድ በዚሁ ግዴታ ዉስጥ ይጠቃለላል:: 2ኛው:- እጆችን ከጣት ጫፍ አንስቶ እስከ ክርን ድረስ ማጠብ፤ 3ኛው:- ሙሉ እራስን ከጆሮች ጋር አንድ ጊዜ ማበስ:: 4ኛው:- እግርን ከቁርጭምጭሚት ጋር ማጠብ 5ኛው:- ቅደም ተከተሉን /ተራዉን /መጠበቅ 6ኛው:- ማጠጋጋት.

ዋጂቦቹ፤- መጀመሪያ ላይ ቢስሚላህ ማለት[1]፤ ከሌሊት ዕንቅልፍ የነቃ ሰው በዉሃ ዉስጥ እጁን ከማስገባቱ በፊት መዳፎቹን ሶስት ጊዜ ማጠብ ናቸው::

ሱናዎች:- ሲዋክ፤ መጀመሪያ ላይ መዳፎችን መታጠብ፤ ፊትን ከመታጠብ በፊት መጉመጥመጥና አፍንጫን ውሃ ማስቀደም፤ በመጉመጥመጥና አፍንጫን በሚታጠቡበት ጊዜ ፆመኛ ላልሆነ ሰው በደንብ ማዳረስ፤ ብዛት ያለዉን የፂም ፀጉር መፈልፈል፤ ጣቶችን መፈልፈል፤ በቀኝ በቀኝ መጀመር፤ አካሎችን ሁለትና ሶስት ጊዜ ማጠብ፤ አፍንጫን በቀኝ እጅ መማግና በግራ ማስወጣት፤ አካሎችን መፈግፈግ፤ ዉዱእን ማሳመር፤ በስተመጨረሻ ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በተነገረው ዱዓ ማሳረግ::

በዉዱእ ጊዜ የሚጠሉ ነገሮች- በሙቅ ዉሃም ሆነ በጣም በቀዘቀዘ ዉሃ ዉዱዕ ማድረግ፤ ለሚታጠቡ አካሎች ከሶስት በላይ መጨመር፤ ከዉዱዕ በኋላ ዉሃን ከአካሉ ማራገፍ፣ ዉስጥ አይንን ማጠብ ሲሆን በፎጣ ማዳረቅ ግን ችግር የለዉም::

ማሳሰቢያ:- በመጉመጥመጥ ጊዜ ዉሃን በአፍ ዉስጥ ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል:: በአፍንጫ ዉሃን መሣብ ሲባልም ዉሃን በእጁ ብቻ ሳይሆን በትንፋሽ ወደ ዉስጥ ማስገባቱና መሳቡ አስፈላጊ ነው:: እንደዚሁም በመናፈጥ ዉሃዉን ከአፍንጫ ማስወጣት ይገባል:: መጉመጥመጥም ሆነ በአፍንጫ ዉሃን ማስገባት በዚህ መልኩ ካልሆነ በስተቀር አይሆንም::

የዉዱእ ስርአት:- የዉዱእ አደራረግ በልብ በማሰብና የአላህን ስም በማውሳት ዉዱዕ ይጀመራል፤ አስቀድሞ መዳፎችን ማጠብ ዉዱዕ በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ ይወደዳል:: በጣም የሚወደደው ግን በተለይ ከእንቅልፉ ለተነሳ ሰው ነው::

ማሳሳቢያ:- በዉዱእ ጊዜ የሚታጠቡ አካሎችን ከሶስት ከሶስት ጊዜ በላይ ማጠብ ይጠላል:: አንድ ጊዜ መጉመጥመጥ ግዴታ ሲሆን ከዚያ በላይ መጨመሩ ግን የበለጠ ነው:: አንድ ጊዜ አፍንጫን ማጠብ ግዴታ ሲሆን ሶስት ጊዜ ማድረጉ ግን ተመራጭ ነዉ::

የፊት ክልሉ/ገደቡ/ በርዝመቱ በተለምዶ የፀጉር መብቀያ ተብሎ ከሚጠራው ቦታ አንስቶ እስከ መንጋጭላ ድረስ ሲሆን በወርዱ ደግሞ ከአንዱ ጆሮ አንስቶ እስከዚያኛዉ ጆሮ ድረስ ነው:: አንድ ጊዜ እስከ ክርኖቹ ድረስ እጆቹን ማጠብ ግዴታ ነው:: ሶስት ጊዜ ማድረጉ ግን ይበልጣል::

በመቀጠል የራሱን ፀጉር ይበስ:: አመልካች ጣቶቹን በጆሮዎቹ ክፍተት ዉስጥ ያስገባ:: በአውራ ጣቶቹ ደግሞ የጆሮቹን ጀርባ ይበስ:: ይህ ሁሉ አንድ ጊዜ ብቻ ነው::

ልዩ ልዩ ማሳሰቢያዎች:- 1) በመጉመጥመጥ ጊዜ ዉሃን አስገብቶ ማውጣቱ ብቻ በቂ አይደለም በዉስጡ ማንቀሳቀስ አስፈላጊ ነው:: 2) በዉዱእ ዉስጥ ሲዋክን መጠቀም ይወደዳል:: 3) ፂም አልፎ አልፎ /ስስ/ ከሆነ መብቀያ ቆዳዉን ማጠብ ግዴ ነው:: ጥቅጥቅ ያለና ብዙ ከሆነ ግን የፀጉሩን ላይ ላዩን ብቻ ማጠብ ይበቃል:: 4)ቀኝ ጁጁን ከግራው በፊት ማጠብ ይወደዳል:: ከዚያም እግሮቹን ከቁርጪምጭሚቶቹ ጋር ይጠብ:: አንድ ጊዜ ማጠቡ ግዴታ ሲሆን ሶስት ጊዜ ማጠቡ ግን ይበልጣል:: 5) ከራስ ማበስ የሚገደደው ከፊቱ መጀመሪያ አንስቶ ወደ ኋላው ነው:: 6) ከጆሮ በላይ ያለው ባዶ ቦታ ከራስ አካል ጋር ነው የሚቆጠረው:: 7) ከዉዱዕ በኋላ አሽሀዱ አንላ ኢላህ ኢለሏህ ወህደሁ ላሸሪከለሁ ወአሽሀዱ አነ ሙሐመድን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ ማለት ያስፈልጋል::

(በኹፍ) ጫማ ላይ ማበስ:- ኹፍ ማለት በእግር ላይ የሚለበስ ቆዳም ይሁን ሌላ ነገር ማለት ነው:: ሱፍና መሰሉ ከሆነ ግን ጀውረብ ይባላል:: በነሱ ላይ ማበስ በትንሹ ሐደስ

[1] በአህመድብን ሐንበል መዝሀብ ላይ የተመሰረተ ነው::

ላይ ብቻ ሲሆን ይቻላል፡፡
**ማበስ የሚቻለውም፡-**
1) በተሟላ ንፅህና የተለበሱ ከሆነ፤
2) ንፅህናው በዉሃ ከሆነ፤
3)ጫማዎቹ ማጠብ ግዴታ የሆኑ ቦታዎችን መሸፈን የሚችሉ ከሆኑ፤
4) ጫማዎቹ ከተፈቀደ ነገር የተሰሩ የተፈቀዱ መሆንና፤
5) ጫማዎቹ ንፁህ የሆኑ እንደሆነ ነዉ፤
**ስለ ጥምጣም፡-** በጥምጣም ላይ ማበስ የሚቻለው ከዚህ የሚከተሉት ከተሟሉ ብቻ ነው፡፡ 1) ጥምጣሙ ለወንድ መሆን፤
2) ጥምጣሙ የተለመደዉን የራስ ቅል አካል ሙሉዉን መሸፈን መቻል፤
3) የሚያብሰው ከአነስተኛው ሐደስ[1] ሲሆን፤
4) ንፅህናዉ በዉሃ የሆነ እንደሆነ ነዉ፡፡
**ስለ ሴቶች ጉፍታ ፡-** ሴቶች በጉፍታ ላይ ማበስ የሚቻለው ከዚህ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ካሟላ ብቻ ነው፡፡ 1) ጉፍታው ለሴት መሆን 2) በአንገት ስር የሚጠመጠም ሲሆን 3) ጉፍታው የተለመደዉን የራስ አካል መሸፈን 4) ከአነስተኛው ሐደስ መሆን 5)ንፅህናዉ በዉሃ የሆነ እንደሆነ ነዉ፡፡
**የሚታበስበት ዘመን ርዝመት፡** በሀገሩ ለሚኖር ሰው አንድ ቀን ከነሌሊቱ ብቻ ሲሆን ሶላት የሚያሳጥሩበት ጉዞ ላይ ለሆነ መንገደኛ ደግሞ ሶስት ቀን ከነሌሊቱ ነው፡፡
**የሚጀመርበት ወቅት** ሁሉን አሟልቶ ከለበሰ በኋላ ዉዱዕ ፈትቶ ከሚያደርገው ማበስ አንስቶ በሁለተኛው ቀን እስከ መሰል ሰዓቱ ድረስ ነው፡፡
**ጠቃሚ ነገር፡-** በጉዞ ላይ እያለ ማበስ ጀምሮ ከዚያም ወደ አገር ቤት የገባ / የደረሰ / ሰው፤ ወይም በአገር ቤት እያለ ማበስ ጀምሮ ከዚያ ወደ ጉዞ የገባ ሰው፤ ወይም መቸ ማበስ እንደጀመረ የተጠራጠረ ሰው በአገሩ እንዳለ ሰዉ ሆኖ የማበሻ ቀኑን ይጨርስ፡፡
**በታሰረ (ታጀለ) ቁስል ላይ ማበስ፡-** ከዚህ በታች ያሉትን መስፈርቶች ያሟላ ሰው በታሰረ (ታጀለ) ቁስል ላይ ማበስ ይችላል፡፡ መስፈርቱም
1)ማጀያዉ ከጤናው አኳያ መፈለጉ፤
2)ማጀያዉ ከተፈላጊው ቦታ ዉጭ አለመሆኑ፤
3)በማበስና በሚታጠቡ አካሎች መካከል ማከታተል ነው፡፡ ከተፈላጊው ቦታ በላይ ተጨማሪ ከታሰረ የተጨመረዉን ማንሳትና ማጠብ ግድ ይሆናል፡፡ ችግር ያመጣብኛል ብሎ ከሰጋ ግን አለማንሳቱ ችግር የለዉም፡፡
**ከጫማ መታበስ ያለበት ልክ** ከእግር ጣቱ አንስቶ እስከ ቅልጥሙ ድረስ ካለው የጫማው ዉጫዊ አካል ብዙዉን ማበስ ነው፡፡ አስተባበሱም በሁለት እጆቹ ጣቶች በተን አድርጎ ማበስ ነው፡፡
**ጠቃሚ ነገሮች፡-** የሚመረጠው የሁለቱንም እግሮች ጫማ አንድ ጊዜ ማበስ ነው፡፡ የጫማዉን ስሩንም ሆነ ኋላዉን ማበስ ሱና አይደለም፡፡ ብሎም እነሱን ብቻ አብሶ ቢቀር እንዳበሰ አይቆጠርም፡፡ በማበስ ፈንታ ጫማ ማጠብም ሆነ ማበሱንም መደጋገም ይጠላል፡፡ ጥምጣምንም ሆነ ጉፍታን አብዛኛዉን ክፍላቸዉን ማበሱ በቂ ነው፡፡
**ዉዱእን የሚያበላሹ ነገሮች፡-**
1) ከሽንትና ከሰገራ መውጫ የሚወጣ ነጅሳ ያልሆነ ነገር ለምሳሌ ፈስና የዘር ፍሬ ወይም ነጃሳ ነገር ሽንትና መዝይ፤
2) በእንቅልፍም ሆነ በአውድቅ አዕምሮን መሳት (ቀላል የሆነ እንቅልፍ ቁጭ ብሎም

[1] ሐደስ ማለት ዉዱእ መፍታት ጀናባ መሆን የወር አበባና የወሊድ ደም መኖር ማለት ነው፡፡

ሆነ ተቁሞ ዉዱዕ አያበላሽም፤

3) ሽንት ወይም ሰገራ ከተለመደው መውጫቸው ዉጭ በሌላ ከወጡ፤

4) ከሽንትና ከሰገራ ሌላ የሆኑ አስጠይ ነጃሳ ነገሮች ለምሳሌ ብዙ ደም

5) የግመል ስጋን መብላት[1]

6) ብልትን መንካት[2]

7) ሴት የወንድን ሀፍረተገላን ወይም ወንድ የሴትን ሀፍረተ ገላ በስሜት ላይ ሆኖ ያለምንም መከላከያ መንካት[3]፤

8) ከዲን /እስልምና/ መውጣት /መክፈር/ ናቸው፡፡ንፁህነቱን ያረጋገጠና ጠሃራውን የተጠራጠረ ወይም የዚህ ተቃራኒ ሀሳብ ያጋጠመው ሰው በእርግጠኛነት ባመነበት ላይ ይጓዝ፡፡

ገላ ትጥበት ፡-ገላ ትጥበትን ግዴታ የሚያደርጉ ነገሮች፡፡

1) የዘር ፈሳሽ  በሀይል ስሜት ታጅቦ ወይም እንቅልፍ ከተኛ ሰው በስሜትም ሆነ ያለስሜትም መፍሰስ

2)የወንድ ብልት አካሉ የዘር ፈሳሽ ባይወጣዉ እንኳን በሴት ልጅ ብልት ዉስጥ መግባት

3)ካፊር የነበረ ሰውም ይሁን ቀድሞ ሙስሊም የነበረና ከፍሮ የተመለሰም ቢሆን መስለም፤

4)የወር አበባ ደም መታየት፤

5)የወሊድ ደም መፍሰስ

6)የሙስሊም መሞት ናቸው፡፡

የትጥበት ግዴታዎች፡-

ሙሉ አካላቱንና የአፉንና የአፍንጫዉን ዉስጥ አካል ማዳረሱ በቂ ነው፡፡

ትጥበት የተሟላ የሚሆነው በዘጠኝ ነገሮች ነው፡፡ 1)መነየት 2)ቢስሚላህ ማለት 3)እቃው ዉስጥ ሳያስገቡ በፊት ሁለት እጆችን መታጠብ 4)መፀዳጃዉንና እሱ የነካካዉን አካባቢ ማጠብ 5) ዉዱዕ ማድረግ 6)በራሱ ላይ ዉሃን ሶስት ጊዜ ማፍሰስ 7)በሰዉነቱ ላይ ዉሃን ማፍሰስ 8) በሁለት እጆቹ አካሉን ማሸት 9) በቀኝ በቀኝ ጎኑ መጀመር ናቸው፡፡

ዉዱእ የሌለው ሰው 1)ቁርአንን መንካት 2)ሶላት መስገድ፤ 3)ጠዋፍን ሲከለከል፤ ጀናባ ያለበት ሰው ደግሞ ከዚህ በተጨማሪ 4)ቁርአንን ማንበብ 5)በመስጂድ ዉስጥ መቆየት ይከለከላል፡፡

ጀናባ ያለበት ሰው ያለ ዉዱዕ መተኛቱና በትጥበት ጊዜ ዉሃን ማባከኑ ይጠላል፡፡

*ተየሙም፡ ተየሙም ለማድረግ ቅድመ መስፈርቶቹ

1)ዉሃን ማጣት

2)በንጹህ፣ በተፈቀደ፣ አቧራ ባለውና ያልተቃጠለ አፈር መሆኑ ናቸው፡፡

የዉዱእ ግዴታዎቹ፡- ሙሉ ፊትን ማበስ፤ ከዚያም እጆችን እስከመዳፍ[4] መታጠፊያ ድረስ ማበስና በተራቸዉና በተከታታይ ማድረግ ናቸው፡፡

ዉዱእን የሚያበላሹት፡

1)ዉዱዕን የሚያበላሹ ነገሮች ሁሉ፤

2)ዉሃን አጥቶ ከሆነ ተየሙም ያደረገዉ ችግሩ ለቆ ዉሃ መገኘቱ፤

---

[1] ይህ ጉዳይ በሐንበሊ መዝሐብ ነው እንጂ በሀገራችን በብዛት በሚሰራባቸው መዝሐቦች አያበላሽም፡፡

[2] ይህም ጉዳይ ዉዝግብ አለበት፡፡

[3] ይህ ጉዳይ በመዝሀቦች መካከል ከፍተኛ ልዩነትና ክርክር ያለበት ነገር ነው፡፡ እዚህ ላይ የሰፈረው የአንዱ ብቻ ነው፡፡ ከመረጃ አኳያ ፈሳሽ ከሌለው አያበላሽም፡፡

[4] እስከ ክርን ድረስ ነው መታበስ ያለበት የሚልም አለ፡፡

3)ተየሙም እንዲያደርግ ያስቻለው ምክንያት መወገድ ለምሳሌ ታሞ የነበረው የዳነ እንደሆነ ናቸው፡፡

**የዉዱእ ሱናዎች፡-**

1) ከትልቁ ዉዱእ መፍታት ከሆነ ተራዉን መጠበቅና ማከታተል ናቸው
2) ወደ መጨረሻ ማዘግየት
3) ውዱእ ካጠናቀቁ በኋላ የሚባሉ ዱዓዎችን ከተየሙም በኋላም ማለት ናቸው።

**የሚጠሉት፡-** በመሬት ላይ ለተየሙም አፈር መምታትን መደጋገም ይጠላል፡፡

**የተየሙም ስርአት፡-** መጀመሪያ ለተየሙም መነየት፤ ቢስሚላህ ማለት፤ በሁለቱም እጆች አንድ ጊዜ አፈርን መምታት፤ ከዚያም በመጀመሪያ የሁለት እጆችን ዉስጣዊ አካል በፊቱና በጺሙ ላይ በማሳለፍ ፊትን ማበስ፤ ቀጥሎም የቀኝ እጁን መዳፍ ዉጫዊ አካል በግራ እጁ ዉስጣዊ አካል ማበስና የግራ እጁን መዳፍ ዉጫዊ አካልም በቀኝ እጁ ዉስጣዊ አካል ማበስ ነው፡፡

**ነጃሳን ማስወገድ፡፡ ነጃሣዎች** ለሁለት ይከፈላሉ 1)አካላዊ ነጃሳዎች የሚባሉትና በምንም ነገር ማፅዳትየማይቻለው ሲሆን እሱም እንደ አሳማ ነው፡፡ **2) ዉስጣዊ ነጃሳ ሲሆን እሱም ንፁህ በሆነ ነገር ልብስ፤ ምድር ይመስል ነጃሳ ሲያርፍበት ነው፡፡ ይኸዎም ከዚህ ነው፡፡**

| አካላት | | ዉሳኔያቸው |
|---|---|---|
| እንሰሳዎች | ነጃሳዎች | ዉሻ፤ አሳማ፤ ከሁለቱ የተወለደ ፤ አካላቸዉ፤ ከድመት በላይ ትልቅ ሆኖ ከጋቸው የማይበላ በራሪም ሆነ የማይበር እንስሳ ሲሆን ይህ ክፍል ሽንቱ፤ ፋንድያዉ፤ ምራቁ፤ ላቡ፤ የዘር ፍሬው፤ ወተቱ፤ ንፍጡና ተዉከቱ ሁሉ ነጃሳ ነው፡፡ |
| | ጡሃራዎች | 1)የሰው ልጅ ሲሆን፤ ራሱም ፤ የዘር ፍሬው፡ ላቡ፡ ምራቁ፡ ወተቱ፤ ንፍጡ፤ ቀልሻቱ፤ የሴቶች ብልት እርጥበት ንፁህ ነው፡፡ እንደዚሁም ከሽንቱ፤ ከሰገራው ከመግዩና ከወድዩ ሌላ ያለው አካሉ በሙሉ ንፁህ ነው/ነጃሣ አይደለም/፡፡<br>2) ከጋው የሚበላ ሁሉ ሲሆን ይህም ሽንቱ፡ ፋንድያዉ፤ ምራቁ፡ ላቡ፡ የዘር ፍሬው፤ ወተቱ፤ ንፍጡና ያከታወከው፤ መግዩና ወድዩ ሁሉ ንጹህ ነው፡፡<br>3)መጠንቀቅ የማይቻል ነገር ለምሳሌ አህያ ድመት፤ አይጥና መሰላቸው ሲሆን የነኚህ ምራቃቸውና ላባቸው ብቻ ንፁህ ነው፡፡ |
| ሙታን /የሞቱት/ | ነጃሳ የቸው | 1) ሰው፤ አሳ፤ አንበጣና ፈሳሽ ደም የሌላቸው ነገሮች ለምሳሌ ፘንጥ፤ ጩጫን/ ጉንዳን/ና ተኋን ሲቀር የሞቱ ነገሮች ሁሉም ነጃሳ ነው፡፡ |
| ጠጣር ነገሮች | | መሬት፤ ድንጋይና መሰሎቹ ንፁኅ የቸው፡፡ |

**ጠቃሚ ነገሮች፡-** ✸ ደም፤ እዥና መግል ነጃሳዎች የቸው፡፡ ከንጹህ እንሰሳዎች ከሆኑ መጠኑ ጥቂት እስከሆነ ድረስ ችግር የለዉም፡፡ ✸ **ደምከሁለት ነገሮች** 1) ከአሳ የሚወጣ፤ 2)ከታረደ እንሰሳ አካል ላይ የሚቀር ደም ንፁኅ ነው፡፡ ✸ በህይወት እያሉ ከጋቸው ከሚበሉ እንሰሳት የተቆረጠ ማንኛዉም አካልና ቁራጭ ሠጋ **ነጃሳ የቸው፡፡** ✸ ነጃሳን ለማስወገድ ምንም ኒያ አያስፈልግም፡፡ በዝናብ እንኳን ቢወገድ ይፀዳል፡፡ ✸ ነጃሳ ነገሮችን በእጅ መንካት ወይም በቺሱ ላይ መጓዝ ዉዱእን አያበላሽም፡፡ የነካዉን ቦታና ልብስ ማፅዳት ብቻ በቂ ነው፡፡

**ነጃሳዎች የሚፀዱት** 1) በንፁህ ዉሃ በማጠብ 2) የሚጨመቅ ከሆነ በመጭመቅ 3) ማጠቡ ካላስለቀቀው በእጅ መፈግፈግ 4) ነጃሳው የዉሻ ልጋግ ከሆነ ሰባት ጊዜ በዉሃ አጥቦ ከምንተኛውን[1] በአፈር በማጠብ ነዉ፡፡

**ማሳሰቢያዎች፡-** ✸ በመሬት ላይ ያሉ ነጃሳዎች ፈሳሽ ከሆኑ ነጃሳው መልኩም ሆነ ጠረኑ እስከሚወገድ ድረስ ዉሃ ማፍሰሱ ይበቃል፡፡ በአይን የሚታይ አካል ያለው ለምሳሌ የሰገራ ዓይነት ከሆነ እራሱንና ምልክቱንም ማሰወገድ ግዴታ ነው፡፡ ✸ ያለ ዉሃ በምንም ማስወገድ ካልተቻለ ዉሃን መጠቀም ግድ ይሆናል፡፡ ✸ የነጃሳው ቦታ ባይታወቅ ሁሉም መታጠቡ እስከሚረጋገጥ ድረስ ማጠብ ግዴታ ነው፡፡ ✸ ለተርፍ /ሱና/ ሶላት ዉዱእ ያደረገ ሰው ፈርድ ሶላትም ሊሰግድበት ይችላል፡፡ ✸.የተኛ ወይም ፌስ የወጣው ሰዉ ዉዱእ ብቻ እንጂ ኢስተንጃእ ማድረግ አይጠበቅበትም፡፡ ምክንያቱም ፌስ ንፁህ ነዉና፡፡

---

[1] የግድ ስምንተኛው መሆን አለበት ሳይሆን። ከስምንቱ እንደኛው በአፈር መሁን ብቻ ነው።

# ሴት ነክ ህግጋት

## የሴት ልጅ የተፈጥሮ ደሞች መጀመሪያ (ሐይድና የበሽታ ደም)፡፡

### በመጀመሪያ የወር አበባ እና የበሽታ ደም

| ጉዳዩ | ዉሳኔው |
|---|---|
| ሴት ልጅ የወር አበባ[1] የምታይበት ትንሹና ብዙው ቀን | አነስተኛው ዘጠኝ አመት ሲሆን፣ ከዚህ በፊት የምታየው ደም ሁሉ የበሺታ ደም ነው፡፡ ብዙው ግን ገደብ የለዉም |
| አነስተኛ የወር አበባ የሚቆይበት ቀናት | ሀያ አራት ሰዓት ነው፡፡ |
| ከፍተኛ የወር አበባ የሚቆይበት ቀናት | አስራ አምስት ቀናት ነው ፡፡ ከዚህ ቁጥር በላይ ካየች የበሽታ ደም (ኢስቲሃዷህ) ነው፡፡[2] |
| በሁለት የሐይድ ዘመናት መካከል ያለው የንፅህና ቀናት | አስራ ሶስት ቀናት ነው፡፡ ይህ ከመሆኑ በፊት ደም ብታይ የበሽታ ደም ነው፡፡ |
| የአብዛኛ ሴቶች የወር አበባ የሚቆይበት ቀናት | ስድስት ወይም ሰባት ቀናት ነው፡፡ |
| የብዙ ሴቶች የንፅሕና ቀናት | ሀያ ሶስተ ወይም ሀያ አራት ቀናት ነው፡፡ |
| በዕርግዝና ዉሥጥ የሚታይ ደም የወር አበባ ይባላልን? | ከዕርጉዝ ሴት የሚፈስ ደምም ይሁን ድፍርስ[1] ወይም ብጫ[2] ነገር ሁሉ የበሽታ ደም ነው፡፡ |
| የወር አበባ የመጣባት ሴት መፅዳቷን በምን ታውቃለች? | በዚህ ጉዳይ ሴቶች ሁለት አይነት ናቸው፡-1-ነጭ ፈሳሽ[3] የምታይ ከሆነ. 2-ብልቷ መድረቅ ከቻለ |
| በንፅህና ጊዜ የሚፈሰው ፈሳሽ ደም | ነጭ ከሆነ ወይም ነጭና የሚላጠቅ ከሆነ ንፁህ ነው፡፡ ደምና ድፍርስ ነገር ከሆነ ግን ነጃሳ ነው፡፡ ሁሉም ግን ዉዱዕ ያበላሻል፡፡ የደም መውጣት ከቀጠለ ደግሞ የበሽታ ደም ነው፡፡ |
| ድፍርስና ብጫ መልክ ፈሳሽ | ከወር አበባ ዘመን ጋር በተያያዘ ከፊትም ሆነ ከኋላ የወር አበባ ሁኖ ይቆጠራል፡፡ የተለየ ከሆነ ግን ደም ነው፡፡ |
| በየወሩ የታወቁና የተለመዱ የወር አበባ ቀናት ያላትና ከዚህ በፊት የቆመላት ሴት | ንፁህ ናት |
| ደም ከጊዜው ቀድሞ ወይም ዘግይቶ ቢመጣባት | የወር አበባ ባህሪ ያለው ከሆነ በየትኛዉም ሰዓት ቢሆን በመካከል ከአስራ ሶስት ቀን ካላነሰ የወር አበባ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የበሽ ነው፡፡ |
| ከተለመደው የወር አበባ ዘመኑን ያለፈባት ወይም የጨመረባት ሴት | ከወር ዘመን ከብዙው (አስራ አምስት) ያልበለጠ ከሆነ የወር አበባ ነው፡፡ |
| ለብዙ ጊዜ ለወርና ከዚያም በላይ ደም የፈሰሳት ሴት | አራት ባህሪያት አሏት፡- 1) የወር አበባዋን መምጫ ዘመንና ቀናት የምታውቅ የወር አበባን ደም ከሌላው መለየት የቻለች በቁጥሩና በሰዓቱ መሰረት ነው የምትጓዝ እንጂ በደሙ ቀለም አይደለም፤ 2) የወር አበባዋን ቀናትና ዘመን የምታውቅ የወር አበባዋም ደም አንድ ዓይነት ባህሪ ያለው ከሆነ የምታውቀውን ዘመንና ቁጥር ታሳልፍ፤ 3) የወር አበባዋን መምጫ ዘመን የምታውቅ ነገር ግን የወር አበባ ቀናቷን የማታውቅ ከሆነ ሴቶች በብዛት የሚያሳልፉትን ሰባት ወይም ስምንት ቀናትን ታሳልፍ፡<br>4-የወር አበባዋን መምጫ ዘመን አታውቅም ቁጥሩን ታውቃለች የጨረቃው ወር በተወለደ በመጀመሪያው ላይ ካሉት ቀናቶች ትሰበው፡፡ |

[1]የወር አበባ ደም ያለምንም በሽታ አለመውለድ የሚመጣ የተፈጥሮ ደም ነው፡፡ ኢስቲሃዷህ ማለት ከማህፀን ስር ከሚገኝ ዓዝል ከሚባል የደም ስር የሚፈስ የበሽታ ደም ነው፡፡ በወር አበባና በበሽታ ደም መካከል ያለው ልዩነት፡- 1) የወር አበባ ደም ወደ ጥቁረት የቀረበ ሲሆን የበሽታው ደም ደግሞ ንፁህ የነስር ደም የመሰለ ነው፡፡ 2) የወር አበባ ደም ወፍራምና ሊቋረጥ የሚችል ሲሆን የበሽታው ደም ደግሞ ቀጭንና በተከታታይ እንደ ቁስል ደም የሚፈስ ነው፡፡ 3) የወር አበባ ደም በአብዛኛው የሚገማ የሚከረፋ ሽታ ያለው ሲሆን፤ የበሽታ ደም ደግሞ ልክ እንደማንም ንፁህ ደም ሽታ ነው፡፡ ከኢስላም አኳያ የሚሰጠው ብይንን በተመለከተ ግን የወር አበባ ደም ያለባት ሴት ጀናባ ያለበት ሰው የሚከለክለውን ሁሉ ማለትም፡- ሶላት መስገድ፤ በመስጊድ ውስጥ መቆየት፤ ቁርአን መቅራት፤ ፆም መፆምና መሰሎችን ትከለከላለች፡፡

[2] ጨለም ያለ መልክ ያለው ቡኒ ደም ነው፡፡ ወደ ብጫነት ጠጋ ያለ መልክ ያለው ደም ነው፡፡

[3] የወር አበባ ደም ሲያበቃ የሚፈስ ንፁህ ደም ሲሆን ውዱዕን ከማበላሸቱ በስተቀር ንፁህ ነው፡፡

# የወሊድ ደም

| ጉዳዩ | ዉሳኔው |
|---|---|
| ወልዳ ደም ያላየች | የወለደች ሴት ያላትን ውሳኔ አታገኝም፣ ትጥበትም የለባትም ብትፆምም ፆሟ አይበላሽም:: |
| የመውለድ ምልክት ያየች ሴት | ሴት የምታየው ደምም ይሁን ፈሣሽ ከመውለዷ በፊት ከህመም ጋር ከሆነ የወሊድ ደም ተብሎ አይጠራም:: ይህ ከበሽታ የሆነ ደም ነውና:: |
| በመውለድ ላይ እያለች የሚፈሳት ደም | ይህ የወሊድ ደም ነው:: ልጁ ወጥቶም ይሁን ሳይወጣ ወይም በከፊል ቢወጣ በዚሁ ሰዓት ያለፋትን ሶላት ቀዷ ማውጣት አትገደድም:: |
| የወሊድ ቀናት መቆጠር የሚጀምረው ከመቼ ነው? | ፅንሱ ሙሉ በሙሉ ከእናቱ ሆድ ወደ ውጭው ዓለም ከወጣበት ጀምሮ ነው:: |
| አነስተኛው የወሊድ ደም የሚቆይበት ቀን ስንት ነው? | ለአነስተኛው መጠን የሌለው ሲሆን እንደወለደች ወዲያዉኑ ደሟ ቢቆም ታጥባ መስገድ ይኖርባታል:: የግድ አርባ ቀንን መሙላት መጠበቅ የለባትም:: |
| ከፍተኛው የወሊድ ደም ቆይታ ጊዜ ስንት ነው? | አርባ ቀን ነው :: ከዚህ ከጨመረ ግን የበሽታ ደም ነው:: ከወር አበባ ደም ዘመኗ ጋር ካልተገናኘ በስተቀር ታጥባ መስገድ አለባት:: |
| መንታ ወይም ከዚያ በላይ የወለደች ሴት የወሊድ ቀናት መቁጠር የምትጀምረው ከመቼ ነው? | የመጀመሪያው ፅንስ ሙሉ በሙሉ ከእናቱ ሆድ ከወጣበት ጀምሮ ነው:: |
| ከዉርጃ በኋላ ያለ ደም | ዉርጃው የተከሰተው ከሰማኒያ ቀን ወይም ከዚያ ያነሰ ከሆነ የበሽታ ደም ነው:: ከዘጠና በላይ ከሆነ ደግሞ የወሊድ ደም ነው:: በሰማኒያና በዘጠና መካከል ያለው ደግሞ አፈጣጠሩ ታይቶ የሰው ቅርፅ ከያዘ የወሊድ ደም ይባላል:: ከሌለው ግን የበሽታ ደም ይባላል:: |
| ከአርባ በፊት ፅድታ ከዚያም ከአርባ በፊት ቢመለስባት | በአርባ ቀን ዉስጥ በምታየው ንፅህና ታጥባ መስገድ አለባት:: በዚሁ ዉስጥ ከተመለሰባት ደግሞ የወሊድ ደም ነው ይባላል:: እንዲሁ እያለ ደሙ እስኪቆምና አርባው ቀን እስኪሞላ ድረስ ይቀጥላል:: |

ማሳሰቢያዎች:- ✸ ኢስቲሃዳ /ከወሊድም ሆነ ከሀይድ ደም ያልሆነ/ የበሽታ ደም ያለባት ሴት ሶላት መስገድ ግዴታ ያለባት ሲሆን ለየሶላቱ ዉዱዕ የማድረግ ግዴታ አለባት::

✸ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ከወር አበባና ከወሊድ ደም ስትፀዳ የዕለቱን ዙህርና ዐስር መስገድ ግዴታዋ ነው:: ጎህ ከመውጣቱ በፊትም ብትፀዳ የዕለቱን መግሪብና ዒሻዕ መስገድ ትገደዳለች::

✸ የሶላት ወቅት ከገባ በኋላ የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም የፈሰሳት ሴት ስትፀዳ ያን ሶላት ቀዷ ማውጣት አለባት::

✸ ከወር አበባና ከወሊድ ደም የምትታጠብ ሴት ሹሩባዋን መፍታት ግዴታ ይኖርባታል:: ለጀናባ ትጥበት ግን ሹሩባ መፍታት አትገደድም::

✸ የወር አበባና የወሊድ ደም የታያት ሴት የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ክልክል ነው:: መሳሳምና መሰል ቅድመ ወሲብ ንክኪዎች ግን ይፈቀዳሉ።

✸የበሽታ ደም ያለባትን ሴት በግብረ ሥጋ ግንኙነት አካሏን በብልት መገናኘት ይፈቀዳል::

✸ የበሽታ ደም የሚፈሳት ሴት ለየሶላቱ መታጠብ ይወደዳል:: ካልቻለችም ለዙህርና ለዐስር አንድ ጊዜ ለመግሪብና ለዒሻ አንድ ጊዜ ለሱብሂ ሶላት አንድ ጊዜ ትታጠብ:: ይህን ካልቻለችም ለየቀኑ አንድ ጊዜ ታጥባ ለየሶላቱ ዉዱዕ ታድርግ:: ይህም ካቃታት ከወር አበባዋ ታጥባ ለየሶላት ዉዱዕ ታድርግ::

✸ የሐጅንም ሆነ የዑምራን ጸሎት ላለማቋረጥ ወይም ፆምን በአንድ ለመጨረስ በራሷ ላይ ችግር የማያደርስ የወር አበባን የሚያስቆም መድሐኒት መጠቀም ትችላለች::

# ሴት ልጅ በኢስላም

እምነትንና መልካም ስራን መሰረት አድርጎ አላህ ዘንድ በሚገኝ ምንዳና ትሩፋት ሴት ልጅ ከወንድ ጋር እኩል ናት። ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ ‹ሴቶች የወንዶች ክፋዮች ናቸው›› ብለዋል።
መብቷን መጠየቅ የደረሰባትን ግፍ መከላከል መብቷ ነው። ኢስላማዊ አስተምህሮቶች በግልፅ ወንድና ሴት የሚለያዩባቸውን ጥቂት ጉዳዮች ላይ ካል ሆነ በስተቀር ሌላው ነገሮች በሁሉም እኩል ናቸው። ሸሪዓ የፆታ ልዩነቶችንና ተስማሚነትን ይጠብቃል። አላህ በቁርአን ‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀት ረቂቁ ውስጥ ዐዋቂው ሲሆን (ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን ? ›› ብሏል።
ሴት ልጅ ለራሷ ተስማሚ የሆነ ስራ ያላት ሲሆን ወንድም እንዲሁ የራሱ የሆነ ስራ አለው። አንዱ በሌላው ተግባር ጣልቃ መግባት በሕይወት ሚዛን ላይ ችግር ይፈጥራል።
ሴት ልጅ በቤቷ ቁጭ ብላ ወንድ በየቦታው ለፍቶ የሚያገኘውን ያህል ታገኛለች
ሀ. ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በይሀቂ በዘገቡት ሐዲስ አስማእ ቢንት የዚድ የተባላች ሴት ነብዩ ከሱሃቦቻቸው መካከል ባሉበት መጥታ እኔ ወደ እርስዎ የተላኩ የሴቶች መልዕተኛ ነኝ በምስራቅ ትሁን በምዕራብ የእኔን ተልዕኮ ትስማም አትስማ ሁሉም ሴቶች በዚሁ ሀሳብ ላይ ይስማሙበታል፡ ይኸው አላህ ለወንዶችም ለሴቶቹም በትክክል ልከዎታል እናም በእርስዎም በላከዎት ጌታም በአላህ አምነናል። እኛ ሴቶች በቤት ውስጥ የተገደበንና የተወሰነን የቤቶቻችሁ ጠባቂዎች የስሜታችሁ መውጫዎች የልጆቻችሁ ተሸካሚዎች ነን። እናንተ ወንዶች ግን ከእኛ በተለየ በጁመዓና በጀመዓ በሺተኞችን በመጎብኘት የሞተን በመቅበር በየጊዜው ሐጅ በማድርግ ታድላችኋል። ከዚህ ሁሉ የሚበልጠው ደግሞ ለአላህ ሲባል እስከ ሕይወት መስዕዋት ለመክፈል ተመርጣችኋል። ወንዶች ለሐጅ ወይም ለዑምራ ለጅሃድ ስትወጡ ንብረታችሁን እንጠብቃለን ልብሶቻችሁን እንፈትላለን ልጆቻችሁን እናሳድጋለን እና በምንዳው አንጋራችሁምን አለች በዚህ ነብዩ ወደ ሶሃቦች መለስ ብለው ስለ ዲኗ የጠየቀች ሴት ከዚህች ሴት የበለጠች ሰምታችኋል ሱሃቦችም የአላህ መልዕክተኛ ሴት ልጅ እንዲህ ያለ ጥያቄ ታቀርባለች ብለን አስበን አናውቅም አሉ። ከዚያም ነብዩ ወደ እሷ ዘወር ብለው ‹‹ተመለሺ የላኩሽን ሴቶች ማንኛውም ሴት ለባሏ ጥሩ ሚስት መሆኗ የእሱን ደስታ ማሰቧ ፈቃዱን መከተሏ ይህን ሁሉ ይመዝናል ብለሽ አስተምሪ ሲሏት ላኢላሀኢለሏ አላሁ አክበር እያለች በደስታ ተመለሰች››
ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)በይሀቂ በዘገቡት ሐዲሰ ‹‹ውስን ሴቶች ወደ ነብዩ መጥተው ወንዶች ከእኛ በጂሃድ በለጡን እነሱን የምንደርስበት ሌላ ስራ የለንም ወይ በማለት ጠይቀዋቸዋል ሴት ልጅ የቤት ስራዋን በመስራቷ ብቻ የሙጃሂዶችን አጅር ያስጣታል» ብለዋል።
ከዚህ ም አልፎ ለሴት ዘመድ በጎ መዋል ከፍተኛ ተግባር እንደሆነ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድና ጦቦራኒ በዘገቡት ሐዲሰ ‹‹ሁለት ሴት ልጆች ወይም ለሁለት እህቶች ወይም ለሁለት ለዝምድና ባለቤት ሴቶች አላህ እስከሚያበቃቃቸው ድረስ ለአላህ ብሎ የረዳቸው ሰው ከጀሀነም እሳት መከላከያ ይሆኑለታል» ብለዋል።

## ✸ ከሴቶች ጉዳዩች በጥቂቱ ✸

✸ ዘመዱ ካልሆነች ሴት ጋር ብቻውን መሆን ክልክል ነው። ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹ዘመዷ አብሯት ከሌለ ሴት ጋር ለብቻው አይሁን› ብለዋል።[1]
✸ ሴት ልጅ ወደ መስጊድ ሂዳ መስገድ ትችላለች ። ፍትና ከፈራችግን ይጠላባታል። እናታችን አኢሻ ነብዩ ‹‹ሴቶች አሁን አሁን ያመጡትን ቢያውቁ ኑሮ የበኒ ኢስራኤል ሴቶች እንደተከለከሉ ሁሉ ይከለክሏቸው ነበር)) ብለዋል። የወንድ ልጅ ሶላት በመስጊድ ሲሰገድ እጥፍ ድርብ እንደሚሆን ሁሉ የሴት ልጅ ሶላት ደግሞ በቤት ሲሰገድ እጥፍ ድርብ ይሆናል። ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹አንዲት ሴት ወደ

[1] የሴት ልጅ ዘምድ ማለት

ነብዩ (ﷺ) መጥታ ከእርስዎ ጋር መስገድ ደስ ይለኛል ስትላቸው አዎ! ከእኔ ጋር መስገድ ደስ እንደሚልሽ አውቃለሁ ፡፡ ነገር ግን በጓዳሽ ዉስጥ መስገድሽ ምንዳው በቤትሽ ውስጥ ከመስገድሽ ይበልጣል ፡፡ በቤትሽ ዉስጥ መስገድሽ ምንዳው በግቢሽ ውስጥ ከመስገድሽ ይበልጣል ፡፡በግቢሽ መስግድሽ በሰፈርሽ መስጂድ ዉስጥ ከመስገድሽይበልጣል፡ ፡ በሰፈርሽ መስጂድ ዉስጥ መስገድሽ ምንዳው በእኔ መስጊድ ውስጥ ከመስገድሽ ይበልጣል ፡፡) ብለዋል፡፡ እንደዚሁም ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ ከሴቶች መስጊዶች የሚበልጠው ቤቶቻቸው ናቸው » ብለዋል፡፡

✷ ሴት ልጅ አብሯት የሚሄድ ወንድ ዘመድ ካላገኘች በስተቀር ሐጅም ሆነ ዑምራ ግዴታ የለባትም፡፡ ያለ ዘመድ መጓዝም አይፈቀድላትምና ነው ፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ‹‹ሴት ልጅ ከሶስት ሌሊት በላይ የሆነን መንገድ ያለ ዘመድ እንዳትጓዝ » ብለዋል፡፡

✷ ሴት ልጅ መቃብር መጎብኘትና ጀናዛ መሸኘት ክልክል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ‹‹ቀብር ጎብኚ ሴቶችን አላህ እርግማኑን ያውርድባቸው›› ብለዋል፡፡ ሙስሊም በዘገቡት ዘገባ ኡሙ ዐጢያ ‹‹ጀናዛ መከተል ተከልክለናል ግዴታ ግን አልተደረገምብንም ነበር › ብለዋል፡፡

✷ እጮኛን በማያታልል መልኩ ሴት ልጅ ፀጉሯን ከጥቁር ቀለም በስተቀር በፈለገችው ከለር ማቅለም ትችላለች፡፡ ጥቁር ግን ይጠላል፡፡

✷ሴት ልጅ አላህ የወሰነላት የውርስ ድርሻ ልትወስድ ይገባታል፡፡ መከልከሉ አይፈቀድም ፡፡

✷ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ኢብኑ ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹የወራሹን ውርስ ያቋረጠ በጀነት የሚወርሰው የቂያማ እለት አላህ ይቆርጥበታል›› ብለዋል፡፡

✷ ባል ሚስትን መቀለብ ግዴታው ነው፡፡ ይህም ሲባል ሴት ልጅ የሚያስፈልጋትን ልብስ ምግብ መጠለያ ያጠቃልላል፡፡ አላህ ‹‹የችሎታ ባለቤት በችሎታው ልክ ይቀልብ፡፡ በእርሱም ላይ ሲሳዩ የተጣበበበት ሰው አላህ ከሰጠው ይስጥ ፡፡ ነፍስን የሰጣትን ያህል እንጂ አያስገድድም›› ብሏል፡፡ ሴት ልጅ ባል የሌላት ከሆነች አባቷ ወይም ወንድሟ ወይም ልጇ መቀለብ ግዴታ ነው፡፡ የቅርብ ዘመድ የሌላት ሴት ከሆነች የምት ኖርበት ማህበረሰብ ሊቀልባት ይገባል፡፡

ምክንያቱም ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ለድሆች ባል አልባዎች የሚለፉ ሰው ጂሃድ እንደወጣ ወይም ሌሊቱን ቆሞ ቀኑን ያሞ እንደሚያሳልፍ ነው) ብለዋል፡፡

ሴት ልጅ እስካለገባች ድረስ ከቀድሞ ባሏ የወለደቻቸው ልጆችን በማሳደግ ላይ ባለ ሙሉ መብት ናት፡፡ አባትም በዚህ ጊዜ የልጁን ቀለብ ለእናት መስጠት አለበት፡፡

✷ ሴት በተለይ ወጣት ሴት ወንዶችን በሰላምታ እንድትጀምር አይወደድላትም፡፡

✷ በየ ጊዜው እንደ ሁኔታው ጉያን መላጨት ፤ብትብቻን መንጨት፤ ጥፍሮችን መቁረጥ ይወደዳል፡፡ እኒህን ነገሮች ከአርባ ቀን በላይ ማዘግየት ይጠላል፡፡

✷የፊትንና የቅንድብን ፀጉር መንጨት ክልክል ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ «ቀነዳቢን እና ተቀንዳቢን የአላህ እርግማን ይውረድባቸው›› ብለዋል፡፡

✷ ሐዘን ሴት ከባሏ በስተቀር ከሶስት ቀን በላይ ማዘን ክልክል ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹በአላህና መጨረሻ ቀን የምታምን ሴት ከባሏ በስተቀር ከሶስት ቀን በላይ ማዘን አይፈቀድላትም›› ብለዋል፡፡

ለባሏ ግን አራት ወር ከአስር ቀን ድረስ ልታዝንለት ግዴታ አለባት ፡፡

በሐዘን ስዓት ጌጣጌጥና ዘዕፍራንን የመሰለ ሽቶዎች መጠቀም ቀለበትም ቢሆን ወርቅ መልበስ የሚያሸበርቁ ቀይና ቢጫ ቀለም ያለው ልብስ መልበስ ሂናና ማኪያጅ መጠቀም በጥቁር ኩል በቅባት እራሷን መሳመር የለበትም ፡፡

ጥፍሯን መቁረጥ ብትብቻዋን መንጨት መታጠብ ይፈቀድላታል፡፡

የምትለብሰው ልብስ በቀለም ለምሳሌ ጥቁር... ተብሎ አይወሰንም፡፡ ዒዳዋን መቆጠር ያለባት ባሏ ሲሞት በነበረችበት ቤት ውስጥ ሁና ነው፡፡ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ከዚያ ቤት መውጣት አትችልም፡፡ ለወሳኝ ነገር ያውም በቀን ብቻ እንጂ በዒዳዋ

ዘመን ከቤት መውጣት የለባትም፡፡

✷ሴት በጣም ችግር ካልገጠማት በስተቀር የራስ ፀጉሯን መላጨት ክልክል ነው፡፡ ከወንድ ጋር በማያመሳስል መጠን ማሳጠር ትችላለች፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ በወንድ የሚመሳሰሉትን ሴቶች ነብዩ ረግመዋቸዋል» ወይም ከካፊር ሴቶች በማያስመስላት መልኩ ነብዩ ኢባዳ ‹‹ከሰዎች ጋር የተመሳሰለ ሰው ከእነሱ ነው›› ብለዋል፡፡

✷ሴት ከቤቷ ስትወጣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ባሟላ ጂልባብ አካሏን መሸፈን ግዴታ ነው፡፡ 1) ገላዋን ሁሉ መሸፈን 2) በራሱ ውበት ያልሆነ 3) የማያሳምር ወፍራም የሆነ 4) የማያጣብቅ ሰፊ የሆነ 5) ሽቶ ያልተቀባ 6) የወንድ ልብስ የማይመስል 7) የካፊር ሴቶችን ልብስ የማይመስል 8) ልዩ የሚያደርጋት ልብስ ያልሆነ የሚሉት ናቸው፡፡ የሰውም ሆነ የእንስሳ ስዕል ያለበትን መልበስ ክልክል ነው፡፡ ማንጠልጠል ግድግዳ ም ላይም መለጠፍ ክልክል ነው፡፡ መሸጥም እንዲሁ ክልክል ነው፡፡

የሴት ልጅ ሀፍረተ ገላ ከሌላ ጋር ስትሆን ሶስት ክፍል አለው፡፡ ፩)ባል እሱ ከሷ የፈለገውን ገላ ማየት ይችላል፡፡ 2)ሴቶችና ወንድ ዘመዶቿ አብዘሀኛውን ጊዜ የሚታየውን አካሏን ማለትም ፊቷን ፤ፀጉሯን ፤ትከሻዋን ፤እጆቿዋን ፤ክንድ፤ እግርና የመሳሰለውን ማየት ይችላሉ፡፡ 3) ሌሎች ወንዶች ለማጨት፤ ለህክምና እና ለመሳሰሉ ምክንያቶች ካልሆኑ በስተቀር ምኗንም መቼም ጊዜ ማየት አይፈቀድላቸውም ፡፡ ምክንያቱም ሴት ልጅ የምትፈተነው በፊቷ ነውና፡፡ ፋጡማ ቢንቱ ሙንዚር ሀኪም በዘገቡት ሐዲስ ፊቶቻችንን ከወንዶች እንሸፈን ነበር ብለዋል፡፡ አኢሻ አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ እኛ ከነብዩ ጋር ኢህራም ላይ እያለን የወንድ ቡድኖች በአጠገባችን ሲያለፉ እያንዳንዳችን ጅልባባችንን ከራሳችን ወደ ፊታችን እናወርደው ነበር፡፡ ሲያልፉን ደግሞ ፊታችንን እንገልጥ እና እንደልባችን እንንቀሳቀስ ነበር፡

✷ ዒዳዎች፡- ዒዳዎች ብዙ ናቸው፡፡ እነሱም፡- 1) ነፍሰ ጡር የሆነች ሴት የፍችም ይሁን የሞት ዒዳዋ ፅንሷን መውለዷ ብቻ ነው፡፡ 2) ባሏ የሞተባት ሴት ዒዳዋ አራት ወር ከአስር ቀን መጠበቅ ነው፡፡ 3) የወር አበባ የምታይ ሁና የተፈታች ሴት ዒዳዋ ሶስት የወር አበባን ማየት ሲሆን፡-ዒዳዋ የሚያበቃው ከሶስተኛው የወር አበባ ደም በፀዳች ጊዜ ነው፡፡ 4) የወር አበባዋ የማታይ ሴት ደግሞ ዒዳዋ ሶስት ወር ብቻ መጠበቅ ነው፡፡ በአስመላሽ ፍች ዒዳ ስር ያለች ሴት ሁሉ ከባሏ ጋር መኖር ግዴታዋ ነው፡፡ ሲኖሩም ከእሷ ጋር መቀመጥም ሆነ ከእሷ የፈለገዉን አካል ማየት ይፈቀድለታል፡፡ ምን አልባትም አላህ ቢመልሳቸውና ቢያስታርቃቸው ተብሎ ዒዳዋ እስከሚያበቃ ድረስ ከእሷ ጋር ብቻቸዉን መሆንም እንኳን ይችላሉ፡፡ 'መልሼሻለሁ' በማለት ወይም የግብረ ስጋ ግንኙነትን በመፈፀም ብቻ የተፈታች ሴት ወደ ሚስትነት ትመለሳለች፡፡ በዚህ ላይ የሴትዮዋ መስማማት አያስፈልግም/ግዴታ አይደለም/፡፡

✷-ሴት ራሷን አትድርም ነብዩ አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ «ያለዘመዷ ፈቃድ ራሷን የዳረች ሴት ጋብቻዋ ውድቅ ነው» ብለዋል፡፡

✷-የሌላ ሴት ፀጉርም ሆነ የእንስሳ ፀጉር በፀጉሯ ላይ መቀጠል ክልክል ነው፡፡ ከአካሎቿ መካከል አንዱንም መነቀስ ክልክል ነው፡፡ ሁለቱም ተግባሮች ከታላለቅ ወንጀለች የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ነብዩ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ቀጣየም አስቀጣያዋም ነቃሿም ተነቃሿም የአላህ እርግማን ይውረድባቸው›› ብለዋል፡፡

✷ያለምንም ምክንያት ፊቺ መጠየቅ ክልክል ነው፡፡ ነብዩ አቡዳው በዘገቡት ሐዲስ «ያለምንም ምክንያት ከበሏ ፍቺ የጠየቀች ሴት የጀነት ሽታ በእሷ ላይ እርም ነው›› ብለዋል፡፡

✷ ሴት በሏን በአግባብ መታዘዝ አለባት በተለይም ለመኝታ ከጠየቃት ነብዩ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ባል ሚስቱን ለመኝታ ጠየይቋት እምቢ ካለች እና ተቆጥቶባት ካደረ እስከ ጠዋት ድረስ መላኢካ ይረግማታል››ብለዋል፡፡

✷ በመንገዷ ላይ ወንዶች እንደሚኖሩ ያወቀች ሴት ሽቶ ተቀብታ በእነሱ አጠገብ ማለፍ የለባትም፡፡ ነብዩ አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ሴት ሽቶ ተቀብታ ወንዶች ሽታውን እንዲያጣጥሙላት ብላ ከወንዶች አጠገብ ካለፍች እሷ እንደዚህ (ዝሙተኛ) ናት›› ብለዋል፡፡

# ሶላት

አዛንና ኢቃማ በሀገራቸው ውስጥ በሚኖሩ ወንዶች ላይ ግዴታ ናቸው ። ለብቻዉ ለሚሰግድ ሰጋጅና ለመንገደኛ ሰው ደግሞ ሁለቱም ሱና ናቸው ። ለሴቶች አዛንና ኢቃማ ማድረጉ ይጠላል ። የሱብሂ ሶላት ካልሆነ በስተቀር ወቅት ሳይገባ አዛን ማድረግ አይቻልም ። ለሱብሂ ሶላት ከሆነ ግን ወቅቱም ባይገባ የመጀመሪያውን አዛን ከግማሽ ሌሊት በኋላ ማድረግ ይቻላል።

**ለሶላት መሟላት ያለባቸዉ** ቅድመ ሁኔታዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው ፡፡ 1) ሙስሊም መሆን፤ 2) የአዕምሮ ጤነኛነት፤ 3) ደግና መጥፎውን መለየት መቻል /ከህፃንነት መዉጣት/፤ 4) አቅም ያለው ሰው መፅዳት/ ጠሃራ ማድረግ/፤ 5) የሶላት ወቅት መግባት፤- **የዙህር ወቅት** ፀሐይ ከግማሽ ሰማይ ወደ መግቢያዋ ከተዘነበለች ጀምሮ የያንዳንዱ ነገር ጥላው በልኩ እስከሚሆን ድረስ ነው ። **የዐስር ሶላት ወቅት** ሁለት አይነት ሲሆን፡ የምርጫው ወቀት የየአንዳዱ ጥላ ሁለት ጊዜ ልኩ እስከሚሆን ድረስ ሲሆን፡ የችግር ጊዜው ወቀት ደግሞ እስከ ፀሐይ መጥለቅ ድረስ ነው ። **የመግሪብ ሶላት ሰዐት** ከፀሃይ መጥለቀ በኋላ የሚታየዉ ቀዩ አድማስ እስከሚገባ ድረስ ነው፡፡ **የዒሻ ሶላት ወቅት** ምርጫው እስከ ግማሽ ሌሊት ድረስ ሲሆን የችግር ወቅቱ ደግሞ እውነተኛው ጎህ እስከሚወጣ ድረስ ነዉ። **የሱብሂ ወቅት** ከንጋቱ ጀምሮ ፀሐይ እስከምተወጣበተ ፂዜ ድረስ ነው።

6) አቅም ካለው ሐፍረተ ገላዉን[1] በማያሳይ ወፌር ባለ ነገር ሰዉነትን መሸፈን ነው ፡፡
7) አቅሙ በፈቀደለተ ልክ ከሰውነቱ፤ ከልብሱና ከቦታው ቆሻሻን ማከወገድ ፡
8) ከቻለ ቂብላን መቀጣጨት/ወደ ካዕባ መዞር/ 9) ለሶላት መነየት/ማሰብ/ የሚሉት ናቸው።

**<u>የሶላት ማዕዘናት</u>** የሶላት ማእዘናት፡- የሚባሉት አስራ አራት ናቸው። እነሱም፡-
1) በፈርድ ሶላት አቅም ላለው ሰጋጅ መቆም፤ 2) የመጀመሪያው አላሁ አክበር ማለት፤
3) ፋቲሃን ማንበብ 4) በሁሉም ረከዐ ላይ ሩኩዕ ማድረግ መነምበክ 5) ከሩኩዕ መነሳት 6)ከዚያም ተነስቶ ቀጥ ብሎ መቆም. 7) በሰባት አካሎቹ ላይ ሱጁድ ማድረግ
8) በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ተከተካክሎ መቀመጥ 9) የመጨረሻው ተሸሁድ 10) ለዚሁ ለተሸሁድ መቀመጥ 11) በመጨረሻው መቀመጥ ፂዜ በነቢዩ ላይ ሶለዋት ማዉረድ
12) የመጀመሪያው ሰላምታ 13) በሚተገበሩት ግዴታዎች ሁሉ መረጋጋት/ ጡማእኒና/
14) እነዚህን ግዴታዎች ቀደም ተከተል መጴፀም ናቸው፡፡

**እነዚህ ግዴታዎች ያለ እነሱ ሶላት ጭራሽ ተቀባይ የማይሆንበት ናቸው። ከእነዚህ መካከል አንዷን እንኳን ረስቶም ሆነ አውቆ የተወ ሰው ሶላቱ ይበላሻል።**

**<u>የሶላት ዋጂባቶች</u> /ግዴታዎች/ ስምንት ናቸው።** እነሱም፡- 1) ከመጀመሪያው በስተቀር ያለው ተክቢራ (አላሁ አክበር ማለተ) ሁሉ 2) ለጀመዐ አሰጋጅም ሆነ ብቻዉን ለሚሰግድ ሰሚዐ አሏህ ሊመን ሐሚደህ ማለት 3) በሩኩዕ ላይ ሁኖ አንድ ጊዜ - ሱብሀነ ረቤል ዐዚም ማለት 4) ከሩኩዕ ሲነሱ - ረበና ወለከል ሐምድ - ማለት፤ 5) በሱጁድ ላይ ሆኖ አንድ ጊዜም ቢሆን- ሱብሀነ ረቢየልአዕላ - ማለት፤ 6) ረቢግፊርሊ ማለት 7)የመጀመሪያው ተሸሁድ/ ለተተሒያተ/ና 8) ለተሸሁዱ መቀመጥ ናቸው፡፡ **እነዚህን ዋጂባቶች አውቆ የተዋቸው ሶላቱ የሚበላሽ ሲሆን ረስቶ ከተዋቸው ግን በሱጁድ የሚጠገኑ ናቸው።**

**<u>የሶላት ሱናዎች</u>-** እነሱም፡- ንግግሮችና ተግባሮች ናቸው፡ አንዳቸዉንም መተው አውቆ እንኳን ቢሆን ሶላትን አያበላሽም። ንግግሮች የተባሉት ሱናዎች፡-መክፈቻ ዱዓ፡ አዑዙ ቢላህ ቢስሚላህ አሚን ማለት፤ ድምፅ ከፍ ማደረግ ባለበት ቦታ ላይ ድምፅን ከፍ ማድረግ፤ ከፋቲሃ ቀጥሎ የቻሉትን የቁርአን አንቀጽ ማንበብ፤ ኢማም የሆነ ሰዉ ድምፅን ከፍ ማድረግ፤ (የተከታይ ድምፅን ከፍ ማድረግ የተከለከለ ሲሆን ብቻዉን የሚሰግድ ሰዉ ግን ምርጫ አለው፣ ሰሚዐሏህ.... ካለ በኋላ ሀምደን ከሲረን ጦይበን ሙባረከን ፊሂ- ሚልአከሰማዋቲ ወሚልአልአርዲ - ማለት ፣ በሩኩዕም ሆነ በሱጁድ የሚባሉተን ተስቢሆች ከአንድ ጊዜ በላይ ማለት፤ ረቢ ግፊርሊ....ማለትና ከማሰላሞተ በፊት ዱዓ ማብዛት ናቸው።

**<u>ተግባራዊ/ ድርጊታዊ/</u> ሱናዎች ደግሞ፡-** በመጀመረያው ተክቢራ ላይ፤ በሩኩዕም ጊዜ፤ ከሩኩዕም ሲነሱ እንዲሁም ከመጀመሪያው ተሸሁድ ወደ ሶስተኛው ሲነሱ እጅን ማንሳት፤ በሚቆምበት ጊዜ ቀኝ እጅን በግራ ላይ አድርጎ በደረት ስር ማስቀመጥ፤ ሱጁድ ወደሚያደርግበት ቦታ ላይ መመልከት፤ ሲቆሙ በሁለት እግሮች መካከል ማስፋት፤ ሱጁድ

[1] አስር አመት የደረሰ ወንድ ልጅ ሐፍረተ ገላው በዕንብርትና በጉልበት መካከል ያለው አካሉ ነው፡፡ የደረሰች ሴት ልጅም ለሶላት ስትቆም ሐፍረተ ገላዋ የሚባለዉ ፊቷ ሲቀር ሁሉም አካሏ ነው ።

በሚያደርግበት ጊዜ በጉልበቶቹ ጀምሮ ከዚያም እጆቹን ማከከተል፤ በሱጁድ ግንባሩንና አፍንጫዉን መሬት ማከኑካት፣ ጡንቻዎችን ከጎኖቹ ማራቅ፣ ሆዱን ከጭኖቹ፣ ጭኖቹን ከባቶቹ ማራቅ፤ በጉልበቶቹ መካከል መለየት፣ ሁለት እግሮቹን ማራራቅ፤ የጣቶቹን የዉስጥ ክፍል በምድር ላይ ማድረግ፣ እጆችን አጠጋግቶና ዘርግቶ በትክሻው ልክ ማድረግ፣ በሱጁድ መካከልና በመጀመሪያዉ ተሸሁድ እግርን አንጥፎ መቀመጥ፣ በሁለተኛዉ ተሸሁድ ተወሩክ፣ እጅን ዘርግቶ በጭን ላይ ማስቀመጥ፣ የሚሉት ናቸው፡፡

**የመርሣት ሱጁድ፤** ይህ ሱጅድ ሱናነቱ የሆነዉ በአንድ ቦታ መደረግ ያለበት ድርጊት በበሌላ ቦታ ላይ የተደረገ እንደሆነ ነዉ፡ ለምሳሌ በሱጁድ ላይ ቁርአን መቅራትን ይሙከል ነው፡፡ ሱናን ቢተዉ ይህን ሱጁድ ማድረግ ይፈቀድለታል፡፡ሩኩዕን አሊያም ሱጁድን ወይም ረከዓን ከጨመረ፤ወይም ሰላቱንሣይሞላ ካሰላመተ፤ ትርጉሙን በሚቀይር መልኩ ቁርአንን ካነበበ፤ ግዴታን ከተወ፡ መጨመር መቀነሱን ከተጠራጠረ .. ይህ ሱጁዱ ግዴታ ይሆናል፡፡ ሱጁዱ ሰህውን ግዴታ የሚስደርግን ነገር ሰርቶ በሱጁዱ ያልጠገኑ ሶላቱ ይበላሻል:: አፈጻጸሙም ከማሰላመቱ በፊት ሁለት ሱጁድ ማድረግ ይችላል፡፡ ሱጁዱን ለረጅም ጊዜ ረስቶ የቆየ ሰው በሱጁዱ አይጠየቅም::

**የሶላት ስርአት** ሶላት ለመስገድ ስትፈልግ ወደ ቂብላ ዞረህ ቀጥ ብለህ ቁመህ አላሁ አክበር በል:: ኢማም የሆነ ሰው በዚህና በመሰሉ ተክቢራዎች ድምፁን ከፍ አድርጎ ተከታዩችን ማሰማት ተገቢ ነው:: ከኢማም ሌላ የሆነ ሰጋጅ ግን ድምጹን ዝቅ ያደርጋል::
አላሁ አክበር ሲል ጣቶቹን አጠጋግቶ በተከሻው ልክ ያንሳቸው::
ተከታይ አላሁ አክበር የሚለው ኢማሙ አላሁ አክበር ካለ በኋላ ነው::
ከዚያም በቀኝ እጁ መዳፍ የግራ እጁን መዳፍ ይጨብጥና በደረቱ ስር ያድርግ፣ በአይኑ ወደ ሱጁድ ማድረጊያ ቦታው ይመልከት::
ከዚያም ከነቢዩ (ﷺ) ከተዘገቡት ዱዓዎች
ሱብሀነከላሁመ ወቢሐምዲከ ወተባረከከሙከ ወተዓላ ጀዱከ ወላ ኢላሀ ገይሩከ (አላህ ሆይ! ጥራት ለአንተ ይገባሃል፡፡ ምከጋናዬንም አቀርባለሁ፡፡ ከምህ የተቀደሰ ነው፡፡ ልዕልዕናህ ከፍ ያለ ነው፡፡ ከአንተ ሌላ አምላክ የለም፡፡) (ወይም መሰሉን በማንበብ ሰላቱን ይክፈት፣
ከዚያም አዑዙ ቢላህ ሚነ ሸይጧኒረጂም (እርጉም ከሆነው ሰይጣን እጠበቃለሁ) ይበልና፣
ቢስሚላሂ አር–ረህማን አር–ረሂም (በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ) የሚለውን ያከከተል፣ እነዚህን ሁሉ የሚለው ድምፅን ዝቅ አድርጎ ነው:: ከዚያም ፋቲሃን ያንብብ፣ተከትሎ የሚሰግድ ሰጋጅ ኢማሙ ድምፅን ከፍ በሚያደርግባቸው ረከዓዎች ላይ ምንም ማንበብ አይገደድም[1]::
ኢማሙ ድምፁን ዝቅ በሚያደርግበት ክፍተተ ፋቲሃን መቅራቱ ይወደዳል:: ቀጥሎም የቻለዉን ከቁርአን አናቀፅ ያንብብ::
ኢማሙ ድምፁን ከፍ የሚያደርገው በሱብሂ፣ በመግሪብና በዒሻ ሶላቶች ውስጥ በሁለቱ የመጀመሪያ ረከዐዎች ነው:: ከነዚህ ሌላ ባለው ዝቅ ያደርጋል ::
ከዚያም አላሁ አክበር ይበልና እጆቹን አንስቶ ሩኩዕ ያድርግ፡፡ እጆቹን በጉልበቶቹ ላይ የጨበጣቸው አስመስሎ ይያዛቸው:: ጣቶቹንም በተን ያድርግ፡፡ ጀርባዉን በእኩል ይለጥጠው:: ራሱንም በሱ ትክክል ያድርግ::
ከዚያም ሱብሃነ ረቢየል ዐዚም ሶስት ጊዜ ይበል:: ከዚያም ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ እያለ ራሱን ቀና ያድርግ:: እጆቹንም እንዲሁ ያንሳ፡ ቀጥ ብሎ ሲቆም (ረበና ወለከል ሐምድ ሀምደን ከሲረን ጦይበን ፊህ ሚልዑ ሰማዋት ወሚልዑልአርድ ወሚልዑ ማሺዕተ ሚን ሸይኢን በዕዱ) (ጌታችን ሆይ! ብዙና የተባረከ ምከጋና የሚገባው ለአንተ ነው፡፡ በሰማያት፤ በምድር፤ መካከላቸው ባሉ ነገሮች ሁሉ እና ከነኚህ ዉጭ ባሉ ነገሮች ሁሉ የሞላ ምከጋና ለአንተ ነው የሚገባው፡፡) ይበል ::
ከዚያም አላሁ አክበር በማለት ወደ መሬት ለሱጁድ ይውረድ፡ በሱጁድ ላይም ጡንቻዎቹን ከጎኖቹ፣ ሆዱን ከጭኖቹ ያርቅ:: እጆቹን በትከሻው ልክ ሰፋ ያድርጋቸው:: በ እግሮቹ ጫፍ ላይ ይሁን:: የእግሮቹንም ሆነ የእጆቹን ጣቶች ወደ ቂብላ ያዙር፡፡ ሱብሀነ ረቢየልአዕላ(ልዑሉ አላህ ጥራት ይገባው፡፡) ሶስት ጊዜ ይበል፡፡ በዚሁ ቦታ ላይ በሀዲስ

---

[1] በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ክርክር ያለ ሲሆን የሚመረጠው ሁልጊዜም ፋቲሃን ማንበቡ ነው::

የመጣዉን ሌላ ዱዓዕ ማድረግም ይችላል፡፡
ከዚያም አላሁ አክበር በማለት ራሱን ያቃናና ይቀመጥ:: በሁለት ሱጁዶች መካከል በሚደረገው አቀማመጥ ሁለት ትክክለኛ የሆኑ የአቀማመጥ ስርአቶች አሉ ::
1ኛው፦ ግራ እግሩን አንጥፎ በላይዋ ላይ መቀመጥና ቀኝ እግሩን ተክሎ ጣቶቹን ወደ ቂብላ አጥፎ መቀመጥ ሲሆን 2ኛው፦ ሁለት እግሩን ተክሎ ጣቶቹን ወደ ቂብላ አዙሮ በተረከዙ ላይ መቀመጥ ነው:: ከዚያም ረቢግፊርሊ፦ሶስት ጊዜ ይበል:: ወርሐምኒ ወጅቡርኒ ወርፈዕኒ ወርዙቅኒ ወንሱርኒ ወህዲኒ ወዓፍኒ ወዕፉ ዐኒ) (አላህ ሆይ! ማረኝ፤ እዘንልኝ፤ትክክለኛዉን ጎዳና ምራኝ፤ ጠግነኝ፤ ሲሳይን ለግሰኝ፤ የላቀን ደረጃም ለግሰኝ፤ጤና ከጠኝ፤ ይቅር በለኝ) የሚለዉን ቢጨምር መልካም ነው::
ከዚያም ሁለተኛዋን ሱጁድ ልክ እንደ መጀመሪያዋ ሱጁድ ይስገድና አላሁ አክበር በማለት ራሱን ያቃና:: ከዚያም በሁለት እግሮቹ ደረት ላይ ተደግፎ ይነሣ::
ከዚያም ሁለተኛዋን ረከዐ ልክ እንደ መጀመሪያዋ ይስገድ:: ከሁለቱ ረከዐዎች ሲያበቃ ለተሸሁድ /አተህያት.../ ይቀመጥ:: ቀኝ እጁን ከቀኝ ጭኑ ላይ ግራ እጁን ከግራ ጭኑ ላይ ያስቀምጥ:: የቀኝ እጁን ትንሽ ጣትና ቀጥላ ያለችዉን ጨብጦ በአውራ ጣቱና በመሀል ጣቱ አካቦ በአመልካች ጣቱ እያመለከተ «አተሂያቱ ሊላህ ወከሰለዋቱ ወጥጦይባቱ አስሰላሙ ዐለይከ አዩሃ ነቢዩ ወረህመቱላሂ ወበረካቱ አስሰላሙ ዐለይና ወዐላ ዒባዲላሂ አስሷሊሂን አሽሀዱ አላ ኢላሀ ኢለላህ ወአሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ) ((ሰላምታ ለአላህ ነው፡፡ ሶላተና መልካም ነገሮች ሁሉ ለአላህ የቸው፡፡ አንተ ነብይ ሆይ! ሰላም በአንተ ላይ ይውረድ የአላህ እዝነትና ዉዴታም ይከፈንብህ፡፡ በእኛና በአላህ ቀን ባርያዎችም ላይ ሰላም ይውረድ፡፡ ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ:: ሙሐመድ አገልጋዩና መልዕክተኛው መሆናቸዉንም እመሰክራለሁ፡፡) ይበል::
ከዚያም በሶስትና በአራት ረከዐዎች ሰላት ላይ እጆቹን አንስቶና አላሁ አክበር በማለት ይነሳ:: የቀረዉን ይስገድ፡፡
በቀሩት ረከዐዎች ላይ ድምፅ ከፍ አይደረግም፡፡ የሚነበበውም ፋቲሃ ብቻ ነው፡፡
ከዚያም ሶላቱ ባለ ሶስት ወይም ባለ አራት ረከዐ ከሆነ ለመጨረሻው መቀመጥ ተወሩክ አድርጎ ይቀመጥ:: ተወሩክ ሲባል፦ ግራ እግሩን አንጥፎና በቀኝ እግሩ ቅልጥም ስር ወደ ቀኝ አውጥቶ ቀኝ እግሩን አንጥፎ መቀመጫዉን ከመሬት ላይ ማስቀመጥ ነው:: ተወሩክ የሚደረገው ሁለት ፲ዜ መቀመጥ ባለባቸው ሶላቶች መጨረሻ ላይ ነው:: ከዚያም በመጀመሪያዉን ያነበበዉን ተሸሁድ (አተሒያቱ ሊላህ ወሰለዋቱ ...) ይበል፡፡
ከዚያም (አላሁም ሶሊ ዐላ ሙሐመዲን ወዐላ ኣሊ ሙሐመዲን ከማ ሶለይተ ዐላ ኢብራሂም ወዐላ ኣሊ ኢብራሂም ኢነከ ሀሚዱን መጂድ አላሁመ ባሪክ ዐላ ሙሐመዲን ወዐላ ኣሊ ሙሐመዲን ከማ ባረክተ ዐላ ኢብራሂም ወዐላ ኣሊ ኢብራሂም ኢነከ ሀሚዱን መጂድ) (አላህ ሆይ! በሙሐመድ ላይና በሙሐመድ ቤተሰቦች ላይ እዝነትህን አስፍን፡፡ በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ እዝነትን እንዳሰፈንክ ሁሉ፡፡ አንተ ምስጉንና የላቅህ ነህና፡፡ አላህ ሆይ! በሙሐመድ ላይና በሙሐመድ ቤተሰቦች ላይ ፀጋኤትህን አውርድ፡፡ በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ ፀጋኤትህን እንዳወረድክ ሁሉ፡፡ አንተ ምስጉንና የላቅህ ነህና፡፡) ይበል፡፡
ከዚያም በኋላ ከ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በተዘገቡ ዱዐዎች ለምሳሌ (አኡዙ ቢላሂ ሚን ዐዛቢን ናር ወዐዛቢልል፦ቀብር ወፊትነቲ፦ልመህያ ወልመማት ወፊትነቲል፦መሲሂ ደጃል) (አላህ ሆይ! ከቀብር ቅጣትና ከጀሀነም ቅጣት ፤ከሕይወት እና ከሞት ፈተና እንዲሁም ከአታላዩ መሲህ ደጃል ፈተና በአንተ እጠበቃለሁ፡፡) በሚለዉ ዱዓና በመሣሰሉት በሀዲስ የመጡትን ዱዓዎች ያንበብ::
ከዚያም በመጀመሪያ በቀኝ በኩል (አሰላሙ ዐለይኩም ወረህመቱላህ) በማለትና በግራውም እንደዚሁ በማለት ያሰላምት:: ከሰላት ካሰላመተ በኋላም በመስገጃው ቦታ ላይ ተቀምጦ ከ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በትክከለኛ የዘገባ ሰንሰለት የተዘገቡ ዱዐዎችን ያንብብ::[1]

[1] አስተግፊሩሏህ- ሶስት ጊዜ፤ ከዚያም አላሁመ አንተስሰላም ወሚንከሰላም ተባረክተ ያዘልጀላሊ ወልኢክራም ላኢላሀ ኢለሏህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁልሙልኩ ወለሁልሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩሉ ሸይኢን ቀዲር ላሐውለ ወላቁወተ ኢላ ቢላህ ላኢላሀ ኢለሏህ ወላ ነዕቡዱ ኢላ ኢያሁ ለሁ-ኒኒዕመቱ ወለሁልፈድሉ ወለሁ ስሰናኡልሐሰን፡ ላኢላሀ ኢለሏህ ሙኽሊሲነ ለሁድዲነ ወለው ከረሀል ካፊሩን፤አላሁመ ላማኒዐ ሊማ አዕጠይት ወላ ሙዕጢ ሊማ መነዕት ወላ የንፊዑ ዘልጀዲ ሚንከል ጀዱ፡፡ ከሱብሂና ከመግሪብ በኋላ ከላይ ያለፈዉን ከማለቱ ጋር ላኢላሀ ኢለሏህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁልሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ዩህዪ ወዩሚት ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር (10ጊዜ) ይጨምራል፡፡ ከዚያም በመቀጠል ሱብሓነሏህ (ሰላሳ ሶስት ጊዜ)፣ አልሐምዱ ሊላህ (ሰላሳ ሶስት ጊዜ)፣ አሏሁ አክበር (ሰላሳ ሶስት ጊዜ) ይልና መቶ መሙያ ላኢላሀ ኢለሏህ

**የበሽተኛ ሰው ሶላት አሰጋገድ፡** መቆም በሽታዉን የሚያባብሰበት በሽተኛ ወይም ጭራሹኑ መቆም የማይችል ከሆነ ቁጭ ብሎ ይሰግድ፡፡ ይህን ካልቻለ በጎኑ ተጋድሞ ይሰግድ፡፡ ይህንንም ካልቻለ በጎኑ ተኝቶ ይሰግድ፡ ከሰበደዉ በደርባው ተኝቶ ይሰግድ፡፡ ሩኩዕና ሱጁድ ማድረግ ካቃተው በጥቅሻ ይሰግድ፡፡ በሽተኛ ያለፉት ሶላቶች ካሉ ቀዷ ማውጣት አለበት፡፡ ይህን ከፌሉ ሶላቶችን በየጊዜያቸው ጠብቆ ይሰግድ፡ ካልቻለ ዙህርና ዐስርን በአንድ ኢሻንና መግሪብን በአንድ ላይ ከሁለቱ ሰዐት በአንዱ መርጦ መሰገድ ይችላል፡፡

**የመንገደኛ ሶላት፡** የሚሄድበት ክፍሉ ከ 85 ኪ.ሜ የራቀ ከሆነና ጉዞዉ ከምንም ወንጀል ጋር የተያያዘ ካልሆነ ባለ አራት ረከዐዎችን ሁለት ሁለት አድርጎ መስገድ ይችላል፡፡ ከአራት ቀን (20 ፌርድ/የግዴታ ሶላቶች) በላይ እንደሚቆይ ከወሰነ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ሞልቶ መስገድ አለበት፡፡ መንገደኛ መንገደኛ ያልሆነን የአገሬዉን ነዋሪ ሰዉ ተከትሎ ቢሰግድ፤ ወይም መንገደኛ ሳይሆን በቤት ያልሰገዳትን ሶላት ቢያከታዉስ መሙላት ይኖርበታል፡፡ መንገደኛ ማሳጠሩ የሚበልጥለት ቢሆንም ሞልቶ መስገድ ግን ይችላል፡፡

**የጁሙዓ ሶላት፡-** የጁሙዓ ሶላት በደረጃ ከዙህር ሶላት ተበልጣለች፡፡ እሷ የተቀነሰች ዙህር ሳትሆን ራሷን የቻለች ሶላት ናት፡፡ አራት ተደርጋም አትሰገድም ፡፡ በዙህር ኒያም አትሰገድም፡፡ እንደ ዙህር ከዐስር ጋርም አትሰበሰብም/ ጀምዕ ተደርጋ አትሰገድም፡፡

**የዊትር ሶላት፡-** የዊትር ሶላት ሱና ናት፡፡ ጊዜዋም ከዒሻ ሶላት አንስቶ እስክ ጎህ መውጣት ድረስ ነው፡፡ በአነስተኛው አንዲት ረከዐ ስትሆን ከፍተኛው ቁጥሯ ደግሞ አስራ አንድ ነው፡፡ በየሁለቱ ረከዐ እያሰላመቱ መስገዱ የበለጠ ሲሆን አራት አራት ወይም ከዽከት ከዽከት ረከዐ ወይም ከምንት ከምንት ረከዐ አድርጎ ሰግዶ በመጨረሻ በአንድ ረከዐ ማጠናቀቅም ይቻላል፡፡ ወይም ሶስት ሶስት ረከዐ ወይም አምስት አምስት ረከዐ ወይም ሰባት ሰባት ረከዐ ወይም ዘጠኝ ረከዐ አድርጎ በአንድ መስገድም ይቻላል፡፡ አነስተኛው ሙሉ ዊትር ሶስት ረከዐ በሁለት ሰላምታ መስገዱ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ቁጭ ብሎ ሁለት ረከዕ መስገድ ይፈቀዳል፡፡

**የጀናዛ ሶላት፡-** የሞተን ሙስሊም ማጠብ፤ መገነዝ፤ በእርሱ ላይ መስገድ፤ አስክሬኑን መሸከሙና መቀበሩ ፈርዶል ኪፋያ[1] ነው፡፡ በጁሣድ የሞተ ሰማዕት /ሸሂድ/ሲቀር፡፡ ሸሂድ አይታጠብም፤ አይገነዝምም፡፡ ሊሰገድበት ግን ይችላል፡፡

ከዚያም እንዳለ በሞተበት ሁኔታ ከነልብሱና ከነደሙ ይቀበራል፡፡ የወንድ አስከሬን በሶስት ነጫጭ ልብሶች ይጠቀለላል፡፡ የሴት ደግሞ በአምስት ልብሶች ማለትም በሽርጥ በጉፍታ በቀሚስና በሁለት ጋቢዎች ተጠቀለላለች፡፡ ኢማም የሆነዉም ሆነ ብቻዉን የሚሰግድ ሰው በጀናዛው ወንድ ከሆነ በደረቱ ትክክል ሴት ከሆነች ደግሞ መሀል የሰዉነት ክፍሏ ላይ መቆም ሱና ነው፡፡ የጀናዛ ሶላት አራት ተክቢራዎች/ አላሁ አክበር ማለት/ አሉት፡፡ በየተክቢራውም እጅ ይነሣል። ከመጀመሪያው ተክቢራ ቀጥሎ አዑዙ ቢላሂ ሚነ ሸይጧኒ ረጂም ቢስሚላሂ አር-ረህማኒ አር-ረሂም ይበልና ፋቲሃን በውስጡ ያንብብ፡፡

ከዚያም ሁለተኛ አላሁ አክበር ካለ በኋላ ለነቢዩ ሶለዋት ያወርዳል፡፡ በሶስተኛዉ አላሁ አክበር ካለ በኋላ ለሟቹ ዱዓ ያድርግ፡፡ ከዚያም አራተኛውን አላሁ አክበር ካለ በኋላ ትኒሽ ቆም ብሎ በቀኝ በኩል አንድ ጊዜ ብቻ ሰላምታ ያድርግ[2]፡፡

ከስንዝር በላይ ቀብርን ማሳደግ፤ በከሚንቶ ማነፅ፤ ቀብርን መሳም፤ በዉስጡና በአካባቢዉ ማጫጫስ፤ በቀብር ላይ መፃፍ ወይም መቀመጥ ወይም በላዩ ላይ መሄድ ክልክል ነው፡፡ ቀብርን ማብራት፡ መጠወፍ/ እንደ ከዕባ ዙሪያውን መዞር/ በእሱ ላይ መስጊድ መገንባት ወይም በመስጊድ ዉስጥ መቀበር ክልክል ነው፡፡ በመቃብር ላይ ያሉትን ቁባዎች ማፍረስ ግዴታ ነው፡፡

✹ በታዕዚያ አባባል ቃሎች ላይ ይህ ብቻ ነዉ ተብሎ የተወሰነ ነገር የለም፡፡ ከእነዚህም መካከል (አዕዞመላሁ አጅረከ ወአህሰነ ዐዛአክ ወገፌረ ሊመይቲከ) ማለት አንዱ ነው፡፡ ካፊር ዘመድ የሞተበትን ሙስሊም በማጽናናት ጊዜ (አዕዞ መላሁ አጅረከ ወአህሰነ ዐዛአክ) ይበል

✹ ሲሞት ዘመዶቹ እንደሚያለቀሱበት ያወቀ ሰው እንዳያለቅሱበት መናዘዝ አለበት:: አለበለዚያ

---

ወሀደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁልሙልኩ ወለሁልሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር ይላል፡፡ ከዚያም አየተልኩርሲን ያነባል፡፡ከዚያም ቁል ሁወሏሁ አሀድን፤ቁል አዐኡዙ ቢረቢል ፈለቅን፤ ቁል አዑዙ ቢረቢ ናስን ያነባል፡፡ ከሱብሂና ከመግሪብ በኋላ ግን ቁል ሁወ አሏሁ አሀድን፤ቁል አዐኡዙ ቢረቢል ፈለቅን ፤ ቁል አዑዙ ቢረቢ ናስን ሶስት ሶስት ጊዜ ያነባቸዋል፡፡

1 ይህ ማለት የተወሰነው ክፍል ከሰራው ሌላው የማይጠየቅበት ሁሉም ካልሰራው ግን እያንዳንዱ ሰዉ ተጠያቂ የሚሆንበት ጉዳይ ማለት ነው፡፡

2 የዚህ መጽሐፍ ዋና የሆነው በዐረበኛ የተዘጋጀው አብዛኛው ኢማሙ የአህመድ ብን ሐንበልን መዝሀብ ተከትሎ የተዘጋጀ በመሆኑ አንዳንድ ቦታ ላይ ከሌሎች መዝሀቦች ለየት ያለነውና ግር ሊለን አይገባም፡፡ ሁሉም ማስረጃውን ነው መከታተል ያለብን፡፡

ግን በልቅሶአቸው ይቀጣበታል፡፡

✸ኢማሙ ሻፌዒ ለሐዘን መቀመጥ ይጠላል ብለዋል፡፡ ይህም ማለት የሟች ዘመዶች ሊያፅናናቸው የሚፈልገዉን ሁሉ ለመቀበል መቀመጣቸው ሲሆን ይህ ተግባር ለወንድም ሆነ ለሴት አግባብ አይደለም:: ሁሉም ወደ ጉዳዩ መንቀሳቀስ አለበት፡፡

✸ለሟች ቤተሰብ ምግብ ሰርቶ ማቀረብ ሱና ነው፡፡ ከእነሱ ምግብ መመገብ ግን ይጠላል፡፡ በቤታቸዉም ለሚሰበሰቡት ሰዎች ምግብ መከሩት ይጠላል፡፡

✸ የሙስሊምን ቀብር መዘየር ሱና ነው፡፡ የከሓዲዎችን መቃብር መዘየር ይፈቀዳል፡፡ ከሓዲዎች የሙስሊሞችን ቀብር ቢጎበኙ አይከለከሉም፡፡

✸ወደ ቀብር ግቢ የገባ ሰው (አሰሰላሙ ዐለይኩም ዳረ ቀውሚን ሙእሚኒን ወይም- አህለዲያሪ ሚነል ሙእሚኒን-ወሊና ኢንሻአሏህ ቢኩም ለላሒቁን የርሀሙሏሁል ሙስተቅዲሚን ሚንኩም ወልሙስተእኺሪን ነስአሉሏሁ ለና ወለኩም አል-ዐፊየህ አላሁመ ላተህሪምና አጅረሁም ወላ ተፍቲንና በዕደሁም ወግፊርለና ወለሁም) (በዚህ መካነ መቃብር የምተገኙ ምእምኖች የአላህ ሰላም ለእናንተ ይሁን፡፡ አላህ ሲፈቅድ ከእናንተ እንቀላቀላለን፡፡ለእኛም ለእናንተም አላህ ምህረቱን እንማፀነዋለን) *አላህ ሆይ፣ ምንዳቸዉን አትከልክለን። ከነርሱ በኋላም አትፈትነን። ለኛም ለነርሱም ምህረት አድርግልን>* ማለቱ ሱና ነው፡፡

✸ እንዳይነጀስና ክብሩ እንዳይደፈር ለመጠንቀቅ ዲኖዊ መሊዳ ከለሌለው በስተቀር ላይ ቁርአንን መጻፍ የተከለከለ ነው፡፡

✸ ለሞቱ ሰዎች ጠቀለል ያለ ዱዓ ማድረግ ተገቢ ነዉ፡፡ *ነቢዩ ሙሐመድ* (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ለሞተ ሰው ይህን ዱዓ አድርገዋል፡፡ (አላሁመ ግፊርለሁ ወርሀምሁ ወዓፊሂ ወዕፉ ዐንሁ ወአክሪም ኑዙለሁ ወወሲዕ ሙድኸለሁ ወግሲልሁ ቢልማኢ ወሰልጂ ወልበረዲ ወነቂሂ ሚነል ኸጣያ ከማ ኑቀይተ ሰውበል አብየደ ሚነ ደነሲ ወአብዲልሁ ዳረን ኸይረን ሚንዳሪሂ ወአህለን ኸይረን ሚን አህሊሂ ወዘውጀን ኸይረን ሚን ዘውጂሂ ወአድኺልሁል ጀነተ ወአዒዝሁ ሚን ዐዛቢልቀብሪ ወሚን ዐዛቢ ናር) (አላህ ሆይ! ማረው፤ እዘንለት፤ ሰላም ለግሰው፤ ይቅር በለው፤መስተንግዶዉን አሳምርለት፤መግቢያዉን አሳምርለት፤በዉሃና በበረዶ እጠበው፤ ነጭ ሸማ ከቆሻሻ እንደሚጠራ ሁሉ ከወንጀል አጥራው፤ ከቤቱ የተሻለ ቤትን ለዉጠው፤ ከቤተሰቡም የተሻለ ቤተሰብ ከጠው፤ ጀነት አስገባው፡፡

<u>የኢድ ሶላት፡-</u> በተወሰነ ሰው ላይ ግዴታ የሆነ ነው:: ማለትም የተወሰኑት ሰግደዉ ሌሎች ባይሰግዱ ጥፋተኛ አይሰኙም፡፡ ዘዜዋም ልክ እንደ ለዱሓ ሶላት ወቅት ነው፡፡ ከግማሽ ቀን በኋላ ዒድ መሆኑ ቢታወቅ በበነጋው ቀዷ ሆኖ ይሰገዳል፡፡ ሙከፊርቱ ከሁለቱ ኹጥባዎች በስተቀር ልክ እንደ ጁሙዐ ነው፡፡ በመከገጃው ቦታ ላይ በቤትም ሆነ በኋላ ሱና ሶላት መከገድ ይጠላል፡፡

<u>የኢድ ሶላት</u> አሰጋገዷ ሁለት ረከዐ ነው፡፡ በመጀመሪያው ረከዐ ላይ ከኢህራም ተክቢሩ በኋላና ከአዑዙ ቢላህ በፊት ከድከት ዘዜ አላሁ አክበር ይባላል፡፡ በሁለተኛው ረከዐ ከንባብ በፊት አምስት ዘዜ አላሁ አክበር ይባላል፡፡

ከየተክቢራዉ ጋር ሁለቱም እጅ መነሣት አለበት፡፡ ከዚያም አዑዙ ቢላሂ ይበል፡፡ ከዚያም ፋቲሓን ድምፁን ከፍ አድርጎ ያንብብ፡፡ ከዚያም ሱረቱ አል አዕላን በመጀመሪያዋ ረከዐ ሱረቱል አልጋሺየህን በሁለተኛዋ ረከዐ ያንብብ፡፡

ከዚያም ሲያሰላምት እንደ ጁሙዐ ኹጥባ ሁለት ኹጥባ ይኸጥብ፡፡ ሆኖም ግዩ በኹጥባው ውስጥ ተክቢሩ /አላሁ አክበር / የሚለዉን ቃል በብዛት ማለቱ ይወደዳል፡፡ የኢድን ሶላት እንደ ተርፍ ሶላት ቢሰግዱትም ምንም ችግር የለዉም፡፡ ምክኒያቱም ተክቢራዎቹ ተጨማሪ ሱናዎች ናቸዉ፡

<u>የፀሐይ ግርዶሽ ሶላት፡-</u> የፀሐይ መሸፈን ሶላት ሱና ነው፡፡ ዘዜው ፀሐይ ወይም ጨረቃ ከተሸፈኑችበት ዘዜ ጀምሮ ግርዶሹ እስከሚወገድ ድረስ ባለው ሰዐት ነው፡፡ ካለፈ በኋላ ቀዷ የሚወጣ አይደለም፡፡ እሱም ሁለት ረከዐ ነው፡፡ በመጀመሪያው ረከዐ ላይ ፋቲሓንና ረዘም ያለ ሱራን ማንበብና ከዚያም ረጂም ሩኩዕ ማድረግ ነው፡፡ ከዚያም ሰሚአላሁ ሊመን ሀሚደህ ረበና ወለከልሀምድ ብሎ ሱጁድ ሳያደርግ እንደገና ፋቲሓንና ረዘም ያለች ሱራን ማንበብና ከዚያም ረጂም ሩኩዕ ማድረግ ነው፡፡ ከዚያም ተነስቶ ሁለት ረዳጅም ሱጁዶች ማድረግ ነው፡፡ ከዚያም ሁለተኛው ረከዐ ልክ እንደ መጀመሪያው መስገድና አተሒያቱን አንብቦ ማሠላመት ነው፡፡ ከመጀመሪያው ሩኩዕ በኋላ ይህን ሶላት ተከትሎ ለመስገድ የመጣ ሰው ሰላቱን አልደረሰበትም፡፡

<u>የዝናብ ፍለጋ ሶላት፡-</u> የዝናብ ፍለጋ ሶላት ምድር ከተደርቀና ዝናብ ሲጠፋ የሚሰገድ ሱና ሰላት ናት፡፡ ዘዜው የአሰጋገዷ ከርአትና ሌሎችም ህግጋቶቹ፤ ኹጥባው ከሶላት በኋላ ከመሆኑ በስተቀር ልክ እንደ ዒድ ሶላት ነው፡፡ በመጨረሻው ላይ የሁኔታዎችን መቀየር ለማመልከት ልብሱን/ ነጠላን፣ ጋቢን/ መቀየር/መገልበጥ ሱና ነው፡፡

# ዘካህ

**የዘካህ አይነቶች:** ዘካ በአራት የሀብት አይነቶች ላይ ግዴታ ነው:: እነሱም፡- 1)ከቤት እንሰሳት፤ 2) ከመሬት ከሚበቅሉ ነገሮች፤ 3) ከማዕድናት፤ 4) ከንግድ ሸቀጣ ሸቀጦች ነዉ::
**ግዴታ ለማድረግ የሚችሉ ቀድመ መከፈርቶች፡፡ አምስት ነገሮች ካልተሟሉ በቀር ዘካ ግዴታ አይሆንም::** እነሱም፡- 1) ሙስሊም መሆን፤ 2) ከባርነት ነፃ መሆን፤ 3) ዘካዉ የሚወጣበት ነገር ኒሷብ /የግዴታ ገደብ/መድረስ፤ 4) በሀብት ላይ የተሟላ ባለቤትነት መኖር፤ 5) ከህሎች ሌላ ለሆነው ነገር በሙሉ ዓመት መሙላት ናቸው::
**የቤት እንሰሳት ዘካ:** እነሱም ሶስት አይነት ሲሆኑ ግመል፤ የቀንድ ከብትና ፍየል/ በግ/ ናቸው:: የእንሰሳ ዘካ የሚወጣዉ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው:: 1) ዓመቱን ሙሉ ወይም አብዛኛዉን ጊዜ በግጦሽ ላይ ካሳለፈች፤ 2) ለስራ ሳይሆን ለማርባትና ለወተት የተዘጋጁ ከሆኑ ነው:: ለንግድ የተዘጋጁ ከሆኑ ደግሞ ዘካቸው እንደ ንግድ ሸቀጥ ይወጣል::

**1- የግመል ዘካህ**

| ቁጥሩ | ከ1-4 | ከ5-9 | ከ10-14 | ከ15-19 | ከ20-24 | ከ25-35 | ከ36-45 | ከ46-60 | ከ61-75 | ከ76-90 | ከ91-120 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዘካው | የለበትም | አንዲት ፍየል | ሁለት ፍየሎች | ሶስት ፍየሎች | አራት ፍየሎች | የአመት ግመል | የሁለት አመት ግመል | የሶስት አመት ግመል | የአራት አመት ግመል | ሁለት የአመት ግመል | የሁለት አመት ግመል |
| ቁጥሩ ከመቶ ሀያ ግመል በላይ ከጨመረ በየሃምሳው አንዲት ሂቀህ በየአርባው ቢንተ ለቡን እየከፈለ ይቀጥላል:: | | | | | | | | | | | |

**2- የከብት ዘካህ**

| ቁጥሩ | ከ1-29 | ከ30-39 | ከ40-59 |
|---|---|---|---|
| ዘካው | ምንም የለበትም | አንዲት አመት የሞላት/ው | አንዲት ሁለት አመት የሞላት/ው :: |
| ስልሳ ከደረሱ በየሰላሳው ተቢዕ ፤በየ አርባው ሙሲና ይሰጣል :: | | | |

**3- የፍየል ዘካ**

| ቁጥሩ | ከ1-39 | ከ40-120 | ከ121-200 | ከ202-399 |
|---|---|---|---|---|
| ዘካው | የለበትም | አንደ ፍየል | ሁለት ፍየል | ሶስት ፍየል |
| አራት መቶ ሲደርስ በየ መቶው አንዲት ፍየል እየሰጠ ይቀጥላል:: በፍየል ዘካ ላይ ወጠጤ፤ ያረጀች፤ አይነ ከዉር፤ ዕመጫት፤ እርጉዝ ተብሎ ተመርጦ አይወሰድም:: | | | | |

**ከምድር የወጡ ነገሮች ዘካ አወጣጥ:-** ከምድር የወጡ ፍራፍሬዎችም ሆነ እህሎች ሶስት ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉላቸው ዘካ ግዴታ ነው :: እነሱም:-
**1-የሚሰፈርና** የሚቀመጥ መሆን፤ ይኸውም እንደ ስንዴ፤ ገብስ፤ ተምርና ወይንን የመሰሉ ነገሮች ናቸው:: የማይሰፈርና ለማስቀመጥ የማይቻለው እንደ አትክልትና ስራስር ያለው ዘካ የለበትም ::
**2-የግዴታ ገደብ** መሙላት ሲሆን እርሱም 653 ኪ.ግ.ና ከዚያም በላይ ሲሆን ነው ::
**3-ዘካው በወጀበበት /ግዴታ በሚሆንበት/** ጊዜ የራሱ ንብረት መሆን ሲሆን፡፡ ግዴታ የሚሆነዉም ፍሬው ለመበላት ሲደርስ ነው፡፡ ፍሬዉ መድረሱ የሚታወቀዉ ሲቀላና ሲገረጣ ሲሆን እህል ከሆነ ደግሞ ፍሬዉ ሲደርቅና ሲጠነክር ነዉ:: ያለምንም ልፋት በዝናብና በጅረት ዉሃዎች ለጠጡ እህሎች አንድ አስረኛ 1/10ኛ (10%) መስጠት ግዴታ ነው:: ሰዎች በጉልበት ለጠጡና ላፈሩ ደግሞ የአንድ አስረኛ ግማሽ 1/20ኛ (5%)ውን መስጠት ግዴታው ነው:: በሁለቱም የሚጠጡ ከሆነ ደግሞ በአብዛኛው በምን አንደጠጣ ታይቶ በዚያው መሰረት ዘካው ይወጣል::
**የወርቅ ዘካህ፡-** ወርቅ 85 ግራም እስከሚሞላ ድረስ ዘካህ የለበትም::
**የብር ዘካህ:-** ብር 595 ግራም እስከሚሞላ ድረስ ዘካህ የለበትም:: በሌሎች ብሮችና የወረቀት ገንዘቦች ዋጋቸው ከሁለቱ የአነስተኛዉን ልክ ግምት ሳይደርስ ለዘካህ አይገደዱም:: የወርቅና የብር ዘካህ የአንድ አስረኛ አንድ አራተኛው 1/40ኛ (2.5%):: ሰው ለመጠቀም የተዘጋጀ ጌጣጌጥ ዘካ የለበትም:: ለማከራየትና ለማስቀመጥ የተዘጋጀ ከሆነ ግን በየአመቱ ዘካ አለበት::
**ሴቶች በተለምዶ:** የሚጠቀሙበትን የወርቅና የብር ጌጣጌጥ መጠቀም ይፈቀድላቸዋል:: በእቃዎች ላይ ትንሽ የብር ዱቄት መጨመር ይቻላል:: ወንዶችም ከብር ጥቂት ጥቂትን ለምሳሌ የጣት ቀለበት፤ መነፅርና የመሳሰሉትን መጠቀም ይችላሉ:: ወርቅን ግን በዕቃ ላይ መጠቀም ፍፁም አይፈቀድም:: ወንዶች ከሌላ ጋር ብር (ወርቅ) ተጨምሮ ትንሽ ትንሽ ለምሳሌ የልብስ ዚብና የጥርስ ማሰሪያን ይመስል ከሴቶች በማይመሳሰሉበት መልኩ

መጠቀም ይፈቀድላቸዋል::

**በየጊዜው የሚጨምርና** የሚቀንስ ገንዘብ ያለውና ለያንዳንዱ በየአመቱ ዘካ መስጠት ያስቸገረው ሰው በአመት ዉሰጥ በራሱ በወሰነው ዕለት ስንት አንዳለው አስቦ ያለበትን ሊያወጣ ይችላል:: የተወሰነው ገንዘብ አመት ባይሞላዉም ቀን ወከኖ በዚያ ጊዜ ባለው ሀብት ያውጣ:: ያሞዝተኛ ወይም የሚከራይ ነገር ያለው ሰው ተቀማጭ ከሌለው ብዙም ቢሆን ዘካ የለበትም:: ተቀማጭ ካለው ግን አመት ሲሞላው ዘካ ያወጣል:: አመቱ የሚያስቸግረው ከሆኑም ከአመቱ ዉስጥ አንድ ቀን ወስኖ ዘካዉን ያውጣ::

**የብድር ዘካ:-** ለሀብታም ያበደረ ወይም ሊለቀቅ የሚችል ገንዘብ ከሰው ዘንድ ያለው ሰው ገንዘቡን ሲቀበል ላለፉት አመታት ጭምር ቢበዛም ዘካ ያወጣል:: ብድሩ ካልተመለሰለት ግን ፦ ለድሃ ያበደረን ይመስል ዘካ የለበትም::

**የሸቀጣ ሸቀጥ ዘካ:-** አራት ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ ዘካ ማውጣት ግዴታ ነው:: እነሱም:- 1) የተሟላ ባለ ንብረትነት፤ 2) ንግድ የታሰበበት መሆን፤
3) ከወርቅ አሊያም ከብር አነስተኛዉን የግዴታ ገደብ መጠን ሲደርስና፤
4) ሳይጎድል አመት መድረስ ናቸው:: እነዚህ ከተሟሉ በሂሳቡ ዘካ ይሰጣል:: ወርቅና ብር ወይም ሌላ ገንዘቦች ቢኖረው ከሸቀጡ ዋጋ ጋር ደምሮ ገደቡን ከደረሰ ዘካዉን ያውጣ:: ለንግድ ሳይሆን ለግል አገልግሎት ለሚጠቀምባቸው ነገሮች፣ ለምሳሌ ልብሱን ሊለብሰው፤ ቤቱን ሊኖርበት፤ መኪናዉን ለራሱ ሊነዳው ቢፈልግ ዘካ የለበትም:: ተመልሶ ንግድ ቢነይትበተ ደግሞ እንደገና ቅድመ ሁኔታዉን ሲያሟላ ዘካ ያወጣል::

**የፊጥር ዘካ:-** የኢድ ቀንና ሌሊት ራሱና ቤተሰቡ ሊበላው ከሚበቃው በላይ ትርፍ ንብረት ያለው ሰው ሁሉ የፊጥርን ዘካ መስጠት ግዴታው ነው:: መጠኑም ለያንዳንዱ ሰው በአካባቢው ከሚበላው እህል ሁለት ኪሎ ከሩብ (2.25) ያላነሰ መስጠት ግዴታ ነው:: የፊጥር ዘካ ግዴታ የሆነበት ሰው መቀለቡ ግዴታ ለሆነበት የቤተሰብ አካላት ሁሉ ሊሰጥላቸው ግዴታ ነው:: የዒድ ቀን ከሶላት በፊት መስጠቱ ይወደዳል:: ከዒድ ሶላት ማዘግየቱ አይፈቀድም፡፡ ከዒድ በፊት ለአንድ ቀን ወይም ለሁለት ቀን ያህል ማስቀደም ይፈቀዳል:: የብዙ ሰዎችን ግዴታ አንድ ሰው ሊያወጣ ይችላል:: ብዙ ሰዎችም የአንድን ሰው ግዴታ ሊያወጡ ይችላሉ::

**ስለዘካ አወጣጥ:-** ዘካን በቶሎ ማውጣት ግዴታ ነው:: የሕፃናትንና የአዕምሮ በሽተኞችን ዘካ ሀላፊዎቻቸው / አስተዳዳሪዎቻቸዉ / ያወጡላቸዋል:: በይፋ መስጠቱና በገዛ ራሱ ባለቤቱ ማከፋፈሉ ሱና ነው:: ዘካ ሲወጣ ኒያ ግዴታ ነው:: ሁሉንም ገንዘብ በሶደቃ ሐሳብ ቢሰጥ ዘካው ተቀባይነት የለዉም:: የሚመረጠው የዘካ ገንዘቦችን ለአካባቢው ድሆች ማከፋፈሉ ነው:: የተሻለ ጥቅም ከታሰበበት ግን ወደ ሌላ ሀገርና አካባቢ መላክ ይቻላል:: ገደቡን ለሞላ ገንዘብ በቅድሚያ የሁለት አመት መክፈልም ይቻላል::

**ዘካ የሚሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ስምንት ናቸው::** 1) ምንም የሌላቸው ድሆች፤
2) በቂ ያልሆነ ሀብት ያላቸው ምስኪኖች ፤ 3) ለዘካ አስተባባሪዎች፤ 4) ልቦቻቸዉ የሚለማመዱ ሰዎች/አዲስ ወደ እስልምና የገቡ ሰዎች/፤ 5) ሰዎችን ከባርነት ነፃ ለማውጣት፤ 6) /ዕዳ/ ብድር ያለባቸው ሰዎች ለማላቀቅ፤ 7) በአላህ መንገድ ላይ ለሚደረጉ ትግሎች(ለጂሃድ፤ 8) በመንገድ ላይ የተቋረጠ ሰው ናቸው:: ሁሉም የሚሰጣቸው የችግራቸዉን ያህል ሲሆን አስተባባሪው ግን ሀብታምም ቢሆን መስሎቹ የሚከፈላቸዉን ደመወዝ ያህል ይከፈለዋል:: ሽፍቶች ወይም አመፀኞች ሀገሩን ተቆጣጥረው የዘካ ገንዘብ ለእነሱ ባሉበት ቢሰጣቸው ይሆናል:: መሪው በግድም ሆነ በዉድ ዘካን ከወሰደ ቢያጠፋበተም ቢያለማበትም ዘካው እንደተወጣ ይሆናል:: ለከሃዲ: ለባሪያ: ለሀብታም: መቀለብ ለሚወጅብበትና ዘሞዶቹ ለበኒ ሀሺሞች ዘካን መስጠት አይሆንም:: አይፈቀድም፡፡ ለማይገባው ሰው ሳያዉቅ የዘካን ገንዘብ የሰጠ እና ሁዋላ ላይ እንደማይገባዉ ቢያዉቅ የሰጠው አይሆንለትም:: አይቆጠርለትም ድሃ መስሎት የሰጠና ሁዋላ ሀብታም መሆኑን ቢረዳም ዘካው ይበቃለታል::

**ትርፍ ሶደቃ:-** ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ኢብኑ ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል (አማኞች ከሚከተሏቸው መልካም ተግባሮች መካከል ያከተማረውና ያስፋፋው ትምህርት: መልካም ልጅ፤ ያወረሰው ቁርአን፤ ወይም የገነባው መስጀድ: ወይም ለመንገደኞች ማረፊያ ይሆን ዘንድ የገነባው ቤት፤ ወይም የቀደደው የጅረት ዉሃ፤ ወይም በጤናውና በሕይወቱ እያለ የለገሰው ስጦታ/ሶደቃ/ ከሞተ በኋላ ይከተሉታል::) ብለዋል፡፡

# ፆም

ሙስሊም በሆነ፤ ጤናማ አእምሮው ባለዉ፤ ለአቅመ አዳም በደረሰ፤ ለመፆም በሚችል፤ ከወር አባባና ከወሊድ ደም ነፃ በሆነች ላይ ሁሉ የረመዷንን ወር መፆም ግዴታ ነው:: ህፃን ልጅ ከቻለ እንዲለማመደው ፆም እንዲፆም ይታዘዛል:: ይበረታታል፡፡

**የረመዷን ወር መግባት** ከሁለት ነገር በአንዱ ይታወቃል፡፡ **1)** ሴትም ሆነ ወንድ ፍትሃዊና ታማኝ የሆነ ጨረቃን በማየቱ፤ **2)** የሸዕባን ወር ሰለሳ ቀን መሙላት ነው:: የፆም ጊዜ እዉነተኛዉ ጎህ ከቀደደበት (ከወጣበት) ጀምሮ እስከ ፀሐይ መጥለቅ ድረስ ነው:: በፈርድ/ግዴታ/ ፆም ጊዜ ከመንጋቱ በፊት መነየት/ለመጾም ሀሣብ ማሣደር/ ግዴታ ነው::

**ፆምን የሚያበላሹ ነገሮች፡-1)** በግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ነው፡፡- ይህን ተግባር የፈፀመ ሰዉ አንድ ባሪያ ነፃ ማውጣት ይኖርበታል፡፡ ይህን ካላገኘ ደግሞ ሁለት ወር በተከታታይ መፆም አለበት፡፡ ይህን ያልቻለ ደግሞ ስልሳ ድሆችን ለእያንዳንዳቸው የአንድ ጊዜ ምግብ መመገብ ይኖርበታል፡፡ ይህን ያልቻለ ሰው ምንም የለበትም::

**2)** በመሳሳም ወይም በመነካካት ወይም በእጅ ብልትን በመነካካት የዘር ፈሳሽን ማፍሰስ፤

**3)** ሆን ብሎ መብላትና መጠጣት:: ረስቶ ከሆነ ፆሙ ምንም ችግር የለበትም::

**4)** በመታገምም ይሁን ደም ለመለገስ ደምን ማስወጣት ሲሆን ለምርመራና መሰል ነገሮች የሚወሰድ ጥቂት ደም ወይም ከቁስልና ነስር በመሳሰሉ የሚወጣ ደም ፆምን አያበላሽም::

**5)** አውቆና ሆን ብሎ ማስታወክ:: አቧራ ጉሮሮ ቢገባ፤ወይም ቢጉመጠመጥ ወይም ለሰላት በዉዱዕ ጊዜ በአፍንጫዉ ዉሃ ቢወስድና ዉሃው ወደ ጉረሮው ቢደርስ ወይም ስለ ሴት አስቦ የዘር ፈሳሽን ቢያፈስ ወይም በህልሙ የዘር ፈሳሽ ቢወጣዉ ወይም ከየትኛዉም የአካል ክፍሉ ደም ቢፈሰው ወይም ሳይፈልግ ቢያስታዉክ ፆሙ አይበላሽም:: ያልነጋ መስሎት የበላና ኋላ ላይ መንጋቱን ያረጋገጠ ያችን ቀን ብቻ ቀዷ አለበት:: መንጋት አለመንጋቱን እየተጠራጠረ የበላ ሰው ፆሙ አይበላሽም:: ፀሐይ መጥለቅ አለመጥለቋን እየተጠራጠረ በቀን የበላ ሰው ግን ፆሙ ይበላሻል:: እናም የዚያ ቀዷ አለበት::

**የአፍጣሪዎች ብያኔ:-** ምንም ምክኒያት ለሌለው ሰው በረመዷን ወር ማፍጠሩ ክልክል ነው:: የወር አበባና የወሊድ ደም ያለባቸው ሴቶችና ክቡሩን የሰው ልጅ ከሞት ለማዳን ማፍጠር ያስፈለገው ሰው ማፍጠር ግዴታቸው ነው:: ሶላት ለማሳጠር የሚያስችል ጉዞ ላይ ያለና ፆም የከበደው እንዲሁም በመፆሙ ችግር በራሱ ላይ የፈራ በሽተኛ ማፍጠራቸው ሱና ነው:: በቀን ጉዞ ለጀመረ ሰውና በራሳቸዉም ላይ ሆነ በልጆቻቸው ላይ ለሚፈሩ ነፍሰ ጡርና እመጫት/የሚያጠቡ ሴቶች ማፍጠር ይፈቀድላቸዋል:: እነዚህ ሁሉ ቀዷ ብቻ ነው ያለባቸው:: በልጆቻቸው ላይ ብቻ የፈሩ ነፍሰ ጡርና እመጫት ሴቶች ለየቀኑ ከቀዷ በተጨማሪ አንዳንድ ድሃ ማብላት አለባቸው:: በዕድሜ መግፋት ምክኒያት ወይም የመዳን ተስፋ በሌለው በሽታ መፆም ያቃተው ሰው ለየቀኑ አንዳንድ ድሃ ማብላት አለበት:: ቀዷ የለባቸዉም::

በችግር ምክኒያት ሌላ ረመዷን እስከሚመጣ ድረስ ቀዷን ያዘገየ ሰው ቀዷ ብቻ ነው ያለበት:: ያለበቂ ምክኒያት ከሆነ ግን ቀዷ ከማውጣቱ ጋር ለየቀኑ አንዳንድ ድሃ ማብላት ይበቅበታል፡፡ በችግር ምክኒያት ቀዷ ሳያወጣ የሞተ ሰዉ ምንም የለበትም:: ያለ ችግር ከሆነ በያንዳንዱ ቀን ስለርሱ በመሆን ዘመዶቹ አንድ አንድ ድሃ ማብላት ያስፈልጋል፡፡ ዘመዱ የሆነ ሰው ያዘገየዉን የረመዷንን ቀዷ፤ የስለት ፆሙንና ለአላህ ሲል የተሳለዉን የአምልኮ ተግባር ሁሉ መፈፀም ሱና ነው:: በችግር ምክኒያት አፍጥሮ ግማሽ ቀን ላይ ያፈጠረበት ችግሩ የተወገደለት፤ እንዲሁም ከሃዲ የነበረ ቢያምን፤ ወይም በሽተኛው ቢድን ወይም መንገደኛው ከመንገድ ቢመለስ ወይም ህፃኑ ለአቅመ አዳም /ሂዋን/ ቢደርስ ወይም የአዕምሮ በሽተኛ ቢሻለዉ ሁሉም የቀረዉን ቀን ማፍጠር ይችላሉ፡፡ ቀሪዉን ቀን ቢፆሙም እንኳዋን ቀዷ/ካሳ አለባቸው:: ረመዷንን እንዲያፈጥር የተፈቀደለት ሰው ሌላ ፆም በዚያው ቀን ዉስጥ መፆም አይፈቀድለትም::

**በትርፍ ፆም ዙሪያ ተመራጩ** ፆም አንድ ቀን መፆምና አንድ ቀን ማፍጠር ነው:: ከዚያም

ሰኞና ሐሙስን መፆም ነው:: ከዚያም በየወሩ ሶስት ሶስት ቀን መፆም ነው:: ሶስቱም ቀናት በየወሩ በዐረብኛ አቆጣጠር 13ኛ፤14ኛና 15ኛ ቀኖች መሆናቸው:: ይሞርጣል የሙሐረምና የሸዕባንን ወሮች አብዛኛዉን ቀናት፣ የዐሹራን ቀን ፡ የሸዋልን ስድስት ቀናት መፆም ይወደዳል:: የረጀብን ወር፤ ጁሙዓንና የቅዳሜን ቀን በመነጠል መጾም፤ ተጠርጣሪው ቀን ማለትም ዳመና በሌለበት ቀን የሸዕባንን ሰላሰኛ ቀን በፆም መነጠል ይጠላል:: የኢድ አል-ፍጥር ቀንና የአድሃን ቀን መፆም የተከለከለ ነዉ፡፡ የተሸሪቅ ቀናቶችን/ከዐረፋ ቀኑ በኋላ ያሉትን ሶስት ቀናት በተመቱዕ ወይም በቂራን ሐጅ አድርጎ ደም ማፍሰስ/ማረድ ያለበት ሰው ሲቀር መፆም ክልክል ነው::

**ጠቃሚ ማሳሰቢያዎች:-** ✸ ጀናባ ያለበት እንዲሁም ከወር አበባና ከወሊድ ደም ከመንጋቱ በፊት የፀዳች ሴት ሱሁርን በመብላት ከነጋ በኋላ ቆጥበው ፆማቸዉን መቀጠል ይችላሉ::

✸በጤናዋ ላይ ችግር የማያስከትል ከሆነ ሴት ልጅ ከሙስሊሞች ጋር ለመፆም ብላ የወር አበባዋን የሚያዘገይ መድሀኒት መውሰድና ማራቆም ይፈቀድላታል::

✸ፆመኛ ምራቁን ወይም አክታዉን መዋጥ ችግር የለዉም::

✸ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድ በዘገቡት ሐዲስ «ህዝቦቼ ፍጥርን እስካፋጠኑና ሱሁርን እስካዘገዩ ድረስ ቁኸይር ላይ ናቸዉ »:: ብለዋል፡፡

✸ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡዳዉድ በዘገቡት ሐዲስ «ሰዎች ፍጥርን እስካፋጠኑ ድረስ ይህ ሃይማኖት የበላይ ከመሆን አይወገድም:: ምክኒያቱም አይሁዶችና ክርስቲያኖች ፍጥራቸዉን/ ፆም ለመግደፍ/ ያዘገያሉና» ብለዋልም፡፡

✸በፊጥር ሰዐት ዱዓ ማድረግ ይወደዳል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ኢብኑ ማጀህ በዘገቡት ሐዲስ (ፆመኛ ሲያፈጥር ተመላሽነት የሌለው ዱዓ አለው::) ብለዋል፡፡

✸በፊጥር ጊዜ ከሚባሉ ዱዓዎች መካከል ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡዳዉድ በዘገቡት ሐዲስ (ዘሀበ-ዞመኡ ወብተለቲልዑሩቁ ወሰበተል አጅሩ ኢንሻ አላህ) የሚለዉ ዋናዉ ነዉ::

✸ሱናው በተምር እሸት ማፍጠር ሲሆን፤ ይህን ካላገኘ በደረቅ ተምሮች፤ ይህ ካልተገኘም በዉሃ ማፍጠር ነው::

✸ፆመኛ ኩል መጠቀምን፤ የጆሮም ሆነ የአይን ጠብታን፤ በዐሊሞች መካከል ያስፈጥራል አያስፈጥርም ከሚለው ክርክር ነፃ ለመሆን ሲባል መታቀብ ችለዋል:: ለህክምና ምክኒያት አስፈልጎት ቢፈፅመው ግን ጣዕሙ ወደ ጎሮሮዉ ቢደርስም ምንም ችግር የለዉም::

✸ በየትኛዉም ሰዐት በፆም ጊዜ ሲዋክ መጠቀም ካለ ማከሌጠኑ አልፎ ሱና ነው::

✸ፆመኛ ሀሜትን ፤ነገር ማሳበቅን፤ዉሸትንና የመሳሰሉትን መተው ይገባዋል:: ሰው ቢሰድበው «እኔ ፆመኛ ነኝ» ይበል:: ምላሱንና ሌላ ሰዉነቱን ከወንጀል በመጠበቅ መፆም ይገባዋል:: ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ (ዉሸት ንግግርንና በሱ መሥራትን ያልተወ ሰው ምግብንና መጠጥን በመተዉ አላህ ከሱ ምንም ጉዳይ የለዉም) ብለዋል::

✸ፆመኛ ሆኖ ግብዣ የተጠራ ሰው ለጋባዡ ዱዓ ያድርግለት:: ያልፆመ ከሆነ ግን ይመገብለት::

✸ለይለተ አል-ቀድር በአመቱ ዉስጥ ካሉ ሌሊቶች ሁሉ ብልጫ ያላት ናት:: የምትገኘውም በረመዷን በመጨረሻዎቹ አስርት ቀናት ዉስጥ ነው:: በጣም የሚጠበቀው በሀያ ሰባተኛዋ ሌሊት ነው:: በዚህች በለይለተልቀድር ሌሊት የሚሰራው ኸይር ስራ በሌላዉ አንድ ሺ ወር ዉስጥ ከሚሰሩ ኸይር ስራዎች የበለጠ ነው:: ይህች ሌሊት ብዙ ምልክቶች አሏት:: ከነዚህም መካከል - የዕለቷ ፀሐይ ያለ ብዙ ጨረር ነጭ ሆና መውጣቷ፤ አየሩ መስተካከሉ ነው:: ማንኛዉም ሰው ሳያስብ ይህችን ሌሊት ሊያገኛት ይችላል:: አስፈላጊው ነገር በረመዷን ዉስጥ ዒባዳ ማብዛትና በተለይም በመጨረሻዎቹ አስር ሌሊቶች ላይ በይበልጥ በማተኮር የትኛዉንም ሌሊት ሳይቆምበት ላለማሳለፍ መጠናከር ነው:: ተራዊህም ሲሰግድ ሙሉ ሌሊት እንደቆመ እንዲቆጠርለት ኢማሙ እስከሚጨርስ ድረስ አብሮ መቆም አለበት::

✸ትርፍ ፆም ላይ የገባ ሰው መጨረሱ ሱና ነው:: ግዴታው ግን አይደለም:: አውቆ

ቢያፈርሰው ቀዷም ሆነ ሌላ ነገር የለበትም።

**✷ኢዕቲካፍ ማለት** ጤናማ አዕምሮ ያለዉ ሙስሊም ለዒባዳ ብሎ በመስጊድ ዉከጥ የተወሰነ ጊዜ ማሳለፍ ነው። ኢዕቲካፍ የሚያደርግ ሰው ከጀናባ፤ ከወር አበባና ከወሊድ ደም መፅዳት አለበት፤ በጣም አስፈላጊ ለሆነ ነገር ለምሳሌ ለመብላት ለመፀዳዳት፤ ካልሆነ በስተቀር ከመስጂድ መውጣትም የለበትም። ያለምንም ችግር በመውጣትና የግብረ ስጋ ግንኙነት በማድረግ ኢዕቲካፍ ይበላሻል። ኢዕቲካፍ ሁልጊዜም የሚወደድ ተግባር ሲሆን በረመዷን ዉስጥ ግን በጣም ይወደዳል። በይበልጥ የሚወደደው ደግሞ በረመዳን ወር በመጨረሻኖቹ አስር ቀኖች ዉስጥ ነው። አነስተኛው የኢዕቲካፍ ጊዜ አንድ ሰዓት ነው። ከአንድ ቀን ከነሌሊቱ አለማሳነሱ ይወደዳል። ሴት ልጅ ያለባሏ ፍቃድ ኢዕቲካፍ ማድረግ አትችልም። ኢዕቲካፍ ያደረገ ሰው ዒባዳ ማብዛት አለበት፡፡ ሙባህ /የተፈቀዱ/ነገሮችን መሥራት ባያበዛ ጥሩ ነዉ፡፡ አስፈላጊ ያልሆነ ነገርን ከመፈፀም ሊርቅ ይገባል።፡

# ሐጅና ዑምራ:

ሀጅንም ሆነ ዑምራን **በዕድሜ አንድ ጊዜ መፈፀም ግዴታ ነው::** ግዴታ የሚሆነውም ከዚህ በታች ያሉት ቀድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ ነው:: 1)ሙስሊም መሆን፤ 2)አዕምሮው ጤናማ መሆን፤ 3) ለአቅመ አዳም/ ለአካለ መጠን መድረስ፤ 4) ከባርነት ነፃ መሆን፤ 5)የገንዘብ አቅም መኖር ሲሆን፤ ይህም ማለት ስንቅና መጓጓዣ መኖር ማለት ነው[1]::
ቋባባቱ በኑዋላ ችላ ብሎ ሐጅ ሳያደርግ የሞተ ሰው ከተወው ገንዘብ ሐጅና ዑምራ የሚደከያርግ ገንዘብ ከዉርከ በፊት ይቀነሳል:: ከሃዲ ወይም ዕብድ ሀጅ ቢያደርጉ ተቀባይነት የለዉም:: ህፃንና ባሪያ ሀጅ ቢያደርጉ ግን ትክክል ነው:: ሆኖም የግዴታዉን ሀጅ አይሸፍንላቸዉም:: አቅሙ የሌለዉ ድሃ ተበድሮ ሐጅ ቢያደርግ ተገቢ ባይሆንም ሐጁ ችግር የለበትም:: የራሱን ሐጅ ሳይወጣ ለሌላ ሰው ሐጅ ያደረገ ሰው **ሀጁ ለራሱ ነው የሚሆነው::**
**ኢህራም:** ለሀጅ ኢህራም ማድረግ የፈለገ ሰው መታጠብ፤ መፀዳዳት፤ ላሮቅቄ፤ የተሰፉ ልብሶችን ማውለቅ፤ ንፁህና ነጫጭ የሆኑ ሽርጥና ኩታ መልበሱ ሱና ነው:: ከዚያም ኘ ለበይከ አላሁመ **ዑምረተን**፤ ወይም **ሀጀን**፤ ወይም **ሀጀን ወዑምረተን** ይበል:: ወደ ሀጅ ሠርዓት ከገባ በኋላ በሆነ ችግር ምክንያት ኢህራሜን እሌታ ይሆናል የሚል ስጋት ከገባዉ **የምፈታው ባገድከኝ ቦታ ላይ ነው** በማለት ቀድሞ ሁኔታ ማስቀመጥ ይችላል::
**ሐጅ የሚያደርግ ሰው ከሶስት የሐጅ አሰራር ሠርዓቶች መካካል አንዱ መምረጥ መብቱ ነው::** እነሱም ተመቱዕ[2]፤ኢፍራድ[3] ና ቂራን[4] ይባላሉ:: ከሁሉም የሚመረጠው **በተመቱዕ ሀጅ** ማድረጉ ነው:: ተሙቱዕ ማለት የዑምራን ፀሎት ለመፈፀም በበማሰብ በሐጅ ወራቶች ኢህራም ማድረግና ከሷ ተፈቶ ከስነበተ /ከታጨ/ በኋላ በዚያው አመት ሀጅን ለመፈጀም ኢህራም ማድረግ ነው::
**ኢፍራድ** ማለት ደግሞ በቀጥታ ሀጅ ለማድረግ ኢህራም ማድረግ ነው::
**ቂራን** ማለት ደግሞ ሁለቱንም ለማድረግ ወይም ዑምራን አስቦ ከገባ በኋላ ጠዋፍ ከማድረጉ በፊት ሀጅን በዚያው ዉስጥ ማስገባቱ ነው::
ሐጅ ማድረግ የሚፈልግ ሰው በፈረሱ ላይ ሆኖ[5] **ለበይክላሁመ ለበይክ ላሸሪከ ለከ ለበይክ ኢነልሀምደ መንነዕመተ ለከ ወልሙልኩ ላሸሪከ ለከ**) በማለት ይጀምር:: ይህንንም ማብዛቱ፤ ከሴቶች በስተቀር ድምፅን ከፍ ማድረጉ ይወደዳል::
**በኢህራም ምክንያት የሚከለከሉት** ዘጠኝ ነገሮች የቸው:: 1) ፀጉርን መላጨት 2) ጥፍርን መቁረጥ፤ 3) ለወንድ የተሰፋ ልብስ መልበስ፤ ሽርጥ በማጣቱ ሱሪ ቢለብስ ፤ወይም ነጠላ ጫማ አጥቶ ሙሉ ጫማ ከቁርጭምጭሚት በታች አሧጥሮ ቢለብስ ምንም የጥፋት ማካካሻ የለበትም:: 4) ለወንድ እራሱን መሸፈን፤ 5) ለልብሰም ሆነ ለሰዉነት ሽቶ መጠቀም፤
6) አውሬ ማደን፤ ማለትም የዱር አውሬ ሆኖ ሙብላቱ የተፈቀደዉን ማለት ነው ፤
7) ጋብቻን መፈፀም፤ ይህን ማድረግ ክልክል ቢሆንም ቢፈፅማ ግን ምንም ማካካሻ የለበትም::
8) ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ዉጭ በስሜት መተሻሸት ሲሆን፤ የዚህም ማካካሻው አንዲት ፍየል ወይም ሶስት ቀን መፆም ወይም ስድስት ድሆችዩ ማብላት ነው::
9) የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጀም፤ ከመጀመሪያው መፈታት በፊት ከሆነ ሐጁ ይበላሻል:: ሆኖም ሀጁን ጨርሶ በሚቀጥለው አመት ቀዷ ማውጣት የኖርበታል:: ይህም የሚሆነው ለሙካ ድሆች የሚከፋፈል አንድ ግመል ከማረድ ጋር ነው:: ከመጀመሪያው መፈታት በኋላ ከሆነ ግን ሐጁ አይበላሽም:: አንድ ግመል ግን ማረድ አለበት:: በዑምራ ፆሎት ላይ እያለ የግብረ ስጋ ግንኙነት ቢፈፅም ዑምራው ይበላሻል:: እናም አንዲት ፍየል ማረድ አለበት:: ዑምራንም በሌላ ጊዜ ቀዷ ማውጣት አለበት:: ከግብረ-ስጋ ግንኙነት ዉጭ በሆነ ነገር ሐጅ ወይም ዑምራ አይበላሽም:: ሴት ልጅ በእነዚህ ሁሉ ልክ እንደ ወንድ ናት:: ሆኖም የተሰፋ ልብስ መልበስ ትችላለች:: ፊንትና የአይን እርግብ ወይም ኒቃብ መልበስ ግን አትችልም::
**ማካካሻ** ሁለት አይነት ነው:: 1) **በምርጫ የሚደረግ** ነገር ሲሆን እሱም፡ ፀጉሩን የተላጨ ፤ ሽቶ የተቀባ፡ ጥፍሩን የተቆረጠ፤ ለወንድ ራሱን የሸፈነ ነወሐ የተሰፋ ልብስ የለበሰ ይህን የፈፀመ ሰው

---

[1] ሴት ልጅ ስድስተኛ ቅድመ ሁኔታ ትጨምራለች:: እሱም አብሮ ዘመድ የሚሄድ መኖር ነው:: ዘመድ ማለት ለሁልጊዜም እሷን ማግባት ክልክል የሚሆንበት ሰዉ ማለት ነው:: ያለ ዘመድ ሐጅ ብታደርግ ግን ወንጀለኛ ብትሆንም ሀጇ ይሆናል::
[2] - ዑምራን ጨርሶ በዚያው አመት ሐጅን መፈፀም ነው::
[3]- ሐጅን ብቻ መፈፀም ነው::
[4] - ዑምራን ና ሐጅን በአንደ አመት መፈፀም ነው::
[5]ፈረስ የግድ ነው ማለት አይደለም:: ዘመን አመጣሹ መጓጓዣም፡- መኪና፤ አውሮፕላን፤ መርከብ... ቢሆንም እንደዚያው ነው::

ከዚህ በታች ያሉትን ማካካሻዎች ይተግቃር:: ሶስት ቀን መፆም ወይም ለስንድ ድሃ በስንድ ኪሎ ተኩል ሂሳብ ከድስት ድሆችን ማብላት፤ ወይም ስንዲት ፍየል ማረድ ነው፡፡ በሀጅ ላይ እያለ ስዉሬ ያደነ ሰዉ ከተገደለዉን ስዉሬ ተመሳሳዩን ከቤት እንሰሳ ማረድ ያለበት ሲሆን፡ መሰል ከሌለው ደግሞ ዋጋዉን ይከፍላል፡፡ 2) ተራዉን ጠብቆ መተግበር ያለበት ማካካሻ ሲሆን፤ ይህም የሙተመቴዕና የቃሪን መካካሻ /በግ ፤ፍየል ነው፡፡ የግብር ከጋ ግንኙነት ማካካሻዉ ግመል ሲሆን፤ ይህን ካላገኘ ሶስት ቀን በሐጅ ላይ እያለ፤ ሰባት ቀን ደግሞ ወደ ሀገሩ ሲመለስ የሚፆመው ነው፡፡ ለእርድ የሚደርሰዉ እንሰሳም ሆነ ማብላቱ ለሐረም ድሆች ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

ወደ መካ መግባት፡- ሐጅ የሚያደርግ ሰው መካ ሲገባ፤ ወደ ሌሎች መከዖዎች ሲገባ የሚያነባቸዉን ዚክሮች ያንብብ፡፡

ከዚያም ሙተመቴዕ ከሆነ የዑምራ ጠዋፍ ይጀምር ቃሪንና ሙፍሪድ ከሆነ ደግሞ ጠዋፈልቁዱም/ መካ የመድረስ/ ጠዋፍ ያድርግ፡፡ በዚህ ጠዋፍ ቀኝ እጁን ያውጣና ለሐጀረል-አስወድ ሰላምታ ያቅርብ:: ከቻለም ከሞ ሰለበለዚያም ወደ እሱ ሰመልክቶ ቢስሚላህ ወላሁ ስክበር ብሎ ይጀምር፡፡ ይህንኑ ተግባር በየዙሩ ሁሉ ያድርግ፡፡ ከዚያም ካዕባን በግራው ሰድርጎ ሰባት ዞዜ ይዞር፡፡ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ዞሮች እያለተለተ [1] ይዞርና በቀሩት ደግሞ እንደ ስቀሙ እየሄደ ይጨርሳል፡፡ ሩክነል-የማኒ በሚባለዉ ማዕዘን ባለሬ ቀጥር ሰላምታ ማድረግ ከቻለ ሰላም ይበለው፡፡ በሁለቱ ማለትም በሩክነል-የማኒና በሐጀረል ስስወድ መካከል (ረበና ሳቲና ፊዱንያ ሀሰነተን ወፊል-ሳኪረተ ሀሰነተን ወቂና ስዛብ-ስልናር) ይበል፡፡ በሌላው ቦታ ላይ የፈለገዉን ዱዓ ያድርግ፡፡ ከዚያም ከተቻለው ከኢብራሂም መቆሚያ በኋላ ሱረቱል ካፊሩንና ሱረቱል ኢኽላስን በማንበብ ሁለት ረከዓ ይስገድ፡፡ ከዚያም ከዘምዘም ዉሃ በብዛት ይጠጣ፡፡ ከቻለ ተመልሶ ሀጀረል-ስስወድን ይሰላመት፡፡ ከዚያም በሀጀረል ስስወድና በበሩ መካከል ባለው ሙልተዘም በሚባለዉ ቦታ ላይ የቻለዉን ያህል ዱዓ ያድርግ፡፡ ከዚያም ሶፋ ጋራ ላይ ወጥቶ ስላህ በጀመረበት እጀምራለሁ ካለ በኋላ

﴿إِنَّ ٱلصَّفَا وَٱلۡمَرۡوَةَ مِن شَعَآئِرِ ٱللَّهِۖ فَمَنۡ حَجَّ ٱلۡبَيۡتَ أَوِ ٱعۡتَمَرَ فَلَا جُنَاحَ عَلَيۡهِ أَن يَطَّوَّفَ بِهِمَاۚ وَمَن تَطَوَّعَ خَيۡرٗا فَإِنَّ ٱللَّهَ شَاكِرٌ عَلِيمٌ﴾

የሚለዉን የቁርስን ስንቀፅ ስንብቦ ስላሁ ስክበር ላኢላሀ ኢለሏህ በማለት ወደ ከዕባ ዞሮ እጆቹን ስንስቶ ዱዓ ያድርግ፡፡ ከዚያም ወደ ቀጠላማው ስረንጓዴ ምልክት ይሂድና እስከመለሱ ምልክት ድረስ በፍጥነት ይራመድ፡፡ ከዚያም መርዋ እስከሚደርስ ድረስ በቀስታ ሂዶ በሶፋ ላይ እንዳደረገው በመርዋም ላይ ይስራ፡፡ ከዚያም ወርዶ በመጀመሪያው ዙር ላይ እንደሰራው ይስራ፡፡ልክ እንደዚሁ እያደረገ ሰባት ዙሩያ ይሙላ፡፡ ከሶፋ እስከመርዋ ስንድ ዙር ሲሆን ከመርዋ እስከ ሶፋ ደግሞ ሌላ ዙር ነው፡፡ ከዚያም ፀጉሩን ያሳጥር ወይም ይላጭ:: መላጨቱ ግን ይመረጣል፡፡ በሙተመቴዕ ዑምራ ላይ ብቻ ሲቀር። ምክኒያቱም ከኋላው ሐጅ ከለሚያደርግ ነው፡፡ ቃሪንና ሐጅን ብቻ የሚያደርግ ሰው የዒድ ቀን ጀምረተል-ዐቀበህን እስከሚወረዉር ድረስ ከኢህራሙ ስይፈታም፡፡ ሴት ልጅ በጠዋፍም ሆነ በሰዕይ ዞዜ ስታረተርትም እንጂ በሌላው ሁሉ ልክ እንደ ወንድ የት፡፡

የሐጅ ከርስት፡- ከዚያው መካ ውስጥ እና ከኢህራም የተፈታ ከሆነ የዙልሒጃህ ስምንተኛው ቀን ሲሆን ካለበት ቦታ (ከቤተ) ኢህራም ሰድርጎ የዘጠነኛዉን ቀን ሌሊት በሚና ለማደር ስስቦ ወደ ሚና ጉዞዉን ይጀምር፡፡

የዘጠነኛው ቀን ፀሐይ ከተወጣ ረፋዱ ላይ ወደ ዐረፋ ጉዞዉን ይቀጥል፡፡ ፀሐይ ከግማሽ ሰማይ ወደ ፀሐይ መግቢያ ከታዘነብል ዙህርና ዐስርን በስንድ ወቀት ስንድ ላይ ሰብስቦና ስሳጥሮ ይስገድ፡፡ የዐረፋ ምድር የዑረነህ ወንዝ ሲቀር ሁሉም መቆሚያ ነው፡፡ (ላኢላሀ ኢለሏህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር) የሚለዉን ዚክርም ያብዛ፤ ዱዓ ያብዛ:: ተውበት ያድርግ፤ ወደ ስላህ ተከፋን ያጠንክር፡፡ ፀሐይ ከተገባ በተዕግስተና በእርጋታ ዚክር እያደረገ፤ ለበይክላሁም ለበይክ እያለ ሙዝደሊፋ ይመለስ፡፡ ሙዝደሊፋም ሲደርስ ዒሻና መግሪብን በስንድ ላይና ስሳጥሮ ይስገድ፡፡ ከዚያም እዚያዉ ስድሮ የሱብሂን ሶላት በስወሉ/ በወቀቱ መጀመሪያ ላይ/ ሰግዶ ዱዓ እያደረገ እዚያው ቆይቶ በጣም ሲነጋ ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት በሙሐሲር ሸለቆ /ቦታ/ሲደርስ የስቀሙን ያህል ፈጠን ፈጠን እያለ ሚና እስከሚደርስ ድረስ ይሂድና ጀምረተል ዐቀበህ ጠጠር ዉርወራ ይጀምራል፡፡ ሰባት ትናንሽ ጠጠሮችንም ይወርዉር፡፡ በየጠጠሩም ስላሁ ስክበር እያለ ሲወረዉር እጆቹን ያንሳ፡፡ ጠጠሮች ቋሚዉን ባይመቱም በገንዳው ዉስጥ መግባት ይኖርባቸዋል፡፡ ጠጠር መወርወር ሲጀምር ለበይክ.... የሚለዉን ያቁርጥ፡፡ ከዚያም የመስዋእት እንስሳውን ይረድ፡፡ ከዚያም የራሱን ፀጉር ይላጭ ወይም ያሳጥር:: መላጨቱ ይመረጣል፡፡ ጠጠር ከወረወረ በኋላ ከሴት በስተቀር ሁሉ ነገር ይፈቀድለታል፡፡ ይህም

[1] እርምጃን በማቀራረብ መፍጠን ማለት ነው፡፡

# ልዩ ልዩ ጠቃሚ ትምህርቶች

✸ ጥቃቅን ወንጀሎች የሚታበስባቸው ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል፡ እዉነተኛ ተውበህ፤ ምህረትን መለመን፤ መልካም ነገሮችን መስራት፤ በልዩ ልዩ ችግሮች መፈተን፤ ሰደቃን መስጠት፤ የሌላ ሰው ዱዓ፤ ከዚህ ሁሉ በኋላ የቀረ ቢኖር በቀብር ዉስጥ ወይም የቂያማ ዕለት ወይም በገሀነም ዉስጥ ከእሱ ከወንጀሉ እስከሚፀዳ ድረስ ይቀጣበታል፡፡ ከዚያም በተውሒድ ላይ ከሞተ ጀነት ይገባል፡፡ በሽርክ ወይም በክህደት ላይ ወይም በንፍቅና ላይ ከሞተ ግን በገሀነም ዉስጥ ለዘላለም ይማቅቃል፡፡

✸ወንጀሎች/ሀጢዓቶች/ በሰው ልጅ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደርጋሉ፡

✸ወንጀሎች በቀልብ ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ብዙ ነው፡፡

ከእነዚህ መካከል፡- ወንጀል ልብን ያጨልማል፡፡ ብቸኝነትን ያወርሣል፤ ዉርደትን ያስከትላል፡፡ የልብ በሽታን ያመጣል፤ ከአላህ (ﷻ) እዝነት ይጋርዳል፡፡

✸ወንጀሎች ዲን ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ልክ እንደ ቀልብ ሁሉ ሲሆን በተጨማሪም ከኢባዳ ያሣንፋል፣ የነቢዩን፤ የመላኢካንና የአማኞችን ዱዓ ይከለክላል፡፡

✸ወንጀሎች /ሀጢዓቶች / በሪዝቅ ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ -- ሪዝቅን ይከለክላሉ ፣ ፀጋን ያስቀማሉ፣ የገንዘብን ረድኤት ያጠፋሉ፡፡

✸በግል ህይወት ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ፡- እድሜን በረካ ያሳጣሉ፣ የኑሮ ጥበትን ያመጣሉ፡፡ ቀላል ነገሮችን አስቸጋሪ ያደርጋሉ፡፡ (ነገሮችን ያወሳስባሉ)

✸በስራ ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ፡- በአላህ ዘንድ የሥራ ተቀባይነትን ያሣጣሉ፡፡

✸በማህበረሰብ ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ የሰላምን ፀጋ ያጠፋሉ፣ ለኑሮ ዉድነት ምክኒያት ይሆናሉ፣ በዳይ መሪዎችንና ጠላቶችን በሰዉ ልጅ ላይ ይጥላሉ፣ የዝናብን ጠብታ ያስከለክላሉ፡፡ ሌሎችንም ችግሮች ያደርሳሉ፡፡

✸ሀሣብና ጭንቀት፡- ለልብ እርካታና ደስታን ማስገኘት፣ የልብ ጭንቀትን ማስወገድ የያንዳንዱ ሰው ጥያቄ ነው ፡፡ በዚሁ ነዉና መልካም ህይወት የሚገኘው፡ ይህ እንዲሆን የሚያስችሉ ብዙ ሀይማኖታዊ ፤ ተለምዶአዊና ተግባራዊ ምክኒያቶች አሉ፡፡ እነዚህ ተግባሮች ደግሞ በአንድ ላይ የሚሰባሰቡት ትክክለኛ ለሆነ አማኝ ብቻ ነው፡፡

ከእነዚህም መካከል፡- 1)በአላህ (ﷻ)ማመን፤ 2) መልካምን መስራትና መጥፎ ነገሮችን መራቅ፤ 3) ለፍጡራን በንግግርም ሆነ በተግባር የተለያዩ መልካም ነገሮችን መስራት፤ 4) በስራ መጣበብ፡ ጠቃሚና ሀይማኖታዊም ሆነ ዐለማዊ ትምህርቶችን በመስጠት መጠመድ፡ 5) በዕለት ከዕለት ተግባር እንጂ ባለፈውም ሆነ ወደፊት በሚሆነዉ ነገር እራስን አለማስጨነቅ፡፡ 6) በብዛት አላህን(ﷻ) ማውሳት፡፡ 7)በስውርም ሆነ በይፋ አላህ (ﷻ) የዋለልንን ፀጋዎች ማስተዋል 8) በዱኒያ ጉዳይ ከእኛ በታች ወዳሉት አካላት መመልከት በዲን ጉዳይ ካልሆነ ከእኛ በላይ ወደሆኑት ብዙም አለማሰብ፤ 9) ጭንቀትን ሊያመጡ የሚችሉት ነገሮችን ለማስወገድና ደስታን ለማምጣት መጣር፤ 10) ወደ አላህ (ﷻ) ለመጠጋት ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጭንቀትን ለማስወገድ ይጠቀሙበት በነበሩት ዱዓዎች መጠቀም፡፡

## ጠቃሚ ትምህርት

✸ኢብራሂም-ልኸዋስ (የልብ መድሀኒት አምስት ናቸው ይላሉ፡፡ እነሱም፡-ቁርአንን በጥሞና ማንበብ፤ ሆድን ባዶ ማድረግ፤ ለሊትን ቁሞ ማሳለፍ፤ በስሁር ሰዐት/ንጋት ላይ በመተናነስ ወደ አላህ መቃረብና ከሷሊሆች ጋር መቀማመጥ ናቸው፡፡

✸ጋብቻ- ጋብቻ ስሜት ለማያሸንፈውና ዝሙት ላይ እወድቃለሁ ብሎ ለማይፈራ ሰው ሁሉ ሱና ነው፡፡ ፍፁም ስሜት ለሌለው ሰው ደግሞ የተፈቀደ ነዉ፡፡ ዝሙት ላይ መውደቅን ለሚፈራ ሰው ግን ማግባት ሀጅ ከማድረግም ቅድሚያ የሚሰጠው ኢስላማዊ ግዴታ ነው ፡፡ አጅነቢያን/ ባዕድ ሴትን/ አትኩሮ መመልከት በኢስላም የተከለከለ ነው፡፡ በስሜት ከሆነ አሮጊትንና ወጣት ወንድ ልጅንም እንኳን መመልከት ክልክል ነው፡፡

✸ የሴት ልጅ ጋብቻ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች መሰረት ይሟላል፡፡ እነሱም፡- 1) ሁለቱን ተጋቢዎች ለይቶ ማስታወቅ ሲሆን ብዙ ሴት ልጆች ያሉት ሰው ‘ አንዷን ልጄን ድሬሃለሁ’ ቢል ጋብቻው አይሆንም፡፡
2) ለአቅመ አዳም የደረሰ፤ ጋብቻዉን የተቀበለ አዕምሮዉ ጤናማ የሆነ ወንድና ለአቅመ ሀዋ የደረሰች ኒካሁን የወደደች ጤናማ አዕምሮ ያላት ሴት
3) ዘመድ/ በሴቷ ጉዳይ ሀላፊነት ያለዉ ሰዉ/ መኖር አለበት፤ ሴት ልጅ እራሷን ልትድር አትችልም፡፡ የሚገባትን ሰው እንዳታገባ ካልከለከሏት በስተቀር ከዘመዷ/ አስተዳዳሪዋ/ ሌላ የሆነ ሰው ሊድራት አይችልም፡፡ ሴትን ልጅ ለመዳር ስልጣን ያለው በመጀመሪያ ደረጃ አባት ሲሆን ፤ ከዚያም አያቱ እያለ በቅደም ተከተል ወደላይ ይቀጥላል። ከዚያም ልጇ ከዚያም ወደ ታች ቢወርድም የልጅ ልጇ ነው፡፡ ከዚያም በአባትና በእናት ወንድሟ የሆነው፣ ከዚያም በአባት ብቻ ወንድሟ የሆነው፤ ከዚያም የወንድም ልጅ ከዚያም እንዲሁ .. ነዉ፡፡ 4) ሁለት ታማኝና ፍትሃዊ ለአቅመ አዳም የደረሱና በአዕምሮ ጤናማ የሆኑ ወንዶች ምስክርነት ያስፈልጋል፡፡
5) ሁለቱም በመሀከላቸው ጋብቻን ከሚከለክሉ ነገሮች ነፃ መሆን አለባቸው፡፡ ይህዉም ጡት መጥባት፤ ዝምድናና፣ የጋብቻ ትስስርን ይመስል ነው፡፡
ጋብቻን የሚከለክሉ ነገሮች ሁለት ናቸው፡፡
✸አንደኛው ለዝንተ አለም ጋብቻን የሚያስከለክል ሲሆን፤ ይህም ብዙ ክፍል አለው፡፡ 1) የስጋ ዝምድና ነው፡፡ በዚህም የተከለከሉት ሴቶች -- እናት ወደ ላይ ብትርቅም አያት...፤ ሴት ልጅና ወደታች ብትርቅም የልጅ ልጆቿ ፤ እህት የተባሉ ሁሉ፤ የእህት ልጅና የልጆቿ ልጆች፤ የወንድም ልጅና ወደ ታች ቢርቁም የልጅ ልጆቿ፤ የአባትና የእናት እህቶች የቱን ያህል ቢርቁም፤ 2) በማጥባት ምክኒያት የሚከለከል ጋብቻ ሲሆን፡-እሱም በጋብቻም ጭምር ሳይቀር ልክ እንደ ዝምድናው ነው፡፡ 3) በጋብቻ ምክኒያት የሚከለከሉ ሲሆኑ እነሱም የሚስቱ እናትና ቢርቁም አያቶቿ፤ የሁለቱ የዝምድና ስንሰለቶች የሆኑት ሰዎች ሚስቶችና፣ እንዲሁም የሚስት ልጆችና ቢርቁም የልጅ ልጆቿ ናቸው፡፡
ሁለተኛው ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ የሚከለከል ሲሆን እነሱም ለሁለት ይከፈላሉ፡፡ 1)በተናጠል እየተፈቀደ በአንድ ላይ ሲሆኑ የሚከለከል ሲሆን እሱም ሁለት እህትማማቾችን ወይም ከአክስቷ ጋር በአንድ ጊዜ ማግባትን ይመስል ነው፡፡ 2)ሊወገድ በሚችል ምክኒያት የሚከለከል ነው፡፡ ይኸውም የሌላ ሰው ሚስትን ይመስል ነው፡፡
✸<u>ጠቃሚ ትምህርት</u> ወላፀች ወንድን ልጅ የማይፈልጋትን ሴት እንዲያገባ ማስገደድ አይችሉም:: ልጅም በዚህ እነሱን ባለመታዘዙ አመፀኛ ነዉ ሊባል አይቸልም።
✸ ፍች፡- ሴትን ልጅ በወር አበባና በወሊድ ደም ላይ እያለች ፤ወይም ግንኙነት ባደረገበት ንፅህና ላይ እያለች መፍታት ክልክል ነው፡፡ ከፈታት ግን ፍቺዉ ፍች ይሆናል፡፡ ያለምንም ምክኒያት ፍች የተጠላ ነዉ፡፡ በቂ ምክኒያት ካለው ግን ይፈቀዳል፡፡ በጋብቻው ምክኒያት ለተጎዱ አካሎች ደግሞ ፍቺ ሱና ነው፡፡ በፍቺ ጉዳይ ላይ አባትና እናትን መታዘዝ ግዴታ አይደለም፡፡ ሚስቱን መፍታት የፈለገ ሰው በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ መፍታት የለበትም /ክልክል ነው፡፡ በሚፈታበት ጊዜ ምንም አይነት የግብረስጋ ግንኙነት ባልተፈፀመበት ንፅህና ላይ ያለችበት ወቅት መሆን ይኖርበታል፡፡ አንድን ፍች ከፈታ በኋላ ሌላ ሳይጨምርባት ዒዳዋ እስከሚያበቃ ድረስ መጠበቅ አለበት፡፡ አስመላሽ እድል ያለው ፍች የተፈታች ሴት ዒዳዋ ሳያበቃ ከቤቷ በራሷ ፍቃድ መውጣትም ሆነ ባሏ በግድ ሊያስወጣት ክልክል ነው፡፡ ፍች ፍች የሚሆነው በምላስ አውጥቶ በመናገር እንጂ በሐሳብ ስላሰቡ ብቻ አይደለም፡፡
✸ መሀላዎች በመሀላ ላይ መቀጫን ለማስገደድ መሟላት ያለባቸው አራት ቅድመ ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነሱም፡- 1) መሀላን አስቦ ማድረግ ነው፡፡ መሀላን ሳያስብ (በልቡ ሣያስር) በምላሱ ብቻ የመሀላዉን ቃል ቢናገረው መሀላ አይሆንም፡፡ ይህም ምሳሌው

በንግግራቸው መካከል ላይ ጣልቃ በማስገባት ሣያስቡትና ለምዶባቸዉ ላ ወላህ፣ በላ ወላህ እንደሚሉት አይነት ነው፡፡ ይህም ወድቅ መሀላ ይባላል፡፡
2) መሀላው ወደፊት ሊሆን በሚችል ነገር ላይ መሆን አለበት፡፡ ባለፈ ነገር ላይ ሳያውቅ ወይም እውነት ላይ ነኝ ብሎ አስቦ ወይም አውቆ በሀሰት ቢምል ግን መሀላ አይሆንም (የገሙስ መሀላ የሚባለዉና ከታላላቅ ወንጀሎች አንዱ የሆነው ይህ ነው፡፡) ወይም ወደፊት በሚሆን ነገር ላይ ራሱን እውነተኛ አድርጎ የማለና በኋላ በተቃራኒው መሆኑ የተገለፀት ነው፡፡
3) መሀላዉን የፈፀመው ሰው እራሱ በፈቃዱ ወዶ እንጂ ተገዶ አለመሆኑ፣
4) መሀላዉን ካፈረሰ ለምሳሌ አልሰራም ያለዉን ከሰራ ወይም እሰራለሁ ያለዉን የተወ እንደሆነ ነው፡፡ ሲምል ነገሩን በሌላ ነገር ያያያዘ ሰው መቀጫ/ማካከሻ/ የለበትም፡፡ ይህም የሚሆነው ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡፡ እነሱም፡-
1) ጉዳዩን ማያያዙን ወዲያዉኑ ከመሃላው በኋላ ከሆነና
2) ማያያዙን አስቦበት ከሆነ፣ ምሳሌው ወሏሂ ...ኢንሻ አሏህ ማለትን ይመስል ነው፡፡ በአንድ ነገር ላይ ምሎ እያለ ጥቅሙ ግን ተቃራኒው ላይ መሆኑን ያየ/የተገነዘበ/ ሰው ማድረግ ያለበት/ ሱናው/ ማካካሻዉን ፈፅሞ የተሻለዉን ነገር መሥራት ነው፡፡
የመሀላ ማካከሻ - አስር ድሆችን ማብላት ሲሆን ለያንዳንዱ ድሃ ግማሽ ቁና (ኒስፍ ሷዕ) አንድ ኪሎ ከሩብ ስንዴ መስጠት ነው፡፡ ወይም አስሩንም ማልበስ ነዉ ፣ወይም አንዲት ባሪያን ነፃ ማውጣት ነው፡፡ ይህን ማድረግ ያልቻለ ሰው ሶስት ቀን በተከታታይ መፆም አለበት፡፡ ማብላት ወይም ማልበስ እየቻለ ፆም የፆመ ሰው እዳው አይለቀዉም /ከተጠያቂነት ነፃ አይሆንም/፡፡ ማካካሻዉን መሀላዉን ካፈረሰ በኋላ ወይም ከማፍረሱ በፊት ማድረግ ይችላል፡፡ በአንድ ነገር ላይ ብዙ ጊዜ የማለ ሰው አንድ ማካካሻ ብቻ ማድረጉ ለሁሉም ይበቃለታል፡፡ የማለባቸው ጉዳዩች ከበዙና በዓይነት የተለያዩ ከሆኑ ግን ማካካሻዉም ለያንዳንዱ መሆን አለበት፡፡
✸ **ስለት፡-** የስለት አይነቶች አሉት፡- እነሱም፡- 1) ገደብ ያልተደረገበት ስለት ሲሆን ምሳሌው ከዳንኩኝ ለአላህ ስለት አለብኝ ብሎ የስለቱን አይነት ሳይወስን ከዳነ የመሀላ ማካካሻ መክፈል አለበት፡፡ 2) የቁጣና የክርክር ጊዜ የሚገባበት ስለት ሲሆን እሱም ስለትን ከሆነ ቅድመ ሁኔታ ጋር በማያያዝ አንድን ነገር ላለመስራት ወይም ለመሰራት በማሰብ ለምሳሌ ' ካናገርኩህ አንድ አመት እፆማለሁኝ ማለትን ይመስል ነው፡፡ ይህን ቃል ያለ ሰው ያለዉን በማክበርና አፍርሶ ማካካሻዉን በመክፈል መካከል ይማረጣል፡፡ 3) የተፈቀደ ስለት ሲሆን ምሳሌ ለአላህ (ﷻ) ስል ልብሴን እለብሳለሁ ማለትን ይመስል ነው፡፡ ይህንን ያለ ሰው ልብሱን በመልበስና ወይም መካካሻዉን በማውጣት መካከል በእኩልነት ይማረጣል፡፡ 4) የተጠላ ስለት ነው፡፡ ምሳሌም ለአላህ (ﷻ) ስል ሚስቴን መፍታት አለብኝ ብሎ መሳልን ይመስል ነው፡፡ ይህንንም ያለ ሰው ለሱ ሱናው ማካካሻዉን መክፈልና አለመተግበሩ ሲሆን ቢተገብረው ግን ምንም ማካካሻ መክፈል የለበትም፡፡ 5) የወንጀል ስለት ነው፡፡ ለምሳሌ ለአላህ (ﷻ) ስል መስረቅ አለብኝ ማለትን ይመስል ነው፡፡ ይህንንም ላለ ሰው ስለቱን መሙላት የተከለከለ ሲሆን ቢተገብረው ግን ወንጀለኛ ቢሆንም ማካካሻ የለበትም፡፡ 6) አላህን (ﷻ) ለመገዛት/ለመታዘዝ/ የሚደረግ ስለት ነው፡፡ ለምሳሌ ለአላህ (ﷻ) መስገድ አለብኝ ብሎ መሳልን ይመስል ነው፡፡ይህን አባባል ከሆነ ነገር ጋር ካያያዘው ለምሳሌ ከዳንኩኝ ለአላህ (ﷻ) መስገድ አለብኝ..ብሎ ያሰበው ከተሳካለት ስለቱን መሙላቱ ግድ ይሆናል፡፡ ከምንም ጋር ካላያያዘው ግን ለምሳሌ ለአላህ (ﷻ) መስገድ አለብኝ ካለ ወዲያዉኑ መሙላቱ ግዴታ ይሆናል፡፡
✸ጡት ማጥባት፡- በዝምድና የሚከለከሉ ነገሮች ሁሉ ሶስት ነገሮች ከተሟሉ በማጥባት ምክኒያትም ይከለከላሉ፡፡ እነሱም፡- 1) ጡት መጥባቱ በመውለዱ ምክኒያት የመጣ መሆን፣ 2) በወለደች እስከ ሁለት አመት ዉስጥ ድረስ ባለው

እድሜ መሆን፤ 3) መጥባቱ አምስትና ከዚያም በላይ መሆኑ እርግጠኛ ሲሆን ነው፡፡ በማጥባት የተፈለገው ጡቱን ይዞ እስከሚተወው ድረስ ጠባ ማለት እንጂ እስከሚጠግብ መጥባት ሸርጥ/መስፈርት/አይደለም፡፡ በማጥባት ምክንያት ቀለብና ውርስ አይረጋገጥም፡፡

**✷ንዛዜ፡፡** ምስክር የሌለው እዳ ያለበት ሰው ከሞተ በኋላ መክፈሉ ግዴታ ነው፡፡ ዕዳ ያለበት ሁሉ ዕዳዉ ለባለቤቱ እንዲሰጥ መናዘዝ አለበት፡፡ ብዙ ንብረት ጥሎ ለሞተ ሰው ደግሞ ንዛዜ ሱና ስትሆን የሚመረጠዉም አንድ አምስተኛዉን ወራሽ ላልሆነ ቅርብ ደሃ ዘመዱ መናዘዝ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ለድሃ፣ ለዓሊም፣ ለጥሩ/ሷሊህ/ ሰው ቢናዘዝ መልካም ነው፡፡ ድሃ ሆኖ ወራሽ ያለው ሰው መናዘዝ ይጠላል፡፡ ወራሾቹ ሀብታም ከሆኑ ብቻ ይፈቀድለታል፡፡ ዘመድ ላልሆነ፣ ዉርስ ለማይገባዉ ለባዳ ሰዉ ከሙሉ ንብረቱ ከሲሶ በላይ መናዘዝ ክልክል ነው፡፡ ዉርስ ለሚገባው ሰው ግን መናዘዝ ትንሽም ቢሆን ክልክል ነው፡፡ ወራሾች ተናዛዡ ሰዉ ከሞተ በኋላ ተስማምተዉ ቢያፀድቁት እንጂ፡፡ ንዛዜ ተናዛዡ ሰዉ ተመልሻለሁ፣ ትቸዋለሁ፤ ቀይሬዋለሁና መሰል ቃል በመናገሩ ይበላሻል፡፡ በንዛዜው መግቢያ ላይ (ቢስሚላሂረህማኒ ረሂም. ይህ የእገሌ ኑዛዜ ነው. ከአላህ ሌላ በትክክል የሚመለክ ማንም የለም:: አጋር የለዉም:: ሙሐመድ የአላህ አገልጋይና መልዕክተኛ ናቸው፡፡ ጀነት ሀቅ ነዉ፡፡ እሳትም ሀቅ ነዉ:: ቂያማ ጥርጥር የለባትም:: መምጣቷ እርግጥ ነዉ:: አላህ (ﷻ) በየመቃብሩ ያለን ሁሉ አስነሺ ነው፡ ወራሾቼን አማኝ እንዲሆኑ፣ አላህን (ﷻ) እንዲፈሩና በመሐከላቸው መልካም ህይወትን እንዲኖሩ፤ አላህን (ﷻ)ና ነቢዩን (ﷺ). እንዲታዘዙ አደራዬ የፀና ነው፡፡ በአጠቃላይ ነቢዩ ኢብራሂም ለልጆቻቸው የዕቁብም (ልጆቼ ሆይ ! አላህ ለናንተ ሀይማኖትን መረጠ፡፡ ስለዚህ እናንተ ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጂ አትሙቱ (አላቸው)::) በማለት አላህ እንዳለዉ እሣቸዉ አደራ ያሉትን እኔም አደራ እላለሁ) የሚለዉን መፃፍ ይወደዳል፡

✷ በነቢዩ ሙሐመድ ላይ ሶለዋት ሲያወርዱ ሶላትና ሰላምታን በአንድ ላይ አጣምሮ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአንደኛው ላይ ማሳጠር/ በሰላም አሊያም በሶለዋት ብቻ/ አይፈቀድም፡፡ ከነቢያት በስተቀር ሌሎች ሰዎች ሶለዋት አይደረግላቸዉም፡፡ ለምሳሌ አቡበክር ሶላለሁ. አለይሂወሰለም (ዐ.ሰ). አይባልም፡፡ ይህን ማለት ይጠላል፡፡ ከነቢዩ በማስከተል ግን ለምሳሌ አላሁመ ሶሊ ዐላ ሙሐመድ ወዐላ አሊ ሙሐመድ ወአስሃቢሂ ወአዝዋጂህ ወዝርየቲሂ..ማለት ለሁሉም ይፈቀዳል፡፡ ለሰሃቦች ለተከታዩቻቸውና ከኋላቸዉም ለመጡ ዐሊሞችና ሌሎችም ደጋግ ሰዎች:- አላህ (ﷻ) ይውደድላቸው፡፡ አላህ (ﷻ) ይዘንላቸው ማለት ይወደዳል፡፡ እናም አቡ ሐኒፋ፤ ማሊክ፤ሻፊዒና አህመድ.. ‘ረሂመሁሙላህ’ አላህ (ﷻ) ይዘንላቸው ይባላል፡፡

**✷ እርድ፡፡** ሊበሉ የተፈቀዱ፤ በየብስ የሚኖሩና ለማግኘት የሚቻሉ እንስሳትን ሁሉ ሊበሉ ዘንድ ማረድ የግድ ነው፡፡ መስፈርቶቹ ደግሞ:-

እንስሳዉ፤ 1) ሊበላ የተፈቀደ መሆን አለበት፤ 2) ለመያዝም ሆነ ለማረድ የሚቻል መሆን ፤ 3) የየብስ /እንሰሳ መሆን፤

ለማረድ አራት መስፈርቶች አሉት፡፡ 1) አራጁ አዕምሮ ጤናማ መሆን፤
2) ማረጃው ከጥፍርና ከጥርስ ሌላ መሆን፣ ምክኒያቱም በሁለቱም ማረድ አይፈቀድምና ነው፡፡ 3) ጉሮሮን (በልዑም)፣ የምግብ ቧንቧንና ሁለቱን የደም ስሮች ወይም አንዱን መቁረጥ፤ 4) ለማረድ እጁን ሲያንቀሳቅስ ቢስሚላህ ማለት ሲሆን በአረብኛም ባይሆንም ይቻላል፡፡ ከቢስሚላህ ጋር አላሁ አክበር የሚለዉን ቢጨምር ሱና ነው፡፡ አውቆ ሳይሆን ቢስሚላህን ረስቶ ከተወ ችግር የለዉም፡፡

✷ ስለ ዱር አውሬ አደና- ለማዳ ያልሆነንና መመገቡ ግን የሚፈቀድን እንስሳ ማደን የተፈቀደ ነው፡፡ የሚታደነዉ አዉሬ 1) ሊበላ ሀላል /የተፈቀደ/ መሆን 2)የዱር አዉሬ መሆን 3) ለመያዝ አስቸጋሪ የሆነ ለመበላት የሚታደንና ለመጫወቻ ያልታሰበ መሆን አለበት:: አደኑ ሰዎችን በመኖሪያቸውና በአዝርዕቶቻቸው ላይ

የሚጎዳቸው ከሆነ ማደኑ ክልክል ነው:: ለአደኑ አራት ነገሮች መሟላት አለባቸዉ

1) አዳኙ እራሱ በሀላፊነት እርዱን መፈፀም የሚችል መሆን፤

2) ማደኛዋ መሳሪያ ለማረጃነት የተፈቀደች ከሆነ ለምሳሌ ስለት የሆነች ጦርና አንካሴ መሰል መሆን፤ የሚታደነዉ በእንሰሳ ማለትም በአሞራ በዉሻና በመሣሠሉት ከሆነ እንሰሳዉ ለዚሁ ጉዳይ ልዩ ስልጠና የተሰጠውና የተማረ መሆን፤

3) ተግባሩን/ አደኑን ሲፈፀም/ አስቦበት መሆን፤ይህም ማለት ገና ጦሩን ሲወረዉር አውሬ ለማደን መሆን፤ ሳያስበው ቢያድንለት ግን ለመብላት የተፈቀደ አይደለም፡፡

4) ማደኛዋን ለመወርወር ገና እጁን ሲያንቀሳቅስ ቢስሚላህ ማለት:: እዚህ ላይ ቢስሚላህን ረስቶ እንኳን ከተወ ችግር አለዉ፡፡ መመገቡ ክልክል ነው፡፡

✷ **ምግብ፡-** በሚበላና በሚጠጣ ነገር ዙሪያ መሰረቱ የሁሉም መፈቀድ ነው፡፡ እናም ሶስት ነገሮች ከተሟሉ የትኛዉንም የምግብ አይነት መመገብ ይፈቀዳል፡፡ እነሱም፡- 1) ምግቡ ንፁህ/ጣህር/ መሆን፤ 2) ጉዳት የማያስከትል መሆን፤ 3) አፀያፊ አለመሆን ናቸው፡፡ ነጅስ የሆኑ ነገሮችና ደምና በክት የመሣሠሉትን መብላት ሀራም ነዉ፡፡ ጉዳት የሚያመጡ ነገሮች ለምሣሌ መርዝ፤ ቆሻሻ ነገሮች - የአህያ ፋንድያ፤ ሽንት፤ ቅማል ቁንጫ/ትኋን/ና የመሣሠሉት ሁሉ ክልክል ናቸው፡፡ ከየብስ እንሰሳትም የቤት አህያ፤ በቀንጣጤው /በዉሻ ክራንቻው/ የሚያድን አውሬ ሁሉ ክልክል ነው፡፡ ይኸው  አንበሳ፤ ነብር፤ ተኩላ፤ ደቦል/ደልጌ/ ዉሻ፤ ከርከሮ/አሳማ/፤ ዝንጀሮ፤ ድመት፤ የሜዳዳሞት ቢሆን/አነር ድመትም/ ቀበሮና ሲንጃብ  ይመስል ነው፡፡ ጅብ ግን የተፈቀደ ነው፡፡ ከበራሪዎች በጥፍሩ የሚያድን ሁሉ ክልክል ነው፡፡ ለምሳሌ ጁቢራ አሞራ፤ ጭልፊት አሞራ፤ጥንብ አንሳ አሞራ፤ሻሂን፤ገዴ፤ጩልሌ፤ ጉጉት፤ የመሳሰሉ ሁሉ ክልክል ናቸው፡፡ በክትን/ጥንብን የሚመገቡ አሞራዎች ሁሉ ለምሳሌ ጆፌ አሞራ፤እርኩም፤ ለቅለቅ፤ክልክል ናቸው፡፡ የከተማ ሰዎች ዐረቦችም ሆኑ ሌሎች ያንቋሸሿቸው ነገሮች ለምሳሌ፡-የሌሊት ወፍ፤ አይጥ፤ ተርብ-፤ ንብ፤ ዝንብ፤ ክረምት አግባ፤ ጃርት፤ እባብን ይመስል... ከነፍሳትም ለምሳሌ -- ትላትል፤ አይጥ፤ እንቃቅለዎች ኢስላም እንዲገደሉ ያዘዘባቸው ለምሳሌ ጊንጥን ይመስል ወይም እንዳይገደሉ የከለከላቸውን ለምሳሌ ጉንዳን፤ ከሚበላና ከማይበላ መካከል የተወለደ ለምሳሌ በጅብና በተኩላ መካከል የተወለደን ይመስል ነው፡፡ ሁለቱም የሚበሉ ከሆኑ ነገሮች የተዳቀለ ለምሳሌ በዱር አህያና በፈረስ መካከል የተወለደ ክልክል አይደለም፡፡ ዐረቦች የማያውቁትና በኢስላምም ያልተወሳው ሁሉ ከዐረብ ሀገር እንሰሳዎች ወደሚቀርበው ይጠጋጋል:: ከተከለከለው ጋር ከተመሳሰለ ክልክል ነው፡፡ ከተፈቀደ ጋርም ከተቀራረበ ይፈቀዳል፡፡ ከሁለቱም ጋር ከተመሳሰለ ወደተከለከለው እናስጠጋዋለን፡፡ ከእነዚህ ሌላ ያለው ሁሉ የተፈቀደ ነው፡፡ ለምሳሌ የቀንድ እንሰሳዎችንና ግመሎችን ፈረሶችን ይመስል ነው፡፡ የዱር አውሬ ቀጭኔ፤ ጢንቸል፤ ወበር፤ የርቡዕ፤ ወከሎ፤ ፊቆ፤

**በራሪዎች**፡- ለምሳሌ ሰጎን፤ ዶሮ፤- ዋነስ/ እርግብ፤በዉሃ ላይ የሚኖሩ በራሪዎች በሙሉ፤ ኳጉንቸር፤ እባብና አርጃኖ ሲቀር የባህር እንሰሳዎች ይፈቀዳሉ፡ እንደዚሁም በነጃሳ ነገር የተጠጡ የአትክልት ፍሬዎች ሁሉ የነጃሳው ጠአምም ሆነ ሽታው በይፋ ካልወጣ በስተቀር መመገቡ ይፈቀዳል፡፡ ከታየ ግን ክልክል ነው፡፡ ከሰል፤ አፈር፤ ጭቃ፤ የተከለከለ ነዉ:: ነጭም ሆነ ቀይ ሁለቱም የሽንኩርት አይነት ከመቀቀሉ በፊት መመገብ ክልክል ነው፡፡ ከራበውና ከተቸገረ ሕይወቱን የሚያድንበት ያህል የተከለከለ ነገርም ቢሆን መመገብ ግዴታ ነው፡፡

**ከሃዲዎችን** በበዐላቸው ቀን እንኳን አደረሳችሁ ማለት ወይም በስፍራው መገኘት ወይም እነሱን ቀድሞ ሰላም ማለት ክልክል ነው፡፡ እነሱ ከጀመሩን ግን 'በናንተም ላይ' በሚል መመለስ ግዴታ ነው፡፡ ለእነሱም ሆነ ለቢድዐ ሰዎች በማክበር መቆም ክልክል ነው፡፡ እነሱን መጨበጡም ይጠላል፡፡ ሰዉ ሲሞትባቸው ማፅናናትና ሲታመሙ ማየት መጎብኘት ኢስላማዊ ጥቅም እንዳለው ካልተረጋገጠ በስተቀር ክልክል ነው፡፡

# ሸሪዓዊ ሩቅያች / መንፈሳዊ ህክምና አደራረግ

(ከሸሪዐ ጋር ግጭት የሌላቸው መንፈሳዊ የህክምና/ስልቶች/

የአላህ (ﷻ) ተፈጥሮአዊ ክንውንን በጥልቀት ያስተዋለ ሰው ፈተና አላህ (ﷻ) በሰዎች ህይወት ላይ ያስተላለፈዉ ነባራዊ ዉሣኔ መሆኑን በትክክል ይረዳል፡፡ አላህ (ﷻ) እንዲህ አለ (ሙሐመድ ሆይ ከፍርሃትና ከርሀብም በጥቂት ነገር፤ ከገንዘቦችና ከነፍሶችም ከፍራፍሬዎችም በመቀነስ በዕርግጥ ዕንሞክራችኋለን፡ ታጋሾችንም (በገነት) አብስር፡፡) 2፡ 155 መልካም ሰዎች በላእ/መከራና ችግር አይደርስባቸዉም የሚል ሰው ፈፅሞ ተሳስቷል፡፡ እንዲያዉም መፈተን ከኢማን/እምነት/ ምልክቶች ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ኢብኑ ማጀህ በዘገቡት ሐዲስ (ከሰዎች ሁሉ ፈተና የሚበዛባቸው እነማን ናቸው ተብለው ተጠይቀው፡- ነቢያት፤ ከዚያም ሷሊሆች ፤ከዚያም የተሻሉት/በኢማን ከነሱ የሚጠጉት/..የተሻሉት...) ሲሉ መልሰዋል፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ የሚፈተነው በእምነቱ ልክ ነው፡፡ በእምነቱ ጠንከር ያለ ከሆነ ፈተናዉም እንደዚያዉ ይበዛበታል:: በእምነቱ ደከም ያለ ከሆነ ፈተናዉም ይቀንሳል›› ብለዋል፡፡ ፈተና አላህ (ﷻ) ባሪያዉን የመውደዱ ምልክትም ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ አህመድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ አሉ (አላህ የተወሰኑ ሰዎችን ሲወድ ይፈትናቸዋል). ብለዋል፡፡

ፈተና አላህ (ﷻ) ለባሮቹ ኸይር መሻቱን ከሚያመለክቱት አያሌ ነገሮች አንዱም ነው፡ ፡ ነቢዩ ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ አሉ (አላህ ለባሪያው ኸይር ሲያስብ ቅጣቱን በዚህች ዐለም ያፋጥንለታል፡፡መጥፎ ሲያስብበት ደግሞ ከነወንጀሉ ዝም ይለዉና ቅጣቱን ለዚያኛው ዐለም ያዘገይለታል፡፡) ብለዋል፡፡ ቢያንስም ፈተና ለወንጀል ማሳበሻ ነው፡፡ ነብዩ ቡኻሪና ሙስሊም. በዘገቡት ሐዲስ (በእሾህም ሆነ ከዚያ በላይ በሚያጋጥመው ችግር ለሙስሊም ዛፍ ቅጠሏን እንደምታራግፍ ሁሉ ወንጀሉን የሚያራግፍለት ቢሆን እንጂ ሌላ አይደለም፡፡) ብለዋል፡፡ ስለዚህ የተፈተነው ሙስሊም ጠንካራ ከሆነ ላለፉት ወንጀሎቹ ማሳረዣ ወይም ለደረጃ እድገቱ ምክኒያት ናቸው፡፡ ወንጀለኛ ከሆነ ግን ለወንጀሉ ማሰረዣና አደገኝነቷን መግለጫ ናቸው፡፡ አላህ (ﷻ) (የሰዎች እጆች በሰሩት ኃጢአት ምክንያት የዚያን የሰሩትን ከፊሉን ያቀምሳቸው ዘንድ መከራው በየብስና በባህር ተገለጠ/ተሰራጨ/)፡፡ ብሏል፡፡

የፈተና ዓይነቶች ብዙ ናቸው:: በኸይር መፈተን ማለትም ለምሳሌ ገንዘብን በማብዛት መፈተን አለ፡ በመጥፎ ነገሮች ማለትም በፍርሃት፤ በረሃብ በድህነት መፈተንም አለ፡፡ አላህ (ﷻ)"በኸይርና በሸር እንፈትናችኋለን ወደኛም ትመለሣላችሁ" መነሻቸው ከምቀኝነት የሆኑት ድግምትና አይነናስ/ የሰዉ ዐይን/ እንዲሁ መታመምና መሞትም ከፈተና ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ አቡዳውድ ጦያሊሲ በዘገቡት ሐዲስ (ከህዝቦቼ ብዙዎች የሚሞቱት ከአላህ ዉሳኔ በኋላ በአይነናስ/ በሰዉ ዐይን/ ነው፡፡) ብለዋል።

ከሲህር/ድግምትና/ከዐይን ስለ መጠንቀቅ፡ መተትና ድግምትም ሆነ አይነ-ናስ ከመከሰቱ በፊት ራሳችንን ከእሱ እንዴት እንደምንጠብቅ ማወቅ ያስፈልገናል፡፡ በቅድሚያ መጠንቀቅ ከተያዙ በኋላ በህክምና ከማቀቅ ይሻላልና፡፡ መጠንቀቅ በብዙ ነገሮች ይቻላል፡፡ ከእነዚህም መካከል ዋናው፡- ✷ ነፍስን በተዉሂድ ማጠናከር- ይህችን ዐለም እንደ ፈለገ የሚያስተናብር አላህ (ﷻ) ብቻ መሆኑን ማወቅና መልካም ተግባሮችን ማብዛት፤ ✷ ከአላህ (ﷻ) ደግን ማሰብና መጠርጠር፣ በእሱ ብቻ መመካት፣ በሽታዉን ከየት መጣ፤በምን መጣብኝ ብሎ አለማሰብ አለመጨነቅ፡፡ ምክኒያቱም ሐሳብ እራሱ በሽታ ነውና፡፡ ✷ አይኑ ጉዳት ያደርሳል/ በተለምዶ ቡዳ ነዉ/ተብሎ የታወቀን ሰው ፈርቶ ሳይሆን ለጥንቃቄ ሲባል መሸሽ ያስፈልጋል፡ ✷ደስ የሚል ነገር ሲታይ ባረከሏህ/ ማሻአላህ/ በማለት አላህን (ﷻ) ማውሳት ይገባል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ ሐኪም በዘገቡት ሐዲስ (ከራሱም ሆነ ከገንዘቡ ወይም ከወንድሙ የሚያስደስተው ነገርን ያየ ሰው ባረከሏሁ ይበል ምክኒያቱም አይነናስ/ ዐይን/ ሐቅ ነዉና፡፡) ብለዋል፡፡

- ጧት ጧት በባዶ ሆድ ከዐጀዋ/የመዲና ቴምር/ ሰባት ፍሬ መብላት፤
- ወደ አላህ መጠጋትና በሱ ላይ መመካት፣ የጧትና የማታን ዚክር ማዘውተር፣[1] ከሁሉ ነገር በአላህ መጠበቅ፡ ዚክሮች ብዙ ዉጤቶች አሏቸው፡፡ በአላህ (ﷻ) ፍቃድም ዚክሮች በአላህ ፈቃድ በሁለት ነገሮች ምክኒያት ሊቀንስና ሊጨምር የሚችል ተፅእኖ አላቸዉ፡፡ 1) በዉስጡ ያለው ነገር ሁሉ ሐቅ ነው፡፡ በአላህ (ﷻ) ፍቃድም ይጠቅማል ብሎ ማመን፤ 2) ምላሱ ሲናገረው ጆሮው አዳምጦ ፤በልቡ ህያዉ ሆኖ ዱዓ መሆኑን ሳይዘናጋ ካደረገው ነው፡፡

**የዚክርና የተዓዊዝ/ከአላህ (ﷻ) ጥበቃን የምንጠይቅበት/ጠብቀን የምንልበት/ሰዓቶች-** የጧት ዚክሮች የሚባሉት ከሱብሂ ሶላት በኋላ ነው፡፡ የማታ ዚክሮች ደግሞ ከአስር ሶላት በኋላ ነው የሚባሉት፡፡ ከረሳት ወይም ከተሳነፈ ሲያስታዉሳት ይበላት፡፡

**በአይንናስ (በሰዉ ዐይንም) ሆነ በሌላ የመያዝ ምልክቶች - በዘመናዊ ህክምናና በሸሪዓዊ** ሩቅያ/ በኢስላም መንፈሣዊ ህክምና/ መካከል ግጭት ብዙም የለም፡፡ ቁርአን ለአካላዊም ሆነ ለመንፈሳዊ በሽታዎች ሁሉ ፍቱን ፈውስ ነው፡፡ ሰዉየዉ ከአካላዊ በሽታዎች ነፃ ከሆነ የዓይንናስ መሰል በሽታ ምልክቶቹ - የሚፈራረቅ የራስ ህመም ፤የፊት መገርጣት፤ የላብና ሽንት መብዛት፤ የፍላጎት መቀነስ፤ በሰዉነት ጫፎች ላይ ተነሙል/የደረመን ቁስል መብዛት/ ወይም ሙቀት ወይም ቅዝቃዜ መታየት፤ የልብ ማንቋራት፤ ከወገብ በታችና በትከሻ ላይ በሁለቱ መካከል የሚመላለስ የህመም ስሜት፤ ሀሳብ፣ ሀዘንና ጭንቀት በልብ ላይ መብዛት፤ የሌሊት እንቅልፍ ማጣት፤ ያልተለመደ የቁጣ የፍርሃትና የመገንፈል ስሜት፤መብዛት፤ ብቸኝነትን መውደድ፤ መስነፍና መሰላቸት፤ እንቅልፍ እንቅልፍ የማለት ስሜት፤ ሌሎች በህክምና ምክኒያታቸዉ ያልታወቁ የጤና መታወክ ማጋጠም ናቸው፡፡ በበሽታዉ የጥንካሬና ድክመት ልክ ከተጠቀሱት ምልክቶች ሁሉም ወይም አንዳንዶቹ በበሽተኛዉ ላይ ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡

**አንድ ሙስሊም ሁልጊዜም ማንኛዉም ወስዋስ የማያጠቃዉ ጠንካራ እምነትና ቀልብ ሊኖረዉ ይገባል፡፡** ከእነኚህ ምልክቶች አንዱን በማየቱ ብቻ በሆነ በሽታ ተለክፌያለሁ ብሎ ሊጨነቅ አይገባም:: ጭንቀት ራሱ ለህክምና አስቸጋሪ የሆነ በሽታ ነውና፡፡ በአንዳንድ ጤነኛ ሰዎች ላይም እነኚህ ምልክቶች ሊታዩ ይችላሉ::፡ በሽታው አካላዊም ሆኖ እነዚህ ምልክቶች ሊታዩ ይችላሉ፡፡ የህሣብና የጭንቀት መብዛት ምክኒያቱ የኢማን/እምነት/ ድክመት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ አንድ አማኝ ሁሌም ከአላህ (ﷻ)ጋር ያለዉን ግንኙነት መገምገምና ራሱን ማጠናከር ይገባዋል፡፡

**ህመሙ በአይነናስ[2] ምክኒያት ከሆነ** ፈውሱ/ ህክምናዉ/ በአላህ ፈቃድ ከሁለት በአንዱ ይሆናል፡፡ 1) ባለ አይኑን ሰዉ ካወቅከው እንዲታጠብልህ ጠይቀህ ወይም ከሱ አሰሮች/ወዞች/[3] አንዱን ወስደህ በዚያ ዉሃ መታጠብና መጠጣት ነው፡፡
2) አይናማው ሰዉ ካልታወቀ በሸሪዓዊ ሩቅያ፤ በዱዓና በዋግምት ነው፡፡

**ህመሙ በመተት/ ድግምት /አስማት[4] ምክኒያት የተከሰተ ከሆነ ደግሞ ፈውሱ**

---

[1] የጧትና ማታ ዚክሮችን ገፅ፣ 159፣ ላይ ተመልከት

[2] ዐይን ማለት ተጠቂዉን ሊጎዳ የሚችል ተመልካቹ የተደነቀበት ሁኔታ ሲኖርና የዚክርም ሆነ የሶላት መከላከያ በሌለበት ሰይጣን የሚያደርሰው ጥቃት ነው፡፡ ይህን አባባል ቡኻሪ( አይን እውነት ነው) በሚል የዘገቡት ሐዲስ ያጠናክረዋል፡፡ ምክንያቱም ሌላኛው ዘገባ (ሰይጣንና ምቀኝነት ይካፈሉበታል፡፡) የሚል ስላለበት ነዉ:: አይን የተባለበት ምክንያት መግለጫ ስለሆነች እንጂ ማጥቂያ በመሆኗ አይደለም፡፡ አይነ ስዉር ሰው ሳይመለከት ሊያጠቃ እንደሚችል ስለሚታወቅ፡፡

[3] ወዞች፣ ትራፊዎችና ንክኪዎች እንደ ማለት ነዉ......

[4] ድግምት፣ አስማት፣ መተት፣ ሲህርም ይባላል፡፡ እሱም የተቋጠረ ክር፣ የተጠቀለለ ወረቀት የሚተበተብ ማውተምተም ሲሆን የተጠቂዉን አካል ፤ልብ፤አዕምሮ ሊጎዳ ይችላል፡፡ እውነታ ያለዉና የሚያሳምም፤

በአላህ ፈቃድ ከዚህ በታች ከተጠቀሱት በአንዱ ይሆናል፡፡

1) አስማቱ ያለበትን ቦታ ካወቀው ሁለቱን ቁል አዑዙዎች (ቁል-አዑዙ ቢረቢናስን እና ቁል-አዑዙ ቢረቢልፈለቅን) እያነበበ መተቱን/ድግምቱን አውጥቶ በእሳት ማቃጠል፤

2) በሸሪዓዊ የፈዉስ አደራረግ -ይህም ከቁርአን አንቀፆች በተለይም ቁል አዑዙዎች በበቀራህ ምዕራፍና ከዚህ ቀጥለዉ በሚመጡት ዱዓዎች እያነበቡ ሩቅያ ማድረግ ነው፡፡

3) ድግምቱን ማስፈታት ሲሆን፡- ይኸዉም በሁለት አይነት ይከፈላል፡፡ 1) ክልክል የሆነዉ ሲሆን - ይኸዉም ድግምትን በድግምት መፍታትና ለዚሁ ጉዳይ ወደ ድግምተኞች መሄድ ነው፡፡ 2) የሚፈቀድ አይነት ሲሆን- ይህም (ሰባት የቁርቁራ ቅጠል በድንጋይ ፈጭቶ ከዚያም ሶስት ጊዜ ሱረቱል-ካፈሩን፤ ሱረቱል-ኢኽላስንና ሁለቱን ቁል አዑዙዎች አንብቦ በዉሃ በጥብጦ መጠጣትና መታጠብ እስከሚድን ድረስ ይህን ደጋግሞ ማድረግ ነው፡ ኢንሻአላህ በአላህ ፈቃድ ፈዉስ ይገኝበታል፡) ዐብዱረዛቅ የዘገቡት ሐዲስ ነው፡፡

4) ድግምቱ በሆድ ዉስጥ ከሆነ ወደታች በሚያስቀምጥ ነገር ማስወጣት ይቻላል። ከሌላ ላይ ከሆነ ግን በዋግምት[1] ማስወጣት ነው፡፡

የሩቅያ / መንፈሳዊ የፈዉስ አደራረግ / ቅድመ ሁኔታዎች፡- 1) በቁርአን አንቀፆችና ከነብዩ በተዘገቡ ዱዓዖች መሆን፤ 2) በዐረብኛ መሆን ሲሆን ዱዓዎችን በሌላም ቋንቋ ማለት ይቻላል፡፡ 3) መዳን በአላህ እጅ ብቻ መሆኑን ሩቅያ ምክንያት እንጂ ብቻዋን ፈዉሰ አለመሆኗን ማመን ናቸው፡፡

ይበልጥ ለመጠቀም በሩቂያ ወቅት ቁርአንን የሚቀራ ሰዉ መዳንንና ለሰዎችም ሆነ ለጅኖች መስተካከልንና ማስተማርን[2] አስቦ ያንብብ፡፡ ምክንያቱም ቁርአን የወረደው ሰዎች እንዲማሩበትና እንዲቀኑበት ነው፡፡ አልወጣም ብሎ ካላስቸገረ በስተቀር ጂኑን ለመግደል ብሎ ማንበብ የለበትም፡፡

ሩቅያ የሚያደርግ ሰው ሊያሟላቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች፡- 1) ሙስሊም ከመሆኑ ጋር ተቂይ /አላህን የሚፈራ/ ሷሊህ መሆኑ ይወደዳል፡፡ የአላህ ፍራቻው በጨመረ ቁጥር ዉጤቱም የበለጠ ጥሩ ይሆናል፡፡ 2) ሩቅያ ሲያደርግ ወደ አላህ ልቡ ከምላሱ ጋር በትክክል የተሰበሰበ መሆን አለበት:: ለዚህም የሚበልጠው ሰዉየዉ የጉዳዩ ባለቤት እራሱ ለራሱ ሩቅያ ማድረጉ ነው፡፡ምክኒያቱም ብዙ ሰዎች እንደራሳቸው አድርገው አይጨነቁም:: እንደ ባለጉዳዩም አድርገው ሁኔታዎችን አይመለከቱምና፡፡ የተጨነቁትን ደግሞ አላህ ምላሽ ሊሰጣቸዉ ቃል ገብቷል::

ሩቅያ የሚደረግለት ሰው ማሟላት ያለበት ቅመ ሁኔታዎች

1) ጥሩ አማኝ መሆን አለበት፣ ምክንያቱም አምርቂ ዉጤት ሊገኝ የሚችለው በእምነት ልክ ስለሆነ። ከቁርአንም ለምእምናን መድሓኒትና እዝነት የሆነን እናወርዳለን። በደለኞችንም ኪሳራን እንጂ አይጨምርላቸዉም።) 17፡82

2) እንዲያድነው ብሎ በልብና ከእዉነት ወደ አላህ ፊትን መመለስ፤

3) ለመዳን አለመቸኮል:: ምክኒያቱም ሩቅያ ዱዓ ነው:: ዱዓ ደግሞ አልተቀበለኝም እያሉ ካጣደፉት ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ዱዓ አድርጌ ተቀባይነት አጣሁኝ እስካላለ ድረስ የሁላችሁም ዱዓ

---

ግንኙነት የሚያግድ፤ባልና ሚስት የሚያጣላና ሊገድል የሚችል ፀያፍ ተግባር ነው፡፡ ተግባሩ ከትልቅ ወንጀልነት አንስቶ ወደ ሽርክ ሊደርስም ይችላል፡፡

[1] ነብዩ (ከታከማችሁበት ነገር ሁሉ የተሻለው ዋግምት ነው) ብለዋል፡፡ በዋግምት አያሌ አካለዊና አይነ ናስ በሽታዎች ድነዋል፡፡ ድግምት በብዙ ሁኔታዎች ልክ እንደ ነቀርሳ ነው፡፡

[2] ይህ ሙከራ ብዙ ዉጤቶችን አሳይቷል፡፡ ጂኑም ተመክሮ ሰዉየዉን ከማጥቃት ይገታል፡፡ ለመግደል የተቀራው ግን ጂኑ እልህ ይይዘዉና በሽተኛዉንም ሆነ ሩቂያ አድራጊዉን ሊተናኮል ይችላል፡፡ ነብዩ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (አላህ አዛኝ ነው፡፡ በሀይል የማይሰጠዉን በእዝነት ይሰጣል፡፡) ብለዋል፡፡

ተቀባይነት አለው፡፡)ብለዋል፡፡

**ሩቅያ ብዙ መንገዶች አሉት፡፡** ከእነሱም መካከል 1) ከትንሽ ምራቅ/እትፍ እትፍ ከማለት/ ጋር ሩቅያዉን ማንበብ፤ 2) ያለምንም ቱፍታ ማንበብ፤
3) ምራቁን በእጅ ይዞ በአፈር መደባለቅና ህመም የሚሰማበትን ቦታ/ አካል/ በሱ ማበስ፤
4) የህመሙ ስሜት ያለበትን ቦታ እየነካኩ ማንበብ ናቸው፡፡

**ሩቅያ የሚደረግባቸው ልዩ ልዩ ቁርአናዊ አንቀፆችና ነቢያዊ ሐዲሶች**

(ሱረቱ -አል ፋቲሃ፡-አልሐምዱ ሊላሂ ረቢልዓለሚን)1፡1-7

(አየቱል ኩርሲ

﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡحَيُّ ٱلۡقَيُّومُۚ لَا تَأۡخُذُهُۥ سِنَةٞ وَلَا نَوۡمٞۚ لَّهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۗ مَن ذَا ٱلَّذِي يَشۡفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذۡنِهِۦۚ يَعۡلَمُ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَمَا خَلۡفَهُمۡۖ وَلَا يُحِيطُونَ بِشَيۡءٖ مِّنۡ عِلۡمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَۚ وَسِعَ كُرۡسِيُّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَۖ وَلَا يَـُٔودُهُۥ حِفۡظُهُمَاۚ وَهُوَ ٱلۡعَلِيُّ ٱلۡعَظِيمُ ﴾

(አላሁ ላኢላሀ ኢላሁወ- ልሐዩል ቀዩሙ ላተእኹዙሁ ሲነቱን ወላ ነውም ለሁ ማፊሰማዋቲ ወማ ፊል አርዲ መንዘለዚ የሽፈው ዒንደሁ ኢላ ቢኢዝኒሂ የዕለሙ ማበይነ አይዲሂም ወማ ኸልፈሁም ወላ ዩሂጡነ ቢሸይኢን ሚን ዒልሚሂ ኢላ ቢማሻአ ወሲዐ ኩርሲዩሁ ሰማዋቲ ወልአርዶ ወላ የኡዱሁ ሂፍዙሁማ ወሁወል ዐልዩል አዚም፡፡)[1]2፡255

**የሱረቱል በቀራህ የመጨረሻዎቹ ሁለቱ አንቀፆች ማለትም**

﴿ ءَامَنَ ٱلرَّسُولُ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيۡهِ مِن رَّبِّهِۦ وَٱلۡمُؤۡمِنُونَۚ كُلٌّ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ لَا نُفَرِّقُ بَيۡنَ أَحَدٖ مِّن رُّسُلِهِۦۚ وَقَالُواْ سَمِعۡنَا وَأَطَعۡنَاۖ غُفۡرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيۡكَ ٱلۡمَصِيرُ ٢٨٥ لَا يُكَلِّفُ ٱللَّهُ نَفۡسًا إِلَّا وُسۡعَهَاۚ لَهَا مَا كَسَبَتۡ وَعَلَيۡهَا مَا ٱكۡتَسَبَتۡۗ رَبَّنَا لَا تُؤَاخِذۡنَآ إِن نَّسِينَآ أَوۡ أَخۡطَأۡنَاۚ رَبَّنَا وَلَا تَحۡمِلۡ عَلَيۡنَآ إِصۡرٗا كَمَا حَمَلۡتَهُۥ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِنَاۚ رَبَّنَا وَلَا تُحَمِّلۡنَا مَا لَا طَاقَةَ لَنَا بِهِۦۖ وَٱعۡفُ عَنَّا وَٱغۡفِرۡ لَنَا وَٱرۡحَمۡنَآۚ أَنتَ مَوۡلَىٰنَا فَٱنصُرۡنَا عَلَى ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡكَٰفِرِينَ ﴾

(ኣመነርረሱሉ ቢማ ኡንዚለ ኢለይሂ ሚን ረቢሂ ወልሙእሚኑን ኩሉን ኣመነ ቢላሂ ወመላኢከቲሂ ወኩቱቢሂ ወሩሱሊሂ ላኑፈሪቁ በይነ አህዲን ሚን ሩሱሊሂ ወቃሉ ሰሚዕና ወአጠዕና ጉፍራነከ ረበና ወኢለይከል መሲር ላዩከሊፉላሁ ነፍሰን ኢላ ዉስዐሃ ለሃ ማከሰበት ወዐለይሃ መክተሰበት ረበና ላቱአኺዝና ኢን ነሲይና አው አኽጦእና ረበና ወላ ተህሚል ዐለይና ኢስረን ከማ ሀመልተሁ ዐለለዚን ሚን ቀብሊና ረበና ወላ ቱህሚልና ማላ ጣቀተ ለና ቢሂ ወዕፉ ዐና ወግፊርለና ወርሀምና አንተ መውላና ፈንሱርና ዐለልቀውሚልካፊሪን)[2] 2፡285-286.፤ ሱረቱል-ካፊሩን፤[3] ሱረቱል-ኢኽላስ፤[4] ቁል አዑዙ ቢረቢልፈለቅ፤[5] ቁል አዑዙ ቢረቢንናስ፤[6]

---

[1] ትርጉሙም (አላህ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም:: ህያው ራሱን ቻይ ነው :ማንጉላጀትም እንቅልፍም አይዘውም፡ በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው:: ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጂ የሚያማልድ ማን ነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል:: ባሻው ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር (ፍጡሮች) አያካብቡም (አያውቁም)፡፡ ዙፋኑ /መንበሩ/ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ (በለጠ):: ጥበቃቸውም አያቅተውም:: እርሱ የሁሉ በላይና የላቀ ነው:):

[2] ትርጉሙም (መልዕክተኛው (ሙሐመድ) (ﷺ) ከጌታው ወደ እርሱ በተወረደለት አመነ:: ምዕምናንም እንደዚሁ አመኑ፡፡ ሁሉም በአላህ፤ በመልአክቱ፤ በመጸሕፍቱና በመልክተኞቹ ከመልክተኞቹ በአንድም መካከል አንለይም (የሚሉ ሲሆኑ) አመኑ:: ትዕዛዛትንም ሰማን፤ ታዘዝንም አሉ:: ጌታችን ሆይ! ምህረትህን (እንሻለን):: የሁሉም መመለሻም ወደ አንተ ብቻ ነው (አሉ):: 286. አላህ የትኛዋንም ነፍስ ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም:: ለርሷ የሰራችው መልካም ሥራ (ምንዳ) አላት:: በእራሷም ላይ የሰራች (ሀጢአት) ቅጣት አለባት:: (በሉ):- ጌታችን ሆይ! ብንረሳ ወይም ብንሳሳት አትያዘን (አትቅጣን)፡፡ ጌታችን ሆይ! ከባድ ሸክምን ከኛ በፊት በነበሩት ላይ እንደጫንከው ሁሉ በኛ ላይ አትጫንብን:: ጌታችን ሆይ! የማንችለውን ነገር አታሸክመን፡፡ ይቅርታም አድርግልን፡፡ ምህረትም ለግሰን፡፡ እዘንልንም:: ረዳታችን አንተ ነህና፡፡ በከሓዲ ህዝቦች ላይም እርዳን/ድል ስጠን/ አሉ፡፡

[3] ትርጉሙ ተፍሲሩ ላይ አልፏል፡፡

[4] ትርጉሙ ተፍሲሩ ላይ አልፏል፡፡

[5] ትርጉሙ ተፍሲሩ ላይ አልፏል፡፡

[6] ትርጉሙ ተፍሲሩ ላይ አልፏል፡፡

﴿ وَأَوْحَيْنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰٓ أَنْ أَلْقِ عَصَاكَ ۖ فَإِذَا هِىَ تَلْقَفُ مَا يَأْفِكُونَ ﴿١١٧﴾ فَوَقَعَ ٱلْحَقُّ وَبَطَلَ مَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴿١١٨﴾ فَغُلِبُوا۟ هُنَالِكَ وَٱنقَلَبُوا۟ صَٰغِرِينَ ﴾
**(ወአውሐይና ኢላ ሙሳ አን አልቂ ዐሷከ ፈኢዛ ሂየ ተልቀፉ ማየእፈኩን ፈወቀዐል ሐቁ ወበጦለ ማካኑ የዕመሉን:: ፈጉሊቡ ሁናሊከ ወንቀለቡ ሷጊሪን::)**[1]

﴿ أَمْ يَحْسُدُونَ ٱلنَّاسَ عَلَىٰ مَآ ءَاتَىٰهُمُ ٱللَّهُ مِن فَضْلِهِۦ ﴾
**(አም የህሱዱነናሰ ዐላማ አታሁሙ ላሁ ሚን ፈድሊሂ)**[2]

﴿ وَإِذَا مَرِضْتُ فَهُوَ يَشْفِينِ ﴾ **(ወኢዛ መሪድቱ ፈሁወ የሽፊኒ)**[3]

﴿ قَالُوا۟ يَٰمُوسَىٰٓ إِمَّآ أَن تُلْقِىَ وَإِمَّآ أَن نَّكُونَ أَوَّلَ مَنْ أَلْقَىٰ ﴿٦٥﴾ قَالَ بَلْ أَلْقُوا۟ ۖ فَإِذَا حِبَالُهُمْ وَعِصِيُّهُمْ يُخَيَّلُ إِلَيْهِ مِن سِحْرِهِمْ أَنَّهَا تَسْعَىٰ ﴿٦٦﴾ فَأَوْجَسَ فِى نَفْسِهِۦ خِيفَةً مُّوسَىٰ ﴿٦٧﴾ قُلْنَا لَا تَخَفْ إِنَّكَ أَنتَ ٱلْأَعْلَىٰ ﴿٦٨﴾ وَأَلْقِ مَا فِى يَمِينِكَ تَلْقَفْ مَا صَنَعُوٓا۟ ۖ إِنَّمَا صَنَعُوا۟ كَيْدُ سَٰحِرٍ ۖ وَلَا يُفْلِحُ ٱلسَّاحِرُ حَيْثُ أَتَىٰ ﴾
**(ቃሉ ያሙሳ ኢማ አን ቱልቂየ ወኢማ አን ነኩነ አወለ መን አልቃ:: ቃለ በል አልቁ ፈኢዛ ሂባሉሁም ወዒሲዩሁም ዩኸየሉ ኢለይሂ ሚን ሲህሪሂም አነሃ ተስዓ :ፈአውጀሰ ፊ ነፍሲሂ ኺፈተን ሙሳ:: ቁልና ላተኸፍ ኢነከ አንተል አዕላ:: ወአልቂ ማፊየሚኒከ ተልቀፍ ማሰነው ኢነማ ሶነው ከይዱ ሳሂር ወላ ዩፍሊሁ ሳሂሩ ሀይሱ አታ::) 20:65-69**

﴿ وَنُنَزِّلُ مِنَ ٱلْقُرْءَانِ مَا هُوَ شِفَآءٌ وَرَحْمَةٌ لِّلْمُؤْمِنِينَ ۙ وَلَا يَزِيدُ ٱلظَّٰلِمِينَ إِلَّا خَسَارًا ﴾
**(ወኑነዚሉ ሚነልቁርኣኒ ማሁወ ሺፋኡን ወረህመቱን ሊልሙእሚኒን ወላየዚዱ ዟሊሚን ኢላ ኸሳራ)** [4]

﴿ قُلْ هُوَ لِلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ هُدًى وَشِفَآءٌ ﴾ **(ቁል ሁወ ሊለዚነ አመኑ ሁደን ወሺፋኡን)** [5]

﴿ لَوْ أَنزَلْنَا هَٰذَا ٱلْقُرْءَانَ عَلَىٰ جَبَلٍ لَّرَأَيْتَهُۥ خَٰشِعًا مُّتَصَدِّعًا مِّنْ خَشْيَةِ ٱللَّهِ ﴾ **(ለው አንዘልና ሃዛልቁርአነ ዐላ ጀበሊን ለረአይተሁ ኻሺዐን ሙተሶዲዐን ሚን ኸሽየቲላህ)** [6]

﴿ وَإِن يَكَادُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لَيُزْلِقُونَكَ بِأَبْصَٰرِهِمْ لَمَّا سَمِعُوا۟ ٱلذِّكْرَ وَيَقُولُونَ إِنَّهُۥ لَمَجْنُونٌ ﴾ **(ወኢን የካዱ ለዚነ ከፈሩ ለዩዝሊቁነከ ቢአብሷሪሂም ለማ ሰሚዑ ዚክረ ወየቁሉነ ኢነሁ ለመጅኑን)** [7]

﴿ ثُمَّ أَنزَلَ ٱللَّهُ سَكِينَتَهُۥ عَلَىٰ رَسُولِهِۦ وَعَلَى ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴾ **(ሱመ አንዘለሏሁ ሰኪነተሁ ዐላ ረሱሊሂ ወዐለል ሙእሚኒን)** [8]

﴿ فَأَنزَلَ ٱللَّهُ سَكِينَتَهُۥ عَلَىٰ رَسُولِهِۦ وَعَلَى ٱلْمُؤْمِنِينَ وَأَلْزَمَهُمْ كَلِمَةَ ٱلتَّقْوَىٰ وَكَانُوٓا۟ أَحَقَّ بِهَا وَأَهْلَهَا ﴾
**(ፈአንዘለሏሁ ሰኪነተሁ ዐለይሂ ወአየደሁ ቢጁኑዲን ለም ተረውሃ** [9]

﴿ هُوَ ٱلَّذِىٓ أَنزَلَ ٱلسَّكِينَةَ فِى قُلُوبِ ٱلْمُؤْمِنِينَ لِيَزْدَادُوٓا۟ إِيمَٰنًا مَّعَ إِيمَٰنِهِمْ ﴾
**(ሁወለዚ አንዘለ ሰኪነተ ፊ ቁሉቢልሙእሚኒን ሊየዝዳዱ ኢማነን መዐ ኢማኒሂም)** [10]

**ከሃዲሶች፡**

**(أَسْأَلُ اللهَ العَظِيْمَ رَبَّ العَرْشِ العَظِيْمِ أَنْ يَشْفِيَكَ) (አስአሉ ሏሀልዐዚም ረበል ዐርሺ ዐዚም አን የሽፊየከ)**[11] **7 ጊዜ**

---

[1] (ወደ ሙሳም -በትርህን ጣል ስንል ላክን:: (ጣላትም::) ወዲውኑም የሚቀጣጥፉትን (ማታለያ) ሁሉ መዋጥ ጀመረች::118. እውነቱም ተገለጸ:: ይሠሩት የነበሩት (ድግምትም) ተበላሸ:: 119. እዚያ ላይ ተሸነፉና ወራዶች ሆነው ተመለሱ:: 120. ድግምተኞቹም ሰጋጆች ሆነው ወደቁ /ሱጁድ ወረዱ/::) 7:117-119

[2] (ይልቁንም ሰዎችን አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ነገር ላይ ይመቀኛሉን?::)4:54

[3] በታመምኩም ጊዜ እርሱ ያሽረኛል::) 26:80

[4] ከቁርአን ለምእምናን መድሓኒትና እዝነት የሆነን እናወርዳለን:: በዳዮችን ከሳራን እንጂ ሌላ አይጨመርላቸውም::)17:82

[5] የአማኝ ህዝቦችን ልቦችም ያሽራል::41:44

[6] ይህንን ቁርአን በተራራ ላይ ባወረነው ኑሮ ከአላህ ፍራቻ ተዋራጅና ተሰንጣቂ ሆኖ ባየኸው ነበር። 59:21

[7] እነሆ እነዚያ የካዱት ሰዎች ቁርአኑን በሰሙ ጊዜ በዓይኖቻቸው ሊጥሉህ ይቃረባሉ፤ እርሱም በእርግጥ እብድ ነው ይላሉ። 68:51

[8] ከዚያ አላህ ሰላሙን በመልዕከተኛውና በምዕመናኖቹ ላይ አወረደ:: 9:26

[9] አላህም በመልክተኛው ላይ እርጋታውን አወረደ:: ባላያችሁት ሰራዊትም ደገፈው:: 48:26

[10] እርሱ ያ በምእምናን ልቦች ውስጥ ከእምነታቸው ጋር እርጋታን ያወረደ ነው:: 48:4

[11] የታላቁን ዐርሽ/ ዙፋን ፈጣሪ ከበሺታህ ይፈዉስህ ዘንድ እማፀናለሁ።

(أُعِيذُكَ بِكَلِمَاتِ اللهِ التَّامَةِ مِنْ كُلِّ شَيْطَانٍ وَهَامَّةٍ وَمِنْ كُلِّ عَيْنٍ لامَّةٍ) (ዑዒዙከ ቢከሊማቲላሂ ታመህ ሚን ኩሊ ሸይጧኒን ወሃመህ ወሚንኩሊ ዐይኒን ላመህ)[1] 3 ጊዜ
(اللَّهُمَّ رَبَّ النَّاسِ أَذْهِبِ البَأسَ اشْفِ أَنْتَ الشَّافِي لا شِفَاءَ إِلا شِفَاؤُكَ شِفَاءً لايُغَادِرُ سَقَمًا) (አላሁመ ረበናስ አዝሂቢል በዕስ ኢሽፊ አንተሻፊ ላሺፋአ ኢላ ሺፋኡከ ሺፋአን ላ ዩጋዲሩ ሰቀማ)[2] 3 ጊዜ
اللَّهُمَّ أَذْهِبْ عَنْهُ حَرَّهَا وَبَرْدَهَا وَوَصَبَهَا (አላሁመ አዝሂብ ሐረሃ ወበርደሃ ወወሶበሃ)[3] 1 ጊዜ
حسبِيَ اللهُ لا إِله إِلا هُو عليهِ توكّلت وهو ربُّ العرشِ العظِيمِ
(ሐስቢየላሁ ላኢላህ ኢላ ሁወ ዐለይሂ ተወከልቱ ወሁወ ረቡል ዐርሺልዐዚም.)[4] 7ጊዜ
بِسمِ اللهِ أَرقِيكَ مِن كُلِّ داءٍ يُؤذِيكَ ومِن شَرِّ كُلِّ نَفسٍ أَو عَينِ حاسِدٍ، اللهُ يَشفِيكَ بِسمِ اللهِ أَرقِيكَ
(ቢስሚላህ አርቂከ ሚን ኩሊ ዳኢን ዩዕዚከ ወሚን ሸሪ ኩሊ ነፍሲን አው ዐይኒ ሃሲዲን አላህ የሽፊከ ቢስሚላህ አርቂከ )[5] 3ጊዜ
بِسْمِ اللهِ እጅህን ህመም በሚሰማዉ ቦታ ላይ ታደርግና 3 ጊዜ ቢስሚላህ' '
أَعوذُ بِعِزَّةِ اللهِ وقُدرتِهِ مِن شَرِّ ما أَجِدُ وأُحاذِرُ (እንዲሁም አዑዙ ቢዒዘቲላህ ወቁደረቲሀ ሚን ሸሪ ማ አጂዱ ወኡሃዚር)[6] ሰባት ጊዜ በል።

ማሳሰቢያዎች፡-

❶ በአይነናስ ዙሪያ ያሉ አላስፈላጊ እምነቶችን ለምሳሌ ሽንቱን መጠጣት፣ ከታወቀ አሰሩ/ፋናዉ ምንም አይጠቅምም የሚሉትን ማመንና መቀበል አይገባም።

❷ ከቆዳ፤ ከብረት፣ ከወረቀት... ከተለያዩ ነገሮች የተሰሩትንና፤ ለአይን ፍራቻ ተብሎ በአንገት የሚንጠለጠሉትን ማንጠልጠል አይፈቀድም፡፡ ነቢዩ ሙሀመድ (አንድን ነገር ያንጠለጠለ ሰው ወደዚያ ነገር እራሱን ያስጠጋል/በዚያ ነገር ይተማመናል/፡፡ ብለዋል) ቲርሚዚ ዘግበዉታል የሚንጠለጠለዉ ነገር ቁርአንም ቢሆን እንኳ በዑለሞች መካከለ ኪላፍ ያለው በመሆኑ መተዉ ይመረጣል፡፡

❸ ማሻ አሏህ ተባረከሏህን መፃፍ ወይም የሰይፍ ምስልን መሳል ወይም የቢላዋን ወይም የዐይንን ስዕል መሳል ወይም ቁርአንን ለዚሁ ጉዳይ አስቦ መኪና ዉስጥ ማስቀመጥ ወይም አንዳንድ የቁርአን አንቀፆችን በቤት ዉስጥ ማንጠልጠል ይህ ሁሉ አይነናስን አይከላከልም፡፡ ብሎም ተማኢም/ከሚንጠለጠሉትና/ክልክል ከሆኑት ነገሮች ነው የሚሆነው፡፡

❹ በሽተኛው አላህ (ﷻ) እንደሚያድነው እርግጠኛ መሆንና ዘገየብኝ ብሎ አለማማረር ይኖርበታል፡፡ እድሜ ልክ ከተወሰደ ብቻ ነው የሚያድነው ቢባል እንኳን መደናገጥ የለበትም፡ የሰዉ ልጅ ይህን መድሃኒት እድሜ ልክህን ዉሰድ ቢባል አይደነግጥም:: ነገር ግን ሩቅያ ሲረዝምበት ይደነግጣል:: ሲቀራበት በየፊደሉ አንድ ሐሰነህ /መልካም ምንዳ/ እንዳለዉ መርሳት የለበትም፡ አንድ ሀሰነህ ደግሞ በአስር ነው የሚመነዳው:: ሰለዚህም ዱዓና ኢስተግፋር ማድረግ አለበት:: ሶደቃንም ማብዛት ፈውስ ከሚገኝባቸው ነገሮች ነው፡፡

❺ በህብረት ማንበብ ከሱና ጋር ይፃረራል፡፡ ስለዚህ የተዘገበው ሐዲስ ደካማ ነው፡፡

---

[1] ከማንኛዉም ሰይጣን፤በክፉ ከሚያስቡ ተንቀሳቃሾችና፣ ጎጅ ከሆነች ዐይን፣ ሙሉና ፍፁም በሆኑት በአሏህ ቃላቶች እጠብቃለሁ።
[2] የሰዎች ፈጣሪ የሆንከው አሏህ ሆይ! በሽታን አስወግደህ ፈውስ ትሰጥ ዘንድ እማፀነሐለሁ፣ ፈውስ ሰጪ አንተ ብቻ በመሆንህ፣ ፈውስ ያንተ ብቻ ነው፣ ህመም የማያስቀርና የማይተካ ፈውስ አድርገው።
[3] አሏህ ሆይ! የበሽታዋን ሙቀት፤ ቅዝቃዜና ህመም ከሱ አስወድለት።
[4] አሏህ በቂየ ነው ከሱ ዉጭ በሀቅ የምገዙት አምላክ የለም። በእሱ ላይ ብቻ ተመካሁ እሱም የታላቁ ዙፋን ፈጣሪ ነው።
[5] ከሚያሰቃይህ በሽታ ሁሉ፤ ከማንኛዋም ነፍስ ተንኮል፣ እንደዚሁም፣ ከምቀኛ ዐይን፣ በአሏህ ስም፣ እጠብቅሀለሁ፣ አሏህ ይፈዉስህ፣ በአሏህ ስም እጠብቅሀለሁ።
[6] በአሏህ ስም፣ ከሚሰማኝም ሆነ ከሚያሰጋኝ ጎጅ ነገር ሁሉ በአሏህ ሀያልና ችሎታ እጠበቃለሁ።

እንደዚሁም በካሴት ንባብ ብቻ መብቃቃት አይገባም፡፡ ምክኒያቱም ሩቅያ የሚያደርግ ሰው ሊያሟላው ከሚገቡ ነገሮች አንዱ ኒያ ነው:: ይህ ደግሞ በካሴት አይቻልም፡፡ ሆኖም መስማቱ ጠቀሜታ አለው፡፡ በጣም የሚያታክት ካልሆነ በስተቀር እስከሚድን ድረስ መደጋገሙ ይወደዳል፡፡ አንቀፆችን በተወሰነ ቁጥር መደጋገም/ይህን ያህል ጊዜ ነዉ የሚገባዉ ማለት በመረጃ ካልሆነ ተቀባይነት የለዉም፡፡

❻ ሩቅያ አድራጊው በቁርአን ሳይሆን በድግምት እየተጠቀመ መሆኑን የሚያመላክቱ መረጃዎች አሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ሀይማኖተኛ መስለዉ በመቅረቡ ሊያሞኙን አይገባም፡፡ አንዳንድ ሰዉ በቁርአን ይጀምርና ወዲያዉኑ ሊቀይር ይችላል፡፡ ሰዎችን ለማሞኘት መስጊድን የሚያዘወትር ሊሆንም ይችላል፡፡ ሰዉ ፊት አላህን በብዛት የሚያወሳም ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ እንዳያሞኝህ፡፡

✸ ከመተተኞች ድግምተኞች አስማተኞችና አባይ ጠንቋዩች ምልክቶች መካካል ከዚህ በታች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ✸ የበሽተኛዉን ስም ወይም የእናቱን ስም መጠየቅ፡፡ ስምን ማወቅና አለማወቅ ከህክምናው ጋር ምንም ግንኙት የሌለዉ መሆኑ እየታወቀ ✸ የበሽተኛውን ልብሶችን ከናቲራና መሰሎችን አምጡ ብሎ መጠየቅ፤ ✸ እንዲህ እንዲያ ዓይነት መልክ ያላትን እንሰሳ ለጅን እረዱ ማለት ከዚያም አልፎ ከደሙ ተቀባ ማለት፤ ✸ ምንም ትርጉም የሌላቸዉን ቃላት መፃፍ ወይም ማንበብ፤ ✸ አራት ረድፍ የታጠፉ ወረቀቶችን ፅፎ እንዲያንጠለጥል ማዘዝ፤ ✸በሽተኛው ከሰዉ ተነጥሎ ለብቻው በጨለማ ቤት እንዲያሳልፍ ማድረግ፤ ✸ ለተወሰነ ጊዜ ዉሃ እንዳይነካ ማዘዝ፤ ✸ በሽተኛው የሚቀብረው ነገር ወይም አቃጥሎ የሚሞቀው ወረቀት መስጠት፤ ✸ በሽተኛው ሳይናገር አስቀድሞ ስለሱ ማንም የማያውቃቸዉን አንዳንድ ነገሮችን ወይም ስሙን አገሩን በሽታዉን መናገር፤ ✸ ስለ በሽተኛው ሁኔታ ገና ሲገባ ወይም በስልክ ወይም በፖስታ መናገርና የመሣሠሉት ናቸው፡፡

❼ የሱና ተከታዮች ጂኖች በሰው መመሰል እንደሚችሉ ነው የሚያምኑት፡፡ መረጃዉም የአላህ እነዚያ አራጣን (ሪባን) የሚበሉ ያ በሰይጣን በመነካቱ የተነሳ የሚጥለው ሰው (ከውድቀቱ) እንደሚነሳ ብጤ እንጂ (ከመቃብራቸው) አይነሱም፡፡) የሚለዉ ነዉ። በሁሉም የቁርአን አብራሪዎች ስምምነት መሰረት ይህ አባባል በሰይጣን መጠናወት ምክኒያት የሚፈጠር እብደት ነው ብለዋል፡፡

ማጠቃለያ፡-ድግምት መኖሩ የታወቀ ነው፡፡ በሰዎች ላይ ተፅኖ ማሳደሩ በቁርኣንምሆነ በሐዲስ የተረጋገጠ ነው፡፡ ድግምት ክልል ነው ፡፡ ትልቅ ወንጀልም ነው፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ሰባት አደገኛ የሰዉን ልጅ ጎጂ የሆነ ወንጀሎችን ተጠንቀቁ ብለው ሲያስተምሩ ምንምን ናቸው ሲሏቸው በአላህ ማጋራት፤ድግምት........) ብለዋልና ነው፡፡አላህም (የገዛው ሰው በመጨረሻይቱ አገር ምንም ዕድል የሌለው መሆኑን በእርግጥ ተገንዝበዋል፡፡)

ብሏል፡፡ ድግምት ለሁለት ይከፈላል፡፡ 1) በወረቀት የሚተበተብና ድግምተኛው ሰይጣንን እንደፈለገ ለመጠቀም የሚችልበት ነው፡፡ 2) ድግምት የተደረገበትን ሰው አካል፤አዕምሮ፤ፍላጎትና ስሜት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር መድሀኒት ነው፡፡ ከዚያም የተደገመበት ሰው ጎዳዩ የተቀየረ ይመስለዋል፡፡ የቆመው የሚሄድ ፤ነገሩ ሁሉ በተገላቢጦሽ ይታየዋል፡፡ይህም ክፍል መስተፋቅር ይባላል፡፡

የመጀመሪያዉን ክፍል መተግበር ከኢስላም የሚያወጣ ክህደት ነው፡፡ምክንያቱም ሰይጣናት ለዚህ አገልግለት የሚተባበሩት በአላህ መካዱን ሲያረጋግጡ ብቻ ነዉና፡፡ ሀሁለተኛዉን መስራት ግን ከታላለቅ ወነጀሎች አንዱ ነው፡፡ ሁሉም የሚሆነው በአላህ ዉሳኔ ብቻ ነው፡፡

# ዱዓ

ሁሉም ፍጡር ወደ አላህ (ﷻ) ከጃይ ነው፡፡ እሱ ዘንድ ያለዉ ነገር ያስፈልገዋል፡፡ እሱ ደግሞ ከፍጡራኑ የተብቃቃ ነው፡፡ አላህ (ﷻ) ባሮቹን እንዲለምኑት (ጌታችሁም አለ፡፡ለምኑኝ እቀበላችኋለሁና፡፡ እነዚያ እኔን ከመገዛት የሚ ኩሩት ተዋራጆች ሆነው ገሀነምን ይገባሉ፡፡) 40፡60 በማለት እንዲለምኑት ግዴታ አድርጓል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድም (ﷺ) ኢብኑ ማጀህ በዘገበው ሐዲስ (አላህ ልመናዉን የተወን ሰው ይቆጣበታል)ብለዋል፡፡ ከዚህም ጋር አላህ (ﷻ) አገልጋዩ ሲለምነው ይደሰታል፡፡ እሱን በመለመን ችክ ባዩችንም ይወዳል፡፡ ወደ ራሱም ያቀርባቸዋል፡፡ የነቢዩ ባልደረቦችም ይህን እውነታ ተረድተውት የትኛዋንም አነስተኛ ጉዳይ አላህን (ﷻ) ከመጠየቅ አይንቁም ነበር፡፡ የትኛዉንም ጉዳይ ለአላህ እንጂ ለማንም ተራ ፍጡር አያቀርቡትም ነበር፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው (ባሮቼ ከኔ በጠየቁህ ጊዜ በላቸው - እኔ ቅርብ ነኝ፡ የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ፡፡) ባለው ቁርአናዊ አባባል መሰረት እነሱ በጌታቸው ላይ ካላቸው የሙጥኝ ባይነት፤ ወደ አላህ (ﷻ) ካላቸው ቅርበትና እሱም ወደ እነሱ ካለው ቅርበት እንጂ ሌላ አይደለም፡፡

ዱዓ በአላህ (ﷻ) ዘንድ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ነው፡፡ በአላህ (ﷻ) ዘንድ ትልቅ ቦታ አለዉ፡፡ የአላህንም ቀደር ሊመልስ/ሊቋቋም/ይችላል፡፡ የሙስሊም ዱዓ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉና እንቅፋቶች ከተወገዱለት ሁልጊዜም ተቀባይነት አለው፡፡ ዱዓ የሚያደርግ ሰው አህመድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ነቢዩ (ማንም ሙስሊም ወንጀል ወይም ዝምድናን መቁረጥ ያልተቀላቀለበት ዱዓ ካደረገ ከሶስት ነገሮች አንዱ ይሰጠዋል:: የለመነው በዚሁ በዱንያ ህይወት ሊፋጠንለት፤ ወይም ወደ አኺራ ተላልፎ ሊቀመጥለት ወይም ሊያገኘዉ የነበረዉን ክፉ ነገር በዱዓው አቅም ልክ ሊከላከልለት ነዉ፣ ሲሉ ሰሃቦችም እንግዲያውማ- እናብዛ ማለት ነው- ሲሏቸው- የአላህ ይበዛል) በማለት መልሰዉላቸዋል፡፡ የዱዓ አይነቶች ሁለት ናቸው፡፡

1) አምልኮታዊ ዱዓ-: ሶላትና ፆም የመሳሰሉት፡፡ 2) የልመናና የጥያቄ ዱዓ፡፡

ተግባሮች አንዱ ከሌላው ስለመበላለጣቸው፡፡ ቁርአን ማንበብ ወይስ ዚክር ወይስ ዱዓ ይበልጣል? ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ቁርአን ማንበብ ከሁሉም ኸይር ስራ ይበልጣል:: ከዚያም ዚክር ይከተላል:: ከዚያም ዱዓ ይለጥቃል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለው ቅድሚያ ሊሰጠው የሚችልበት ጊዜ አለ፡፡ ለምሳሌ የዐረፋ ዕለት ዱዓ ማድረግ ቁርአንን ከማንበብ ይበልጣል፡፡ ከየፈርድ ሶላቶች በኋላ ከነቢዩ በተዘገቡት ዚክሮች ላይ ማትኮር ደግሞ በዚያ ሰዐት ቁርአንን ከማንበብ ይበልጣል፡፡

✸ለዱዓ ተቀባይነት ምክኒያቶችና መስፈርቶች- እዚህ ላይ ግልፅና ድብቅ ምክኒያቶች አሉ፡፡ 1) ግልፅ ምክኒያቶች… መልካም ስራዎችን ማስቀደም፣ ለምሳሌ ሰደቃ፤ ዉዱዕ፤ ሶላት፤ ወደቂብላ መዞር፤ እጆችን ማንሳት፤ አላህን (ﷻ) በተገቢው ሁኔታ ማወደስ፤ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የአላህን (ﷻ) ስሞችና ባህሪያት እያነሱ መለመን፤ ለምሳሌ ጀነትን የሚለምን ሰው የአላህን ትሩፋት የሚያሳዩና የሚያመለክቱ ስሞችንና ባህሪያትን ማውሳት፣ ግፍ በዋለበት ላይ የሚለምን ከሆነ ደግሞ መጠቀም ያለበት ጀባር ቀሃር/ሀያሉ ጌታ/ …የመሳሰሉትን ስሞችና ባህሪያትን በማዉሳት፤ በዱዓዉ መግቢያ በመሀከሉና በመጨረሻው ላይ በነቢዩ ላይ ሶለዋት ማውረድ፤ በሰራዉ ወንጀል ማመን፤ የአላህን ዉለታ ማመስገን፤ ዱዓ ተቀባይነት ይኖረዋል የተባለባቸዉን ሰዐቶችና ቦታዎች መምረጥ ሲሆን እነሱም ብዙ ናቸው፡፡ ከብዙ በጥቂቱ

✸በቀንና በሌሊት ዉስጥ የሚገኙ፡- አላህ ወደ ቅርቢቱ ሰማይ በሚወርድበት በመጨረሻው አንድ ሶስተኛ የሌሊት ክፍል፤ በአዛንና በኢቃማ መካከል፤ ከዉዱዕ በኋላ፤ በሱጁድ ላይ እያለ ፤ ከሶላት ማሰላመት በፊት፤ ከየሶላቶች በኋላ፤ ቁርአን በሚኸተምበት ጊዜ፤ ዶሮ ሲጮህ፤ በመንገድ ላይ እያለ/ሙሳፊር ሰዉ ዱዓ፤ የተበደለ ሰው ዱዓ፤ የተቸገረ ሰው ዱዓ፤ አባት ለልጁ የሚያደርገው ዱዓ፤

ሙስሊም ወንድሙ በርቀት ለሌለው የሚያደርግለት ዱዓ ከጠላት ጋር ሲገናኙ የሚደረግ ዱዓ ናቸው፡፡ ✸ ከሳምንት ዉስጥ - የጁሙዓ ዕለት በተለይም በቀኑ የመጨረሻዋ ሰዐት ላይ፤ ✸ ከወሮች ዉስጥ - በረመዷን ወር በፊጥር ና በሱሁር ሰዐት፤ ለይለተልቀድርና፤ ✸ የዐረፋ ቀን ናቸው፡፡ ✸የተከበሩ ቦታዎችን በተመለከተ- በአጠቃላይ መስጂዶች በተለይም በመካ ከዕባ አጠገብ፣ ሙልተዘም ዘንድ፤ ካዕባ መቃሙ ኢብራሂም/የኢብራሂም መቆሚያ ዘንድ፤ ሶፋና መርዋ ላይ፤ በሐጅ ጊዜ በዐረፋ፣ በሙዝደለፋና በሚና ላይ፤የዘምዘምን ዉሃ በሚጠጡበት ጊዜና በሌሎችም ቦታዎችና ሰዐቶች ነው፡፡

1) ድብቅ ምክኒያቶች- እነኝህም፡- እውነተኛ ተውበትን ማስቀደም፤ በበደል የወሰዱትን ነገር መመለስ፤ ምግብን፤ መጠጥን፤ ልብስንና መኖሪያን ማሳመርና ከሐላል ማድረግ፤ዒባዳን ማብዛት፤ ወንጀሎችን መራቅ፤ ከሹብሃዎችም/ ከአጠራጣሪ ነገሮችም/ ሆነ ከስሜቶች ነፃ መሆን፤ በዱዓዕ ጊዜ- ዱዓን ከልብ ማድረግ፤ በአላህ (ﷻ) መተማመን፤የተስፋ ስሜትን ማዳበር፤ ወደ አላህ መጠጋት፤ ራስን ማስተናነስና በአላህ (ﷻ) መለመን ላይ ችክ ማለት፣ ሁሉን ነገር ወደ እሱ ማስጠጋትና ከሱ ሌላ ከሆኑ ሁሉ ተስፋ መቁረጥ ናቸው፡፡

ዱዓን ተቀባይነት የሚያሣጡ ነገሮች፡፡የሰው ልጅ አንዳንድ ጊዜ ዱዓ አድርጎ ተሰሚነት ያጣ ይሆናል፡፡ ወይም ይዘገይበት ይሆናል፡፡ ታዲያ የዚህ ምክኒያቶቹ ብዙ ናቸው፡፡ ከነሱም ውስጥ

✸ከአላህ ጋር ሌላን አካል መጣራት/ሽርክን መፈፀም፤ ✸ በልመናው ዉስጥ ዝርዝር ነገሮችን መጥቀስ፡- ለምሳሌ ከእሳት ጠብቀኝ የሚለው በቂ ሁኖ ሳለ ከጀሀነም ከጥበቷ፤ ከጨለማዋ ጠብቀኝ ማለትን ይመስል፤ ✸አንድ ሰው በራሱ ላይ ወይም በሌላው ላይ በግፍ ዱዓ ማድረግ፤ ✸በወንጀልና ዝምድናን በመቁረጥ ዱዓ ማድረግ፤ ✸ልመናዉን ከፈለክ አድርግልኝ ስትፈልግ ማረኝ--ብሎ መለመን፤ ✸ዱዓ አድርጌ ነበር ነገር ግን ተቀባይነት አላገኘሁም በማለት መልሱን ለማግኘት መቸኮል፤ ✸ዱዓ ከማድረግ መሰላቼት፤ ✸በተዘናጋ ልብ ዱአ ማድረግ፤

✸ ከአላህ ፊት ተገቢዉን ስርአት አለመያዝ፤ ነቢዩ አቡዳውድ እና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ (አንድን ሰው በሶላት ዉስጥ በርሳቸው ላይ ሶለዋት ሳያወርድ ዱዓ ሲያደርግ ሰምተዉት (ይህ ሰው ቸኮለ) አሉና እሱን ጠርተው ወይም ለሌላ ሰው (ማንኛውም ሲሰግድ በመጀመሪያ አላህን በማመስገንና በማወደስ ይጀምር፤ ከዚያም በነቢዩ ላይ ሶለዋት ያዉርድ፤ ከዚያም የፈለገዉን ይጠይቅ) ብለዋል፡፡ አቡዳዉድና ቲርሚዚ ዘግበዉታል። ሊሆን የማይችልን ነገር መለመን፣ ለምሳሌ በዚህች ዐለም ላይ ለዝንት ዐለም አኑረኝ ማለት፣ በግድ በግጥም መልክ ለማድረግ መልፋት ተገቢ አይደለም። ምክኒያቱም አላህ እንዲህ ብሏል (ጌታችሁን ተናንሳችሁና ተዋርዳችሁ በድብቅ ለምኑት፤ እርሱ ወሰን አላፊችን አይወድምና፡፡) ቡኻሪ በዘገቡት ሀዲስ ኢብኑ ዐባስ ስንኝ ያለበትን ዱዓ እያየህ ራቀው:: ነቢዩና ባልደረቦቻቸውን ያገኘሁት እንዲህ ያለዉን ዱዓ ሲርቁ ነው ብለዋል፡፡ድ ምፅን ከመጠን በላይ ማጉላት አይገባም። አላህ (ﷻ) እንዲህ አለ (በስግደትህ (ስታነባ) አትጮህ። በርሷም ድምጽህን ዝቅ አታድርግ በሁለቱ መካከል መንገድ ያዝ፡፡) እናታችን ዐኢሻ እንደሚሉት- ይህ የወረደው በዱዓ ምክኒያት ነው ብለዋል፡፡

በኢስላም ከሚወደዱ ነገሮች መካከል አንዱ ዱዓ የሚያደርግ ሰው በመጀመሪያ- አላህን ማመስገንና ማወደስ፤ በሁለተኛ- ለነቢዩ (ﷺ) ሶለዋት መለመን፤ ሶስተኛ- ወንጀለኛ መሆኑን ማመን፤ አራተኛ- አላህን (ﷻ) ስለፀጋው ማመስገን፤ አምስተኛ- ወደ ዱዓው ገብቶ ከነቢዩና ከሰለፎች ከተዘገቡት ዱዓዎች መካከል ብዙ ነገሮችን ሊያጠቃልሉ የሚችሉ ጠቅላይ ዱዓዎችን በተቻለ መጠን መምረጥና፤ ስድስተኛ- ዱዓዉን በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ላይ ሶለዋት በመለመን ማጠናቀቅ ነው፡፡

## ሁሉም ሰው በቃሉ ሊሓፍዛቸው የሚገቡና አስፈላጊ የሆኑ ዱዓዎች ዱዱዓዎች፡፡

| የዱዓው አጋጣሚ ሰዐቱና ቦታው | (የዱዓው አባባል) ነቢዩ ሙሐመድ{ﷺ} እንዲህ አሉ፡- |
|---|---|
| ከመተኛት በፊትና በኋላ | بِاسْمِكَ اللَّهُمَّ أَمُوتُ وَأَحْيَا (ቢስሚከላሁመ አሙቱ ወአህያ፡፡)[1] |
| ከእንቅልፍ ሲነቃ | الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي أَحْيَانَا بَعْدَمَا أَمَاتَنَا وَإِلَيْهِ النُّشُورُ<br>(አልሀምዱሊላህ አለዚ አህያና በዕደማ አማተና ወኢለይሂ ኑሹር፡፡)[2] |
| መናም ሲያይ | የሚያስደስተው መናም ሲያይ ከአላህ የተላከችለት ብስራት ናትና እሱኑ ያመስግን ለሰዎችም እንደልቡ ያውራ፡፡ የሚጠላዉን ነገር ካየ ግን ከሰይጣን በመሆኑ በአላህ ይጠበቅና ለማንም አይንገር ምንም ጉዳት ሊያመጣበት አይችልም፡፡<br>(መልካም ህልም ከአላህ ነው፡፡ ቅብዥር ደግሞ ከሰይጣን ነው፡፡የሚወደውን ነገር ያየ ሰው ለሚወደው ሰው እንጂ ለሌላ ሰው አይግለጽ፡፡) |
| ከቤቱ ሲወጣ | اللهم إني أعوذ بِك أن أضِل أو أضل، أو أزِل أو أزل، أو أظلِم أو أظلم، أو أجهل أو يجهل علي<br>አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ አን አዲለ አው ኡዶለ አው አዚለ አው ኡዘለ አው አዝሊመ አው ኡዝለመ አው አጅሀለ አው ዩጅሀል ዐለየ፡፡[3]<br>بسمِ اللّهِ تَوكّلتُ على اللّهِ لا حوْلَ ولا قُوّةَ إلا باللّهِ<br>ቢስሚላህ ተወከልቱ አለላህ ላሐውለ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላህ [4] |
| ወደ መስጊድ ሲገባ | ወደ መስጂድ ሲገባ ቀኝ እግሩን በቅድሚያ ያስገባ፡፡<br>بِسْمِ اللَّهِ وَالسَّلَامُ عَلَى رَسُولِ اللَّهِ اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي ذُنُوبِي وَافْتَحْ لِي أَبْوَابَ رَحْمَتِكَ (ቢስሚላህ ወሰላሙ ዐላ ረሱሊላህ አላሁመግፊርሊ ዙኑቢ ወፍተህሊ አብዋበ ረህመቲከ::[5] |
| ከመስጊድ ሲወጣ | ከመስጂድ ሲወጣ ግራ እግሩን በቅድሚያ ያስወጣ፡፡<br>بِسْمِ اللَّهِ وَالسَّلَامُ عَلَى رَسُولِ اللَّهِ اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي ذُنُوبِي وَافْتَحْ لِي أَبْوَابَ فَضْلِكَ (ቢስሚላህ ወሰላሙ ዐላ ረሱሊላህ፡፡ አላሁመግፊርሊ ዙኑቢ ወፍተህ ሊ አብዋበ ፈድሊከ::[6] |
| አዲስ ያገባ | بارك الله لك، وبارك عليك، وجمع بينكما في خيرٍ<br>ባረከላሁ ለከ ወባረከ ዐለይከ ወጀመዐ በይነኩማ ፊኸይር::[7] |
| የዶሮ ጩሀት ወይም የአህያ ማከላላት የሰማ | የአህያን ማናፋት በሰማችሁ ጊዜ ሰይጣን አይቶ ስለሆነ በአላህ ተጠበቁ:: የአውራ ዶሮን ጩኸት በሰማችሁ ጊዜም መላይካ አይቶ ስለሆነ የአላህን ቱሩፋት ለምኑ፡፡ በሌሊት የዉሻ ጩኸትንና የአህያና ማናፋትን ስትሰሙ በአላህ ተጠበቁ፡፡ (የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- “የዶሮ ጩኸት ስትሰሙ አላህን ከትሩፋቱ ጠይቁት ምክንያቱም መላአክ በማየቷነው (የጮኸችው)፡፡ የአህያ ማናፋት ስትሰሙ ደግሞ አሳሳች ከሆነው ሰይጣን (በአላህ) ተጠበቁ፡፡ (የጮኸው) ሰይጣንን በማየቱ ነውና፡፡”) |
| ለአላህ ብሎ እንደሚወድህ ሲነግርህ | አነስ ኢብኑ ማሊክ ሲናገሩ አንድ ሰው ከነቢዩ (ﷺ) ጋር እያለን ባጠገባቸው ሌላ ሰው አለፈ፡፡ የሆነ ሰው ይህን ሰውዬ እወደዋለሁ ብሎ ለነቢዩ (ﷺ) ሲነግራቸው ‹ነግረሀዋልን› በማለት ጠየቁት፡፡ ‹አልነገርኩትም› በማለት ሲመልስላቸው ‘ንገረው’ አሉት፡፡ ተከታትሎ ሂዶ:- ለአላህ ብዬ እወድሃለሁ፣ ሲለው:- ለእሱ ብለህ የወደድከኝ ጌታ ይውደድህ’ አለው ብለዋል፡፡) |

[1] (አላህ ሆይ! በአንተ ስም እሞታለሁ:: ነፍስም እዘራለሁ፡፡)
[2] (ሕይወታችንን (በከፊል) ከወሰደ በኋላ ነፍስ ለዘራብን እንድንነቃ ላደረገን አላህ ምስጋና ይገባው፡፡ ወደ እርሱም ተጓዦች ነን፡፡)
[3] (አላህ ሆይ! ከመጥመም ወይም ከማጥመም ከማዋረድ ወይም ከመዋረድ ከመበደል ወይም ተበዳይ ከመሆን ሰዎችን ስህተት ላይ ከመጣል ወይም እራሴ ስህተት ላይ ከመውደቅ ባንተ እጠበቃለሁ፡፡)
[4] በአላህ ስም፣ በአላህ ተመካሁ፣ ብልሐትም ሐይልም በአላህ ቢሆን እንጅ የለም።
[5] (በአላህ ስም እገባለሁ፡፡ የአላህ ሰላምና ደህንነት በአላህ መልዕክተኛ ላይ ይስፈን፡፡ አላህ ሆይ! ወንጀሌን ማረኝ፡፡ የእዝነትህን በር ክፈትልኝ፡፡)
[6] (በአላህ ስም፣ የአላህ ሰላምና ደህንነት በአላህ መልዕክተኛ ላይ ይውረድ:: አላህ ሆይ! ወንጀሌን ማርልኝ:: ፀጋህንም ለግሰኝ፡፡)
[7] (አላህ (ባለቤትህን) ይባርክልህ፡፡ አንተንም (ለርሷ)ይባርክህ፡፡ በመካከላችሁ ያለው ትስስርም መልካም ይሁን፡፡)

| | |
|---|---|
| ሙስሊም ወንድምህ ሲያስነጥሰው | ማንም ሰው ሲያነጥስ 'አልሀምዱ ሊላህ' (ለአላህ ምስጋና ይገባው፡፡) ይበል፡፡ ወንድሙም ሆነ ጓደኛው የርሀሙከላህ (አላህ ይዘንልህ)ይበለዉ፡፡ የርሀሙከላህ በተባለ ጊዜም 'የህዲኩሙላህ ወዩስሊሁ ባለኩም (አላህ ይምራህ ያለህበትን ሁኔታም ያሻሽልልህ (የልብ ፅዳት ይስጥህ) ይበል፡፡ ከሃዲ ሲያነጥስና አላህን ሲያመሰግን ደግሞ 'የህዲኩሙላህ' (አላህ ይምራህ ያለህበትን ሁኔታ ይለውጥልህ በል እንጂ "የርሀኩሙላህ" (አላህ ይዘንልህ) አትበለው፡፡ |
| የችግር ጊዜ ዱዓ | « لا إله إلا الله العظيم الحليم، لا إله إلا الله رب العرش العظيم، لا إله إلا الله رب السموات ورب الأرض ورب العرش الكريم »<br>(ላኢላሀ ኢለሏሁል ዐዚሙል ሐሊም ላኢላሀ ኢለሏሁ ረቡል ዐርሺል ዐዚም ላኢላሀ ኢለሏሁረቡ ሰማዋቲ ወረቡል አርዲ ወረቡል ዐርሺል ከሪም[1]<br>« اللهُ رَبِّي، لا أُشرِكُ بِهِ شَيئًا » አላሁ ረቢ ላኡሽሪኩ ቢሂ ሸይአን[2]<br>« ياحيُّ يا قيوم برحمتك أستغيث » ያሐዩ ያቀዩሙ ቢረህመቲከ አስተጊሱ[3]<br>« سبحان الله العظيم » ሱብሃነላሂል ዐዚም::[4] |
| በጠላት ላይ ዱዓ ለማድረግ | اللهم منزل الكتاب ومجري السحاب سريع الحساب اهزم الأحزاب، اللهم اهزمهم وزلزلهم<br>አላሁመ ሙጅሪ ሰሃብ ሙንዚለል ኪታብ ሰሪዑል ሂሳብ ኢህዚሚል አህዛብ አላሁመ ኢህዚምሁም ወዘልዚልሁም::[5] |
| በእንቅልፍ ላይ እያለ የሚደነግጥ ሰው | أعوذ بكلمات الله التامات من غضبه، ومن شر عباده ومن همزات الشياطين وأن يحضرون<br>አዑዙ ቢከሊማቲላሂ ታማት ሚን ገዶቢሂ ወዒቃቢሂ ወሚንሸሪ ዒባዲሂ ወሚን ሀመዛቲ ሸያጢን ወአን የህዱሩን::[6] |
| የሆነ ጉዳይ ሲጠነክርብህ | اللهم لا سهل إلا ما جعلته سهلا وأنت تجعل الحزن إذا شئت سهلا አላሁመ ላሰህለ ኢላ ማጀዐልተሁ ሰህላ ወአንተ ተጅዐሉል ሀዘነ ኢዛ ሺእተ ሰህላ፡፡[7] |
| ብድር ሲበዛብህ | اللهم إني أعوذ بك من الهم والحزن، والعجز والكسل، والجبن والبخل، وضلع الدين، وغلبة الرجال<br>አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነልሀሚ ወልሀዘኒ ወል ዐጅዚ ወል ከሰሊ ወል ጁብኒ ወል ቡኽሊ ወዶለኢ ደይኒ ወገለበቲ ሪጃል፡፡[8] |
| ልትፀዳዳ ስትፈልግ | اللهم إني أعوذ بك من الخبث والخبائث<br>ወደ መፀዳጃ ሲገባ (አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ኹቡሲ ወልኸባኢሲ)[9]<br>ሲወጣ ደግሞ غُفْرَانَك (ጉፍራነከ) (ማርታህን እከጅላለሁ) ይበል፡፡ |
| በሶላት ዉስጥ ላሉ ወስዋሶች | ያ ኽንዘብ የሚባለው ሰይጣን ነው፡፡ ስሜቱ ሲሰማው ከእሱ በአላህ ይጠበቅ፡፡ በግራው ሶስት ጊዜ ይትፋ፡፡ |
| ሱጁድ ላይ የሚደረጉ | اللهم اغفر لي ذنبي كله دقه وجله وأوله وآخره وعلانيته وسره አላሁመግፊርሊ ዘንቢ ኩለሁ ዲቀሁ ወጂለሁ ወአወለሁ ወአኺረሁ ወዐላኒየተሁ ወሲረሁ[10]<br>« سبحانك ربي وبحمدك اللهم اغفر لي ሱብሃነከ ረቢ ወቢሀምዲከ አላሁመግፊርሊ[11] |

[1] (ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ታላቅና ቻይ ነው፡፡ ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ የታላቁ ዐርሽ ፈጣሪ ነው፡፡ ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ የሰማያትና የምድር ፈጣሪ ነው፡፡ እንዲሁም የተከበረው ዐርሽ ፈጣሪ ነው፣ይበል፡፡)

[2] ፈጣሬና አምላኬ አሏህ ነው በእሱ ምንንም አላጋራም።

[3] ህያውና ራሱን ቻይ የሆንከው አምላክ ሁይ! በእዝነትህ እታገዛለሁ።

[4] ታላቁ ፈጣሪየ ጥራት ተገባው።

[5] (አላህ ሆይ! አንተ (ቅዱሳን) መጻሕፍትን የምታወርድ ነህ፡፡ ምርመራህም ፈጣን ነው፡፡ የጠላት ጭፍራዎችን አሸንፋቸው፤ አንቀጥቅጣቸውም፡፡) ይበል፡፡

[6] (ምሉዕ በሆነው የአላህ ንግግር ከቁጣው፣ ከቅጣቱ፣ ከባሪያዎቹ ተንኮል፣ ከሰይጣን ጉትጎታና ቀረቤታ እጠበቃለሁ፡፡)

[7] (አላህ ሆይ! አንተ ያገራኸው ነገር ካልሆነ በቀር ገር ነገር የለም አስቸጋሪ የሆነውን ነገር የምትሻ ከሆነ ገር ታደርገዋለህ ፡፡)

[8] (አላህ ሆይ የተፈቀዱ ነገሮች ብቻ እንዲበቁኝ፤ ከክልክል ነገሮችም እንድቆጠብ አድርግ፡፡ በአንተ ትሩፋትም ካንተ ውጪ ያለን አካል (ከመለመን) አድነኝ (ጠብቀኝ)፡፡

[9] (በአላህ ስም) አላህ ሆይ ከወንድ ሰይጣንና ከሴት ሰይጣን በአንተ እጠበቃለሁ)

[10] (አላህ ሆይ! ሁሉንም ወንጀሌን ማረኝ፡፡ ትንሹንም ትልቁንም፡፡ የመጀመሪያውንም የኋለኛውንም፡፡ ይፋ የሆነውንም ምስጢራዊ የሆነውንም፡፡)

[11] ጌታዬ ሆይ፣ ጥራት ይገባህ፣ ምስጋናም ይረስህ፣ አላህ ሆይ ማረኝ።

| | |
|---|---|
| ዱዓዎች | « اللهم إِني أعوذ بِرِضاك مِن سخطِك وبمعافاتِك مِن عقوبتِك وأعوذ بِك مِنك لا أحصِي تناء عليك أنت كما أَثْنَيْت عَلَى نَفْسك<br>አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢሪዷከ ሚን ሰኽጢከ ወቢ ሙዓፋቲከ ሚን ዑቁበቲከ ወአዑዙ ቢከ ሚንከ ላኡህሲ ሰናአን ዐለይከ አንተ ከማ አስነይተ ዐላ ነፍሲከ::[1] |
| በቁርአን ሱጁድ ላይ የሚደረግ ዱዓ | اللّهُمّ لَكَ سَجَدْتُ وَبِكَ آمَنْتُ وَلَكَ أَسْلَمْتُ سَجَدَ وَجْهِي لِلّذِي خَلَقَهُ وَصَوّرَهُ وَشَقّ سَمْعَهُ وَبَصَرَهُ تَبَارَكَ اللّهُ أَحْسَنُ الْخَالِقِينَ<br>አላሁመ ለከ ሰጀድቱ ወቢከ ኣመንቱ ወለከ አስለምቱ ሰጀደ ወጅሂ ሊለዚ ኸለቀሁ ወሶወረሁ ወሸቀ ሰምዐሁ ወበሶረሁ ተባረከላሁ አህሰኑል ኻሊቂን::[2] |
| ሶላት ሲጀምር | اللَّهمّ باعِدْ بيني وبين خطاياي كما باعدتّ بين المَشْرِقِ والمغْرِبِ، اللَّهمّ نقِّنِي من خَطَايايَ كما يُنقَّى الثّوبُ الأبيضُ من الدَّنَسِ، اللَّهمَّ اغْسِلْني بالماءِ والثّلجِ والبرد<br>አላሁመ ባዒድ በይኒ ወበይነ ኸጣያየ ከማ ባዐድተ በይነል መሽሪቂ ወልመግረቢ አላሁመ ነቂኒ ሚን ኸጣያየ ከማ ዩነቀ ሰውቡል አብየዱ ሚነደነሲ አላሁመ ግሲልኒ ቢልማኢ ወሰልጂ ወልበረዲ::[3] |
| በሶላት መጨረሻ | اللّهمّ إنى ظلمتُ نفسى ظلمًا كثيرا ولا يغفر الذّنوب إلا أنت فاغفر لى مغفرة من عندك وارحمنى إنّك أنت الغفور الرّحيم<br>አላሁመ ኢኒ ዞለምቱ ነፍሲ ዙልመን ከሲራ ወላ የግፊሩ ዙኑበ ኢላ አንተ ፋግፊርሊ መግፊረተን ሚን ዒንዲከ ወርሀምኒ ኢነከ አንተል ገፉሩ ረሂም::[4] |
| ከሶላት በኋላ | اللهم أعِني على ذِكرِك وشكرِك وحسنِ عِبادتِك<br>አላሁመ አዒኒ ዐላ ዚክሪከ ወሹክሪከ ወሁስኒ ዒባደቲከ[5]<br>اللّهمّ إِنّي أعوذُ بِكَ مِنَ الكُفْرِ والفَقْرِ وعذابِ القَبْرِ<br>አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነልኩፍሪ ወልፈቅሪ ወዐዛቢልቀብሪ::[6] |
| ደግ ለዋለልህ ሰው | ኸይር የተዋለለትና ላደረገለት ሰዉ ‘ጀዛከሏህ ’ያለው በማወደስ ተገቢዉን ተወጥቷል፡፡ ያኛዉም ‹ወጀዛከ› ወይም ‹ወኢያከ› በማለት ይመልስለት:: (ለፈፀምከው በጎ ስራ አላህ ምንዳ ይለግሥህ፡፡ ያለ ሰው ተገቢውን ምስጋና አቅርቧል፡፡) |
| ዝናብ ሲያይ | اللّهم صيبًا نافعا አላሁመ ሶይበን ናፊዓ (ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ)[7]<br>مطرنا بفضل الله ورحمته (ሙጢርና ቢፈሊላሂ ቢረህመቲሂ)[8]<br>ከዚያም ዱዓ ያድርግ ምክኒያቱም ዝናብ ሲዘንብ ዱዓ ማድረግ ተቀባይነት አለውና:: |
| አዉሎ ንፋስ ሲነሳ የሚደረግ ዱዓ | اللهم إني أسألك خيرها وخير ما فيها وخير ما أرسلت به وأعوذ بك من شرها وشر ما فيها وشر ما أرسلت به<br>አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ኸይረሃ ወኸየረ ማፊሃ ወኸይረ ማ ኡርሲለት ቢሂ ወአዑዙቢከ ሚንሸሪሃ ወሸረማፊሃ ወሸሪ ማ ኡርሲለት ቢሂ::[9] |
| አዲስ ጨረቃ ሲያይ | اللهم أهله علينا باليمنِ والإيمانِ والسلامةِ والإسلامِ، هلال خيرٍ ورشدٍ، ربي وربك الله<br>አላሁመ አሂለሁ ዐለይና ቢልዩምኒ ወል ኢማን ወሰላመቲ ወል ኢስላም› ‹ሂላሉ ኸይሪን ወሩሽዲን ረቢ ወረቡከሏህ›[10] |

1 አላህ ሆይ፣ በውዴታህ ከቁጣህ፣ በይቅርባይነትህ ከቅጣትህ እጠበቃለሁ። ከአንተ ባንተ እጠበቃለሁ። አንተን በተገቢው ሁኔታ ማወደስ አይቻለኝም። ራስህን እንደገለጽከው ነህ።

2 (አላህ ሆይ! ለአንተ ሱጁድ አድርጌያለሁ (በግንባሬ ተደፍቻለሁ)፤ በአንተም አምኛለሁ ለአንተም ራሴን አሳልፌ ሰጥቻለሁ፤ ፊቴ ለዚያ ለፈጠረውና ለቀረፀው መስሚያውንና መመላከቻውን ላበጀለት (ጌታ) ተደፍቷል፡፡ አፈጣጠሩን ያሳመረ አላህ የተባረከ ነው፡፡)

3 (አላህ ሆይ በኔና በወንጀሌ መካከል በምስራቅና በምዕራብ መካከል ያራራቅከውን ያክል አራርቀን፡፡ አላህ ሆይ ነጭ ልብስ ከእድፍ እንደሚፀዳ እኔንም ከኃጢያት አጽዳኝ፡፡ አላህ ሆይ! (ወንጀሌን) በቀቅ በውሃና በበረዶ እጠብልኝ፡፡)

4 (አላህ ሆይ! እኔ ነፍሴን በርካታ በደል በድያለሁ፡፡ወንጀልን ደግሞ ከአንተ በቀር የሚምር የለም፡፡ ከአንተ የሆነን ማርታ ማረኝ፡፡ እዘንልኝም፡፡ አንተ አዛኝና መሓሪ ነህ፡፡)

5 (አላህ ሆይ! አንተን ለማስታወስ ለማመስገንና በሚገባ እግገዛህ ዘንድ አግዘኝ፡፡)

6 አላህ ሆይ፣ ከክህደት፣ ከህነትና ከቀብር ቅጣት በአንተ እጠበቃለሁ።

7 (አላህ ሆይ! ጠቃሚ የዝናብ ደመና አድርገው፡፡)

8 (በአላህ ትሩፋትና እዝነት ዘነበልን፡፡)

9 (አላህ ሆይ (የዚህችን ነፋስ) በጎ ነገር እጠይቅሃሁ፡፡ ከተንኮሏም በአንተ እጠበቃለሁ.......)

10 አላህ ሆይ! ይህች ጨረቃ በጤናና በእምነት፤ በሰላምና በኢስላም፤ አንተ በምትወደውና በምታፊቅረው መልኩ በዙሪያችን እንድትበራ አድርጋት፡፡ (አንቺ ጨረቃ ሆይ!) የአንቺም የኛም ጌታ አላህ ነው፡፡)

| | |
|---|---|
| መንገደኛን ሲሸኝ | ሸኚው እንዲህ ይበል:- أَسْتَوْدِعُ اللَّهَ دِينَكَ وَأَمَانَتَكَ وَخَوَاتِيمَ عَمَلِكَ<br>አስተውዲዑላህ ዲነከ ወአማነተከ ወኸዋቲመ ዐመሊከ።[1]<br>ተጓዡም እንዲህ ይበል:- أَسْتَوْدِعُكُمُ اللَّهَ الَّذِي لاَ تَضِيعُ وَدَائِعُهُ<br>(አስተውዲዑኩሏህመ ለዚ ላተዲዑ ወዳኢዑሁ) በማለት ይመልስለት::[2] |
| የምትወደው ወይም የምትጠላው ነገር ስት መለከት:: | የሚወደውን የተመለከተ:- «الحمد لِلهِ الذي بِنِعمتِهِ تتِمِ الصالحات» አል ሐምዱ ሊላሂ ለለዚ ቢኒዕሞቲሂ ተቲሙ ሷሊሓቱ ይበል፡፡<br>የሚጠላውን የተመለከተ:- «الحمد لِلهِ على كل حالٍ» አል ሐምዱ ሊላሂ ዐላ ኩሊ ሓሉ ይበል፡፡ |
| መንገድ ሲኬድ የሚደረግ ዱዓ | « اللَّهُ أَكْبَرُ اللَّهُ أَكْبَرُ اللَّهُ أَكْبَرُ ﴿ سُبْحَانَ الَّذِي سَخَّرَ لَنَا هَذَا وَمَا كُنَّا لَهُ مُقْرِنِينَ ۞ وَإِنَّا إِلَى رَبِّنَا لَمُنْقَلِبُونَ ﴾ اللَّهُمَّ إِنَّا نَسْأَلُكَ فِي سَفَرِنَا هَذَا الْبِرَّ وَالتَّقْوَى وَمِنَ الْعَمَلِ مَا تَرْضَى اللَّهُمَّ هَوِّنْ عَلَيْنَا سَفَرَنَا هَذَا وَاطْوِ عَنَّا بُعْدَهُ اللَّهُمَّ أَنْتَ الصَّاحِبُ فِي السَّفَرِ وَالْخَلِيفَةُ فِي الأَهْلِ اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنْ وَعْثَاءِ السَّفَرِ وَكَآبَةِ الْمَنْظَرِ وَسُوءِ الْمُنْقَلَبِ فِي الْمَالِ وَالأَهْلِ »<br>አላሁ አክበር አላሁ አክበር አላሁ አክበር (ሱብሃነለዚ ሰኸረ ለና ሃዛ ወማ ኩናለሁ ሙቅርኒን ወኢና ኢላ ረቢና ለሙንቀሊቡን) አላሁመ ኢና ነሰአሉከ ፊሰፈሪና ሀዛ አልቢረ ወትተቅዋ ወሚነልዐመሊ ማተርዷ አላሁመ ሀዊን ዐለይና ሰፈረና ሃዛ ወጥዊ ዐና ቡዕደሀ አላሁመ አንተ ሷሂቡ ፊሰፈር ወልኸሊፈቱ ፊልአህል አላሁመ ኢኒአዑዙ ቢከ ሚን ወዕሳኢ ሰፈር ወከኣበቲል መንዞር ወሱኢል ሙንቀለብ ፊልማሊ ወልአህል›፡[3]<br>ከጉዞ ሲመለስም የተጠቀሰውን ፀሎት ካነበቡ በኋላ ይህን ይበል:<br>آيِبُونَ تَائِبُونَ عَابِدُونَ لِرَبِّنَا حَامِدُونَ ኣይቡን ታኢቡን ዓቢዱን ሊረቢና ሃሚዱን›[4] |
| ሲተኛ የሚደረግ ዱዓ | « اللهم أسلمت نفسي إليك وفوضت أمري إليك وألجأت ظهري إليك رهبة ورغبة إليك لا ملجأ ولا منجا منك إلا إليك آمنت بِكِتَابِكَ الَّذِي أَنْزَلْتَ وَبِنَبِيِّكَ الَّذِي أَرْسَلْتَ »<br>አላሁመ አስለምቱ ነፍሲ ኢለይከ ወፈወድቱ አምሪ ኢለይከ ወአልጀእቱ ዞህሪ ኢለይከ ረህበተን ወረግበተን ኢለይከ ላመልጃ ወላ መንጃ ሚንከ ኢላ ኢለይከ ኣመንቱ ቢኪታቢከለዚ አንዘልተ ወቢነቢዪከለዚ አርሰልት››[5]<br>« الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي أَطْعَمَنَا وَسَقَانَا وَكَفَانَا وَآوَانَا فَكَمْ مِمَّنْ لاَ كَافِيَ لَهُ وَلاَ مُؤْوِيَ » ‹‹አልሀምዱሊላሂ ለዚ አጥዐመና ወሰቃና ወከፋና ወኣዋና ፈከም ሚመን ላካፊየ ለሁ ወላ ሙዕዊ››[6]<br>« اللَّهُمَّ قِنِي عَذَابَكَ يَوْمَ تَبْعَثُ عِبَادَكَ » ‹‹አላሁመ ቂኒ ዐዛበከ የውመ ተብዐሱ ዒባደከ››[7]<br>« سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ رَبِّي بِكَ وَضَعْتُ جَنْبِي وَبِكَ أَرْفَعُهُ إِنْ أَمْسَكْتَ نَفْسِي فَاغْفِرْ لَهَا وَإِنْ أَرْسَلْتَهَا فَاحْفَظْهَا بِمَا تَحْفَظُ بِهِ عِبَادَكَ الصَّالِحِينَ » ‹‹ሱብሃነከላሁመ ረቢ ቢከ ወዶዕቱ ጀንቢ ወቢከ አርፈዑሁ ኢን አምሰክተ ነፍሲፈግፊርለሃ ወኢን አርሰልተሃ ፈህፈዝሃ ቢማ ተህፈዙ በሂ ዒባደከ ሷሊሂን››[8]<br>‹‹በእጆቹ ላይ ምራቁን በትንሹ ተፍቶ ቁል አዑዙ ቢረቢልፈለቅንና ቁል አዑዙ ቢረቢናስን አንብቦ ሰዉነቱን ያብሰዉ፡፡ በየቀኑ ሱረቱ ሰጅደህንና ሱረቱል ሙልክን ሳያነብ አይተኛ› |

[1] ሐይማ ትህን፣ አደራ ሞይነትህንና የሥራህን ፍጻሜ ለአላህ አደራ ሰጥቻለሁ።
[2] (ለአላህ አደራ ትቻችኋለሁ፡፡ (የአላህ) አደራ የሚዛነፍ አይደለምና፡፡
[3] (አላህ የታላቆች ታላቅ ነው! አላህ የታላቆች ታላቅ ነው! አላህ የታላቆች ታላቅ ነው፡፡ ይህን መጓጓዣ ያገራልን ጌታ ፍጹማዊ ነው፡፡ እኛ ይህን ለመፈፀም የምንችል አልነበርንም፡፡ የመጨረሻ መዳረሻችንም ወደ ጌታችን ነው፡፡ አላህ ሆይ! በዚህ ጉዟችን መልካም መሥራትን (ቢር) ከመጥፎ መከልከልን (ተቅዋ) የምትወደውን ነገር እንድንፈጽምም እንጠይቅሃለን፡፡ አላህ ሆይ! ይህን ጉዞአችንን አመቻችልን፤ በአጭር ጊዜም የምንቀርጠው አድርገን፡፡ አላህ ሆይ! አንተ በጉዞ ላይ ጓደኛ (ባልደረባ) ነህ፡፡ የቤተሰብም ምትክ (ዋቢ) ነህ፡፡ አላህ ሆይ! እኔ ከጉዞ ጣጣ ከአመለካከት ለውጥና በንብረትና በቤተሰብ ላይ መጥፎ ነገር ደርሶ ከመመለስ በአንተ እጠበቃለሁ፡፡)
[4] (ተውበት አድርገ፤ (አላህን) እየተገዛና ጌታችንን አመስጋኞች ሆነን ተመልሰናል፡፡)
[5] (አላህ ሆይ! ነፍሴን ላንተ ሰጥቻለሁ፡፡ ጉዳየን ሁሉ ለአንተ ሰጥቻለሁ፡፡ ፊቴንም ወዳንተ አዙሬአለሁ፡፡ ጀርባዬንም ወዳንተ አስጠግቻለሁ፡፡ ወዳንተ በመከጀልና በመፈለግ፡፡ መመለሻ፤ መጠጊያም ሆነ ነፃ መውጫ የለም- በአንተ ቢሆን እንጂ፡፡ ባወረድከው መፅሀፍ አምኛለሁ:: በላክከው ነብይም አምኛለሁ፡፡)
[6] |ያበላንና ያጠጣን፣ አለኝታ የሆነንና ያስጠጋን አላህ ምስጋና ይረሰው። አለኝታና አስጠጊ ያጣ ስንት ሰው አለ።
[7] አላህ ሆይ፣ ባሮችህን በምትቀሰቅስበት ቀን ከቅጣትህ ጠብቀኝ።
[8] አላህ ሆይ፣ ጥራትይገባህ። ጌታዬ ሆይ፣ ጎኔን ባንተ አሳረፍኩ። ባንተም አነሳዋለሁ። ነፍሴን ካስቀረሐት ማራት። ከመለስካት ደግሞ ደጋግ ባሮችህን በምትጠብቅበት ጥበብህ ጠብቃት።

| | |
|---|---|
| ወደ ሶላት ሲወጣ | اللّهمّ اجْعلْ فِي قلْبِي نورا، وفي لساني نورا، وفي سمْعِي نورا، وفي بصري نورا، ومن فوْقي نورا، ومن تحْتِي نورا، وعن يمِينِي نورا، وعن شِمالِي نورا، ومن أمامي نورا، ومن خلْفِي نورا، واجعل في نفسي نورا، وأعظم لي نورا، وعظم لي نورا، واجعل لي نورا، واجعلني نورا، اللهمّ أعطني نورا، واجعل في عصبي نورا، وفي لحمي نورا، وفي دمي نورا، وفي شعري نورا، وفي بشري نورا<br>አላሁመ ኢጅዐል ፊቀልቢ ኑረን፤ ወፊ ሊሳኒ ኑረን፤ ወፊ ሰምኢ ኑረን ፤ወፊ በሶሪ ኑረን፤ ወሚን ፊውቂ ኑረን፤ ወሚን ተህቲ ኑረን፤ ወዐን የሚኒ ኑረን፤ ወዐን ሺማሊ ኑረን፤ ወሚን አማሚ ኑረን፤ ወሚን ኸልፊ ኑረን፤ ወጅዐል ፊነፍሲ ኑረን፤ ወአዕዚምሊኑረን፤ ወዐዚምሊኑረን፤ ወጅአልሊኑረን፤ ወጅአልኒ ኑረን፤ አላሁመ አዕጢኒ ኑረን፤ ወጅዐል ፊዐሶቢ ኑረን፤ ወፊለህሚ ኑረን፤ ወፊደሚ ኑረን፤ ወፊ ሸዐሪ ኑረን፤ ወፊበሶሪ ኑረን::[1] |
| ከነገሮች መካከል የተሻለዉን ለማማረጥ የሚደረግ ዱዓ | የሆነ ጉዳይ ባሰባቹሁ ጊዜ ከፈር ሶላት ሌላ ሁለት ረከዐ ስገዱና እንዲህ በሉ፡<br>اللّهمّ إنّي أستخيرك بعلمك، وأستقدرك بقدرتك، وأسألك من فضلك، فإنّك تقدر ولا أقدر، وتعلم ولا أعلم، وأنت علام الغيوب، اللّهمّ فإن كنت تعلم هذا الأمر( ثم تسميه بعينه ) خيرا لي في ديني ومعاشي وعاقبة أمري. أو قال: عاجل أمري وآجله. فاقدره لي ويسره لي ثم بارك لي فيه، وإن كنت تعلم أن هذا الأمر شر لي في ديني ومعاشي وعاقبة أمري. أو قال في عاجل أمري وآجله. فاصرفه عني واصرفني عنه واقدر لي الخير حيث كان ثم رضني به<br>‹‹አላሁመ ኢኒ አስተኺሩከ ቢዒልከ ወአስተቅዲሩክ ቢቁድረቲከ ወአስአሉከ ሚን ፈድሊከ ፊኢነከ ተቅዲሩ ወላ አቅዲር ወተዕለሙ ወላ አዕለም ወአንተ ዐላሙል ጉዩብ፡፡ አላሁመ ፊኢን ኩንተ ተዕለሙ አነ ሀዛል አምር (እዚህ ሲደርስ ጉዳዩን ይሰይማል) ኸይረን ሊ ፊዲኒ ወመዓሺ ወዓቂበቲ አምሪ - ወይም- ዓጂሊ አምሪ ወአ ጂለህ ፈቅዱርሁ ሊ ወየሲርሁ ሊ ሱመ ባሪክሊ ፊሂ፡፡ ወኢን ኩንተ ተዕለሙ አነ ሀዛል አምር ሸረን ሊ ፊዲኒ ወመዓሺ ወዓቂበቲ አምሪ-ወይም-ዓጂሊ አምሪ ወአ ጂለህ ፈስሪፍሁ ዐኒ ወስሪፍኒ ዐንሁ ወቅዱር ሊል ኸይረ ሀይሱ ካነ ሱመ ረዲኒ ቢሂ.››[2] |
| ለሞተ ሰው | « اللهم اغفر له وارحمه وعافه واعف عنه وأكرم نزله ووسع مدخله واغسله بالماء والثلج والبرد ونقه من الخطايا كما نقيت الثوب الأبيض من الدنس، وأبدله دارا خيرا من داره، وأهلا خيرا من أهله وزوجا خيرا من زوجه، وأدخله الجنة، وأعذه من عذاب القبر ومن عذاب النار »<br>አላሁመ ግፊርለሁ ወርሀምሁ ወዓፊሂ ወዕፉ ዐንሁ ወአክሪም ኑዙለሁ ወወሲዕ ሙድኸለሁ ወግሲልሁ ቢልማኢ ወሰልጂ ወልበረዲ ወነቂሂ ሚነ ልኸጣያ ከማ ዩነቁ ሰውቡ ል አብየዱሚነ ደነሲ ወአብዲልሁ ዳረን ኸይረን ሚንዳሪሂወአህለንኸይረን ሚን አህሊሂ ወዘውጀን ኸይረን ሚን ዘውጂሂ ወጂራነን ኸይረን ሚን ጂራኒሂ ወአድኺልሁል ጀነህ ወአዒዝሁ ሚን ዐዛቢ ልቀብሪ ወዐዛቢናር[3] |

1 (አላህ ሆይ! ልቦናዬ ውስጥ ብርሃን አድግልኝ፡፡ ምላሴ ላይ ብርሃን አድርግልኝ፡፡ ጆሮዬ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ፡፡ ከበላዬ ብርሃን አድርግልኝ፡፡ ከበታቼም ብርሃን አድርግልኝ፡፡ በስተግራዬም ብርሃን አድርግልኝ፡፡ከፊቴ ብርሃን አድርግልኝ፡፡ ከኋላዬም ብርሃን አድርግልኝ፡፡ በነፍሴ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ፡፡ የገዘፈ ብርሃን ለግሰኝ፡፡ ብርሃኔን ግዙፍ አድርግልኝ፡፡ አላህ ሆይ! ብርሃንን ለግሰኝ፡፡ ሥጋዬ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ፡፡ ደሜ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ፡፡ ፀጉሬ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ፡፡ ቆዳዬ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ፡፡ አላህ ሆይ! ቀብሬ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ፡፡ አጥንቴ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ፡፡ ብርሃንን አክልልኝ፡፡ ብርሃንን አክልልኝ፡፡ ብርሃንን አክልልኝ፡፡ ከብርሃን ላይ ብርሃን ለግሰኝ፡፡)

2 (በዕውቀትህ (በጎውን ነገር) እንድትመርጥልኝ እጠይቅሃለሁ፡፡ በችሎታህም (እተማመናለሁ፤ በጎውን ምረጥልኝ)፡፡ ከታላቁ ትሩፋትህም እጠይቅሃለሁ፡፡ አንተ እንጂ እኔ ወሳኝ አይደለሁም፡፡ አንተ የሩቅን ዐዋቂ ነህ፡፡ አላህ ሆይ! ይህ ጉዳይ (ጉዳዩን ይጥቀስ) ለኔ፤ ለሃይማኖቴ፤ ለሕይወቴና ለመጨረሻዬ በጎ ከሆነ ወስንልኝ፤ አቅልልኝም፤ ረድኤትህንም ሙላልኝ፡፡ ይህ ጉዳይ ለኔ፤ ለሃይማኖቴና ለሕይወቴ መጥፎ ሆኖ የሚገኝ መሆኑን የምታውቅ በመሆኑ (መጥፎ ከሆነ አስወግደው፤ እኔንም ከርሱ አርቀኝ፤ ምንም ይሁን ምን መልካም ነገርን ወስንልኝ፤ ከዚያም እኔ (ውሳኔውን) እንድወድ (እንድቀበል) አድርገኝ፡፡ ይበል፡፡

3 (አላህ ሆይ! ማረው እዘንለት ሰላም ለግሰው፤ ይቅር በለው፤መስተንግዶዉን አሳምርለት፤መግቢያዉን አሳምርለት፤በዉሃና በበረዶ እጠበው፤ ነጭ ሸማ ከቆሻሻ እንደሚጠራ ሁሉ ከወንጀል አጥራው፡፡ ከቤቱ የተሻለ ቤትን ለዉጠው፡፡ ከቤተ ሰቡም የተሻለ ቤተ ሰብ ስጠው ጀነት አስገባው፡፡

| ጭንቀትን ለማስወገድ | « اللهم إني عبدك وابنِ عبدك وابنِ أمتك ناصيتي بِيدك ماضٍ في حكمك عدل في قضاؤك أسألك بِكل اسم هو لك سميت بِهِ نَفْسَكَ أَوْ علَّمْتَهُ أَحدًا مِنْ خَلْقِكَ أَوْ أَنْزَلْتَهُ فِي كِتَابِكَ أَوِ اسْتَأْثَرْتَ بِهِ فِي عِلْمِ الْغَيْبِ عِنْدَكَ أَنْ تَجْعَلَ الْقُرْآنَ رَبِيعَ قَلْبِي وَنُورَ صَدْرِي وجِلاءَ حزْنِي وذَهاب همي »<br>ማንም ጭንቀትን የደረሰበት ሰው እንዲህ ካለ (አላሁመ ኢኒ አብዱከ ወብኑዐብዲከ ወብኑ አመቲከ ናሴቲ ቢዲከ ማዲን ፊዩ ሑክሙከ ዐድሉን ፊዩ ቀዷኡከ አስአሉከ ቢኩሊ ኢስሚን ሆወ ለከ ሰመይተ ቢሂ ነፍሰከ አው ዐለምተሁ አሀደን ሚን ኸልቂከ አው አንዘልተሁ ፊ ኪታቢከ አዊ ስተዕሰርተ ቢሂ ፊ ዒልሚል ገይቢ ዒንደከ አን ተጅዐለል ቁርኣነ ረቢዐ ቀልቢ ወኑረ ሶድሪ ወጀላአ ሑዝኒ ወዘሃበ ሀሚ) ሀዘኑን ጭንቀቱን ያስወግድለታል፡፡በደስታም ይቀይርለታል፡፡[1] |
| --- | --- |

[1] አኋህ ሆይ! እኔ ባሪያህ ነኝ፣ የወንድና የሴት ባሮችህም ልጅ ነኝ፣ ቅንጤ በእጅህ ነው፣ ዉሳኔህ በኔ ላይ ተፈፃሚ ነው፣ ብያኔህም በኔ ላይ ፍትሀዊ ነው፣ ቁርአንን የቀልቤ መርኪያ፤ የልቦናየ ብርሃን፤የሀዘኔ መፅናኛና የጭንቀቴ ማስወገጃ ታደርግልኝ ዘንድ አንተ ራስህን በሰየምክባቸው፤ ከኪታብህ ዉስጥ ባሰፈርካቸው፤ከፉጡራንህ ለአንዱ ባስተማርካቸውና ለማንም ባልገለፅካቸው ስሞችህ እማፀንሀለሁ።

# ትርፋማው ንግድ

አላህ የመናገርን ፀጋ በመስጠት የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጡራን በላይ አስበለጠው:: ለዚህም ምላስን የመናገሪያ መሳሪያው አደረገለት:: በመሆኑም ምላስ ለደግም ሆነ ለመጥፎ ያገለግላል:: ምላሱን ለኸይር ነገር የተጠቀመበት ሰው በዱንያ ለመልካም ደስታ በአኼራም ለገነት ትልቅ ዕድል ይደርሳል:: ከዚህ ሌላ የተጠቀመበት ሰው ግን በሁለቱም ዐለም ለከፋ ዉድቀት ይዳረጋል::

ከቁርአን መቅራት በኋላ ጊዜ ሊጠፋበት የሚገባ ታላቅ ነገር ቢኖር አላህን ማውሳት (ዚክር) ነው::

የዚክርን ታላቅነት የሚያሳዩ ሐዲሶች ብዙ ሲሆኑ ከነዚህም መካከል ነብዩ ﷺ ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ (አዋጅ! ከስራዋቻችሁ ሁሉ በላጭ በጌታችሁ ዘንድ እጅግ ተመራጭ ለደረጃችሁም ከፍ አድራጊ፣ ብርና ወርቅን ከመስጠት የምትበልጥላችሁን፣ ከጠላቶቻችሁ ጋር ተገናኝታችሁ አንገት ላንገት ከመሞሻለቅ የተመረጠች የሆነችዉን ተግባር ልንገራችሁ? ሲሉ 'አዎን' ባሏቸው ጊዜ - አላህን ማውሳት- ነው::) ብለዋል::

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ደግሞ (ያ ጌታዉን የሚያወሳና ጌታዉን የማያወሳ ሰው ምሣሌዉ በህይወት እንዳለ ሰዉና በሞተ ሰው መካከል ያለው ልዩነት አይነት ነው) ብለዋል።

በሐዲሰል ቁድስ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ (እኔ ባሪያዬ ባሰበብኝ ቦታ ነኝ:: ባስታወሰኝ ጊዜ አብሬው አለሁ:: ለብቻው ካወሳኝ ለብቻዬ አወሳዋለሁ:: በሰዎች መካከል ካወሳኝም ከእነሱ በተሻሉ ቡድኖች መካከል አወሳዋለሁ:: ወደ እኔ ስንዝር ያህል ቢቀርብ እኔ ወደሱ የክንድ ያህል እቀርበዋለሁ::)ብለዋል።

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ሙፈሪዶች ቀደሙ! ሲሉ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሙፈሪዶች እነማን ናቸው? ተብለዉ ሲጠየቁ - አላህን በብዛት የሚያወሱ ወንዶችና አላህን በብዛት የሚያወሱ ሴቶች ናቸው ::)ብለዋል።

ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ አንድን ሰህባቸዉን ሲመክሩ (ምላስህ አላህን በማውሳት ከመርጠብ ሁል ጊዜም አይወገድ) ብለዋል ያሉትና ሌሎችም ሐዲሶች አሉ::

የምንዳዎች መነባበር- ቁርአንን የማንበብ ምንዳ እንደሚነባበር ሁሉ የሌሎችም መልካም ስራዎች ምንዳ እንዲሁ ይነባበራል:: ይኸዉም

1) በልብ ዉስጥ ባለው ኢማን፣ ኢኽላስ፣ ለአላህ ያለው ዉዴታና ከነሱ ጋር ተያያዥነት ካላቸው ነገሮች ጋር በተያያዘ መልኩ፣

2) በምላሱ ብቻ ሳይሆን ልብ በዚክሩ /አላህን በማዉሳቱ/ ባለው ማስተዋልና ማስተንተን ልክ :: ይህ ከተሟላ አላህ ሙሉ ወጀንሉን ያብስለታል:: ሙሉ ምንዳዉን ይሰጠዋል:: ጉድለት ያለዉም በመጠኑ ይቀነስበታል::ኢብኑ ተይሚያ የተባሉት እውቅ ዐሊም ሲናገሩ (ለልብ የዚክር አስፈላጊነት ዉሃ ለአሳ ያለዉን አስፈላጊነት ያህል ነው:: አሳ ከዉሃ ሲለይ እንዴት ነው የሚሆነው!!) ሲሉ ጠይቀዋል::

## የዚክር ጥቅሞች

✸ከአላህ ዘንድ ዉዴታን፣ ቅርበትን፣ እሱን መጠበባበቅንና መፍራትን፣ ወደሱ መመለስን ያወርሳል:: አላህን ለመታዘዝም ይረዳል::

✸ከልብ ጭንቀትን፣ ልዩ ልዩ ሀሳቦችን ያሰወግዳል:: ደስታን ያጎናፅፋል:: ለልብ ህይወት፣ ሀይልና ንፅህናን ይለግሣል::

✸በልብ ዉስጥ ዚክር ካልሆነ በስተቀር ሌላ ነገር የማይዘጋት ቀዳዳ አለች:: ዚክር ካልሆነ በስተቀር ሌላ የማያለዝባት ድርቀትም አለች::

✱ዚክር የልብ ፈውሱ፤ ሀይሉና የትኛዉም ጣዕም የማይስተካከለው ምግቡ ነው፡፡ ከዚክር መዘንጋት ደግሞ የልብ ዋነኛ በሽታው ነው፡፡
✱ዚክር ማነሱ የንፍቅና ምልክት ነው፡፡ ዚክርን ማብዛት ደግሞ የኢማንና አላህን የመውደድ ምልክት ነው፡፡ ምክኒያቱም አንድን ነገር የወደደ ሰው በየጊዜው ያነሳዋልና፡፡
✱የሰው ልጅ ከጌታው ጋር በደስታ ዘመን በማስታወስ ከተዋወቀው በችግሩ ዕለት ያውቀዋል፡፡ በተለይም በሞት ዕለት ፡፡
✱ዚክር ከአላህ ቅጣት ነፃ ለመሆን፤ የቀልብ እርካታን ለማግኘት፤ የአላህ ረድኤት እንዲወርድ ለማድረግና መላኢኮች የአላህን ምህረት እንዲለምኑልን ምክንያት ነው፡፡
✱ዚክር ከሀሜት፤ ነገር ከማዋሰድ፤ ከዉሸትና ከሌሎችም አሉባልታዎች፣ ከሌሎችም ከሚጠሉና ከሚከለከሉ ነገሮች ምላስን ለመጠበቅ ይረዳል፡፡
✱ዚክር ከዒባዳዎች ሁሉ ገር፤ ከትላልቅና በላጭ ኢባዳዎች የሆነ፣ ምንዳው ብዙ፤ የጀነት አትክልት ነው፡፡
✱አዘዉትሮ ዚክር የሚያደርግ ሰው ግርማ ሞገስን፤ የአንደበት ጥፍጥናን፤የፊት ብርሃንን፤ ይላበሳል፡፡ ዚክር በዚህች ዐለም፤ በቀብርና በቂያማ ቀንም ብርሃን ነው፡፡
✱ዚክር በሚያደርግ ሰዉ ላይ ከአላህ እዝነት ይወርድለታል:: መላኢኮች ምህረትን ይጠይቁለታል፡፡ አላህም በመላኢኮች ላይ ይፎካከርበታል፡፡
✱ከመልካም ሰሪዎች ሁሉ የበለጠው ዚክር የበዛለት ሰው ነው፡፡ ከፆመኞች ሁሉ የበለጠው በእሱ ዉስጥ ዚክር የበዛለት ሰው ነው፡፡
✱ ዚክር የቸገረን ነገር ያገራል፤ የጠናን ጉዳይ ያለዝባል፤ መከራን ያቀላል፤ ሪዝቅን ያበዛል፤ ሰዉነትን ያጠነክራል፡፡
✱ሰይጣንን ያባርራል፤ ያዋርዳል፤ ያሣፍራል፤ አላህን ያስደስታል፡፡

# በጧትና በማታ ዕለት ከዕለት የሚደረጉ ዚክሮች ዉዳሴዎች /ዱዓዎች/ ::

| | የሚባሉ ዱዓዎች | ቁጥሩና የሚባልበት ጊዜ | ትሩፋቱና ምንዳው |
|---|---|---|---|
| 1 | አየተልኩርሲ[1] | ጧትና ማታ ከንቅልፍ በፊት: ከየፈርድ ወቅቶች በኋላ:: | ሰይጣን ፈፅሞ አይቀርበዉም:ለጀነት መግባትም ምክንያት ነው:: |
| 2 | የሱረቱል በቀራህ ሁለቱ የመጨረሻ አንቀፆች[2] | ማታ አንድ ጊዜ ከመተኛት በፊት :በቤት ሁልጊዜ | ከክፉ ሁሉ ትጠብቀዋለች |
| 3 | ሱረቱል ኢክላስና ፡ሙዐዊዘተይን ምዕራፎች[3] | ጧት 3 ጊዜ ማታ3 ጊዜ : | ከሁሉ ነገር ትበቃዋለች |
| 4 | بسم الله الذي لا يضر مع اسمه شيء في الأرض ولا في السماء وهو السميع العليم<br>ቢስሚላሂ ለዚ ላየዱሩ መዐ ኢስሚሂ ሽይኡን ፊል አርዲ ወላ ፊሰማእ ወሁወ ሰሚዑል ዐሊም::<br>(በአላህ ስም (እጠበቃለሁ) ከርሱ ስም ጋር በምድርም ሆነ በሰማይ ያለ ነገር ሊጎዳ አይችልም:: ሰሚና አዋቂ ነው::) | ጧት 3 ጊዜ ማታ3 ጊዜ:: | ድንገተኛ ችግር አያጋጥመዉም:: ምንም ነገርም አይደርስበትም:: |
| 5 | أعوذ بكلمات الله التامات من شر ما خلق<br>አዑዙ ቢከሊማቲላሂ ማት ሚን ሸሪ ማኸለቅ::<br>(ሙሉ በሆነው የአላህ ንግግር ከፈጠረው ነገር ሁሉ ተንኮል እጠበቃለሁ::) | ጧት 3ጊዜ ማታ 3ጊዜና ከሆነ አገር /ቦታ /ላረፈ | ቦታቹን ከችግሮች ሁሉ ይጠበቃሉ:: |
| 6 | حسبي الله لا إله إلا هو عليه توكلت وهو رب العرش العظيم<br>ሐስቢየላህ ላኢላሀ ኢላ ሁወ ዐለይሂ ተወከልቱ ወሁወ ረቡል ዐርሺል ዐዚም::<br>(አላህ በቂዬ ነው:: ከእርሱ ውጪ ሌላ አምላክ የለም:: በእርሱ ተመክቻለሁ:: እርሱ የግዙፉ አርሽ ጌታ ነው::) | ጧት 7 ጊዜ ማታ7 ጊዜ | ያስጨነቀውን የዱንያም ሆነ የአኺራ ጉዳይ አላህ ይበቃዋል:: |
| 7 | رضيت بالله ربا، وبالاسلام دينا، وبمحمد ﷺ نبيا<br>ረዲቱ ቢላሂ ረበን ወቢልኢስላሚ ዲነን ወቢሙሐመድን ነቢየን::<br>(በአላህ አምላክነት፣ በኢስላም ሀይማኖትነት፣ በነብዩ ሙሀመድ መልዕክተኛነት ረክቻለሁ::) | ጧት 3 ጊዜ ማታ3 ጊዜ | አላህ የሚያስደስተውን ነገር ይሰጠዋል፡ |
| 8 | اللهم بك أصبحنا وبك أمسينا وبك نحيا وبك نموت وإليك النشور.<br>አላሁመ ቢከ አስበህና ወቢከ አምሰይና ወቢከ ነህያ ወቢከ ነሙቱ ወኢለይከ ኑሹር፣<br>(አላህ ሆይ በአንተ (ኃይል) ከንጋት ደርሰናል:: ምሽቱንም በአንተው (ኃይል) አሳልፈናል:: በአንተ (ኃይል) እንኖራለን:: በአንተ (ኃይልም) እንሞታለን:: ወደ አንተም ተመላሾች (ተጓገሮች) ነን::<br>ምሽት ላይ አስበህና የሚለውን አምሰይና፣ አምሰይና የሚለውን አስበህና፣ እንዲሁም ኑሹር የሚለውን መሲር በሚለወ ይተኩ:: | ጧት 1 ጊዜ : የማታዉን ማታ1ጊዜ | ይሕን በማለት የሚያነሳሳ ነብያዊ አስተምህሮት አለ:: |

[1] አላሁ ላኢላሀ ኢላሁወ ... ከነ ትርጉሙ ሩቅያ ላይ አልፏል::

﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلْحَيُّ ٱلْقَيُّومُ لَا تَأْخُذُهُۥ سِنَةٌ وَلَا نَوْمٌ لَّهُۥ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ مَن ذَا ٱلَّذِى يَشْفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذْنِهِۦ يَعْلَمُ مَا بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَمَا خَلْفَهُمْ وَلَا يُحِيطُونَ بِشَىْءٍ مِّنْ عِلْمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَ وَسِعَ كُرْسِيُّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَلَا يَـُٔودُهُۥ حِفْظُهُمَا وَهُوَ ٱلْعَلِىُّ ٱلْعَظِيمُ ﴾

[2] ሩቅያ ላይ ከነ ትርጉማቸው አልፈዋል::

﴿ ءَامَنَ ٱلرَّسُولُ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيْهِ مِن رَّبِّهِۦ وَٱلْمُؤْمِنُونَ كُلٌّ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّن رُّسُلِهِۦ وَقَالُوا۟ سَمِعْنَا وَأَطَعْنَا غُفْرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيْكَ ٱلْمَصِيرُ ﴿٢٨٥﴾ لَا يُكَلِّفُ ٱللَّهُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَا لَهَا مَا كَسَبَتْ وَعَلَيْهَا مَا ٱكْتَسَبَتْ رَبَّنَا لَا تُؤَاخِذْنَآ إِن نَّسِينَآ أَوْ أَخْطَأْنَا رَبَّنَا وَلَا تَحْمِلْ عَلَيْنَآ إِصْرًا كَمَا حَمَلْتَهُۥ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِنَا رَبَّنَا وَلَا تُحَمِّلْنَا مَا لَا طَاقَةَ لَنَا بِهِۦ وَٱعْفُ عَنَّا وَٱغْفِرْ لَنَا وَٱرْحَمْنَآ أَنتَ مَوْلَىٰنَا فَٱنصُرْنَا عَلَى ٱلْقَوْمِ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٢٨٦﴾ ﴾

[3] በተደጋጋሚ አልፈዋል::

| | | | |
|---|---|---|---|
| 9 | أصبحنا على فطرة الإسلام، وكلمةِ الإخلاصِ، ودين نبينا محمد ﷺ وملة أبينا إبراهيم ﷺ حنيفا مسلما وما كان من المشركين<br>አስበህና ዐላ ፊጥረቲል ኢስላም ወከሊመቲል ኢኽላስ ወዲኒ ነቢይና ሙሐመዲን ወሚለቲ አቢና ኢብራሂም ሐኒፈን ሙስሊመን ወማ ካነ ሚነል ሙሽሪኪን፡፡<br>(በኢስላም ተፈጥሮ ላይ ጥርት ባለው ንግግር (በላኢላሃኢለላህ) በነብያችን መሀመድ ላይ እንዲሁም በአባታችን በኢብራሂም ጎዳና ላይ ሆነን አንግተናል፡፡ (ኢብራሂም) እውተኛኛ ሙስሊም ነበሩ፡፡ ከአጋሪዎችም አልነበሩም፡፡ | ጧት 1 ጊዜ | ነቢዩ (ﷺ) በሷ ያደርጉ ነበር |
| 10 | اللّهمّ ما أصبحَ بِي مِن نعمةٍ أو بأحدٍ من خلقك فمنك وحدك لا شريك لك فلك الحمد ولك الشّكْر. وفي المَساء يقول: ما أمسى بي أو....<br>አላሁመ ማ አስበሀ ቢ ሚን ኒዕመትን አው ቢአዲን ሚን ኸልቂከ ፈሚንከ ወህደከ ላሸሪከ ለከ ፈለከልሀምዱ ወለከ ሹክር<br>አላህ ሆይ፣ በኔ ወይም ከፍጠራ ችህ በአንዱ ላይ ያነጋው ጸጋህ ካንተ ብቻ የመነጨ ነው። አጋር የለህም። ምስጋና የሚገባወ ለአንተ ብቻ ነው።<br>ምሽት ላይ አስበሃ የሚለውን አምሳ በሚለው ተክቶ ያንብብ። | ጧት 1 ጊዜ ማታ1 ጊዜ | የሀያ አራት ሰዐቱን የማመስገን ሀላፊነቱን ተወጥቷል፡፡ |
| 11 | اللّهمّ إنّى أصبحتُ أشهدك وأشهد حملةَ عرشك وملائكتك وأنبيائك وجميع خلقك بأنك أنت الله لا إله إلاّ أنت وأنّ محمدا عبدك ورسولك. وفى المساء يقول: إنّى أمسيتُ ....<br>አላሁመ ኢኒ አስበህቱ ኡሽሂዱከ ወኡሽሂዱ ሐመለተ ዐርሺከ ወመላኢከቲከ ወአንቢያኢከ ወጀሚአ ኸልቂከ ቢአነከ አንተ አሏህ ላኢላሀኢላ አንተ ወአነ ሙሐመደን ዐብዱከ ወረሱሉከ ማታ ከሆነ ኢኒ አስበህቱ ባለዉ ቦታ ላይ...አምሰይቱ የሚለዉን ተክቶ አምሣያይቱን ይበል፡፡<br>(አላህ ሆይ! አንተንና አርሽህን የተሸከሙ (ፍጡራንም) መላኢኮችህንና ፍጡራንህን ሁሉ በአጠቃላይ ሳስመሰክር አንግቻለሁ፡፡ አንተ አላህ ነህ፡፡ ከአንተ ውጪ ሌላ አምላክ የለም፡፡ አንድ ነህ፡፡ አጋር የለህም፡፡ ሙሀመድ ደግሞ ባሪያህና መልዕክተኛህ ናቸው፡፡) | ጧት 4 ጊዜ ማታ 4 ጊዜ | አራት ጊዜ ያላት አላህ ከእሳት ነፃ ያወጣዋል፡፡ |
| 12 | اللهم فاطر السموات والأرض عالم الغيب والشهادة رب كل شيء ومليكه أشهد أن لا إله إلّا أنت، أعوذ بك من شر نفسي ومن شر الشيطان وشركه وأن أقترف على نفسي سوءا أو أجرّه إلى مسلم.<br>አላሁመ ፋጢረ ሰማዋቲ ወል አርድ ዓሊሚ ልገይብ ወሺሃደህ ረቡ ኩሊ ሸይኢን ወመሊኩሁ አሽሀዱ አንላ ኢላህ ኢላ አንተ አዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ነፍሲ ወሚንሸሪ ሸይጣን ወሽርኪህ ወአን አቅተሪፈ ዐላ ነፍሲ ሱአን አው አጁረሁ ኢላ ሙስሊም<br>የሰማያትና የምድር ፈጣሪ፣ ሚስጥሩንም ይፋውንም አዋቂ፣ የሁሉም ነገር ጌታና ባለቤት የሆንከወ አላህ ሆይ፣ ከአንተ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ። ከነፍሴ ክፋት፣ ከሰይጣንና ከአጋሮቹ ክፋት እንዲሁም ከራሴ ወይም በሌላ ሙስሊም ላይ ሐጢአት ከመፈጸም በአንተ እጠበቃለሁ። | ጧትና ማታ እንዲሁም ሲተኛ | ከሰይጣን ጉትጎታ ነፃ ይሆናል፡፡ |
| 13 | للهم إنى أعوذ بك من الهم والحزن وأعوذ بك من العجز والكسل وأعوذ بك من الجبن والبخل وأعوذ بك من غلبة الدين وقهر الرجال<br>አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነ ልሀሚ ወል ሀዘኒ ወ አዑዙ ቢከ ሚነል ዐጅዚ ወል ከሰሊ ወአዑዙቢከ ሚነልጁብን ወልቡኽል ወአዑዙቢከ ሚን ገለበቲ ደይን ወቀህሪ ሪጃል፡፡<br>አላህ ሆይ፣ ከሐሳብና ከሐዘን ባንተ እጠበቃለሁ። ከአቅም ማጣትና ከስንፍናም ባንተ እጠበቃለሁ። ከፍርሃትና ከስስትም ባንተ እጠበቃለሁ። ከእዳ ጫናና ከሽንፈትም ባንተ እጠበቃለሁ። | ጧት 1 ጊዜ ማታ 1 ጊዜ | ሐሳቡንና ጭንቀቱ ይወገድለታል እዳዉም ይቃለልለታል፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 14 | اللّهمّ أنت ربّي لا إله إلا أنت خلقتني وأنا عبدك وأنا على عهدك ووعدك ما استطعت أعوذ بك من شر ما صنعت أبوء لك بنعمتك علي وأبوء لك بذنبي فاغفر لي فإنّه لا يغفر الذّنوب إلا أنت<br>አላሁመ አንተ ረቢ ላኢላሀ ኢላ አንተ ኸለቅተኒ ወአነ ዐብዱከ ወአነ ዐላ ዐህዲከ ወወዕዲከ ማስተጠዕቱ አዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ማሰነዕቱ አቡኡ ለከ ቢኒዕመቲከ ዐለየ ወአቡኡ ለከ ቢዘንቢ ፈግፊርሊ ፈኢነሁ ላ የግፊሩ ዙኑበ ኢላ አንተ::<br>(አላህ ሆይ! ፈጣሪዬ አንተ ነህ፡፡ ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም ፈጥረኸኛል እኔ ደግሞ ባሪያህ ነኝ፡፡ እኔ የአንተን ቃልኪዳንና ትዕዛዝ መሙላት አልቻልኩም ከሰራሁት ተንኮል ሁሉ በአንተ እጠበቃለሁ ማረኝ ያለ አንተ በቀር ሀጢያትን የሚምር የለም፡፡) | ጧት 1 ጊዜ ማታ 1 ጊዜ የኢስቲግፋር አለቃ የሚባለዉ ዱዓ ነዉ | እርግጠኛ ሁኖ በቀን ያለዉና በዚያው ቀን ዉስጥ የሞተ ወይም ሌሊት ብሎት በዚያው ለሊት የሞተ ሰው የጀነት ነው፡፡ |
| 15 | يا حى يا قيوم برحمتك أستغيث أصلح لى شأنى كله ولا تكلنى إلى نفسى طرفة عين<br>ያ ሐዩ ያቀዩም ቢረህመቲከ አስተጊስ አስሊህ ሊ ሽዕኒ ኩለሁ ወላተኪልኒ ኢላ ነፍሲ ጦርፈተዐይን::<br>ህያውና ራሱን ቻይ የሆንከወ አምላክ ሆይ፣ በእዝነትህ እታገዛለሁ። ጉዳዮን ሁሉ አስተካክልልኝ። ቅጽበትም ያህል ወደራሴወ አትተወኝ። | ጧት 1 ጊዜ ማታ 1 ጊዜ | ነቢዩ ለፋጢማ አደራ ያሏት ዱዓ ነው፡፡ |
| 16 | اللهم عافني في بدني، اللهم عافني في سمعي، اللهم عافني في بصري، اللهم إني أعوذ بك من الكفر والفقر، اللهم إني أعوذ بك من عذاب القبر لا إله إلا أنت<br>አላሁመ ዓፊኒ ፊ በደኒ አላሁመ ዓፊኒ ፊ ሰምዒ አላሁመ ዓፊኒ ፊበሶሪ .አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነ ል ኩፍር ወልፈቅሪ አላሁመ ኢኒ አዑዙቢከ ሚን ዐዛቢ ልቀብሪ ላኢላሀ ኢላሀ አንተ::<br>(አላህ ሆይ ለአካሌ ጤንነት ለግሰው አላህ ሆይ ጆሮዬን ጤነኛ አድርግልኝ አላህ ሆይ አይኔን ጤነኛ አድርግልኝ ካንተ ውጪ ሌላ አምላክ የለም፡፡ አላህ ሆይ ከክህደትና ከድህነት እንዲሁም ከቀብር ውስጥ ቅጣት በአንተ እጠበቃለሁ ካንተ ውጪ ሌላ አምላክ የለም) | ጧት 3 ጊዜ ማታ 3 ጊዜ | ነቢዩ በዚህ ዱዓ ያደርጉበት እንደነበር ተዘግቧል፡፡ |
| 17 | اللهمّ إنى أسألك العفو والعافية فى الدنيا والآخرة اللهمّ إنى أسألك العافية فى دينى ودنياى وأهلى ومالى، اللهمّ استر عوراتي وآمن روعاتى، اللهمّ احفظنى من بين يدي ومن خلفى وعن يمينى وعن شمالى ومن فوقى وأعوذ بعظمتك أن أغتال من تحتى<br>አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ልዓፊየተ ፊዲኒ ወዱንያየ ወአህሊ ወማሊ አላሁመ ስቱር ዐውራቲ ወኣሚን ረውዓቲ አላሁመ ኢህፈዝኒ ሚን በይኒ የደየ ወሚን ኸልፊ ወዐን የሚኒ ወዐን ሺማሊ ወሚን ፈውቂ ወአዑዙ ቢዐዞመቲከ አን ኡግታለ ሚን ተህቲ›፡፡<br>(አኋህ ሆይ! በቅርቢቱም ሆነ በመጪዋ አለም ጤንነትና ምህረትን እለምንሐለሁ አላህ ሆይ! እኔ ምህረትንና ጤንነትን እጠይቅሃለሁ፡፡ በዚህም ሆነ በተከታዩ አለም አላህ ሆይ! ምህረትንና ጤንነትን በእምነቴ በአለማዊ ህይወቴ በቤተሰቦቼ በገንዘቤ እጠይቅሃለሁ፡፡ አላህ ሆይ! ደካማ ጎኔን ሸፍንልኝ፡፡ አላህ ሆይ! ከበስተፊቴ ጠብቀኝ፡፡ ከበስተኋላዬም ጠብቀኝ፡፡ ቀኜንም ግራዬንም ጠብቅልኝ፡፡ ከስሬም ጥቃት እንዳይደርስብኝም በታላቅነትህ እጠበቃለሁ፡፡) | ጧትና ማታ | ነቢዩ እነዚህ ዱዓዎችን ጧትና ማታ ያደርጉበት እንደነበር ተዘግቧል፡፡ |
| 18 | سبحان الله وبحمده عدد خلقه ، ورضا نفسه ، وزنة عرشه ، ومداد كلماته<br>ሱብሀነላህ ወቢ ሀምዲህ ዐደደ ኸልቂሂ ወሪዷ ነፍሲሂ ወዚነተ ዐርሺሂ ወሚዳደ ከሊማቲሂ::<br>(አላህ ሆይ! እንከን አልባ ነህ ምስጋናም ላንተ ነው። በፍጡራኑ ቁጥር ልክ አንተ በወደድከው ነገር ሁሉ ልክ በአርሽህ ውበትና በንግግርህ ዘውታሪነት ልክ፡፡) | ጧት 3 ጊዜ | ከንጋቱ አንስቶ እስከ ምሳ ድረስ አላህን ለማዉሳት ከመቀመጥ ይበልጣል፡፡ |

## ከፍተኛ ምንዳ እንዳላቸው ከነቢዩ ሙሐመድ የተነገረላቸው አንደበታዊና ተግባራዊ ጉዳዮች ::

| | ተግባሩ | ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የተነገረለት መረጃው |
|---|---|---|
| 1 | ላኢላሀ ኢለሏህ ወህደሁ ላሸረከ ለሁ ለሁል ሙልኮ ወሁወ ዐላ ኩሊሸይኢንቀዲር | በቀን መቶ ጊዜ ይህን ያለ ሰው አስር ባሪያዎችን ነፃ እንዳወጣ ይቆጠራል፡፡ መቶ ኸይር ስራ ይመዘገብለታል፤ መቶ ወንጀሎች ይታበሱለታል፤በዚያ ዕለት ዕስከ ሚመሽ ድረስ ከሰይጣን ጥበቃ ይሆንለታል፡፡ እሱ ከሰራው የበለጠ ከሰራ ሰው በስተቀር የሚበልጠው የለም፡፡ |
| 2 | ሱብሐነ አላህ ወል ሐምዱ ሊላህ ላኢላሀ ወኢለሏህ ወ ሏሁ አክበር፡፡ | ወደ ሰማይ በሄድኩበት ሌሊት ኢብራሂምን አገኘቼ ነበር፡፡እናም ሙሐመድ ሆይ! ለህዝቦችህ ሰላምታ አድርስልኝና ጀነት አፈሯ መልካም፤ ዉሃዋ ጣፋጭ መሆኗንና እሷ---ስለሆነች አትክልቷ ሱብሐነ አላህ ወል ሐምዱ ሊላህ ወ ላኢላሀ ኢለሏህ ወሏሁ አክበር መሆኑን ንገራቸው፡፡ |
| 3 | ሱብሀነ አላህ አልአዚም ወቢ ሀምዲሂ /ሱብሀነ አላህ ወቢ ሀምዲሂ ሱብሀነ አላህል- ዐዚም ማለት፡፡ | ጧትና ማታ (ሱብሀነ አላህ ወቢ ሀምዲሀ) መቶ ጊዜ ያለ ሰው ወንጀሉ የባህር አረፋት ቢሃል እንኳን ይታበስለታል፡፡ እሱ እንዳለው ወይም ከእሱ በላይ ያለ ካልሆነ በስተቀር በቂያማ ዕለት ከእሱ የተሻለ አይመጣም፡፡ ሁለት ቃሎች በምላስ ላይ ቀላሎች በሚዛን ላይ ግን ከባዶች አላህ ዘንድ የተወደዱ ናቸው፡፡ እነሱም (ሱብሀነ አላህ ወቢ ሀምዲህ ሱብሀነ አላህ አል- ዐዚም) |
| 4 | ላሀውለ ወላ ቁወ ተኢላ ቢላህ | ከጀነት ድልቦች አንዱን ልንገራችሁን? አሉ። አዎ አልኳቸው:: ላሀውለ ወላ ቁወ ተኢላ ቢላህ ነው አሉ። |
| 5 | ጀነትን ጰንዲሰጠው ና ከእሳት እንዲጠብቀው መለምን | አላህን ሶስት ጊዜ ጀነትን እንዲሰጠው የለመነ ሰው ራሷጀነት ይህንን ሰው ወደ አስገባወልን ብላ ትለምንለታለች፡፡ አላህን ሶስት ጊዜ እሳትን እንዲጠብቀው የለመነ ሰው ራሷ እሳት ይህንን ሰው ከእኔ ጠብቀው ብላ ትለምንለታለች፡፡ |
| 6 | የዉይይት ማሳረጊያ / መደምደሚያ/ | በአንድ ቦታ ተቀምጦ ዛዛታው የበዛበት ከቦታው ሳይነሳ (ሱብሃነከ ላሁመ ወቢሐምዲከ አሽሀዱ አላኢላህ ኢላ አንተ አስተግፊሩከ ወአቱቡ ኢለይከ) ያለ ሰው በዚያ ቦታ ላይ የነበረዉን ሁሉ ስህተት ያብስለታል፡፡ |
| 7 | ከዋሻ ሰዎች ምዕራፍ አልፎ አልፎ ማንበብ | ከዋሻ ሰዎች ምዕራፍ አስር አንቀፅን የሐፈዘ ሰው ከደጃል ተንኮል ይጠበቃል፡፡ |
| 8 | በነቢዩ ሙሐመድ ላይ ሶለዋት ማውረድ | አንድ ጊዜ በእኔ ላይ ሶለዋት ያወረደ ሰው በእሱ ላይ አላህ አስር ጊዜ ሶለዋት ያወርድለታል፡፡ አስር ወንጀልም ይሰረዝለታል ፡፡ አስር ደረጃም ይጨመርለታል፡፡ |
| 9 | አንዳንድ የቁርአን አንቀፆችን ማንበብ | በቀንና በሌሊት አስር የቁርአን አንቀፅን ያነበበ ሰው ከዝንጉዎች አይመዘገብም፡፡ መቶ አንቀፅን ያነበበ ሰው ደግሞ ከፍርሀያኖች ይፃፋል፡፡ ሁለት መቶ ያነበበ ሰው በቂያማ እለት ቁርአን አይሟገተዉም፡፡ አምስት መቶ ያነበበ ሰው አንድኩንታል አጅር ይፃፍለታል፡፡ |
| 10 | የአዛን አድራጊች ምንዳ | የአዛን አድራጊን ድምፅ የሚሰማ ጂን፤ ሰውና ሌላም ይሁን የቂያማ ዕለት ምስክር ነው ፡፡ |
| 11 | አዛን አድራጊን መከተልና ከአዛን በኋላ ዱዓ ማድረግ | አዛንን ሰምቶ (አላሁመ ረበ ሀዚሂ ደዕወቲ ታመህ ወሶላቲልቃኢመህ ኣቲ ሙሐመደን አል ወሲለህ ወል ፈዲለህ ወብዐስሁ መቃመን መህሙደን አለዚ ወዐድተሁ) ያለ ሰው የቂያማ ዕለት የእኔን ሺምግልና ያገኛል፡፡ |
| 12 | ዉዱዕን ማሳመ ር | ዉዱዕን አሳምሮ ያደረገ ሰው ወንጀሉ ከሙሉ አከላቱ ከጥፍሩ ስር ሳይቀር ነው ተመዞ የሚወጣው |
| 13 | ከዉዱዕ በኋላ ዱዓ ማድረ ግ | ዉዱዕ አድረጎ ያሳመረ ወይም ያዳረሰና ከዚያም አሽሀዱ አላኢላሀ ኢለሏህ ወአነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ ያለ ሰው ስምንቱ የጀነት በሮች ተከፍተዉለት በፈለገው እንዲገባ ይደረጋል፡፡ |
| 14 | ከዉዱዕ በኋላ ሁለት ረከዐ መስገ ድ | ዉዱዕን አሳምሮ አድርጎ ከዚያም ሁለት ረከዓን በሙሉ ልብ የሰገደ ሰው ጀነት ለእሱ ትሆናለች፡፡ |
| 15 | ወደ መስጊዶች ጉዞን ማብዛት | ወደ ጃሚዕ መስጊድ የተጓዘ ሰው ሲሄድና ሲመጣ አንዷ እርምጃ ወንጀል ማበሻ ስትሆን ሌላዋ ደግሞ ሐሰና ይፃፍለታል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 16 | ለጁሙዐ ሶላት መዘጋጀትና መማለድ | ለጁሙዐ ሶላት ያስታጠበና የታጠበ ከዚያም የማለደና በመጓጓዣ ሳይሆን በእግሩ የሄደና ከኢማሙ ቀርቦ ሳያላግጥ ያዳመጠ በየእርምጃው ሌቱን ቁሞ ቀኑን ፁሞ እንዳሳለፈው አንድ አመት ዒባዳ ምንዳ ያገኛል። የጁሙዐ ዕለት ታጥቦና በሚችለው ፀድቶ ቅባቱን ተቀብቶ ወይም ከቤተሰቡ ሽቶ እንኳን ቢሆን ተቀብቶ ወደ መስጊድ የሄደና በሁለት ሰዎች መካከል ሳይለያይ አላህ ያለለትን ሰግዶና ኢማሙ ሲናገር ፀጥ ብሎ አዳምጦ የተመለሰ ሰው እስከሚቀጥለው ጁሙዐ ድረስ ያለዉ ወንጀል ይማርለታል። |
| 17 | የመጀመሪያን የሶላት መግቢያ ተክቢራን ማግኘት | የመጀመሪያን / መግቢያ ተክቢራን/ እያገኘ አርባቀን ጀመዐ የሰገደ ሰው ሁለት ነፃነት ይፃፍለታል። ከዕሳትና ከንፍቅናነፃይሆናል። |
| 18 | ሶላትን በጀመዐ መስገ ድ | ሶላትን በጀመዐ መስገድ ለብቻ ከመስገድ በ፳፯ ደረጃ ይበልጣል። |
| 19 | የዒሻንና የሱብሒን ሶላቶች በጀመዐ መስገድ | የዒሻን ሶላት በጀመዐ የሰገደ ሰው ግማሽ ሌሊትን ቁሞ እንዳሳለፈው ይቆጠራል።የሱብሒን ሶላት በጀመዐ የሰገደ ሰው ሙሉ ሌሊትን ቁሞ እንዳሳለፈው ይቆጠራል። |
| 20 | በአንደኛ ሶፍ ላይ ሶላት መስገድ | ሰዎች በአዛንና በአንደኛ ሰልፍ ያለው ምንዳ ምን እንደሆነ ቢያውቁና በእጣ ካልሆነ በስተቀር የማይገኝ ቢሆን እንካ እጣ ይጣጣሉ ነበር። |
| 21 | ራቲባ ሱናዎችን ጠብቆ መስገድ | በሌትና በቀን አስራ ሁለት ረከዓዎችን የሰገደ ሰው በጀነት ቤት ይሰራለታል። እነሱም አራት ከዙህር በፊት፤ሁለት ረከዐ በኋላ፤ሁለት ረከዐ ከመግሪብ በኋላ፤ሁለት ረከዐ ከዒሻ በኋላ፤ሁለት ረከዐ ከሱብሂ በፊትናቸው። |
| 22 | ትርፍ ሶላቶችን ማብ ዛት | ለአላህ ሱጁድ አብዛ፤ ምክኒያቱም ለአላህ አንድም ሱጁድ አታደርግም፣ በየ ሱጁዱ ደረጃህን ያሳደገና ወንጀልክንም የሰረዘልህ ቢሆን እንጂ። |
| 23 | የሱብሂ ዋናው ሶለትና ሱናው ሶላ ት | የሱብሂ ሱናዎች ከዱንያና በሷዉስጥ ካሉ ነገሮች ሁሉ ይበልጣሉ። የሱብሂን ግዴታዊ (ፈርዽ) ሶላትን የሰገደ በአላህ ጥበቃ ስር ነው። |
| 24 | የአዱሓ ሶላት | በእያንዳንዳችሁ አካል ላይ ሶደቃ አለባችሁ ። አንዲት ሱብሀነላህ ሶደቃ ናት። አንዲት አልሐምዱሊላህ ሶደቃ ናት። አንዲት ላኢላሀ ኢለሏህ ሶደቃ ናት። አንዲት አላሁ አክበር ሶደቃ ናት። በደግ ነገር ማዘዝ ሶደቃ ናት። ከመጥፎ ነገር መከልከል ሶደቃ ናት። ነገር ግን ከዚህ ሁሉ የአዱሃ ሁለት ረከዐ ሶላቶች ይበቁታል። |
| 25 | አላህን እያወሳ በመስገጃው ላይ የተቀመጠ | ከመስገጃው ላይ ተቀምጦ ዉዱዕ ሳይፈታ ያለ ሰጋጅ ሁሉ መላይኮች አላሁመ ግፊር ለሁ አላሁመ ርሀምሁ ይሉለታል። |
| 26 | ሱብሂን በጀማዐ ሰግዶ ፀሐይ ዕስከምትወጣ ድረስ በዚክር ቆይቶ ሁለት ረከዐ መስገድ | ሱብሂን በጀማዐ ሰግዶ ፀሐይ እስከምትወጣ ድረስ በዚክር ቆይቶ ሁለት ረከዐ የሰገደ ሰው ሙሉ ሐጅና ሙሉ ዑምራ እንዳደረገ ይቆጠራል። |
| 27 | ሌሊት ለሶላት የነቃና ሚስቱን ያነቃ | ሌሊት ለሶላት የነቃ፤ሚስቱን ያነቃና አብረው ሁለት ረከዐ የሰገዱ ከሆነ አላህን ከሚያወሱት ዉስጥ ይመደባሉ። |
| 28 | ሌሊት ለመስገድ አስቦ እንቅልፍ የጣለው ሰው | ሌሊት መስገድ አስቦ እንቅልፍ የጣለው ሰው የሶላቱ ምንዳ ይፃፍለታል። እንቅልፉም እንደ ሶደቃ ይቆጠርለታል። |
| 29 | ገበያ የገባሰው የሚያደርገው ዚክር | ላኢላሀ ኢለሏህ ወህደሁ ላሸረከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱወሁወ ዩህዪ ወዩሚቱ ወሁወ ዐላ ኩሊሸይኢንቀዲር..}ያለ ሰው ሚሊዮን ሞልካም ስራ ይፃፍለታል።።ሚሊዮን ወንጄል ይታበከለታል።።ሚሊዮን ደረጃም ይጨምርለታል።። |
| 30 | ከሶላት በኋላ ሱብሃነ አላህ ወል ሀምዱ ሊላህ ወላሁ አክበር 33 ጊዜ ያለና በመጨረሻም ላኢላሀ ኢለሏህ ማለት | ከሶላት በኋላ ሰላሳ ሶስት ጊዜ ሱብሐነ አላህ፤ ሰላሳ ሶስት ጊዜ አልሐምዱሊላህ ሰላሳ ሶስት ጊዜ አላሁ አክበር ያለና መቶኛ ላኢላሀ ኢለሏህ ያለ ሰው ወንጀሉ የባህር ማዕበል ያህል እንኳን ቢሆን ይማርለታል። |
| 31 | ከሶላት በኋላ አየተል ኩርሲን ማንበብ | ከየሶላቱ በኋላ አየተል ኩርሲን ያነበበ ሰው ጀነት ለመግባት ሞት ብቻ ነው የሚከለክለው። |
| 32 | በሺተኛን ማየት | አንድ ሙስሊም ሙስሊም ወንድሙን ከጎበኜ አንድ ሺህ መላይካ እስከ ማታ ድረስ ዱዓ ያደርጉለታል። ማታ ካየው ደግሞ አንድ ሺህ መላይካ እስከ ጧት ድረስ ዱዓ ያደርጉለታል። |

| | | |
|---|---|---|
| 33 | ችግር የደረሰበት ሰው ያየ | አልሐምዱ ሊላህ አለዚ ዓፉኒ ሚመብተላከ ቢሂ ወፈዶለኒ ዐላ ከሲሪን ሚመን ኸለከ ተፍዲላ )ያለ ሰው ያችግር አይነካዉም:: |
| 34 | ችግር የደረሰበትን ያፅናና | ችግረኛን ያፅናና ሰው ተመሳሳይ ምንዳ አለው:: |
| 35 | በጀናዛ ላይ ሰግዶ እስከምት ቀበር ድረስ የተከተላት | በጀናዛ አሸኛኜት ላይ ተገኝቶ እስኪሰገድበት የቆየ ሰው አንድቂራጥ ምንዳ አለው:: ሰግዶ እስከሚቀበር ድረስ የተከተለ ሰውሁለት ቂራጥ አለው:: |
| 36 | ለአላህ ብሎ መስጊድ የገነባ ወይም በግንባታ ላይ የተባበረ | የድንቢጥ ቤት የሚያህል እንኳን ለአላህ ብሎ መስጊድ የገነባ ሰው በጀነት ቤት ይሰራለታል:: |
| 37 | መስጠት | በየቀኑ ሁለት መላይካዎች ይወረዱና አንዱ ጌታየ ለሰጠ ሰው ምትክ ስጠው:: ሌላኛው ደግሞ የከለከለን አጥፋበት እያሉ ይለምናሉ:: |
| 38 | ሰደቃ መስጠት | ሶደቃ ገንዘብን አታጎልም:: አላህ (ﷻ)ይቅር ባይን ባሪያዉን ክብር እንጂ ሌላ አይጨምርለትም:: ለአላህ ብሎ የተናነሰ ሰው አላህ ከፍ ያደርገዋል:: (አንድ ዲርሀም አንድ ሺ ዲርሀምን ቀደመች:: ሲሉ እንዴት ሁኖ ነው የአላህ መልእክተኛ? ብለው ሲጠይቋቸው አንድ ሰው ሁለት ዲርሀሞች ነበሩትና አንዱን ሰጥቶ ሁለተኛዉን ለራሱ ያስቀረ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ብዙ ንብረት ያለውና ከዚያም ንብረት ዉስጥ አንስቶ አንድ ሺ ዲርሀም የሰጠ ማለት ነው አሉ:: |
| 39 | ያለ ምንም ጥቅም ማበደር | ሁለት ጊዜ ሙስሊም ወንድሙን ያለምንም ጥቅም ያበደረ ሰው አንድ ጊዜ በነፃ እንደሰጠው ይቆጠራል:: |
| 40 | ድህነት ያለበትን ባለዳ ሰው ማለፍ | ሰዎችን የሚያበድር አንድ ሰው ነበርና ለሰራተኛው:- የቸገረው ሰው ካጋጠመህ እለፈው:: እሱን በማለፋችን አላህ ቢያልፈን፣ ብሎ ነበርና ከጌታው ጋር ተገናኝቶ አለፈው:: |
| 41 | በጂሃድ ላይ ሁኖ አንዲት ቀን መፆም | በጂሃድ ላይ እያለ አንድ ቀን የፆመ ሰው አላህ ፊቱን ከእሳት የሰባ አመት መንገድ የሚያስከድ ያህል ያርቅለታል:: |
| 42 | በየወሩ ሶስት ቀንንና የዐረፋንና የዐሹራን ቀናት መፆም | በየወሩ ሶስት ቀኖችንና ረመዷንን ወር የፆመ ሰው እድሜዉን ሙሉዉን እንደፆመ ነው:: (ስለ ዐረፋ ቀን ፆም ተጠይቀው ያለፈዉንና የመጪዉን አመት ወንጄል ያስምራል ብለዋል::) ስለ ዐሹራእ ቀን ፆም ተጠይቀውም ያለፈዉን አመት ወንጄል ያስምራል ብለዋል::) |
| 43 | ከሼዋል ስድስት ቀኖችን መፆ ም | ረመዷንን ፁሞ ከሸዋል ስድስት ቀንን የፆመ ሰው እድሜዉን ልክ እንደ ፆመ ነው ብለዋል:: |
| 44 | የተራዊህን ሶላት ከኢማሙ ጋር ዕስከሚያበቃ ድረስ መስገድ | ኢማሙ እስከሚያበቃ ድረስ አብሮ የሰገደ ሰው ሌቱን ሙሉ ቁሞ እንዳደረ ሰው ይቆጠርለታል:: |
| 45 | ትክክለኛ ሐ ጅ | ሐጅ አርጎ ጸያፍ ድርጊት ያልፈጸመ ሰው እናቱ በወለደችው ዕለት እንደነበረ ንፁህ ይሆናል:: (ትክክለኛ ሐጅ ከጀነት በስተቀር ምንዳ የለዉም ::) |
| 46 | በረመዷን ወር ዑምራን መፈፀ ም | በረመዷን ዑምራ ማድረግ ሐጅ እንደማድረግ/ከእኔ ጋር ሐጅ እንደማድረግ/ ይቆጠራል:: |
| 47 | በመጀመሪያዎቹ የዙልሒጃ ወር አስርት ቀናት የሚሰራ መልካም ተግባር | ከእነዚህ አስር ቀኖች የበለጠ መልካም ስራዎች አላህ ዘንድ ተወዳጅ የሚሆኑበት ቀን የለም:: ጂሃድም ቢሆን:: ያአላህ መልክተኛ ከእነ ገንዘቡ ለጂሃድ ወጥቶ ምኑም ሳይመለስ የቀረ ካልሆነ በስተቀር ጂሃድም ቢሆን:: ብለዋል:: |
| 48 | የኡድ ሂያ ዕርድ | ሱሃቦች ነቢዩ እኒህ ኡድሂያዎች ምንድን ናቸው ሲሏቸው የአባታችሁ የኢብራሂም ሱና ነው አሏቸው:: እኛ በእሷ ምን አለን ሲሏቸው በፀጉሯ ልክ ሐሰና አላችሁ አሏቸው:: በሱፉስ ምን አለን ያአላህ መለክተኛ ሲሏቸው በሱፉ ፀጉርም ልክ ሐሰና አላችሁ አሏቸው:: |
| 49 | የዐዋቂ ሰው ክብርና መዐረግ | አዋቂ ሰው ካለ እውቀት ዒባዳ ከሚያደርግ ሰው ላይ ያለው ብልጫ እኔ ከእናንተ መካከል አነስተኛ ከምትሉት ሰው ጋር ያለኝን ብላጫ ያህል ነው:: ከዚያም ነቢዩ (አላህ፤መላይኮች፤የሰማይና የምድር ባለቤቶች በዋሻዋ ዉስጥ ያለች ጬጯን እንኳን ሳትቀር ሰዎችን ኸይር ለሚያስተምር ሰው ዱዓ ያደርጋሉ) ብለዋል:: |

| | | |
|---|---|---|
| 50 | በአላህ ዲን ላይ መሰዋትን በትክክል መመኜት /አላህን መለመን/ | በትክክል በሸሀዳ መሞትን የተመኜ ሰው በቤቱ በፍራሽ ላይ እንኳን ቢሞት የሸሂድ ማእረግ ይሰጠዋል። |
| 51 | አላህን ፈርቶ ማልቀስና ለአላህዲን ጥበቃ መቆም | ሁለት አይኖች እሳት አይነካቸዉም። እነሱም አላህን ፈርታ ያለቀሰች አይንና ለጅሃድ ዘብ ስትጠብቅ ያደረች አይን። |
| 52 | ትናንሽ ልጆች የሞቱበት ሰው | ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ሶስት ልጆች የሞቱበት ሙስሊም አላህ ጀነት ያከገባዋል። |
| 53 | አይኑ ጠፍቶበት የታገሰ ሰው | አላህ:- በሁለት ወዳጆቹ(አይኖቹ) የፈተንኩትና የታገሰ ባሪያየ በሁለቱ ምትክ ሁለት ጀነቶች እለዉጠውአለሁ፣ ብሏል። |
| 54 | ለአላህ ብሎ አንድን ወንጀል የተወ ሰው | አንድን ነገር አላህን ፈርተህ አትተዉም፣ በእሱ የተሻለን ነገር የለወጠህ ብትሆን እንጂ። |
| 55 | ምላስንና ብልትን መጠበቅ | በሁለት ፂሞቹና በሁለት ጭኖቹ መካከል ያሉት አካሎችን ለመጠበቅ ዋስትና የገባልኝ ሰው እኔ ደግሞ ለጀነት ዋስ እሆነዋለሁ። ምላስንና ብልትን የጠበቀ ማለት ነው። |
| 56 | ወደ ቤት ሲገባም ሆነ በምግብ ጊዜ ቢስሚላህ ያለ | ወደቤቱ ሲገባና ሲመገብ አላህን ያወሳ ሰው ሰይጣን (ለባልንጀሮቹ):- ማደሪያም ሆነ እራት የላችሁም ይላል። ሲገባ አላህን ካላወሳ ደግሞ:- ማደሪያ አግኚታችኋል ይላል።ሲመገብም አላህን ካላወሳ:- እራትም አግኚታችኋል ይላል። |
| 57 | ከምግብ፣ ከመጠጥና ከአዲስ ልብስ በኋላ አልሀምዱ ሊላህ በማለት አላህን ያመሰገነ | ምግብን በልቶ(አልሐምዱሊላሂለዚ አጥዐመኒ ሀዛ ወረዘቀኒሂ ሚን ገይሪ ሐውሊን ሚኒ ወላቁወህ) ያለ ሰው ያለፈ ወንጀሉ ይሰረዝለታል። የሚጠጣ ነገር ጠጥቶ (አልሐምዱሊላሂለዚ ሰቃኒ ሀዛ-፣ አዲስ ልብስ ሲለብስ (አልሐምዱሊላሂለዚ ከሳኒ ሀዛ) ያለ ሰውም እንዲሁ። |
| 58 | አላህ የስራዉን ቁብደትእ ንዲያቃልልለት የፈለገ | ፋጢማ:- ሰራተኛ ይሰጠኝ፣ ብላ ነቢዩን ስትጠይቅ ለእሷና ለዐሊይ:- (ከጠየቃችሁኝ የሚሻል ነገር ልንገራችሁን? ከመኚታችሁ ላይ ስትሆኑ ሰላሳ አራት ጊዜ አላሁ አክበር፤ ሰላሳ ሶስት ጊዜ ሱብሀነላህ፤ሰላሳ ሶስት ጊዜ አልሐምዱሊላህ፤ ማለት ከሰራተኛ ይሻላችኋል።) አሏቸው። |
| 59 | ከግብረ-ስጋ ግን ኙነትን በፊት ዱዓ ያደረገ | ከሚስቱ ጋር ግንኙነት ማድረግ ሲፈልግ (ቢስሚላህ አላሁመ ጀኒብና ሸይጧን ወጀኒቢ ሸይጧን ማረዘቅተና) ያለ በዚያ ዕለት ልጅ ቢፈጠር ሰይጣን ለዝንት ዐለም አያጠቃዉም። |
| 60 | ሴት ልጅ ባሏን ማሰደሰት | አምስት አወቃት ሶላቷን የሰገደች፤ወሯን የፆመች፤ ብልቷን የጠበቀችና ባሏን የጠበቀች ሴት ከጀነት በሮች በፈለገሺው በር ግቢ ትባላለች።(ባሏ እንደተደሰተባት የሞተች ሴት ጀነት ትገባለች) |
| 61 | ዝምድናን መቀጠል | ሲሳዩ እንዲሰፋለትና ፋናው እንዲቆይለት የፈለገ ሰው ዝምድናን ይቀጥል። |
| 62 | የቲምን ማሳደግ | እኔና የቲም አሳዳጊ በጀነት ዉስጥ እንደዚህ ነን ብለው አመልካች ጣታቸዉንና መካከለኛ ጣታቸዉን በአንድ አድርገው አሳዩ። |
| 63 | ጥሩ ስነ ምግባር | (ሙዕሚን በጥሩ ስነ ምግባር የፆመኛንና የትክክለኛ ሰጋጅን ምንዳ ያገኛል።) (ባህሪያቸዉን ለሚያሳምሩ ሰዎች በከፍተኛው የጀነት ማዕረግ ዉስጥ ቤት እንዳላቸው አብስር።) |
| 64 | ለህዝቦች ማዘን | አላህ ከባሮቹ ሁሉ የሚወደው ሰው አብዛኞችን ነው። በምድር ላይ ያሉትን ሕዝቦች እዘኑላቸው። በሰማይ ያለው ያዝንላችኋል። |
| 65 | ለሙስሊሞች ጥሩ ነገሮችን መውደድ | ከናንተ አንዳችሁ ለራሱ የሚወደዉን ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ አመነ አይባልም። |
| 66 | አይን አፋርነት | እይነ አፋርነት ኸይር ይዞ ነው የሚመጣው።) (እይነ አፋርነት ከእምነት ነው።) (አራት ነገሮች ከነቢያት ሱና ናቸው ሽቶ፤እይነአፋርነት፤ ሲዋክና ጋብቻ) |
| 67 | በሰላም መቅደም | አንድ ሰው ወደ ነቢዩ መጥቶ:- አሰላሙ ዐለይኩም ሲል (አስር) አሉ። ሌላ ሰው መጥቶ:- አሰላሙዐለይኩም ወረህመቱላህ ሲል (ሀያ) አሉ። ሌላ ሰው መጥቶ:- አሰላሙ ዐለይኩም ወረህመቱላህ ወበረካቱሁ ሲል (ሰለሳ) አሉ። (ምንዳ ማለት ነው።) |

| | | |
|---|---|---|
| 68 | ሲገናኙ መጨባበጥ | ሁለት ሙስሊሞች ተገናኝተው አይጨባበጡም፣ ከመለያየታቸው በፊት ወንጀላቸዉን የተማሩ ቢሆን እንጂ፡፡ |
| 69 | የሙስሊም ወንድሙ ክብር ሲነካ መከላከል | ከወንድሙ ክብር የተከላከለ ሰው አላህ የቂያማ እለት ከፊቱ እሳትን ይከላከልለታል፡፡ |
| 70 | መልካም ሰዎችን መውደድና ከዕነሱ ጋር መቀማመጥ | (አንተ ከወደድከው ጋር ነህ) አነስ እንደሚሉት የነቢዩ ሱሃቦች በዚህ ሐዲስ የተደሰቱትን ያህል በምንም ተደስተው አያውቁም፡፡ |
| 71 | ለአላህ ክብር ሲሉ የተዋደዱ ሰዎች | አላህ (ለእኔ ብለው የተዋደዱ ሰዎች የብርሃን ወንበር አላቸው፡፡ ነቢዮችም ሆኑ ሰምአታት የሚቀኑባቸው ናቸው፡፡) |
| 72 | ለሙስሊም ወንድሙ ዱዓ ማድረግ | ለወንድሙ በርቀት ላይ እያለ ዱዓ ያደረገለት ሰው ለእሱ የተወከለው መላይካ፡- ኣሚን ለአንተም ተመሳሳዩ ይገባህ፣ ይለዋል፡፡ |
| 73 | ለወንድምሆነ ለሴት አማኞች ምህረትን መለመን | ለወንድም ሆነ ለሴት አማኞች ምህረትን የለመነ ሰው በያንዳንዱ አማኝ ሰው አንዲት ሐሰነህ አለችው፡፡ |
| 74 | ከመንገድ ላይ እንቅፋትን ማስወገድ | አንድ ሰው፣ ሰዎችን በመንገድ ላይ ስቸግር የነበረችን ዛፍ በመቁረጡ ምክኒያት ብቻ በጀነት ዉስጥ ሲደሰት አየሁት፡፡ |
| 75 | ክርክርንና ዉሸትን መተው | በእውነትም ቢሆን ክርክርን ለተወ ሰው በጀነት ዳርቻ ላይ ቤት እንደሚኖረው ዋስትና እገባለሁ፡፡ እየቀለደም ቢሆን ዉሸትን ለተወ ሰው በጀነት ውስጥ ቤት እንደሚኖረው ዋስትና አገባለሁ፡፡ |
| 76 | ቁጣዉን የተቆጣጠረ ሰው | መተግበር አየቻለ ቁጣዉን የተቆጣጠረ ሰው አላህ የቂያም ቀን በህዝቦች መካከል ጠርቶ ከሁሩል ዐይኖች ያማርጠዋል፡፡ |
| 77 | ኸይር የተወራለት ሰው | ኸይር ያወራችሁለት ሰው ጀነት ለእሱ ናት፡፡ መጥፎ ያወራችሁበት ሰው ደግሞ እሳት ለእሱ ናት፡፡ ምክኒያቱም እናንተ በምድር ላይ የአላህ ዋቢች ናችሁና፡፡ |
| 78 | የሙስሊምን ችግር ያቃለለ፣ የደበቀና የተባበረው | ከሙስሊሞች የዱንያ ችግር ያቃለለ ሰው አላህ ከመጭው አለም ችግሩ ያቃልለታል፡፡ በተቸገረ ላይ ያግራራ ሰው በዱንያም ሆነ በመጭው አለም ያቃልልለታል፡፡ የሙስሊምን ነውር የደበቀ በዱንያም ሆነ በመጭው አለም አላህ ነውሩን ይደብቅለታል። አንድ ሰው ሙስሊም ወንድሙን እስከተባበረ ድረስ አላህ እርሱን ከማገዝ አይወገድም፡፡/አይቆጠብም/ |
| 79 | ጭንቀቱ አኺራው የሆነ | የሆነለት ሰው ክብረቱን በልቡ ዉስጥ ያደርግለታል፡፡ ሐሳቡን ይሰበስብለታል፡፡ ዱንያም በግዷ ትመጣለታለች፡፡ |
| 80 | ፍትሃዊ አስተዳዳሪ/መልካም ወጣት/ከመስጂድ ጋር መቆራኘ ኃት/ለአላህ ብሎ መውደድ/ | አላህ የእሱ ጥላ አንጂ ሌላ ጥላ በሌለበት ጊዜ ሰባት ሰዎችን በጥላው ስር ያዉላቸዋል፡፡ ፍትሃዊ አስተዳዳሪ፤ በጌታው አምልኮ ተኮትኩቶ ያደገ ወጣት፤ልቡ ከመስጊድ ጋር የተሳሰረ ሰው፤ ለአላህ ብለው የተዋደዱ፤ ቆንጆና ባለስልጣን ሴት የጠየቀችውና እኔ አላህን እፈራለሁ ያለ ሰው፤ ቀኝ እጁ የሚሰጠዉን ግራ እጁ እስከማያውቀው ድረስ ስጦታዉን የሚደብቅ፤ ብቻዉን ባለበት አላህን አስታውሶ እንባው የረገፈለት ሰው ናቸው፡፡ |
| 81 | ኢስቲግፋር ማብዛት | ኢስቲግፋር ያበዛ ሰው ለሚያጣብበው ሁሉ መውጫ ያደርግለታል፡፡ ለሚያስጨንቀው ሁሉ መፍትሄ ይሰጠዋል፡፡ ካላሰበ በኩል ይመግበዋል/ሲሳይን ያመጣለታል፡፡ |

# እንዳንሰራቸው የተከለከሉ ነገሮች፡፡

| ተ/ቁ | የተከለከሉ ነገሮች | ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የተዘገበ ው ትክክለኛው የሐዲስ መረጃ |
|---|---|---|
| 1 | ይዉልኝና ይስሙልኝ | ለይስሙልኝ የሰራ ሰው አላህ ስራዉን ያሰማበታል፡፡ ለይዩልኝ የሰራ ሰው ሚስጥሩን ያወጣበታል፡፡ |
| 2 | ላዩን አሳምሮ ውስጡ የተበላሸ | በቂያማ እለት የቲሃማን ጋራ የሚያህል ነጫጭ በጎ ተግባርን ይዘው የሚመጡ ከዚያም አላህ እንደተበተነ ትቢያ የሚያበንባቸው ክፍሎች አሉ፡፡ ሲሉ ሰውባን እነሱን ሳናውቅ እንዳንመስል እነማ እንደሆኑ ይግለፁልን ሲላቸው እነሱ ከእናተው የተወለዱ የእናተው ናቸው፡፡ ሌሊት እናተም እንደምትቆሙ እነሱም የሚቆሙ ግን አላህ የከለከለውን ነገር ብቻቸውን ሲያገኙት የሚደፍሩ ናቸው ብለዋል፡፡ |
| 3 | ኩራት | በልቡ ቅንጣት ታህል ኩራት ያለበት ሰው ጀነት አይገባም፡፡ ኩራት ማለት እውነትን ማውገዝና ሰዎችን መናቅ ነው፡፡ |
| 4 | ልብስ ማስረዘም | ሸርጥንም ቀሚስን እና ጥምጣምን ያጠቃልላል፡፡ አንድን ነገር ለኩራ ብሎ የጎተተ የቂያማ ዕለት ወደ እሱ አይመለከትም፡፡ |
| 5 | ምቀኝነት | ምቀኝነትን ተጠንቀቁ። እሳት እንጨትን እንደሚበላው ሁሉ ምቀኝነት ኸይር ስራን ይበላል፡፡ |
| 6 | ወለድ መብላት | ነቢዩ ወለድ በይንና አብይን ረገሙ፡፡ «እያወቀ በወለድ የሚበላት አንዷት ዲርሀም ቅጣት ከሰላሳ ስድስት ዝሙት ቅጣት የበረታ ነው፡፡» አሉ። |
| 7 | አስካሪ መጠጦችን ማዘውተር | አምስት ነገሮችን የሚሰራሰው ጀነት አይገባም፡፡ አስካሪ ነገር የሚያዘወትር፤ በጥንቆላ የሚያምን፤ ዝምድናን የሚቆርጥ፤ ጠንቋይ፤ የሚመፃደቅ፡፡ |
| 8 | ዉሸት | ሰወችን ለማሳቅ ብሎ ዉሸት የሚያወራ ሰው ወዩለት፡፡ |
| 9 | መሰለል | የሚጠሉትን ወይም የሸሹትን ሰዎች ወሬ ያዳመጠ ሰው የቂያማ ዕለት ነሐስ በጆሮው ላይ ይቀለጥበታል፡፡ |
| 10 | ስዕል መሳል | (የቂያማ ቀን ቅጣት የሚበረታባቸው ሰዐሊያን ናቸው) ፡፡ (ስዕል ወይም ዉሻ ካለበት ቤት መላይካ አይፉባም፡፡) |
| 11 | ነገር ማዋሸክ/ማዋሰድ/ | (አዋሻኪ ሰው ጀነት አይገባም)፡ |
| 12 | ሐሜት | ሐሜት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁን? በማለት ነብዩ ጠየቁ፡፡ ሱሃቦችም፡- አላህና መልዕክተኛው ያውቃሉ፤ አሉ፡፡ (ወንድምህን በሚጠላው ነገር ማንሳት ነው) አሏቸው፡፡ (የምናነሳበት ነገር ያለበትስ ቢሆን) ሲሏቸው፡- (የምትለው ካለበት አማህው፤ ከሌለበት ደግሞ ቡህ ን /ጫንክበት ይባላል) አሉ፡፡ |
| 13 | መራገም | አማኝን ሰው መርገም እንደ መግደል ይቆጠራል፡፡ ተራጋሚች የቂያማ ቀን ሸማግሌም ሆነ ምስክር አይሆኑም፡፡ |
| 14 | ሚስጥርን ማባከን | የቂያማ ቀን መጥፎ ደረጃ ካላቸው ሰዎች መካከል አንዱ ከሚስቱ ጋር ሚስጥር አውርቶ ሚስጥሯን የሚዘራ ነው፡፡ |
| 15 | መጥፎ ነገር መናገር | ‹‹የቂያማ ዕለት አላህ ዘንድ መጥፎ ቦታ ያለው ማለት ሰዎች መጥፎ ምላሱን ፈርተው የሚሸሱት ነው›› ‹‹ከአደም ልጆች ወንጀሎች ብዙ በምላሱ ነው›› |
| 16 | ሙስሊም ወንድመን በካፊርነት መጠርጠር | ሙስሊም ወንድሙን (ከሃዲ) ያለ ሰው ከሁለት አንዳቸው ይሆኗታል፡፡ እንዳለው ከሆነ ሆነ፡፡ ካልሆነ ግን ወደ እሱው (ወደተናጋሪው) ትመለስበታለች፡ |
| 17 | ያለ አባቱ መጠጋት | «እያወቀ አባቱ ያልሆነን ሰው አባቴ ነው ያለ ጀነት ለእሱ እርም ናት፡፡» «የአባቱን አባትነት ያስተባበለ ሰው ከሃዲ ነው» |
| 18 | ሙስሊምን ማስደንገጥ | ሙስሊም የሆነ ሰው ሙስሊም ወንድሙን ሊያስደነግጥ አይፈቀድም፡፡ ወደ ወንድሙ በብረት መሳሪያ ያመለከተ ሰው ድርጊቱን እስከሚያቆም ድረስ መላይካ ይረግመዋል፡፡ |
| 19 | በሙስሊሞች ሀገር የሚኖርን ሰላማዊ ሰው መግደል | ነፍስን ያለ አግባብ የገደለ ሰው መቶ አመት በሚያስኬድ ርቀት ላይ የሚገኘውን የጀነት ሺታ እንኳን አያገኝም፡፡ |
| 20 | የአላህን ወዳጆች መጣላት | አላህ፡- «ወዳጄን ያስቸገረ ሰው ጦርነት እዉጄበታለሁ» ብሏል፡፡ |
| 21 | ሙናፊቅንና ፋሲቅን ማላቅ | ለሙናፊቅ (አለቃዬ) አትበሉት፡፡ እሱ አለቃ ከሆነ ጌታችሁን ታስቆጣላችሁና፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 22 | በሀላፊነት የሚያስተዳድራቸዉን ህዝቦች ማታለል | አላህ አንዳች ሀላፊነትን የጣለበትና እያታለለ የሞተ ሰው ጀነትን በእሱ ላይ እርም አድርጓታል፡፡ |
| 23 | ያለ እውቀት ፍትዋ መናገር | ያለ እውቀት የተናገረ ሰው ወንጀሉ በተናጋሪው ላይ ነው፡፡ |
| 24 | የጁሙዐን ወይም የአስርን ሶላት ችላ ብሎ ማሳለፍ | ያለ በቂ ምክኒያት በቸልተኝነት ሶስት ጊዜ ጁሙዐን የተወ ሰው አላህ በልቡ ላይ ያትምበታል፡፡ |
| 25 | ሶላትን ማጓደል | በእኛና በእነርሱ መካከል ያለው ገመድ ሶለት ነው፡፡ እሷን የተወ ሰው በትክክል ክዷል፡፡ (በሰውየውና በክህደት እንዲሁም በሺርክ መካከል ያለው መለያ ሶላት መተው ነው፡፡ |
| 26 | በሰጋጅ ፊት ለፊት ማለፍ | በሰጋጅ ፊት ለፊት ቆርጦ የሚያልፍ ሰው ያለበትን ቅጣት ቢያውቅ ኖሮ ቆርጦ ከሚያልፍ አርባ ክረምት መቆሙ በተሻለው ነበር፡፡ |
| 27 | ሰጋጆቹን ማስቸገር | ነጭ ሺንኩርት ወይም ቀይ ሺንኩርት ወይም ኩራስ የበላ ሰው ወደ መስጊድ አይቅረብ፡፡ ምክኒያቱም መላይኮች የአደም ልጆች በሚቸገሩበት ነገር ሁሉ ይቸገራሉና፡፡ |
| 28 | መሬትን መቀማት /ድንበር መግፋት/ | በግፍ ስንዝር ታህል መሬት የወሰደ ሰው ከሰባቱ መሬቶች በአንገቱ ይጠለቅበታል፡፡ |
| 29 | አላህን የሚያስቀይም ንግግር መናገር | የሰው ልጅ በቀልድ አላህን የሚያስቆጣ ነገር ይናገራል ፡፡ በእሷም ምክኒያት በገሀነም ዉስጥ ሰባ አመት ይወርዳል፡፡ |
| 30 | ከዚክር ዉጭ የሆነ ንግግርን ማብዛት | ከአላህ ዚክር ዉጭ ወሬ አታብዙ፡፡ ከዚክር ሌላ በሆነ ነገር ወሬን ማብዛት የልብ ድርቀት ነው፡፡ |
| 31 | በንግግር መመጻደቅ | ከእኔ ዘንድ ይበልጥ የተጠሉትና መጭው አለምም ከኔ በጣም የሚርቁት በንግግራቸው የሚራቀቁና የሚመጻደቁት ናቸው። |
| 32 | አላህን ከማስታወስ መዘናጋት | ‹‹ሰዎች አንድ ቦታ ተቀምጠው አላህን ሳያወሱና ለነብዩ ሶለዋት ሳይለምኑ ከተለያዩ ክስረት የሆነባቸው ቢሆን እንጂ ከፈለገ ይቀጣቸዋል ከፈለገ ይምራቸዋል›› |
| 33 | ሙስሊም ወንድሙ አደጋ ሲደርስበት መደሰት | ‹‹በሙስሊም ወንድምህ መከፋት አትደስት አላህ እሱን ይምረውና አንተን ይፈትነሃልና›› ‹‹ወንድሙን በወንጀለ ያነወረ ራሱ ሳይተገብረው አይሞትም›› |
| 34 | መኮራረፍ | አማኝ የሆነ ሰው አማኝ ወንድሙን ከሶስት ቀን በላይ ማኩረፉ አይፈቀድም፡፡ አማኝ ወንድሙን አመት ሙሉ ያኮረፈ ሰው ደሙን እንዳፈሰሰ ቁጥር ነው፡፡ |
| 35 | ወንጀልን በይፋ ማውራት | ‹‹ ሕዝቦቼ ሁሉ ይማራሉ ወንጀላቸውን ይፋ ያወጡ ሲቀሩ›› |
| 36 | መጥፎ ባህሪ | ‹‹መጥፎ ባህሪ ተግባርን ያበላሻል፡፡ ኮምጣጤ ማርን እንደሚያበላሽ ሁሉ›› |
| 37 | ስጦታውን መልሶ የሚወስድ | ስጦታን የሚያስመልስ ሰው ያስታወከዉን መልሶ እንደሚልስ ዉሻ ነው፡፡ «አንድ ሰው የሰጠዉን ማስመለስ አይፈቀድለትም» |
| 38 | ጎረቢትን መበደል | አስር ሴቶች ጋር ዝሙት መፈፀም ከአንዲት ከጎረቢት ሚስት ጋር ዝሙት መፈፀሙ ይቀላል፡፡ ከአስር ቤቶች መስረቅ ከአንድ ጎረቢቱ ከመስረቅ ይቀላል፡፡ |
| 39 | ወደ ተከለከሉ ነገሮች መመልከት | የአደም ልጅ ከዝሙት ድርሻው ተፅፎበታል፡፡ ማግኙቱ አይቀሬ ነው፡፡ የአይን ዝሙት ማየት ነው፡፡ የጆሮ ዝሙት ማድመጥ ነው፡፡ የምላስ ዝሙት መናገር ነው፡፡ የእጅ ዝሙቷ ደግሞ-መዳሰስ ነው፡፡ ልብም ይመኛል፡፡ የግንኙነት አካል ደግሞ በተግባር ያረጋግጣል ወይም ያስተባብላል፡፡ |
| 40 | የማትፈቀድለትን ሴት ሰውነት መንካት | የማትፈቅድለትን ሴት አካል ከመንካት በብረት ወስፌ ራሱን መውጋት ይሻላል፡፡ ‹‹ እኔ ሴቶችን አልጨብጥም›› |
| 41 | የጋብቻ ልዉዉጥ | ነቢዩ (ﷺ) ሺጋርን ከልክለዋል» ሺጋር ማለት ወንዶች አንዱ የሌላዉን ልጅ ለማግባት ብሎ ሴት ልጁን መዳር ነው፡፡ |
| 42 | ሙሾ መውረድ | ሙሾ የተለቀሰበት ሰው የቂያማ ቀን ሙሾ በተደረገበት ይቀጣል፡፡ ነቢዩ ሙሾ አልቃሿንም አድማጮችንም ረግመዋል፡፡ |
| 43 | ከአላህ ሌላ በሆነ ነገር መማል | ከአላህ ሌላ በሆነ የማለ ሰው ከሀዲ ወይም አጋሪ ይባላል፡፡ መማል የፈለገ ሰው በአላህ ይማል፡፡ ወይም ዝም ይበል፡፡ |
| 44 | የሐሰት መሐላ | የአንድን ሙስሊም ገንዘብ ለመውሰድ ብሎ በሐሰት የማለ ሰው አላህ ተቆጥቶበት ይገናኛሉ፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 45 | በገበያ ላይ መማል፤ | በገበያ ላይ ማህላን ተጠንቀቁ። ምክኒያቱም መሀላ እቃን ያስወድድና በረካን ይነሳል። |
| 46 | ከከሃዳዎች ጋር መመሳሰል | «ከሰዎች ጋር የተመሳሰለ የእነሱው አካል ነው።» «ከእኛ ሌላ በሆኑት የተመሳሰለ ሰው ከእኛ አይደለም።» |
| 47 | በቀብር ላይ መገንባት | ነቢዩ ቀብር እንዳይገነባ፤ እንዳይቀመጡበትና ቤት እንዳይሰራበት ከልክለዋል። |
| 48 | መክዳትና ማታለል | አላህ የቂያማ ቀን ሁሉንም የሰበሰበ ዕለት ለከዳተኛ ሁሉ ባንዲራ ይሰቅላል። ይህ የገሌ ክዳት ነው ይባላል። |
| 49 | በቀብር ላይ መቀመጥ፤ | በፍም ላይ መቀመጥና ልብሱን ጨርሳ ወደ ቆዳው ማለፏ በቀብር ላይ ከመቀመጥ ይሻላል። |
| 50 | ሲገባ እንዲቆሙለት መፈለግ | ‹‹ሰዎች ሲገባ ቆመው እንዲቀበሉት የሚፈለግ ሰው መቀመጫው እሳት ይሆን›› |
| 51 | ሳይቸገሩ መለመን | አንድ ሰው የልመናን በር አይከፍትም፤ የድህነት በር የተከፈተበት ቢሆን እንጂ። |
| 52 | ሳይገዙ መጫረት፤ | ነቢዩ ከተሜ ለገጠሬው ወኪል ሁኖ እንዳይሸጥ ከልክለዋል ። የማትገዙትን አትጫረቱ/ገበያ አታሳቅሉ/። በወንድሙ ሺያጭ ላይ አይሺጥ። |
| 53 | በመስጊድ ዉሰጥ የጠፋ እቃ ማፈላለግ- | በመስጊድ ዉስጥ የጠፋን ሲፈልግ የሰማችሁትን ሰው አላህ አይመልስልህ በሉት። ምክኒያቱም መስጊድ ለዚህ አልተሰራችምና። |
| 54 | ሰይጣንን መሳደብ | ሰይጣንን አትሳደቡ ከተንኩሉ ግን በአላህ ተጠበቁ ‹‹አንድ ሲሃቡ ከነብዩ ጋር እየተፈናጠጥኩኝ እየሄድኩኝ የጋለብናት እንሰሳ አደናቀፋትና ሰይጣን ጠፋ አልኩኝ ነብዩ እንደዚህ አትበል ይህ ካልክ እኮ ሰይጣን ይኩራራና ቤት ያክል ግን ቢስሚላህ በል ይህን ስትልበት እንደዝንብ ያንሳል አሉ››። |
| 55 | ወባን መሳዳብ | ወባን አትሳደቢ የብረትን ቆሻሻ እሳት እንደሚያስወግድ ሁሉ የሰው ልጆችን ወንጀል ታስወግዳለችና። |
| 56 | ወደ ጥሜት መንገድ መጥራት | ሰዎችን ወደ ጥፋት የጠራ ሰው ከእነሱ ምንም ሳይቀነስላቸው በተከተሉት ሰዎች ልክ ቅጣት አለበት። |
| 57 | በመጠጥ ላይ የተከለከሉ ነገሮች | ነቢዩ ከእቃ ወይም ከቀርበታ አፍ ላይ መጠጣትን ከልክለዋል። ቁሞ መጠጣትንም ከልክለዋል። |
| 58 | በብር ወይም በወርቅ ዕቃ መጠጣት | በወርቅና በብር ዕቃ አትጠጡ። ስስ ሐርንም ሆነ ወፍራሙን አትልበሱ። ምክኒያቱም ወርቅና ብር በዚህች አለም የነርሱ (የከሓ-ያን ሲሆኑ በመጭወ አለም ደግሞ የናንተ ናቸውና። |
| 59 | በግራ ዕጅ መጠጣት | ከናንተ አንዳችሁ በግራው እንዳይበላ፤ እንዳይጠጣም። ምክኒያቱም ሰይጣን በግራው ይበላል፤ ይጠጣልና። |
| 60 | ዝምድናን መቁረጥ | ዝምድናን የሚቆርጥ ሰው ጀነት አይገባም። |
| 61 | በነቢዩ ሙሐመድ ላይ ሶለዋት አለማውረድ | ንፉግ ማለት በአጠገቡ ስሜ ተነስቶ ለእኔ ሰለዋት ያላወረደ ነው። |
| 62 | ዉሻ ማርባት | ለአደን ወይም ለጥበቃ ሳይሆን ዉሻን ያሳደገ ሰው በየቀኑ ከሚያገኘው ምንዳ ሁለት ሁለት ቂራጥ ይቀነስበታል። |
| 63 | እንሰሳን ማሰቃየት | አንዲት ሴት በድመት ተቀጣች። እስክትሞት አስራት በሷ የተነሳ ገሀነም ገባች። «ሕይወት ያለዉን ነገር ኢላማ አድርጋችሁ አትያዙ» |
| 64 | በእንሰሳት ላይ ደወል ማሰር | ዉሻ ወይም ቃጭል የያዙ ወገኖችን መላይካ አይጎዳኛቸዉም። «ቃጭል የሰይጣን ዘፈን ነው» |
| 65 | አላህ ከፀጋው ሲቸረው ማመስገን ሲገባው የሚወነጅል | አላህ የሰውን ልጅ ወንጀል እየሰራ ዱኒያ ሲሰጠው ካየህ ኢስቲእራጅ ነው። አሉና ‹‹ በእርሱም ይገሰጹበት የነበረውን ነገር በዘነጉ ጊዜ ለእነሱ የሁሉን ነገር ደጃፎችን ከፈትንላቸው (በኑሮ አስመቸናቸው)። በተሰጡትም ነገር በተደሰቱ ጊዜ በድንገት ቀጣናቸው። ወዲያውኑም እነርሱ ተስፋ ቆራጮች ሆኑ›› የሚለውን የቁርአን አንቀፅ አነበቡ። አንዓም 44 |
| 66 | ጭንቀቱ ዱንያ የሆነ ሰው | ጭንቀቱ የዚህች ዐለም ዱንያ የሆነ ሰው ድህነቱን በሁለት አይኖቹ መካከል ያደርግበታል። ሐሳቡን ይበትንበታል። ከዱንያም የተወሰነለትን እንጂ አይሰጠዉም። |

# ዘላለማዊዋ ጉዞ

ጉዞህ ወደ ጀነት ወይንም ወደ እሳት ነው:: አላህ በቁርአን እንዲህ አለ "እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! አላህን ፍሩ፡፡ ማንኛዋም ነፍስ ለወደፊቷ ያሰቀደመችዉን ትመልከት"

ቀብር የመጀመሪያው የአኺራ ጉዞ ነው:: ለከሃዲዋችና ለሙናፊቃን የእሳት ጉድጓድ ሲሆን ለአማኞች ደግሞ ጨፌ ነው:: በቀብር ዉስጥ ከሚያስቀጡ ነገሮች መካከል- ከሽንት በደንብ አለመጸዳዳት፤ ሐሜት፤ ከምርኮ ገንዘብ መስረቅ፤ ዉሸት፤ ሶላትን ተኝቶ ማሳለፍ፤ ቁርአንን ችላ ብሎ መተው፤ዝሙት፤ግብረ ሰዶም፤ ወለድ፤ ብድርን አለመመለስና ሌሎችም ናቸዉ::

ከእርሱ ነፃ የሚያወጡ ነገሮች ደግሞ:- መልካምና ለአላህ ንፁህ የሆኑ ስራዎች፤ ከቀብር ቅጣት በአላህ መጠበቅ፤ የተባረክን ምዕራፍ በብዛት መቅራትና ሌሎችም ናቸው::

በቀንድ መነፋት-ቀንድ የሚባለው ትልቅ ቀንድ ሲሆን ኢስራፊል የተባለ መላኢካ በአፉ ይዞ ለመንፋት መቼ እንደሚ ዘዝ እየጠበቀ ነው::

የፈዝዕ/ ማስደንገጫው መነፋት- (በቀንዱ በተነፋ ቀን ከዚያም አላህ የሻለት ሲቀር ሁሉም የሚደናበርበት ቀን) ያኔ ዐለም በሙሉ ትፈርሳለች:: 27:፹፯ ከአርባ በኋላ የመቀስቀሻው ንፊት ይነፋል:: አላህ እንዲህ አለ (ከዚያም እንደገና በቀንዱ ይነፋል፡፡ ወዲያዉኑ ተነስተው ይተያያሉ፡፡) 39፡68

መቀከቀስ - ከዚያ አላህ ዝናብን ያዘንባል፡፡ ከዚያም ወዲያው አካላቶች ዐጅበ ዘነብ (የጀርባ አጥንት ከተባለው) የሰው ልጅ ክፍል አዲስ ፍጥረት፤ራቁት፤ ጫማ የሌላቸውና የማይሞቱ ሆነው ይበቅላሉ:: መላኢኮችና ጅኖች ተቀከቅሰው ከተግባራቸው ጋር ያዩዋቸዋል::

ሐሽር/መሰብሰብ - አላህ በዚያ ከባድና አምሳ ሺ አመት ያህል እርዝመት ያለው ፤ ሰዎች ከመደንገጣቸው የተነሳ እንደሰካራም የሚደናበሩበት፣ ያሳለፏትን የዱኒያ ዓለም እንደ አንዲት ሰዐት የሚያዩበት ቀን ፍጡሮችን ሁሉ ለምርመራ ይሰበስባል:: ፀሐይ ወደነሱ የአንድ ሚል ያህል ትቀርባለች፡፡ ሰዎች በስራቸው ልክ በላብ ይዘፈቃሉ:: ጉልበተኞችና ደካሞች ይጨቃጨቃሉ፡፡ ከሃዲ ከጓደኛው ከሰይጣንና ከገዛ አካላቶቹ ጋር ይሟገታል:: እርስ በራሳቸውም ይረጋገማሉ:: ግፈኞች እጃቸዉን ይነክሳሉ:: ገሀነም በ70ሺ ገመድ ትጎተታለች:: እያንዳንዱን ገመድ 70ሺ መላኢካ ይስባል:: ካፊር ባያት ጊዜ ቤዛ ከፍሎ ራሱን ማዳን ወይም አፈር መሆንን ይመኛል:: ዘካ የከለከሉት አመፀኞች ገንዘቦቻቸው እሳት ሆና ትነጠፍና በሷ ይተኮሳሉ:: ትዕቢተኞች/ኩራተኞች/ ጉንዳን /ቁንጫ መስለው ይቀሰቀሳሉ:: የከዳ፤ ያለፍቃድ ከምርኮ ገንዘብ የወሰደ ፤የቀማም በህዝብ ፊት ይጋለጣል:: ሌባ የሰረቀዉን ነገር በገሀድ ያመጣል:: የተደበቁት ሁሉ ይፋ ይወጣሉ:: አላህን የሚፈሩት ግን ምንም ሳይፈሩ የዙህር ሶላት ያህል ሆና ያልፋሉ::

ሽፋዐ/ሽምግልና /ምልጃ /:- ሽምግልና ትልቅና ትንሽ ተብሎ የሚከፈል ሲሆን ትልቁ በሕዝቦች መሰብሰቢያ ቀን ችግራቸዉን ለማስወገድ ሲባል ለነቢዩ ሙሐመድ ብቻ የሚፈቀደው ነው:: ትንሹ ደግሞ ለነቢዩም ሆነ ለሌሎች ለምሳሌ አማኞችን ከእሳት ለማውጣትና ደረጃቸዉን ለማስጨመር ሲባል የሚደረግ ሽምግልና ነዉ::

ሒሳብ/ ምርመራ - ሰዎች በጌታቸው ፊት በሰልፍ ሁነው ይቀርባሉ:: ከዚያም ተግባራቸዉን ያሳያቸዋል:: ከያንዳንዱ ነገርም ይጠይቃቸዋል:: ከእድሚያቸው፣ ከወጣትነት፤ ከእውቀት፤ ከቃል ኪዳን/ዐህድ/ ይጠይቃቸዋል:: ከዋለላቸው ፀጋዋች ከአይን፤ከጆሮ፤ ከልብ ፀጋዎች ይጠየቃሉ:: ከሃዲና ሙናፊቅ እንዲዋረዱና ማስረጃ በእነሱ ላይ ለማቆም በህዝብ ፊት ይጠየቃሉ:: ሰዎች፤ምድር፤ ቀናትና ሌሊት፤ ገንዘብ፤ መላኢካ እንዲሁም የገዛ አካሉ በሱ እንዲመሰክሩ ይደረጋል:: ይህም እንዲያረጋግጡበት ለማድረግ

ነው:: አማኝ ግን አላህ ለብቻው አድርጎ በጥፋቱ እንዲያምን ከተደረገ በኋላና ራሱም በጥፋቱ የተነሳ እንዳለቀለት ተስፋ ሲቆርጥ (በዱንያ እንደደበቅኩልህ ሁሉ አሁንም ምሬሃለሁ::) ይለዋል::
የመጀመሪያ ተቀስቃሾች የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ተከታዮች ሲሆኑ የመጀመሪያው ምርመራ የሚካሄድበትና ጥያቄ የሚቀርብበት ጉዳይ ሶላት ነው:: በመጀመሪያ ዉሳኔ የሚሰጠው ደግሞ የደም ጉዳይ ነው::

የመዝገቦች መበተን- ከዚያም መዝገቦች ይበተናሉ፡፡ ሰዎች አላህ (.... (ከሥራ) ትንሽንም ትልቅንም ሳያስቀር የሚመዘግብ ምን አይነት ኪታብ ነዉ!! ) እንዳለው ሁሉ መፅሐፋቸዉንም ይቀበላሉ:: አማኙ በቀኝ እጁ ከሃዲውና ሙናፊቁ ደግሞ ከበስተ ጀርባው በግራ እጁ ይሰጠዋል::

ሚዛን - ከዚያም ምንዳቸዉን እንዲያገኙ በእውነተኛና አስተማማኝ በሆነ ሁለት ሳህን ባለው ሚዛን የሰዎች ተግባር ይመዘናል:: ለአላህ (ﷻ)ንፁህ የሆነና ሸሪዐዉን ገጥሞ የተፈፀመ ተግባር ሁሉ ሚዛኑን ያከብደዋል:: ለምሳሌ ላኢላሀ ኢለሏህ ማለት፣ መልካም ስነ ምግባር፣
አልሐምዱሊላህ፣ ሱብሃነሏህ ወቢሐምዲህ፣ ሱብሓነሏህ ልዐዚም የሚለዉን ዚክር ይመስል:: ሰዎች በመልካም ተግባራቸዉም ሆነ በመጥፎው ይመነዳሉ::

ሐውድ - ከዚያም አማኞች ወደ ሐውድ ይወርዳሉ፡፡ ከርሱ የተጎነጨ ዝንተዓለም አይጠማዉም:: ለእያንዳንዱ ነቢይ ሐውድ አለው:: ግዙፉ ሐውድ ግን የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሐውድ ነው:: ዉሃው ከወተት የነፃ፣ ከማር የጣፈጠ፣ ከሚስክ የሚያዉድ፣ እቃዎቹ ወርቅና ብር ሲሆኑ እንደሰማይ ከዋክብት የበዙ፣ ርዝመታቸው በኡርዱን ሀገር ከሚገኘው ከአይለህ እስከ ኤደን ካለው ርቀት የረዘመ፣ ዉሃው ከከውሰር ጅረት የሚመነጭ ነዉ::

የአማኞች መፈተን - የሐሽር የመጨረሻው ቀን ከሀዲዎች እኒያን ያመልኳቸው የነበሩትን አማልክት ይከተላሉ:: እናም እንደ ፍየል በመንጋ እየሆኑ በእግራቸው ወይም በፊታቸው እየኳተኑ ወደ እሳት ያደርሷቸዋል:: በዚያ ቦታ አማኞችና ሙናፊቆች ብቻ እንጂ ሌላ አይቀርም:: ከዚያም አላህ ይመጣና - ምን ትጠብቃላችሁ - በማለት ይጠይቃቸዋል:: እነሱም:- ጌታችንን ነው የምንጠብቀው ይላሉ:: ማንቱተን ያሳውቃቸዋል። እናም ሙናፊቆች ሲቀሩ ሁሉም ሱጁድ ይወርዳሉ:: አላህ እንዲህ አለ (ባት የሚገለፅበትንና ከሓዲዎች ወደ መስገድም የሚጠሩበትን ከዚያም የማይችሉበትን ቀን አስታውስ) ከዚያም ይከተሉታል:: ሲራጥም ትዘረጋለች:: ትክክለኛ አማኞች ብርሀን ይሰጣቸዋል:: ሙናፊቆች ግን ይከለከላሉ::

ሲራጥ - ሲራጥ ማለት አማኞች ወደ ጀነት እንዲያልፉ በገሀነም ላይ የተዘረጋ ድልድይ ነው:: ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ማንዳለጫና መውደቂያ ነው:: በሱ ላይ እንደ ሰዕዳን እሾህ የሆነ ቀንጣፋና ከላሊብ አለበት:: ከፀጉር የቀጠነ ከሰይፍ የሰላ ነው::) በዚያ ቦታ አማኞች በስራቸው ልክ ብርሃን ይሰጣቸዋል:: ከፍተኛው እንደ ትልቅ ጋራ ሲሆን አነስተኛው የእግሩን አውራጣት የምታህል ነው:: ከዚያም ይበራላቸውና በስራቸው ልክ ያልፉታል:- እንደ አይን ብልጭ፣ እንደ መብረቅ፣ እንደ ነፋስ፣ እንደ ወፍ፣ እንደ ፈጣን ፈረስ ሆነው ያልፋሉ:: በሰላም ነፃ የሚወጣ፣ ቆሳስሎ የሚለቀቅ፣ ወደ ገሀነም የሚገፈተር አለ) ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበዉታል:: ሙናፊቆች ግን ምንም ብርሃን ስሌላቸዉ ይመለሱና በነሱና በመሐከላቸው ግርዶሽ ይደረጋል:: ከዚያም ሲራጥን ለማለፍ ሲሞክሩ እየተንጠባጠቡ ወድቀው ያልቃሉ::

**እሳት** - በመጀመሪያ ከሃዲዎች ከዚያም አማኝ ወንጀለኞች ከዚያም ሙናፊቆች ከ1000 ሰው 999 ሰው ጀሀነም ይገባል:: ጀሀነም ሰባት በሮች አሏት:: ከዱንያ እሳትም 70 ጊዜ ያህል እጥፍ ሀይል አላት:: የከሃዲዎች ሰውነት ከቅጣቱ በደንብ እንዲቀምስ ተብሎ በትከሻዋቹ መካከል ያለው ስፋት ሶስት ቀን የሚያስከድ ያህል ከመጠን በላይ ይገዝፋል:: መንጋጋው እንደ ኡሁድ ተራራ ይሆናል:: አካሉ የሚገዝፍበትና ቆዳው የሚቀየረው ቅጣቱ እንዲበረታበት ነው:: የጀሀነም ሰዎች መጠጣቸው አንጀታቸውን የሚቆራርጥ የፈላ ዉሃ ነው:: ምግባቸው ዘቁም ጊስሊንና መግል ነው:: አነስተኛው ተቀጭ በግሮቹ ስር ሁለት ፍሞች ተቀምጠዉ አናቱ የሚፈላ ሰው ነው:: በዉስጧ ስጋዎች ይበስላሉ፣ ይቀልጣሉ፣ ይገፈፋሉ፣ በዉስጧ ይጎተታሉ፣ በሰንሰለት ይታሰራሉ፣ እግር ከአንገት ይጠረነፋሉ:: ጥልቀቷ እጅግ ሩቅ፣ አዲስ የተወለደ ሕፃን በዉስጧ ቢጣል መሰረቷ እስከሚደርስ 70 አመት ይሆነዋል:: ማቀጣጠያዋ ከሃዲዎችና ድንጋዮች፤ አየሯ የተመረዘ፤ ጥላዋ ነዲድ፤ ልብሷ እሳት ነዉ፤ ሁሉን ነገር ትበላለች:: አንድንም ነገር አትተዉም:: ትፈላለች፣ ቆዳዎችንም ታቃጥላለች፣ ልብንና አጥንትንም ታዳርሳለች::

**ቀንጦራህ** - ነቢዩ ሙሐመድ (صلى الله عليه وآله وسلم) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ (አማኞች ከእሳት ሲወጡ በጀነትና በእሳት መካከል ባለ (ቀንጦራህ) ድልድይ ላይ ይታገታሉ:: በዱንያ ሳሉ እርስ በርስ የተበዳደሉትን ያካክሳሉ። ከወንጀል እዳ ከፀዱ በኋላ ጀነት እንዲገቡ ይፈቀድላቸዋል:: የሙሐመድ ህይወት በእጁ በሆነው ጌታ ይሁንብኝ በዱንያ ካሉት ቤ ታችሁ ይልቅ በአኺራ ያላችሁን ታውቃላችሁ፡፡) ብለዋል፡፡

**ጀነት** - የአማኞች መኖሪያ መመለሻ ናት:: ስሪቷ ብርና ወርቅ ነው:: መተኛዋ ሚስክ ነው:: ንጣፏ ሉልና ያቁት ነው:: አፈሯ ዘዕፈራን ነው:: ስምንት በሮች አሏት:: (100) መቶ ደረጃዎች አሉ:: ከአንዱ እስከሌላኛው በሰማይና በምድር መካከል እንዳለው ርቀት ያህላል:: ከፍተኛው ማዕረግ ፊርደውስ ይባላል:: የጀነት ወንዞች የሚመነጩት ከእሷ ነው:: የጀነት ጣሪያዋ የአላህ ዐርሽ ነው:: ወንዞ ማር፣ ወተት፣ ጠጅና ዉሃ ናቸው:: ያለ ቦይ ነው የምትፈሰው:: አማኙ በፈለገው ቦታና በፈለገው አይነት ያፈሰዋል::
ፍፍዋቿ ዝንታለም ቅርብና ገር ናቸው:: በዉስጧ ወርዱ 60 ማይል የሆነ የሉል ድንኳን አለ:: በየጥጉ ቤተሰብ አለው:: ኮረዳ አይነ ኩሌ የሆኑ:: ወጣትነታቸዉም ሆነ ልብሶቻቸው አያረጅም:: ሽንትም ሰገራም ቆሻሻም የለም:: ሚዷቸው/ማበጠሪያቸዉ/ ከወርቅ ነው:: ላባቸው ሚስክ፤ ሴቶቻቸው ቆንጆዎች፤ ልጃገረዶች፤ በተመሳሳይ የዕድሜ ክልል ያሉ፤ ጡቶቻቸው ያልወደቁ ናቸው:: መጀመሪያ የሚገቡት ነቢዩ ሙሐመድ (صلى الله عليه وآله وسلم) ሲሆኑ ከዚያም ሌሎች ነቢያት ናቸው:: ዝቅተኛ ማዕረግ ያለው ሲጠይቅ ለጠየቀው አስር እጥፍ የሚሰጠው ነው:: አገልጋዮቻቸው እንደተበተኑ ሉሎች የሆኑ ልጅ ጁግር ናቸው:: ከፀጋዋቹ ሁሉ ትልቁ አላህን ማ የት፤ የአላህን ዉዴታ ማግኘትና በጀነት ዉስጥ ለዘላለም መኖር ነው::

**ማሳሰቢያ**:- አማኝ፤ሙናፊቅ፤ከሃዲ ወደ መጨረሻቸው እስከሚደርሱ ድረስ በተከታይ የሚያሳልፏቸው ግዙፍ ክስተቶች ናቸዉ::

# የዉዱእ ስርአት



ያለ ዉዱእ ሶላት የለም። ዉዱእም በንፁህ ዉሃ እንጂ አይሆንም። ይህም ማለት ከዉሃነቱ ምንም ያልተቀየረ የዉቅያኑስ፣ የጉድጓድ፣ የምንጭና የጅረት ዉሃን የሚመስል ነው።
**ማሳሰቢያ :** በቀዝቃዛ ወይም በሙቅ ዉሃ ዉዱእ ማድረግ ይጠላል። በዉዱእ ላይ እያሉ ወሬ ማውራት ይጠላል ፡ትንሽ ዉሃ ነጃሳ ሲወድቅበት ብቻ ይነጀሳል።ብዙ ግን(፪፩0 ሌትር የሚቃረብ ማለት ነው) መልኩ ወይም ጣዕሙ ወይም ሽታዉ ካልተለወጠ በስተቀር አይነጀስም።



ዉዱዕ የሚጀመረው በቢስሚላህ ነው። በዉዱእ ጊዜ አስቀድሞ መዳፎችን ማጠብ ይወደዳል። ከለሊት እንቅልፍ ለነቃ ሰው ግን ሶስት ጊዜ ማጠቡ የበለጠ ይወደዳል።
**ማሳሰቢያ :-**ቢስሚላህን የረሳ  በዉዱኡ ላይ ምንም ችግር አያስከትልም። የዉዱዕ አካሎችን በማጠብ ከሶስት ከሶስት በላይ መጨመር ይጠላል።



ከዚያም አንድ ጊዜ ይጉመጥመጥ ። ሶስት ጊዜ ማድረጉ ይወደዳል።
**ማሳሰቢያ :** ዉሃዉን በአፍ ዉስጥ ማንቀሳቀስና ማዘዋወር ግድ ነው። እየተጉመጠመጡ ባለበት ሰዐት ሲዋክ መጠቀም ይወደዳል።



ከዚያም አንድ ጊዜ በአፍንጫው ዉሃ ይስባል።ሶስት ጊዜ ማድረጉ ይወደዳል።
**ማሳሰቢያ:-** በቀኝ እጁ ዉሃዉን ማስገባትና በግራው ማስወጣት ይወደዳል።



ከዚያም ፊቱን ይጠብ።እሱም አግድም ከጆሮ እስከጆሮ ድረስ ሲሆን ቁመቱ ደግሞ ከፀጉር መብቀያ አንስቶ እስከ አገጭ ድረስ ነው።
**ማሳሰቢያ :** ስስ ፂምን ፈልፍሎ ማጠብ ግዴታ ሲሆን ጭፍግግ ያለዉን ግን መፈልፈሉ ይወደዳል።



ከዚያም ከጣቱ ጫፎች አንስቶ ከክርኖቹ ጋር እጁን ያጥባል።
**ማሳሰቢያ :** ቀኙን ከግራው ማስቀደሙና ማሸቱ ይወደዳል።



ከዚያም ራስን ሙሉውን ከፊት ለፊቱ አንስቶ እስከ ማጅራቱ ድረስ በመውሰድና ከዚያም ወደኋላ በመመለስ አንድም ቦታ ሳይተው ይበስ።ከዚያም አመልካች ጣቶቹን በጆሮዎቹ ቀዳዳዎች ዉስጥ ያስገባቸው።በአውራጣቶቹ ደግሞ የጆሮዎቹን ጀርባ ይበስ።
**ማሳሰቢያ :** የወረደ ፀጉር ማበስ ግዴታ አይደለም። ፀጉር ከሌለው የራስ ቅሉ ይታበሳል።-በፀጉራችንና በጆሯችን መካከል ያለው ባዶ ቦታ የራስ አካል በመሆኑ መታበስ ይኖርበታል።-ከአንድ ጊዜ በላይ ደጋግሞ ማበስ ይጠላል።-በማበስ ፈንታ ፀጉርን ማጠብየሚፈቀድ ቢሆንም ይጠላል።



ከዚያም ከነቁርጭምጭሚቱ እግሮቹን ያጥባል።
**ማሳሰቢያ:** ቀኙን ከግራው ማስቀደሙና ማሸቱ ይወደዳል። ጣቶቹን መፈልፈልም ይወደዳል።

**ማሳሰቢያዎች:-**

1- የዉዶእ አካሎች አራት ናቸው። እነርሱም :

ሀ) መጉመጥመጥ፤በአፍንጫ ዉሃን መሳብና ፊትን ማጠብ፤ ለ) እጆቹን ማጠብ፤ ሐ) ራሱንና ጆሮዎችን ማበስ፤

መ) ከነቁርጪምጪምቱ እግሮቹን ማጠብ ነው፤ ማከታተል ግዴታ ሲሆን አንዱን ከሌላው ማስቀደም ዉዱእን ያበላሻል።

2- ፊተኛው እስከሚደርቅ ድረስ ባለማቆየት መከታተል ማለጣጠቅ ግዴታ ነው።

3- ከዉዱእ በኋላ አሽሀዱ አላ ኢላሀ ኢለሏህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ ወአሽሀዱ አነሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ ማለቱ ይወደዳል።

# የሶላት ስርአት



ለመስገድ አስቦ ሲቆም አላሁ አክበር በማለት ይጀምር፡፡ ኢማም የሆነ ሰው መግቢያዉንም ሆነ ሌሎችን ተክቢራዎች ተከታዮቹ እንዲሰሙ ድምፁን ከፍ አድርጎ ነው ማለት ያለበት፡፡ ከእሱ ሌላ የሆነ ሰው ግን ድምፁን ዝቅ ያድርግ ፡፡ አላሁ አክበር ማለት ሲጀምር ጣቶቹን አጠጋግቶ በትክሻው ድረስ ያንሳቸው፡፡ተከታይ አላሁ አክበር የሚለው ኢማሙ ብሎ ከጨረሰ በኋላ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ :** ቁርአንንና ዚክሮችን ድምጽን ሳያሰሙ በሚቀራባቸው ሶላቶች ውስጥም ቢሆን ራሱን የሚያሰማበትን ያህል ድምፁን ከፍ ማድረግ ግዴታ ነው፡፡



በቀኝ እጁ መዳፍ የግራ እጁን መዳፍ ወይም ክንድ ይጨብጥና ከደረቱ ስር ያድርጋቸው፡፡አይኑ የሱጁድ ቦታዉን ይመልከት፡፡ ከዚያም ከነቢዩ ከተዘገቡት የዱዓ አይነቶች በአንዱ ይጀምር ፡፡ ከዚያም አዑዙ ቢላህ ሚነ ሹ-ሸይጣኒ ረጂም ይበል፡፡ ቀጥሎም ቢስሚላሂ ረህማኒ ረሂም ይበል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ድምፁን ዝቅ አድርጎ ነው፡፡ ከዚያም ፋቲሃን ያንብብ፡፡ ከዚያም የመረጠዉን የቁርአን አንቀፅ ያንብብ፡፡ ኢማም የሆነ ሰው ከሱብሂ ሶላት፣ ከመግሪብና ከኢሻ ሶላቶች በመጀመሪያዎቹ ረከዐዎች ላይ ድምፁን ከፍ ያድርግ፡፡ በሌሎቹ ግን ድምፁን ዝቅ ያድርግ፡፡

**ማሳሰቢየ :** የቁርአኑን ቅደም ተከተል መጠበቁ ይወደዳል፡፡ተቃራኒዉን ማድረግ ግን ይጠላል፡፡በአንድ ምዕራፍ ላይ ያሉ አረፍተ ነገሮችን ወይም አንቀፆችን ማቀያየር ክልክል ነው፡፡



ከዚያም አላሁ አክበር በማለትና እጆቹን በማንሳት ሩኩዕ ያድርግ፡፡ እጆቹን ልክ ጉልበቶቹን የጨበጠ አስመስሎ ጣቶቹን ዘርግቶ ያስቀምጥ፡፡ ወገቡን ይለጥጠውና በራሱ ትክክል ያድርገው፡፡ ከዚያም ሱብሀነረቢየልዐዚም ይበል፡፡ አነስተኛው ሙሉ ሶስት ሲሆን በአንድ ጊዜ መብቃቃቱ ይጠላል፡፡

**ማሳሰቢያ :** አላሁ አክበርና ሰሚዐ-አላሁ ሊመን ሐሚደህ የሚለዉን መናገር ያለበት ተግባሩ እየተሰራ ባለበት ሰዐት ነው፡፡ ማስቀደሙም ሆነ ማዘግየቱ አይፈቀድም፡፡ አውቆ ከሆነ ሶላት ያበላሻል፡፡ሩኩዕን በማግኘት ረከዐዋን ማግኘት ይቻላል፡፡ቢሆንም ረከዐዋን አገኘ ለመባል የግድ ሩኩዑ ላይ ከኢማሙ ጋር መገናኘት አለበት፡፡



ከዚያም ሰሚዐ-አላሁ ሊመን ሐሚደህ እያለ ራሱን ቀና ያድረግ፡፡ እጆቹንም አብሮ ያንሳቸው፡፡ቀጥ ብለው ከቆሙ በኋላም ረበና ወለከል ሐምድ ሐምደን ከሲረን ጦይበን ሙባረከን ፊሂ ሚልኡ-ሰማዋቲ ወሚልኡል አርዲ ወሚልኡ ማሺእተ ሚን ሸይኢን በዕዱ›››› ይበል

**ማሳሰቢያ :** ቀጥ ብሎ ሳይቆም ረበና ወለከል ሐምድ አይባልም፣፣ ምክኒያቱም ቦታው ከተቆመ በኋላ ነዉና፡፡



ከዚያም አላሁ አክበር በማለት ወደ መሬት ይውረድ፡፡ የእጆቹን ጡንቻዎች ከጎኖቹ ራቅ ያድርጋቸው፡፡ ሆዱን ከጭኖቹ፣ ጭኖቹን ከባቶቹ ያርቃቸው፡፡ እጆቹን በትከሻው ልክ አድርጎ በእግሮቹ ጫፎች ላይ በመሆንና የእጆቹንም ሆነ የእግሮቹን ጣቶች ወደ ቂብላ በማዞር ሱብሃነ ረቢየል አዕላ ይበል፡፡ ሶስት ጊዜ ማድረጉ ሱና ነው፡፡ ከዚህም በላይ መጨመር የሚችል ሲሆን ሌላም ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከተዘገቡት የዱዓ አይነቶች በፈለገው ማድረግ ይችላል፡፡

**ማሳሰቢያ :** ሱጁዱ በሰባቱም የሱጁድ አካሎች ላይ መሆን ግዴታው ሲሆን እነሱም ሁለት የእግርጫፎች፤ሁለት ጉልበቶች፤ሁለት መዳፎች፤አፍንጫና ፊት ናቸው፡፡ በሱጁድ ወቅት ከእነዚህ አካሎች አንዱንም ከመሬት -እያወቁ- አለማሳረፍ ሶላት ያበላሻል፡፡



-ከዚያም አላሁ አክበር በማለት ራሱን ቀና አድርጎ ይቀመጥ። በሁለት ሱጁዶች መካከል ለመቀመጥ ሁለት አይነት መንገድ አለው። 1-ግራ እግሩን አንጥፎ በእሱ ላይ መቀመጥና ቀኝ እግሩን በማቆም ጣቶቹን ብቻ ወደቀኝ ማዞር ነው። 2-ሁለቱንም እግሮቹን ተክሎ ጣቶቹን ወደቂብላ አዙሮ በተረከዞቹ ላይ መቀመጥ ነው። ከተቀመጠ በኋላም ረቢ-ግፊርሊ የሚለዉን ሶስት ጊዜ ያንብብ። ወርሐምኒ ወጅቡርኒ ወርዙቅኒ ወንሱርኒ ወህዲኒ ወዓፊኒ ወዕፉ-አኒ የሚለዉን መጨመርም ይችላል። ከዚያም ልክ እንደመጀመሪያው ሱጁድ ሁለተኛዉንም ሱጁድ ያድርግ። ከዚያም አላሁ አክበር በማለት ራሱን ቀና ያድርግና ወደ ሁለተኛዋ ረከዐ ይነሳ። ሁለተኛዋንም ረከዐ ልክ እንደመጀመሪያዋ ረከዐ ይስገዳት።

**ማሳሰቢያ ፡** ፋቲሃ የምትነበበው ቀጥ ብሎ ከተቆመ በኋላነው። ከዚያ በፊት ያነበባት መመለስ አለበት ምክኒያቱም ያለ ፋቲሃ ሶላት የለምና ነው።



ሁለቱን ረከዐዎች ሲያጠናቅቅ ለመጀመሪያው ተሸሁድ ግራዉን አንጥፎ ይቀመጥ።ግራ እጁን በግራ ጭኑ ላይ ቀኝ እጁን በቀኝ ጭኑ ላይ ያስቀምጥ። ትንሽ ጣቱንና ቀለበት ጣቱን ይጨብጣቸው። በአውራጣቱና በመሀል ጣቱ ክብ ይስራ። በአመልካች ጣቱ ደግሞ ይጠቁምና አተሂያቱ ሊላህ ወሶለዋቱ ወጦይባቱ አሰላሙ ዐለይከ አዩሃ-ነቢዩ ወረህመቱሏሂ ወበረካቱሁ አሰላሙ ዐለይና ወዐላ ዒባዲላሂ አሷሊሂን አሽሀዱ አላ ኢላሀ ኢለሏህ ወአሽሀዱ አነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ፤ የሚለዉን ያንብብ። ከባለ አራትና ከባለ ሶስት ረከዐ ሶላቶች ላይ ከሆነ አላሁ አክበር በማለት ይነሳ። እጆቹንም ያንሳ። የቀረዉን ሶላት ረከዓ ልክ እንዳለፈው አይነት አድርጎ ይስገድ። ባይሆን ድምፅ ከፍ አይደረግም። የሚነበበዉም ፋቲሃ ብቻ ነው።

በተሸሁድ ጊዜ የቀኝ አመልካች ጣቱን መመልከት ይወደዳል።




ከዚያም ለመጨረሻው መቀመጥ ተወሩክ አድርጎ ይቀመጥ። እሱም ትክክለኛ የሆኑ ሶስት አይነት የአቀማመጥ ስርአቶች አሉት። ተወሩክ የሚደረገው ሁለት ጊዜ የመቀመጥ ስርዐት ባለባቸው ሶላቶች በሁለተኛው እንጂ በሌላ ጊዜ አይሆንም። ከዚያም አተሂያቱን ያንብብ ። ከዚያም አላሁመ ሶሊ ዐላ ሙሐመዲን ወዐላ ኣሊ ሙሐመዲን ከማ ሶለይተ ዐላ ኢብራሂም ወዐላ ኣሊ አብራሂም ኢነከ ሀሚዱን መጂድ...አላሁመ ባሪክ ዐላ ሙሐመዲን ወዐላ ኣሊ ሙሐመዲን ከማ ባረክተ ዐላ ኢብራሂመ ወዐላ ኣሊ አብራሂም ኢነከ ሀሚዱን መጂድ..... በሚለው የዱዐ አይነት ለነቢዩ ዱዓ ይለምን። ከዚያም በፈለገው የዱዓ አይነት አላህን ይለምን።

**የተወሩክ አቀማመጥ ፡** 1-ግራዉን አንጥፎና በቀኝ በኩል ከባቱ ስር አውጥቶ ቀኝ እግሩን ተክሎ ታፋዉን ከመሬት ላይ ማድረግ ። 2-ልክ እንዳለፈው ሆኖ ቀኝ እግሩን ማንጠፍ፤ 3-ልክ እንደመጀመሪያው ሆኖ ግራ እግሩን በባቱና በጭኑ መካከል ማስቀመጥ ነው።



ከዚያም ወደቀኝ በኩል ዞሮ አሰላሙ ዐለይኩም በማለትና ወደግራዉም ዞሮ እንዲሁ በማለት ሁለቱን ሰላምታዎች ይፈፅም። ሰላምታዉን እንደጨረሰ በሰገደበት ቦታ ላይ ቁጭ ብሎ ከነቢዩ የተሰሙትን የዱዓ አይነቶች ያንብብ።

# እውቀት ተግባርን ስለ መጠየቁ

ያለ ተግባር እውቀት ብቻ ከአላህ፤ከመልዕክተኛዉና ከሙስሊሞች ዘንድ የተወገዘ ነው። (የማትሰሩትን ነገር መናገራችሁ አላህ ዘንድ በመጠላት ተለቀ /እጅግ ከበደ/።) አቡሁረይራ (ያ! የማይሰራበት እውቀት ምሳሌው ለጂሃድ ምንም የማይሰጥለት የገንዘብ ድልብ አይነት ነው።) ብለዋል። ፉዶይል ኢብኑ ዒያድ የተባሉ ዐሊም (ባወቀው እስከሚተገብር ድረስ ከአላዋቂዎች ነው የሚመደበው) ብለዋል። ማሊክ ብን ዲናር (አንድም ፊደል ስህተት የሌለው ሆኖ ተግባሩ ግን ሁሉም ስተት የሆነ ሰው አለ) ብለዋል።

ስለዚህ ሙስሊም ወንድሜና ሙስሊም እህቴ! አያሌ ጥቅም ያዘለዉን ይህን መፅሐፍ ለማንበብ አላህ (ﷻ) አግርቶላችኋል። የቀረውም የንባቡ ዉጤት የሆነው ነው። ይኸዉም በእሱ መሰረት ህይወትን መምራት ነው። አያሌ የቁርአን አንቀፆችና ተፍሲሮቻቸው አልፈዉልሃል። እናም በተረዳኸው የቁርአን ምክር ተመከር። የነቢዩ ሙሐመድ ባልደረቦች ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አስር አኖቀፅን ይማሩና ወደ ሌሎች አስርት አናቅፅ ከመተላለፋቸው በፊት የእነዚህን መልእክትና ተግባር ነበር የሚያስቀድሙት። እውቀትንም ተግባርንም በአንድ ተማርን ይሉ ነበር። የኢስላምም መመሪያ በዚሁ ላይ ነው የሚገፋፋው። ኢብኑ ዐባስ (አግባብነት ያለዉን ንባብ ያነቡታል)። የሚለዉን አንቀፅ ሲተረጉሙ፦ በትክክል የሚከተሉት ማለት ነው ሲሉ ፡ፉዶይል ደግሞ ቁርአን የተወረደው ሊሰራበት ሲሆን ሰዎች ግን ማንበቡን እንደ ትልቅ ስራ አድርገው ያዙት ብለዋል።

ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሱናዎችና ሐዲሶች የተወሰኑ አልፈዋል። ለእነሱም ለመ ዘዝና በእነሱ ለመስራት ተዘጋጅ። ስመ ጥሩ ሰዎች ሁሉ አንድን ነገር ባወቁ ቁጥር ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (በአንድ ነገር ሳዛችሁ የአቅማችሁን ያህል ተግብሩት የከለከልኳችሁን ግን ሁሉንም ተዉት።) ያሉትን መመሪያ ለማክበር ብለዉና አላህ (እነዚያ ትእዛዙን የሚጥሱ ሰዎች በዱንያ መከራ እንዳትደርስባቸው ወይም በአኺራ አሳማሚ ቅጣት እንዳያገኛቸው ይጠንቀቁ በማለት የተናገረዉን ለመተግበር አቅማቸው በፈቀደው ልክ ሲሯሯጡና ሰዎችንም ወደ ዚያው ተግባር ለመጥራት ሲጣደፉ ነበር የሚ ዩት። በዚህ ጉዳይ ሞዴል ከፍተኛ አርአያ ነበሩ ከሚባሉት ሰዎች መካከል፦

ከነቢዩ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (በቀንና በሌሊት አስራ ሁለት ረከዐ የሰገደ ሰው በእነዚህ ምክኒያት በጀነት ዉስጥ ቤት ይገነባለታል) ተብሏል። ይህን ሐዲስ ከነቢዩ (ﷺ) ያወሩት እና ችን ኡሙ ሐቢባ፦ (ይህን ሐዲስ ከሰማሁኝ ጀምሮ አንድም ቀን አልተውኳቸዉም) ይላሉ።

(አንድ ሙስሊም ኑዛዜ ማድረግ ያለበትን ነገር ሳይናዘዝ ሶስት ሌሊት ሊያልፈው አይገባም) የሚለዉን ሐዲስ ያወሩ ታላቅ ሱሓቢ ዐብዱላህ ኢብኑ ዑመር፦ አንድም ቀን ኑዛዜ ሳላደርግ አድሬ አላውቅም፣ ብለዋል።

ታላቁ መሪ አህመድ ብን ሐንበል (አንድም ሐዲስ ፅፌ አላውቅም፤ የተገበርኩት ቢሆን እንጂ። ነቢዩ ታግመው ለአቡ ጠይባ አንድ ዲናር ሰጡ የሚለውን ሐዲስ ስሰማ ታግሜ አንድ ዲናር ሰጠሁ።) ብለዋል።

ታላቁ መሪ ቡኻሪም እንዲህ ብለው ነበር (ሐሜት ሐራም መሆኑን ከሰማሁ ጀምሬ አንድም ቀን አምቼ አላውቅም። አንድንም ሰው አምተሃል ብሎ ንደማይመረምረኝ አላህን ተስፋ አደርጋለሁ።)

ነሳኢ የዘገቡት ሐዲስ (ከየሶላት በኋላ ኣየተል ኩርሲን ያነበበ ሰው ጀነት ከመግባት ከሞት በስተቀር የሚከለክለው ነገር የለም፡፡) ይላል፡፡ ኢብኑል ቀይም ስለዚህ ጉዳይ ሲናገሩ፡- ኢብኑ ተይሚያ (ረስቹ ወይም በሌላ ችግር ምክኒያት ካልሆነ በስተቀር ከሶላት በኋላ አያተል ኩርሲን አንድም ቀን ትቻት አላውቅም፡፡) ብለዋል፡፡

ከማወቅና ከመተግበር ቀጥሎ ሊሎችም በዚሁ አይነት እንዲ ደሉ፣ ወደ እዚሁ አላህ ወደ ዋለልህ ፀጋ መጥራትና እራስህንም ሆነ ሌሎችን የኸይር ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ኸይርን ያሳየ ሰው የሰራው ሰው የሚያገኘዉን ምንዳ ያህል ያገኛል፡፡) ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ (ምርጣችሁ ቁርአንን ተምሮ ያስተማረው ነው፡፡) ብለዋል፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ((ከእኔ የሰማችሁትን አንድም አንቀፅ ቢሆን ላልሰማ አሰሙ፡፡) ብለዋል፡፡ ወንድሜ ሆይ! ኸይር ነገርን ባስፋፋህ ልክ አጅርህ ይበዛል፡፡ በህይወት እያለህም ሆነ ከሞትክ በኋላ ምንዳህ ይበረክታል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (አንድ ሰው ሲሞት ከሶስት ነገር ሌላ የሆነው ተግባሩ ሁሉ ይቋረጣል፡፡ እነሱም ቀጣይነት ያላት ሰደቃ፤ሌሎች የሚጠቀሙበት ትምህርት፤ለእሱ ዱዓ የሚያደርግለት መልካም ልጅ ) ብለዋል፡፡

ማብራሪያ፡ እኛ ሙስሊሞች በየቀኑ ከአስራ ሰባት ጊዜ በላይ የፋቲሀን ምእራፍ እናነባታለን፡፡ በዚህም ጊዜ አላህ ከተቆጣባቸውና ከተሳሳቱት ሰዎች ተግባር በእሱው እንጠበቃለን፡፡ በተግባር ግን እነሱን እንመስላለን፡፡ ምክኒያቱም አንዳዶቻችን ሳንማር በድንቁርና ተውጠን ወደ ስራ እንገባና በተግባራችን የተሳሳቱትን ክርስቲያኖች እንመስላለን፡፡ ሌሎቻችን ደግሞ እንማርና ባወቅነው መሰረት ባለመተግበር እኒያን አላህ የተቆጣባቸዉን አይሁድ እንመስላለን፡፡ ለእኛም ሆነ ለአንተ እውቀትንና ተግባርን በአንድ እንዲሰጠን አላህን እንማፀነዋለን፡፡

ትክክለኛዉን አላህና መልዕክተኛው ብቻ ያውቃሉ፡፡

አላህ በነቢያችን፤በቤተሰቦቻቸውና በሁሉም ጓዶቻቸው ሰላሙንና ርህራሄዉን ያወርድላቸው፡፡ ተፈፀመ፡፡

ሙሐመድ ዘይን ዘህረዲን ኸሊል

أمهري

# تفسير العشر الأخير

## من القرآن الكريم